

ደቂቀ እስጢፋኖስ

"በሕግ አምላክ"

(ትርጉም)

ጌታቸው ኃይሌ

ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፲፱፻፺፯ ዓ. ም.



የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

© 2004 by Getatchew Haile, Avon, Minnesota
All Rights Reserved

Daqiqa Estifanos

ISBN: 0-9706663-2-2

Library of Congress Control Number: 2003099646

የመጽሐፉንና የሽፋኑን መልክ እንዲሁም መጠቀሙን ያዘጋጀው፡ አምነ አስፋው


የፊት ሽፋን፡ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ
(EMML 7219, f. 21b)

ይህን መጽሐፍ ለመግዛት
ከታች ባለው አድራሻ መጠየቅ ይቻላል::

Inquiries can be sent to:

Daqiqa Estifanos
P.O. Box 113
Avon, MN 56310, USA

ለሁለተኛ ጊዜ አያት ለመሆን ለበቃሁበት ዕለት ለጎዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺ ዓ. ም.



እንደ እናትህ ንጹሐ ኅልያ፡ ፈታሔ ጽድቅ፡ ርኅሩኀ ልብ፡
መፍቀሬ ሰብእ ወኮሉ ዘነፍስ ያድርግህ።

Deqiqe Istifanos: "behigg amlak" is a hagiographical history of the rise and fall of a group of Ethiopian monks who founded a fundamentalist movement that rocked both Church and State during the fourteenth and fifteenth centuries. The monks refused to bow before the cross, the icon of Madonna and Child or the king, maintaining that that form of worship was preserved only for the Trinity. They also insisted that asceticism, not observed at that time in the major monasteries, should be observed in all monasteries. These views were not shared by the establishment, and as the number of people attracted to the movement steadily grew, the palace and senior clergy became increasingly concerned. Ultimately, when the monks refused to compromise their principles, the palace destroyed them by meting out the most inhumane punishment.

Deqiqe Istifanos is a unique historical document about Ethiopia, especially of the 15th century. The book contains a translation into Amharic of preexisting Ge'ez texts that chronicle the lives of the leader of the movement, Abba Istifanos (Stephen), and his two successors, Abba Abekrezun and Abba Izra (Ezra). It includes also the translation of a Ge'ez text that describes the martyrdom of the many monks and nuns involved in the movement. The translations are preceded by the translator's extensive introduction about the movement. The document concludes with a bibliography and an index.



ማውጫ

ቀዳሚ ቃል (ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም) 13
መቅድም 17
መግቢያ 21
ደቂቀ አስጢፋኖስ 23
የአፄ ዘርአ ያዕቆብ አገዛዝ (1426-1460) 25
የሃይማኖት ውዝግብ 28
ብሔረ ብዙኃን 32
ቤተ ክርስቲያንን ያመሰጠ ዕድል 35
ውዝግብና ሥነ ጽሑፍ 36
ምንጮች 41
የገድለ አበው ወአኃው ምስክር 46
የመተርጉም ችግር 49
ደብረ ብርሃን 51

የእባ እስጢፋኖስ ገድል 55
መግቢያ 57
ትውልድና አድገት 57
መንፈሳዊ ጥሪ 59
ዓለምን ስንብት 61
ምንኵስና ለጻማ መጠመድ 62
አስተማሪነትና ጻማ 67
ብቃት 68
ቅናትና ግጭት 70
ከጳጳሱ ከአባ በርተሎሜዎስ ዘንድ 71
የመጀመሪያው ስደት 73
በተቈለፈ አግር ብረት በተቈለፈ አስር ቤት 74
ሁለተኛ ስደት--የደብረ ገርዜን መመሥረት 75
ሰይጣን የክስ መርዙን በደብሮቹ ላይ ረጨ 79
ከንጉሡ (ከአፄ ይሥሐቅ) አደባባይና ችሎት 82
የንጉሡና የንጉሡ መነኵሴዎች ፍርድ 89

አዲስ ንጉሥ (አፄ ዘርአ ያዕቆብ) ነገሠ፡ ክሱም ታደሰ 90
ከንጉሡ ጋራ የመጀመሪያው ግጭት 92
ፍርድና የግርፊያ ቅጣት 95
"መምህርህ ማነው?" 95
"አዲስ" የገዳም ኑሮ 96
ያለ ንጉሥ ፈቃድ "የእስጢፋኖስ ስም ከፍ ከፍ አለ" 98
ስለደብረ ጽዮን ጉባኤ ተጠራ 99
የንጉሥ ጥሪ 99
"ለምንድን ነው ሁል ጊዜ እንተ የምትለኝ?" 102
ቅጣት 103
ብርቱ ሕመም 104
የንጉሥ ምሕረት 104
አዲስ ክሰ፡ ግርፊያና እስራት 105
ወዲያው የተሻረ አዲስ ምሕረት 105
ለፍርድ ቀረቡ 108
በንጉሡ አደባባይ 109
ክትቦ ወደ ኤፋትና ወደ ጓትር ግዞት 110
አቡነ ገብረ ክርስቶስ ከንጉሡ ፊት 111
የአቡነ አስጢፋኖስ ዕረፍት 111
አስከሬኑን ለማፍለስ የተደረገ ሙከራ 112
ከመቃብሩ ፈውስ ማግኘት አስቆጣ 113
ሬሳቸው አስላም አገር እንዲቃጠል ትእዛዝ መጣ 114
የደቂቀ አስጢፋኖስ አዲስ ስደት 114
አስከሬኑን ከመቃብር አውጥተው ደበቁት 115

ገድለ አበው ወአኃው 117
የታኅሣሥ ፷፩ ምንባብ 119
መግቢያ 119
የደቂቀ አስጢፋኖስ ትምህርትና የአባ አስጢፋኖስ ገድል 119
ጦጵያ ላይ ዓሥር ሞቱ 119
"ለምን እንደ ሰው ሁሉ አታደርጉም?" 120
አስረኛ መጠየቅ ያሳስራል 120
የአባታቸውን ዐፅም ሲያፈልሱ የተያዙ 121
ለመበታተን ገዳም የማማረጥ ዕድል 122
በደጅ ጥናት መጉላላትና "ደብረ ጽዮን"--60 ሰው ተገረፈ 122
አቡነ በርተሎሚዎስና ፈላጊዎቹ ጉንጽ "ክርቸሌ" ገቡ 123
ከመንበርታ ወደ ጓትር--30ውም 123
ወንድም ገብረ ማርያም 124
የቍጥራቸው መብዛት አሰጋ--ጓደኛም ከዳ 126

የንግሥተ ማርያም ዕውቀት፥ ቄራጥነትና ቀኝጅና 127
አምሳ ስባቱንም በማነቆ አስረው አመጧቸው 128
"ተአምረ ማርያምን አጅ አይነሡም" 128
ለመቀጣት አሽቀድድም 128
የንጉሡ ጉባኤና የብሔረ ምርጋይ ስደት 129
አቡነ ገብረ ክርስቶስ 130
አቡነ ዞሲማስ 130
አንደገና ስበስቧቸው--136ቱ የጋሳ ግዞተኞች 130
አቡነ ይሥሐቅና ሊቀ ማኅበሩ 131
ከፍ ያለ ስደትና ብዙ ችግር 132
"ገድለ" ንግሥተ ማርያም 132
ወደ ጦር መምጫ ግዞት 133
የሊቀ ማኅበሩ ጉብኝት 134
"ዶክተር" ያፍቅረነ አግዚእና ባሕታዊቷ 134
ከንጉሡ እደባባይ--ክርክርና ዱላ 136
ፍሬምናጦስ ዘደብረ መገራን እና ቀሌምንጦስ ዘሀገረ ማርያም
ጠላት ሆኑ 137
ንጉሡ በነገሠባት የበዓሉ ቀን ጭቅጭቅ የለም 138
ትልቅ ጉባኤና ክርክር 138
የጸሎት ስዓት ደረስ 140
በአሳት አንፈታተን 140
"ገድለ" አማሆይ መክብዩ 142
የሰንበት ዕለት ምሕረት 142
ወደ ደብረ ቅፍርያ ግዞት--በአስጨናቂ ጉዞ 143
እንደገና ወደ ብሔረ ምርጋይ--40፥ 40 ለመገረፍ 144
አባ ተወልደ መድኅንና የደብረ ዕንፍራዙ መጋቢ 145
የዝራጐን ልጅ ብርሃነ መስቀልና ጉዳሌ 145
ለሐርላ ለዓደል ነጋዴዎች ሳይሸጥ ያመለጠ ወንድም 146
አባ ኤርምያስ ዘገዳመ በኬት 146
"የኢትዮጵያን ሃይማኖት ለምን ከሁለት ትከፍላላችሁ?" 147
የአባ መክሲሞስ ዘደብረ መዓራ ጠላትነት እና የቅፍርያ አስረኞች . . . 147
ጳጳሱ አንዲያወግዟቸው ታዘዙ 148
የቄርቁራ እስረኞችም ወደ ጳጳሱ ተላኩ 150
የጳጳሱ መፍትሔ 150
ወሳኝ ጉባኤ ታዘዘ 151
አዘራት ወደምትባል ምድር ግዞት 153
በአዲስ ክስ አዘራት ከምትባለው ምድር መልስ 154
ንጉሡ ከሹመቱ ያባረረው ተክለ ኢየሱስ ጠላት ሆነ 155
ምላስና አፍንጫ የመቁረጥ ቅጣት ተጀመረ 156

ስለ ደብረ ጽዮን ነገር--እንደገና 157
የቋንጃ መዘዛ ቅጣት ተጀመ፤ የ"ዘ" ክትባትና የጣና ግዞት 158
የረኀብ አድማ 162
የአድማው ውጤት 165
ጸጸትና ንስሐ 166
ተክለ ኢየሱስ ጠላት ሆነ--የንጉሡ ዓዋጅ 167
ሠራተኞቹንና ሠራዊቱን ተቆጣ 170
ግብጻውያን እንግዶች--በምድረ ፈራኅ 170
የሞት ፍርድ 171
ለመቀጣጫ በአምስት ከተሞች ተወገሩ 172
ብርሃን ወረደ 172
ታላቅ ተስቦ በንጉሡ ሰፈር 172
በማኑቆ ከታሰሩ ጋራ ስለሃይማኖት ክርክር 173
"አንዱ እግሬ ተረስቷችሁ ቋንጃውን አላወጣችሁምና ተመለሱ" 173
በአህያ ጭኖ ወደ ብሔረ ኤፋት--በሥቃይ 173
ባለጋራን ለማጥቃት የጠቀመ ዓዋጅ 175
የምድረ ፀጋም ኢትዮጵያውያን 176
"ገድለ" መርቆርዮስ 177
የፈጸጋር መልእክተኞችና መነሾሲቷ 178
መድኃኒት የማጠጣት ቅጣት ተጀመረ--
"ደሙ ... በሱ በራሱ ላይ ነው" 178
የምድረ ጸጋም ዘመቻ 179
አስላሙ የንጉሡ አማች ጠላት ሆነ 179
ኢባ "ደብረ ብርሃን" ተባለች 180
አበስኪሮንና እስጢፋኖስ ዋጋቸውን አገኙ 181

የመጋቢት ጅጅ ምንባብ 183
መግቢያ 183
ከመንበርታና ከዓጋሜ የተያዙ አስረኞች 183
ሃይማኖት የሚያስተው ሥቃይ 184
የዕርቅ ድርድር 184
የጦር ጎይሉ (የሠራዊቱ) ዓይነት 185
ተለቅቆ እንደገና ተያዘ 186
የግራ ስዎች ወረራ 187
ጉዳት ያደረሰው ከዳተኛ ወንድም 187
ምስጢረ ሥላሴ--ክርክር 187
ወደ ሀገረ በሊ ግዞት 189
አባ ሀብተ ማርያም ዘደብረ ሊባኖስ ጠላት ሆኑ 190
መጽሐፈ ብርሃን 191

መሐላ አልታዘዘም--ጊዮርጊስና ኢሳይያስ 191
እስረኛ ጎብኚዎቹ ታሰሩ 192
ያላለቀ የብሔረ በሊ የግዞት ጉዞ--"ስይፈን እታደንዝብኝ" 192
ከቆገት ወደ ፈጸጋር የተላኩ ታሰሩ 196
ተስቦ ገባ 196
ሹም ተስፋኑ ክርስቶስ ጠላት ሆነ 196
አባ ብእሴ ሰላምና አባ ሳሙኤል ጠላት ሆኑ 197
"በል እንደ ወንድ ውጋ" 198
እንደገና ተስቦና እፈላ--"እጆን እንድንላስመው የታለ?" 199
ብእሴ ሰላምና ሳሙኤል ሌሎችን አስገደሉ 200
በምድረ ቆገት የተያዙ 2 ወንድሞች 201
"እንደፈሪ ... ፊቴን አልሸፋፈንም" 202
በምድረ ጠዞ በረኃብ የሞተው 203
ምድረ ጋዘም ላይ የተያዙት ታረዱ 203
አባ ዘታኦስ ዘሰርማት ያመጡት ጉዳት 205
የወንድም ገብረ ዋሕድና የእማሆይ ማርያም ሠምራ ጸሎት 206
ቍራን የሚያመጣ የደብረ ብርሃን ብርድ 206
አባ ዕዝራ የያዟቸው በቀጋ እሾክ ተገረፉ 206
በገን ያሉት ደቂቀ አስጢፋኖስና ነገረ ፈጃቸው 207
የለከማ አስረኞች÷ እነ አባ አቡናፍር 208
የመጋርዳ አስረኞች 209
የመጨረሻው ታላቅ ጉባኤ 209
የወንድም ፍሬ ክርስቶስ አጠቃላይ ክስ 212
የደራሲው ማጠቃለያ 212
የንጉሡ የመጨረሻ ሙከራ 214
የሶስቱ የጦር ኀይል ክፍሎች ፍርድ 215
ምዕዳን 215
አሁንም አልሞቱም፤ ይነጋገራሉ 218
ወንድም ሊቃኖስና ረዳቱ 219
ቦሌ የሚጠጣው መምህር በርሶማና ወንድም መንቆርዮስ 219
የንጉሡ ፍጻሜ 221

የአባ አበክረዙን ገድል 225
መግቢያ 227
ትውልድና እስተዳደግ 227
መንፈላዊ ጥሪ 229
ምንኵስና 230
ከአባ አስጢፋኖስ ጋራ 230
መነኮሳቱ በአባ አስጢፋኖስ ላይ ተነሡ 231

ተሰድደው ለሥቃይ ተመለሱ 232
ተሰድደው የራሳቸውን ማኅበር (ገዳም) አቋቋሙ 233
ሰላማዊ ኑሮና እድገት 235
አባ አበክረዙን እልቅና ተመረጡ 236
ሰይጣን ሞገድ አሰነሣ 236
አባ አበክረዙን ከንጉሡ ፊት--ዕርቅ አልተቻለም 237
አባ እስጢፋኖስ ከንጉሡ ፊት 237
በአፈሳ ከንጉሡ ፊት 238
ወደ ምሥራቅ ስደት 239
አባታቸውን ሲፈልጉ ተያዙ 240
ምህልላ ያዙ 241
ወደ ሌሎች አገሮች ስደትና እስራት 241
በእርሻ ላይ ረኀብ 241
ሱባኤ 242
በየሀገሩ ያሉ እስረኞችን ጉብኝት 243
ሱባኤ 246
ብቃት 248
በብዙ አገሮች በዙል ወደ ትግራይ መልስ 248
ሰይጣን ተነሥቶ የአጋንንቱን ሽብር አሰነሣ 249
የመነኮሲቶቹ ጥያቄ መልስ አገኘ 249
የአባታቸውን ተዝካር ሲያወጡ ተከበቡ 250
ደጋፊ ከሚያገኙበት አገር ደረሱ--ዮሐንስና በኮረ ጽዮን 251
ታብርሃ ጽዮን 252
ለአዲስ ሰይጣናዊ ክስ መዘጋጀት 253
ዋሻ ውስጥ ወምበዴ ዘረፋቸው 255
በተምቤን ምድረ በዳ 256
በተቃጠለችባቸው ቤተ ክርስቲያን ምትክ 257
ቃለ ምዕዳን 258
ከዳተኛው ባስልዮስ 265
ከማይድን በሽታ ላይ ወደቁ 269
ሶስቱ የምንኮስና መንገዶች 273
"ከኢትዮጵያ ጋራ እየተፋረድኩ ነው" 276
ዘለዓለማዊ ዕረፍትና ቀብር 276


የአባ ዕዝራ ገድል 279
መግቢያ 281
ትውልድና አስተዳደግ 281
ምንኮስና 282
በቤተ እስጢፋኖስ ላይ ስለመጣ ግፍ 283

ካህን ቸገረ--የኢየሩሳሌም ጉዞ 283
በመንገድ ላይ የተነሣ ሁከት 285
የማርያው ሹም አስታራቂ ዳኝነት 286
በበረሐ የአምላክ ረድኤት 286
የአባ አስጢፋኖስ ዕረፍት 287
በምድረ በዳ ስንበት ማክበር 287
ኢየሩሳሌምም ተጨቃጨቁ 288
ለነአባ ዕዝራ ብርሃን ወረደላቸው 290
የአቡነ ዕዝራ ተግሣጽ 291
ፈተና 291
ክህነት ከማን መንበር ጳጳስ ይቀበሉ? 292
ወደ ኢትዮጵያ መልስ 293
ንጉሥ ናኦድ አቡነ ዕዝራን ስለመፈለጉ 293
ንጉሥ ናኦድ አቡነ ዕዝራን በክብር ተቀበላቸው 294
ከጳጳሱ (ከአቡነ ይሥሐቅ) ፊት 296
በቀድሞ ጳጳሳት የተገዘቱት ተፈቱ 297
አቡነ ዕዝራና ወንድሞቻቸው ከንጉሡ ፊት ቀረቡ 297
በንጉሡ ትእዛዝ የሃይማኖት ክርክር ተደረገ 297
የንጉሡ ፍርድ 301
ስለ ተግባረ እድ የንጉሡ ጥያቄና የአባ ዕዝራ መልስ 301
አባ ዕዝራና ወንድሞቻቸው ለሥራ ወደ አለመሌ ተላኩ 302
የአባ ዕዝራ ጸሎት በሽተኛ ፈወሰች 302
የወፍጮው መሣሪያ ተገጣጠመ 303
ወፍጮው በንጉሡ ፊት ተሞከረ 304
አቡነ ዕዝራና ደቂቀ አስጢፋኖስን የሚጠላ መኰንን 305
የጳጳሱ በጎ ሥራ 307
አቡነ ዕዝራ ለንጉሡ የሬሳ ሳጥን ሠሩለት 309
አቡነ ዕዝራና የቀንጡራሬ መነኮሳት 309
የንጉሥ ናኦድ ዕረፍት፥ የአቡነ ዕዝራ ሽሽት 310
ሰይጣን ሞገዶቹን አስነሣ 311
በጠና በሽታ ላይ 311
ዘለዓለማዊ ዕረፍት 312
መርዶ 312
አስከሬኑን አምጡ 313

ዋቢ መጻሕፍት 315
መጠቀሚም (በአቶ አምጎ አስፋው) 321

ሥዕሎች

ተርጓሚው እና ዓለማየሁ 3
የአርባዕቱ ወንጌላት አቅማራት (EMML 7219, f. 13a.) 20
አግዝአትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ
(ከደቂቀ አስጢፋኖስ መጽሐፍ÷ MS Spencer 7, f. 4a.) 22
የንቅናቄው መሪ አቡነ አስጢፋኖስ
(ከደቂቀ አስጢፋኖስ መጽሐፍ÷ MS Spencer 7, f. 4b.) 56
የማቴዎስ የማርቆስ የሉቃስ ወንጌል አቅማራት
(EMML 7219, f. 14b.) 116
በግብጽ ምድረ በዳ የብሕትውና ምንኵስናን የጀመሩ አባ አንጦንስ
(ከደቂቀ አስጢፋኖስ መጽሐፍ÷ MS Spencer 7, f. 3b) 118
በግብጽ ምድረ በዳ በብሕትውና የኖሩ አባ ጳውሊ
(ከደቂቀ አስጢፋኖስ መጽሐፍ÷ MS Spencer 7, f. 2a.) 182
በግብጽ ምድረ በዳ የማኅበር ምንኵስናን የጀመሩ አባ ጳኮሚስ
(ከደቂቀ አስጢፋኖስ መጽሐፍ÷ MS Spencer 7, f. 2b.) . . . 224
የደብረ ገርዜን ሁለተኛው አበምኔት አቡነ አበክረዙን
(ከደቂቀ አስጢፋኖስ መጽሐፍ÷ MS Spencer 7, f. 113b.) 226
የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌል አቅማራት (EMML 7219, f. 15a.) 278
አግዝአትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ
(EMML 7219, f. 21b.) 280



ቀዳሚ ቃል

በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተተረጎመው የደቂቀ አስጢፋኖስ ስቆቃ ያስደነግጣል፤ ያሳዝናል፤ ያስቆጣል፤ የማናውቀውን ራሳችንን እርቃናችንን ያሳየናል። ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላም ፍንክች አለማለታችን ውስጣችንን አንድንመረምር ያስገድደናል። ይህንን መጽሐፍ ሳነብብ ምዕራባውያን (በእንግሊዝኛ) "ቶርቸር" (የግዕዝ ጸሐፊዎች "ኮነኔ") የሚሉትን ስውን የማሰቃየትን ዘዴ እኛ የፈጠርነው መሰለኝ። ቻይናውያን በዚህ ክፉ ዘዴ እንደሚታሙ አውቃለሁ፤ እኛም ሆንን ቻይናውያን የታሪካችንን ርዝመትና ያለንበትን የደኻነት አዘቅት ለመገንዘብ ይህ የክፋት ዘዴአችን ማስረጃ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ይመስለኛል። ከሰዎች በፊት በሥልጣኔ በራፍ ላይ ደርሰን ከኋላችን የመጡት በአዳራሹ ሲገቡ እኛ አሁንም ውጭ ቆመን መቅረታችንና በልመና የምንኖር መሆናችን የገዢዎቻችን የአፈና ተግባር የማይቀር ውጤት ሆኖ ነው። በሕገ አራዊት አየተመራን የሰውነት ህብታችንን፥ አእምሮአችንንና መንፈሳችንን ታፍነን ኑሮአችንን የምናሻሽልበትን ዘዴ ለመፍጠር አልቻልንም።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ መንፈሳዊ ወኔ የነበራቸውና ሐሳባቸውንና አምነታቸውን ማንንም ሳይፈሩ በአደባባይ ለማውጣት የቻሉ ሰዎች መገኘታቸው ከአፈናው ባሻገር ጭራሹን ባዶ አለመሆናችንን ያሳየናል። ትልቁ ነገር የነዚህን የደቂቀ አስጢፋኖስን ሐሳብና አምነት መቀበል ወይም አለመቀበል አይደለም፤ ትልቁ ቁምነገር አባ አስጢፋኖስ በማንም አፍአዊ ኃይል ተመርተው ወይም ተገድደው ሳይሆን በራሳቸው የውስጥ የአእምሮ ብርሃን ተጉዘው ከ"ሲወርድ ሲዋረድ" አስተሳሰብ ተላቅቀው ወደአንድ መደምደሚያ ላይ መድረሳቸው ነው። ለማንም ማጎበረስብ ለትምህርትና ለዕውቀት፥ ለአድገትና ለመሻሻል፥ የልማትና ለብልጽግና አዲስ ፊርን አየቀደዱ አዳዲስ ደረጃ ላይ የሚያደርሱት እንደዚህ ያሉ ሰዎች ናቸው። በኢትዮጵያ አንዲህ ያሉ ሰዎች እንደተወርዋሪ ኮከብ ብልጭ አያሉ ድርግም በማለታቸው አገሪቱ ከነሱ ልታገኝ የምትችለውን ዘለቄታ ያለው ጥቅም አጣች። የኢትዮጵያ ሊቃውንት "ሲወርድ ሲዋረድ" በሚል በማያስብና በማያሳስብ የቁልቁለት አስተሳሰብ ለብዙ ምእት ዓመታት ተጓዙ፤ ውጤቱ ዛሬ ያለንበት ደረጃ ነው።

የኢትዮጵያ የቤተ ክህነት ትምህርት አእምሮን የመሳል ከፍተኛ ችሎታ እንዳለው አያጠራጥርም። የተሳለና የሠለጠነ አእምሮ በጥልቀት ያስባል፤ ትክክለኛ የአስተሳሰብ ስልት በመከተልም አዲስ ሐሳቦችን

ያፈልቃል፣ አዲስ ሐሳቦች አዲሱን ትውልድ ወደአዲስ የእድገት ደረጃ ሳይ ያወጡታል፤ አዲስ ሐሳቦች ከቀዩ ሐሳቦች ጋራ እየተጋጩ በሕገ ጎልዮት ያሸነፈው ይቀጥላል፤ የተሸነፈው ይሞትና ወደታሪክ ማጎደር ይገባል። ወይም አዲሱና አሮጌው ተፋጭተው ከሁለቱም ውሕደት ሌላ አዲስ ሐሳብ ይወጣል። የምዕራቡ ጎብረተሰብ የተጓዘበት ዕውቀትን የማስፋት መንገድ ይህ ነው። በደቂቀ እስጢፋኖስ ሰቆቃ በግልጽ የምናየው ግን በእኛ ማጎበረሰብ አዲስ ሐሳብ ጠፋት ሆኖ መታየቱን ነው፣ ሕገ ጎልዮት በሕገ አራዊት መደቆሱን ነው። ሐሳብን በሐሳብ መቋቋም የማይችሉ የሥልጣን ጉጉት የእእምሮ ስንኩላን ያደረጋቸው የሚቀናቸውና የሚቀልላቸው የሚጠሉት ሐሳብ ማጎደር የሆነውን ሰው ማጥፋቱ ነው። የኖረውን ያለውን በግድ ተቀበሉ እየተባለ አዲስ ነገርን ማሰብና መግለጽ አደገኛ ተግባር እየሆነ ይሄዳል። በዚህም ምክንያት ማሰብን ማስቀረት የማይቻል ቢሆንም ሐሳብን በግልጽና በማያሻማ ቋንቋ ማውጣቱ ለኢትዮጵያውያን እስከዛሬ አስቸጋሪ ነው፤ ስውርና የተለባበሰ አነጋገር እስከዛሬም ባህላችን ሆኖ የቆየ ይመስለኛል።

ስለደቂቀ እስጢፋኖስ የተጻፈው ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክና ባህል በአዲስ መንፈስ እንደገና እንድንመረምር የሚጋብዘን ይመስለኛል። ኢትዮጵያን የአይሁድ አገር ለማድረግ፣ የክርስቲያን አገር ለማድረግ፣ የእስላም አገር ለማድረግ የጠፋው የሰው ሕይወት፣ የፈሰሰው የሰው ደም፣ የወደመው ንብረት ለሕገ አራዊት እንደተገበረ መሥዋዕት ልንወስደው የምንችል ይመስለኛል። የሚያሳዝነው ለሕገ አራዊት መገበሩ ገና ዛሬም አለማብቃቱ ነው። ይህ ነው እያንዳንዳችን ራሳችንን እንድንጠይቅ የሚያስገድደን፣ ምንድን ነው በእኛ ውስጥ ወይም በባህላችን ውስጥ ሐሳብን እንደጠር የሚፈሩ ሰዎች አናታችን ላይ እንዲወጡ የሚያደርጋቸው? በተራው ኢትዮጵያዊም ዘንድ ቢሆን ይኸው ሐሳብን የመፍራት አዘማማያ እንዴት ባህል ሆነ? ጭቆናን የኢትዮጵያውያን ባሕርይ ያደረገው ምንድን ነው? ከማንም ሕዝብ የተለየ የጭቆና ዝንባሌ የለንም የሚሉ ሰዎች አሉ። ይህንን እውነት ለመካድ መሞከሩ አይረዳንም፣ መድኃኒት የሚሆነን መቀበሉና መመርመሩ ነው።

ጌታቸው በመግቢያው ላይ ደቂቀ እስጢፋኖስ ከማርቲን ሉተር ሠላሳ ዓመታት ቀድመው ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያመጡ ሰዎች ነበሩ ይላል። ይህ ትልቅ ነጥብ ነው፣ ማርቲን ሉተር በአውሮፓውያን አእምሮ ላይ ያመጣው የአስተሳሰብ ለውጥ በሃይማኖት ላይ ብቻ ሳይሆን በይበልጥም በዓለማዊው ጉዳይ ላይ የነበረው ተጽእኖ ማክስ ቬበር በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መሀከል የተፈጠረውን ልዩነት ለማሳየት በዘገበው አንድ የቀልድ አባባል ይገለጣል፤--"ወይ በደንብ ብላ፣ ወይ በደንብ ተኛ።"[1] ለዚህ የቬበር መጽሐፍ ቀዳሚ ቃሉን የጻፈው የእንግሊዙ የኢኮኖሚክስ ታሪክ ሊቅ ታውኒ ፕሮቴስታንትነት በአመጣው ለውጥ "ሥራ የኑሮ ዘዴ ብቻ ሳይሆን

1. Max Weber (tr. Talcott Parsons), *The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism*, New York, 1958, p. 41.

መንፈሳዊ ዓላማም አገኘ" ይላል::[2] እአምሮ ከአፈና ሲወጣና ነፃነትን ሲያገኝ ከሰው ልጅ ውስጥ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ይወጣል፤ ወሰኑ የማይታወቅ የመፍጠር ችሎታ በተጨባጭ ተግባር ይገለጣል:: በዓለም ውስጥ ዛሬ በበለጸጉትና በሚደኸዩት አገሮች መሀከል ያለው ትልቁና ዋናው ልዩነት የአእምሮ ነፃነት ነው:: ለምሳሌ በሚደኸዩት አገሮች ውስጥ ባለው ግዙፍ የተፈጥሮ ሀብት ይበልጥ የሚጠቀሙበት የበለጸጉት አገሮች ናቸው:: በደቂቀ እስጢፋኖስም ላይ ቢሆን የአእምሮ ነፃነት ከሃይማኖት እጥር ውጭ ያለውን ዓለም የማሻሻል ችሎታን እያሳየ ነበር፤ እባ ዕዝራ ስለተግባረ እድ ተጠይቀው ሊያደርጉ የሚችሉትን ሁሉ ሲዘረዝሩ፤ የእግዚአብሔር እስትንፋስ በውስጣቸው መኖሩን ያልተገነዘበው የንጉሡ መልእክተኛ መልስ "ይህን ሁሉ እደርጋለሁ የምትለው እግዚአብሔር ነህ እንዴ?" የሚል ነበር::

እንድ ተጨማሪ ነጥብ መነሣት ያለበት ይመስለኛል፤ ከዕለት ተዕለት የኑሮ ትግል በቀር ማሰብን እንደሙያ የያዙ ሰዎች ከሃይማኖት ውጭ በኢትዮጵያ ነበሩ ለማለት ያስቸግራል፤ እነዚያውም በሃይማኖት እጥር ውስጥ ሆነው የማሰብ ችሎታቸውን ያሳዩ ሰዎች--እንደእባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው፥ ከዚያም በኋላ እንደፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ ያሉት--ለስደትና ለስቃይ መዳረጋቸው፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ማሰብ የተከለከለ ተግባር መሆኑን ነው:: ትምህርቱ በተራቀቀበት በሃይማኖቱ እጥር ውስጥ ማሰብ ከተከለከለ ትምህርት በሌለበት ከሃይማኖቱ እጥር ውጭ ማሰብ ጨንግፎአል ማለት ላይሆን እይቀርም:: በሃያኛው ምእት ዓመት የዘውዱ ሥርዓት ከፈጠረውና ከብዙ ዓመታት ትግል በኋላ የኢትዮጵያ መካነ ጎልዮት ከሆነው፥ ደርግ ቢያዳክመውም ካልገደለው ዩኒቨርሲቲ ወያኔ እርባ መምህራንን ማስወጣቱና ብዙዎቹን ለስደት መዳረጉ የሚያመለክተው እለመለወጣችንን ብቻ እይደለም፤ ከሃያኛው ምእት ዓመት ወደኋላ ተመልሰን እውንም በኢትዮጵያ ማሰብ የተከለከለ መሆኑን ነው:: በዚህም እኩይ የወያኔ ማን አለብኝነት ዩኒቨርስቲውን ቢያንስ ሠላሳ ዓመታት ወደኋላ እንደመለሱት ማሰብ ስለሚሳናቸው ሊገባቸው እይችልም፤ የአገሪቱን ዓይን እንደማጥፋት የሚቆጠር ነው::

ጌታቸው ስለደቂቀ እስጢፋኖስ "እበባቸውን አረገፉት፤ የእንቅስቃሴያቸውን ነበልባል ውሐ ቸልሰውበት ሳይቀጣጠል ቀረ" ሲል የደቂቀ እስጢፋኖስን ሐሳብና እምነት መዳፈን በሚገባ ይገልጠዋል:: ውጤቱ ግን በደቂቀ እስጢፋኖስ የተወሰነ እልነበረም፤ በእጠቃላይ በኢትዮጵያ የእእምሮ ነፃነት ተዳፍኖ እንዲቀርና ኢትዮጵያ በልጆቿ የእእምሮ ኃይል እንዳትጠቀምበት ሆኗል:: ይህም ደኻነታችንንና ኋላቀርነታችንን ፍንትው እድርጎ የሚያስረዳን ይመስለኛል::


ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ባንቱስታን-መሰል የጎሳ ክፍፍል በሚታመስበትና በጥላቻና በመፈራራት መንፈላዊ ወኔው ተሙዋጥጦ ባለበት ጊዜ የደቂቀ እስጢፋኖስ ታሪክ ልዩ መልእክት አለው፤ እገዛዙ ምንም ያህል

2. *Ibid.*, p. 3.

በሕገ አራዊት ላይ የተመሠረተ ክፉ ጭካኔ ቢያላይም የሰው ልጅ መንፈስ የማይበገርና አምቢ ባይ መሆኑን ያሳየናል። ቁምነገሩ ደቂቀ እስጢፋኖስ መሸነፋቸው አይደለም፤ ቁምነገሩ እየተሰቃዩ መታገላቸው ላይ ነው፤ ለሕገ እራዊት እንንበረከክም ማለታቸው ነው። በጣም የሚያስደንቀው ነገር እንድም የደቂቀ እስጢፋኖስ እባል ሲሞት ሞተ እለመባሉ ነው፤ "ሰማዕትነቱን" ወይም "ገድሉን ፈጸመ" ይላሉ። ይህ እስተሳሰብ ጥልቅ መልእክት ያለው ሆኖ ይሰማኛል። የሰው ልጅ ሕይወት እንደእንስሳ ሕይወት አይደለም፤ ዓላማ እለው፤ መልእክት እለው። ቁምነገሩ ዓላማውን ወይም መልእክቱን መፈጸም ነው አንጂ መኖር ብቻ አይደለም፤ ሐሳብንና እምነትን እንደያዙ በነፃነት ማለፍ ሐሳብንና እምነትን አስረግጠ ከመኖር የተሻለ ነው ብለው የሚያምኑ ይመስለኛል። ለዛሬው ትውልድ ይህ ኃይለኛ መልእክት ነው።

የዛሬው ትውልድ ለፕሮፌሰር ጌታቸው ባለውለታ ነው፤ እነዚህ ለዐዋቂው ለውጪው ዓለም ክፍት ሆነው፥ ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተቆልፈውበት የነበሩ ጽሑፎች ናቸው። እስከዛሬ እንድም ንጉሥ ወይም ፕሬዚዳንት እነዚህን ታሪካዊ ሰነዶች እላስተረጎመና አላሳተመም። ጌታቸው በራሱ ጥረት ብቻ እነዚህን ጽሑፎች በእማርኛ አየተረጎመ ለመጀመሪያ ጊዜ ለንባብ ስላበቃቸውና ስለራሳችን እንድንማር በሩን ስለከፈተልን ከፍተኛ ምስጋና ይገባዋል። በበኩሌ የምጨምረው በዚህ ሳያበቃ እግዚእብሔር ዕድሜውንና ብርታቱን ሰጥቶት ሌሎቹንም እንዲያበረክትልን ነው።

መስፍን ወልደ ማርያም



መቅድም

አባቶቻችን በግዕዝ ያወረሱንን የባህልና የታሪክ ቅርስ በአማርኛ ለዛሬው ትውልድ ለማላወቅ ባለኝ ምኞትና አቅድ መሠረት አነሆ ይህንን ሶስተኛውን መጽሐፍ--የአባ አስጢፋኖስንና የተከታዮቻቸውን ገድሎች--አቀርባለሁ። አንደኛው መጽሐፍ *ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቁጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ* በሚል ርእስ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.፥ ሁለተኛው መጽሐፍ *የአባ ባሕርይ ድርሰቶች አሮምኛን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ* በሚል ርእስ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. ታትመዋል። አምላክ ፈቃዱ እስከሆነ ድረስ ጥረቱ ይቀጥላል፤ ፈቃዱ ቢሆንም ባይሆንም፥ መከሩ ብዙ ስለሆነ ለአማርኛ አንባቢዎች የመከሩን ጌታ የምለምንላቸው ወደ መከሩ ብዙ ሠራተኞች እንዲልክ ነው (ማቴ 9: 37-38)።

ለዚህ መጽሐፍ የመረጥኳቸው "የአባ አስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ገድሎች" የምላቸው *ገድለ አባ አስጢፋኖስን፥ ገድለ አበው ወአኃውን፥ ገድለ አባ አበክረዙንን፥ ገድለ አባ ዕዝራን* ሲሆን የማቀርበው የገድሎቹን የአማርኛ ትርጕሞቼን ነው። በመግቢያው እንደምገልጸው፥ የአባ አስጢፋኖስ ተከታዮች የሚታወቁት "ደቂቀ አስጢፋኖስ" በመባል ነው። ክረጅሙ ታሪካችን ውስጥ ለዛሬው አነዚህን ገድሎች የመረጥኩት ደቂቀ አስጢፋኖስ ከአኛ ዘመን በፊት ለእምነታቸው ምሳሌ የሌለው ከፍተኛ ትግል ያሳዩ ሆነው ስላገኘኋቸው ነው።

አዚህ በስደት በምኖርበት አገር አንዲት ኢትዮጵያዊት የዩኒቨርስቲ ተማሪ አግኝቼ ስንወያይ በጨዋታችን ላይ የደብረ ብርሃን ልጅ መሆኗን ነገረችኝ። "ከተማዋን የቁረቁሯት ዘርአ ያዕቆብ ናቸው ይባላል፤ መነኮሴ ነበሩ ወይ?" ብላ ጠየቀችኝ። የሀገርሽን ታሪክ አንቺ ንገሪኝ አንጂ" ብዬ ግዴታዋን ካስታወስኳት በኋላ የማውቀውን ነገርኳት።

"ደብር" የሚለው ቃል አንደ ደብረ ሊባኖስ፥ አንደ ደብረ ዳሞ ከገዳም ጋራ የተያያዘ ስለሆነ ስለ ደብረ ብርሃን ያላት ግምት ጭፍን ሙላ አልነበረም። ሆኖም ገዳም ያልሆኑትን አነደብረ ማርቆስን፥ አነደብረ ሲናን ልታስታውስም ትችል ነበረ።

ጥያቄዋን እዚህ ያነሣሁት ከዚህ ዛሬ ከማቀርበው መጽሐፍ ጋራ በሁለት በኩል በመያያዝ የትርጓሜ ጥረቴን የሚያጸድቅልኝ ሆኖ ስላገኘሁት ነው። የተያያዘው ባንድ በኩል ስለ ደብረ ብርሃን ስያሜ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ስለአሁኑ ወጣት ትምህርታዊ አስተዳደግ ነው። የስያሜውን ታሪክ ቀጥሎ የማቀርበውን መግቢያ እደመድምበታለሁ። አሁን የዛሬው ወጣት


ትምህርታዊ እሰተዳደግ ከዚህ ዛሬ ከማቀርበው መጽሐፍ ጋራ ግንኙነት አለው ያልኩበትን ምክንያት ላብራራ::

ያሁኑ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው መንገድ ታሪኩን እንዳያውቅ ህገሪቱ ብዙ መሥዋዕት ከፍላ ያመጣችው ዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርት ከዚያ መንገድ እውጥቶ መስዶታል፤ ያ ሊያስተምረው የወለደው ሥርዓት እንዳያስተምረው ደግሞ የህገሩን ታሪክ ለማስተማር በቂ ዝግጅት አልነበረውም:: ሰለዚህ የህገሪቱ ጥረት በብዙ ረገድ የሚመሰገን ሆኖ ሳለ÷ ልጆቿን የህገር ታሪክ መሃይምናን አድርጎባታል:: አዲሱ ሥርዓት ታላቁ ዘርአ ያዕቆብ ማን እንደሆነ የማያውቁ የኮሌጅ ተማሪዎች (ያውም የደብረ ብርሃን ልጅ) አፍርቷል::

መቸም ያላስተማሩትን ልጅ ለምን አታውቅም ብሎ የሚወቅስ የለም:: እንግዲህ የፈሰሰ ሰለማይታፈስ የተሻለው መፍትሔ ወተቱን እንዳዲስ ማለብ ይመስለኛል:: ሙከራዬ ያንን ለማድረግ ነው::

ባንዱ መጽሐፌ ውስጥ የገለጽኩት ዕውቀት በሌላው መጽሐፌ መነሣት ሲያስፈልገው÷ በጽሕፈት ዓለም እንደተለመደው÷ ቀደም ብሎ በተጻፈው መጽሐፍ ውስጥ የተገለጠበትን ገጽ አመለክታለሁ እንጂ÷ እንደገና በመግለጽ ጊዜያችሁንና ጊዜዬን አላጠፋም:: ሰለዚህ ከኔ ጋራ ለመቆየት የፈለገ ሁሉ ቀድመው የታተሙትን መጽሐፎቼን ቢያገኝ ይጠቅመዋል::

ሌላው በዚህ አጋጣሚ ላስታውሰው የምፈልገው÷ በውጭ አገር ሊቃውንትና በኔም የታተሙ ብዙ ምንጮችን የምጠቅስ መሆኔን ነው:: ሆኖም ምንጮቹ የውጪ አይደሉም፤ ዋቢ ሰነዶቹ በውጭ ሊቃውንትና በኔም ተጠንተው ይታተሙ እንጂ÷ ደራሲዎቹ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ናቸው::



የፊተኞቹን ሁለቱን መጻሕፍት ሳዘጋጅ የረዱኝ ባለቤቴ ምሥራቅ አማረ÷ አጎታችን ወይዘሮ ማርታ አማረ÷ ወዳጄ አቶ አምነ አሰፋው ይኸንን መጽሐፍ ሳዘጋጅም በዚያው መጠን አብረውኝ ነበሩ:: ምሥራቅ ረቂቁን በመቀምር በመምታት፤ ማርታ የፊደል ግድፈት በመልቀም፤ አምነ ግልጽ ያልሆኑ አነጋገሮችን በመጠቆም÷ የፊደል ግድፈት በማረም÷ መጠቀሙንና ዋቢ መጻሕፍቱን በማዘጋጀት÷ በመጨረሻም ለመጽሐፉ ይኸንን መልክ በመሰጠት ረድተውኛል:: ይኸንን ሁሉ እኔው ራሴ ብቻዬን ለማድረግ ባለመገደዴ ራሴን ዕድለኛ አደርገዋለሁ:: በተለየ የአምነን እርዳታ ባላገኝ መጽሐፉ ለኅትመት አይበቃም ነበረ:: የረጅም ዘመን ወዳጄ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ረቂቁን አንብቦ እንደሱ "ሕግ ይዳኘን" ከማለት በምንም ምክንያት ወደ ኋላ ላላሉ ኢትዮጵያውያን ታሪክ መግቢያውን የሚያዳብር "ቀዳሚ ቃል" ስለጻፈልኝ አመሰግናለሁ::

ለገድለ እስጢፋኖስና ለገድለ አበክረዙን ጥናቴ የኒው ዮርክ ሕዝባዊ ቤተ መጻሕፍት (Spencer Collection, The New York Public Library, Astor,

Lenox and Tilden Foundation) የSpencer 7ን ቅጂ፥ ለገድለ አስጢፋኖስ በተጨማሪ የሮማው የሊንቼ ሕዝባዊ አካዴሚ (Accademia Nazionale dei Lincei, Roma) በወዳጄ በፕሮፌሰር ላንፍራንኮ ሪቺ (Professor Lanfranco Ricci) እርዳታ የConti Rossini 48ን ቅጂ ስላቀረቡልኝ፥ መሥሪያ ቤቴ የቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ የማይክሮፊልም ቤተ መጻሕፍት (Hill Monastic Manuscript Microfilm Library, Saint John's University, Collegeville, Minnesota) የገድለ አበው ወአኃውን ቅጂ (EMML 4) እና አስፈላጊ የቢሮ ድጋፍ ስላቀረበልኝ፥ ወዳጄ ዶ/ር ታየ አሰፋና አቶ ውዱ ጣፈጠ ካሱ አዲስ አበባ አለ የተባለውን የገድለ አስጢፋኖስን ቅጂ ሊያገኙልኝ ስለደከሙ፥ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጻሕፍት የገድለ አበው ወአኃውን ቅጂ (ቍጥር 496) ዶ/ር ታየ አሰፋ እንዲቀዳልኝ በአቶ ደመቀ ብርሃኔ አማካይነት ስለፈቀደ ለሁሉም ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።


ይህ መጽሐፍም እንደ የአባ ባሕርይ ድርሰቶች ከአሜሪካኖቹ ዕለተ አኰቴት (Thanksgiving Day) ጋራ የተያያዘ ታሪክ አለው። የአባ አስጢፋኖስን ገድል ወደ አማርኛ የተረጐምኩት ልጃችን ሶስና የ2002 ዓ. እ.ን ዕለተ አኰቴት በዓል አብረናት ከቤተሰቧ ጋራ እንድናከብር፥ በዚያውም የሚኒሶታን ብርድ ለአንድ ወር ያህል አንድንርቅ፥ ከሁሉም ይበልጥ ግን ዓለማየሁን ስትገላገል አጠገቧ ሆነን "ማርያም፥ ማርያም" እንድንል ጋብዛን ሎስ አንጀለስ (ፓሳዲና) በነበርንበት ጊዜ ነው። በአምላክ ቸርነት ልጂን በሰላም ተገላግላ እንደገና አያቶች ለመሆን በቃን። የአኰቴቱን ዕለት ግን አብራን አልነበረችም፤ "ልጅ" ዓለማየሁ በመምጣት ላይ መሆኑን የበዓሉ ዋዜማ ላይ ስላስታወቀ፥ እናት አባቱ አራቱንም አያቶች ከቤታቸው ትተው ሐኪም ቤት ሄደው እዚያው አደሩ፤ ዕለቱንም እዚያው ዋሉ። ታሪኩ መጽሐፉን ለዚህ ዕለት መታሰቢያ ለማድረግ ተጨማሪ ምክንያት ሆነ።

ማስታወሻ:

(1) ምንጮችን በማስረጃነት በግርጌ ጎዳግ ላይ ስጠቅሳቸው መጀመሪያ ሙሉ አርእስታቸውን እስማለሁ፤ ከዚያ በኋላ እነሱኑ መጥቀስ ሲያስፈልገኝ መጀመሪያቸውንና ገጾቹን ብቻ እንጂ ሙሉ አርእስታቸውን አልደጋግምም። ሙሉ አርእስታቸውን ለማወቅ የሚፈልግ ወደ መጨረሻው በ"ዋቢ መጻሕፍት" ክፍል በየደራሲዎቻቸው ስም ተዘርዝረው ያገኛቸዋል።

(2) ስተረጉም የገድሎቹን የግዕዝ ገጾች/ቅጠሎች እየሰጠሁ ነው። ጥቅሙ ግዕዙን ከኔ ትርጉም ጋራ ለማስተያየት የሚፈልግ ያለበትን በቀላሉ እንዲያገኘው ነው። መቸም የግዕዝና የአማርኛ የዓረፍተ ነገር አሰካክ የተለያየ ስለሆነ አቅራቢያውን እንጅ ግዕዙ የሚጀምርበትን ልኩን ለማሳየት ፈጽሞ አይቻልም።

ጌታቸው ኃይሌ



የአርባዕቱ ወንጌላት አቅማራት
(EMML 7219, f. 13a.)

መግቢያ

"ጽኑ ነቢይ ሲነግ እንደዚሁ ጽኑ ንጉሥ ያስነግል"

አባ እስጢፋኖስ



እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ
(ከደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሐፍ፡ MS Spencer 7, f. 4a.)



ደቂቀ እስጢፋኖስ

ታሪካቸውን እዚህ የማቀርበው አባ አስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው (ደቂቀ አስጢፋኖስ) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸው አንዲያውም የተወገዙ አድርጋ የምታያቸው በዓሥራ አምስተኛው ምእት ዓመት ያበቡ የተሐድሶ አንቅስቃሴ መሪዎች ናቸው። አሕይዎና ተሐድሶ (Revival and Renewal or Reformation) ተደላድሎና ተመቻችቶ በተቀመጠው ሥርዓት (Establishment) ውስጥ የዛገና የሚራገፍ ነገር የሚያይ የአእምሮ ችሎታና የተፈጥሮ ተሰጥዎ ካላቸው ታላላቅ ሰዎች ዘንድ የሚመጡ ሐሳቦች ናቸው። እነዚህ ሰዎች "መለወጥ አለበት" የሚሉትን ለመለወጥ ቁርጠው ሲነሡ ደግሞ ታላቅነታቸው ወደ ገናናነት ያድጋል። ትውልድም አገሪቱ የነባ ሐሳብና የምርምር ሰዎች እንደነበሯት ሲያውቅ ይኰራል። የደቂቀ አስጢፋኖስን ገድሎች የማሳትመው በኛም አገር የሚያኰራ የአእምሮ አንቅስቃሴና ለአምነት መሞት የነበረ መሆኑን ላላዩ ለማሳየት ነው አንጂ አንቅስቃሴውን ለመደገፍ ወይም ለመቃወም ወይም እንደነሱ የንጉሥ ግርማ የማይፈሩ መንፈሳዊ አባቶች አልነበሩም ለማለት አይደለም። አባ አኖርዮስና አባ ፊልጶስ አፄ ዓምደ ጽዮን የአባቱን ዕቅብት ቢያገባ ሳይፈሩ ተናግረውታል፤ የቀጣቸው ቅጣትም ቀላል አልነበረም። ገድላቸው እንደሚመስክረው÷ ደማቸው እንደውሐ አስኪፈስ ገርፏቸዋል፤ ራቁራቸውን በገበያ መካከል አስኪዷቸዋል፤ አግዟቸዋል።[1] ቅጣቱ ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ቅጣት ቢያንስ የነሱን ቈራጥነት አያላንስውም።

ከላይ እንዳመለከትኩት÷ የአባ አስጢፋኖስ ተከታዮች "ደቂቀ አስጢፋኖስ" ይባላሉ። ደቂቅ ማለት "ልጆች" ማለት ሆኖ÷ እንደ "ደቀ መዝሙር" የተከታዮች መጠሪያ ነው። አንድ መነኮሴ በአንድ ገዳም መንኮሰ ሲኖር÷ በአንዳች ምክንያት ከዚያ ይወጣና የራሱን የብሕትውና (የባሕታዊነት) ኑሮ ይጀምራል። የአባትነት ስሙ አየገነነ ሲሄድ÷ ቀስ በቀስ

---

1. K. Conti Rossini, *Vitae Sanctorum Indigenarum I Gadla Baṣalota Mikā'ēl seu Acta Sancti Baṣalota Mikā'ēl, II Gadla Anorēwos seu Acta Sancti Honorri, CSCO*, vol. 28/11 (1962); Getatchew Haile, "The Translation of the Relics of Abunä Filəppos of Däbrä Libanos," *RSE*, vol. XXXIV (1992), pp. 75-113; B. Turaiev, *Vitae Sanctorum Indigenarum III Gadla Aron seu Acta Sancti Aaronis, IV Gadla Filpos seu Acta Sancti Philippi, CSCO*, vol. 30/13 (1961).

ሌሎችም እየመጡ የሱ ተከታዮች ይሆናሉ። በዚህ መንገድ ራሱን የቻለ አዲስ ደብር ይቋቋማል። የገዳሙ መሥራች "አባት"፥ "መምህር"፥ "አበምኔት"፥ ከተሾመም "ንቡረ እድ" ይባላል፤ ተከታዮቹ ገዳሙን የጀመረው መነኮሴ ልጆች ("ደቂቅ") ይባላሉ። ተከታዮችን ልጅ የሚያደርጋቸው ሥርዓቱን ሥርዓታቸው እምነቱን እምነታቸው ማድረጋቸውና ከገዳሙ መመንከላቸው ነው። ለምሳሌ፥ የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት ገዳሙን ባቋቋሙት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም "ደቂቀ ተክለ ሃይማኖት" እንደሚባሉት ነው። የአባ አስጢፋኖስ ተከታዮችም "ደቂቀ አስጢፋኖስ" የሚባሉት ስለዚህ ነው፤ እምነታቸውን ለብዙ ዘመን እምነታቸው አድርገው ባወጡት ሥርዓት ኖረዋል። ሥርዓታቸው ሌሎች አድባራት ትተውታል የሚሉት የድኽነት፥ የስግደት፥ የጸሎት፥ የዝምተኝነት ኑሮ ሲሆን፥ እምነታቸው ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር (ለወላዲተ አምላክ) ሥዕል፥ ለመስቀል፥ ለንጉሥ አንሰግድም (አራስን የሚያስነብስ እጅ አንነሣም) ከቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ውጪ የሆኑትን አንቀበልም ነው።

ደቂቀ አስጢፋኖስ ይወቁት አይወቁት አይታወቅም እንጂ፥ ለሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም ማለት በኢትዮጵያ ታሪክ አዲስ ሐሳብ አይደለም። አነሱ ከመነሣታቸው ከመቶ እምሳ ዓመት ግድም በፊትም እዚያው እትግራይ ለሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም፤ "ምክንያቱም ሥዕል ሰሌዳ ነው፤ መስቀልም የጎልጎታ ዕንጨት ነው" የሚሉ ታላላቅ ሰዎች ተነሥተው ነበረ። ግን አፄ ያግብአ ጽዮን (1278-1286) እመቤታችን ተገልጻልኝ፥ "ለሥዕሌና ለልጄ መስቀል መስገድ ይገባል" ብላኛለችና ያልታዘዘ "አንገቱ ለገመድ፥ ያከማቸው ንብረቱ ለሠራዊቱ፥ ቤቱ ከጠመንጃዬ አፍት ለምትወጣ እሳት ይዳረጋል" ሲል ስላወጀ ያገሩ ሰዎች ሁሉም፥ "ንጉሡ ያዘዘንን ሁሉ እናደርጋለን፤ ለመስቀልና ለሥዕል እንሰግዳለን" ብለው በመታዘዛቸው እንቅስቃሴው በዚህ አክትሟል።[2]

ደቂቀ አስጢፋኖስ የተነሡት በአፄ ይሥሐቅ (1406-1421) ዘመን ሲሆን ማርቲን ሉተር ጀርመን ላይ ተመሳሳይ ሐሳብ ይዞ ከመነሣቱ ከሰላሳ ዓመት ግድም በፊት ነው። ግን በየትም አገር ቢሆን በተደላደለው ሥርዓት ላይ ተመቻችተው የተቀመጡ ጎላፊዎች የሚነካቸውን ለውጥ ስለሚጠሉ እንዲህ ያለውን የለውጥ ጥሪ ይቃወሙታል። እንዲያውም ተጣሪዎቹን ባላቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ ጎይል ሁሉ ሊያጠፏቸው ይሞክራሉ። በአባ አስጢፋኖስና በተከታዮቻቸው በደቂቀ አስጢፋኖስ ላይ የደረሰው ይህ ነው። አበባቸውን እረገፉት፤ የእንቅስቃሴያቸውን ነበልባል ውሐ ቸልሰውበት ሳይቀጣጠል ቀረ። የመንግሥቱ ጎይል የሚጋፉት አልነበረም። ሆኖም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውጉዛን ታድርጋቸው እንጂ ተልእኳቸውን ውስጥ ውስጡን በጽሙና እየተቀበለችው በመሄድ ላይ እንዳለች ሥነ ጽሑፏ ይመሰክራል። እንደሚባለው ሳይሆን ሁል ጊዜ ሰላማዊና የማይቈረቍር

2. K. Conti Rossini, *Vitae Sanctorum Indiginarum I Acta Marqorēwos*, *CSCO*, vol. 33/16 (1965), pp. 12-14.

ተሐድሶን የሚቀበሉ መሪዎች አሏት። ቤተ ክርስቲያኗ ቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክን ታከብራለች እንጂ አታመልከም። ከእምነቷ ውጪ የሆኑ ሐሳቦች ሲነሡም በጉባኤ በውይይት ታስቀራቸዋለች።

ገድሎቻቸው እንደሚያሳዩት ደቂቀ አስጢፋኖስን መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸው ጳጳሳቱ ያወገዟቸው ለመሆኑ የማያከራክር ማስረጃ የለንም። ያወገዟቸው ወይም ተወግዘዋል የሚለው ንጉሡ አፄ ዘርአ ያዕቆብ (1426-1460) ነው። ታሪካቸውን ስናነብ እንደምናየው፥ መወገዛቸውን እነሱ አያምኑም፤ እንዲያውም ራሳቸውን የሚጠሩት "ቅዱሳን" (ቅዱሶች) አያሉ ነው። አባ አስጢፋኖስ በክሓዲነት ተከስሰው ከሱ በፊት በነገሡው በአፄ ይሥሐቅ ችሎት ቀርበው የገለጡት አምነታቸው አፄ ዘርአ ያዕቆብ ችሎት ሲቀርቡ ከገለጡት እምነታቸው የተለየ አልነበረም። ሆኖም በአፄ ይሥሐቅ ችሎት የተመሰገኑ መነኮሴ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ችሎት ተወገዙ።

የአፄ ዘርአ ያዕቆብ አገዛዝ (1426-1460)

ራቅ ብለው ሲያዩት ዘመኑ ሁሉ ያው ካልሆነ፥ የአፄ ዘርአ ያዕቆብን ዘመን ታሪክ ሳነብ "ምነው በዚያን ጊዜ በተወልድኩ" እና "እንኳን በዚያን ጊዜ ያልተወለድኩ" የሚሉ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ይመጡብኛል። አፄ ዘርአ ያዕቆብ የስለት ልጅ ነበረ። እናቱ የፊተኛው ልጃ ስለሞተባት፥ "ያሁኑ ፅንሴ ተወልዶ በጤና ካደገ ለቅድስት ድንግል እመቤታችን አሰጠዋለሁ" ብላ ተስላ እንደነበረ ተጽፏል።[3] በእመቤታችን እርዳታ በሰላም በጤና ስለተወለደ ለሷ ከፍ ያለ ግዴታ የተሰማው ይመስላል። አባቱ ዳዊት የጀመረውን በፈረንሳይ፥ በእስፓኝ፥ በግብጽ፥ በፍልስጥኤም የተሠሩትን ታምሮቿን ወደ ግዕዝ መተርጐም[4] በሰፊው ቀጠለበት፤ የውጪውን አገር ማስተርጐም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ የሠራቻቸውን ተአምራት ሁሉ አየሰበሰበ በጽሑፍ አሰፈራቸው።[5] ጸሐፊዎች ሰብስቦ፥ *ተአምረ ማርያምን* እያስቀዳ በቅዳሴ ጊዜ አንደ ወንጌል በሥርዓት ቆመው እንዲያነቡት ለየገዳማቱ ላከላቸው፤ ይኸም አንድ የጭቅጭቅ ምንጭ ሆነ።

ለገዳማቱ በላከላቸው የ*ተአምረ ማርያም* መጽሐፍ መግቢያ ውስጥ "ፍጥረት ሁሉ ስለ እመቤታችን ተፈጠረ። አዳምና ሔዋንም ስለ እመቤታችን ተፈጠሩ"[6] የሚል፥ በሥርዓቱ ውስጥ "ቍርባን መቍረብ

3. Enrico Cerulli, "Le Etiopia del secolo XV in nuovi documenti storici," *Africa Italiana*, vol. V (1933), pp. 82-83.
4. Enrico Cerulli, *Il libro etiopico dei miracoli di Maria e le seu fonti nelle letterature del Medio Evo latino*, Rome 1943.
5. Getatchew Haile, *The Mariology of Emperor Zär'a Ya'əqob of Ethiopia*, Rome 1992, pp. 3-12.
6. *ተአምረ ማርያም። በግዕዝ ሥና በአማርኛ።* አዲስ አበባ ፲፱፻፷፭ ዓመተ ምሕረት፥ ገጽ 9.

ያልቻለ ተአምሯን ሰምቶ ወደ ቤቱ ይሂድ፤ አንደ ቊርባን ይቈጠርለታል"[7] የሚል፥ በተአምሮቿ ውስጥ ደግሞ ስንት ሰው በልቶ የፈጀ በላዔ ሰብእ (ሰው በላ) በቅድስት ማርያም ስም ለአንድ ሰተጠማ ሰው ውሐ ስለሰጠ ብቻ መንግሥተ ሰማያት ገባ የሚል ስላለበት አበምኔቶቹ ስለ ንጉሡ ትእዛዝ ምን እንደሚያደርጉ ተቸገሩ፤ አንዳንዶቹ ደፍረው ተቃውሞ ጀመሩ፤[8]

ወሰምዐ አሐዱ መነኮስ ንቡረ እድ ከመ ፈነወ ንጉሥ መጽሐፈ ተአምሪሃ ውስተ አብያተ ክርስቲያናት ወይቤ አንሰ ኢያበውእ ውስተ ደብርየ መጽሐፈ ተአምሪሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በፀኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ ምንተኒ ለእመ ረሰዩኒ። ወይቤሎ አሐዱ ብእሲ ዘሰምዖ አንዘ ይብል ከመዝ ለምንትኑ አእባ ዘኢታብውእ ውስተ ደብርከ ተአምሪሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በፀኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ። ወይቤ አንሰ አሜሀሮሙ ለደቂቅየ ጽኑዐ ትምህርተ (ትሕርምተ?) በከመ ገድለ መነኮሳት። ቦ አለ ሀለው ውስተ ጻማዕት ወቦ አለ ሀለዉ በትሕርምት። መሰለ ይሰምዑ መጽሐፈ ተአምሪሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በፀኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ ዘከመ አድኅነቶሙ ለብዙኃን ኃጥአን እለገብሩ ኃጣውኢ ዓበይተ የኃድጉ አመንቱኒ ጻማሆሙ ወገድሉሙ ወይገብኡ ውስተ ንዝሕላል።

❖

አንድ ንቡረ እድ መነኮሴ ንጉሡ የተአምሯን መጽሐፍ ወደየቤተ ክርስቲያኖቹ እንደላክ ሲሰማ፥ "እኔ ምንም ቢያደርጉኝ የእመቤታችንን በፀ መንገድ ድንግል ቅድስት ማርያም ወላዲተ አምላክን የተአምሯን መጽሐፍ ከደብሬ አላስገባም" አለ። እንደዚህ ሲል የሰማው አንድ ሰው፥ "የእመቤታችንን በፀ መንገድ ድንግል ቅድስት ማርያም ወላዲተ አምላክን ተአምር ከገዳምህ የማታስገባው ለምንድን ነው?" አለው። "ልጆቼን በመነኮሳት ገድል ውስጥ እንዳለው ጽኑ ትምህርትን/ ጭምተኝነትን አስተምራለሁ፤ እነሱም አንዳንዶቹ በዋሻ ኑሮ ይኖራሉ፤ አንዳንዶቹ በጭምተኝነት ላይ ናቸው። ታላላቅ ኃጢአቶችን የሠሩ ብዙዎች ኃጢአተኞችን እንዳዳኑቻቸው የእመቤታችንን በፀ መንገድ ድንግል ቅድስት ማርያም ወላዲተ አምላክን ተአምር ሲሰሙ እነሱም ጻማቸውንና ገድላቸውን ትተው ንዝሕላሎች ይሆናሉ" አለው።

አፄ ዘርአ ያዕቆብ የተአምረ ማርያምን ቅጂ ለደቂቀ አስጢፋኖስ ገዳምም ልኮ እንደነበረና ከቤተ ክርስቲያናቸው ሥርዓት እንዳላስገቡት ምንጫቸው ይመስክራል፤[9]

---

7. አዚያው፥ ገጽ 19።
8. Cerulli, *Il libro etiopico dei miracoli di Maria*, pp. 18-19.
9. *ገድለ አበው ወአኃው*፥ EMML 4, f. 36b-37a, W. F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian*

(36^ሀ) ንጉሡ "መጽሐፈ ተአምረ ማርያምን አጅ አይነሡም" በሚል ከስ ወዳመጧቸው ወደ ፪ቱ፡ "የሚሏችሁ እውነት ነውን?" (ብሎ) ላከባቸው:: ፩ዱ ወንድም፡ "እኛ አጅ አንነሣም አላልንም፤ ብቻ አንድ ተሳላኪ ከወንጌል ንባብ በኋላ (እንዲነበብ) አንድ መጽሐፍ አመጣልኝ፤ "ይኼ መጽሐፍ ምንድን ነው?" አልኩት:: "መጽሐፈ ተአምረ ማርያም ነው" አለኝ:: "የሐዋርያት ሥርዓት አኮ እንደዚህ አይደለም:: ከአሪት፡ ከነቢያት፡ ከሐዋርያት ዜና መጻሕፍት ሁሉ (ተነብቦ)፡ ከዚያ ቀጥሎ፡ ወንጌል ይነበባል፤ ከጸሎት ፍጻሜ በኋላ ወንጌልና መስቀል አጅ ይነሣል" አልኩት:: የቃሌን መጨረሻ ሰምቶ መጽሐፉን ይዞ ሄደ:: ከዚያ በኋላ ያንን መጽሐፍ (37 ^ህ) እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት፡ ሰጠኝ፤ አንብቤ አጅ ነሣሁት" አለ:: ንጉሡ፡ "ይኸን የምትለው ንቀህ አይደለምን?" አለው:: ያ ወንድም፡ "የምንቅ እንደሆነ አውን ፈትኑኝ" አለው:: ንጉሡ፡ "አጐንብሶ፡ ማንስ ተጐንብሶ?" አለ:: ከዚያ፡ ንጉሡ እንዲደበድቡት አዘዘ:: በዱላ ደበደቡት::

ዘመኑን የሚያንጓ የሚያደርገው ዘርአ ያዕቆብ በአንድ ገዳም ውስጥ ራሱን ሳይገልጽ በትምህርት እየታነጸ ያደገ ታላቅ ሊቅ[10] ከመሆኑም በላይ ድርጊቶች በጽሑፍ እንዲመዘገቡ ማድረጉ ነው:: ከሱ በፊት የነበሩ ሊቃውንት ያተኮሩት የውጪ መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ በመተርጐም ዕውቀትን ከውጪ አገር ከማምጣቱ ላይ ነበረ:: ዘርአ ያዕቆብ ያንንም እያደረገ በተጨማሪ በካህናተ ደብተራነት[11] ከቤተ መንግሥት ከሚያገለግሉ ሊቃውንት ጋራ ብዙ ድርሰቶች ደርሷል::[12] ብሔራዊ ሥነ ጽሑፍ ከሱ አስቀድሞ በነበሩት በነቅዱስ ያሬድ፡ በነርቱዓ ሃይማኖትና በነአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ቢጀመርም መዳበር የጀመረው በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመንና ጥረት ነው:: ስለ አርቶዶክስ ሃይማኖት ያለው እምነት ለጥቂቶቹ ሊቃውንት እልጥም ስላላቸው

Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa, and for the Monastic Manuscript Library, Collegeville, vol. I: Project Numbers 1-300, Collegeville, (Minnesota) 1975, p. 7. እዘህም ገጽ 128::

10. Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia 1270 - 1527*, Oxford 1972, p. 220-221.

11. "ካህናተ ደብተራ" (የድንኳን ካህናት) የሚባሉት ዱሮ ከቤተ መንግሥት ግቢ "በድንኳን" ባለው ታቦት አያገለግሉ ነገሥቱን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት የሚያማክሯቸው ሊቃውንት ናቸው:: "ደብተራ" ማለት "ድንኳን" ሚለት ነው:: ግን ንጉሡ ሲጓዝ ካልሆነ በቀር ታቦቱ ሁል ጊዜ በደብተራ ውስጥ የሚቀመጥ አይመስለኝም:: "ደብተራ" የሚባለው ድንኳን ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጋራ የተያያዘ ነው:: ንጉሥ ሰሎሞን መቅደስ እስኪሠራላት ድረስ ታቦተ ጽዮን የምትቀመጠው በደብተራ (በድንኳን) ነበረ:: ካህናቱም "ካህናተ ደብተራ" (ካህናተ ድንኳን) እንዳንዴም "ደብተራ" ይባላሉ::

12. የሚታወቁት መጻሕፍት ጌታቸው ኃይሌ፡ *ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቁጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ*፡ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፲፱፻፺ ዓ. ም. ገጽ 236 ላይ ተዘርዝረዋል::

(አንዳንዶቹም ዘንድ ኑፋቄ ስለነበረባቸው) ይቃወሙት ነበረ። እነሱን በየገዳማቸው እየዞረ መገሠጽ ስለማይችል ጉባኤ እየጠራ በራሱ ዳኝነት እየተከራከረ ይረታቸው ነበረ። የጉባኤውን ታሪክና ውሳኔ በጽሑፍ ስላስቀረልን አፄ ዘርአ ያዕቆብ ታሪክ ሠርቷል።[13] ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸሙት ንጉሡ የሰበሰባቸው ተአምራትም የሥነ ጽሑፍና የታሪክ ምንጭነት አላቸው። ይህንን መግቢያ ለማዘጋጀት ካስቻሉኝ ምንጮች ውስጥ አንዱ *ተአምረ ማርያም* ነው።

ዘመኑን የማያንጓ የሚያደርገው ንጉሡ ከእሚያምነው በተለየ እምነታቸው በጸኑት ሊቃውንትና የሃይማኖት ሰዎች ላይ ያደርስባቸው የነበረው ጽኑ ቅጣት ነው። ምን ማለቴ እንደሆነ እዚህ የማቀርባቸው የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ገድሎች ይገልጹልናል።

አፄ ዘርአ ያዕቆብ አባ እስጢፋኖስን "እስጢፋ"፥ ተከታዮቻቸውን "ደቂቀ እስጢፋ" ("የእስጢፋ ልጆች") ነበር የሚላቸው። አባ እስጢፋኖስን ለምን "እስጢፋ" እንደሚላቸው አልነገረንም፤ ግን ንጉሡ የሸሙጥ ስም ማውጣት ይችልበት ነበረ። ደቂቀ እስጢፋኖስ ሽሙጡ እንደገባቸው ከሆነ፥ "እስጢፋ በግብጽ ቋንቋ የሰይጣን ስም ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቤት አስተዳዳሪ ሰይጣን፥ እኛን ልጆቹን የሰይጣን ልጆች ለማለት ነው" ይላሉ።[14] እነሱም አጻፋውን ሲሰጡት "ድብ ፀር" ("ጅብ ጠላት"--አያ ጂቦ)፥ "ዝራጐን" (ድራጎን) ይሉት ነበር።

የሃይማኖት ውዝግብ

የዘመኑ ዋና ዋና አከራካሪ ጥያቄዎች ስለ ምሥጢረ ሥላሴ፥ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ፥ ስለ ሰንበት አከባበር፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሕግ መጻሕፍት ቍጥር፥ ቅድስት ድንግል ማርያምን፥ የቅዱሳን/ት ሥዕልን፥ መስቀልን ስለማክበር፥ ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣትና ከጻድቃኑ ጋራ አንድ ሺህ ዓመት ስለ መንገሥ (ማለት ስለ "ደብረ ጽዮን" ወይም "ስለ ስምንተኛው ሺህ") ነበረ።

---

13. Getatchew Haile, "Religious Controversies and the Growth of Ethiopic Literature in the Fourteenth and Fifteenth Centuries," *OrChr*, vol. 65 (1981), pp. 102-136. ለምሳሌ፥ ዘሚካኤልና ገማልያል የሚባሉ ሁለት ሊቃውንት "አልቦቱ መልክዐ ለእግዚአብሔር ከመ መልክዐ ሰብእ" ("እግዚአብሔር የሰውን መልክ የሚመስል መልክ የለውም") በማለታቸው ንጉሡ ተቆጥቶ ሊከራከራቸውና ሊረታቸው የሊቃውንት ጉባኤ ሰብስቦ ነበረ። የዘመኑ ታላላቅ ሰዎች እነማን እንደነበሩ በከፊልም ቢሆን ለማወቅ የቻልነው ንጉሡ በጉባኤው ላይ የነበሩትን ሰዎች የሰም ዝርዝር ስለመዘገበልን ነው፤ Getatchew Haile, "The Homily of Zär'a Ya'əqob in honour of St. John the Evangelist," *OrChr*, vol. 67 (1983), pp. 150-151.

14. *ገድለ አበው መጻኑው*፤ EMML 4, ff. 84a and 142a. እዚህም ገጽ 167 እና 208።

እሁን ገድሎቻቸውን ወደ አማርኛ ተርጉሜ እዚህ ያቀረብኩት እባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ከእዬ ዘርአ ያዕቆብ ጋራ የሚያጣላቸው ጉዳይ ንጉሡ እንደሚለው ከሆነ፥ ለመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያምና ለክቡር መስቀል ስለማይሰግዱ ነው::[15] እነሱ የሚሉት ደግሞ ይሄ ሰበብ ነው፤ የሚያሳድዳቸው ለሱ ስላልሰገዱለት ነው::

እባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ስግደትን ከእምልኮት ጋራ ስላያያዙት ከሰው ጋራ ሰላምታ ሲሰጣጡ እንኳን አንገታቸውን ሰብር አያደርጉም:: ሰነዶቻቸው እንደሚመሰክሩት፥ ስግደት ለእግዚአብሔር (ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ) ካልሆነ በቀር ለሌላ አይገባም ይላሉ:: ንጉሡን ከችሎቱ ለጉባኤ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉም ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ (ምናልባትም ከመሬት ላይ በመውደቅ) ሰላምታ ሲሰጡት እነእባ እስጢፋኖስ ከፊቱ እንደ ጂብራ ተገትረው ይቀራሉ:: "ለምን እታሳነብሱም" ሲላቸው፥ "ለሰው መስገድ አይገባም፤ ለሰው መስገድ እምልኮ ባዕድ (እምላክ ያልሆነን ማምለክ) ነው:: ይገባል ካልክ ሕግ ይዳኘን" ብለው ምንም ነገር ሳይፈሩ በሕግ ቀጥ አድርገው ይከራከሩታል:: ጻድቆች ሳይቀሩ ለታላቅና ለባለሥልጣን ሰላምታ ሲሰጡ እንደሚያሳንብሱ (እንደሚሰግዱ) መጽሐፍ ሲጠቅስባቸው፥ "ለማስረጃነት ከነሱ ድክመት ይልቅ የማያልፈው የእግዚአብሔር ቃል ይበልጣል፤ ከኔ በቀር ለሌላ ለማንም እትሰገዱ ብሏል" ይሉታል፤ በእምነታቸው ሲጸኑበት አይቀጡ ቅጣት ይቀጣቸዋል::

ሕግ የሚሉት በብሉይና በሐዲስ ውስጥ ያሉትን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና *በመጽሐፈ ሲኖዶስና በመጽሐፈ ዲድስቅልያ* ውስጥ የተደነገገውን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ነው::[16] ይኸም ሆኖ የነሱ ምንጮች ናቸው እንጂ፥ ዘርአ ያዕቆብ በተወልን ሰነዶች ውስጥ "ስላልሰገዱልኝ ተጣላኋቸው" ሲል አላገኘሁም፤ እንዲህ ብሎ ይጽፋል ተብሎም አይገመትም፥ አይጠበቅምም::

ለንጉሡ ላለመስገድ የሰጡት ምክንያት በቂ ቢመስልም፥ ጦሩ እየተሰበቀ፥ ሰይፉ እያውለበለበ ፊት ለፊት ሲመጣባቸው፥ "ለንጉሥ አንገትን ሰብር አድርጎ እጅ መንሣት አምልኮ አይደለም" ብለው ማምለጥ ሲችሉ እስከመጨረሻው እንዲጨክኑ ትልቅ ተጽዕኖ ያደረገባቸው አንድ ከመጽሐፈ መነኮሳት ያገኙት ታሪክ ይመስለኛል:: ታሪኩ እንዲህ ይላል፤[17]

> ደግሞ ያ ወንድም እባ ቆረኒሰ ከአስቄጥስ የወጣው ጊዜ ያለኝን ነገረኝ፤ የግብጽን ምድረ በዳ አልፌ አዚያ ትንሽ ሰሌን ሰጐነጉን ብዙ አርኩስ መንፈሶች በጣም በሚያስፈራ ግርማ ሆነው ወታደሮች መሰለው ``

15. *ተአምረ ማርያም*፥ ገጽ 112-121::
16. በእጅ የተቀዳ *መጽሐፈ ሲኖዶስ* በታላላቅ ቤተ ክርስቲያኖችና በውጪ አገርም በአንዳንድ የምርምር ቤተ መጻሕፍት ይገኛል፤ ግን ሰላልታተመ ሁሉም በቀላሉ አግኝቶ የሚጠቅሰውን አንድ ምንጭ መጥቀስ አልተቻለም::
17. Victor Arras, *Collectio Monastico, CSCO*, vol. 238/45 (1963), p. 123.

መጡ። ከነዚያ መንፈሶች ውስጥ ጥቂቶቹ ወደኔ ወደ ውስጥ ገቡና፡ "ተነሥ ውጣ፤ ንጉሡ ጠርቶሃል" አሉኝ። "አልወጣም" አልኳቸው። የምጐነጉነውን ከአጀ ነጠቁኝና "ና ተነሥ፤ ንጉሡ ጠርቶሃል ስንልህ ቁጭ ብለህ ትጐነጉናለህ!" ብለው ደበደቡኝ። በግድ እየጎተቱ ወደ ውጪ አወጡኝ። ለመለከት ፩ ከዙፋን ላይ የተቀመጠ አየሁ። "ንጉሥ ነው፤ ስገድለት" አሉኝ። "አልሰግድም" አልኳቸው። እንደገና ደበደቡኝና የሞተ ያህል ከመሬት ላይ ጣሉኝ።

ከመሬት ላይ ስወድቅ ትተውኝ ሄዱ። አንድ (መንፈስ?) ወደኔ መጥቶ ቀስቀስኝና "ያንተው ነኝ፤ ከዚህ ተነሣ" አለኝ። ሲያነሣኝ ጎይል አግኝቼ ተነሣሁ። ማርፋትም ሆነ ወይም በሥጋዬ ላይ አንዳች ቍስል ምንም ነገር አላየሁም። "አስካሁን የት ነበርክ?" ብለው፤ "እዚሁ ነበርኩ፤ ዝም ያልኩህ ትታገሥ ወይም ያቅትህ አንደሆነ ለማየት ነው" አለኝ።

አስጢፋኖሳውያንም ለሥዕልና ለመስቀል (ከመጀመሪያው ላይ ለቅድስት ድንግል ማርያምም) አንስግድም ማለታቸውን አይክዱም። ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር "ለሌላ" አለመስገዳቸው ከተረጋገጠ፡ "ሌላ" ንጉሥን እንደሚጨምር ሁሉ መስቀልን፡ ሥዕልን፡ ከዚያም አልፎ መላእክትን፡ ቅዱሳንን፡ (ቅድስት ማርያምን) መጨመር አለበት፤ አለዚያ "ሌላ" የሚለው ቃል ትርጉሙ ይቃወሳል። እንዲያውም ከጳጳሱ ከአባ ገብርኤል ዘንድ ባቀረቧቸው ጊዜ፡ ጳጳሱ *"ለምን ኢትሰግዱ ለማርያም"* ("ለማርያም ለምን አትስግዱም?") ብለው ቢጠይቋቸው፡ *"አኮ ዘረከብነ ቅድመዝ እንዘ ይብል እሰግድ ለማርያም ዘእንበለ ዘይትበሀል እሰግድ ለአብ ወወልደ ወመንፈስ ቅዱስ"* ("ከዚህ በፊት ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ ቅዱስ እስግዳለሁ የሚባል እንጂ ለማርያም እስግዳለሁ የሚል አላገኘንም") የሚል መልስ እንደሰጧቸው ራሳቸው ነግረውናል።[18]

አለመስገድን እንደ አለማክበር አያዩትም፤ እመቤታችንን ማክበራቸው አያጠራጥርም፤ "ምስለ ፍቁር ወልዳ" የሚባለውን ቅድስት ማርያም ልጇን (ጌታችንን) ታቅፋ የሚያሳየውን ሥዕል በየመጽሐፎቻቸው ውስጥ ሥለው ተገኝቷል፤ በራሳቸው በአባ አስጢፋኖስ ገድል ውስጥም አለ (ገጽ 22ን ተመልከት)። በዚያ ላይ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የቅዱስ ኤፍሬምን *ውዳሴ ማርያም* እና የቅዱስ ያሬድን *አንቀጸ ብርሃን* ይደግሙ ነበረ። እነዚህ ሁለት ድርሰቶች እመቤታችንን የሚያደንቁና የሚያመሰግኑ፡ በየአንቀጹ *"ለአሊ ለነ ቅድስት"* (ቅድስት ሆይ፡ ጎጢአታችንን ይቅር እንዲለን ክልጇሽ ከወዳጂሽ ዘንድ አማልጂን) የሚል ንባብ ያለባቸው ናቸው። ጳጳሱም ለቅድስት ድንግል ማርያም ብትስግዱ ስሕተት አይሆንባችሁም ብለዋቸው አብረው መስገዳቸውን ራሳቸው መስክረዋል።

ንጉሡ ያገኘባቸው ወንጀል (ጎጢአት) ለቅድስት ማርያም አለመስገዳቸው ሳይሆን፡ *"ወቅድመ ሥዕላ ሰግዱ"* (በሥዕሏ ፊትም ስገዱ)[19]

---

18. *ገድለ አበው ወአኃው*፤ EMML 4, f. 62b. አዚህም ገጽ 149።

19. *ተአምረ ማርያም*፤ ገጽ 11።

ብሎ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ያወጀውን ዓዋጅ አለመቀበላቸው መሆኑ ግልጽ ነው። አንድ ጊዜ "ምስለ ፍቁር ወልዳ" የሚባለውን ሥዕል ቢያሳዩዋቸው ሥዕሉን እድንቀው፥ "ለሰው ሥራ አትስገድ" የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ለማስታወስ፥ "የሰው ሥራ ነው" አሉ። ግን ለቅድስት ማርያም ሥዕልና ለክቡር መስቀል አንሰግድም ማለታቸውንም ቢሆን የአስጢፋኖሳዊው አባ ዕዝራ ገድል እንደሚመሰክረው የኋለኞቹ ልጆች ትተውታል።[20]

አፄ ዘርአ ያዕቆብ ደቂቀ አስጢፋኖስን ስለ ምስጢረ ሥላሴ የሚከሳቸው፥ አብ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስን ለየራሳቸው በራሳቸው ቃል ይናገራሉ ስለሚሏቸው ሶስት አማልክት እደረጋችኋቸው ብሎ ነው። ወልድ ቃል ስለሆነ ቃልነቱ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስም ነው ሲሳቸው አብ እና መንፈስ ቅዱስ በራሳቸው ቃል እንደተናገሩ መጽሐፍ ይጠቅሱበታል።

"ደብረ ጽዮን የለም" ብለው የሚከራከሩ ግን ደቂቀ አስጢፋኖስ ሳይሆኑ ዘሚካኤልና ገማልያል የሚባሉ ሌሎች ሊቃውንት ናቸው። "ደብረ ጽዮን" ክርስቶስ ከጻድቃኑ ጋራ የሚገዛበት የአንድ ሺህ ዓመት ዘመን ነው፥ "ምሳሕ በደብረ ጽዮን" ("በደብረ ጽዮን ምሳ") አንዳንዴም "ምሳሐ ከብካብ" ("የሠርግ ምሳ")፥ "መብልዕ ዘ፲፻" ("የአንድ ሺህ (ዓመት) መብል")፥ "ማእድ ዘ፲፻" ("የአንድ ሺህ (ዓመት የምግብ) ገበታ") ይሉታል፤ መጽሐፈ ድጓው "መንግሥተ ደብረ ጽዮን" ይለዋል። *መሠረቱ ራእየ ዮሐንስ፥ ተእምረ ኢየሱስ፥ ትምህርተ ሃቡላት* ሲሆኑ ሌሎች የጸሎት ድርሰቶች፥ በተለየም አንዳንድ አኩቴተ ቍርባኖች፥ ይጠቅሱታል፤ አምነቱ ስለ ስምንተኛው ሺህ ከሚታመንበት ጋራ የተያያዘ ነው። ንጉሡ ደቂቀ አስጢፋኖስን ጎትቶ አዚህ ክርክር ውስጥ አስገባቸው እንጂ ይኸ የነሱ ጉዳይ አልነበረም። እነሱ ሲጠየቁ የሚሉት ወደ ፊት እንደምናየው፥ የክርስቶስ መንግሥት የክርስትና ዘመን ስለሆነ የክርስቶስን ሕግ ለሚጠብቅ ሁሉ ዘመን ሳይለያት ሁል ጊዜም እለች ነው። ንጉሡ ግን ወደ ፊት እንደሚሆን በስፊው እየጻፈ ያስተምራል።[21] "በእንተ እለ ያስትቱ ደብረ ጽዮን" ("ደብረ ጽዮንን ስለሚያቃልሉ") በሚል

---

20. André Caquot, "Les Actes d'Ezrā de Gunda-Gundē," *AÉ*, vol. 4 (1961), pp. 80-81. አዚህም ገጽ 285-6።

21. ጌታቸው ኃይሌ፥ *ባሕረ ሐሳብ፥ የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ*፥ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ)፥ 1993 ዓ. ም.፥ ገጽ 21-24፤ *መጽሐፈ ቅዳሴ* በግዕዝና በአማርኛ፥ አዲስ አበባ 1951 ዓመተ ምሕረት፥ ለምሳሌ፥ ገጽ 9 (ሥርዓተ ቅዳሴ)፥ 123 (ቅዳሴ ማርያም)፥ 134 (ስለስቱ ምእት)፥ 177 (ባስልዮስ)፥ 206-207 (ዮሐንስ አፈ ወርቅ)፥ 227 (ቄርሎስ)፥ 286 (መስተብቍዕ በእንተ ሙታን)፤ Ernst Hammerschmidt, *Äthiopische Liturgische Texte der Bodleian library in Oxford*, Berlin (1960), p. 70; Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity of Emperor Zär'a Ya'əqob (Ṭomarä Tæsbə't)*, *CSCO*, vol. 522/95, p. 4, 39, and 83; Getatchew Haile, "A New Look at Some Dates on Early Ethiopian History," *Le Muséon*,

ርእስ አንድ ተአምረ ማርያምም (አስ)ጽፏል።[22] አሁን ስምንተኛው ሺህ ከገባ ከ485 ዓመት በላይ ስላለፈው ስለ ደብረ ጽዮን የተጻፈውን ከዘመን ጋራ አያይዘው አያስተምሩትም።

ብሔረ ብፁዓን

የእስጢፋኖሳውያን ሥቃይ መንሥኤው የኢትዮጵያ መነኮሳትን ሕይወት መንቀፋቸው ነው። ምንኮስናቸው ለስም እንጂ ሕይወታቸው ካልመነኮሰ ሰው ሕይወት አይለይም፤ ይኸ መለወጥ አለበት ባዮች ነበሩ። ምንኮስና የተጀመረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም" (ዮሐ 18፡ 36) ባለው መሠረት በምድር ላይ ያቋቋመውን ለማያዊ መንግሥት (መንግሥተ ሰማያት) ለማጠናከር ነበረ።

ክርስትና በተጀመረበት ዘመን ክርስቲያኖቹ በየቦታው አናሳ ማኅበሮች (minorities) ስለነበሩ የሚኖሩት እዚህ አሜሪካን አገር እንደምናያቸው እንደ አሚሾች ንብረታቸውን አንድ አድርገው በእንድነት ነበር (የሐ ሥራ 4፡ 32-5፡ 11)። ሐሳቡ ወደ ዘለዓለሙ ኑሮ እስኪሄዱ ድረስ የሚኖሩባትን ምድር ብሔረ ብፁዓን አድርጎ የብፁዓን ኑሮ ለመኖር ነበረ።

የክርስቲያኖች ቍጥር እያደገ ሲሄድ ያንድነቱ ኑሮም እየቀረ ሄደ። ሆኖም ምንኮስና ተካው እንጂ ጨርሶ አልቀረም። እንዲያውም "ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ፤ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፤ መጥተህ ተከተለኝ" (ማቴ 19:21) ያለውን የጌታን ቃል በማስታወስ የምንኮስና ክርስትና (የከፍተኛ ደረጃ ክርስትና) በመካከለኛው ምሥራቅ፥ በተለያም በግብጽና በሶርያ፥ ተስፋፋ። የዚህ ከፍተኛ ክርስትና፥ ማለት፥ የምንኩስና መሪዎች አባ እንጦንስ፥ አባ መቃርስ፥ አባ ጳኮሚስ የሚባሉ ግብጻውያን ናቸው። ሐሳባቸው ከዓለም በሕይወት ተለይቶ ለእግዚአብሔር በጸሎትና በአምልኮ ለመጠመድ ሆኖ ሳለ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካለው ስእለትና ቅድስና ጋራ ተያያዘ። ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚጠቅሱት ሥርዓት ይኸንን ዘኍ 6፡ 1-8 ላይ የተደነገገውን ነው፤

> ወንድም ሆነ ሴት እንድ ለው ራሱን ለእግዚአብሔር ሲሳል፥ ከወይን ጠጅና ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን የተለየ ያድርግ፤ ከወይን ወይም ከሴላ ነገር የሚገኘውን ሆምጣጤ (አልኮሆል) አይጠጣ፤ የወይን ጭማቂ አይጠጣ፤ የወይን እሸት ወይም ዘቢብ አይብላ። ራሱን የተለየ ባደረገበት ዘመን ሁሉ ከወይን የተገኘውን ነገር ሁሉ ከውስጥ ፍሬ ጀምሮ እስከ ገፈፎው ድረስ አይብላ። ራሱን ለመለየት ስእለት ባደረገበት ዘመን ሁሉ በራሱ ላይ ምላጭ አይደርስም። ለእግዚአብሔር የተለየበት ዘመን እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰ

---

vol. 95 (1982), pp. 311-322; Kurt Wendt, *Das (Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis) des Kaizers Zar'a Yā'qob*, *CSCO*, vol. 235/43, Louvain 1963, pp.34-44.

22. *ተአምረ ማርያም*፥ ገጽ 132-136።

ይሆናል፤ የራሱንም ጠቅር ያላድጋል። ለእግዚአብሔር ራሱን የተለየ ባደረገበት ዘመን ሁሉ ወደ ሬሳ አይቅረብ፤ ለአምላኩ ያደረገው ሰአለት በራሱ ላይ ነውና አባቱ ወይም እናቱ ወይም ወንድሙ ወይም እኅቱ ሲሞቱ ሰውነቱን አያርክሰባቸው፤ ራሱን የተለየ ባደረገበት ዘመን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው።

መነኮሳቱ ራሳቸውን ብዙ ነገር ከመንፈግ እልፈው በዱር (በገዳም)፥ በዋሻ (በበአት፥ በጸማዕት)፥ አንዳንዴም እንደ ስምዖን ዘዓምድ በዓምድ ላይ ቁጢጥ ብለው ይኖሩ ነበር። ራስን ድሎት የመንፈጉ ደረጃ ወሰን የለውም፤ በራሳቸው ላይ መማቀቅን ይጋብዛሉ። የሚያነቡት *መጽሐፈ ዜና አበው* የሚጀምረው እንዲህ በሚለው በአባ እንጦንስ ምክር ነው፤ *"እስመ ለእመ ርኁብነ ወጸማዕነ መዐረቅነ ወሐዘነ ወጸዐርነ ዘእምልብነ ንስውን ድልዋነ ለእግዚአብሔር። ናብድራ ለሐዘን ከመ ንርከበ ለእግዚአብሔር፤ ንመንና ለሥጋነ ከመ ትድኅን ነፍስነ"* ("ከልብ ስንራብ፥ ስንጠማ፥ ስንራቆት፥ ስናዝን፥ በጣር ላይ ስንሆን ለእግዚአብሔር የተገባን እንሆናለን። እግዚአብሔርን እንድናገኘው ሐዘንን እናስቀድማት፤ ነፍሳችን እንድትድን ሥጋችንን እንጣላት")። ከመነኮሳት እንዱ ስለ ጽድቅ የውሐ ጥም ሲያቃጥለው በጽዋ ቀዝቃዛ ውሐ ይሞላና ከፊቱ ያስቀምጣል፤ እምሮቱ የባሰውን ያቃጥለዋል። "ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?" ቢሉት፥ "ዋጋዬ በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲበዛልኝ በጸማዬ ላይ ጸማ (በሥቃዬ ላይ ሥቃይ) መጨመሬ ነው" አለ ይባላል።

ፍትሐ ነገሥቱ መነኮሳትን *"መላእክተ ምድራውያን ወሰብእ ሰማያውያን"* ("የምድር መላእክት የሰማይ ሰዎች") ይላቸዋል። ሰዎች የሚመነኮሱት እንደ መላእክት በንጽሕና ለመኖር ስለሆነ ከሰይጣን ጋራ የሚያደርጉት ትግል ልባቸውንና ሕሊናቸውን ከሐሜት፥ ከቅንአት፥ ከቁጣ ለማጽዳት፥ ሥጋቸውን ከዝሙት ለመጠበቅ ነው። በምንኮስና ከገዳም የገባ ሰው ያለ አበምኔቱ ፈቃድ ከገዳም ምን ጊዜም አይወጣም፤ ጳጳስ ሲያደርጉት ከሀገረ ጵጵስናው የሚያለያየው እክል ሲያጋጥመው መሸሻው ወይም ማኮረፊያው ገዳሙ ነው። ከገዳሙ የራቀን መነኮሴ የሚያመላስሉት ከውሐ በራቀ ዓሣ ነው።

አባ እስጢፋኖስ በሳቸው ዘመን የነበሩ መነኮሳት ኑሮ ከዚህ የምንኮስና መሥራች አባቶች ከደነገጉት ሥርዓት የተለየ ሆኖ ስላገኙት አስቆጥቷቸው፥ የኢትዮጵያ አድባራት ኑሮ የምንኮስና አባቶች ካወጡት ሕግና ሥርዓት ርቆ ሄዷል ብለው "አብዮት" ጀመሩ። "በሕጉ በሥርዓቱ እንሂድ፤ ሕጉንና ሥርዓቱን በያዙት መጻሕፍት እንዳኝ (በሕግ አምላክ)" የሚል ክርክር ይዘው የትግራይን አድባራት እናወጧቸው፥ አራወጧቸው።

በተለይ ታላላቆቹ አድባራት፥ ነገሥቱ፥ መኳንንቱ፥ ወይዛዝርቱ በየጊዜው የሚሰጧቸው ርስት እንደ ምንኮስናው ሥርዓት በድኽነት ለመኖር ከገቡት ቃል ኪዳን አውጥቷቸው እንደነበረ ይገመታል። አንዳንድ ገዳማት ርስታቸውን ቢያርሱም ብዙዎቹ በበዓልና በተዝካር ቀን ምግብና መጠጥ ለሚገብር አራሽ ያጋዙት ነበረ። አንዳንድ ሰዎችማ እንደሚጠበቅባቸው ገዳም ሳይሄዱና ሳይደኸዩ ሙሉ ሀብታቸውን (ባሮቻቸውን ጭምር) ይዘው

በየቤታቸው "በምንኵስና"ይኖሩ ነበር። በዚያ ላይ በዕውቀትና በመንፈሳዊነት የታወቁ መነኮሳትም ከገዳማቸው እየወጡ የነገሥቱ ባለሟሎች እየሆኑ ከነገሥቱ ችሎት ለፍርድ ይቀመጡ ነበረ።

ደቂቀ እስጢፋኖስ በነዚህ ላይ የሚወረውሩት "ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም" (ሉቃ 9: 62) የሚለው ጦር እና የሚሰነዝሩት "ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል፣ ደግሞ የታጠበች እሳማ ከጭቃ ላይ ለመንከባለል ትመለሳለች" (2 ጴጥ 2: 22) የሚለው ሰይፍ መነኮሳቱን አቆሰላቸው፣ በአድማ አስነሣባቸው።

በምንኵስና ሥርዓት ለመኖር የሚፈልጉ ብዙ መነኮሳት የገዳሙ ኑሮ ላይጥማቸው ሲቀር ሕጉን ተከትለው ለማሻሻል በመሞከር ከሰው ጋራ ከመጣላት እያሉ በማኅደራቸው ስብስብ ብለው (ወይም ከማኅበሩ ወጥተው) በብሕትውና ኖረዋል፤ እንደዚህ የሚያደርጉ አሁንም ይኖራሉ፤ "ግሑሳን" (ዞር ብለው የሚኖሩ) "ስውራን" (ተሰውረው የሚኖሩ) ይባላሉ። አባ እስጢፋኖስና "ደቂቀ እስጢፋኖስ" የሚባሉት ልጆቻቸውም እንደዚያ በማድረግ ከሌሎች ጋራ ሳይጋጩ በራሳቸው ለመኖር በ1481 ዓ. ም. ሞክረዋል።

ንጉሡም በራሳቸው ተወስነው ቢኖሩ ምናልባት አይቃወማቸውም ነበር። ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት፥ በተለይም እንደኛ፥ በተቃዋሚዎቻቸው እፍ ዝናቸው ስለተሰማ፥ ሁለተኛ፥ የተሰማቸውን የማስተማር ግዴታ ሲፈጽሙ፥ ሶስተኛ፥ ሲያሳድጿቸውም በተሰደዱበት ግብራቸውን ስዒ ስለወደደላቸው፥ ብዙዎች የሌሎች ገዳሞች መነኮሳት ገዳማቸውን እየተዉ ወደነሱ መምጣት ጀመሩ፤ ከምእመናኑም ብዙዎች የነሱን መንፈሳዊነት ይመርጡ ጀመር። ስለዚህ ተከታዮቻቸው እየበዙ ሄዱ።

እንዲህ ከሆነ የጥንቶቹ አድባራት አለቆች አድባሮቻቸው የሚራቆቱባቸው ስለመሰላቸው፥ ንጉሡም የሚደፍረው (የማይስግድለት) ስው ብዛት የሚያድግ ስለመሰለው ሁሉም በየበኩላቸው የየራሳቸውን ጥቅም ለመጠበቅ ያዋጣ የመሰላቸውን እርምጃ በጎብረት ወስዱባቸው። ደቂቀ እስጢፋኖስም ለመፈተኛ ለሚያቀርቡላቸው ሥዕለ ማርያምና መስቀል አንስግድም ማለታቸው ለጠላቶቻቸው የተመቹ የጋራ ዒላማ አደረጋቸው። ገድለ ዕዝራ እንዳለው፥ *"ወተማሰጥዎሙ ለደቂቁ ክመ ዘይመስጥ ዐንቂ ለአዕዋፍ"* ("ልጆቹን ጭልፊት ወፎችን እንደምትቀልብ ተቃለቧቸው")።

ሊገመት የሚያዳግት ስደትና ሥቃይ ቢደርስባቸውም፥ ገዳማቸው ዛሬም አለ፤ መነኮሳትም አሉበት። እስካሁን በልዩ ልዩ ምክንያት ተራቀኑቶባቸው ካልሆነ፥ እቃ ቤታቸውም የመጻሕፍት ባለጸጋ እንደሆነ የሞርዲኒ ዘገባ አስረድቶናል።[23] እነዚህ የተረጉምኳቸው ገድሎች ሁሉም የተገኙት ከነሱ ገዳም ነው። በአቋም ወይም በእምነት ረገድ ግን ከሌሎቹ ገዳማት በምን እንደሚለዩ ግልጽ የሆነ ነገር የለም።

23. Antonio Mordini, "Il Convento di Gunde Gundiè," *RSE*, vol. 12 (1953), pp. 29-70 (+ 31 figures).

ቤተ ክርስቲያንን ያመለጠ ዕድል

ቤተ ክርስቲያኑን በማገልገል ረገድ እዬ ዘርአ ያዕቆብን የሚወዳደረው ንጉሥ በተጻፈው በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ የለም። ለቤተ ክርስቲያኑ ከልቡ አሳቢ ከሆነ፥ ሲሆን ከደቂቀ ኤምስጣቴዎስ ጋራ ያደረገውን ዕርቅ[24] ዓይነት ከደቂቀ እስጢፋኖስም ጋራ አድርጎ አብሮ ቢሠራ፥ አለዚያም እንዳሳየ ቢያያቸው ኖሮ ምናልባት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ተአምር ይታይ ነበረ። ንጉሡ ደቂቀ አስጢፋኖስን ሲቀጣቸው ክርስቲያኖችን የሚጠሉ ወገኖች አግኝተው አንዲያውቃዩዋቸው፥ በዚያውም ክርስትናቸው ረክሶ በስማይም አንዲኰነኑ ቤተ ክርስቲያን ከሌለበት ክርስቲያን ካልሆኑ ሕዝቦች መካከል ወስደው አንዲጥሏቸው ያዝዛል። ብዙ ጊዜ የፈለገው ሆኖለታል፤ የሰማዩ ኮነኔ በነሱ ላይ መድረስ አለመድረሱን ባናውቅም፥ እስላሞቹ ደም በማስተፋት "ቁጣውን አስተንፍሰውለታል።"

አንዳንድ ጊዜ ግን እግዚአብሔር የተጋዙበትን ሀገር "እየከፈተላቸው" ብዙዎቹን በስብከታቸው እያሳመኑ ክርስቲያኖች አንዲያውም መነኮሳት አድርገዋቸዋል። ንጉሡ ያንን ሲሰማ የታየው የቤተ ክርስቲያኗ ማደግ ሳይሆን፥ ለሱ የማይስማዱ ስዎች ቍጥር እየበዛ መሄድ ነው። እዚህ ላይ ለምሳሌ የሚጠቀስ ጥሩ ማስረጃ በፈጸጋር የሆነው ነው። ሰገቢ የሚባለው የፈጸጋር እንዱ ክፍል የእስላም ሀገር ኖሯል፤ እዚያ የሚኖሩት ደቂቀ እስጢፋኖስ እንደ ንጉሡና አንደ ዋናው ገዢ እንደ ራስ ዓምዱ ክርስቲያኖች ስለሆኑ አስላሙ የሰገቢ ሹም በሚሠሩት እየተናደደ የንጉሡንና የሀገረ ገዢውን "ወገኖች" ሊያጠፋቸው አልደፈረም ነበር። *ገድለ አበው ወአኃው* አንደሚያስረዳው፥ አሁን አየያዘ እንዲያመጣቸው ታዘዘ፤ አንዲበቀላቸው ፈቃድ አገኘ፤

> (138^ሰ) (ዘታኦስ) የሚባል መነኮሴ የስርማት መምህር ስለ ቅዱሳኑ የውሸት ደብዳቤ ጽፎ ከንጉሡ ዘንድ አመጣ። ንጉሡ የደብዳቤውን ቃል ስምቶ (139^ሀ) ዓምዱ ለሚባለው ለፈጸጋር አገረ ገዢ በሀገሩ (በግዛቱ) ያሉትን ቅዱሳን (ደቂቀ እስጢፋኖስን) እንዲያመጣቸው ነገረው። እሱም እነሱ ዘንድ (በስራቸው) ያሉትን ቅዱሳን አንዲያመጧቸው ለሀገሩ ፫ ሹማምንት የንጉሡን ተላላኪዎች ላከባቸው። የንጉሡ ተላላኪዎች ከነዚያ ሹማምንት ጋራ በየሀገሩ ሄዱ። ዘታኦስ የሚባለው መነኮሴም አብሯቸው ነበረ። ሲዲ የሚሉት የሰገቢ ሹም የቅዱሳኑ ጠላት ስለሆነ (ተላላኪዎቹን ቅዱሳኑ ካሉበት) ወለዳቸው። ቅዱሳኑ በስደት በሀገሩ ዱር ይኖሩ ነበር፤ እንኮይ፥ ናኬ፥ ኮሽም፥ ጣንጠ፥ ቀምጠሮ የሚባሉ የዛፍ ፍሬዎችና ከሰራሰርም ቀጠቤሉ፥ ኡሰስ፤ ከዛፍ ቅጠልም ቀረሞ የሚባል፤ ከምድር አትክልትና ከእህልም ሲያገኙ ይበሉ ነበረ። ከሰው ዘንድ ሲደርሱም

24. ደቂቀ ኤምስጣቴዎስ ቅዳሜ እንደ እሑድ ካልተከበረች ብለው ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥለው ነበረ፤ ንጉሡ ጥያቄያቸውን ተቀብሎ ዕርቅ አወረደ፤ Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia*, pp. 229-231.

ወንዱንም ሴቱንም ያስተምሩ ነበረ። ሲያጸምጧቸው ሕሊናቸው ይመሰጥ ነበረ። ከዓለማቸው እየወጡም ከነሱ ጋራ ሰለተደባለቁ (ቅዱሳኑ) ብዙዎች ሆኑ። (እሰላሙ) ሲዲ የሚባለው የዚያ ሀገር ሹም ቁጣ በዚህ ምክንያት ነበረ። እነዚያን የንጉሥ ተላላኪዎች ምክንያት አግኝቶ በውሾችና (139^ሰ) በሰዎች አደናቸው፤ ከዱር ሰበሰባቸውና በማነቆ እንደታሰሩ ከንጉሡ አደባባይ አመጧቸው።

ውዝግብና ሥነ ጽሑፍ

ደቂቀ እስጢፋኖስን የምናስታውሳቸው በሐሳብ አፍላቂነት ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎቻቸውን ብሔራዊ ሥነ ጽሑፍን እንዲያዳብሩ በማድረጋቸው ጭምር መሆን አለበት። በነሱ ምክንያት፥ ማለት እነሱን በመቃወም፥ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ እንደዳበረ በመጠኑም ቢሆን ልብ ያልን ይመስለኛል። ቦታው አይደለም እንጂ ተቃውሞው ስላስገኘው ሥነ ጽሑፋዊ አስተዋጽኦ ከዚህ የበለጠም ሰመጻፍ ይቻላል። ግን ሌላው ቢቀር በነሡ ምክንያት ተደርሰው ከመጽሐፈ ቅዳሴያችን የገቡትን ***መስተብቍዕ ዘማርያም*** እና ***መስተብቍዕ ዘመስቀል*** ("የ/ሰለማርያም ልመና" እና "የ/ስለመስቀል ልመና") የተባሉትን ሁለት ጸሎቶች ማሳየት ተገቢ ይመስለኛል።

መስተብቍዕ ዘማርያም[25]

ወካዕበ ናስተበቍኅ ለነቅዓ ሕይወት ለቅድሰት ደብራ፤
ዘወለደት ወአግመረት ጽርሰፎራ፤
ይትነከር ዕበየ ከብራ፥
ጊዜ ይትነበብ ተአምራ።
ጽልሕወ ልብ ብእሲ ሥጋ ቢጹ ዘበልዐ፥
ስመ ማርያም ዘፀውዐ፥
በሕፍነ ማይ ቈሪር መንግሥተ ለማያት ቦእ።
ሰሚዐክሙ አንክሩ፤
ዜና ዝክራ አፍቅሩ፤
መንግሥተ ዚአሃ ተዘከሩ፤
ዘከሶሎ ታድጎን እግዝእትነ ማርያም።
ንዑ ንሰግድ ወንግነይ ለንግሣ፤

25. ይህን መስተብቍዕ የቀዳሁት ካንድ የብራና መጽሐፍ ውስጥ ነው፤ EMML 2969, ff. 14b-15a, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, vol. VII: Project Numbers 2501-3000,* Collegeville, Minnesota, 1983, p. 282. ከታተሙት መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ያለው ከዚህ ይለያል።

ዘጸረት ወአግመረት በከርሣ፡
አግዚአ ስማይ ወምድር መስተስርየ ኃጢአት ወአበሳ፡
አንዘ ኢትሌሊ ባዕላየ ወኢትሜንን ነዳየ፡
ማርያምስ ታፈቅር ዘይገብር ሠናየ።
ዛቲ ይእቲ እኅተ ትጉሃን መላእክት፡
ወወለተ ኄራን ነቢያት፡
ብዕሎሙ ለሐዋርያት፡
ሞገስ ጻድቃን ወሰማዕት።
ላቲ ይደሉ ክብር ወስብሐት፤
ዘምስለ ወልዳ አምልኮ ወስግደት፡[26]
በምድር ወበሰማያት፡
በባሕር ወበቀላያት።
ለዓለመ ዓለም አሜን።

❖

<u>የማርያም መስተብቍዕ</u>

የሕይወት ምንጭ ቅድስት ድንኳንንም[27] አንለምናታለን፤
ጽርስፎራን (መሥዋዕትን) የወለደችና የቻለች ናትና፡
የክብሯ ታላቅነት ይደነቅ፡
ተአምሯ ሲነበብ።
አንድ ልበ ክፉ ሰው የመስሉን ሥጋ የበላ፡
የማርያምን ስም በመጥራቱ፡
በአንድ አፍኝ ቀዝቃዛ ውሐ መንግሥተ ሰማያት ገባ።
ሰምታችሁ አድንቁ፤
የዝክሯን ዜና ውደዱ፤
የሷን መንግሥት አስታውሱ፤

---

26. ከታተሙት የቅዳሴ መጻሕፍት ውስጥ ያለው ከዚህ የሚለይበት ዋናው ምክንያት ያልታተመው "*ዘ/ወምስለ ወልዳ አምልኮ ወስግደት*" ("ከልጇም ጋራ አምልኮትና ስግደት ይገባታል") ማለቱ ነው። "ማርያም ከልጇ ጋራ መመለክ ይገባታል" የሚለው ኑፋቄ በ1870 ዓ. ም. በቦሩ ሜዳ ጉባኤ·ላይ ተወግሟል፤ ጌታቸው ኃይሌ፡ *ባሕረ ሐሳብ*፡ ገጽ 266-267፤ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፡ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*፡ አዲስ አበባ ፲፱፻፺፱ ዓ ም፡ ገጽ 92።

27. ቅድስት ማርያም ድንኳን (ደብተራ) የምትባለው በብሉይ ኪዳን ታቦተ ጽዮን (የሙሴ ጽላት) መቅደስ አስኪሠራላት ድረስ በድንኳን ትኖር ስለነበረ ነው። ጽዮን የክርስቶስ ምሳሌ፡ ማርያም ክርስቶስ በማሕፀኗ ስለነበረ የድንኳኑ ምሳሌ ናቸው።

ሁሉን የምታድን እመቤታችን ማርያም ነች።
ኑ ለንግሷ እንሰገድ፥ እናመስግናትም/እንገዛላትም፥
በሆዷ የተሸከመችና የቻለች ናት÷
ኃጢአትንና አበሳን የሚያስተሰርይ የሰማይና የምድር ጌታን።
ሀብታምን ሳትለይ (ከፍ ሳታደርግ?)÷ ደኻንም ሳትንቅ÷
ማርያም ጥሩ የሚሠራውን (ሁሉ) ትወዳለች።
ይቺ ናት የትጉዎች መላእክት እኅት÷
የደኅች ነቢያት ልጅ÷
የሐዋርያት ሀብት÷
የጻድቃንና የሰማዕታት ሞገስ።
ለሷ ክብርና ስብሐት ይገባታል፥
ከልጇም ጋራ አምልኮና ስግደት፥[26]
በምድርም በሰማዮችም÷
በባሕርም በውቅያኖስም፥
ለዓለመ ዓለም እሜን።

መስተብቍዕ ዘመስቀል[28]

ወካዕበ ናስተበቍዖ ለዕፀ ቅዱስ መስቀል፥
ጽኑዕ ሥልጣን ወኃይል፥
ወሊሉየ መልክዕ ወአካል÷
አመልክዐ በትሩ ለአሮን ካህነ ጽላሎት ወአምሳል።
በትረ አሮንሰ ዘሠረፀት ወፈረየት ከርካዐ ዘአንበለ ተክል÷
እንዘ ትቀውም በአፍአ÷
ኢያድኅነት ጻድቀ ወኢቤዘወት ኃጥአ፥
አስመ አልባቲ ክሂለ ወኢመዊአ።
መስቀለ ክርስቶስሰ ቤዛነ ወኃይልነ፥
እግዓዘ ጻድቃነ ወኃጥኣነ፥
አምግብርናተ ሰይጣን ጸላኢነ÷
ነሚአ ሥልጣነ እግዚአብሔር አምላክነ።

ይ. ዲ.፤

ጸልዩ ቅድመ መስቀል ኮልክሙ መሃይምናን÷
እንዘ ትእኅዝዎ በየማን÷

---

28. *መጽሐፈ ቅዳሴ*÷ አስመራ÷ በ፲፱፻፺፯ ዓመተ ምሕረት÷ ገጽ 191. ስለ መስቀል መስተብቍዕም ቢሆን ስምምነት የለም። ለምሳሌ በታተሙት መጽሐፎች ውስጥ ሁሉ የለም። ይኸ የአስመራው *መጽሐፈ ቅዳሴ*ም ቢሆን÷ *"መስተብቍዕ ዘመስቀል"* የሚለው ከውስጡ ነው፥ ከማውጫው ላይ ግን *"መስተብቍዕ ዘመድኃኔ ዓለም"* ("የመድኃኔ ዓለም መስተብቍዕ") ነው የሚለው፥ ገጽ 211።

ወትክህድዎ ለሠይጣን፤
እስመ ተቀደሰ በደመ ክርስቶስ መድኅን::

ይ. ሕ.

ክቡር እንተ ንጉሠ ዕፀዋት መስቀል፤
ክቡር እንተ ዕፀ መስቀል፤
ወክቡር ዘተቀደስከ በደመ ክርስቶስ ቃል::

ይ. ካ.

ለክብረ ዝንቱ መስቀል ክርስቶላውያን ንሰግድ÷
በፍርሃት ወበረዓድ፤
ኪያሁ ፈጣሪ ህላዌ ወልድ
እስመ ቀደሶ በደሙ ወእኩ በደመ ባዕድ፤
መልዕልተ ዝንቱ መስቀል እመ ሞተ መለኮት በትሰብእቱ::
ትስብእትሰ እመለኮቱ ኢተፈልጠ ወኢተቶስሐ ቦቱ::
በበትረ ዝንቱ መስቀል ሐዋርያቲሁ ለዘሞተ÷
እንዘ ይገብሩ መንክራተ÷
ሰደዱ እጋንንተ፤
ወሰበሩ ጣኦታተ::
በእንተ ዝንቱ እዘዙ መምህራኑ ቅዱስ ወንጌል÷
አምላለ ፈጣሪ ልዑል÷
ንሰግድ ለመስቀል ወለማርያም ድንግል::
ለማርያምሰ ዘንሰግድ ላቲ÷ እስመ ነሥአ ሥጋ እምሥጋሃ
እግዚአብሔር ፈጣሪሃ፤
ወረከብነ ንሕነ መድኃኒተ እምኔሃ::
ለዕፀ መስቀልሂ ከመ ተናገርነ ቅድመ÷
(እስመ) ላዕሌሁ እንጠብጠበ ደመ÷
ቃል ኢሐማሚ በባሕርየ ሥጋ ዘሐመ::
ለእሉ ፪ቱ ፍጡራን ስብሐተ ፈጣሪ ይደልዎሙ፤
እስመ ተዐረዩ በክብሮሙ::
ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን::

❖

<u>የመስቀል መስተብቍዕ</u>

የቅዱስ መስቀል እንጨትንም እንለምነዋለን÷
የሥልጣንና የኃይል ጥንካሬ ያለውን::
በመልክና በእካልም የተለየ የሆነውን÷

ከጥላውና ከምሳሌው (ከብሉይ ዘመን) ካህን ከአሮን በትር።
የአሮን በትር ሳትተከል ብትበቅልና ኮክ ብታፈራም
እደጅ ቆማ
ጻድቅን አላዳነችም፤ ኃጥእንም አልተበዠችም፤
ችሎታና ማሸነፍ የሰባትምና።
የክርስቶስ መስቀል ግን ቤዛችንና ኃይላችን ነው፤
ጻድቆችንና ኃጢአተኞችን ነፃ አውጥቷል፤
ከጠላታችን ከሰይጣን ባርነት፥
ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ሥልጣን ወስዶ።

ዲያቆን እንዲህ ይበል

ሁላችሁም ምእመናን በመስቀል ፊት ጸልዩ፤
በቀኝ እጅ ይዛችሁት፥
ሰይጣንንም ክዳችሁ፤
በመድኅን በክርስቶስ ደም ተቀድሷልና።

ሕዝብ እንዲህ ይበል

የእንጨቶች ንጉሥ መስቀል ሆይ፥ ክቡር ነህ፤
የመስቀል እንጨት ሆይ፥ ክቡር ነህ፤
በክርስቶስ በቃል ደም የተቀደስክ ክቡር ነህ።

ቄስ እንዲህ ይበል

ስለዚህ መስቀል ክብር (እኛ) ክርስቶላውያን እንሰግዳለን፤
በፍርሀትና በመራድ።
እሱ ራሱ ፈጣሪ በወልድ የተገለጸው
በሌላ ደም ላይሆን በራሱ ደም ቀድሶታልና።
በዚህ መስቀል ላይ መሰከት በሰውነቱ የሞተ ጊዜ፥
ሰውነትም ከመለኮቱ አልተለየም፥ አልተጨመረበትም።
በዚህ መስቀል ዘንግ የሚቹ (የክርስቶስ) ሐዋርያት
ታምር ሲሠሩ፤
አጋንንትን አባረሩ(በት)፤
ጣኣቶችን ሰበሩ(በት)።
ስለዚህ የቅዱስ ወንጌል መምህሮች አዝዘዋል፥
የልዑል ፈጣሪ ምሳሌዎች፥
ለመስቀልና ለድንግል ማርያም እንድንሰግድ።
ለማርያም የምንሰግድላት ከሥጋዋ ሥጋ ስለወሰደ፥
እግዚአብሔር ፈጣሪዋ
እኛም ከሷ መድኃኒትን (ክርስቶስን) ስላገኘን ነው።
ለመስቀል እንጨት ደግሞ፥ በፊት እንደተናገርነው፥

አሳዩ ላይ ደም ስላንጠባጠበ
የማይሰቃይ ቃል በሥጋ ባሕርይ የተሰቃየው።
ለነዚህ ሁለት ፍጡሮች የፈጣሪ ስብሐት ይገባቸዋል፤
በክብራቸው ተካክለዋልና።
አሁንም፥ ሁል ጊዜም፥ ለዓለመ ዓለምም፤ አሜን።

ምንጮች

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ጀምሮ፥ የአውሮፓ ሊቃውንት ኢትዮጵያን ማጥናት ካፋፋሙበት ዘመን ጀምሮ ስለ ደቂቀ እስጢፋኖስ በስፊው ያውቃሉ። ስለዚህ ታላቅ ብሔራዊ የአእምሮ አንቅስቃሴና አስተሳሰብ የማያውቀው ከላይ እንዳመለከትኩት፥ ከኢትዮጵያ ባህላዊ ትምህርት የተገለለው የዘመኑ የተማሪ ትውልድ ብቻ ነው። ሊቃውንታችን ደቂቀ አስጢፋኖስን የሚያውቋቸው ዘርአ ያዕቆብና ተከታዮቹ ካቆዩት ሥነ ጽሑፍ ስለሆነ በተወገዙ ክሓዲዎችነት ነው።[29] እንዳንዶቹ ምንጮች ደቂቀ እስጢፋኖስ ለቅድስት ድንግል ማርያም የሚገባትን ክብር ስላልሰጧት የሠራችባቸው ተአምርና የጻጻሳቱ ግዝት ነው ተብለው በእንዳንድ *ተአምረ ማርያም* መጻሕፍት ውስጥ ተቀድተው ይገኛሉ።[30] ሌሎቹ ከላይ እንደጠቀስኳቸው ሁለት የመስተብቁዕ ጸሎቶች፥ ለቅድስት ማርያምና ለክቡር መስቀል ለምን መስገድ እንደሚገባ የሚያስረዱ ብዙ ድርሰቶች ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የደቂቀ እስጢፋኖስን ጽሑፎች ስለማያነቡ ደቂቀ እስጢፋኖስ ስለራሳቸው የሚሉትን የሚያውቁት አይመስለኝም።

የኢትዮጵያን ታሪክ የሚመራመሩ የውጪ አገር ሊቃውንት ደቂቀ እስጢፋኖስን የሚያውቋቸው ከ*ተአምረ ማርያም* መጻሕፍት፥ ከነገሥቱ ታሪክ እና ከራሳቸው ከደቂቀ እስጢፋኖስ ገድሎች ነው። እነዚህ የውጪ አገር ሊቃውንት ከሁለቱም በኩል ተጽፎ የተገኘውን አየመረመሩ ጠቃሚ የታሪክ ምንጮች አሳትመዋል።

ከቅርቡ ጊዜና አብዛኛውን ጊዜ በሚጠቀሱት ልጆምርና፥ የመጀመሪያው ድርሰት ዲልማን በ1884 ዓ. እ. (A.D.) ስለ አፄ ዘርአ ያዕቆብ

---

29. የዘመኑ ሁለቱ ጳጳሳት አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል እንዳወገዟቸው የ*ተአምረ ማርያም* መቅድም ይናገራል፤ *ተአምረ ማርያም* ፥ ገጽ 20። እነሱ ግን ጳጳሱ አባ ገብርኤል ይደግፏቸው እንደነበረ ይናገራሉ፤ *ገድለ አበው ወአንሙ*፤ EMML 4, f.62b-64a. እዚህም ገጽ 148–9።

30. የኢትዮጵያን ታሪክ ለመጻፍ ተአምራቱና ገድላቱ የቱን ያህል ጠቃሚዎች እንደሆኑና በጥንቃቄ፥ በአክብሮት ሊያዙና ሊመረመሩ እንደሚገባ በዚህ አጋጣሚ ለማየት እንችላለን። ስለ ታሪክ ምንጭነታቸው ከዚህ ይበልጥ ለማወቅ የፈለገ ከላይ በጎዳግ ቍጥር 10 የተሰጠውን የታደሰ ታምራትን መጽሐፍ ማንበብ ይችላል። ሌላው ማስታወስ ያለብን "*ተአምረ ማርያም*"

አገዛዝና ስለ አቋቋመው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በጀርመንኛ ያሳተመው ጥናት ነው::[31] ጥናቱ ስለ ደቂቀ አስጢፋኖስ ስፋ ያለ ትችት አለበት:: ከዚያ ቀጥሎ ዢፉል ፔሩሾ የአፄ ዘርአ ያዕቆብንና የተከታዮቹን ነገሥት ታሪክ በ1893 እና በ1894 ዓ. እ. ከፈረንሳይኛ ትርጉሙ ጋራ አሳተመ::[32] አነዚህ ታሪክ ነገሥት ደቂቀ አስጢፋኖስን የሚመለከቱ ክፍሎች አሉባቸው:: ቀጥሎ ኮንቲ ሮሲኒ የአባ አበክረዙንን ገድል በ1910 ዓ. እ. ከላቲንኛ ትርጉሙ ጋራ አሳተመ::[33] አባ አበክረዙን የአባ አስጢፋኖስ (የመንፈስ) ልጅና አበምኔትነቱን ወራሻቸው ነበሩ:: ኤንሪኮ ቸሩሊ በ1943 ዓ. እ. ተአምረ ማርያምን አጥንቶ የደቂቀ አስጢፋኖስን ታሪክም ያለበት አንድ ትልቅ መጽሐፍ በኢጣልያንኛ አወጣ::[34] አንቶኒዮ ሞርዲኒ ጉንዳጉንዴ ላይ ያለውን የአስጢፋኖሳውያንን ገዳም (ደብረ ገርዜንን) ጎብኝቶ ሲመጣ በ1953 ዓ. እ. ስለ ጉብኝቱ ስፋ ያለ ሁል ጊዜ የሚጠቀስ ዘገባ በኢጣልያንኛ አሳተመ::[35] በ1961 ዓ. እ. አንድሬ ካኩ የአቡነ ዕዝራን ገድል ከፈረንሳይኛ ትርጉሙ ጋራ አሳተመ::[36] አቡነ ዕዝራም የአባ አስጢፋኖስ ተክታይና የአንዱ ገዳማቸው አበምኔት ነበሩ:: ኩርት ቬንት በ1962 ዓ. እ. እና በ1963 አከታትሎ ከጀርመንኛ ትርጉሙ ጋራ ያሳተማቸው የአፄ ዘርአ ያዕቆብ መጽሐፈ ሚላድና መጽሐፈ ሥላሴ[37] ፡ ከዚያ፡ ኮንቲ ሮሲኒና ላንፍራንኮ ሪቺ በ1964/5 ዓ. እ. ከኢጣልያንኛ ትርጉማቸው ጋራ ያሳተሙት የዚሁ ንጉሥ

የሚባል አንድ መጽሐፍ አለመኖሩን ነው:: አያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የራሱን ተአምረ ማርያም ስለሚያሰቀዳ በየመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ታምራት ቍጥርና ዓይነት ይለያያሉ:: በ1961 ዓ. ም. በተሰፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት የታተመውም ተአምረ ማርያም የያዘው አሳታሚው የመረጣቸው ታምራት ብቻ ናቸው::

31. August Dillmann, "Über die Regierung, insbesondere die Kirchenordnung des König Zar'a-Jacob," *Abhandlungen der Königl. Akademie der Wissenschaften zu Berlin*, vol. 2 (1884), Philos.-histor. Klasse (1885).
32. Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm, rois d'Éthiopie de 1434 a 1478*, Paris 1893; Perruchon, "Histoire d'Eskender, d'"Amda-Ṣeyon II et de Nâ'od, rois d'Éthiopie," *Journal asiatique*, vol. 9, ser. 3 (1894), pp. 319-366.
33. Conti Rossini, *Gadla Abuna Abakerazun seu Acta Sancti Abakerazun*, *CSCO*, 56/25, Louvain 1954.
34. Enrico Cerulli, *Il libro etiopico dei miracoli di Maria.*
35. Antonio Mordini, "Il Convento di Gunde Gundiè."
36. A. Caquot, "Les Actes d'Ezrā de Gunda-Gundē," pp. 72-121.
37. Kurt Wendt, *Das Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis) des Kaizers Zar'a Yā'qob*, *CSCO*, vol. 221/41, Louvain 1962 and *CSCO*, vol. 235/43, Louvain 1963.

መጽሐፈ ብርሃን[38] ደቂቀ እስጢፋኖስን (ደቂቀ እስጢፋን) የሚያወግዙ አንቀጾች አሉባቸው። ታደሰ ታምራትና ሮቤር ቤሎ ገድለ እስጢፋኖስን እና ሌሎችን ገድሎች አጥንተው ታደሰ ታምራት በ1966 ዓ. እ. በእንግሊዝኛ ስለ ንቅናቄው ጠቃሚ ጠቅላላ ታሪክ፥ ቤሎ በ1970 ዓ. እ. በፈረንሳይኛ ስለ አምነታቸው አንዳንድ ድርሰቶች አሳትመዋል።[39] ከነሱ ቀጥሎ በ1976 ዓ. እ. አሌክሳንደር ፌሬንክ ገድለ አቡነ ኢሳይያስን ከፈረንሳይኛ ትርጉሙ ጋራ አሳተመ።[40]

ከሞርዲኒ ዘገባ ያወቅናቸው እስካሁን ገና ያልታተሙ ብዙ የእስጢፋኖሳውያን ገድሎች አሉ፤ አንዱ ይኸ አሁን ከሌሎቹ ገድሎች ጋራ ለጎትመት ያቀረብኩት ገድለ እስጢፋኖስ ነው። ብዙ ዋጋ የሚሰጠው፥ ቅጂው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጻሕፍት የመታወቂያ ቁጥር 496 ተሰጥቶት የሚገኘው (እዚህ ከተረጐምኳቸው ገድሎች አንዱ) ገድለ አበው መአጋው የሚባለው ስንክሳር መሰል መጽሐፋቸው ነው።[41]

ከጥቂቶቹ ጥናቶችና ድርሰቶች በቀር የእነዚህ ሊቃውንትና በመሰኩ ያለነው የሌሎቻችን ጥናቶች ሁሉ የታተሙት በውጭ አገር ተመራማሪዎች

---

38. Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 250/47, Louvain 1965, and *CSCO*, vol. 261/51, Louvain 1965.

39. Taddesse Tamrat, "Some Notes on the Fifteenth Century Stephanite 'Heresy' in the Ethiopian Church," *RSE*, vol. 22 (1966), pp. 103-115; and Robert Beylot, "Un épisode de l'histoire ecclésiastique de l'Éthiopie. Le mouvement Stéphanite. Essai sur sa chronologie et sa doctrine," *AÉ*, vol. 8 (1970), pp. 103-116.

40. Aleksander Ferenc, "Les Actes d'Isaïe de Gunda-Gundē," *AÉ* , vol. 10 (1976), pp. 243-294; የስታኒስላው ኩር ማስታወሻም እዚህ ላይ ሊታወስ ይገባል፤ Stanislaw Kur, "Les stéphanites à la lumière des *Actes d'Isaïe* de Gunda-Gundē" (ed. Claude Lepage *et al*), *Étude éthiopiennes vol. I, Actes de la X^e conférence Internationale des études éthiopiennes*, Paris 1994, pp. 359-361. እኔም ገድለ አበው መአጋውን እና ድርሰቱን እስካጠናቀኩበት ድረስ የታተሙትን ዋና ዋና ምንጮች (ድርሰቶችና ገድሎች) አጥንቼ በ1983 ዓ. እ. አንድ መጣጥፍ በእንግሊዝኛ አሳትሜያለሁ፤ Getatchew Haile, "The Cause of the Ǝstifanosites: A Fundamentalist Sect in the Church of Ethiopia," *Paideuma*, vol. 29 (1983), pp. 93-119.

41. EMML 4, William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa, and for the Monastic Manuscript Library, Collegeville, vol. I: Project Numbers 1-300*, Collegeville, (Minnesota) 1975, p. 7.

መድረክ ላይ ስለሆነ፥ ብዙ የተማሩ ኢትዮጵያውያን፥ በተለየም ከሁሉ እስቀድሞ ማወቅ የሚገባቸው ብዙ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወገኖች፥ ያነበቧቸው እይመስለኝም። ግን አንድ ሕዝብ ስለራሱ የሚባለውን ቢያንስ ቢያንስ የነቃፊዎቹንና የአድናቂዎቹን ያህል ካላወቀ ጉዳቱ ጥቂት አይሆንም፤ ቤትን ከአፍራሾች ለማስጣል የሚቻለው ነቅቶ በመጠበቅና ማፍረሻውን በመንጠቅ ነው። አንድ ሕዝብ ነቃፊዎቹን ማሳፈር፥ በራሱ አባቶች ሐሳብ መጠቀም፥ ራሱንም ማረም የሚችለው፥ ሐሳብ አፍላቂዎችና ለእምነታቸው የሚሞቱ የሚያኮሩ አባቶች እንደነበሩትና አሁንም እንዳሉት ሲያውቅና ሲያዳምጥ ነው። የውስጥ ነቃፊ ጠንቃ፥ የውጪ ነቃፊ አፍራሽ መሆኑ የታወቀ ነው።

ይህን ሶስተኛ መጽሐፍ ስጀምር በአንድ ቅጽ ላቀርብ ያሰብኩት የገድለ አስጢፋኖሰን ትርጉሜን ብቻ ነበረ። ገድሉ አጭር ስለሆነ፥ ሁለተኛም የሌሎቹን ገድሎች ማስቀረቱ የንቅናቄውን ሙሉ ሥዕል በብዙው የሚያስቀር ሆኖ ስላየሁት ከገድለ አስጢፋኖሰ ጋራ የገድለ አበው ወአንው፥ የገድለ አበክረዙን፥ የገድለ ዕዝራ ትርጉሞቼ አብረው እንዲታተሙ ወሰንኩ። በነዚህ የተወሰንኩት በነሱ መወሰኔ ቀላል ስለሆነልኝና በቂ ስለመሰለኝ ነው። ሌሎቹ ገድሎች ለጊዜው በእጄ የሉም፤ ፈሬንክ ያሳተመው ገድለ አቡነ ኢሳይያስ ስለንቅናቄው እንዳችም የሚያስተምረን ነገር አላገኘሁበትም።

ገድለ አስጢፋኖስ አሁን በስንት ቅጂ እንዳለ በትክክል አይታወቅም። ግን ሶስት ቅጂዎች እንዳሉ እናውቃለን፤ ሁለቱን ሞርዲኒ ከዘገባው ውስጥ ዘርዝሯቸዋል።[42] ከነዚህ አንዱ አሁን Spencer 7 በሚል የመታወቂያ ቁጥር በኒው ዮርክ ሕዝባዊ ቤተ መጽሐፍት (New York Public Library) የሚገኘው ነው። *Christentum am Nil* በሚባል ካታሎግ ውስጥ Gunda Gunde MS 103 በሚል መታወቂያ ቁጥር እንደተመዘገበው፥ መጽሐፉ እስከ 1964 ዓ. እ. ድረስ በአንቶኒዮ ሞርዲኒ እጅ ነበረ። በ1972 ዓ. እ. ግድም ሚላኖ ከተማ ከአንድ ነጋዴ እጅ ይወድቃል። በመጨረሻ በ1973 ዓ. እ. በአንድ ሀብታም (በስፔንስር) ልገሳ ተገዝቶ አሁን በዚህ በኒው ዮርክ ሕዝባዊ ቤተ መጻሕፍት ይገኛል። ይህ መጽሐፍ የቅርብ ጊዜ እጅ አልፎ አልፎ እርማት አስገብቶበታል እንጂ፥ በዓሥራ አምስተኛው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ የተቀዳ ስለሆነ ቁጥሩ የጥንት ከሚባሉት ብርቅ መጻሕፍት ነው።[43]

ሁለተኛው ቅጂ በዚያው ዘመን የተቀዳ አሁን በአዲስ አበባ የአርኬዎሎጂ ኢንስቲትዩት ቤተ መጻሕፍት አለ የሚባለው[44] ሳይሆን

42. Mordini, "Il Convento di Gunde Gundiè," p. 50 (no. 103 and 146).

43. ሲኞር ሞርዲኒ የአስጢፋኖሳውያንን ገዳም የጐበኘ ጊዜ አግረ መንገዱን የሚያበለጽጉ አንዳንድ መረጃዎች ሸጉጦ አንጂ፥ ባዶ እጁን አልተመለሰም ማለት ይሆን?

44. Kinefe-Rigb Zelleke, "Bibliography of the Ethiopic Hagiographical Traditions," *JES*, vol. 13, no. 2 (1975), p. 69 (entry no. 48).

አይቀርም። ሶስተኛው ኮንቲ ሮሲኒ ለራሱ ያስቀዳው፥ አሁን ሮማ በሊንቼ ሕዝባዊ አካዴሚ (Accademia Nazionale dei Lincei) ቤተ መጻሕፍት ውስጥ በመታወቂያ ቁጥር 24 የተቀመጠው ነው።[45]

ለዚህ ጥናት የተጠቀምኩት በኒው ዮርኩና በሮማው ቅጂዎች ነው። ገጾቹን የሰጠሁት ግን የኒው ዮርኩን ነው። ቅጂዎቹን በማይክሮፊልም በራሳቸው ወጪ ያስመጡልኝ የኒው ዮርኩን የምሠራበት የቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ የማይክሮፊልም ቤተ መጻሕፍት፥ የሮማውን ፕሮፌሰር ላንፍራንኮ ሪቺ (Professor Lanfranco Ricci) ናቸው። ጥናቴን የመሠረትኩት በኒው ዮርኩ ቅጂ ላይ ነው። የሮማው ያሁኑ ምእት ዓመት (የቅርብ ጊዜ) ቅጂ ከመሆኑ በላይ ከኒው ዮርኩ ቅጂ ጋራ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚመሳሰል በኒው ዮርኩ ቅጂ ውስጥ የሚታዩትን ግልጽ ያልሆኑ ቃላት በማብራራት ረገድ አስተዋጽኦው የተመጠነ ነው።

የአዲስ አበባውን ቅጂ ዶ/ር ታየ አሰፋና አቶ ውዱ ጣፈጠ ካሱ ሊያገኙልኝ ብዙ ደክመው እንዳልተገኘላቸው ጸፉልኝ። ቅጂው የጥንት ስለሆነ ለጥናቴ እንድጠቀምበት ብዙ ጓጉቼ ነበረ። በያዝኳቸው ቅጂዎች ውስጥ ያሉ አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑ ነጥቦች ምንም እንኳን ትርጉሜን ያልተሟላ ባያደርጉትም፥ የግምት እርማቴን የአዲስ አበባው ምስክር ወይ ያጸድቅልኛል ወይ የተሻለ እርማት ይሰጠኛል ብዬ ተስፋ ጥየበት ነበረ።[46]

ገድለ አበው ወአኃውን የተረጐምኩት ከላይ ከጠቀስኩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጻሕፍት የመታወቂያ ቁጥር 496 ተሰጥቶት ከሚገኘው መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ በፊልም ተነሥቶ በምሠራበት HMML በተባለው ቤተ መጻሕፍት በመታወቂያ ቁጥር EMML 4 ይገኛል። የተጠቀምኩት በዚህና ዶክተር ታየ አሰፋ ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጻሕፍት አስፈቅዶ በፊልም በላከልኝ ቅጂ ነው። ይኸንን ገድል የተረጐምኩት የአባ አስጢፋኖስን ገድልና ትምህርት የሚደግሙትን የመጀመሪያዎቹን 23 ተኩል ቅጠሎች ዘልዬ ነው። ይኸንን ውሳኔ የወሰድኩት ከተረጐምኩት ራሱን ከቻለው ገድላቸው የተለየ ትምህርት ስላላየሁበት ነው።

ገድለ አበው ወአኃው የቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት የገጽ ቁጥር ሰጥቶ በመታወቂያ ቁጥር EMML 4 በፊልም ካስነሣው ወዲህ ለሁለተኛ ጊዜ የገጽ ቁጥር ተሰጥቶታል። ሁለቱ የተለያዩ ስለሆኑና አንዱን መከተል ስላለብኝ፥ የተከተልኩትና በቅንፍ የሰጠሁት የEMML 4ን ነው። የምተረጐመውን መጽሐፍ ገጽ የምሰጠው የኔን ትርጉም ከግዕዙ ጋራ ለማመሳከር የሚፈልግ ወይም አሻሽሎ ለመተርጐም የሚሻ ካለ እንዲቀናው

45. Stefan Strelcyn, *Catalogue des Manuscrits Éthiopiens de l'Accadwmia Nazionale dei Lincei Fonds Conti Rossini et Fonds Caetani 209, 375, 376, 377, 378,* Roma 1976, p. 88.

46. ሁኔታው ሲኞር ሞርዲኒን ለመውቀስ አያመችም።

በማሰብ ነው። ሆኖም፥ ቍጥር ሰጪው 100 ብሎ 101 በማለት ፈንታ 110 ብሎ እንደቀጠሰና አንዳንድ ጊዜም ቍጥር እንደሚደግም ማስታወስ ያስፈልጋል። ለማንኛውም EMML 4 የተገለጠበትን ካታሎግ ማየት ይረዳል።

የአባ አበክረዙንን ገድል የተረጐምኩት በኒው ዮርክ ሕዝባዊ ቤተ መጽሐፍት (New York Public Library) በሚገኘው Spencer 7 በተባለው የብራና መጽሐፍ ውስጥ ከአባ አስጢፋኖስ ገድል ቀጥሎ ከተቀዳው ገድል ነው። ሁለቱም ባንድ ዘመን የተቀዱ ስለሆኑ አኩል ጥንታዊ ናቸው። ከላይ እንዳመለከትኩት፥ የአባ አበክረዙንን ገድል ኮንቲ ሮሲኒ በ1910 ዓ. አ. አሳትሞታል። ኮንቲ ሮሲኒ ገድሉን ለጎትመት ያዘጋጀው በዚያው ባሳ-ተመበት በሃያኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ ለሱ ከተቀዳለት ላይ ነው። በዚያ ላይ ግዕዙ የሰዋሰው ስሕተት አለበት፤ (Spencer 7ትም እንደዚሁ ነው)። የኮንቲ ሮሲኒ ጥረት የሚደነቅ ቢሆንም ብዙዎቹን ስሕተቶች ሳያርማቸው ቀርቷል። እንዲያውም አንዳንድ ቦታ ላይ ትክክሉ ግዕዝ ስሕተት እየመሰለው አርማለሁ ሲል አሳስቶታል። ለማንኛውም የኮንቲ ሮሲኒ ጥረት በተለየ ጥቅሶቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመፈለግ ረገድ ጊዜ እንዳላጠፋ ረድቶኛል፤ ለመፈለግ የሞከርኩት እሱ ያላገኛቸውን ነው። ይኸም ሆኖ እኔም ስሕተቶቹን በሞላ ላርማቸው አልቻልኩም፤ ጥቅሶቹንም በተለየ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ከጠቀሷቸው ውስጥ የጥቂቶቹን ምንጭ ላገኝ አልቻለኩም።

የአባ ዕዝራን ገድል ካኩ ካሳተመው ላይ ነው የተረጐምኩት (የማመለክተው ገጽም የሱን ነው)። ጥቅሶቹንም ካኩ እየፈለገ ስላገኛቸው በጥረቱ ተጠቅሜያለሁ።

የገድለ አበው መአጎው ምስክር

ገድለ አበው መአጎው ከፍተኛ የታሪክ ምንጭ ነው፤ አጻጻፉም እንደ ገድል ብቻ ሳይሆን እንደ ታሪክም ነው። ከዚህ ምንጭ እንደምናየው አንደኛ፥ ዛሬ ስማቸው የቀረ ወይም የተለወጠ ብዙ የቦታ ስሞች ያነሣል። ሁለተኛ፥ የደቂቀ አስጢፋኖስ እንቅስቃሴ ትግራይ ላይ ተጫረ እንጂ በሌሎቹም የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች ተቀባይነት አግኝቶ እንደነበረ ይመሰክራል። እንዲያውም የሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች ከሚባሉት ክርስቲያኖች (ከአማርኛና ከትግርኛ ተናጋሪዎች) አልፎ "ሌሎችንም" አቅፎ ነበር። *ገድለ አበው መአጎው* የተጻፈው ወይም የተቀዳው እነዚህ "ሌሎች" በምላቸው ኢትዮጵያውያን ጭምር ለመሆኑ ቋንቋው ያሳያል። ምን ማለቴ እንደሆነ የቋንቋ አስተማሪዎች ከሁሉ ቀድመው ይረዱታል። ማንም ሰው ካደገ በኋላ በተማረው (ባላደገበት) ቋንቋ ሲጠቀም ያደገበት የቤተሰቡ ቋንቋ በዚህ በአዲሱ ቋንቋ ላይ ያንጸባርቅበታል። በ*ገድለ አበው መአጎው* ላይ የሆነው ይህ ነው፤ ያፍ መፍቻ ቋንቋው ትግርኛ ወይም አማርኛ ያልሆነ ሰው ቋንቋ አንጸባርቆበታል። ጸሐፊው የትግራይ መነኩሳት ብቻ አልነበሩም፤ የሐዲያ ወይም የወላይታ ወይም የጋሞ ወይም የአናርያ (የበሻ) ወይም የአገው ቋንቋ ተናጋሪዎችም ያሉበት ይመስላል።

የገድለ አበው ወአኃው አሐፊዎችን "ሌሎች" መሆናቸውን የጠረጠርኩት ግዕዙን ካደጉ በኋላ ስለተማሩት ነው። ሌሎቹ የሐዲያ፥ የወላይታ፥ የጋሞ፥ የቦሻ፥ የትግሬ፥ የእማራ ወዘተ. ልጆች እንደሚያደርጉት በሕፃንነታቸው ተምረውት ቢሆን ኖሮ ስሕተቶቹ ሳይደረጉ ይቀሩና የወረስነው የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ "የእማሮችና የትግሬዎች ብቻ ቅርስ ነው" የሚባለው ውሸት ዙፋኑ ሳይደፈር እንደነገሠ ይኖር ነበር።

የእማሮችና የትግሬዎች ሊሆኑ እይችሉም ከምላችው በገድለ አበው ወአኃው ላይ ከሚታዩት ስሕተቶች ውስጥ ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን ልጥቀስ፤

ወሚማ (*"ወሚመ"* በማለት ፈንታ)
እትዮጵያ (*"ኢትዮጵያ"* በማለት ፈንታ)
ቀለ (*"ቃለ"* በማለት ፈንታ)
ካነ (*"ካነ"* በማለት ፈንታ)
የጠውቁዎሙ (*"ያጠውቅዎሙ"* በማለት ፈንታ)
መርየም/ማርየም (*"ማርያም"* በማለት ፈንታ)
በሀየ (*"በሀየ"* በማለት ፈንታ)
እይሰግድ (*"ኢይሰግድ"* በማለት ፈንታ)
እዋ (*"እወ"* በማለት ፈንታ)
ምሕወረ (*"ምሕዋረ"* በማለት ፈንታ)
ዘተመለኩሱ (*"ዘታመነኰሱ"* በማለት ፈንታ)
ዘንታለ (*"ዘንተለ"* በማለት ፈንታ)
ከማ (*"ከመ"* በማለት ፈንታ)
ዕላተ (*"ዕለተ"* በማለት ፈንታ)
መህራና (*"መህረነ"* በማለት ፈንታ)
ሐዋርየት (*"ሐዋርያት"* በማለት ፈንታ)
ማነንክሙ (*"መነንክሙ"* በማለት ፈንታ)
ወማንገለ (*"ወመንገለ"* በማለት ፈንታ)
ፈነዋ (*"ፈነወ"* በማለት ፈንታ)
እምንቱ (*"እሙንቱ"* በማለት ፈንታ፤ ይኸ እንኳን የትግሬዎች ስሕተት ነው)
እሰማ ማርዓት ማርዓዊ (*"እሰመ መርዓተ መርዓዊ"* በማለት ፈንታ)

ከዚህ የበለጠ ማምጣት ይቢዛል እንጂ እንዲህ ያለው ስሕተት ገጹን ሁሉ ሞልቶታል። ሆኖም እነዚህ ስሕተቶች የተጻፉት ተደጋግመው ቢሆንም ቃላቱ ሁል ጊዜ የሚታዩት ይኸንን መልካቸውን ብቻ ይዘው እይደለም። እንዲያውም አብዛኛውን ጊዜ የተጻፉት በትክክሉ መልካቸው ነው።

እነዚህ የቅርጽ ስሕተቶች ሊባሉ ይቻላል፤ የቃላቱ ቅርጻቸው "ተበላሽቷል።" ስሕተቶቹ በከፍተኛ ደረጃ ሲታዩ ታሪካዊ ብሔራዊ እገልግሎት አላቸው፤ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የሁሉ እንጂ የተወሰኑ ጎሳዎች ንብረት እለመሆኑን ይመሰክራሉ። በዝቅተኛ ደረጃ ሲታዩ ግን ጉዳት እይጠፋባቸውም፤ የቦታ ስሞችን አስተካክለው አልሰጡንም። መሳሳታቸው

የሚታወቀው ያንኑ ስም ደጋግመው ሲያነሡት የተለያየ ቅርጽ እየሰጡ ስለሆነ ነው። ትክክሉ የትኛው መልኩ ነው? ያልተለመዱ የአንድ አካባቢ ቃላትንም (ለምሳሌ የፍራፍሬዎችን ስም) ሲለጡን በትክክል ለመስጠታቸው ማስረጃ የለንም።

ሌላው ስሕተት ሰዋሰዋዊ ነው፤ *ገድለ አበው* መጎነው ውስጥ ብዙ ጊዜ አንድና ብዙ፥ ወንድና ሴት፥ ሩቅና ቅርብ ይምታታሉ። ለምሳሌ፥ ወይራራ የምትባለዋን (አንስታይ ፆታ) ወንዝ ወታደሮቹ "ሞልታ አገኟት" ለማለት፥ "ወረከብዋ ምልአተ" ወይም "ወረከብዋ በዘመልአት" በማለት ፈንታ "ወረከብዎሙ በዘመልአ" ("ሞልቶ አገኟቸው") ይላል። እንደዚህ ያለ ስሕተት በአማርኛና በትግርኛ ተናጋሪዎች ዘንድ ይኸንን ያህል የተለመደ አይደለም። በትግሬዎች ዘንድ የተለመደ ስሕተት "እሙንቱ" በማለት ፈንታ "እምንቱ" ማለት ነው፤ ይኸም በ*ገድለ አበው* መጎነው በብዙ ይታያል። ማንም የሚያደርገው ስሕተት ዘርፍና ተዛራፊን ማማታት ነው። ይህም በ*ገድለ አበው* መጎነው አልፎ አልፎ ይታያል፤ ለምሳሌ "በወንዚ ውሐ" ለማለት "በማየ ፈለጋ" በማለት ፈንታ "በፈለገ ማያ" ("በውሐዋ ወንዝ") ሲል ይገኛል።

የገድለ አበው መጎነው ጸሐፊዎች ትግሬ ወይም አማራ ብቻ ላለመሆናቸው ማስረጃው ግዕዙ ብቻ ሳይሆን ገለጻውም ምልክት አለበት፤

> (96^ሰ) ከዚያ፥ ይኸ ተንኮለኛ (ዘርአ ያዕቆብ) ቅዱሳኑ (ደቂቀ እስጢፋኖስ) በምድሩ እንዳይኖሩ ባጠበበባቸው ጊዜ እስከ (97^ሀ) ብሔሩ ዳርቻ፥ (ነዋሪዎቹ) ቤታቸው ከዛፍ ላይ ከሆነው እስከ ምድረ ፀጋም (ግራ ምድር) ደረሱ። (የዚህ አገር ሰዎች) አገርና አገር፥ የቅርብና የቅርብ መዋጋት ልማዳቸው ነው። እንዳንዶቹ ምድር ቆፍረው ለሰው፥ ለከብት፥ ለንብረት መኖሪያ ዋሻ ያበጁና ከዋሻው በላይ ቤታቸውን ይሠራሉ። ጦርነት ሲያይልባቸው በየሸንቁሮቹ ይገባሉ። ወደ ክርስቲያኑ ምድር ሲዘምቱ ወንድ ወንዱን ይገድላሉ፥ የዓመት የመንፈቅ ሕፃን እንኳን እይተዉም፤ መነኮሲም ካህንም አይምሩም። ቤተ ክርስቲያናቸውን ይመዘብሩታል፤ ሴቶቻቸውንና ንብረታቸውን ሁሉ ይማርኩና ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ። (ከነሱ ውሰጥ) አንድ ሰው የለው ግድያውን ከዓሥር ካደረሰ እንገቱና እጆቹ ላይ ቀይ ፈትል ያሰራል፤ የደም ምልክት ነው።
>
> በሌላ ላይ ይኸንን ሲሠሩ፥ ቅዱሳኑን ተቀበሏቸው፤ የሚገባውን ደግ ሥራ (ሁሉ) ሠሩላቸው፤ "ከሀገራችን ኑሩ" አሏቸው። እግዚአብሔር (97^ሰ) ለቅዱሳኑ እስከ ጊዜው ዕረፍት ሰለሰጣቸው አመሰገኑት። እዚያ ኖሩ፤ ከተበተኑበትም ተሰባሰቡ። ከዚያ ሀገር ሰዎች ከወንዱም ከሌቱም ብዙዎችን ወደ ትምህርታቸው መለሱ። ከዓለም ወጥተው (መነኮሰው) ለማዕት እስከ መሆን ደረሱ። እግዚአብሔር ያንን ሀገር ለቅዱሳኑ በሚፈልጉት ሁሉ ከፍቶላቸው ቤተ ክርስቲያን እስከ መትከል ደረሱ። የወንድሞቻቸውንም ተዝካር አወጡ።

መቸም ሁሉም በሰማዕት አያልቁም፤ ይኸንን ጽሑፍ ያቆዩልን ከነሱ ውስጥ የተረፉት የትግራይና እነዚህ "የግራ ምድር" ሰዎች ይመስሉኛል።

የመተርጐም ችግር

ከዘመን ብዛት የተነሣ አማርኛ ከግዕዙ እየራቀ በመሄዱ ይሁን፥ ወይም ከላይ በተቸሁት ምክንያት፥ ወይም በሌላ ግልጽ ባልሆነልኝ ምክንያት፥ ገድሎቹን ከግዕዝ ወደ አማርኛ ቃል በቃል ስተረጕማቸው አንዳንድ ቦታ ላይ ሐሳቡ ግልጽ ላይሆን ይቀራል። እንደዚህ ሲሆንብኝ፥ እንዳለ ጥዬው ከማለፍ በቅንፍ () ውስጥ ማሟያ ቃላትና በግርጌ ጎዳግ ማብራሪያዎች ስጥቻለሁ፥ በጣም ጥቂት ጊዜ ደግሞ ግዕዙን የማይተረጕም፥ መልአክቱን ግን የሚጠብቅ አማርኛ አምጥቻለሁ። ቅንፎቹ አንባቢን እንደማያደናቅፉ ተስፋ አለኝ፤ ዘዴው ያቀፏቸውን ቃላት አንጂ ቅንፎቹን አንዳላዩ አያዩ ማንበብ ነው። ይኸም ሁሉ ሆኖ፥ አንዳንድ ላቃናቸው ያልቻልኳቸው ዓረፍተ ነገሮች ቀርተውኛል።

ትርጕማቸው ከሚያስቸገሩ ቃላት ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ይገኙባቸዋል፤

"ሀገር"፥ "ምድር"፥ "ብሔር"፤ ምንጮቹ አንድን ቦታ "ሀገር"፥ ወይም "ምድር"፥ ወይም "ብሔር" ሲሉት የቦታውን ሁኔታ (ማለት፥ ጥበት ስፋቱን፥ ወይም የሰዉን ስፈራ) ስለማላውቀው እንዳለ ለመተው ሞክሬያለሁ። ግን ያንኑ ቦታ አንድ ምንጭ ለምሳሌ "ሀገር" ሲለው ሌላው "ብሔር" ብሎት ይገኛል። "ሀገር" በመሠረቱ "ከተማ"፥ "መንደር" ሲሆን፥ ክፍለ ሀገርንም (ቀበሌን፥ ወረዳን፥ አውራጃን፥ ጠቅላላውን ሀገርም) "ሀገር" ብለውት ይገኛል። ስለዚህ እነዘህ ቃላት የሚያመለክቱትን ቦታ በአጠራሩ ሁኔታውን ማወቅ የሚቻል አይመስለኝም። "ብሔር" ትርጕሙ "ሀገር" ሲሆን በብዙ ቊጥር "በሐውርት" ሲል "ሕዝቦች" ማለትም ይሆናል። "ምድር" ብቻ ነው ሕዝብን የማያመለክት።

መካን፤ ("ካ" ላይጠብቅ) የመካን ጥሬ ትርጕሙ "ቦታ" ነው። በተጨማሪ ዛሬ "ማእከል" የምንለው፥ (እንደ ገዳም ያለ) "የትምህርትና የሃይማኖት ቦታ" (ለምሳሌ "መካነ ሥላሴ")፥ "የንጉሥ እና የጳጳስ ግቢ" ሁሉ "መካን" ይባላሉ።

መኰንን/መኮንን፤ ቃሉ የተገኘው "ኰነነ/ኮነነ" ከሚለው የግዕዝ ግስ ሲሆን ትርጕሙ እንደኛ፥ "ፈረደ"፥ "ዳኘ" ("እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ" ማቴ 7፡ 1)፤ ሁለተኛ፥ "(አገር) ገዛ"፥ "(አገር) አስተዳደረ" ነው። "**መኰንን/መኮንን**" ማለት "ዳኛ"፥ "ፈራጅ"፥ "ገዢ"፥"አስተዳዳሪ" ማለት ነው። እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተረጎምኩት "ሀ/አገረ ገዢ" እያልኩ ነው። "**መኰንን** " የሚሉት የጠቅላይ ግዛት/የአውራጃ አስተዳዳሪውን ነው፤ ለምሳሌ፥ "መኰንነ ትግራይ"፥ "መኰንነ ፈጸጋር" ይላል። የወረዳ ገዢዎችን "ስዩም" ነው የሚሏቸው፤ ይኸንን "ሹም" እያልኩ ተርጕሜዋለሁ።

ሜጎበር፤ ሜጎበር የሚሉት የአንዱን ገዳም መነኮሳት ነው። በእንግሊዝኛ "ኮሚዩኒቲ" የሚባለው ነው።

ሜጎደር፤ ቃሉ "ነደረ" "አደረ" ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን ትርጕሙ "መኖሪያ" ማለት ነው። መነኮሳቱ የግል መኖሪያቸውን (በአትም ሆነ ጸማአት ወይም በገዳሙ ውስጥ ያለውን የግል መኖሪያ) ሜጎደር ይሉታል።

ምሥዋዕ፤ "ሠውዐ" "ሠዋ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን÷ ትርጉሙ "መሠዊያ" ማለት ነው:: በብሉይ ዘመን እንስሳት ይሠዉበት የነበረው ነው፤ በሐዲስ (በክርስትና) ዘመን በእንስሳቱ ቦታ ቊርባን (ሥጋ ክርስቶስ) ተተክቷል::

ሠራዊት፤ የዚህ ቃል ጥሬ ትርጉም "ሕዝብ" ነው፤ የወታደርን ሕዝብ ብቻ የሚያመለክት አይደለም:: በአማርኛም ቢሆን ባለመሣሪያውን ሠራዊት "የጦር" በሚል ቃል ካላብራራነው ብቻውን ባለመሣሪያ ወታደርን አያመለክትም፤ "የጦር" ሠራዊት ማለት ይኖርብናል:: (መሣሪያው "ጦር" መሆኑ ስለቀረ "ጦርነት"÷ "የጦር ሠራዊት" የሚሉት ቃላት ሁሉ አርጅተዋል):: እንግዲህ ምንጮቹ "ሠራዊት" ሲሉ ወይ "ሕዝብ" ወይም "የጦር ሠራዊት" ማለታቸው ሊሆን ይችላል::

"ስብሐት" እና "አኰቴት"፤ እነዚህ ሁለት ቃላት "ምስጋና" በሚለው ትርጉማቸው ሲመሳሰኩ÷ "ስብሐት" ከምስጋና ጨመር ያደርጋል፤ "ክብር"ን÷ "ከፍ ከፍ ማድረግ"ን ይጨምራል:: ስለዚህ "አኰቴት"ን እየተረጐምኩ÷ "ስብሐት"ን እንዳለ ትቸዋለሁ::

"በአት" እና "ጸማአት"፤ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይነት አላቸው:: ባሕታውያን የሚደበቁባት "ዋሻ"÷ "ጉሮኖ" ሲሆኑ ካስፈለገ "ጓዳ" እና "ጎጆ"ም በ"በአት"ነት እና "ጸማአት"ነት ያገለግላሉ:: ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ "አባ ጳንጠሌዎን ዘጸማአት" ይባላሉ፤ ከዋሻቸው አይወጡም ነበር:: ንጉሥ ካሌብ ወደ ብሔረ ሳባ ሲዘምት እዚያው አዋሻቸው ውስጥ ሆነው ነው የጸለዩለትና የባረኩት::

"ተግሣጽ" እና "ምዕዳን"፤ እነዚህ ሁለት ቃላት ተፈራራቂዎች ሲሆኑ ትርጉማቸው "ምክር"÷ "መጽናኛ ትምህርት"÷ "ስብከት" ማለት ነው:: እንዳሉ የተውኳቸው ምናልባት ለኔ ያልታየኝ ልዩነት ሊኖርባቸው ይችላል ብዬ በማሰብ ነው::

ነጋዲ፤ ("ጋ" ሳይጠብቅ) የተቀደሰ ቦታ ጎብኝቶ ለመጽደቅ ወይም ሸቀጥ ካንዱ አገር ወዳንዱ አገር እየወሰደ ለመሸጥ የሚጓዝ ማለት ነው:: "ነጋዴ" ("ጋ" ጠብቆ) የሚለው ቃል ከዚህ ጋራ ግንኙነት አለው:: የተቀደሰ ቦታ ጎብኝቶ ለመጽደቅ የሚጓዘውን ዐረቦች "ሓጅ"÷ እንግሊዞች "ፒልግሪም" ይሉታል::

አረሚ፤ "የአረሚ" ዋና ትርጉሙ "አረመኔ"÷ "የሚተዳደርበት የሃይማኖት ሕግ የሌለው" ማለት ነው:: ምንጮቹ ግን እስላሞቹንም "አረሚ" ይሏቸዋል:: ዓረቦች "ካፊር" እንደሚሉት ነው::

አቡን፤ በአሁኑ ጊዜ ይህ ቅጽል የሚሰጠው ለጳጳስ ብቻ ነው:: ቀደም ብሎ ግን የመነኮሳት በተለየም የጻድቃን መነኮሳት መጠሪያ ነበረ:: ለምሳሌ÷ አቡነ ተክለ ሃይማኖት÷ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ÷ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ጳጳሳት አልነበሩም:: ደቂቀ አስጢፋኖስም አባቶቻቸውን "አቡነ እገሌ" የሚሉት ይኸንኑ ልማድ ተከትለው ነው እንጂ ጳጳሶች ስለሆኑ አይደለም፤ ጳጳሶች አልነበሩም:: ቃሉ ምናልባት ታሪክ ሳይኖረው አይቀርም፤ ግብጾች መነኰሴን "አቡነ አገሌ"÷ ጳጳስን "አንባ አገሌ" ነው የሚሉት:: እኛም ዘንድ

በአንድ ዘመን መነኮሴን "አቡነ አገሌ"÷ ጳጳስን "አንባ አገሌ" ብለን ይሆናል። ዛሬ ጳጳስን "አንባ አገሌ" የማንል ይመስላል፤ ግን እንላለን። ብቻ "አንባ" ውስጥ ያለችው "ን" አጠገቧ ባለው "ባ" ተውጣ ቃሉ "አባ" ሆኗል። ጳጳሳት "አባ አገሌ" ይባላሉ።

"ገዳም"÷ "ዱር"÷ "ምድረ በዳ"÷ "ደብር"፤ እነዚህ ቦታዎች በመነኮሳት ዓይን የሚመሳሰሉበት ነገር አላቸው፤ የ"ሀገር" ተቃራኒዎች ናቸው። ሀገር የሚያመለክተው ሰው ያለበትን ምድር ሲሆን እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት ሰው የሌለበትን ነው። መነኮሴ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ከሀገር ወጥቶ ወደ "ገዳም"÷ "ዱር"÷ "ምድረ በዳ"÷ "ደብር" ይሄዳል። ከጊዜ በኋላ÷ "ዱር" እና "ምድረ በዳ"÷ ባሕታውያን መነኮሳት በተናጠል ብቻቸውን የሚኖሩባቸው ሲሆኑ÷ "ገዳም" እና "ደብር"÷ መነኮሳት በማኅበር የሚኖሩባቸው መካናትን የሚያመለክቱ ሆነዋል። "ደብር" በመሠረት ትርጕሙ "ተራራ" ማለት ነው። መነኮሳት ከሰው ለመራቅ ከተራራ ላይ እየወጡ ስለሚኖሩ÷ ተራራው ገዳም የሚል ትርጕም አተረፈ። ሁለተኛም÷ ንጉሥና ጳጳስ ያወቋቸውና ያከበሯቸው ገዳማት መካናቸው ከተራራ ጫፍ ላይ ባይሆንም÷ "ደብር" ተባሉ። ግሥም አለው፤ "ንጉሥ እገሌ የደበረው ገዳም" ይባላል። በመነኮሳት ዓለም "ደብር" ሁሉ "ገዳም" ነው፤ "ገዳም" ሁሉ ግን "ደብር" አይደለም።

ጻማ፤ "ጻማ" ማለት "ድካም" ማለት ሲሆን መነኮሳት እግዚአብሔርን ለመለማመጥ ራሳቸውም ሆኑ ሌሎች የሚያመጡባቸው መማቀቅ ነው፤ ለጽድቅ ሲሉ ሰውነታቸው ድቅቅ እስኪልና እስኪደክም ድረስ ይጸማሉ፤ ለሃይማኖታቸው በእሰር ቤት ይማቅቃሉ። የሰማይ ቤቱ ዋጋ በጻማው መጠን እንደሆነ ይታመንበታል። ጻማ "የድካም ፍሬ" ማለትም ይሆናል። "ጻማችንን ቀሙን" ማለት ደክመን በላባችን ያገኘነውን ወሰዱብን" ማለት ነው።

ጽድቅ፤ የ"ጽድቅ" ትርጉሙ "እውነት" ነው። "የጽድቅ ሥራ" ሲባል ግን መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሚሠራ እግዚአብሔር የሚወደው በጎ ሥራ ማለት ነው፤ በአማርኛ ተለምዷል፤ "ጽድቅና ኮነኔ ቢኖርም ባይኖርም÷ ክክፉት ደግነት ሳይሻል አይቀርም" ይላል ደራሲ።

ፈላሲ፤ መነኮሴን ግዕዙ ፈላሲ ይለዋል። ዓለምን ለቅቆ የሄደ ማለት ነው። "መነኮሴ" ከግሪክ ቋንቋ የተወሰደ ቃል ነው።

እነዚህ አንዳሉ የተውኳቸው ቃላት ሁሉ ያማርኛ ቃላት ሆነው ቢቀሩ ምኞቴ ነው። በሊቃውንቱ ዘንድማ ሁልጊዜም ናቸው።

ደብረ ብርሃን

መቅድሜን ሳረቅ÷ የደብረ ብርሃንን "የስያሜውን ታሪክ ቀጥሎ የማቀርበውን መግቢያ አደመድምበታለሁ" የሚል ቃል ገብቼ ነበረ። ቃሌን ከዚህ በታች ባለው ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ታሪክና ከታተመው ተአምረ ማርያም ውስጥ ያገኘሁትን በአማርኛ ተርጉሜ በማቅረብ ልጠብቅ፤

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለእግዝእትነ ማርያምና ለልጇ መስቀል አንሰግድም የሚሉ ደቂቀ እስጢፋ ተነሡ። ስለዚህ ንጉሡ (ዘርአ ያዕቆብ) ከፊቱ አቁሟቸው የሚሉትን ጠየቃቸው። ከራሱ ሊቃውንት ጋራ ሆኖ ተከራክሮ ረታቸው፤ አስፈረደባቸውም። ግን (ቢረቱም) ክፋታቸውን አልተዉም። ስለዚህ ንጉሡ ሕዝበ ክርስቲያኑን ሁሉ ሰብስቦ እንዲፈርዱባቸው አዘዘ።[47]

በዚያ ወራት አባ ማቴዎስ የሚባለው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት መልእክተኞች በኢትዮጵያ ነበሩ።[48] እነዚህም መልእክተኞች ፫ት ነበሩ። እንዱ ሹመቱ ከቅስና ማዕርግ የሚበልጥ ቆሞስ ሆኖ የተመረጠ፥ ጸሎትና ጾምን የሚወድ፥ የሐዲስና የብሉይን መጻሕፍት ዐዋቂ ሽማግሌ መነኮሴ ነበር። ፪ተኛው መጻሕፍት ዐዋቂ፥ በምንኵስና ያለ፥ የተመረጠ ሽማግሌ ዲያቆን ነበር። ፫ተኛውም ዲያቆን ነበር። የመጡት ለኢትዮጵያ ንጉሥ ለዘርአ ያዕቆብ የምሥራች ሊነግሩት ከሊቀ ጳጳሳቱ (ከአባ ማቴዎስ) እና ከግብጽ ሡልጣን[49] ዘንድ ተልከው ነበር፤ ምክንያቱም የግብጽ ሡልጣን የግብጽ ክርስቲያኖች የተዘረፉባቸውንና የፈረሱባቸውን ቤተ ክርስቲያኖቻቸውን መልሰው እንዲሠሩ፥ ያረጁትንም እንዲያድሱ ፈቅዶላቸው ነበር።[50] ሊመጡ ለንጉሡ ስጦታ ከሊቀ ጳጳሳቱ ዘንድ ፫ት ታቦቶች፥ ሕፃን ልጇን ይዛ ወደ ደብረ ቊስቋም እንደሄደች አድርገው በወርቅ የሠሩትን የእመቤታችንን ሥዕል፥ በወርቅ የተሠራ የወልደ እግዚአብሔር የስቅለቱን ሥዕል፥ በወርቅ የተሠራ የሊቀ መላእክት የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል፥ ብዙ የሜሮን ዘይትም አመጡለት።

---

47. Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, pp. 69-70.

48. አባ ማቴዎስ (ዳግማዊ) የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት በ1453-1465 ዓ. እ. ነው።

49. የዚያን ጊዜው የግብጽ ሡልጣን ጀቅማቅ ነበር፤ የገዛው በ1438-1453 ዓ. እ. ነው። Taddesse Tamrat, *Church and State*, pp. 261-264.

50. ታሪኩ ከቅድስት ማርያም ተአምር አንዱ ነው፤ ዝርዝሩን *ተአምረ ማርያም*፥ ገጽ 73-79 እና ከላይ በጎዳግ ቊ. 49 ከተሰጠው ከታደሰ ታምራት መጽሐፍ ውስጥ ማንበብ ይቻላል። የሆነው ባጭሩ እንዲህ ነው፤ ላይላይ ግብጽ ክርስቲያኖቹ ሰንደፋ ከሚባል ቦታ ደብረ ምጥማቅ (ዴር አል-መግጠስ) በምትባል የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በያመቱ ግንቦት ማርያምን አምስት ቀን ሙሉ በታላቅ ክብር ሲያከብሩ እመቤታችን ትታይ ስለነበረና፥ ምናልባትም ከሠራችው ተአምራት አንዱ እስላሞቹን ስላስቆጣቸው ሊሆን ይችላል፥ በሡልጣን በርስበይ ትእዛዝ ቤተ ክርስቲያኗን አፈረሷት። ሡልጣኑን "አሽራፍ ንጉሠ ምስር" እንለዋለን፤ አል-መሊክ አል-አሽራፍ ሰይፉ አድ-ዲን በርስበይ (1422-1438 ዓ. እ.) ማለታችን ነው። የዘመኑ ሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስ (1428-1452 ዓ. እ.) በክርስቲያኖቹ ላይ የደረሰባቸውን በደል ለአፄ ዘርአ ያዕቆብ ላኩበት። ዘርአ ያዕቆብ ለሡልጣኑ፥ "እዚህ (ኢትዮጵያ) ያሉትን እስላሞች ማንም አይነካቸውም። ሌላው ቀርቶ እንደ ሌላው ሕዝብ ግብር

(ንጉሡ) እነዚያን የሊቀ ጳጳሳቱን መልክተኞች ግብጻውያን÷ "ለመቤታችን ለማርያምና ለልጅዋ መስቀል እንሰግድም" በሚሉት ላይ እንዲፈርዱ አዘዛቸው:: የሊቀ ጳጳሳቱ መልእክተኞች እነዚህን ክሓዲዎች መረመሯቸው:: ካህናቱ÷ መዘምራኑ÷ ንቡረ እዶቹ÷ ሠራዊቱ ሁሉ በተሰበሰቡበት÷ "ክርስቲያን ሆናችሁ ሳለ ለበጀ መንገድ ድንግል እመቤታችን ማርያምና ለልጅዋ መስቀል ለምን አትሰግዱም? በጀ መንገድ ድንግል እመቤታችን የእምላክ እናት እንደሆነች አታውቁምን? ለልጅዋ መስቀልስ ለምን አትሰግዱም? ክርስቶስ በሱ ላይ እንደተሰቀለና በመስቀሉም እንደዳንን አታውቁምን?" ሲሉ ጠየቋቸው::

ከሓዲዎቹ÷ "እኛ ለማርያምና ለልጅዋ መስቀል እንሰግድም" አሉ:: በድንጋይ እንዲወገሩ ፈረዱባቸው:: የፊረንጅ÷ የቍስጥንጥንያ÷ የሶርያም[51] ሰዎችም ከዚያ ስለነበሩ በክሓዲዎቹ ላይ በድንጋይ እንዲወገሩ ፈረዱባቸው:: የክርስቲያኖቹ ጉባኤም÷ "በድንጋይ ሊወገሩ ይገባል" አለ:: ፍርድ ተፈርዶ ሲያልቅ ንጉሡ ከሓዲዎቹ በድንጋይ እንዲወገሩ አዘዘ:: (ወታደሮቹ) የክርስቲያኖቹ ጉባኤ እንዳዘዛቸው የተፈረደውን ፈጸሙ:: በየካቲት ፪ቀን በዕለተ ዓርብ ወገሯቸው::

እነዚህን ከአይሁድ ጋራ እንድ የሚሆኑ ከሓዲዎች በወገሯቸው በ፴፯ ቀን እግዚአብሔር ስለ እናቱ በጀ መንገድ ድንግል እመቤታችንና ስለ ክቡር መስቀሉ መጋቢት ፲ቀን÷ በክርስቶስ

እንኳን እናስገብራቸውም... እናንተ ግን የሃይማኖት ነፃነት ትገፍፋላችሁ" የሚሉ ቃላትና ሠልጣኑ የማይሰማ ከሆነም ለመበቀል እንደሚችል የሚያመለክት ጠንካራ ደብዳቤ ጻፈለት:: ለግብጻውያን ክርስቲያኖች ማጽናኛ ትሆን ዘንድም በፈረሰችው ቤተ ክርስቲያን ስም እዚህ ኢትዮጵያ እጉላ ላይ "ደብረ ምጥማቅ" የምትባል ቤተ ክርስቲያን ሠራ:: በዚያ ላይ÷ በዚያን ጊዜ የአደሉን ንጉሥ በድላይን ድባቅ መምታቱ በክርስቲያኑ ዓለም ሰለተሰማ ሠልጣን ጀቅማቅ ተደናግጦ ከሊቀ ጳጳሳቱ ጋራ ቶሎ ታረቀ:: መልእክተኞቹ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ያንን ብሥራት ለማድረስ ነው::

51. "የፊረንጅ÷ የቍስጥንጥንያ÷ የሶርያ" የሚለው "የሮማ የካቶሊኮች÷ የግሪክ አርቶዶክሶች÷ የሶርያ ተዋሕዶዎች" ማለቱ ነው:: "የፊረንጅ (ካቶሊኮች)÷ የቍስጥንጥንያ (የእስጥምቡል አርቶዶክስ ግሪኮች)÷ የሶርያም (ያዕቆባውያን ተዋሕዶ አርቶዶክስ) ሰዎችም" የሚላቸው ለሌላ ሌላ ጉዳይ የመጡና እንዳጋጣሚ እዚያ የተገኙ መሆን እለባቸው:: ሌላ ጊዜ ከሌሎች ሊቃውንት ጋራ ስለሌላ ጉዳይ ሲከራከር ሊቃውንቱ የሱን እምነት÷ "ይህን የሚያስተምሩ ከኢትዮጵያውያን በቀር በግብጻውያንም በሮማውያንም ዘንድ የሉም" ብለውበት ስለነበረ÷ እነዚህን የውጭና የሌላ ሃይማኖት እንግዶች የዘረዘራቸው÷ "ለቅድስት ማርያም ሥዕልና ለክቡር መስቀል የምንሰግድ እኛ ብቻ አይደለንም" ለማለት ይመስላል:: Getatchew Haile, "The Homily of *Aṣe* Zär'a Ya'əqob of Ethiopia in Honour of Saturday," *Orientalia Lovaiensia Periodica,* vol. 13 (1982), p. 210.

መስቀል በዓል ዕለት÷ ስኞ ሌሊት ድንቅ ተአምር ሠራ። በንጉሥ አደባባይ ላይና ከንጉሥ አደባባይ ሩቅ አስከሆነ ቀበሌ ድረስ ትልቅ ብርሃን ወጥቶ እንደ ጐርፍ ፈሰሰ። ያም ብርሃን በቤተ ክርስቲያኖች ላይ÷ በልብሳቸው÷ በውስጥ መጋረጃቸውና በውጭው በሐር መጋረጃ÷ በጥጥ መጋረጃም ላይ ተገለጠ። ዳግመኛም ያ ብርሃን በሰዎች ድንኳን ውስጥ÷ በመጋረጃቸው ላይ÷ በሚለብሱት ልብሳቸው ላይ÷ በሚታጠቁበት ትጥቃቸው ላይ÷ በአቃውም ሁሉ ላይ ሰፍኖ ታየ። በንጉሥ ሰፈር ታላቅ ደስታ ሆነ።

ያ ብርሃን እየታየ ብዙ ቀን ቆየ። የብርሃኑ መልክ የአሳት ነበልባል ይመስላል። ነገር ግን አያቃጥልም። ሰውንም ሲቀርበው ፊቱን ያበራዋል። ብርሃኑን ማየት ልብ ያስደስታል።[52]

ስለዚህ ያችን (ኢባ የምትባለዋን) ቦታ ሁሉም ወደዳት፤ (ንጉሡ) ደብረ ብርሃን ብሎ ጠራት።[53]

ንጉሡ የጥንት ስሟ ኢባ የነበረውን ቦታ ደብረ ብርሃን ቢሳትም ደቂቀ እስጢፋኖስ "ሀገረ ደም" ይሏታል።[54]

---

52. *ተአምረ ማርያም*÷ ገጽ 112-117።

53. Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb*, pp. 70-71. ብርሃን መታየቱን እስጢፋኖሳውያንም መዝግበውታል። ምክንያቱን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ አንጂ የእግዚአብሔር ምሕረት አይሉትም።

53. EMML 4, f.112a, እዚህም ገጽ 183።

የአባ እስጢፋኖስ ገድል

“የሀገራችን ትምህርት ያልሆነ ታስተምራለህ” ሲሉ በጥል ተነሡብኝ። የዚች ሀገር ትምህርት ምንድነው? እንዴትስ የሌላ ነው? በክርስቶስና በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ከሆነው ሁሉ በቀር ሌላ አላውቅም።

አባ እስጢፋኖስ



የንቅናቄው መሪ አቡነ አስጢፋኖስ
(ከደቂቀ አስጢፋኖስ መጽሐፍ÷ MS Spencer 7, f. 4b.)



መግቢያ

(5^{ህ}) በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ::

የብፁዕና የቅዱስ፡ የሃይማኖት ዓምድ፡ የክርስቲያን መብራት፡ (የሰማዕትነት) አክሊል የደፋ፡ ሩጫውን በሀገረ ጎትር በድብ ፀር[1] ዘመን ድል በሚሰጥ ብርታት የፈጸመ፡ የአባ አስጢፋኖስ ገድልና ሰማዕትነት (እነሆ)። የሰማዕትነት አክሊል መድፋትን የፈጸመው[2] በእግዚአብሔር ሰላም በታኅሣሥ ፲፰ ቀን ነው:: ጸሎቱና በረከቱ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ይሁኑ፡ አሜን::

ትውልድና እድገት

ይህ ሰው (5^{ሀ}) ከአክሱም ቤተ ክርስቲያን[3] ወደ ምሥራቅ የአራት ቀን መንገድ ርቀት ላይ ካለ ሀገር ከስቡሐ ሰዎች ወገን ነበረ:: የቤተሰቡ የትውልድ ሀገር ግፍሜላ፡ የአባቱ ርስት መርዋ፡ የአባቱ ስም ብርሃነ መስቀል፡ የእናቱ ስም ሳራ ነበር:: በዘራቸው ክርስቲያኖች ነበሩ:: (ገና) በእናቱ ማኅፀን ሳለ አባቱ ሞተ:: ሲወለድ ስሙን ኀድገ አንበሳ አሉት:: እናቱ ከሕፃንነት አሳደገችው::

በአባቱ ወንድም ቤት ዝቀላይ በሚሏት አገር ለዘመዶቹ በሚገባው ሁሉ እየታዘዘ በሰላማዊነት የማይጨቃጨቅ ሆኖ ጐለመሰ:: ወንድሞቹና ባልደረቦቹ ሲበድሉት (በደሉን) በትዕግሥት ያልፋታል አንጂ (6^{ህ}) በማከፋፋት ወደሚረዱት (ሰዎች) አያመጣም ነበረ:: አንደ ትንሾች ለጨዋታና ለረብሻ አይጓጓም ነበረ:: ማንንም ስለአየበትና ስለሰማበት ነገር ከዘመዶቹ ዘንድ አያሳጣም ነበረ፡ ከባልደረቦቹ የተለየ ሆኖ፡ ኑሮው በመ-ልካምና በጸጥታ ነበረ::

---

1. ድብ ፀር ("ጅብ ጠላት") የሚሉት አፄ ዘርአ ያዕቆብን ነው:: አጠራሩ "አንበሳ በፀር" ከሚለው ከአፄ ናኦድ (1488-1500) ስም ጋራ ስለሚመሳሰል ጎድሉ የተጻፈው ንጉሡ ይህ ሰም ከወጣለት በኋላ እንደሆነ ይገመታል::
2. "ሩጫውን ፈጸመ" የሚለው አነጋገር ከ2ጢሞ 4: 7 የተወሰደ ይመስላል::
3. "አክሱም ቤተ ክርስቲያን" ያልኩት ግዕዙ "ገበዘ አክሱም" ያለውን ነው:: በጥንት ጊዜ የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ስሟ "ገበዘ አክሱም" (የአክሱም ጠባቂ) ይባል ነበረ:: አንድ የግዛት ዘመኑ በትክክል ያልታወቀ ንጉሥም ስሟን የንግሥ (የሹመት) ስሙ አድርጎ "አለ ገበዝ" ተብሎ ተጠርቶበታል:: Getatchew Haile, "The Homily of Abba Eläyas, Bishop of Aksum, on Mäṭṭa'," *AB*, Vol. 108 (1990), pp. 29-47.

ቀጥሎ የበጎች እረኛ ሆነ። በጎቹን በሚጠብቅበት ዱር ሳለ ሙሴ በደብረ ሲና በጎቹን ሲጠብቅ የተሰጠችው ጸጋ ታገኘው ዘንድ ተመኘ። ይህች (የምኞት) ሙቀት በልቡ ውስጥ ጋለች÷ (ሲመኝም÷ ምኞቱን) እስኪደርስባት ድረስ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ለማየት÷ ሕይወት ሰጪ ቃሉን ለመስማትና በሕጉ እንዲያገለግለው የሚያስችል መሠረት በመጣል እንጂ በሚያልፍ ሐሳብ (ብቻ ላይ ሆኖ) አልነበረም።

(6[ሰ]) ይህቺ ንቃት ከተዛመደችው በኋላ አስተማሪ እንዲፈልግ ጥበብ መንገዱን አመለከተችው። ቤተ ኢየሱስ ወደሚሏት መካን[4] ሄዶ እዚያ መዝሙረ ዳዊትን መማር ጀመረ[5]። ወንድሞቹ በሰሙ ጊዜ የሃይማኖት ሰው ለመሆን በመፈለጉ በጣም ተቆጡ። ምክንያቱም እነሱ በጦርና በቀስት መዋጋትና በጓደኞቻቸውም ዘንድ ርስት ለማግኘት ተዘጋጅተው ስለነበረ÷ እሱንም እንደፍላጎታቸው እንዲሆን ፈልገው ነበረ። በቁጣ እንዲህ ሲሉ ገላመጡት÷ "ካልተውክ እንገድልሃለን።" እሺ አላላቸውም። ማባበል ሲያቅታቸው ተዉት። ያቺ መካን ለምድራቸው ጎረቤት ናት።

ትምህርቱ ላይ (7[ሀ]) በጉጉት ተጠመደ። እንድ ቃል ሲነግሩት ትርጉሚን ይጠይቃቸዋል። እነሱም በሚያደርገው መንፈሳዊ ምርምር ምክንያት ያደንቁታል። (እያያዙ) እንደሚማሩ ትናንሽ ልጆች ሳይሆን÷ በርምጃው÷ በመልስ አሰጣጡ÷ በጭምታው (ሁሉ)÷ ፍጹሞች እንደሆኑት ነበረ። የዚያች ቦታ ካህናት የሥራውን ውበት አይተው ስሙን እስጢፋኖስ አሉት። ይህቺ ከቤተ ክርስቲያን መንፈስ የሆነች÷ ከቀዳሜ ሰማዕት ጋራ ሞግሼ ያደረገችው ስያሜው የሰማዕትነት ቅድስት ሩጫውን የሱ ተጋሪ እንድታደርግልን ነው።[6]

የሕግ ትምህርቱን[7] ለአገልግሎት ከሚያስፈልገው (ደረጃ) ሲያደርስ ዲቁና እንዲሾመው ከጳጳሱ ዘንድ ወሰዱት።

---

4. እንደ ቤተ ክርስቲያንና እንደ ገዳም ያሉ ቀዋሚ ሕዝባዊ ቦታዎች በግዕዝ "መካን" ("ካ" ሳይጠብቅ) ይባላሉ፤ "center" እንደማለት ነው።

5. እባ እዚህ ትምህርታቸውን የጀመሩት ዳዊት በመማር ከሆነ÷ ክዚያ በፊት ያሉትን የትምህርት ደረጃዎች ከሌላ ትምህርት ቤት ቢያልፉ ነው። ወይም ዳዊት መማር ማለት ተማሪ መሆንንና ወደ ካህንነት መሸጋገርን ያመለክት ኖሯል።

6. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ "ቀዳሜ ሰማዕት" ("የመጀመሪያው ሰማዕት") የሚባለው ቅዱስ እስጢፋኖስ ነው። የመጀመሪያው ሊቀ ዲያቆንም ይባላል። በዲቁና ሐዋርያትንና የመጀመሪያዎቹን ምእመናን በሚያገለግልበት ጊዜ እይሁድ በድንጋይ ወግረው ገድለውታል፤ በዚህም የመጀመሪያው ሰማዕት ተብሏል። የሐዋ ሥራ 6: 1-8: 2።

7. "የሕግ ትምህርት" የሚባለው የሃይማኖት÷ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው። ሃይማኖትን ሲያመለክት የእይሁድ ሕግ÷ የክርስትና ሕግ÷ የእስላም ሕግ ሲል ይገኛል። የሃይማኖት መጻሕፍት መፋረጃ ስለነበሩ የሕግ መጻሕፍት ይባሉ ነበር።

መንፈሳዊ ጥሪ

(7ሀ) ከጳጳሱ ግቢ እንዳለ፥ ከዚህ በፊት የኖረውንና የወደፊቱንም ሕይወቱን እንዲገመግም፥ እንዴትስ እንደ እነማ እግዚአብሔርን በማገልገል እንደሚኖር ሐሳቦቹን ሁሉ እንዲያመዛዝን መንፈስ ቅዱስ አነቃው። ቀጥሎ ዓለምን በውስጧ እስካለው (ሁሉ) ትቶ ጌታን መከተልና ለሕይወት ሰጪ ትእዛዙቹ መጠመድ የሆነችው የቅዱሳን ሐዋርያት የሥራቸው ውበት ከፊቱ ቦግ አለች። ከዚህ በኋላ ወደ እግዚአብሔር በጋለ ዕንባ እንዲህ ሲል ጸለየ፥

> "አቤቱ ጌታዬ፥ ከትንሽነቴ ጀምሮ አንተን ፈልጌያለሁ። በእናቴ ማኅፀንም ባንተ ጠንክሬያለሁ። (8ሀ) ሁል ጊዜ ትዝታዬ አንተ ነህ።"[8] የምኞቴን ፍላጎት ከዘመዶቼ የፍላጎት ሐሳብ ለይተኸዋል። ሕግህንም የፈለግሁት ፈቃድህን ለማወቅና አንተ እያስተካከልክልኝ በፈቃድህ ለመኖር ነው እንጂ፥ ለዚህ ዓለም ትርፍ፥ ወይም በሰዎች ዘንድ ለመመስገን አይደለም። አሁንም እቤቱ ማረኝ፥ "መሐሪና ይቅር ባይ ነህና።"[9] የልጅነቴንና የሞኝነቴን ኃጢአቴን ሁሉ አታስታውስብኝ። እንደ ይቅር ባይነትህ አስታውሰኝ። መልካም ቀምበርህን በማነቅ እንዳነግብ፥ ቀላል ሸክምህንም እንድሸከም በፍላጎትህ ግቢ ውስጥም አስቀምጠኝ። ሕይወቴም ፈቃድህን ለማገልገል ትዳረግ። እነሆ ከባሪ ጀምሮ (8ሀ) ራሴን ላንተ ሰጥቻለሁ። "አንተ በቃልህ አጠንክረኝ። የዐመፃ መንገድን ሁሉም ከኔ አርቅ። በሕግህም ማረኝ።"[10] "እቤቱ ልመናዬ ካንተ ፊት ትድረስ፥ እንደ ቃልህም አስረዳኝ።"[11] ራስን በመስጫቸው ማኅተም ከቅዱሳን ደቀመዝሙሮችህ ደምረኝ። ካንተ ጋራ የገባሁትን ኪዳኔን እንድጠብቅ፥ ትልሜም ፈለግህን እንዳይስት የእርዳታህን ጎይል አስታጥቀኝ። ራሴን (ላንተ) የሰጠሁትንም እንደ ፍላጎትህ እንዲሆን አድርግ። "ስብሐት ሁል ጊዜ ለዘላለም ያንተ ነውና፤"[12] አሜን።

ዘመዶቹ አደራ የሰጡት አንድ ካህን መነኮሴ አብሮት ነበረ። እሱ ዘንድ ሄዶ ነፍስ ካወቀ ጀምሮ እስከዚች ቀን በግብርም (9ሀ) በቃልም ያዳለጠውን ሁሉ ተናዘዘ። ነፍሱን በመንፈሳዊ አጥበት አጠዳ። ሙሽራውን መቀበያ የሚሆን ድንግልናን ከልብ በሆነ ትጋት ለመጠበቅ ተዘጋጀ።[13] በዚያን ጊዜ እድሜው ፲፰ ዓመት ሆኖት ነበረ። "ከ፳ ዓመት (ዕድሜ) ጀምሮ የሚጐበኝ ለእግዚአብሔር ቍርባኑን አንድ ተኩል የብር ዲድርክም ያግባ"[14]

---

8. መዝ 70: 5-6።
9. ይኸ ጥቅስ ከመዝ 55: 5 እና ከሌላ ብዙ ቦታም አለ።
10. መዝ 118: 28-29።
11. መዝ 118: 170።
12. የእቡነ ዘበሰማያት መጨረሻ፥ ማቴ 6: 13።
13. ማቴ 25: 1-12 ውስጥ እንዳለው ምሳሌ ሙሽራውን ተግተው ይጠብቁ ከነበሩት ደናግል ጋራ ማያያዙ ነው።
14. ዘፀ 30: 13-14።

እንደምትል የአሪት ትእዛዝም ይህ ብፁዕ ያለውን አውጥቶ ብሩን ከቤተ ክርስቲያኑ በር በተቀመጠችው የመፈተኛ መንፈሳዊት ጉሮሮ ጨመረው።[15] በመንፈስ ቅዱስ እሳት አጥድቶ ለሊቀ ካህናቱ ሰጠ። ተቀብሎ (9^ሰ) ለክብር ከሚገባ (ስፍራ) አስቀመጠው።

በዚያን ዘመን አባ በርተሎሜዎስ[16] በገርጌሳ ግቢው ሳለ ዲቁና ሰጠውና ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ዘመዶቹ በመመለሱና የፈለገውን በማግኘቱ ተደሰቱ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያ መነኮሴ ያባቱን ወንድም አስፈቅዶ ይዞት በትራ ወደሚሏት ደብር ሄዱ። እዚያ ሲደርሱ ብፁዑ ለመነኮሴው (እንዲህ) አለው፤ "አባ፥ ወደ ደብረ አባ ሳሙኤል ሂጀ ከመነኮሴዎቹ ጋራ በሰላምታ ለመገናኘት አፈልጋለሁ። ወደዚያ የሚሄድ ጓደኛ አግኝቻለሁ።" (መነኮሴው፥) "ደኅና ነው፤ ግን ወደ ሀገራችን እንድንሄድ (10^ሀ) ቶሎ ተመለስ" አለው። በመልስ ጊዜ (እዚያው) እንዳይተወው ወደዚያ የሚሄደውን ሰው አደራ አለው።

ወደዚያች ስሟን ሓንባር ጎድባ ወደሚሏት ደብር ሄደ። የአበምኔቷ ስም ሳሙኤል[17] ነው። በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው፤ ንጉሦችም ያከብሩታል። እጅ ነሣው፤ የዚያችን ደብር ሽማግሌዎችን ሁሉም እጅ ነሣቸው። ከዚያ፥ ብፁዑ በልቡ ያለውን ሁሉ--መነኮሴ ለመሆን መፈለጉን--ለአበምኔቱ ገለጸለት። አበምኔቱም፥ "ፍላጎትህ መልካም ነው፤ ለእሷ (እንድትበቃ) እግዚአብሔር ይርዳህ" አለው። እዚያው አደረ።

ከዚያ፥ ያ (አብሮት የመጣው) ሰው፥ "ና እንሂድ" አለው። ብፁዑ፥ (10^ሰ) "እኔ ወደዚያ መመለስ አልፈልግም" ብሎ አምቢ አለው። ሰውየው (ብቻውን) ተመልሶ (ብፁዑ) መመለስ እምቢ እንዳለና እዚያው እንደቀረ (ለመነኮሴው) ነገረው።

መነኮሴው ተነሥቶ ወደዚያ ሄደ። ሲያገኘው (እንዲህ) አለው፤ "ምነው እንደዚህ አደረግኸኝ? (እንዴት) ከእጄ ትጠፋለህ? አሁንም ና ከአባቶችህ ልመልስህ። ከዚያ በኋላ የፈለግኸውን አድርግ። አሁን ግን እንደዚሁ ብትቀር አንተን ከእኔ ይፈልጋሉ። (ታዲያ) ምን እላቸዋለሁ?

---

15. ምንጩ ዘካ 11፡ 13 ነው፤ ግን ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ሲሰጥ ገንዘቡ እንዲጸዳ መጀመሪያ ከቤተ ክርስቲያኑ በራፍ ላይ የሚጨመርበት በጉሮሮ ምሳሌ የሚታይ ጉድጓድ ወይም ጎድጓዳ አቃ ያለ ይመስላል። ምናልባትም ልጆች ዲቁና፥ ዐዋቆች ቅስና ሲቀበሉ ለጻጻሱ የሚሰጡት ክፍያ ሊሆንም ይችላል።

16. አባ በርተሎሜዎስ የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው የመጡት በ1391 ዓ. ም. ነው፤ በአፄ ይሥሐቅ ዘመንም ነበሩ፤ Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del Negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 261/51, Louvain 1965, p. 131. ይሥሐቅ የነገሡው በ1406-1421 ዓ. ም. ነው።

17. አባ ሳሙኤል ዘቆየዋ እውነትም ገድል የተደረሰላቸው የታወቁ አበምኔት ነበሩ፤ Kinefe-Rigb Zelleke, "Bibliography of the Ethiopic Hagiographical Traditions," *JES*, vol. 13, no. 2 (1975), p. 89 (entry no. 134).

አሁንም ሐዘን አታምጣብኝ፤ የዘመዶችህን ቁጣ ታውቃለህ::" በእንደዚህ ያለ አነጋገር አስጨነቀው:: የደብሩ ሰዎችም ከአበምኔቱ ጋራ ሁነው መነኮሴውን ረዱት (11ᵇ)፤ ምክንያቱም በፊት ያውቁታል:: ምርር ብሎ እያለቀሰ እሺ አላቸው:: ብፁዑ መነኮሴውን፥ "ይቺን ነፍሴ የምትፈልጋትን ሐሳቤን ለዘመዶቼ እንዳትናገር በል ማልልኝ" አለው:: ማለለት::

ከዚህ በኋላ፥ ወደ ሀገራቸው ሄዱና እዚያ ሲደርሱ መነኮሴው ለአባቱ ወንድምና ለዘመዶቹ እንዲህ[18] አያለ አሰረከበው፤ "እነሆ ልጃችሁ መጥቶላችኋል፤ ግን ካሁን ጀምሮ ልቡ እናንተ ከምትፈልጉት ሩቅ ነው::" (ይኸንን) ስምተው ብፁዑን እንደ አስረኛ ጠበቁት:: የቅዱሱ አባት ወንድም በዚያች አገርና በዘመዶቹ የትውልድ አገር በግፍሜላ ሳይ ሹም (11ᵃ) ነበረ:: ገንዘብ በመስጠትና የአባቱን ርስት በማካፈል ይደልለው ጀመር:: ወንድሞቹም ልቦናውን ከላይ ከነፃነቱ ጠፈር እነሱ ወዳሉበት ለብልሹ ዓለም ወደ መገዛት ባርነት ሊያወርዷት ፈልገው፥ በማግባትና (ልጅ) በመውለድ የሚገኘውን የዓለምን ቃና በፊቱ ያጣፍጡለት ነበረ:: ጓደኞቹ የሚመስሉም የሰይጣን መልእክቶች እንዲህ ሲሉ ይነግሩት ነበረ፤ "እኛ ከወንድሞቻችን ሚስቶችና ከሌሎችም ጋራ በመተኛት ተድላ እናደርጋለን:: እንዴት ነው አንተ ከወንድሞችህ ሚሰቶች ዘንድ የማትሄደው? ከባልደረቦችህ ጋራም በሣቅ (12ᵇ) የማትጫወተው? አንዴትስ ሕይወትህን እንደ ሞኝ ታደርጋለህ?"

እሱ ግን በዚህ የኃጢአት ማጥ በሆነ ጉዳያቸው ሁሉ ሳይታወክ በጸጥታ ይኖር ነበረ:: የዝሙት ደም የሚደርቅበትን የጌታን የልብስ ዘርፍ በመዳሰስ ኃይል ያገኝ ነበረ::[19] በእግሩ ፈለግ ሽቶም ራሱን ያውድ ነበረ::[20] ያቺን ዓመት በዱለታቸው ሳይተባበር ከነሱ ጋራ አሳለፈ:: ብቻ (የመንፈሳዊ) ጦር መሣሪያውን ታጥቆ የወይኑን አትክልተ ቦታ ከጠላት ጥቃት ሁሉ እየጠበቀ ኖረ::[21]

ዓለምን ስንብት

ከዚህ በኋላ ተነሥቶ እናቱ ወዳለችበት ሄደ፤ (12ᵃ) የምትኖረው እሱ ካለበት ርቃ ነበረ:: ቅዱሱን ሕፃንነቱን ካሳለፈችለት በኋላ ሌላ ሰው አግብታት ነበረ:: እሷ ዘንድ ሄዶ በሰላም ሲሰናበታት፥ እናቱ ወደ ዱር ቦታ ዞር አድርጋ

18. በዚህ ገድል ውስጥ "እንደዚህ" ብዬ የምተረጉመው የግዕዝ ቃል የለም፥ ግን "እንደዚህ" ወይም "እንዲህ" የሚለውን ቃል ካልጨመርኩበት አማርኛው እያምርም:: ቃሉ የሚያስፈልግበት ቦታ ብዙ ስለሆነ ሁልጊዜ በቅንፍ ማስቀመጡ ደግሞ ላይን ያታክታል:: ስለዚህ ካሁን በኋላ ያለቅንፍ እስገባዋለሁ::

19. ዓሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም ይፈሳት የነበረች ሴት የጌታን ልብስ ስትነካ ደሟ ቆሞላታል፤ ያንን ታሪክ መጥቀሱ ነው፤ ማቴ 9: 20-22፤ ማር 5: 25-29::

20. ይኸም የጌታን እግር እጥባ በጠጉሯ አድርቃ ሽቱ የቀባችውን ሴት ታሪክ የሚጠቅስ ይመስላል፤ ሉቃ 7: 35-38::

21. የሙነልይ 1: 6 ጥቅስ ያለበት ይመስላል::

እንዲህ አለችው፤ "ልጄ፥ ማኅፀኔንና ያሳደጉህን ጡቶቼን በማስታወስ ሐሳብህን ንገረኝ፤ ይኸ ከወንድሞችህና ከባልደረቦችህ ተለይቶ ብቸኛ መሆን ምንድ ነው? የእርምጃህ ትርጉሙስ ምንድነው? እንግዴህ ለሞት እስከሚያደርስ ጥልቅ በሆነ ሐዘን ላይ አትጣለኝ። በልብህ ውስጥ ያለውን በመንገር ማረኝ።"

.. ቅዱሱ እንዲህ አላት፤ "በሆድሽ እንዳለሁ አባቴ እንደሞተ ታውቂያለሽ። (13[ሀ]) አንቺም በልጅነቴ ጣልሽኝ። እግዚአብሔር ብቻውን አባትም እናትም ሆነኝ። እና ልጅ ሁሉ ለወላጁ ይገዛል። እንደዚሁ እኔም ራሴን ላሳደገኝ አስገዝቻለሁ። አንቺ ግን ልብሽን አረጋጊ። ከዛሬ ጀምሮ ፊቴን በሥጋ አታይውም። ሆኖም መድረሻሽን እንዲያሳምርልሽ ራስሽን ለእግዚአብሔር ስጪ።"

የነገሩን መጨረሻ ስትሰማ፥ እናቶች በሞተ ልጃቸው ላይ እንደሚያለቅሱ ምርር አድርጋ አለቀሰች። ለቅሶዋን አውጥታ እንዲህ ሰትል በሰላም ሸኘችው፤ "የጠራህ እግዚአብሔር እሱ እረኛ ይሁንህ።"

ከዚህ በኋላ፥ (13[ለ]) ከዓለም ጋራ ሰንሰለት ከሆነው ከሥጋ ዝምድና ሁሉ ነፃ ሆኖ ሄደ። ጌታን በመከተል ተረከዙን[22] እያጸዳ በሩጫ እየተጣደፈ ሄደ። በፊት ከጉበኛት ደብርም ደረሰ። የዚች ደብር ርቀት ከቅዱሱ ሀገር የአምስት ቀን መንገድ ነው። ዘመዶቹ ቅዱሱ ሲጠፋባቸው በእግር ተከተሉትና እዚያች ደብር ደረሱ። እሱ ግን ከፊታቸው ተደበቀ። በፍለጋ (በከንቱ) ደከሙ። የሚያደርጉት ሲያጡ ወደ አገራቸው ተመለሱ።

ብፁዑ በዚያች ደብር በቅዱስ ምግባር፥ ማለት በምንኩሰና፥ (14[ሀ]) እምላክን እንደ መላእክት በማመስገንና ልግም የሌለበትን ጻማ[23] በማፍቀር ኖረ። በሽተኞች እየጐበኘ፥ ሽማግሌችን እያጽናና በረከት ያገኝበት ነበረ። ለማንኛውም ለሚሠራው ሥራ ሁሉ (ከበላይ) ፈቃድ ያሰቀድምለት ነበረ። የገዳሙ ሰዎች በጠባዩ ውበት ይደነቁ ነበረ፡ ምክርና ተግሣጽ እንደሚፈልጉ እንደ አዲሶች ሳይሆን እንዲያውም ምግባሩ እነሱኑ መልሶ ይመክራቸው ነበረ። (ኑሮው) በዘመናቸው እንደሚያዩት ሳይሆን ምግባራቸው እንደተተረፈረፈው በመጻሕፍት ውስጥ እንዳሉት (ጻድቃን) ነበረ እንጂ።

ምንኩሰና ለጻማ መጠመድ

ከጥቂት ጊዜ፥ በኋላ አባ ሳሙኤል እንደ መላእክት ለመኖር ራሰን የመስጠት (14[ለ]) ማኅተም የሆነችውን ቅድስት አስኬማ[24] ሰጠው። ይህችም የአባቶቻችን

22. ግዕዙ እዚህ ላይ ግልጽ አይደለም፤ ቀጂ ያሳሳተው ይመስላል።

23. "ጻማ" በእማርኛ "ድካም" ማለት ነው። ግን ሁል ጊዜ ድካም ብሎ ከመተርጐም ቃሉን እንዳንዴ በቁሙም መጠበቁ የተሻለ መስለኝ፤ በገዳማውያን ዘንድ በእማርኛ ንግግር ውስጥ የተለመደ ቃል ሆኗል፤ መግቢያውን ተመልከት። መነኮሳት የምድር መላእክት የሰማይ ሰዎች ይባላሉ።

24. አንድ ሰው ለመመንኮስ ከገዳም ሲገባ መጀመሪያ ሳያመነኵሱ ለተወሰነ ጊዜ (ሶስት ዓመት) እንዲያገለግል ያዙታል፤ የፈተና ጊዜ ነው። ፈተናውን ካለፈ "ሥርዓተ

የሐዋርያትና የተከታዮቻቸው የመነኮሳት አባቶች የእንጦንስና የመቃርዮስ[25] ሥርዓት ናት። በዚያን ጊዜ ዕድሜው ፲፱ ዓመት ነበረ። የክርስቶስን ቀምበር ካንገቱ ላይ በማነቆ በማንገብ ለእማኒዎች ተድላ፥ ለተጠራጣሪዎች ክብደት የሆነችውን ቀላል ሸክሙን ተሸከመ።[26]

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ ዓለማውያን የሚወዱት ቅባት ያለበት ነገር ሁሉ በሥጋው ምኵራብ ውስጥ አላስገባም። ሥጋም፥ ቅቤም አልበላም። ጠጅም፥ ጠላም፥ ሕጉርም[27] ወይም ማንኛውንም የሚያሰክር መጠጥ አልጠጣም። ነፍሱን በእንጀራና በውሐ (ብቻ) አቆያት። ያውም ቢሆን የጌታውን ምስጋና (15[ሀ]) ለማላረግ (ያህል) ነበረ። እግሮቹን ለማላመርም ሆነ ለማሳረፍ አልታጠበም።

ማንኛውንም የሚታይ ነገር ላይቀር ከማግኘት ራሱን አደኸየ።[28] የሚተኛበት ምንጣፍ፥ (ምናምን) የሚከትበት ኮረጆ፥ (ውሐ) የሚጠጣበት ኩባያ፥ ለእግሩ ጫማ፥ ለእጁ በትር አልነበረውም። (እንድ ብቻ እንጂ) ለመቀያየሪያ የሚሆኑ ሁለት ልብስ አልነበረውም። ሕይወቱን በቅድስና መርከብ ውስጥ፥ ማለት በመንግሥተ ወንጌል፥ ጣላት፤ ልቡ ሁል ጊዜ ከእሷ ዘንድ እንዲሆን እሷንም መዝገቡ አደረጋት።[29] ሀብቱ ሰውነቱን የሚሸፍንበት የበፊ ቆዳ (ብቻ) ነበረ። የሚተኛበት ሳርም ከማደሪያው (15[ሰ]) ውስጥ ጐዘጕዘ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ (የቍርባን) ምሥጢር ለመቀበል (ባዶ እጁን) የሚዘረጋ ሆኖ ነው እንጂ፥ ከማደሪያው ውስጥ የሚተወው ወይም የሚወስደው አልነበረውም። ኑሮው እንዲህ (በቀላሉ) ነበረ።

አሲረ ምንኩስና ቅዱስ" የሚባል መጽሐፍ አሳቸው፤ በሱ በሥርዓት ያመነኵሱታል። ሥርዓቱም አንዲህ ነው፤ መጀመሪያ በፈቃዱ ከዓለም መለየቱን፥ ከዚያም የምንኩስና ኑሮው ምን ዓይነት አንደሚሆን የሚያስረዳ ጽሑፍ ያነብለታል። በአግዚአብሔርና በስው ፊት ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲስማማ ከፈታቸው ያጋድሙትና የጠጉር ልጪት፥ ቀጥሎ ለምንኩስናው በሚሆነው ልብሱ፥ በስውየውም ላይ አንደሞተ ስው "ጸሎተ ፍትሐት" ይጸልያሉ። ከዚያ በኋላ መጀመሪያ መምህሩ (የገዳሙ አበምኔት) ቀጥሎ በፍትሐቱ የተካፈለው ሁሉ ይባርከውና ያለብሱታል። የመጨረሻው ጸሎት ተጸልዮለት የምንኩስናውን ሕይወት ይጀምራል። አንደ ሕጉ ቢሆን ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደግሞ "አስኬማ" የሚባል ልዩ ልብስ ይስጠውና ወደ ከፍተኛው ደረጃ ይሸጋገራል። አስኬማ ከነት የሚሠራ 12 የመስቀል ምልክት ያለበት ቆዳ ነው። አንደ ሕጉ ቢሆን ከአስኬማ በኋላ መነኵሴ ከገዳም አይወጣም። የመጀመሪያውን አስኬማ ለመጀመሪያው መነኵሴ ለአባ እንጦንስ/አንጦንዮስ የሰጠው መልአኩ ስለሆነ ልብሱ "አስኬማ መላአክት" ("የመላአክት ልብስ") ይባላል። መነኮሳቱም የምድር ላይ መላአክት ይባላሉ። አሁን ግን ራሱን የመነኮሳቱን ልብስ "አስኬማ" ይሉታል።

25. አንጦንስ/አንጦንዮስና መቃርስ/መቃርዮስ ግብጻውያን የምንኩስና አባቶች ናቸው።
26. 2 ቆሮ 6: 14፥ ማቴ 11: 30።
27. "ሕጉር" አንደ ጠሳና አንደ ጠጅ የሚያሰክር የመጠጥ ዓይነት ነው።
28. 2 ቆሮ 8: 9።
29. ማቴ 6: 21።

ለሥራ ሲያዝዙትም ከርሻ ላይ ለመዋልም ሆነ ወይም (እዚያው) እቤት (በገዳሙ) ውስጥ ለመሥራት በመታዘዙ እየተደሰተ ይሠራል። (ትእዛዙ) የማይሆንለት አስቸጋሪ ሲሆንም በተሰሩ ይሄድና የችሎታውን ያህል ይሠራል እንጂ እይጨቃጨቅም። በእርሻ ላይም ሆነ ወይም በቤት ውስጥ ሆነው የሚያገለግሉ ከመጋቢዎቻቸው[30] ረዳት ሲጠይቁ እሱን ይሰጧቸዋል። ይኸም ባለማፈግፈግ ታዛዥነቱን (እያዩ) እንጂ በሰውነቱ (16^{0}) ጥንካሬ ምክንያት አይደለም።

(እብሯቸው ከሚሠራው) ጋራም ሆነ ወይም ከማንም ጋራ ስለዚህ ዓለም ጥቅም፥ ስለ ልብስም ሆነ ወይም ስለ መብልና መጠጥ አያወራም። ማንንም በማዳላት አያመሰግንም፤ ማንንም በክፋት አያማም። ብቻ ሁልጊዜ በጸሎት ላይ ይሆናል። ሥራውን ሲጨርስ በማደሪያው ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በብቸኝነት ይቀመጣል። ማታ የስብሰባ ምልክት ሲደውሉ ምግቡን ለመቀበል ወደ ማኅበራቸው ይሄዳል። እነሱ ግን የማኅበራቸውን ምግብ የማይበቃ ያደርጋሉ፤ አንዳንድ ጊዜ አንድ አንጀራ፥[31] (16^{0}) እለዚያም ግማሽ አንጀራ ይሰጣሉ። ንፍሮ[32] በሚቀቅሉበት ጊዜ (የሁለት አጅ) እፍኝ ወይም አንድ እጅ ሙሉ አፍኝ ይሰጣሉ። የራሳቸውን ምግብ ግን በየማደሪያቸው እንደፈለጉ ያዘጋጃሉ። ይህ ቅዱስ ግን እዚያው ተኩልኩሎ የሰጡትን አንደ ቍርባን እንድ ጊዜ ይቀበላል። ብዙም ቢያገኝ ወይም ትንሽ አግዚአብሔርን ያመሰግናል። ስላሳነሱት አያጉረመርምም፤ ከሚያማም ጋራ አብሮ አያማም። በዝምታ ወደ ማደሪያው ይመለስና የሥጋውን ፍላጎት እንዳይከታተል ሐሳቦቹን ይዘጋቸዋል።

የማደሪያው ሰዎች ግን ግብር አበራቸው (17^{0}) ባለመሆኑ አደሙበት።[33] በቁጣም ዘለፉት። ነፍሱን ሊበጠብጧት ፈልገው፥ "(ሁኔታው ሁሉ) የሰይጣን ነገር ነው" እስከማለት ደረሱ። እሱ ግን ምንም ነገር አይመልስላቸውም። (ብቻ እንዲህ) ይላል፤ "ዝም አልኩ፤ ራሴንም ዝቅ አደረኩ።"[34]

ቅዱሱ ቀጥሎ ከአንድ ጻማ ከሰበሰ የዋህ ሽማግሌ ዘንድ ሄደና እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ "እባ፥ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ንገረኝ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደማያቸው ሰዎች መንገድ ነው ወይስ የቤተ

---

30. "መጋቢ" የገዳም ሥራ አስኪያጅ፥ በአበምኔቱ ስም ሥራ አከፋፋይና ተቆጣጣሪ ሹም ነው።

31. "እንጀራ" ብዬ የተረጐምኩት "ኅብስት" የሚለውን የግዕዝ ቃል ነው። ግን ማንኛውም የተጋገረ ምግብ ሁሉ ኅብስት ስለሚባል በገዳማቸው የሚበሉት ኅብስት የሚሉት ምኑን እንደሆነ ትክክሉ ከጽሑፉ አይታወቅም፤ "ዳቦ"፥ ወይም "ዳቤ"፥ ወይም "አምባሻ"፥ ወይም "ሪሚጥ" ወይም "እንጀራ" ሊሆን ይችላል፤ እንደየቀበሌው ባህልና እንደየገዳሙ ሥርዓት ነው።

32. ንፍሮ ለማለት ደራሲው የተጠቀመው በትግርኛ ቃል በ "ጥቅጥቆ" ነው።

33. መዝ 2: 1።

34. መዝ 38: 2-3 (ጥቅሶቹ) አብዛኛውን ጊዜ የሚሄዱት ከግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ ጋራ መሆኑን እናስታውስ። በልዩ ልዩ ምክንያት የግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ቦታ ላይ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ይለያል።

ክርስቲያን መጻሕፍት አንደሚሉት?" ሽማግሌው (አንዲህ) አለው፤ "የምታያቸው ስዎች መታገሥ አቅቷቸው ሁሉም አንደየጠባዩ ሄዷል። እግዚአብሔር ግን በመጻሕፍት ውስጥ አንዳለው ቃሉ (17ᴬ) ነው። አንደዚሁም÷ (የእግዚአብሔር) ፈቃድ የተሸነፈውን ይቀጣዋል÷ ያሸነፈውን ይክስዋል።"

በዚህ (መልስ) ቅዱሱ ደስ አለው። ሁል ጊዜ አዘውትሮ አንዲህ አያለ ይጸልይ ጀመር፤ "አቤቱ ፈቃድህ ካልሆነች ከከንቱ ጻማ አድነኝ።" ነፍሱን በአምላክ መጻሕፍት ምስክራ በቆመችው በጌታ ሥምሪት አሠማራት። ከስው ጠባይ የሚድንበትን (የመጻሕፍቱን) ውሳኔዎቻቸውንም መጠበቅ ያዘ[35]። ቅዱሱ ለሚሠራው ሁሉ (አስቀድሞ) አበምኔቱን ይጠይቅና ፈቃድ ይወስዳል። አበምኔቱም ቅዱሱን በጠባዩ ውበት ምክንያት "የልጅ ሽማግሌ" ይለው ነበረ።

ቅዱሱ ግን (18ᵇ) ሥጋው ሁሉ አስኪሟሽሽ ድረስ ያለማቋረጥ በመዘመር በሌሊት ትጋት ነፍሱን ያሰጨንቃታል። አጋንንት ደግሞ በአንዳንድ ሐሳቦች (አንዲህ) ሲሉ ይጨቀጭቁታል፤ "ጥረትህን ለማሟላት ከፈለግህ የታመምክ መስለህ ምግብ ትተህ ተኛ፤ ስዎችም ትሕርምትህን[36] አያውቁብህም።" አሱ ግን ሕጉን ልብ በማለት÷ "ይኸ የአበው መንገድ ስላይደለ እምቢ" አላቸው። በዚህ ሳይችሉት ጊዜ÷ አንዲህ አያሉት ሌላ (ፈተና) አመጡበት፤ "ጥረትህን ከመጨረሻ ታደርስ ዘንድ ና ወደ ምድረ በዳ ውጣ፤ ምክንያቱም እኛ እዚህ ከስው ማህል ስላለህ በግላጭ ልንታገልህ አንችልም። አዚያ ግን (18ᴬ) ፊት ለፊት እንተያያለን።" በዚህም አንዲህ ሲል አሸነፋቸው፤ "ይኸም በመንፈስ ቅዱስ ምክር÷ አስዚያም በቅዱስ መልአክ ምክር÷ አለዚያም በመምህር ቃል ነው እንጂ÷ በኔ ምክር የሚሆን አይደለም። ከዚህ ውጪ አልታዘዘልኝም።"[37] አንደዚህ (ሲላቸው) ተሸነፉ፤ በመጡበት (መንገድ) ሁሉ በ(መንፈሳዊ) ጦር መማሪያ ተዘጋጅቶ ያገኙታል።

ከዚህ በኋላ÷ አንደዚህ ያለ ራእይ በቅዱሱ ፊት ሆነ፤ ሁለመናዋ ነጭ÷ አግሮቿ ቀይ የሆነች ወፍ አንድ ድመት ሊገድላት ፈልጎ ያስጨንቃታል። ቅዱሱ ወፏን ረዳት፤ ድንጋይ አንሥቶ ድመቱን መታው። ወዲያው ወድቆ ሞተ፤ ወፏ አድፍጦ ከሚይዛት ዳነች። (19ᵇ) ከዚህ በኋላ ትርጓሙን መንፈስ ቅዱስ አመለከተው፤ ወፏ የቅዱሱ ነፍስ÷ ድመቱ ሥጋው÷ ሊገድላት ማስጨነቁ ሥጋ ከነፍስ ጋራ የሚያደርገው ጦርነት ነው። ቅዱሱ ድንጋይ አንሥቶ የመታው ቅድስት ሥርዓትና ሥርዓቷን በተግባር ሳይ ማዋል÷

---

35. Fundamentalist የሚባሉት እንደሚያደርጉት መጽሐፉ የሚለውን ቃል በቃል መጠበቅና እንደትእዛዞቹ መሄድ ጀመሩ ማለቱ ነው።

36. "ትሕርምት" በዝምታ ራስን ማጉሳቆል ነው። በእንግሊዝኛ asceticism ይባላል።

37. እባ አስጢፋኖስ በጻማው ሊገፉበት ስለፈለጉና ስለወሰኑ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሲያስቡ እነዚህ ሐሳቦች ይመጡባቸዋል። ንግግራቸው ከራሳቸው ጋራ ነው። ሆኖም÷ ሐሳቦቹን ስላልወደዷቸው ስይጣን እንዳቀበላቸው እድርገው አይተዋቸዋል።

መግደሉ ደግሞ ሥጋን ማንበርከኩ ሲሆን፥ የወፏ እግር ቀይነት በስግዕትነት መንገድ መሄዱ ነው።

ከዚህ በኋላ፥ ቅዱሱ ነፍሱን በማስጨነቅና ሥጋውን በማንበርከክ በየቀኑ ኃይል እየጨመረ ሄደ። ከላይ ድረስ እየወጣ ጫፉን እስኪይዝ ድረስ (በገድል ላይ) ገድል ይጨምር ነበረ። ከዚያ፥ (19ᴬ) የሚፈልገውን (የእምላክን) ቃሉን እስኪሰማ፥ ፊቱን እስኪያይ ድረስ ለዓይኖቹ ሽለብታ፥ ለቅንድቦቹ እንቅልፍ[38] እስኪነሣ ድረስ እንግዳ ነገር ከሆነ ትጋት ራሱን አስገባ። በጎኑ ከመሬት ላይ ሳይተኛ፥ ግድግዳ ሳይደገፍ፥ መጠጊያ ከሌለበት ቆሞ፥ በትር (መቋሚያ) ሳይዝ፥ አየር ላይ እንደምትንሳፈፍ ወፍ ሆኖ እንቅልፉ እስኪጠፋ ድረስ ያለድጋፍ ቆመ። እንዳችም (ሥጋዊ) ፍላጎት የሌለበት ሆነ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድም እንደ ልማዱ ቀጥ ብሎ ይቆማል።

የአካላቱ ገጥታ ሁሉ ተለወጠ፤ አጥንቱ ደረቀ፤ ሥጋውም ሟሸሸ። (20ᵇ) እንደ ዓሣ ቅርፊት ነጭ ሆነ። የሰውነቱ አባላት ሁሉ ሟሙ--ጠረኑ እንደተጠበሰ (ሥጋ) እስኪሸት ድረስ።

ሰዉ ግን የሥጋውን አባላት እንዴት እንደሚያደርጋቸው፥ የሚደርስበትንም የአጋንንት ሥቃይ አያውቅም። ብቻ ቀን ቀን የቻለውን ያህል ወዲያ ወዲህ ሲል ያዩታል። ግን እንዲህ ሲሉ ይገረማሉ፤ "በምን ምክንያት እንዲህ ሆነ?" አንዳንዶቹ ችጋር ላይ መሆኑን ስለሚያውቁ፥ "በእህል እጦት ነው" ይላሉ። ምክንያቱም እንዳንድ ጊዜ (የሚበላ) ያገኛል፤ አንዳንድ ጊዜ ያጣል። ሊጠይቁት ግን አልደፈሩም፤ ምክንያቱም አካሄዱ የሚያስፈራ ነበረ፤ ስለ ነፍስ ጥቅም ብቻ ካልሆነ እንዲያውም አያወራም። አንዳንዶች እንዲህ ሲሉ ይተቻሉ፤ (20ᴬ) "ድብቅ ገድል ላይ ስለሆነ ነው።"

በቅዱሱም እንዲህ ሲሉ ይመራመሩበታል፤ "አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ብሎ ራሱን ቢገድል ጽድቅ ይሆንለታልን?" ግማሾቹ ደግሞ እንዲህ ይላሉ፤ "ራሱን ቢገድል እንዴት ጽድቅ ይሆንለታል?" ቅዱሱ ግን መልስ አይሰጣቸውም። ብቻ ነፍሱን እንዲህ እያለ ይመክራታል፤ "ጌታ ነፍሱን ያገኛት ይጣላት፤ ነፍሱን ስለኔ የጣለ ያገኛታል[39] ብሏል።" ደግሞስ "እግዚአብሔርን ማን ጠርቶት ዝም አለው? ማንንስ የተከተልውን ጣለ?"[40] ይላታል።

ብዙዎች ደግሞ (ፈተናውን) ማለፍ ይችል ወይም ያፈገፍግ እንደሁ ለማወቅ ያስተውሉት ነበረ። ምክንያቱም (21ᵇ) በዚያች ደብር ውስጥ በራሳቸው ምክር ሥጋቸውን ከጸማ ያስገቡ አሉ። ስለዚህ መርከባቸው ከወደብ አልደረሰችም፤ በመርከበኞቹ አለቃ አልተቀዘፉምና በመመስገን ማጥ ዓለም ተይዛለች። እሱንም እንደነሱ ይሆን እንደሁ (ለማየት) ይጠባበቁ ነበረ፤ መሠረቱ በጌታው ቃል ላይ እንደተጣለ ልብ አላሉም።

---

38. መዝ 131፡ 4።
39. ማቴ 10፡ 39፤ ሉቃ 17፡ 33፤ ዮሐ 12፡ 25።
40. ሲራ 2፡ 11-12 እይ።

ቅዱሱ ግን የጌታን ሕማማት በብዛት በመቀበል የሚገኝ ደስታን ሲፈልግ ወዳልደረሰበት ወደ ፊቱ ይጣደፋል እንጂ የሚፈጽማትን ጻማ (ክብደት) አያስባትም። ከመጓጓት ብዛት ሁል ጊዜ ወደ ጌታ እንዲህ እያለ ይጸልይ ነበረ፤ "እቤቱ የሕመሞችህ ተካፋይ መሆንን ዳርገኝ። (21ᴬ) ለቅዱሳን ደቀ መዛሙርትህ ያካፈልካቸው ሕማማትና ችግር በኔ ላይ ይድረሱ። ድካሜን ከነሱ (ድካም) አታሳንስብኝ። ከነሱ ጋራ የምሕረትህ ስጦታ ተካፋይ አድርገኝ።" የሥጋው ኃይል እስኪያልቅና መሄድ እስኪያቅተው ድረስ በእንደዚህ ያለ ጥረት ነፍሱን ያስጨንቃት ነበረ። ከቤተ ክርስቲያን ድረስ የሚሄደው በጭንቅ ሆነ።

እስተማሪነትና ጻማ

ቅዱሱ በዚህ ሁኔታ እንዳለ የዚያ ገዳም መነኮሳት እርሻ ለመጠበቅ እዚያው እንዲኖሩ ወደ እርሻው ቦታ ወጡ፤ ምክንያቱም የአዝመራ ጊዜ ነበረ። (እዚያ በሚሆኑበት ጊዜ) መዝሙረ ዳዊት የሚያስተምራቸው አስተማሪ እንዲሰጣቸው አበምኔቱን ጠየቁት።[41] "እስጢፋኖስን ውሰዱ፤ እሱ (22ᵁ) ያስተምራችኋል" አላቸው። ወሰዱት፤ (አቅም ስለሌለው) በድካምና በችግር እዚያ አደረሱት። ከነሱ ራቅ ብሎ ከወሬያቸው ድምፅ ጸጥ ካለ ቦታ መኖሪያ ሠሩለት። (ቦታው) የብርድ መፍሰሻ ነበረ። ቅዱሱ እዚያ ከአጋንንት ስቃይ በሚመጣ በብዙ ገድል ኖረ። የሚማሩት ብርዱን ከብዛቱ የተነሣ መታገስ አልቻሉም። ቅዱሱን፥ "መኖሪያህን ከሌላ ቦታ እንለውጥልህ" ቢሉት፥ "መታገሥ ይሻላል" አላቸው።

ከዚህ በኋላ፥ እንደ ልማዳቸው ሲማሩ አንድ ትልቅ የሚያስፈራና ጥጥታው የሚያስገርም ዘንዶ መጣ። ሊገድሉት ተነሡ፤ ግን አልቻሉትም። (22ᴬ) እያዩት ከቅዱሱ መኖሪያ ገባ። "ቤቱን እሳት እንልቀቅበት" አሉት። ቅዱሱ ሲከለክላቸው ጊዜ፥ "እኛ ስለምንፈራ እዚህ መምጣት አንችልም" አሉት። ቅዱሱ፥ "ትክክል የሚመስላችሁን አድርጉ፤ እኔ ግን መኖሪያዬን አልተውም" አላቸው።

ከዚያች ቀን ጀምሮ፥ ምግቡን ሊሰጡት ከአንድ ጊዜ ብቻ በቀር ለመማር መምጣት አቆሙ። ቅዱሱ የዘንዶውን መምጣት ሰይጣን በማስፈራት ሊበጠብጠው አስቦ ያደረገው እንደሆነ ዐወቀ። ቅዱሱ የጌታን ኃይል ታጥቆ ወደ መኖሪያው ገባ። ዘንዶው ግድግዳውን እንደሚያነቃንቅ ሆነ፤ ወዲያና ወዲህ ይሄድ ጀመረ። በራሱ ላይ እንደሚጠቀለልም (23ᵁ) ሆነ። ቅዱሱ ግን ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ በክርስቶስ መስቀል አማተበበት። ዘንዶው ተሸንፎ ወጣ። ከዚያች ዕለት በኋላ ቅዱሱ ሞቶ አገኘው፤ ሥጋውን ወፎች በሉት።

ሰይጣን ግን እንደገና በአሸነፈባቸው ላይ የሚመካባትን በተሸነፈባቸው ዘንድ የሚያፍርባትን ፈተናውን ለማካሄድ ወዳጆቹን ውሾቹን

41. መነኮሳቱ ገና ዳዊት ተማሪዎች ከሆኑ ወይ ገና ልጆች ነበሩ ወይም ሲመነኮሱ መሃይምናን ጎረምሶች ነበሩ።

ጠራ። በተፈጥሮ እንደ አንበሶች፥ ነብሮች፥ ጅቦች፥ አባቦች አስፈሪ አውሬዎች ሁሉ እየተመለሱ፥ ሁሉም የየራሳቸውን ማስፈራሪያ መሣሪያቸውን እያሳዩ ለመግደል ተዘጋጅተው ከበቡት፤[42] (አንዳንዱ) (23ሰ) ለመቦጨቅ ይጮሃል፤ አንዳንዱ ለመቧጠጥ ጥፍሮቹን ያንጨበርራል፤ አንዳንዶቹ ለመዋጥ አፋቸውን ይከፍታሉ፤ አንዳንዱ ለመውጋት የቀንዶቹን ኃይል ያሳያል፤ አንዳንዱ እንደሚናከስ ይሆናል። ቅዱሱ ግን ያላንዳች መታወክ ወደ ላይኛው ጌታ እየጸለየ ከሱ እርዳታ ይፈልግ ነበረ። ሆኖም፥ ለነሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "የደካማነታችሁን ዱለት ምን ታበዛላችሁ? እኔን ለመንካት ከጌታ የተፈቀደላችሁ ከሆነ ከናንተ አንዱ በበቃ። አለዚያ ግን እነሆ ውርደታችሁን ነው የምታሳዩት።"

ሰይጣን ቀስቱ ሁሉ ረክሶበት ቅዱሱን ባለመንካቱ በጣም ተቈጣ። እንግዲህ በዚህ (24ሀ) ሲሸነፍ ከዚህ በሚከፋ፥ የውስጥ ሰውነቱን በማሠቃየት፥ ደከመ። ሁለመናውን እንደ እሳት አቃጠለው፤ እንደ ምላጭ አባላቱን ከተፈው፥ እንደ ትል በላው፥ አጥንቱን ሁሉ ቈረጠመው። አነሆ በኢዮብ ላይ እንደሆነው ለማድረግ ፈቃድ እማኝቶ የተፈጥሮውን አባላት ሁሉ በማሠቃየት ስሮቹን መጠጣቸው። ነፍሱ ግን በአንድ (ልጁ) መስቀል ተጋርዳ በደኅና ትኖር ነበር፤ በመስቀል እንጨት ላይ የሆነውን ሕማማቱን ታስታውስ ነበረ።

ከጻማው ክብደት የተነሣ ከመሬት ላይ ወደቀ፤ መናገር አልቻለም፤ መዘመርም አቃተው። ግን ልቡ ባለመቆሙ ችሎታ ካለው (ከላይኛው ጌታ) ዘንድ እርዳታ (24ሰ) ፍለጋ፥ "አቤቱ አድነኝ፥ አቤቱ ማረኝ፥ ክርስቶስ አርዳኝ" እያለ ከንፈሮቹን ያንቀሳቅሳል። ከደረሰበት የጣር ክብደት የተነሣ ከዚህ ሌላ በመለማት ልብ የሚባል፥ ወይም ለማየት የሚስተዋል (ሁኔታ) አልነበረበትም።

ብቃት

ሰይጣን እስከተፈቀደለት ድረስ ማሠቃየቱን ሲፈጽም፥ ጌታ ባርያውን ለመርዳት ከመቅደሱ ጎበኘው። በዚህ ጊዜ ጠላት በባለቤቱ መምጣት ምክንያት ከታየው ውጋጋን ሸሸ። የሸሸቱ ድምፅ ከወደቀ በክት ላይ እንደሚነሡ የብዙ ዝምቦች ትንሣኤ ሆነ። አቅመ ቢስ ሆኖ በቅዱሱ (አምላክ) ፊት ተዘረጋ፤ በጎብኚው የግርማ ወላፈን ተከበበ። በዚያች ጊዜ (25ሀ) ቅዱሱ፥ "የሚወደኝ ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጽለታለሁ"[43] የሚል የጌታን ቃል ሰማ። በዚህ በወንጌሉ ቃል (ጌታ) ፊቱን ለቅዱሱ በመግለጽ ታወቀው። በዚያች ቅጽበት ዳሰሰውና አዳነው። አጥንቱን ሁሉ በደስታ ልምላሜ አለመለመው፤ ከዚያ፥ ጌታ የቅዱሱን እጅ ይዞ ጎይል ሰጠው። ያንን ያሠቃየውን ጠላት እንዲይዘው አደረገው። እሱ እጁን በጌታ እጅ እንደተያዘ እሱ ደግሞ ጠላቱን ይዞ እንደደረቀ ቅጠል

42. እነዚህ አራዊትና እንስሳት ሁሉ እጋንንት ናቸው፤ መዝ 21: 17፤ 22: 16።
43. ዮሐ 14: 21።

ቃው። በዚያን ጊዜ ደግሞ የብዙ ነገደ መላእክትን ድምፅ እንደዚህ ሲሉ ሰማ፤ (25ᴬ) "እውሬውን ያሸነፍከው፥ እንኳን፥ እንኳን።"

ያ ጠላት ትንሽ ራቅ ብሎ ለቅዱሱ እንዲህ አለው፤ "ያሸነፍከኝ ይመስልሃልን?" ቅዱሱ፥ "የእምላኬ ኃይል አሸነፈህ እንጂ፥ ያሸነፍኩህስ እኔ አይደለሁም፥" አለው። ስይጣንም፥ "በማታውቀው (መንገድ) እንደገና እመጣብሃለሁ" አለው። ቅዱሱም፥ "በዚያን ጊዜም እንዳሁኑ እሱ ጌታ እንደገና ያሸንፍሃል" አለው። ባሠቃየው ፈንታ ተሠቃይቶ ወዲያው ከፊቱ ጠፋ፤ ጌታ ባርያውን ረድቶት፥ ለነፍሱ ፈርዶለታልና።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ ቅዱሱ ከሁሉም የመጀመሪያዋ በሆነችው በመንፈሳዊ ቅንዣኤ[44] ውስጥ ሆኖ ቅድስት ድንግል ማርያምንም እስኪያያትና (26ᵁ) ቃሏን እስኪሰማ ድረስ[45] የተመሰገነች ሰማያዊት ምሥጢር በራእይ የሚያይ ሆነ። የዚህ የብልሹ ዓለም ሥራ ሁሉ ከሱ ተወግዶለትና ርቆለት፥ እንደዚህ ከብዙዎች ተጋበጦች ውስጥ ጥቂቶቹ[46] ከሆኑት ፍጹሞች ጋራ በፍጹም ተረድቶ በማወቅ፥ በማስተዋል፥ በመቅመስ፥ በማሽተት በምስጢሮቿ ደስታ ተመላለሰ። ነፍሱን በጸንጠቆስጤ ጊዜ ለቅዱሳን ሐዋርያት እንደሆነው፥[47] የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመጐናጸፍ ብርቱ ሆና አገኛት። ያቺን ዓመት ወአምላካዊ ምሥጢር ራእይ እየተደነቀ አሳለፋት።

ከዚያ፥ (26ᴬ) ከደረሰበት ድንቅ[48] በፊት እንዳስለመደው፥ ቍርባን ሊቀበል ቅዳሜ ዕለት ወደ ገዳም ወጣ[49]። እዚያ ከቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ የሚኖሩ ሽማግሌዎች ነበሩ፤ ንብረት ከማከማቸት የራቁ ድኾች ሆነው፥ በጸሎት የተጠመዱ (ጻድቃን) ነበሩ። ቅዱሱ ሲመጣ ሲያዩ ሊቀበሉት በፍጥነት ሮጡና፥ "ዓለምን ያሸነፍክ፥ እንኳን፥ እንኳን" አሉት። ቅዱሱ፥ "በምን ምክንያት እንዲህ ትላላችሁ?" አላቸው። "ስላንተ፥ ዓለምን ያሸነፍክ፥

---

44. ደራሲው "መንፈሳዊ ትንሣኤ" የሚለው መነኮሳት ጸማ፥ ትሕርምት በማብዛት የሚያገኙት ብቃት ነው። እንድ መነኮሴ ወይም ማንኛውም ሕይወቱን መንፈሳዊ እድርጎ የሚኖር ምእመን ሲበቃ የሰማይ ቤቱ ሁሉ ምሥጢር ይገለጽለታል፤ እምላክ ሊፈጽመው ያሰበው ወይም በማንኛውም ሰው ላይ ሊደርስ የሚችለው ሁሉ ይገለጽለታል። ብቁው ሰው ያየውን እያየ ሰዎችም አገርም ንሰሐ እንዲገቡና ከሚመጣባቸው መቅሠፍት እንዲድኑ ይመክራቸዋል፥ ያስጠነቅቃቸዋል፥ ይገሥፃቸዋልም። ሰዎችም ችግር ሲገጥማቸው እሱ ዘንድ ሄደው ምክር ይጠይቃሉ፤ እንዲጸልይላቸውም ይለምኑታል፤ ተጽናንተው ይመለሳሉ።

45. እባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ይከሰቡበት የነበረው እንዱና ዋናው ቅድስት ማርያምን እያከብሩም እየተባሉ ነበረ።

46. ማቴ 22፡ 14።

47. የሐ ሥራ 2።

48. ደራሲው "ድንቅ" የሚለው እባ እስጢፋኖስ ወደ ብቃት ሲሸጋገሩ የደረሰባቸውን ድንቅ ነገር ነው።

49. እጻጻፉ እባ እስጢፋኖስ ቍርባን የሚቀበሉት ቅዳሜ ቅዳሜ ብቻ ያሰመሰላል፤ የሚያሳየው ግን ከድንቁ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ለቍርባን ወደ ገዳሙ የሄዱት እንዳጋጣሚ ቅዳሜ ቀን መሆኑን ይመሰለኛል።

እንኳን፥ እንኳን የሚል የብዙ መላእክት ጩኸት ከሰማያት ስለሰማን እኛም እንደነሱ አልን" አሉት። (27^{ህ}) ቅዱሱ ገሰጻቸውና፥ "ይኸንን ለማንም አትናገሩ"[50] አላቸው። በገጥታው ውበት የተነሣ የተደነቁም ብዙዎች ናቸው፤ ምክንያቱም በልቡ ኑዛዜ መልኩ ተመስግኗልና።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ ሰብል ሰብሰባ ሲያልቅ ወደ ማደሪያው ተመለሰ፤ ምግቡን እዚያው ያቀብሉት ነበረ። ሥራውም መጻሕፍት መቅዳት ሆነ። ቅዱሳት መጻሕፍትን፥ ነቢያትንና ወንጌሎቹን፥ (የሚሉትን) እየተረዳ ቀዳ። ቅዱሱ እንደዚህ ከባሕር ሞገዶች ተገን ይዞ ኖረ። የመንፈስ ቅዱስ ምስጢርን ለማገልገል የሚሆነውን (27^{ሀ}) የጌታው መዝገብ ከሆኑት ከሐዲስና ከብሉይ እያወጣ ተረድቶ[51]፥ ሁሉንም ምንም ሳይሰወረው በመንፈስ ቅዱስ መስተዋት እያየ፥ ቅዱሳን ከሚቆሙበት ከባሕር ወደብ[52] ተጠግቶ ቆመ። አንድ ድምፅ ስም እየጠራ፥ "እነሆ እገሌ በጠላት ጦር በመፈተን ላይ ነውና በል በቶሎ እርዳው" ሲለው የሚሰማበት ጊዜ ነበረ።

ቅናትና ግጭት

ከዚያ በኋላ፥ ከዚያች ደብርና ከሌላም ቦታ ብዙዎች ከሰይጣን ባርነት ነፃ የሚወጡበትን፥ ለነፍሳቸው (መፈወሻ) መድኃኒት የሚሆን እየፈለጉ ወደሱ ዘንድ ይመጡ ጀመረ። ከእሱ ተምረው የትሕርምቱን ተግባር ይከተሏት ጀመሩ።

በዚህ ጊዜ፥ የደብሩ ሰዎች ቀኑበትና አበምኔቱ ዘንድ ቅዱሱን እንዲህ ሲሉ ከሰሱት፤ "እነሆ (28^{ህ}) የደብሩ ልማድ ባልሆነ በራሱ ምክር ይሄዳል። ደግሞም እነሆ ሌሎችን ወደ ብቸኛነት ትሕርምቱ ይስባቸዋል።"

አበምኔቱም ነገራቸውን ተቀብሎ እሱም ከዱሊታቸው ተጨመረ። አበምኔቱ ቅዱሱን እንዲህ አለው፤ "አንተ ለምንድነው በቃልህም በሥራህም ከደብሩ ልማድ የምትለየው? ሌሎቹ የሚጠሉብህን ለምን አትተውም?" ቅዱሱ፥ "ይቺን ፍርድ የሰጠኸው በሕግ ምስክራ ነው ወይስ ለነሱ አነጋገር በማዳላት? በእውነት ፍርድ ከሆነ የኔን እነጋገርና የነሱን እነጋገር መርምር። በነሱ እነጋገር ብቻ የምትፈርድ ከሆነ ግን እነሆ ግፌ ካንተም ጭምር ነው።"

(28^{ሀ}) ቅዱሱ እንደዚህ ሲለው አበምኔቱ በጣም ተቆጣ። ቅዱሱን፥ "እነሆ፥ አጋንንት አድረውብሃል፤ ነገርህ ከሰይጣን ኃይል የመጣ ነው" አለው።

ቅዱሱ ስድቡን ሰምቶ ለእግዚአብሔር ሶስት ጊዜ ሰገደ። አበምኔቱ ቅዱሱን በተጨማሪም እንዲህ አለው፤ "ካሁን ጀምሮ በወንድሞች ማኅበር

---

50. ማቴ 16፡ 20።

51. አባ አስጢፋኖስ የቤተ ክርስቲያን ትምህርታቸውን ያገኙት ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መሆኑን ለማሳየት የገባ አጻጻፍ ነው።

52. ወደ ብቃት ዓለም መሸጋገሪያው የሚመስለው በመርከብ ጉዞ ነው።

ስብሰባ እንጂ (ተለይተህ) በማደሪያህ አትቀመጥ::" ቅዱሱ እሺ አለው:: ከዚያ፥ ቅዱሱ ወደ ማኅበራቸው እየሄደ ለአስኬማው ትሕርምት የሚገባውን ምግቡን እንድ ጊዜ (ብቻ) ይቀበል ጀመር:: በዚህ ሁኔታ ግማሽ ዓመት አሳለፈ:: ከዚያ፥ አበምኔቱ ቁጣው ሲበርድለት ቅዱሱን ወደ ቤቱ (29^{ህ}) ሰደደው::

ቅዱሱ የግፉን ትእዛዝ ፈጽሞ ከአንድ ወንድም ጋራ ወደ እንዲት ኮረብታ ሄደ:: እዚያ በብቸኝነት ኖረ:: ከዚያ፥ ለቅዱሱ አንድ ራእይ ታየው፤ ትልቅ ባሕር በፊቱ ተንጣልሏል:: ብዙ መነኮሳት ባሕሩን ሲያዩ እንደ አንበጣ ከንፋቸውን እየዘረጉ ተወረወሩበት:: ግን ዋኝቶ መውጣት አቃታቸው፤ ተበሳሹ:: ደግሞ አንዲት ወፍ ከቅዱሱ የእጁ ትንሿ ጣቱ ላይ ታስራለች:: እሷም አባሕሩ ውስጥ እንደሰጠሙት ለመወርወር በኃይል ሞከረች:: ግን ማሰሪያው ገታት:: ዞር ብሳ የቅዱሱን እጅ (29^{ሰ}) እስክማቀሰል ድረስ ቧጨረችው:: በዚያን ጊዜ ለቀቃት፤ ከባሕሩ ተወረወረች::

ይህ ነገር ከሆነ በኋላ፥ ያ ከቅዱሱ ጋራ የነበረው ወንድም በፊት መደነበረበት ሊመለስ ተነሣ:: ቅዱሱ፥ "ይኸ ሐሳብህ ከጠላት የመጣ ነውና ታገሥ" አለው:: ከዚያ፥ ይህ ወንድም በነገሩም በሥራውም ከፋበት፤ ሄዶ በቅዱሱ ላይ ከዶለቱት ጋራ ተደመረ::

ከዚያች ደብር ደጋጎቹ ሰዎች ብዙዎቹ ቅዱሱን በሄደበት ሁሉ ሊከተሉት እየፈለጉ ያጽናኑት ነበረ:: ከዚያ፥ የደብሩ ሰዎች ቅዱሱን (30^{ህ}) ከቀድሞ መኖሪያው ሊመልሱት ከአበምኔቱ ጋራ እንዲህ ሲሉ መከሩ፤ "እዚህ ካልተመለሰ ብዙዎች እሱን ሲፈልጉ እኛን ይተውናል::" ቅዱሱን እንዲመለስ ጠየቁት:: እሺ ብሎ ወደ ማደሪያው ተመለሰ::

ከጳጳሱ ከአባ በርተሎሜዎስ ዘንድ

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ ቅዱሱ በሃይማኖት ጉዳይ ለመወያየት ተነሥቶ ወደ ጳጳስ አባ በርተሎሜዎስ ዘንድ ሄደ:: ዓለት ከምትባለው ግቢው አገኘው:: ቅዱሱ ጳጳሱን እጅ ነሣውና አብሮት ጥቂት ጊዜ ቆየ:: ከዚያ፥ ጳጳሱ ቅዱሱን እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ "ለምን እዚህ መጣህ?" ቅዱሱ እንዲህ አለው፤ "አቋሜን እንድነግርህና በተጨማሪ ካንተም እንድረዳ ነው:: ምክንያቱም (30^{ሳ}) መጻሕፍት በሀገራችን በየቤተ ክርስቲያኑ ሞልተዋል:: ሁሉም እውነትን በማስተማር ከብሉይ እስከ ሐዲስ እየተባበሩ ሳሉ፥ በቃላቸው አፈራረድ የሚረዳ ይግባኝ የሚባልበት የፍርድ አደባባይ የለም፤ ሁሉም አቂሙ በፈቀደለት ይሄዳል:: አንተም ዜናዬን ሌሎች ሲያከፋፉት ስትሰማ በሌላ ነገር እንዳትደናቀፍ ብዬ ጠባዬን ላሳይህ ብዬ መጣሁ::" ጳጳሱ፥ "ደግ አደረግህ" አለው::

ከዚያ፥ ቅዱሱ ፈጣሪ በሥላሴ አካል ሳይቀነስለት ሳይጨመርበት እንደሚኖር፥ (31^{ህ}) ስለሰባተኛዋ ቀንም ከብሯ ከምኵራብ በፊት በፍጥረት መጀመሪያ ላይ በገነት ለነበሩ እንደታዘዘና እንደዚሁም በዓለም መታደስ

ምክንያት ገነት ስለተከፈተች[53] አሁንም ቅዱሳን ሐዋርያት (በዚያች ዕለት) እንድናርፍ እንደደነገጉ አምልኮቱን ለማሳየት ከነቢያት ራእይና ከሐዋርያት ትምህርት ምስክር እያመጣ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ አነጋገረው።[54]

ጳጳሱ የቅዱሱን የነገሩን መረዳት፥ የጠባዩን ውበት አይቶ እንዲህ አለው፤ "ልጄ፥ እነሆ መንፈስ ቅዱስ በላይህ አለ፤ ነገርህ ሁሉ ከጸጋው ስጦታ የመነጨ ነው። እንግዲህ ለሁሉም እንደዚህ አስተምር። እኔም ቃልህን እንዲቀበሉ ፈቃድ መስጠቴን ልጻፍልህ።"

ቅዱሱ ለጳጳሱ እንዲህ አለው፤ (31ᴬ) "አባቴ፥ ለማስተማር በየመካናቸው ብሄድ ለራሴ የሥጋ ክብር የምፈልግ እየመሰላቸው ብዙዎች በኔ ምክንያት ይሰናከላሉ።"

ጳጳሱ እንዲህ አለው፤ "ለዮሐንስ ወንጌላዊ አፍህን ትጥማታለች፥ ሆድህን ግን ትመራታለች[55] ያለውን አልሰማህምን? እንደዚሁ አንተም የሰውን ስድብ አትፍራ።"

ቅዱሱ፥ "አባቴ፥ እየዞርኩ እንዳስተምር አታስገድደኝ፥ ግን ወደኔ ለመጣ እናገራለሁ።" ጳጳሱም፥ "የእግዚአብሔር መንፈስ በላይህ ስላለ በል እንዳልከው አድርግ" አለው። ከዚያ በኋላ፥ የቅስና ሹመት ሰጠው፤ ቅዱሱ በዚያን ጊዜ እድሜው ፴ ዓመት ሆኖት ነበረ።

(32ᵁ) ከዚያ፥ ቅዱሱ ለሚከሱት ምስክር ትሆነው ዘንድ የሃይማኖት ጦማር[56] በጳጳሱ ፊት ጽፎ፥ በጳጳሱ ተባርኮ ወደ መኖሪያው በሰላም ተመለሰ።

---

53. "ከምኵራብ በፊት" ማለት "ከአይሁድ ሃይማኖት በፊት" ማለት ነው። "ዓለም መታደስ" የሚለው በክርስቶስ ሰው መሆንና በሞቱም የተጀመረውን የሐዲስ ኪዳንን (የዓመተ ምሕረትን) ሕይወት ነው። "በሔዋን ምክንያት የገነት በር ተዘጋ፤ በድንግል ማርያም ምክንያት ደግሞ እንደገና ተከፈተልን" ያለውን የጎሙሰ ውዳሴ ማርያም ያስታውሰናል። በዚህ አንቀጽ ውስጥ የዘመኑን የሀገራችንን ሊቃውንት ያነታርኩ የነበሩ ሁለት የሃይማኖት ጥያቄዎች ተመልሰዋል፤ አንዱ ስለ ሥላሴ ትርጉም፥ ሌላው ስለ ሰንበት በዓልነት ናቸው። ሰንበት የሚሉት ቅዳሜን ነው። በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ከብዙ ውዝግብ በኋላ ቅዳሜ እንደ እሑድ በዓል እንዲሆን ተወሰነ። Ernst Hammerschmidt, *Stellung und Bedeutung des Sabbats in Äthiopien*, Stuttgart 1963; Edward Ullendorff, "Hebraic-Jewish Elements in Abyssinian (Monophysite) Christianity," *JSS*, vol. I, no. 3 (1956), pp. 216-256; Getatchew Haile, "The Forty-Nine Hour Sabbath of the Ethiopian Church," *JSS*, vol. 33/2 (1988), pp. 233-254.

54. አባ አስጢፋኖስና ተክታዮቻቸው ይከሰሱባቸው ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ ምሥጢረ ሥላሴን (የአምላክን አንድነትና ሶስትነት ትርጉሙን) አያውቁትም የሚል ነበር።

55. ራእ 10፡ 9፤ ቀጂው ሰዋስው አሳስቷል።

56. ግዕዙ የሚለው "መጽሐፈ ሃይማኖት" ነው። ማንኛውም የተጻፈ ነገር በግዕዝ "መጽሐፍ" ይባላል። ይኸም መጽሐፍ ብቻ ላይሆን ደብዳቤንና ማንኛውንም ሰነድ ይጨምራል። እዚህ ላይ "መጽሐፍ" የሚለውን ግዕዝ "ጦማር" ብዬ የተረጐምኩት "ጦማር" በመንፈሱ ከተራ ደብዳቤ ትንሽ ክብደት ያለው ደብዳቤ ስለሆነ ነው።

የመጀመሪያው ስደት

ቅዱሱ ወደሱ የሚመጡትን በመጻሕፍት ሕግ እንዲቆሙ አስተማራቸው። የሰባልዮስን ስሕተት[57] ከልባቸው ለማስወገድ ወለል ባለች በሥላሴ እምነትንም አስተማራቸው። ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የጠበቁና ዓለምን ያሸነፉ ለቅዱሳን ከተሰጣቸው የጸጋ ሀብት ከሞትና ከትንሣኤ ሥጋ በፊት÷ (32^ለ) አሁን በሥጋ እያሉ÷ በትንሣኤ ነፍስ[58] ለመቀበል እንደሚበቁ አስረዳቸው። ቃሉን የተቀበሉ ብዙዎች ሆኑ። በቀኖናው ሥርዓት በሚያርፉበት ጊዜ የሰንበታትንና የበዓላትን ትምህርት ለመስማት[59] ከቅዱሱ ማደሪያ ይሰበሰቡ ጀመር። (እየተማሩ) በቃልም ሆነ በምግባር ከማወላወል ይጠበቁ ጀመር።

የደብሩ ሰዎች በቅዱሱና ከሱ በሚማሩት ላይ ተቆጡ፤ ግን የሚያደርጉትን አጡ። በእንዳች ነገር ላይ ሊከራከሩት እነሱው ተመልሰው ይረታሉ። በዚያ ላይ ራሷ ትምህርቱ ሥራቸውን ነቃፊ ሆነች። (33^ቡ) ከቅዱሱ የሚማሩትን ከቍርባንና ከገበታቸው ያገሏቸው ጀመር። በሁሉም ስም የሚናገሩት (ጠበቆቻቸው) ተነሥተው ቅዱሱን እንዲህ ሲሉ በእግዚአብሔር ስም ተናገሩት፤ "ከደብራችን አንድትወጣ በአብ÷ በወልድ÷ በመንፈስ ቅዱስ ይዘንሃል።"

ቅዱሱ ከደብሩ ሰዎች የመጣበትን ስደት ሲሰማ አበምኔቱ ከነሱ ጋራ ተስማምቶ እንደሆነ ወይም ይፈርድለት እንደሆነ ሊጠይቀው ወደሱ ሄደ። እሱም የማደሪያውን በር ዘግቶ እንዳይገባ ከለከለው።

ቅዱሱ ሁሉም በመባረሩ እንዳበሩ ሲያውቅ ማደሪያውን ትቶ፤ ግፉን ተሸክሞ ተሰደደ፤ (33^ለ)ብዙዎች አብረውት ተሰደዱ። በዚህኛው ስደቱ እስከ ማና ባሕር ደረሰ። በኋላ ተመልሶ ወገራ ላይ ተቀመጠ።

ከዚህ በኋላ÷ ጥቂት ቆይቶ ያ ያባረረው አበምኔት እንዲህ ሲል ወደ ቅዱሱ ላከበት፤ "እርጅናዬን ይቅር በለው፤ ባንተ ላይ ካደረግሁት ኃጢአቴ ጋራ እንድሞት አትተወኝ። አሁንም ኃጢአቴን ይቅር ብለህ እንድትመጣ ይሁን፤ ላገኘህ እፈልጋለሁና።"

---

57. ሰባልዮስ/ሰብልያኖስ በሰሰተኛው ምእት ዓመት የኖረ የሎንያ (ሊቢያ) ኤጲስ ቆጶስ ነበረ። መምህራችን አባ ጊዮርጊስ ዘጋሰጫ/ዘሰግላ በዓሥራ አምስተኛው ምእት ዓመት እንደጻፉልን÷ ሰሕተቱ "አብ ከመ ብእሲ ወልድ ከመ ልጎኑ ወመንፈስ ቅዱስ ከመ አስትንፋሰ አፉሁ፣ ወበአንተዝ ይቤ ፩ ገጽ" ("አብ እንደ አንድ ሰው፤ ወልድ አንደ አንደበቱ፤ መንፈስ ቅዱስ አንደ አፉ አስትንፋሰ ነው፤ ሰለዚህ ፩ አካል ነው" ማለቱ ነው" Yacob Beyene, *Giyorgis di Saglā Il libro del Mistero (Maṣḥafa Mesṭir)*, *CSCO*, vol. 515/89, Lovanii 1990, p. 106. ይኽም የአግዚአብሔርን ሥላሴ (ሰሰትነት) በሰም ብቻ ሰላሰቀረው እምነቱ ውግዝ ነው።

58. "ትንሣኤ ነፍስ" የሚሉት አንደ አባ አስጢፋኖስ ከጻማ በኋላ የሚደረሰበት ብቃት ነው።

59. በቀኖናው ሥርዓት በሚያርፉበት ጊዜ የሰንበታትና የበዓላት ትምህርት ይማሩ ነበረ። በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመንማ ያለምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ የቀረ ንብረቱ ይዘረፍበት ነበረ።

እንደዚህ ከአንዴም፥ ሁለቴ፥ ሶስቴ እየሳከ ቅዱሱን ስለወተወተው ቅዱሱ አብረውት የነበሩትን ወንድሞች (34ᵘ) እንዲህ አላቸው፤ "ይህቺ መእልክት የኔን መሠቃየት ፈልገው ነው እንጂ ለበጎ ነገር አይደለችም። እናንተም እንግዴህ ሕሊናችሁን አዘጋጁ። በኔ በኩል ምክንያት እንዲያጡ ቅጣታቸውን ሳልፈራ እነሆ እሄዳለሁ።"

ከዚያ በኋላ፥ ሊሄድ ተነሣ። እነሱም አብረውት ሄዱ። ከዚያች ቦተባረሩባት ደብር ደረሱ። አበምኔቱንም ተገናኙት። የደብሩ ሰዎች[60] ተሰበሰቡና ጨው አልባ የሆነ የዱለት ነገራቸውን አበዙ። ከቅዱሱ ጋራ የነበሩትን ወንድሞች ተናጠቋቸውና አሰሯቸው። ቅዱሱን ግን ብቻውን እንዲባረር አደረጉ። (34ᵃ) አንዳንዶች፥ "እሱ ካልታሰረ ሌሎቹን ዝም ልናሰኛቸው አንችልም" አሉ። በዚህ ጊዜ አበምኔቱ ቅዱሱን ከመንገዱ እንዲመልሱት አዘዘ።

በተቈሰፈ እግር ብረት ከተቈሰፈ እስር ቤት

ቍልፍ ያለው ከባድ እግር ብረት አመጡና በዚያ ቅዱሱን ሐምሌ ፲፫ ቀን አሰሩት። አበምኔቱ ሌላ ሰው ለስግያምን የእግር ብረቱን ቍልፍ ራሱ ያዘ። በዚህ ሁኔታ ሁለት ወር ድረስ አኖሩት። ነገር ግን የቅዱሱ ተልእኮ ወደሱ የሚቀርቡትን በማስተማርና በመገሠፅ፥ የመጻሕፍቱን ሕግ የሚቃረኑትንም በመዝለፍ በየቀኑ ኃይል እየጨመረ ሄደ።

ቅዱሱን በማሰር ማሸነፍ ሲያቅታቸው ጊዜ (35ᵘ) ሊገድሉት ጨከነው ምግብ ሳይሰጡት ጭለማ ቤት ውስጥ ሊዘጉበት መከሩ። ቅዱሱን አግሮቹ እንደታሰሩ ጳጕሜን ፭ ቀን ከጭለማ ቤት ውስጥ ዘጉበት። ከዚያ፥ አናጢ አምጥተው መስኮቶቹን ሁሉ ምንም ሳያስተርፉ አስደፍነው እንደተቀበረ በድን ጣሉት።

ከዚህ በኋላ፥ እግዚአብሔር ፍርሀት አመጣባቸው፤ እንዲህ ሲሉም እርስ በርሳቸው ተነታረኩ፤ "እንደዚህ ተዘግቶበት ቢሞት፥ እነሆ አገሪ ገዢዎቹ ይሰሙና ደብራችን እስኪጠፋ ድረስ ማሳችንን ይዘርፉታል። (35ᵃ) እንልቀቀው፤ ከፈቀደበት ይሂድ።"

ከዚያ፥ መስከረም ፩ ቀን ከጭለማው ቤት አውጥተው አግር ብረቱን ከእግሮቹ ላይ ፈቷቸው። አበምኔቱ ቅዱሱን እንዲህ አለው፤ "ያደረግንብህን ክፋት ሁሉ ይቅር በለን። አሁንም በደብሩ ከኖርክ እግዚአብሔር ለሐዋርያት የሰጠውን የጸጋውን ዋጋ ይስጥህ። ወደ ምድረ በዳ ከሄድክም በምድረ በዳ ለነበሩ ቅዱሳን[61] የተሰጠውን ስጦታ እንደዚያ ይስጥህ። በጀመርከው ሁሉ እግዚአብሔር አብሮህ ይሁን፤ እስከመጨረሻው እሽናፈነትን ይስጥህ። ወደፈለክበት ሂድ። ባደረስንብህ በደል አትቀየም።"

---

60. ደራሲው "መነኮሳት" በማለት ፈንታ "የደብሩ ሰዎች" ማለቱ መልእክት ይኑረው አይኑረው ግልጽ አይደለም። ምንኩስናቸውን ማቃለሉ ወይም ያልመነኮሱትን ስመጨመር ሊሆን ይችላል።

61. "በምድረ በዳ የነበሩ ቅዱሳን" የሚባሉት በእንግሊዝኛ "Desert Fathers" ይባላሉ።

(36[ሀ]) ቅዱሱ፥ "ከኔ በኩል ክፉ ነገር አይመጣባችሁም፤ ግን ይቅር እንዲሳችሁ በአግዚአብሔር ዘንድ ንስሐ ግቡ" አሳቸው::

ሁለተኛ ስደት--የደብረ ገርዜን መመሥረት

ከዚያ ደብር ወጥቶ ከመጀመሪያው ጀምሮ በስደቶቹና በአስራቶቹ ከቅዱሱ ጋራ ተካፋይ ከነበረው ደቀመዝሙሩ ከገብረ ክርስቶስ ጋራ ከተከዜ ወንዝ አጠገብ ሄዶ ተቀመጠ:: ሌሎች ወንድሞችም ያስተማራቸውን ውሳኔዎች እየጠበቁ በአቅራቢያው ተቀመጡ:: "የእግዚአብሔርን (36[ለ]) በረከትና ሕይወት ካሁን እስከ ዘላለም አንድታገኙባት አግዚአብሔርን ስለሠራው ሁሉ ለመባረክ በሁሉም ነገር እንደዚህ ጸንታችሁ በደብረ ገርዜን[62] ኑሩ" አሳቸው::

የዚያች አገር አካባቢ መምህራን[63] የቅዱሱን ዜና ሲሰሙ በጣም ታወኩ:: ትምህርቱን ለማስቀረት ፈልገው ዶልተው ከሀገረ ገዢው ዘንድ ሁለት ጊዜ ጉባኤ አደረጉ:: ቅዱሱ (የአግዚአብሔርን) የትእዛዙን ቃል ለምስክራ እየጠራ በሕግ ሰይፍ ገጠማቸው:: የቅዱሱን ነገር ጠንካራነት በመፍራት የምንኵስናውን መጽሐፍ[64] እንደማያውቁት ሆነው እስከ መካድ ደረሱ:: የቅዱሱን የትምህርቱን ዘር (37[ሀ]) ሳይፈልጉ (እየሰሙ) ተሸክመው ወደየደብራቸው ተመለሱ:: ደቀ መዝሙሮቻቸው የቅዱሱን ስብከት ሰምተው እርስ በርሳቸው (በሐሳብ) እየተለያዩ በየአድባራቸው ንትርክ ተፈጠረ--ደጎቻቸው እየተጨመቁ ወጥተው ስብከቱን አስኪቀበሉ ድረስ:: የቅዱሱ ትምህርት በውበቷ ተዘረጋች::

የብቸኝነቱን (የብሕትውናውን) ሥርዓት የጀመሩት አባታቸው እባ አንጠንስ ወይም አንጠንዮስ የሚባሉ የግብጽ ሰው እንደሆኑ ከላይ በጎጻግ ቊጥር 24 እና 25 ስር ተገልጧል:: የአበምኔቱ ምርቃት አባ አስጢፋኖስ የደረሱበትን ብቃት አለማወቃቸውን ያሳያል:: በምድረ በዳ ለነበሩ ቅዱሳን የተሰጠው ስጦታ ብቃትና ራእይ ማየት ነው፤ እባ አስጢፋኖስ ከዚያ ደረጃ እንደደረሱ ገድላቸው ይመስክራል:: የአባ አበክረዙን ገድል አንደሚለው እባን የፈቷቸው ልጆቻቸው ከባለሥልጣኖቹ ዘንድ ተሯሩጠው ሹመን አንዳሚያመጡባቸው ስላወቁ ነው::

62. ስለ ደብረ ገርዜንና ስለ አቡነ ይሥሐቅ ጎጻግ 33 ገጽ 131ን ተመልከት::

63. እዚህ ላይ "መምህራን" የተባሉት የእድባራት አበምኔቶች ናቸው::

64. የምንኵስና መጽሐፍ ወይም መጽሐፈ መነኮሳት የሚባሉት አንደኛው በእክሱም ዘመነ መንግሥት የተተረጐመው የአባ ጳኮሚስ ሥርዓት ("ሥርዓተ ዘአዘዞ መልእክ እግዚአብሔር ለአባ ጳኮሚስ") የሚባለው ነው፤ ዲልማን አሳትሞታል፤ Augusto Dillmann, *Chestomathia Aethiopica*, Darmstadt 1965, pp. 57-76:: ሌሎቹ ገነት (ገነተ መነኮሳት) እና ዜና አበው የሚባሉት የመነኮሳት ፍልስፍና የተስበሰበዓቸው መጻሕፍት ናቸው፤ እነሱን ቪክተር አራስ አሳትሟቸዋል፤ Victor Arras, *Collectio Monastica, CSCO*, vol. 237/45, Louvain 1963; Victor Arras, *Patericon Aethiopice, CSCO*, vol. 277/53, Louvain 1967. ከነአባ አስጢፋኖስ ዘመን በኋላ ወደ ግዕዝ የተተረጐሙ ሌሎቹ መጻሕፍተ መነኮሳት የሚባሉት "ማር ይሥሐቅ"፥ "ፊልክስዩስ"፥ "አረጋዊ መንፈሳዊ" ናቸው:: ኢትዮጵያ ከነአንድም ትርጉማቸው ካንዴ በላይ ታትመዋል፤ *ሦስቱ መጻሕፍተ መነኮሳት አነርሱም ፩ኛ ማር ይስሐቅ ፪ኛ ፊልክስዩስ (ገብረ ክርስቶስ) ፫ኛ አረጋዊ መንፈሳዊ*፤ አዲስ አበባ ፲፱፻፹፪ ዓ. ም.::

ከዚያ በኋላ፥ ዝናው በዚች መንግሥት አገሮች ሁሉ ተሰማ። ብዙዎች ወደሱ መጥተው በትምህርቱ ስብከት ተጠመዱ። በእያንዳንዱ ማኅበራቸው በየ፲፪ቱ በቡድኖች እንዲከፈሉ፥ ለያንዳንዱም ማኅበር ከማህላቸው ተግባረ እዳቸውን ሊያካሂዱ ትእዛዝ በመስጠት የሚያገለግላቸውን የመረጡትን ቀዋሚ (37$^{\Delta}$) እንዲያደርጉ ሥርዓት አወጣላቸው። ደግሞ ከማኅበሩ ተላላኪዎች/ቀዋሚዎች ሁሉ በላይ ሆነው የሚያዝዙ ከማኅበሩ ሁሉ ሁለት አዛዦች እንዲመርጡ አዘዛቸው። በየአድባራቸው እንዲሁ (እንዲሆን አደረገ)።

ለምግባቸው የእንጀራ፥ የአትክልት፥ የውሐ መለኪያዎች አበጀላቸው። ብዙ በመቀበል ከዚያ እንዳያበልጡ፤ በትንሽነቱም ምክንያት (የደረሳቸውን) እንዳይለውጡ አዘዛቸው። ስለ ልብስም እስከ ትንሹ ነገር ድረስ እኩል እንዲያደርጉ እንጂ ማንም ቢሆን በማሻሻል ሳቢያ እንዳይጨምር፥ ለማሳጠርም እንዳይቀንስ እንደዚሁ አዘዛቸው። በሐዋርያት ሥራ (38$^{\vartheta}$) መጽሐፍ ውስጥ እንዳለው የሐዋርያትን ቅድስት ሥርዓት[65] ሠራላቸው። እንዲህ አላቸው፤

> በሰላም ለንለለት ተያይዛችሁ በአንድ ልብና ነፍስ ኑሩ። ከናንተ ማንም ካለው አንድ ሐሳብ በቀር ስለ ልብስም ሆነ ስለ ምግብ በመሄድም ሆነ በመመለስ ጊዜ፥ በሐሳብም ሆነ በግብር ሌላ አይኑረው፤ ለጽድቅ ሥርዓት ባሮች ሁኑ እንጂ። በጠላት በለይጣን ከመያዝ ይልቅ የወንድሞቻችሁን ደስታ በመቀበል[66] የጠፊውን ሥጋችሁን ጠባይ ካዱ። በእጃችሁ ሥራ ኑሩ። የለዎችን የድካም (ፍሬ) በከንቱ አትውሰዱ። ጥሪትም ምንም አይኑራችሁ። በሚያረጅበትና በሚበላሽበት ቦታ (ማለት) በምድር ላይ ጥሪት አታብጁ፤ (38$^{\Delta}$) የጌታን ቃል ተከታዮች ሁኑ እንጂ። ጥሪታችሁ ትልና ምስጥ ከማያገኘው ከመንግሥተ ሰማያት እንድትሆንላችሁ[67] ሁል ጊዜ አድርጓትም። ከድካማችሁ የተረፈውን ምግብም ሆነ ልብስ ጌታ ላዘዘለት ስጡት። ለሚመጣው ጊዜ ብላችሁ ስማግስት አታስተርፉት። አምላካችን በየዓመቱና በየዘመኑ ከረምትን በማመላለስ፥ ፍሬዎችን በመስጠት፥ በረከት በመስጠት ለፍጡሮቹ ያዘጋጀውን የቸርነቱን ሥርዓት ተመልከቱ። እናንተም እንደ ጌታ ትምህርት የዛሬውን ለዛሬ፥ የሚመጣውን ደግሞ ለሚመጣው ዓመት አድርጉ። (39$^{\vartheta}$) እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ያወጣቸው ጊዜ ከምድረ በዳ እስቀምጦ ስምግባቸው መና አዘነበላቸው። ለየቀኑ ብቻ የሚሆነውን እንዲሰበስቡ፥ ለማግሥት እንዳያሳድሩ አዘዛቸው። አንዳንዶች ባለማመናቸው ቃሉን ጥሰው ለማግሥት የሚሆን አሳደሩ። ስለዚህ (ያሳደሩት) ተላ፤ ገማም[68]። ይኸም ለምንኵስና ምልክት ነው። ደግሞ

---

65. "የሐዋርያት ቅድስት ሥርዓት" የሚለው በሐ ሥራ 4: 32-37 ያለውን የማኅበር ኑሮ ነው።

66. የወንድሞችን ደስታ ከራስ ጥቅም አብልጦ መቀበል ከሌላም ቦታ ደጋግመው የተናገሩት ትምህርታቸው ነው።

67. ማቴ 6: 19።

68. ዘፀ 16: 20።

አንደዚሁም፤ "የዕለት ምግባችንን ዛሬ ስጠን"[69] አያልን አንድንለምነው በቅዱስ ወንጌል አዝዞናል።

በመስበስብም ሆነ በሐሳብ ሌላ ትርፍ ነገር አንዳንፈልግ፥ ሳያከማቹ (39ʰ) በቀላል በመኖር ወፎችን እንድንመስላቸው ያዘናል። ወፎች ሲያባርሯቸው በቀላል ይበራሉ፤ ምክንያቱም የሽከም ከብደት የለባቸውም። እናንተም አንደዚሁ ከሚበስብስበት ቦታ ሳታከማቹ በቀላል ኑሩ። የሚተርፋችሁ ከድኾች ሆድ ይቀመጥ፤ ልብስም አንደዚሁ ለተራቆቱ ይሁን። በአሪትም ጌታ እንዲህ ይላል፤ "የመሥዋዕቴ ስብ ለማግሥቱ አይደር።"[70] "ለሌላ (ቀን) የሚያስተርፈውን ነፍሴ አትወደውም።"[71] ስለዚህ እናንተ ዘንድ የተረፈ ነገር አንዳይገኝ እንፈራለን። ለሚያመሰግኑ ስጡት፤ ከማይበላሽበት ቦታ ይከማችላችኋል። ልባችሁም እዚያ በረከት ልትወርሱ ከተጠራችሁበት ከቅድስት የሰማያት ቦታ (40ᵘ) ይስቀላል።[72]

ልብ የሚማርኩ አትክልቶች አትሥሩ፤ በዚህ ምክንያት ቀሚዎች ይወድቃሉ። የአትክልት ቦታዎች የሚያበዙ አነዚያ ርስት ይሆኗቸውና ልባቸው ይማረክባቸዋል፤ መስቀል ለመሸከም ደካሞች ይሆናሉ። ለነፃነታችሁ አንቅፋት አትፍጠሩ። ካንድ (ሀገር) ሲያባርሯችሁ ወደ ሌላው በቀላል አንድትሸሹ ወፎችን በመምሰል ሁል ጊዜ ነቅታችሁ ኑሩ። "እውነት እላችኋለሁ፤ የሰው ልጅ አስኪመጣ ድረስ የአስራኤል ከተሞች አያልቁም"[73] ባለው በጌታ ቃል (40ʰ) ተስፋ በበረከት ጊዜ ታርፉላችሁ። ስንበታትንና በዓላትን በቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ አንደተጻፈው አያከበራችሁ፥ የመንግሥተ ሰማያት በር የሆኑ ቅዱሳን ሐዋርያት የነገሩንን የቤተ ክርስቲያን የብሉይና የሐዲስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ምስክራ ለመጠበቅ የተዘጋጃችሁ ሁኑ[74]።

ሥጋችሁንም በበሽታ ልማድ ምክንያት አትብጡ፤[75] ከክርስቶስ ደም ምስጢር ጋራ ተካፋይ ሆናችሁ ሳለ ደማችሁን አታፍሱ። (41ᵍ) አሕዛብ መፈወሻዎች ከሚሏቸው ከዕፀዋትም[76] ሆነ ከሌላ ነገር

69. ሉቃ 11፡ 3።
70. ዘፀ 23፡ 18፤ ሌዋ 22፡ 30፤ ዘዳ 16፡ 4።
71. ?።
72. ማቴ 6፡ 19-21።
73. ማቴ 10፡ 23።
74. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተነሡት ውዝግቦች ውስጥ በመጽሐፈ ሲኖዶስ ውስጥ ስላሉት የቤተ ክርስቲያን የሕግ መጻሕፍት አቈጣጠርና አንዲከበሩ አዚያው የታዘዙት በዓላት ጉዳይ ነበር። አባ አስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው መጽሐፈ ሲኖዶስን ከተቀበሉ ቅዳሜን ያከብራሉ፤ ገድሉም ይመሰክራል። በመጽሐፈ ሲኖዶስ ውስጥ ያልተዘረዘሩትን መጻሕፍት ግን በሕግ ደረጃ የሚቀበሉ አይመስልም። መጽሐፈ ሲኖዶስ አስካሁን አልታተመም።
75. በአካባቢያቸው ልማድ ልጅ ዓይኑን ሲያመው ሽፋሉ ላይ ከሁለት ቦታ ይበጡታል። ልማዱ ዛሬም የቀረ አይመስልም።
76. ዕፀዋት ይከለክላሉ፤ Getatchew Haile, "The Cause of the Ǝstifanosites: A Fundamentalist Sect in the Church of Ethiopia," *Paideuma*, vol. 29 (1983), p. 114.

እትፈልጉ--ለመቅመስም፥ ለመቀባትም፥ ለማሽተትም፥ ወይም ለምንም ቢሆን፡፡ "እግዚአብሔር የመዳኛዬ አምላክ ነው"[77] ተብሎ እንደተጻፈው የኛ ፈውሳችን እሱ መድኃኒታችን ነው፤ ምክንያቱም መቅሠፍት ከቁጣው፥ ድኅነት ከፈቃዱ የሚመጡ ናቸው፡፡ የጌታን ተግሣጽ በምስጋና ለመቀበል በሁሉም ረገድ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡ "ምክንያቱም ለራሱ የሚኖር የለም፡፡ ብንኖር ለእግዚአብሔር ነው፤ ብንሞትም ለእግዚአብሔር ነው፤"[78] ለራሳችን አይደለም፡፡ ፈውሶችና ምልክቶች የሚሏቸውን ከሕግ መጻሕፍት ያልሆኑ (41ᴬ) ቃላት እየጠሩ በመድገም ጥንቆላ በመፈለግ የሚጨነቁ ሁሉ ነፍሳቸውን ለግዝት ሰይፍ ያስረክባሉ፡፡[79] እንደቀድሞ መምህሮቻቸው የእሳት ጉርፍ ይጠብቃቸዋል፡፡[80] እናንተ ግን የወንጌሉን አምላካዊ ወተት ሁል ጊዜ እየጠባችሁ በአንድ (ልጁ) የትምህርት አዳራሽ ኑሩ፡፡ ለመዳን ትጉለምሱባታላችሁ፤ ከቅዱሳን ጋራም ወንድማማቾች ትሆናላችሁ፡፡ ቅዱሱ ሐዋርያ እንዳለው ከእውነተኛ የተድላ በዓላቸው ዘንድ ለመድረስ በደስታ ተፋጠኑ፤ ቅዱሳን በሚገቡበት ቦታ ዕረፍት አለና፡፡[81] ለይጣንንና ወጥመዶቹን ሁሉ እንድታሸንፉ ድል የሚሰጥን ብርታት የታጠቃችሁ ሁኑ፡፡

(42ᵁ) በእንደዚህ ያለ ትምህርት ሁል ጊዜ ያበረታቸው ነበረ፡፡ በማኅበራቸው መጽሐፍ[82] ውስጥ ተሠርቶ እንዳለው ስለ ማንኛውም ሥራ ሁሉ ምንም ሳያስቀር ሕግ አወጣላቸው፡፡ ማታም ጠዋትም ይጐበኛቸዋል፡፡ ለኑሯቸውም ትርጉም ይሰጠዋል፤ (ከብቃት) ለመድረስ እንዲጎለምሱ ዕውቀት ይጨምርላቸዋል፤ የመጻሕፍትን ምስክራም ያነብላቸዋል፡፡ መስቀሉን ለመሸከም አቅም እንዲያገኙበት ምስጢር ያለበትን ይተረጉምላቸዋልም፡፡ በሳዩ ባደረው በክርስቶስ ሙቀት እስኪያሞቃቸው ድረስ ሁል ጊዜ ይተጋል፡፡ ርግብ እንቁላሎቿ ሕያው እስኪሆኑና በነሱ ላይ ሥጋዊ (42ᴬ) መልኳ እስኪቀረጽባቸውና ዝገት ከነሱ እንድታስወግድ ታቅፋ እንደምታሞቃቸው፥ አድገውም ፈለጓን እስኪከተሉ ድረስ ከተሠራላቸው ምግብ ለመስጠት እንደምትተጋ፥ ይህ ቅዱስ አባታችንም የመንፈስ እናት ሆኖ በትምህርቱ ስብከት የተማረኩትን እንቁላሎች ሰበሰበና በመንፈሳዊት መርከብ፥ ማለትም

77. መዝ 50፡ 16፡፡
78. ሮሜ 14፡ 7-8፡፡
79. የዘመኑ ችግር ነበረ፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብም ልማዱን ለማስቀረት *ጦማረ ትሰብእት* የሚባል መጽሐፍ እስከ መድረስ ብዙ ታግሏል፤ Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity of Emperor Zär'a Ya'əqob (Ṭomarä Təsbə't)*, *CSCO*, text vol. 522/95, tr. 523/96 (1991); Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān)*, *CSCO*, vol. 261/51, p. 51.
80. ስለ ጠንቋዮቹ የቀድሞ መምህሮች መጽሐፈ ሄኖክ 2ን ተመልከት፡፡
81. ዕብ 4፡ 9፡፡
82. "የማኅበራቸው መጽሐፍ" የተባለው አንቶኒዮ ሞርዲኒ ከዘረዘራቸው ውስጥ የትኛው እንደሆን ለማወቅ አልቻልኩም፡፡

በቅድስት ሥርዓት አሳፈራቸው። ፈጣሪያቸውን በማወቅ፥ (ማለት) የሥላሴነታቸውን[83] ህላዌ በመረዳት የቅድስት ሃይማኖትን ዐጽፍ አጎናጸፋቸው። የመንፈስ ምግብ የሆነውን የሕይወት ሰጪ ትእዛዙን መገባቸው። የልቦቻቸውን መስኩቶች (43ᵘ) የጠላት ከሆኑ ሐሳቦች እንዲጠብቁና ለፈጠራቸው ማደሪያ እንዲሆኑ በሁል ጊዜ አምነት ነፍሳቸውን እንዲያጸዱ መንፈሳዊ አጥበት እንዲያደርጉ የማስተዋል ትጋትንም አሰረዳቸው።

እነሱም ይሽንን ተቀብለው፥ መጀመሪያ ያለእናት (የትም) ወድቀው ባገኛቸው ጊዜ የተዋሐዳቸው የኃጢአት ዝገት በአባታቸው መንፈሳዊ ሙቀት ጠፍቶ ሞቃቶች ሆኑ። ከዚያ በኋላ ሕይወት ያለባቸው ሆኑ፤ የሥጋን ፍላጎትና ጠፊ ምኞቶቹን ጥለው በነፍሳቸው መልክ ተንቀሳቀሱ። የአባታቸውን ሩጫ በሁሉ አቅጣጫ ይከተሉ ዘንድ (ልባቸው) በጉጉት ተሰቀለ።

ሰይጣን የክስ መርዙን በደብሮቹ ላይ ረጨ

(43ᵃ) ትምህርቱን የሚፈጽሙ ተባባሪዎቹ ብዙዎች መሆናቸውን ሰይጣን ሲያይ በቅርብና በሩቅ አገሮች ያሉትን ደብሮች ሁሉ ቅዱሱን በሀገሩ ግዞዎች ዘንድ ለመክሰስ እንዲያብሩ ቀሰቀሳቸው። ሰይጣን ጌታ ከአቤል ደም አስክ ዘካርያስ ደም እንደሚፈልግባቸው የተናገረውን[84]፥ የጻድቃኑን ሁሉ ደም ለማፍሰስ ሊተባበሩት ልጆቹ በሆኑት ሁሉ በልባቸው ቦሐቃ የክስ እርሾውን ጨመረበት። ከቤቱ ባለቤት (ከክርስቶስ) ደም ጀምሮ እስከ ቤተሰቡ ሁሉ ደምም እንደዚሁ ሆነ። የጻድቁን ደም ለማፍሰስ (44ᵘ) እንዲህ ሲሉ ከሕሊናቸው የመርዝ ጭማቂ አፈሰሱ፤

> አነሆ ይህ ሰው የደብሮቻችንን ሥርዓት ይሽራል፤ ሽማግሌዎቻችንን ይሳደባል፤ መምህሮቻችንን ይዘልፋል። "ከሕግ ውጪ ውሸት ታስተምራላችሁ" ይላል። ምስጢር የሆነውን የሚናገሩ፥ ራእይም የሚያዩ ዐዋቂዎቻችንን ውሸተኞች ያደርጋቸዋል፤ "በእጋንንት ምትሃት የተሸነገሉ፥ በስሕተት ሕልም ፈተና የተሸነፉ ናቸው" ይላል። እነሆ፥ ልጆቻችን በትምህርቱ ተማረኩ። ሲመስሉ የሚናገረውን ምስክር በማድረግ በጠበጡን።

ይሽንንና የመሰለውን አብዝተው (ለአገረ ገዢዎቹ) ክስ አቀረቡ። አገረ ገዢዎቹ ግን የሚያቀርቡት ክስ ሁሉ በቅናታቸው እንደሆነ ያውቃሉ። (44ᵃ) "እንጠራላችሁና እናከራክራችኋለን" አሏቸው። ከዚያ፥ አገረ ገዢዎቹ ወደኑ አንዲመጣ ሰቅዱሱ ላኩበት። ሲመጣ እንዲህ አሉት፤

> አባት ሆይ፥ የቃልህን እውነትነት፥ የትምህርትህንም ሥርዓት ትክክለኛነት በአውነት የእግዚአብሔር መሆኑን የማናውቅ

---

83. "የሥላሴውን" መሆን አለበት።

84. ማቴ 23: 35።

አይደለንም። አንተ በዚች በምድራችን ላይ ክሄድክባት ጊዜ ጀምሮ ምሕረት ወርዷል። የትምህርትህን ስብከት በመስማት ብዙ ስሕተቶች ተወግደዋል። ይህም እዚህ ብቻ ሳይሆን ዜናህ በተሰማባቸው በሩቆች አገሮች ሁሉ ነው እንጂ። ግን እነዚህ ፈላሲዎች[85] ትምህርትህን በመቃወም ይወተውቱናል። (45^{ሀ}) እኛም አንተንና ደቀ መዛሙርትህን በማጥላላት እንድንተባበራቸው፥ የልጆችህን የድካም (ፍሬ) እንድንዘርፍ ይፈልጋሉ። "ልጆቻችንን ይወስድብናል፥ ገዳሞቻችንን ይዘርፍብናል" ይላሉ። "የሰዎችን ልብ (በምትሃት) ወደሱ ይስባል" ይሉሃል። በቅናት ብዙ ነገር ያወሩብሃል። እኛ ግን ትምህርትህ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነች ዐውቀናል። በአንተ ላይ ያላቸውን ክስ ችላ ስንልባቸው ይገላምጡናል። አንተ ዓመፀኛ/ከሓዲ እንደሆንክና እኛም በዓመፅ/በክሕደት ትምህርትህ ግብር አበሮች እንደሆንን አድርገው ከንጉሡ ዘንድ በሐሰት እንዳይከሱን እንፈራቸዋለን። ስለዚህ (45^{ለ}) ስበብ እንዳያገኙ ስንል "በሱ ላይ ክስ ያላችሁ ተስብሰቡና እናክራክራችሁ" አልናቸው። (እነሆ) የላክንብህ በዚህ ምክንያት ነው።

ቅዱሱ፥ "ይምጡና ይበሉ ክሳቸውን ይናገሩ" አሳቸው።

ከዚህ በኋላ የአደባባይ ሽንጎ አደረጉ። ቅዱሱን (በሐሰት) የሚያሳጡት መጡና ክሳቸውን አሳጥረው፥ ውስጥ ውስጡን ግን ብዙ እያሱ፥ መናገር ጀመሩ። እንዲህ አሉ፤

እነሆ ይኸ ስው በማህላችን ንትርክ ይጥልብናል። አባቶቻችን ያላስተማሩንን ሌላ ትምህርት ያመጣብናል፤ ልጆቻችንን ወደሱ ይወስድብናል፤ ደብሮቻችንንም ይዘርፍብናል። ክሳችን ይኸ ነው።

ከዚያ፥ ቅዱሱ ቃሉን ከፍ አድጎ እንዲህ አለ፤

(46^{ሀ}) ክነሱ ውስጥ አንድም የበደልኩት የለም፤ ዐመፅ የሠራሁበትም ማንም የለም። ግን የሕይወትን መንገድ ለሚፈልግ የእግዚአብሔርን ሕግ ነግራያለሁ። በነገር ዘዴ በመደለልም ሆነ የዚህን የኃላፊ ዓለም ገንዘብ እሰጣለሁ በማለት የጠራሁት የለም። ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ሕይወት እንዲያገኙ፥ ለሱ እንዲጠመዱ የእግዚአብሔርን ሕግ አስተምራያለሁ። በዚህ ሕግ ምክንያት የተባረሩትንም ተቀብያቸዋለሁ፤ ምክንያቱም (መጽሐፉ) "ባልደረባህን እንደራስህ ውደድ"[86] ይላል። "ያባቶቻችን ያልሆነውን አመጣ" የሚሉት እኔ ከእግዚአብሔር ሕግ በቀር ሌላ ያስተማርኩት ነገር የለም። "(ትምህርቴን) የእግዚአብሔር ሕግ አይደለም" ካሉ፥ የእግዚአብሔር ሕግ እንደሆነ እነሆ ምስክሬ (46^{ለ}) የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ናቸው። ሕጉን አባቶቻቸው ስላላስተማሩት የሌለ አያደርጉትም። አባቶቻቸው አልተረዱት እንደሆነ፥ እነሱ በሕግ ትምህርት ቤቱ በር

85. ከዓለም የፈለሱ፥ የመነኑ "መነኩሳት" ማለት ነው።

86. ማቴ 19፡ 19።

ይግቡበት:: ምክንያቱም ቅዱስ ወንጌል፥ "በሌላ በኩል የሚወጣ ሌባና ወንበዴ ነው"[87] ይላል:: እነሱ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ለማስገዛት ካልፈለጉ ሌላው ለእግዚአብሔር እንዳይጠመድ ለምን ይከለከላሉ? "ልጆቻችን ናቸው" የሚሉት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሳያስተምሯቸውና ከኃጢአት የመዳኛ ጸጋ ሳይሰጧቸው (47ᵘ) እንዴት ልጆቻቸው ሆኑ? እነሱስ ቢሆኑ ራሳቸውን ለአባቶቻችን ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለተከታዮቻቸው ለመነኮሳት አባቶች ለእንጦንዮስና ለመቃርዮስ ትእዛዝ ሳያስገዙ የአባትነትን ስም እንዴት ወለዱ? እውነትን የሚፈልገውን በከንቱ የሚቃወሙ ከሆነ እኔ ደግሞ ወይ የእግዚአብሔር ወይ የቁሳር ባሮች ሁኑ እላቸዋለሁ፤ ምክንያቱም ጌታ፥ "የቁሳርን ለቁሳር ስጡ፤ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር አድርጉ"[88] ብሏል::

"እንደዚህ እንድትናገረን በኛ ላይ ማን ሾመህ?" አሉት:: ቅዱሱ "እንዳደርግና (47ᵃ) እንዳስተምር የእግዚአብሔር ሕግ ሾሞኛል" አላቸው::

ከዚያ፥ በቁጣ ተነሡና ልጆቹን በጉልበት ሊቦጫጭቋቸው ወረሯቸው:: ቅዱሱ ለገዢዎቹ፥ "እናንተ ክርስቲያኖች ሆናችሁ፥ ንጉሡም ክርስቲያናዊ ሆኖ ሳለ፥ ለምን እንዲህ ያደርጋሉ? እኔም (ጉዳዩ) በእግዚአብሔር ፍርድ ይፈጸም እያልኩ ሳለሁ፥ በጉልበት እንዲያጠቁን ያለፍርድ ትለቋቸዋላችሁ?" ከዚያ፥ ወታደሮቻቸውን ልከው በግድ አስሟቸው:: ከቁጣቸው ፍንዳታ የተነሣ ቅዱሱን ሲሳደቡ፥ "ይህ አዳኝ ተኩላ፥ ይህ ተናጣቂ ጭልፊት" ይሉት ነበረ:: ቅዱሱ ግን መርበድበዳቸውን እያየ (48ᵘ) በተኩላዎች የጨከት ድምፅ እንደማይታወክ ብርቱ አንበሳ ሆኖ ከላይ በታዘዘው ኃይል በመደሰት ፈገግታ ያሳይ ነበረ:: ያም ሆኖ፥ በሚረግሙት ምትክ ይባርካቸው ነበረ::

ከዚያ፥ ቅዱሱ ስለ ጉዳዩ ፍርድ ለመጠየቅ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ:: ከነሱ ውስጥ ኃጢአት የጠገበው አንዱ የእውነት ጠላት፥ ቅዱሱን እንዲህ አለው፤ "እንዳትናገረን በንጉሥ ይዘንሃል::" ቅዱሱ እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "እኔ የነፍስ ሕይወት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ተናገርኩ እንጂ ንጉሦች ስለሚያዙበት ስለዚህ ዓለም ገንዘብ አልተናገርኩም፤ ምክንያቱም የሰማያዊ (48ᵃ) ንጉሥ ቃል በምድራዊ ንጉሥ እይታገድም፤ ምድራዊ ንጉሥ ግን በሰማያዊ ንጉሥ ቃል ይታገዳል:: የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም::"

ያ አላሳች እንዲህ አለው፤ "እንተስ፥ ንጉሥም አታውቅ::" ቅዱሱም፥ "የክርስቲያኑ ንጉሥ እውነተኛ ክርስቲያን እንደሆነ እውቃለሁ፤ እግዚአብሔር መንግሥቱን ይጠብቅ" አለ:: ይህ ሰበብ ፈላጊ፥ "እኔ እስራኤል አለዋለሁ" አለ:: ቅዱሱ፥ "እኔ ደግሞ ክርስቲያናዊ አለዋለሁ" አለ::

87. ዮሐ 10: 1::
88. ማቴ 22: 21::

ቅዱሱ ያንን ሰው እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ "እስቲ ንገረኝ፥ እኔ ክርስቲያናዊ ነው ስል አንተ እስራኤላዊ ነው ያልከው፥ የእስራኤል ስም ይበልጣል ወይስ (49^{ሀ}) የክርስትና ስም?" ያ ስሕተተኛ፥ "የእስራኤል ስም ይበልጣል" አለ። ቅዱሱ እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "የለም፥ የክርስትና ስም ይበልጣል፤ እስራኤሎች በሥጋ ተወልደው እስራኤል ይባላሉ፤ የክርስትና ስም ግን በመንፈስ ቅዱስ በሰማያዊ ልደት ተወልደው ክርስቲያን ይባሉበታል። ስለዚህ ከሁሉ በላይ የሆነች የሐዋርያት ጉባኤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስም ይበልጣል።"

ከንጉሡ (ከአፄ ይሥሐቅ) አደባባይና ችሎት

አገረ ገዢዎቹ ይሽንን ሲሰሙ እርስ በርሳቸው ተወያይተው፥ "ይህ ነገር ለኛ ከባድ ነው፤ ከንጉሡ ዘንድ ይሂዱ እንጂ እኛ ልንወስነው የምንችለው አይደለም" አሉ። ቅዱሱንና (49^{ሀ}) እነሱን፥ "ከንጉሡ ዘንድ እስከትደርሱ ድረስ ዋስ ጥሩ፤ ጉዳያችሁን ሁሉ እዚያ ትፈጽማላችሁ" አሏቸው። እነሱ ዋስ ጠሩ፥ ቅዱሱ ግን "ከዓለም ሞቻለሁ ያልሁ ሰው ለራሴ መድን ዋስ አልጠራም። ምክንያቱም ቅዱስ ሲኖዶስ ካህን ለራሱ መድን ዋስ እንዳይጠራ ያዝዛል። የጠራ ካለ ከማዕረጉ እንዲወድቅ ያዝዛል። ታመናችሁኝ እንደዚሁ ላኩኝ። ካልፈቀዳችሁ እነሆ አለሁላችሁ፤ (ዋስ) በራሴ።

የነገሩን መጨረሻ ሲያውቁ በስንሰለት እንዲያስሩት ትእዛዝ ሰጡ። በመስከረም በሯ፬ ቀን አሰሩትና ሹመና ያ በሽሬ ላይ የሚሰልለው ባለሥልጣን መልእክተኞቻቸውንም አዘጋጅተው እስኪልኳቸው ድረስ የሽሬ ሹም በግቢው (50^{ሀ}) ውስጥ አቆየው። ሁሉንም አዘጋጅተው ሲፈጽሙ በጥቅምት በሯ፮ ቀን ሊሂዱ ወሰዱት። መልክተኞቻቸውን ጉዳያቸውን ለንጉሡ እንዲያደርሱ በዝርዝር አስጨብጠው ላኳቸው። በዚያን ጊዜ ማስሪያውን ሁሉ ከእጁ ላይ አወለቁለት። ልጆቹ በሰላም ሸኙት። አብረውት የሄዱትም ብዙዎች ነበሩ።

በብዙ ድካም በታኅሣሥ ፲፪ ቀን ከንጉሡ በር ደረሱ። መልክተኞቹ (50^{ሀ}) ከጥቂት ጊዜ በኋላ መልክታቸውን ከንጉሡ ዘንድ አደረሱ፤ ጉዳያቸውን ሁሉ አስረዱ። እነዚያን ከሳሾቹንና ቅዱሱን ግን እውጪ እንዳሉ የሕይወታቸውን ሁኔታ እስኪረዱ ድረስ ወደ ውስጥ አላስገቧቸውም።

እነዚያ ከሳሾች ግን እንዲህ ሲሉ (የንጉሡን) ሰፈር አወኩት፤

> እነሆ ይህ (ተከሶ) የመጣው ሰው መተተኛ ነው፤ ቃሉን እውነት አድርገው እንዲቀበሉለት በመተት የሰውን ልብ ወደሱ ያዞራል። እሱ በእጁ ከነካው ማንም ቃሉን ቸል የሚል የለም፤ ምክንያቱም በአፉ ከመጻሕፍት ይናገራል። ግን በልቡ ውስጥ የተደበቀች ሌላ (51^{ሀ}) ክሕደት አለች። አብረውት እርዝመው መኖር ሳዘወተሩ ለጥቂቶች ካልሆነ በቀር እንዲያውቃት ለማንም አይገልጣትም።

(ከሳሾቹ) ለመነኮሴዎቹ፡ ለልዑላቱና በምንኩስና ስም ለሚጠሩ ልዑላት[89] ደግሞ እንዲህ አሏቸው፤

> እነሆ ይህ ሰው መነኮሳትን ሊቃወም መጥቷል፤ "ኪዳን ሻሪዎች" ይለናል። "እነዚህ ለሱ ብቻ ወታደር ሊሆኑ ዓለምን በመተው ከእግዚአብሔር ጋራ ኪዳን ከገቡ በኋላ ወደ ዓለም ተመልሰዋል፤ ለእግዚአብሔር ያደረጉትን ኪዳን ሽረው የምድራዊያን ወታደሮች ሰለ ሆኑ (51ᴬ) በምድር ላይ መዓት ይመጣል" ይላል። እገረ ገዢዎቹም (የግብር) ድርሻችንን ለራሳቸው ሊያደርጉ ነገሩን ይሰሙታል። እንግዲህ እርዱን፤ ይህ ነገር የሚገደው እኛን ብቻ አይደለም፤ እናንተንም እንጂ፤ የተነሣው በሁሉ ላይ ነው።

እንዳንዶቹ ከሳሾቹን እንዲህ ሲሉ ተጣሏቸው፡ "እናንተንም እኛንም ልታስጠሉን ይህችን ጭቅጭቅ የጐተታችኋት እናንተ እንጂ እሱ አይደለም። ይህችን የእቋሙን እውነትነት ማን ሊያስተባብላት ይችላል? ምክንያቱም (ሁሉም ነገር) በእርግጥ እሱ እንደሚለው ነው።"

ደግሞ ብዙዎች ዜናውን ከከሳሾቹ እየሰሙ ወደ ቅዱሱ እየመጡ የሕይወትን ነገር ይማሩ ነበረ። ንጉሡም ነገሩን እንዲያጣሩ (52ᵁ) ከራሱ የድንኳኑ ካህናት ውስጥ መጽሐፍ ዐዋቂዎችን ወደሱ ላካቸው። እነሱ ስለ ማንኛውም፡ ስለ ድንግልና፡ ስለ ጋብቻ፡ የሃይማኖተኛ ሕይወት እንዴት እንደሆነ፡ የፍች ኑሮ እንዴት እንደሆነ፡ የክህነት ማዕረጎች እንዴት እንደሆኑ፡ (የመንፈሳዊ) አረኞች ሥራቸው እንዴት እንደሆነ፡ (የመንፈሳዊ) መንጋዎች ተግሣጽ እንዴት እንደሆነ፡ ዓለምን በመተው ጌታን የመከተል ምንኩስና እንዴት እንደሆነ ይጠይቁታል። ማናቸውንም ነገር እስከተቻላቸው ጠየቁት፤ እሱም የጠየቁትን ሁሉ እያስረዳ፡ ጥቅሙንም በእጥፍ እያደረገላቸው በልባቸው ውስጥ እስኪያበራ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ መለሰላቸው። በመጽሐፍ ቃል ያልተስማሙ ወደ እሱ እየመጡ (52ᴬ) ይነግሩትና ባልተግባቡት ላይ እውነቱን ነገር ያሳያቸዋል። እነሱም ከሚነግራቸው ተረድተው እየታረቁ በየቀኑ ወደሱ ይመጡ ነበረ። ሙያው በሰቀላው ሰፈር ሆነ።

እንድ ቀን ቅዱሱ እንዳስለመደው ቁጭ ብሎ ሳለ፡ ብዙ ሰዎችና ካህናትም አብረውት ሳሉ፡ እንድ ሰው እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ "አባ፡ በሥላሴ የማመን ሃይማኖትን አስረዳኝ። እንድ ሰው፡ አብ ፀሐይ ነው፡ ወልድ ብርሃኑ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ ሙቀቱ ነው ስል ሰምቶ ተጣላኝ። የምሰውን ልክ አይደለም አለኝ። ትክክለኛውን ንገረኝ ብለው መንገሩን እምቢ አለኝ። (53ᵁ) ስለዚህ ወዳንተ መጣሁ።" ቅዱሱ፡ "ወደዚህ እንዲመጣ ሂድና ጥራው" አለው። "እይመጣልኝም" አለ። እዚያ ከነበሩት እንዳንዶቹ፡ "(አባባሉ) ምን የሚያጣላ ነገር አለበት? ጥሩ ነገር ነው" አሉ።

---

89. መንኩሰው ከሞላ ቤታቸው የሚኖሩ መኳንንት፡ መሳፍንት፡ ልዑላንና ልዑላት ብዙ ነበሩ። ምንኩስና ለነሱ ከጸታዊ የግብረ ሥጋ መለየት እንጂ ዓለምን መንኖ መሄድ አይደለም።

ቅዱሱ እንዲህ አላቸው፤ "አስቲ እናንተ ንገሩኝ፤ ብርሃንና ሙቀት ከሌሰባት ፀሐይ ማለት ምድንነው? እግዚአብሔር (ፀሐይን) የፈጠራት በሞቃት ብርሃን ውበት ነው። ሶስት ትሏታላችሁን? እንደምናየው አንድ አይደለችምን?" አነሱ÷ "በል÷ ንገረን" አሉት። እንዲህ አላቸው፤

> እኔማ "እብ የእውነት ፀሐይ ነው÷ በህላዌው ፍጹም÷ በሁሉ ቦታ የሞላ ነው፤ ወልድም እንደወለደው እንደ አብ የእውነት ፀሐይ÷ (53ᴬ) በህላዌው ፍጹም ነው፤ መንፈስ ቅዱስም እሱን እንዳወጣው እንደ አብ የእውነት ፀሐይ÷ በህላዌው ፍጹም ነው" አላለሁ። የቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነት (ይህ) ነው--ከብርሃን ብርሃን÷ ከአምላክ እምላክ÷ ከጌታ ጌታ።[90] እንዱ ዘንድ የሌለ (ከሶስቱ) ለሌላው (ብቻ የሚሆን) ሌላ ህላዌ የለም። ከእንዱ ሙሉነት (የተቀነሱ) ለሌላው የሚሆኑ ክፍሎችም የሉም። አብ የወለደ÷ ወልድ ከአብ የተወለደ÷ መንፈስ ቅዱስ ከእብ የወጣ የአብና የወልድ መንፈስ ይባላሉ--ሶስት ህላዌዎች÷ ሶስት ገጾች። ሶስቱም በመለኮት÷ በክብር÷ (54ᵁ) በኃይል፤ በእገዛዝ÷ በችሎታ÷ በሥልጣን÷ በፈቃድ÷ በሥራ እኩሎች ናቸው።[91]

ይኸንን እምነት ስምተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ልባቸው ጭማሪ ወይም ቅነሳ በሌለበት በሶስትነት ህልው ለሆነው (አምላክ) እየተገዛ አመሰገኑት። እንደ ቤተ ክርስቲያን መምህሮች የግብራቸው ውበት የሰማይ አባታቸው ይመሰገናል[92] ያለው የጌታ ቃል በሱ ላይ ተፈጸመ።

ንጉሡ የቅዱሱን የትምህርት ውበት ጥንቃቄውን ሲረዳ ቅዱሱን ከፊቱ (54ᴬ) በሚያቆምበት ዕለት በሰፈሩ ያሉት መነኮሴዎች ሁሉ እንዲሰበሰቡ ዓዋጅ እንዲነገር አዘዘ። ጳጳሱን አባ ሚካኤልንም[93] ጠራው። የድንኳኑን ካህናትና መጻሕፍትን በማወቅ የተሾሙትን ሁሉ ጠራቸው። ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ መነኮሴዎች ተሰበሰቡ። አነዚያም ከሳሾች አብረውት ነበሩ፤ እነሱን ሁሉንም ሰብቻቸው ከፊቱ አቆማቸው። ቅዱሱንም ከፊቱ (እንዲቆም) አስገባውና ከደቀመዛሙርቱ ጋራ ሰብቻው አቆመው። ቅዱሱ አባታችን ስጉሡ ለነፍሱ በሚገባት ቅድስት ቡራኬ ስላምታ ሰጠው።

ከዚያ÷ ንጉሡ ቅዱሱን÷ "የመጣህበትን ጉዳይ ተናገር" አለው። ቅዱሱ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ፤

---

90. ጸሎተ ሃይማኖት።

91. ከላይ ጎዳግ ቁጥር 83ን ተመልከት።

92. ማቴ 5፡ 16።

93. በአፄ ይሥሐቅ ጊዜ ጳጳሱ አባ በርተሎሜዎስ ነበሩ። የሚባለው እባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ከኢጲስ ቆጶሱ ከአባ ዮሐንስ ጋራ ወደኢትዮጵያ የመጡት አፄ ይሥሐቅ ከሞተና አፄ ዘርአ ያዕቆብ ከነገሠ በኋላ በ1431 ዓ. ም. እንደሆነ ነው። Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Mashafa Berhān), CSCO*, vol. 261/51, pp. 132 and 134. ደቂቀ አስጢፋኖስ ግንኙነት የነበራቸው ግቢያቸው በራራ (ደቡብ) ከነበረው ከአባ ገብርኤል ጋራ ነበረ። ግን አባ ሚካኤል ቀደም ብለው ለመምጣታቸው ይኸና ሌሎች ምንጮችም ያመለክታሉ።

አስረው አመጡኝ እንጂ እዚህ አመጣጤ በፈቃዴ (55ᵘ) አይደለም። ግን ከፊትህ እንድቆም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኗል፤ እኔም ይሽንን ወድጀዋለሁ። ሆኖም እዚህ የሚያመጣኝ ከሥጋ ግዛት የሚፈለግ የሥጋ ጉዳይ የለኝም። ያለኝ ሌሎቹ ወንድሞች ከእኔ ጋራ የሚካሰሱበት የመንፈስ ጉዳይ ነው። ሕጉን ለመረዳት የልብህን ዓይኖች እግዚአብሔር ያብራ፤ በሥራ ላይ እንድታውለውም ጎይል ይስጥህ። እግዚአብሔር ፍርዱንና እውነቱን በአንተና ነገሬን በሚሰሙት ሁሉ ይሹም። እንግዲህ ቃሌን ስማኝ።

እግዚአብሔር፥ ስሙ ይባረክና፥ (55ᴬ) በሥራው ሁሉ የተባረከ ነው። ስማይን አቁሞ ምድርንም መሥርቶ በውስጣቸው ለሥጋ የሚገባ ሕይወታችንን የምናቆይበት የተድላ በረከት አዘጋጀ። በስማይ ጠፈር ላይም ብርሃኖችን--ፀሐይን፥ ጨረቃን፥ ኮከቦችን--ጊዜዎችን፥ ሰዓቶችን፥ ሳምንቶችን፥ ወራቶችን፥ ዓመቶችን እንድናውቅባቸው ሾማቸው። በተመረጠበት ዓመት ለሚገለጠው የዓለም ምስጢር ምሳሌ አደረጋቸው።[94] ጌታ ዝግጅቱን ሁሉ ሲጨርስ በስድስተኛው ቀን ሰውን፥ ከልጁ (ከማርያም) ሰው ሆኖ ለሥራው በሚገለጽበት አምሳል፥ ፈጠረውና "አዳም" አለው።

(56ᵘ) በስባተኛዋ ቀን አረፈባት፤ ባረካት፥ቀደሳትም። ባደረገው ቀጠሮ ጊዜ ጽዮን ስትሞላና አዲሱ የዓለም አባት ሲገለጽ ልበ ግዙሮች ከእሱ ጋራ እንዲያርፉ ለሚሰጠው ጸጋ ምልክት ሲሰጥ የሁል ጊዜ ኪዳን አደረጋት።[95] በሰው ልጅ ነፍስ ጠፈርም ሾማትና በምክሩ እንዲኖር አዘዘ።

ሁለት ማእዶችም ዘረጋለት--አንድ የመንፈስ፥ አንድ የሥጋ። መንፈስ ቅዱስን ለነፍሱ ምግብ፥ የገነትን ተድላ ለሥጋው (ሰጠው)። የሰው ልጅ ይኸ ህብት በእጁ እያለለት ለነፍሱ ሞትን እስኪያመጣ ድረስ፥ በጠላት ምክር ተደለለ። (56ᴬ) ጌታም ጸጋውን ገፈፈውና በምክሩ ሳጥን ደበቀው። ሰውም ራሱና ዘሩ ሁሉ በሐዘን ማጥ ሰጠመ። ልጆቹ መሬት ስለክፋታቸው እስከታጉረመርም ድረስ የሞት እሾክ አፈሩ። እግዚአብሔር ኪዳኑን ለመጠበቅ ለጽድቅ ተከል ከኖኅና ከልጆቹ በቀር ማንንም ሳያስተርፍ ብዙዎቹን በጐርፍ ግሠጻ አጠፋቸው።

ደግሞ ከትውልድ በኋላ ሲበዙ ግምብ ገነቡ። እዚያም ቋንቋቸውን ከፋፈለው።

ደግሞ ከፈጣሪ ይልቅ (57ᵘ) የጃቸውን ሥራ በማስበለጥ ለአማልክት ለመሠዋት ዳከሩ። እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠና በዘሩ የምድር ሕዝቦች ሁሉ እንዲባረኩ ከሱ ጋራ ኪዳን አደረገ።

ከዚያ ደግሞ የሰዶም ሰዎች አስቈጡት፤ በላያቸው ላይ እሳት አዘነበባቸው። ሎጥንና ልጆቹን ከመጥፋት አዳናቸው።

---

94. "በተመረጠበት ዓመት የሚገለጠው የዓለም ምስጢር" የሚሉት ወይ ክርስቶስ የተወለደበትን፥ ወይም ክርስቶስ እንደገና ሲመጣ ከጻድቃኑ ጋራ አንድ ሺህ ዓመት የሚነግሥበትን፥ ወይም ከምጽአት በኋላ ያሰውን የዘላለሙን ኑሮ ነው።

95. ስለ ደብረ ጽዮን መግቢያውን ተመልከት።

ግብጻች እስራኤላውያንን በግድያና በመራር አገዛዝ አሰቃይዋቸው::[96] እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሴ እጅ ረዳቸው:: ወደ ምድረ በዳም አወጣቸው፤ የግብጽን ሰዎች ግን ከባሕር አሰጠማቸው:: ለእስራኤል ሕጉን እንዲጠብቁ አሪትን ሰጣቸው:: እነሱ ግን (57ᴬ) ልባቸውን ወደ ግብጽ እሥሩ:: ባለማመን አስቆጡት-- በምድረ በዳ እስኪፈጃቸው ድረስ:: የተረፉትን ለአብርሃም ከማለለት ምድረ ርስት አገባቸው::

ቀጥሎ ከትውልድ በኋላ ዳዊትን ነግሦ ሕዝቡን እንዲጠብቅ በእውነተኛ ምርጫ ጠራው:: መጨረሻ ለሌለው (መንፈሳዊ) መንግሥቱ አርአያ አደረገው:: እሱም እስከአንቀላፋ ድረስ አገለገለው::

እስራኤል ግን ሕግን ቸል በማለትና ስለ መምጣቱ የሚያበሥሩትን ነቢያት በመግደል እሱን ማስቆጣቱን አንተውም ቢሉ የባቢሎንን ንጉሥ ላከባቸው:: እሱም አጋዛቸው፤ (58ᵁ) ከሀገራቸውም አፈለሳቸው:: ባደረገው ቀጠሮ የሚፈጽመውን ኪዳኑንም በማስታወስ በደላቸውን ይቅር ብሎ ከሮ ዓመት በኋላ እንደገና ወደ ምድራቸው መለሳቸው:: እስራኤልን ለበዓሉ ዕለት በብዙ መግለጫ ጋበዛቸው:: የግብጥው ጊዜ ሲደርስ በአስደናቂ መገለጥ ያለሰው ዘር ከንጽሕት ድንግል የዳዊት ልጅ[97] ሰው ሆኖ ከዓለም በፊት ያዘጋጃትን ምክሩን ፈጸማት::

ፈጣሪ እራሱ እንጂ ሌላ ሳልፈጠረው ፍጡሩ ሕይወት በመስጠት የሥራውን ውበት ገለጸ:: (58ᴬ) የተጋበዙ እስራኤል ግን ቃሉን ችላ አሉ::[98] (እንዲያውም) ቀኑበት፤ ሰደቡት፤ ስሞት እስኪያደርሱትም አሰቃዩት:: ያለኃጢአት በተፈጸመችበት የሞት ሕመም ሰይጣንን አድድኖ በጥፋቱ የታደነ አዳምን በትክክል ፍርድ ነጠቀው::

ጌታ (ሁሉንም) ፈጽሞ የሞት እንቅልፍ በመስቀሉ አልጋ ላይ እንቀላፋ:: ደምና ውሐ እስኪፈሰው ድረስ ጐኑን በጦር ወጉት:: በዚህም ቤተ ክርስቲያን ታነጸች:: የነፋስና የነርፍ ሞገዶች ማናወጥ በማይሆንላቸው የሰንፔር አልማዝ በሆኑ ቅዱሳን ሐዋርያቱ ላይ መሠረታት::[99] (59ᵁ) በሥጋው ጠፍሯት ጨረሰና በጠፈሩ ላይ ከራሱ ብርሃን የሥርዓት ሕግ ብርሃኖችን ተከለ:: በድግሱ ቤት የተቀመጡት በብርሃኑ እንዲደሰቱ፤ በሌሊት እሾህ እንዳይደናቀፉ የዕለቱን ሰዓታት፤ ዓሥራ ሁለቱን ጊዜያት፤ በብርሃናቸው እንዲያዩ

96. ታሪኩ የሚናገረው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሚሠራለትን ቸርነትና የሰው ልጅ ግን መልሶ መላለሶ በደለኛ መሆኑን ስለሆነ፤ እስራኤላውያን ወደ ግብጽ መውረዳቸውንና የወረዱበትን ምክንያትና በደላቸውን ሳይተርክ፤ ታሪኩን በማሳጠር ድንገት "ግብጻች እስራኤላውያንን በግድያና በመራር አገዛዝ አሰቃዩዋቸው" ያለው በአንዳች ስሕተት ምክንያት መሆን አለበት:: ታሪኩ ያጠረው እጂ የገባውን መጽሐፍ የቀዳው ሰው መሥመሮች ቢዘል ነው::

97. ከቅድስት ድንግል ማርያም ማለት ነው:: ከዘመኑ የቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ጋራ ሊተያይ በአስጢፋኖሳውያን ዘንድ የማርያም ስም ብዙ አይታይም::

98. ሉቃ 14: 17-24::

99. ማቴ 7: 25:: (ስንፔር በአንግሊዝኛ sapphire ነው::)

የማይጠልቁ ከከቦችን ፈጠረ። ቃሉን ችላ ያሉ እስራኤላውያን ግን ትንቢትን፥ ክህነትን፥ መንግሥትን ወስዶባቸው ለቤተ ክርስቲያኑ ሰጣት።[100] ለሕጉ የሚታዘዙት የዚህን ዓለምና የሚመጣውን ዓለም ሕይወት በእጥፍ ድርብ (59^ሀ) እንዲያገኙ በውስጧ የጥቅም ዋጋ እኖረ።

ስለዚህ ንጉሥ ሆይ፥ እኔም ፈለጉን ለመከተል ራሴን በመስጠት በዚህ መገዛት ስር ለመዋልና ራሴንም አፍአዊ ከሆነ የሌሊት ስሕተት[101] እንድድን ባወጣልኝ ሕግ መሠረት ራሴን ለማንጻት ወደድኩ። ከዚያ፥ እንደ ፍላጎቴ (ለመኖር) የሚወዱ ባልደረቦች አገኘሁ። "የእርሻውን ጌታ[102] የአገዛዝ ትእዛዝ ንገረን" አሉኝ። እሱ በሕማሙ እንደጠቀመኝ ልጠቅማቸው ወደድኩ፤ በከንቱ (ያለዋጋ) ከስጠኝ እንድሰጥ አዞኛልና።[103] (60^ሀ) በቤቱ ጠፈር ውስጥ ስለተሰቀሉት ብርሃኖች ትእዛዝ ስመክራቸው በሕጉ ፈለግ መኖር ጀመሩ።

ከዚያ በኋላ ሌሎች ወንድሞች "የሀገራችን ትምህርት ያልሆነ ታስተምራለህ" ሲሉ በጥል ተነሡብኝ። "የዚች ሀገር ትምህርት ምንድነው? እንዴትስ የሌላ ነው? በክርስቶስና በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ከሆነው ሁሉ በቀር ሌላ አላውቅም" እልኳቸው። በዚህ ምክንያት በቁጣ ተነሡብኝ፤ አገረ ገዢዎች ድረስ ወስደው እዚያ በእንደዚህ ያለ ነገር ሕግ ሳይጠቅሱ ከቁም ነገሩ ውጭ ሞገቱኝ። እቋሜና አቋማቸው (60^ሀ) በቤተ ክርስቲያን የሕጎቿ መጻሕፍት እንዲፈጸም ተማፀንኩ። ይኸንን ቸል ብለው በእስራት እዚህ አመጡኝ። ይኸንንም ወድጀዋለሁ፤ ምክንያቱም የክርስቶስ የመንግሥቱ ወንጌል በሁሉ ቦታ የሰፈነች ናት፤ መጽሐፍ፥ "እንግዲህ ንጉሦች አስተውሉ፤ መሬትን የምትገዟት ሁሉ ተገሠጹ፤ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ"[104] ይላል።

ንጉሥ ሆይ፥ ለእግዚአብሔር መገዛት ማለት ሕጉን በመፈጸም ራስክን እየጠበቅህ ሕዝቡን በእውነትና በትክክል ማስተዳደርና በቅዱስ ሲኖዶስ እንደተሠራው ሥርዓት፥ (61^ሀ) ካህናት መንጋውን በትክክል እንዲጠብቁ፥ ሕዝቡም እንደተደነገገው ለእረኞቻቸው እንዲታዘዙ፥ መነኮሴዎችም ፍጹም ለመሆን ለሚፈልጉ ወንጌል እንዳዘዘው ራሳቸውም በስጡት (ቃል) እንዲቆሙ ሁሉንም በየሥርዓቱ ማደራጀት ነው። እንዲህ ሲሆን እግዚአብሔር ባንተና በመንግሥትህ ስር ባሉት ሕዝብ ሁሉ ይደሰታል፤ በጠላታችሁ ላይ

---

100. እባ እስጢፋኖስን ከንጉሡ ችሎት ያስመጣቸው ክስ "ከእስራኤል ስም የክርስትና ስም ይበልጣል" ማለታቸው ስለሆነ፥ ያንን በራሱ በንጉሡ ፊት ለመግለጥ የተመቸ ዕድል እግኝተዋል።

101. "ሌሊት" የሚያመለክተው በቤቱ ጠፈር ውስጥ የተሰቀሉት ከዋክብት የሚሰጡት፥ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ብርሃን የሌለበትን ሕይወት።

102. ማቴ 13: 3 ላይ "ዘሪ ሊዘራ ወጣ" ያለውን ሲያስታውስ ነው።

103. ማቴ 10: 8 (ያለዋጋ፥ በነፃ)።

104. መዝ 2: 10-11።

ድል ታገኛላችሁ። እግዚአብሔር ሕጉ ሲጠበቅ በናንተ ምትክ ይወጋላችኋል። ሕጉን ካልጠበቃችሁ ግን ከጠላታችሁ አያለበልጣችሁም። አንድ ጊዜ እናንተ ታሸንፋላችሁ፤ ሌላ ጊዜ እነሱ ያሸንፋሉ--ልክ በሌሎች (61ᴬ) ሕዝቦች ሁሉ እንደሚሆነው።

አሁንም በፊቱ እንድትመለገን የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቅ፤ የዚህ ዓለም ተድላ ጎላፊ ነውና፤ ሐዋርያው እንዳለው፥ "ከሥጋ የሆነ ሁሉ እንደ ሣር ነው፤ ፍሬውም ሁሉ እንደሣር ፍሬ ነው። ሣሩ እንደደረቀ ፍሬው ይረግፋል። የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል።"[105]

ስለሚሚገቱኝ ወንድሞችም፥ ሕጉን ተከትለህ ፍሪድልን፤ እግዚአብሔር ለነፍስህ መጠጊያ ይሁናት።

ቅዱሱ ተናግሮ ሲጨርስ፥ ንጉሡ መነኮሴዎቹን፥ "እናንተ ከሱ ጋራ ሙግት ያላችሁ፥ ተናገሩ" አላቸው። ከዚያ፥ (62ᵁ) ያ ውሸት ልማዱ ሲኖዳ የሚባል የከሳሾቹ አለቃ (እንዲህ ለማለት) አፉን ከፈተ፤ "አንተን እስራኤላዊ አይደለም ስላለ፥ እነሆ እኔ ለመንግሥትህ ቀናተኛ ሁኜ ካንተ እንዲያደርሱኝ ጠየቅሁ።"

ንጉሡ፥ "ይህ ስድብ ካንተ (የመጣ) ነው፤ የክርስትና ስም ይበልጣል እንዳለህ ነገሩን ተረድተናል። እኛም ትምክህታችን በክርስትና ነው፤ ይልቅስ ከመጀመሪያው ጥል ስለጀመርክበት ጉዳይ ተናገር" አለው።

ሰውየው፥ "ብቻዬን ስለ ሁሉ አልናገርም፤ የሚጣላው ሁላችንንም መነኮሴዎችን ነው" አለ።

ንጉሡ፥ "ሲረዳህ (62ᴬ) የሚፈልግ ካለ አብሮህ ይናገር፤ ከሌለ በጀመርከው ጨርስ" አለው።

ሰውየው "በሁሉም ላይ የሚደርሰው ይደርስብኛል እንጂ ለኔ የግሌ ጉዳይ የለኝም" አለ።

ቅዱሱ ለዚያ ሰው እንዲህ አለው፤ "አንተ መጀመሪያ እዚህ እስክንመጣ ድረስ ስለ ሁሉም ሆነህ ተነሥተህ ዛሬ ጉዳይ የለኝም ትላለህ? ታዲያ ለምንድን ነው ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ ትቼ መንኖለሁ የምትለው? ተገነዝክ፥ ታጠንክ፤ በቤተ ክርስቲያን ፊት፥ ከዛሬ ጀምሮ ራሴን ለእግዚአብሔር ሰጥቻለሁ ብለህ ከእግዚአብሔር ጋራ ቃል ኪዳን ገባህ። ከመሐላና (63ᵁ) ከኪዳን በኋላ ለግዛትና ንብረትህ ያልሆነውን ለራስህ ለማከማቸት እንዴት ወደ ዓለም ትመለሳለህ?"

ሰውየው፥ "ይኸን የምትለውን ሁሉ ለኛ ለመነኮሴዎች ማን ከለከለን?" አለ። ቅዱሱ፥ "እነሆ ጌታን ለመከተል ከዓለም የተለየ መነኮሴ ግንዘብ እንደሌለው የእግዚአብሔር ሕግ ይናገራል" ሲለው ሰውየው ምስክር ስጠኝ" አለ። ብፁዑ፥

እነሆ ምስክሬ ጌታ ሕይወትን ለለ መውረስ ለጠየቀው ባለጸጋ፥ "ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ ሂድና ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ፤ ለደኻ

105. 1 ጴጥ 1: 24-25።

ሰጥተህ ና ተከተለኝ"[106] እንዳለው ቅዱስ ወንጌል ምስክሬ ነው። (63ᴬ) ደግሞ፥ "ለኔ ለመጠመድ የሚፈልግ ራሱን ይጥላ፤ በርትቶም የሞቱን መስቀል ተሸክሞ በየቀኑ ይከተለኝ"[107] ብሏል። ደግሞ "ከገንዘቡ ሁሉ የማይላቀቅና የራሱ የሆነውን ሁሉ ያልከዳ ለኔ የተገባ አይሆንም፤ ለኔ ሊጠመድም አይችልም"[108] ብሏል። ደግሞ "ዕርፍ ይዞ ወደ ኋላ የሚሄድ የለም፤ ምክንያቱም መንግሥተ ሰማያት ቀጥታ ናት"[109] ብሏል። ሐዋርያው ጳውሎስም፥ "በሥጋ ያሉ ሁሉ እግዚአብሔርን ሊያስደስቱት አይችሉም"[110] ብሏል። ደግሞ፥ "ከዚህ ዓለም ኑሮ ከክርስቶስ ጋራ ከሞታችሁ በኋላ እንዴት (64ᴮ) አንደገና በሕይወት እንዳሉት ወደዚህ ዓለም ትመለሳላችሁ? ምክንያቱም አትዳስሱ፥ አትንካ፥ አትቅመስ፥ ይኸ ለጥፋት ነው"[111] ብሏል።

ያ ሰው፥ "ይኸ የምትለው ለክርስቲያን ሁሉ የተሰበከ ነው፤ ለመነኮሳት ለብቻችን አይደለም" አለ። ቅዱሱ እንዲህ አለ፤ "ለክርስቲያን ሁሉ በየሥርዓታቸው እንዲኖሩ በሲኖዶስ ተሠርቷል--ምእመናን በሚስቶቻቸው እንዲጸኑና ልጆቻቸውን በእውነት እንዲያሳድጉ፥ ካህናትም ለመኖሪያቸው ዓሥራትና በኵራት እንዲወስዱ አዟል። ይህ ለናንተ ዓለምን በመተው (64ᴬ) ከጌታ ጋራ ኪዳን ለገባችሁት መነኮሴዎች ምስክር ነው።" ሰውየው፥ "እኔ ለክርስቲያኖች ሁሉ ከሚሆነው የተለየ ሌላ (ሕግ) የለኝም" አለ።

የንጉሡና የንጉሡ መነኮሴዎች ፍርድ

ንጉሡ ካህናቱም መነኮሴዎችም ሁሉም በሰሙት እንዲፈርዱ አዘዘ። ሁሉም፥ "(ሲኖዳ) ምንኮስናውን ክዷል፤ ተማሪ ይሁን እንጂ ማስተማር አይገባውም። ከነልጆቹና ከነደብሩ ለዚህ ቅዱስ ይስጡት፤ ምክንያቱም እሱ ነገሩ እውነት፥ ምስክራውም ትክክል ነው" ሲሉ ፈረዱ። ጳጳሱም በዚህ ፍርድ ተስማማ።

ከዚህ በኋላ፥ (ንጉሡ ሲኖዳን) ከነልጆቹና ከነደብሩ ለዚህ ቅዱስ እንዲሰጡት አዘዙ። ቅዱሱ ለንጉሡ፥ "እኔ ሹመት አልፈልግም፤ እውነትን እንዲያስተምረው (ላመነኮሰው) መምህር ስጠው። (65ᵁ) ግን (ከላሾቹ) ወእግዚአብሔር ሕግ እንዲቆሙ፥ ለእግዚአብሔር መጠመድ የሚፈልገውንም እንዳይከለክሉ ትእዛዝ ስጥ" አለው።

ከዚያ፥ ንጉሡ እንዲህ የሚል ዐዋጅ እንዲያውጁ ትእዛዝ ሰጠ፤ ይኸንን መነኮሴ "አርቶዶክስ አይደለም፤ የሚያስተምረውም ሕጋዊ

106. ማቴ 19፡ 21።
107. ማቴ 16፡ 24፤ ሉቃ 9፡ 23።
108. ቀጥታ ጥቅስ ሳይሆን የማቴ 10፡ 37 ሐሳብ ይመስለኛል።
109. ሉቃ 9፡ 62።
110. ሮሜ 8፡ 8።
111. ቈላ 2፡ 20-21።

ያልሆነ ነው" ብለው በክለ እዚህ (ድረስ) አመጡት። አሁን ግን እኔም የድንኳኑ ካህናትም ነገሩ እውነት፥ ትምህርቱም ትክክል እንደሆነ ተረዳን፥ መረመርንም። የሚሰብከው እንደ ሐዋርያት የወንጌል ትምህርት ነው። አሁንም ተቀበሉት፤ እኛም ትምህርቱን ወደነዋል። (65ʰ) የትምህርቱን ፈለግ ለመከተል የሚፈልግ ሰው ሁሉ፥ ከዚህም ሆነ ወይም ከሌሎች አገሮች (ቢሆን)፥ አይከልክል።

ከዚያ በኋላ፥ ንጉሡ ቅዱሱን ገንዘብ ለራሱ እንዲወስድ ጠየቀው። ቅዱሱ፥ "እኛ ገንዘብ አንፈልግም፤ ጌታ ያዘዘው የዕለት ምግባችን ይበቃናል። ግን ከአግዚአብሔር ዘንድ (ዋጋህን) እንድትከፈል ለድኾችና ለምስኪኖች ስጠው" አለው።

ከዚያ፥ በሰላም አሰናበተው። በንጉሡ ሰፈር እንደተነገረው ዐዋጅ በሸራም እንዲነገር ንጉሡ ወታደሮቹን አብሮ ላካቸው። ቅዱሱ በየካቲት ፳፩ ቀን ከንጉሡ ሰፈር (66ᵇ) ተነሥቶ፥ ሚያዝያ ፲፫ ቀን ከመኖሪያው ደረሰ።

ከዚያ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሺሬ ሹም ንጉሡ እንዳዘዘው በግዛቱ ስር ያሉትን መነኮሳት ጉባኤው ትልቅ እስኪሆን ድረስ ሰበሰባቸው። እነዚያ የንጉሡ ወታደሮች አንደታዘዙት መልእክቱን እንዲህ ሲሉ አስታወቁ፤

እነሆ ይህ "ትምህርቱን ጥሩ አይደለም" ብላችሁ እኔ ድረስ እስክታመጡት የተጣላችሁት መነኮሴ፥ አሁን እኛ እርግጥ የወንጌል ስባኪና የቅዱሳን ሐዋርያት ተካፋይ እንደሆነ ተረድተናል፤ መርምረናልም። (66ʰ) ከናንተ ማህል እሱን የተቃወሙት እነሆ እነሱ በትክክል ፍርድ ተረትተዋል። አሁንም ከቻላችሁ ፈለጉን በመከተል እሱን ምሰሉ። እናንተ ካልቻላችሁ ሊከተለው የሚወደውን አትከልክሉት። በሥላሴ ለለ ማመንና በሰንበትና በበዓሎች አከባበር በቅዱስ ሲኖዶስ እንዳለው ሥርዓት በግብር እሱን ምሰሉ።

ብዙዎች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ይኸንን መልእክት በመስማት ተደሰቱ። በሥጋቸው ድካም የተደለሉ ግን ብፁዕ ሙሴን እንደተቃወሙ የግብጽ ሰዎች ቅዱሱን ያንጓጥጡት ነበረ። (67ᵘ) ሁሉም በቅናት ጣር እየቈሰሉ ወደየደብራቸው ተመለሱ። ቅዱሱም ወደ ማደሪያው ተመለሰ። በቅዱሱ ትምህርት ስር ያሉ አብያተ ክርስቲያን በሰላም ኖሩ።[112]

አዲስ ንጉሥ (እዬ ዘርአ ያዕቆብ) ነገሠ፥ ክሱም ታደሰ

ከዘመን በኋላ፥ በሀገሪቱ ላይ በፊተኛው (ንጉሥ) ምትክ ሌላ ነገሠ።[113] እነዚያ መነኮሳት ሲሰሙ (መቢጠጫ) ጥፍራቸው ተናወጠ። ደብሮቹ ሁሉ በብፁዑ

112. ታላላቅ ደብሮች በስራቸው የሚኖሩ ንኡሳን ገዳማት ነበሯቸው። የአባ እስጢፋኖስ ገዳም ደብረ ገርዜንም ትልቅ ደብር እንደነበረ ይኸና ሌሎችም ምልክቶች ይመስክራሉ። በተጨማሪ ከታች በጎዳግ ቁጥር 159 ስር ያለውን ተመልከት።

113. በተለይ የአባ አስጢፋኖስ ገድልና ስንክሳራቸው የነገሥቱን ስም ከማንሣት ይቆጠባሉ፤ ሆኖም "የፊተኛው (ንጉሥ)" የሚለው አዬ ይሥሐቅን ነው፥ በአባ አበክረዙን ገድል ተገልጧል። አዬ ይሥሐቅ ሲሞት በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ስለ

ላይ ለመዶለት እንዲሰበሰቡ ተቃጠሩ። ከዚያ፥ የሀገራቸው ገዢ በሌለበት ትልቅ ጉባኤ አደረጉ። እዚያ በክፋት ተስማምተው ከብፁዕ አስጢፋኖስ ቃል የቅዱስ ወንጌልን ሕግ (67ᴬ) የሚማሩትን ሁሉ ሰላምታ እንዳይሰጧቸው፥ በእንግድነታቸውም እንዳይቀበሏቸው፥ ደክመው በእጃቸው ከሠሩትም ምንም እንዳይገዙ ቃል ኪዳን ተገባቡ።

ይህችን ምክር (ማንም) እንዳይተዋት እንዲህ ሲሉ በመሐላ አገዟት፥ "ይህቺን ኪዳናችንን የተዋት ዲያብሎስ ከቅዱሳን መላእክት እንደተለየ፥ ይሁዳም ከንጹሐት ሐዋርያት ማህል እንደተለየ የተለየ ይሁን።" እንዲህ አድርገው ራሳቸውን አጥብቀው ረገሙ። ስለነሱ ሁሉ ሆኖ በንጉሡ ዘንድ ነገር የሚፈጅ በላያቸው ዓቃቢ (ጠበቃ) ሾሙ። እነሱም ለመንገድ ስንቅ (68ᴮ) እንዲያዋጡ (ተስማሙ)። ዱለታቸው እንድትፈጸምላቸው በደብሮቹ ሁሉ "የሌሊት" ጾም ዐወጁ--እስራኤላዊ ናቡቴን ለመግደል (የቀን) ጸሎት ያወጀችውን ኤልዛቤልን ለማስወደድ።[114]

ከዚህ በኋላ፥ ብፁዑን ለመግደል ለማበረታታት የምታሳምን፥ ሁለንተናዋ ውሸት የሆነ ጦማር ለንጉሡ ጻፉ። በውሸታቸው ጦማር ላይ (እንደ) ርእስ፥ *"መጽሐፈ ብርሃን ወመጽሐፈ ጽልመት"* ("የብርሃን ጦማርና የጭለማ ጦማር") የሚል ጻፉባት።[115] ሁሉንም እንደዚህ ፈጽመው ጦማራቸውን በዚህ ዓቃቤ ነገርነት በራሳቸው ላይ በሾሙት እጅ ወደ ንጉሡ ላኳት፤ (መልእክተኞቹ) አድርሰው ለንጉሡ ሰጡት።

ንጉሡ ጦማሯን (68ᴬ) እነበባት፤ በስሚም ተደነቀ። ያመጣለትን ሰው ጠየቀው፤ *"መጽሐፈ ብርሃን ወመጽሐፈ ጽልመት* (የብርሃን ጦማርና የጭለማ ጦማር) የሚለው ምንድነው?" አለው። (ሰውየው) የልባቸውን ሐሳብ ተረጐመለት። እንዲህም አለው፤ "የጭለማ ጦማር ያሉት ማንም ሳይሾመው በሀገራችን ላይ ጳጳስ ስለሆነው ስለ አስጢፋኖስ ነው። የብርሃን ጦማር ያሉት ለፈቃዳችን ፍላጎት የመከርናትን የምትፈጽማት ለኛ የነገሥከልንን አንተን ነው።"

ንጉሡ፥ "ስለሱ እናንተ እንደምትሉት ላይሆን፥ ትምህርቱና ምግባሩ እውነትና ኦርቶዶክስ እንደሆነች ሰምቻለሁ" አለው።

ዙፋን ውርስ ጥቂት ውዝግብ ቢኖርም እዚህ ላይ "ምትኩ" የሚለው ንጉሥ አፄ ዘርአ ያዕቆብ መሆኑን አያጠራጥርም።

114. ታሪኩ 1 ነገሥ 21፡ 1-19 ላይ ይገኛል። "የሌሊት ጾም ህወጁ" የሚለው ኤልዛቤል አስራኤላዊ ናቡቴን ለመግደል ካወጀችው የቀን ጸሎት ለማነጻጸርና ለማባስ ነው።

115. ማንኛውም የተጻፈ ነገር በግዕዝ "መጽሐፍ" እንደሚባል፥ ደብዳቤንና ጦማርንም እንደሚጨምር፥ "ጦማር" በመንፈሱ ከደብዳቤ ከብደት ያለው ደብዳቤ እንደሆነ ከላይ በጎዳግ ቍጥር 56 ስር ተነግሯል። አፄ ዘርአ ያዕቆብ *"መጽሐፈ ብርሃን"* የሚባል በውስጡ አስጢፋኖሳውያንን የሚዘልፉ ገጾች ያለበት ትልቅ መጽሐፍ ጽፏል። ርእሱን ከዚህ ጦማር የወሰደው ሊሆን ይችላል፤ Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 261/51, p. 48.

ከዚህ በኋላ፥ ንጉሡ (69ᵘ) ነገር በማጣፋጥ ወደ ቅዱሱ እንዲህ ሲል ላከበት፤ "ሰላም ላንተ ይሁን፤ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ እንደሆንክ ዜናህን አሁን ላይሆን ከመንገሤ በፊት ሰምቻለሁ። አሁንም ሃይማኖቴን ስለሚመለከት (አንድንወያይ) ወደኔ መምጣትህን አታዘግይ። ላገኝህና በሕጉ ፈለግ መሠረት (ሁሉንም) ለእግዚአብሔር ላስተካክል እወዳለሁ።"

እንዳይቀር በዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ጨምሮበታል። (ይኸም ሆኖ) ብፁዑ መሄድ አልፈለገም ነበረ። ነገር ግን መኳንንቱና መልእክተኞቹ ስለወተወቱት በስንት ጭንቅ እሺ አላቸው። ቅዱሱ ለልጆቹ እንዲህ አላቸው፤ (69ᵃ) "ለክፋታቸው ምክንያት እንዳይኖራቸው፥ ስለ ሃይማኖት (እንነጋገር) ብንለውና በእግዚአብሔር ስም ብንይዘው እምቢ አለን እንዳይሉን በሉ ኑ እንሂድ።"

አባታችን ለመሄድ መስከረም ፪ ቀን ተነሣ። በጥቅምት ፭ ቀን ከንጉሡ ለፈር ደረሰ። (ንጉሡ) ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሰው ጋራ ባለበት ጊዜ ከፊቱ አቆመው፤ ግን አላነጋገረውም። ብዙ ጊዜ እንደዚህ አደረገ፤ (ከፊቱ አያቆመ) አያነጋግረውም። ደግሞ ጠርቶ እንደበፊቱ ከፊቱ አቆመው። የሠራዊቱን ታላላቆችና መነኮሴዎችንም (ወደ ውስጥ) አስገባ። ከዚያ፥ የመንግሥቱን ጉዳይ በትጋት ማካሄድ ጀመረ።

ከንጉሡ ጋራ የመጀመሪያው ግጭት

(70ᵘ) (ራሱ ንጉሡ) በከሰለው (በአንድ ሰው) ላይ ሁሉም ፍርድ እንዲሰጡ አዘዘ። መኳንንቱ፥ ካህናቱ፥ መነኮሴዎቹ የሞት ፍርድ ፈረዱበት። ቅዱሱ ግን ዝም አለ። ንጉሡ፥ "አንተስ አትፈርድምን?" አለው። ብፁዑ፥ "አዎን፥ አልፈርድም" አለው። "ለምን?" አለው። ቅዱሱ፥ እንደዚህ አለው፤ "ምክንያቱም ለኛ ለመነኮሴዎች በሥጋ ፍርድ መደመር እርም ነው።[116] ስለ ሃይማኖት፥ ስለ መንፈሳዊ ነገር ብለህ ስላስገደድከኝ ነው እንጂ ለሥጋ ፍርድ (መሆኑን ባውቅ) አልመጣም ነበረ። የሥጋ ገዢዎች ግን በመጽሐፈ ኦሪትና በመጽሐፈ ነገሥት እንዲፈርዱ ታዟል። ያም ቢሆን (70ᵃ) በሕጉ መሠረት በእውነት ፍርድ ነው እንጂ እንደዚህ አይደለም።"

ንጉሡ፥ "የመነኮስከው መጽሐፈ ኦሪትንና መጽሐፈ ነገሥትን ጥለህ ነውን?" አለው። ቅዱሱ፥ "ስለ ስሜ፥ ቤቶች፥ ወንድሞች፥ እኅቶች፥ አባት፥ እናት፥ ሚስት፥ ልጆች፥ እርሻዎቹን የተወ ሁሉ መቶ እጥፉን ይቀበላል፤ የዘለዓለም ሕይወትም ይወርሳል[117] የሚለውን የቅዱስ ወንጌል ቃል ስምቼ ከዓለም ወጥቻለሁ" አለው። ንጉሡ የአገዛዙን ነቀፌታ ሰምቶ በቁጣ ዝም አለ።

ከ፫ ሳምንት በኋላ አንደገና ጠራውና ከፊቱ አቆመው። መነኮሴዎቹን፥ ካህናቱን ሁሉ፥ ቅዱሱን የሚከሱትንም ጭምር፥ (ወደ

116. Victor Arras, *Collectio Monastica, CSCO*, vol. 238/45 (1963), p. 6.

117. ማቴ 19፡ 29።

ውስጥ) እስገባቸው። (71^{ሀ}) ከዚህ በኋላ፥ ቅዱሱን "የመጣህበትን ተናገር" አለው። ቅዱሱ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ፤

> የመጣሁት ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ብለህ ስለጠራኸኝ ነው። ለማንኛውም ራስክን በሕጉ እየጠበቅህ ሕዝብ በእውነት እንድትገዛ እግዚአብሔር የልብህን ዓይን ያብራልህ። ነቢዩ፥ "ብርሃኑን ጭለማ፥ ጭለማውን ብርሃን የሚሉ፥ ጣፋጩን መራር፥ መራሩን ጣፋጭ የሚሉ፥ ጥሩውን መጥፎ፥ መጥፎውን ጥሩ የሚሉ ወዮላቸው"[118] እያለ ከጮኸባቸው ከሰይጣን መልእክተኞች ያድንህ። (71^{ለ}) አሁንም ንጉሥ ሆይ፥ መንገሥህን ለእግዚአብሔር እምላክ እገልግሎት እድርገው እንጂ ለራስህ ክብር እይሁን፤ ምክንያቱም መጽሐፍ፥ "ዓለም በሃይማኖት፥ በእግዚአብሔር ቃል፥ ተፈጠረ፤ የማይገለጠው ተገለጠ"[119] ይላል። እግዚአብሔር ስሙ ይባረክና እነሆ ፍጥረታትን ፈጥሮ ለመንፈሳውያን በመንፈስ፥ ለሥጋውያን በሥጋ የሚኖሩበት ሕግ ለሁሉም አወጣ። ከየወሰናቸው እንዳይተላለፉም ትእዛዝ ሰጣቸው። ከዚያ በኋላ ሕጉን የተላለፉትን ለቅጣት ጦር ዳረጋቸው። ሕጉን በመፈጸም የቆሙትን ግን በመንፈስና በሥጋ የመጠቀም ጸጋ ሰጣቸው። አሁንም (72^{ሀ}) ፍርዱን እያስታወስክ በግዛትህ ሁሉ ለእግዚአብሔር እቃና፤ ምክንያቱም መጽሐፍ፥ "ንጉሦችን በቁጣው ዕለት ይቀጠቅጣቸዋል፤ በአሕዛብም ይፈርዳል፤ በድንም ይበዛል"[120] ይላል።

ከዚያ፥ ንጉሡ፥ "ከመነኮሲዎቹ ሁሉ ጋራ የማትተባበረው ለምንድ ነው?" አለው። ቅዱሱ እንዲህ ብሎ መለሰ፤

> ለጌታ የገባሁትን ኪዳን እንዳልጥስ ነው። ለሰይጣን መጀመሪያ በሕይወት ብርሃን በተድላ እንዲኖር የንጽሕና ሥርዓት ተሰጥቶት ነበረ። ከዚያ፥ በራሱ ውሳኔ ጣርን ፀነሰና ኃጢአትን ወለደ፤ (መልአክነቱ ቀርቶበት) ሰይጣን ሆነ። ከእሱ ጋራ (72^{ለ}) የተባበሩት (መላእክትም) እጋንንት ሆኑ።[121] ለነዚህ መነኮሳትም እንደ ቅዱሳን ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ልጅ ለመከተል ወንጌልን በመሸከም የምትገኝ የሥርዓት ብርሃን ውበት ተሰጣቸው። ከዚያ በኋላ ኪዳናቸውን ትተው እነሆ ወደ ዓለም ተመልሰዋል። እኔም ጋኔን እንዳልሆን ልተባበራቸው እልፈለግሁም፤ ምክንያቱም መጽሐፉ፥ "ከሐዲዎችን የቅናት ፍርድና እሳት ይበላቸዋል"[122] ይላል።

---

118. ኢሳ 5፡ 20።
119. ዕብ 11፡ 3።
120. መዝ 109፡ 5-6።
121. ዋናው ምንጭ ተአምረ ኢየሱስ ነው፤ Sylvain Grébaut, "Les Miracles des Jésus," *Patrologia Orientalis*, vol. XII (1919), pp. 564-566.
122. ?።

ከዚያ በኋላ፥ ንጉሡ ወደ መነኮሴዎቹ ዞር አለና፥ "እናንተስ ለምንድ ነው ከሱ ጋራ የማትተባበሩት?" አላቸው። እንዲህ አሉት፤

> ምክንያቱም እሱ የደብሮቻችንን (73^{ሀ}) ሥርዓት ይቃወማል። አባቶቻችን ባላስተማሩን ላይ ጥል ያነሣል። ልጆቻችንንም ይወስድብናል። *ባርቶስ*[123] የሚሉትን የማርያምን ጸሎትና አንደሱ ያለውን ያስቀራል፤ የማርያም ጸሎት ("ነፍሴ እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ታደርጋለች")[124] ብቻ ነው" ይላል።

ንጉሡ፥ ይኸንን በመጽሐፍ ልትከራከሩበት ትፈልጋላችሁ ወይ?" አላቸው። "የለም፥ አንተ እንደምትለው ይሁን" አሉት።

ደግሞ፥ "አባቶቻችን እንዲበላ ንጹሕ ያደረጉትን ዓሣን አርኩስ ያደርግብናል" አሉት። ንጉሡ ቅዱሱን፥ "ማንኛውንም ዓሣ አትብሉ ትላለህን?" አለው። ብፁዑ፥ "እግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገውን ንጹሕ ነው፥ ብሉ (73^{ለ}) አላለሁ። እግዚአብሔር ያረኰሰው፥ ክንፍና ቅርፊት የሌለው እርኩስ ነው፥ አትብሉት[125] እላለሁ" አለው። ንጉሡ ለከሳሾቹ፥ "(ለዚህስ) የአባቶቻችሁ ምስክራ እይደግፋችሁም። ይኸስ በመጽሐፍ መሆን አለበት" አላቸው። ዝም አሉ።

ደግሞ፥ "ስባተኛዋን ቀን ያከብራል፤ ዕለተ እሑድን ይሽራል። መንገድ ሂዶባታል" አሉት። ንጉሡ ቅዱሱን፥ "እንዲህ ታደርጋለህን?" አለው። ቅዱሱ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠው፤

> ሰንባታትን አልሽርም፤ ምክንያቱም ሰባተኛዋ ቀን የእግዚአብሔር የዕረፍቱ መታሰቢያ ናት። ዕለተ እሑድ ቅድስት ትንሣኤው ናት። (74^{ሀ}) "መንገድ ሂደ" ለሚሉት፥ ክርስቶስ እንዳላየኝ የመንፈስ ሥራ ሠርቻለሁ፤ የሥጋ ሥራ አልሠራሁባትም። ምክንያቱም እነዚህ መነኮሴዎች፥ "ከደብራችን እንድትወጣ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ በክርስቶስ ሥጋና ደም እናምልሃለን" ብለው በእግዚአብሔር ቃል (እሑድ ዕለት) ከማደሪያዬ አባረሩኝ። ስለዚህ በመጥፎ እንዳልቀወም፥ ስለ ክርስቶስ ብዬ (በእሑድ ቀን) ተሰደድኩ እንጂ ለሥጋዬ አድልቼ አይደለም። ምክንያቱም እንዲህ እንዲሆን በወንጌል እንዲህ ሲል አዝሏል፤ "ከዚች ከተማ ሲያሳድዷችሁ ወደ ሌላዋ ሽሹ።"[126] ጌታም እይሁድ ሲያሳድዱት (74^{ለ}) በሰንበት ሂዷል። "ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የነሱ ናትና"[127] ይላል። ሐዋርያው ጳውሎስም፥ "ወንድሞቻችን ሆይ፥

---

123. ሬኔ ባሴ አሳትሞታል፤ René Basset, *Les Apocryphes éthiopiens V. Les prières de la Vierge à Bartos et au Golgotha*, Paris 1895.
124. ሉቃ 1: 47-55።
125. ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር፤ ዘሌ 11: 9-12፤ ዘዳ 14: 9-10።
126. ማቴ 10: 23።
127. ማቴ 5: 10።

በክርስቶስ የደረሰውን ስድብ ተሸክመን ወደ ውጪ እንውጣ፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ያስደስተዋልና"[128] ይላል።

ንጉሡ፦ "ከእንግዲህ ወዲህ (እንዲህ) አታድርግ" አለው። ቅዱሱ፦ "በፊቱም የሥጋ ሥራ አልሠራሁም፤ አሁንም አልሠራም። በፊቱም የመንፈስ ሥራ ሠርቻለሁ፤ አሁንም አልተውም" አለው።

ፍርድና የግርፊያ ቅጣት

ከዚህ በኋላ፦ ንጉሡ መነኮሴዎቹ እንዲያመሰግኑት ፈለገና እነሱን፦ "በሉ ፍረዱ" አላቸው። እንዲህ ሲሉ ፍርድ ሰጡ፤ (75ᵁ) "ሞት ይገባዋል፤ ምክንያቱም ለንበት ሻሪ ነው፤ ለንጉሥም አይታዘዝም፤ ለክብሩም አይሰግድም።" ንጉሡ ግን እንዲገረፍ (ብቻ) ትእዛዝ ሰጠ። እጆቹንና እግሮቹን አስረው ፵፯ ጊዜ ገረፉት። ቅዱሱ ምንም ሳይንቀሳቀስ በትዕግሥት እንደ መጠጥ ጣዕም ተቀበለው፤ እንዲያውም እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበረ። ዕለቱ የሐዋርያው የፊልጶስ በዓል፦ ኀዳር ፲፰ ቀን፦ ነበረ።

ቅዱሱ ሲነሣ ንጉሡ፦ "(የደረሰብህ) ስማዕትነት ይመስልሃልን?" አለው። ቅዱሱ፦ "አዎን፦ በእርግጥ ስማዕትነት ነው" አለው። ንጉሡ፦ (75ᴬ) "እንድትገባበት እሳት ያንድዱልህ" አለው። ቅዱሱ፦ "እኔ (እሳት) እንድታነድ አላዝህም፤ ግን ያመጣኸውን ሁሉ በአምላኬ ስም ልቀበል እነሆ ዝግጁ ነኝ" አለው። ንጉሡ፦ "ስማዕትነት ከኔ አታገኝም፤ (ስማዕት የሚያደርጉህ) ብዙ አረሚዎች ሀገርህ አሉልህ" አለው። ቅዱሱ፦ "ብዙዎች በቅዱሶች ላይ ስማዕትነት እያመጡ፦ ክርስቶሳውያን ነን ይላሉ" አለው።

"መምህርህ ማነው?"

ንጉሡ ቅዱሱን፦ "(ለመሆኑ) መምህርህ ማነው?" አለው።[129] ቅዱሱ፦ "አብ፦ ወልድ፦ መንፈስ ቅዱስ" አለ። ንጉሡ፦ "ከዚያስ ቀጥሎ?" አለው። ብፁዑ፦ "ነቢያትና ሐዋርያት" አለው። ንጉሡ፦ "ከነሱ በኋላስ?" አለው። ቅዱሱ፦ (76ᵁ) "በነቢያትና በሐዋርያት ሥርዓት የሚሄደውን ሁሉ ትልቅም ሆነ ትንሽ አለይም፤ ሁሉም መምህሮቼ ናቸው" አለው። ንጉሡ፦ "ከዚያ በኋላስ?" አለው። ብፁዑ እንዲህ ሲል መለሰለት፤ "ከዚህ በኋላማ ሌላ የለኝም፤ ምክንያቱም ሁሉም የሰይጣን ሠራዊት፦ የአጋንንት ማኅበር ናቸው።"

---

128. ዕብ 13: 13-16።

129. እያንዳንዱ መነኮሴ መምህሬ የሚለው ያመነኮሰውን የገዳሙን አበምኔት ነው። ንጉሡም የጠየቀው ይኸንን ለማወቅና መምህሩን ለመውቀስ ነበረ። አባ አስጢፋኖስ ግን መምህራቸውን አይናገሩም። ያልተናገሩት መምህራቸውን በንጉሡ ዘንድ ላለማሳጣት ሳይሆን የመምህራቸውን የአባ ሳሙኤልን መምህርነት ላለመቀበል ነው።

ንጉሡ፡ "መንፈሰ ቅዱስ ያንተ የብቻህ ነውን?" አለው። ብፁዑ፡ "የብቻዬ አይደለም፤ መንፈሰ ቅዱሰ በሕጉ በሚሄዱት ሁሉ ላይ ያድራል" አለው። (ንጉሡ) ይኸንን ሲሰማ ዝም አለ።

ከዚህ በኋላ፡ ቅዱሱ (ሊሂድ ተነሥቶ) ንጉሡን፡ "እነሆ ሰማዕትነቴ ተፈጽሟል፤ ደኅና ዋል" አለው። ንጉሡ፡ (76^ሀ) "ሁላችሁም ስሙ፤ ሳላሰናብተው ከሄደ ደሙ በራሱ ነው" አለ።

ብፁዑ፡ "ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ?" አለው። "ጉባኤ እድርጌ አንተ እንዳልከው ሁሉንም በመጻሕፍት ሕግ አስካስተካክል አንድትቆይ" አለው። ቅዱሱ፡ "ሁሉንም በእግዚአብሔር ሕግ የምታስተካክል ከሆነማ አልሄድም፤ እፈጽማለሁ እንጂ፤ ጉደሉ ሰማዕት አይደለሁም" አለው።

ከዚህ በኋላ፡ ንጉሡ መነኮሴዎቹን፡ "ከመሐላና ከእግዚአብሔር ጋራ ኪዳን (ከገባችሁ) በኋላ ወደ ዓለም ለምን ትመለሳላችሁ፡ ስለሚላችሁ አትከራከሩትም እንዴ?" አላቸው። እነሱም፡ "ዓለምን ጥለን የት ልንሄድ? ወይስ በዓየር ላይ እንብረር? (77^ሀ) አባቶቻችን ይኸንን ሁሉ (ልማድ) ለተዝካራቸው እንዲሆን አዘጋጅተውልናል፤ እናንተ ንጉሦቻችንም የመሠዊያ ቀንዶች[130]፡ የነፍሳችንና የሥጋችን አባቶች ናችሁ" አሉት። መጽሐፉ፡ "እርስ በርሳቸው ገጸ በረከት ይሰጣጣሉ"[131] እንዳለው እርስ በርሳቸው ተመሰጋገኑ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ (የከሰሱትን) መነኮሴዎች ወደየሀገራቸው ሰደዳቸው። ቅዱሱ ግን (ስላላሰናበተው) እስከ ሁለት ወር ድረስ ታገሠ። ከዚህ በኋላ፡ የደብተራዎቹን አለቆች እንዲህ ሲል ወደ ንጉሡ ዘንድ ላካቸው፤ "አስተካክላለሁ ያልከውን አላስተካከልከም። እነሆ የወንጌልን ሥርዓት የሚቃወሟትን ሁሉ አሰናበትካቸው። (77^ሀ) (ማስተካከል) ካልፈለጋችሁ በሕጋችንና በእጅ ሥራ ድካማችን አንድንኖር አሰናብቱን። በምድርህ ላይ እንደዚህ እንድንኖር ካልፈቀድክ ወደ ምድረ በዳችን ስደደን፤ ለኛ "የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ"[132] ያለው የጌታ ቃል ይበቃናል። ይኸንን ሁሉ ካልፈቀድከና ሌላ ያሰብከው ካለህ አሁን ፈጽመልን።"

(የደብተራዎቹ አለቆች) ይኸንን ለንጉሡ ሲነግሩት፡ "በእጄ የሰማዕትነት ሞት ይፈልጋል፤ ግን (አያገኝም) ወደ ደብርህ ተመለስ በሉት" አላቸው። አሰናበቷቸው። ከዚያ፡ ቅዱሱ በጥር ፳፫ ቀን (78^ሀ) ከንጉሡ ሰፈር ተነሣና የካቲት ፭፱ ቀን ከማደሪያው ደረሰ።

"አዲስ" የግዳም ኑሮ

ልጆቹ ካወጣላቸው ቀኖና ጋራ ልባቸው በሚዛን ላይ እኩል እስኪሆን ድረስ ኑሯቸው በቃልም በምግባርም ትክክል እንዲሆን ይጐበኛቸው ነበረ። እንዲህም ይላቸው ነበረ፤

130. መዝ 117: 27።
131. ራእ 11: 10።
132. ማቴ 6: 26።

ድኾችን የምትረዱበትን አሁኑኑ በድካማችሁ ሳብ ማርኩ፤ ምክንያቱም እንደዚህ መጣር ሁል ጊዜ አይቻልም፤ ጌታ÷ "በዓለም ውስጥ ያለውን ለማድረግ የማይቻልባት ሌሊት ትመጣለች"[133] እንዳለው የሚሆንበት ሁኔታ ይመጣል። እናንተ ይኸንን (የያዛችሁትን) በምትሠሩበት ጊዜ ዓይናችሁን (78ᴬ) በወደፊቱ ላይ አትኩሩ። ጌታ÷ "እኔን ካሳደዱ እናንተንም ያሳድዷችኋል"[134] እንዳለው ለማዕትነት እስከሚፈጸም ድረስ ከዚህ መሰደድና መታሰርም ይኖራል። ደግሞ÷ "ግን እኔ ዓለምን እንዳሸነፍኩ በዚህ አመኑ፤ በርቱም።"[135] ይህቺ ኑሯችሁ እንደዚያን ጊዜዋ የአባቶች መንገድ ናት። እነሱ የመርከባቸውን ፍጻሜ ያሳረፉበትን ታዩ ዘንድ የልባችሁን ዓይን አንሡ--ወደ ቀድሞው ሳይሆን ወደ ላይኛው እንጂ። ነቢዩ÷ "ከጌቶች ማእድ ከተቀመጥክ አንተም እንደነሱ ማቅረብ (79ᵁ) እንዳለብህ ዕወቅ"[136] ያለው ስለዚህ ነው። ጌታም እንዲህ ሲል ያስረዳናል፤ "እንዳትሳሳቱና እንዳትደናቀፉ ይኸንን ነግሬያችኋለሁ፤ ከምኵራባቸው ያስወጧችኋል።"[137]

ከዚህ የሕይወት ምንጭ ሲጠጡ የመላእክትን ሕይወት እግኝተው የሥርዓት ውበት በላያቸው ላይ መዓዛዋን አሳየች።

ከዚህ በኋላ÷ (ተከታዮቹ) ብዙዎች ሆኑ። ገዳሞቻቸውም በውጪና በውስጥ በበረከት ፍሬ እየሞሉ ከአንድ ወደ ሁለት÷ ከሁለት ወደ ሶስት እጥፍ ሆኑ። የድካም ላባቸውን ድኾች እንዲካፈሉት ከየአትክልት ቦታቸው (እያመጡ) በቅዱሱና በማኅበሩ ሁሉ ፊት በማቅረብ በረከት ለመስጠት ይሽቀዳደሙ ጀመር። (79ᴬ) ቅዱሱ ያንን በረከት ተቀብሎ ጠዋት ጠዋት ከሦስት በኋላ ከጸጥታ ማደሪያው ይመጣና በገዳሙ በራፍ ላይ ለድኾችና ለምስኪኖች ሲያካፍል ይውላል። ጸሎት ለማሳረግ ካልሆነ በቀር ምንም ሳያቋርጥ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ እንደዚህ ያደርጋል።

ብዙዎች ከበሽታቸው ፈውስ እየፈለጉ ከቅርብና ከሩቅ ሀገሮች ወደሱ ይመጡና ቅዱሱ እጁን ሲያሳርፍባቸው ከተሳሳፊ በሽታቸው እየዳኑ÷ (80ᵁ) "ነፍስና ሥጋን በመርዳት ለሀገራችን ትልቅ መከታ ተገኘ" እያሉ ሁሉም እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። ከሀገሪቱ ታላላቆችም ብዙዎች ከትምህርቱ ገቡ። ያ በሁሉም ስም ነገረ ፈጅነት የተሾመው የመነኮሴዎቹ አለቃ ሳይቀር በቅዱሱ ላይ የደረሰውን ሰድብ ለመሸከም አሱም ተደመረ። በራስ ሽበት (ጊዜ) እባውንትነት እግኝቶ ከቅዱሱ ጋራ አስራትን÷ ግርፋትን÷ ከሀገር ወደ ሀገር መሰደድን ተካፈለ።

---

133. ዮሐ 9: 4።
134. ዮሐ 15: 20።
135. ዮሐ 16: 33።
136. የምንኵስና ሥርዓት ሲፈጸም ለመንኳሹ የሚነበብለት ነው፤ Victor Arras, *Patericon Aethiopice*, p. 125.
137. ዮሐ 16: 1-2።

ያሰ ንጉሥ ፈቃድ "የእስጢፋኖስ ስም ከፍ ከፍ አለ"

ከዚህ በኋላ፥ ንጉሡን፥ "እነሆ ያለ እንተ ፈቃድ (80ᴬ) የእስጢፋኖስ ስም ከፍ ከፍ አለ፤ ሀገሮቹ ሁሉ ትምህርቱን ከማድነቅ ገቡ። አሱ ደግሞ አንዳይሰግዱልህ ማሳመፅ ይዟል" ብለው አስኪያሳስቡት ድረስ ቅናት በምድር ክቡሮች በሆኑት[138] ላይ በዛች። በእንደዚህ ያለ አነጋገር ቅዱሱን ለማስገደል ብዙዎች ስሕተት ፈለጉበት።

በዚያን ጊዜ፥ ከዕለታት አንድ (ቀን)፥ ቅዱስ አባታችን ደቀ መዝሙሩን ገብረ ክርስቶስንና ያንን አብሮት የሚከተለውን ወንድም ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤

> በዚች ሌሊት ትልቅ ሐዘን ወደቀብኝ፥ አስፈሪ አንበሶች እንደማይ ሆንኩ። ደግሞ ብዙ መነኮሴዎች የማውቃቸው ሰም (81ᵛ) ያተረፉና ሌሎችም ነበሩ፤ መነኮሴዎቹ እነዚያን አስፈሪ አንበሶች ሲያዩ በጣም ፈሩ፤ ሊቀርቧቸው አልቻሉም። ከፊታቸው እርዝመው ሸሹ። እኔ ግን ቀረብኳቸው። ስላምታ ተሰጣጥተን በማህላችን የፍቅር ስምምነት ተፈጥሮ እንደ አንድ ሆንን፤ ብዙዎች አብረውኝ ሆኑ። ከዚያ ቀጥሎ እነሆ ከእንበሳዎቹ አንዲቷ ከባልደረቦቿ ተለይታ ብቻዋን ስትሄድ አየሁ። በመሄዷ ምክንያት በቀሩትና በሷ ማህል ትልቅ ሐዘን ወደቀ። እኔም አለቀስኩ። እናት ከልጆቿ እንደምትለይ መሰለኝ። እንደዚህ (81ᴬ) በሐዘን ላይ እንዳለሁ ነቃሁ። እንባዬ መኝታዬ ላይ ሲወርድ አገኘሁት። ይህ ምልክት ሰላለፈው ይመስላችኋል ወይስ ስለሚመጣው?[139]

ደቀ መዝሙሩ፥ "ስላለፈው ይመስሰኛል" አለው። ቅዱሱ አባታችን፥ "ስ-ለሚመጣው ነው እንጂ ስላለፈው አይደለም" አለ። ቅዱሱ ደግሞ በነገሩ ላይ አከታትሎ እንዲህ አለ፤ "ብዙዎች የዕረፍታቸውን መጨረሻ በቅዱሶች እንደተገለጸላቸው ትሰሙ የለምን? ለኔ ግን እስከ ዛሬ አልነገሩኝም። ነገር ግን ያንን ከመግለጽ የሚበልጥ፥ ሳይገባኝ እግዚአብሔር በቸርነቱ የከፈለኝን የጸጋ ሀብት በኔ ላይ አያለሁ። (82ᵛ) መጨረሻዬን ግን አልገለጹልኝም።"

ደግሞ እንዲህ አለ፤ "ሰምን ይመስላችኋል (መጨረሻዬን) ያልገለጹልኝ? ምክንያቱ ብዙ ገድልና ችግር ስለሚጠብቀኝ ነው። ስለዚህ መጨረሻዬን አልነገሩኝም። ግን በዚች ሌሊት ትልቅ ለቅሶ ደረሰብኝ። ወንጌላዊው ዮሐንስ ለደቀ መዝሙሩ ለሞትም ሆነ ለሕይወት አልተገለጠልኝም[140] አንዳለው ለኔም እንደዚሁ ሆኖብኛል፤ ለማንኛውም

---

138. የምድር ክቡሮች ("ክቡራነ ምድር") የሚላቸው የአድባራት አበምኔቶችን ነው። አጻጻፉ ዓለምን በመናቅ መነከሳት ሆነው ሳለ ተመልለው ምድራውያን መሆናቸውን ሲያሳይባቸው ነው። እዚህ "ምድር" የሚለው ኢትዮጵያን ነው።

139. ካለፈው አተረጓጐማቸው እንደሚታየው "አስፈሪ አንበሶች" የሚሏቸው ሰይጣን የሚያመጣባቸውን የሰማዕትነት ፈተናዎችን ነው። "ያለፈው" የሚሉት ከድንቁ በፊት የደረሰባቸውን ፈተና አና 46 ጊዜ የተገረፉትን ሰማዕትነት መሆን አለበት።

140. "ሰብከቱ ለቅዱስ ዮሐንስ"፥ E. A. Wallis Budge, *The Contendings of the Apostles,* vol. I, London 1899, p. 191.

ጸልዩ፤ ምክንያቱም ዘመኑ የገድል ዘመን ነው። ጌታ፥ ጦርነት፥ ውጊያ፥ የጦርነት ድምፅ ትሰማላቸሁ ብሏልና።"[141]

ስለ ደብረ ጽዮን ጉባኤ ተጠራ

ከዚህ ነገር በኋላ፥ ብዙ ሳይቆይ (82ᴬ) የትግራይ አገር መነኮሴዎች ሁሉ አክሱም ላይ ተሰብስበው ከቅዱሱ ጋራ በደብረ ጽዮን[142] ጉዳይ እንዲከራከሩ ከንጉሡ ዘንድ መልእክት መጣ። (ይህ የሆነው) እነሱ በፈጠሩት ነገር ለመነታረክ እንጂ የሕግ ትምህርት እንዲያገኙ ፈልገው አልነበረም።

(የንጉሡ) ሎሌ ወደ ቅዱሱ መጥቶ እዚያ ሂዶ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲከራከር የንጉሡን መልእክት ነገረው። ቅዱሱ ይቺ ነገር እነሱ ያወጧት የከሳሾቹ ተንኮል እንደሆነች ስላወቀ፥ ለሎሌው፥ "አልሄድም፤ በከንቱ ነገር ምክንያት ልደክም አልፈልግም፤ የሚፈልጉት የመንፈስ ጉዳይ ከሆነ (83ᵇ) የደብረ ጽዮንን ምስጢር እንዲረዱ የወንጌልን ፈለግ ይከተሉ። የሚፈልጉት የነገር ዋዛ ከሆነ፥ እነሆ ባልደረቦቻቸው ከንጉሡ አዳራሽ በከበረ ልብስ እየተመኩ አሉላቸው። የመንፈስ መንግሥትን ማየት ግን በምግባር እንጂ በነገር አይደለም" አለው።

የንጉሡ መልእክተኛ ሂዶ ይኸንን ለነዚያ ለከሳሾቹ፥ ለጉባኤው አለቆች፥ ነገራቸው። በቅዱሱ ላይ ያሰቧት ክፉ ምክር ስለከሸፈባቸው በጣም ተቆጡ።

ከዚያ በኋላ፥ ምክር ያዙ፤ አንዳንዶቹ ክስ ለመመሥረት ሎሌውን ተከትለው ወደ ንጉሡ ሂዱ። አንዳንዶቹ (83ᴬ) የቅዱሱን ገዳም ለመዝረፍና ልጆቹን ለማሰር ተቃጠሩ። ገዢው የሚፈልገው እንደዚህ እንዲሆን ነውና።

የንጉሥ ጥሪ

ንጉሡ ደግሞ እንደገና ሎሌውን እንዲህ ሲል ወደ ቅዱሱ ላከው፤ "እዚህ ሆነህ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ እንድንወያይ ወደኔ ና።" ደግሞ ቅዱሱን በግድ እንዲልከው (በጎን) የሽሬን ገዢ አዘዘው።

እነሱ አባታችንን ሲያጣድፉት፥ እነዚያ መነኮሳት ደግሞ ከቅዱሱ ገዳሞች አንዷን ደብር ከበቧትና ድካማቸውን ሁሉ ምንም ሳይተዉ--ለቊርባን ጎብስት ያዘጋጁትን ሳይቀር--እንደ ዘላን ዘረፉት።[143] ልብሳቸውንም ገፈፏቸው፤ (84ᵇ) ደበደቧቸው፤ አሰሯቸው። የቅዱሱ ልጆች

141. ማቴ 24፡ 6፤ ማር 13፡ 7።

142. ስለ ደብረ ጽዮን መግቢያውን (ገጽ 31) ተመልከት።

143. "እንደ ዘላን ዘረፉት" የሚለው አነጋገር ታሪክ ሊኖረው ይችላል። ንጉሡም አባ አስጢፋኖስን፥ "ሰማዕት የሚያደርጉህ ብዙ አረሚዎች ሀገርህ አሉልህ" ያለውም ከዚህ ጋራ አብሮ ይሄዳል። ምናልባት የኢትዮጵያ ዘላኖች የሰሜን አፍሪካ በርበሮች በግብጽ ገዳማት ላይ ያደርጉት እንደነበረው፤ ገዳማቱን ይዘርፉ፥ መነኰሳቱን ይገድሉ ኖሯል።

ምንም ሳይመልሱላቸው በተኮሎች ማህል አንዳሉ በጎች ሆኑ፤ ብቻ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበረ። (እግዚአብሔር ዋጋቸውን) በዚህ ዓይነት ከፍሏቸዋልና። አገረ ገዢው ሲሰማ ከንጉሡ ሎሌ ጋራ ወደዚያ ሄደና በግድ አስጣሏቸው። ስለቀሙት (ንብረት) ግን ማንም አልከሰሳቸውም፤ የንጉሡን ልብ ዐውቀውታልና።

ከዚያ፥ ኀዳር ፴ ቀን ቅዱሱ ሰመሄድ ተነሣና ጥር ፤ ቀን ከንጉሡ ሰፈር ደረሰ። ያ ሽማግሌ አባ በርተሎሜዎስም አብሮት ነበረ። ንጉሡ መምጣታቸውን (84ᵃ) እያወቀ ወደ እሱ ሊያስገባቸው አልፈቀደም። ብቻ ምግብ ሳይሰጡ እንደ አስረኛ በዓይነ ቁራኛ እንዲከታተሏቸው ወታደሮቹን በማህላቸው ሰገሰጓቸው። በእንደዚህ ያለ አድራጎት ሊበቀላቸው ወድዷል።

ቆይቶ ቆይቶ፥ ሚያዝያ ፰ ቀን ወደሱ አቅራቢያ ጠራቸው፤ ግን ወደ ውስጥ ወደሱ ዘንድ አላስገባቸውም። ንጉሡ የድንኳኑን አስቆች ወደ ቅዱሱ እንዲህ ሲል ላከው፤[144] "ደብረ ጽዮን የለም እንደምትል፥ ደግሞ አረማውያን ከቤተ ክርስቲያን እንደምታስገባ ስማሁ፤ (ሰዎች) ነገሩኝ። ደግሞ በዕንጨት ላይ መሥዋዕት እንደምትሠራ ስማሁ። እውነት ነው ወይስ ውሸት?" ቅዱሱ ለመልእክተኞቹ (85ᵇ) እንዲህ በሉት አላቸው፤

> እኔ ደብረ ጽዮን የለም አልልም፤ ልባቸውን ንጹሕ ያደረጉና የክርስቶስን የወንጌል ቀምበር የተሸከሙ ያገኙታል። አረሚ (ከቤተ ክርስቲያን) ስለ ማስገባት ያለውን (እንዲህ አለ) በሉት፤ "አረሚ ቀርቶ በእፋቸው ክርስቲያን ነን የሚሉትን እንኳን በሕጉ ፈለግ ካልሄዱ ከምሥዋዓችን እናካፍላቸውም።" "በዕንጨት ላይ መሥዋዕት ትሠራለህ" ስላለው ግን "እምን፥ (እንዲህ) እንዲሠሩ ወንድሞቼን መክሬያቸዋለሁ፤ ምክንያቱም በዕንጨት ላይ አይሥሩ የሚል ከመጻሕፍቱ ውስጥ አላገኘሁም። ክርስቶስም የተሰቀለበት ዕንጨት ነው፤ (85ᵃ) የመስቀሉን ዕንጨት በደሙ ቀድሶታል። ታቦት የሚሆነውም ቅዱስ ሚሮን የሚቀባ ዕንጨት ነው። የፈለገ በወርቅና በብር ይሥራ፤ አልከለከልኳቸውም (ብሏል)" በሉት።[145]

እነዚያ የድንኳኑ አለቆች እንደዚህ ብለው ስንጉሡ ነገሩት። (ንጉሡ) እንደዚህ ሲል ደግሞ እንደገና ላካቸው፤ "ይኸስ ጥሩ ነው፤ ግን ከዚህ በቀር ሌላ እምነት እንደሌለህ በል ማል።"

---

144. ንጉሡ የሚከሳቸውን ዜጋዎች አስመጥቶ መጀመሪያ በቀጥታ አያነጋግራቸውም፤ አጠገቡ ሆነው ሳስ የሚያነጋግራቸው በመልአክተኛ (በቀላጤ ወይም በአፈ ንጉሥ) አማካይነት ነው።

145. የእንጨቱ ጉዳይ እውነት ተነሥቶ ከሆነ "አባ አስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ቅዱስ መስቀልን አያከብሩም" ተብለው የሚከሰሱበትን ለማስተካከል ዕድል ስጥቷቸዋል። ስንጉሥ አንሰግድም ካሉ፥ ዘርአ ያዕቆብ "ለመስቀልና ለሥዕል አንሰግድም ብለዋል" ብሎ ቢክሳቸው አይገርምም። Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 250/47, Louvain 1964, p. 43. ማክበርና ማምለክ የተለያዩ ናቸው። ታቦት አንዳላቸው ይኸ አነጋገር ያሳያል፤ ግን ስለ አከባበሩ ምን እንደሚሉ የሚታወቅ ነገር የለም። ሆኖም ከመስቀል ጋራ ካመሳሰሉት ስታቦት እንደማይስግዱ መገመት ይቻላል።

ቅዱሱ፡ "መርቅን ሲጠረጥሩት በአሳት ይፈትኑታል፤ እንደዚሁ ሰውንም ሲጠረጥሩት በእግዚአብሔር ቃል በመጻሕፍት ይፈትኑታል፤ ሥራውም ይታወቃል። ወንጌል፡ ዛፍ በፍሬው ይታወቃል[146] (86ᵛ) ይላልና። መሐላ ስለሚለው ግን ብሞት አልምልም፤ ምክንያቱም፡ አዎ ወይም የለም እንድንል እንጂ፡ በሰማይም፡ በምድርም፡ በኢየሩሳሌምም፡ በራሳችንም ወይም በሌላ መሐላ እንዳንምል ወንጌል አዞናል[147] በሉት" አላቸው።

ለንጉሡ እንደዚሁ ብለው ነገሩት። ንጉሡ እንደገና ደግሞ እንዲህ ሲል ላከበት፤ "ይኸም ጥሩ ነው፤ በል እንዳልከው አዎን በል።"

ቅዱሱ እንዲህ አላቸው፤ "ሃይማኖቴ ይህ ነው፤ አብ የወለደ፡ ወልድ የተወለደ፡ መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ መንፈስ[148] ነው። ለዚህ (ሥላሴ) አሰግዳለሁ፤ አመልካለሁም። የምድር ንጉሦች እንዲወዱኝ (86ᴬ) ብዬ በዚህ ላይ አልጨምርም፤ ደግሞ የምድር ንጉሦች እንዳይጠሉኝ ብዬ ከዚህ አላጕድልም። እንደ ወንጌል ቃል አዎን፡ አዎን።"

ለንጉሡ እንደዚህ ብለው ነገሩት። አሁን የሚለው ሲያጣ ጊዜ እንደገና እንደበፊቱ አዚያው አስቀመጠው።

ከዚያ በኋላ፡ ጥቂት ቆይቶ አስጠራቸውና ከፊቱ አቆማቸው፤ እንደ (መጽሐፉ) ትእዛዝ፡ "ሰላም ላንተ ይሁን" ብለው ሰላምታ ሰጡት። በዚህ ጊዜ መታደሮቹ፡ "ስገዱ፡ ስገዱ" እያሉ ጮኹ። ለማስፈራራት እየተጯጯሁና ወዲያና ወዲህ እየተንጎራደዱ እንደዚህ ቆዩ። ንጉሡ ዝም እንዲሉ አዘዘና መንግሥቱን (87ᵛ) ወደሚመለከት ጉዳይ ገባ። ስለጠራቸው ጉዳይ አላነጋገራቸውም። ሲመሽ እንዲመለሱ አዝዞ አሁንም እንደ በፊቱ በዝምታ አስቀመጣቸው።

ቅዱሱ ልጆቹን፡ "ተነሡ ወደ ምድረ በዳችን እንሂድ፤ ሥራችን የንጉሦች ደጅ ጠባቂነት አይደለም" አላቸው። ሲሄዱ ሠኔ ፷ ቀን ተነሡ። ያ ይጠባበቃቸው የነበረው ሉሌ ሮጦ ለጦር ሠራዊቱ አለቃ ነገረው፤ (የጦር ሠራዊቱ አለቃ) ለንጉሡ ነገረው። (ንጉሡ) እንዲያመጣቸው አዘዘው። መታደሮቹ ሄደው እያባበሉ መለሷቸው።

---

146. ማቴ 7: 16።

147. ማቴ 5: 34-37።

148. አኒጋሩ አን አፄ ዘርአ ያዕቆብ ከሚከሷቸው ጋራ አይመሳሰልም። አፄ ዘርአ ያዕቆብ የሚከሳቸው፡ "አብ ከቃሉና ከመንፈሱ ጋራ አለ፤ ወልድም ከቃሉና ከመንፈሱ ጋራ አለ፤ መንፈስ ቅዱስም ከቃሉና ከመንፈሱ ጋራ አለ ይላሉ፤ አንደዚህ የሚሉ ሶስት አምላክ፡ ሶስት መንግሥት፡ ሶስት ግዛት ያለ አድርገው ለያንዳንዱ ቃልና መንፈስ አንዳላቸው እንደ አዳም፡ ሴት፡ ሄኖስ ይማሰላሉ ..." ይላሉ ብሎ ነው፤ Kurt Wendt, *Das Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis) des Kaisers Zar'a Yā'qob, CSCO*, vol. 221/41, Louvain 1962, p. 18.

ንጉሡ ከፊቱ እንዲያቆሟቸው አዘዘ። ጳጳሳቱንም[149] ጠርቶ ከሱ ጋራ አስቀመጣቸው። ቅዱሱ ንጉሡን (87ᵃ) እንደለመደው ሰላምታ ሰጠው፤ ያ ቅዱስ ሽማግሌም አብሮት ነበረ። ከዚያ፥ ቅዱሱ ንጉሡን እንዲህ አለው፤

> እንደዚህ (ማድረግ) ልክ ነውን? ክመኖሪያችን በምን ምክንያት በግድ ጠራኸን? አዚህ ለንደርስ የዕለት ምግባችንን አልሰጠኸንም። በእጃችን ድካም እንዳንኖርም አላሰናበትከንም። የራስክን ደሰታ በማስቀደም የእግዚአብሔርን ፍርድ ለምን ትተዋለህ? መጽሐፉ፥ "ፍርድ የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው"[150] አላለምን? አንተም በእግዚአብሔር ፍርድ ብትገዛ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ታገኝ ነበረ። ገንዘብ ወዳዶች፥ "ማን አንዳንተ" አያሉ በአድልዎ የሚያመሰግኑህን፥ (88ᵇ) የሚያልፍ ምስጋና በማስቀደም የአምላክን ፍርድ አንደዚህ ቸል ካልክ ልክ አይደለም። አነሆ የድኾችን ዋይታ የማይረሳ አውነተኛ ገዢ አግዚአብሔር አለ። ለተገፉ ሁሉ ይፈርዳል።

ንጉሡ ቅዱሱን፥ "አንተ በየትኛው አቅምህ ነው በድፍረት የምትናገረኝ? ጳጳስ ነህ ወይስ ኤጲስ ቆጶስ። እነሱ ቢናገሩኝ እነሆ እዚህ አሉ። የምንሰማውና የምናየው ትዕቢትህ ሰማይና ምድር ያህላል" አለው። ቅዱሱ እንዲህ አለው፤

> ደፍሬ ምን ሰደብኩህ? የተናገርኩህ አግዚአብሔር የደነገገውን ሕግ ይዤ አይደለምን? አንድናገርህ ካልፈለግህ (88ᵃ) እዚህ አንድመጣ ለምን ጠራኸኝ? መነኮሴ ትክክሉን የማይናገር ከሆነ አዚህ መምጣቱ ልክ አይደለም። እኔም አውነቱን የማልናገር ቢሆን ኖሮ አልመጣም ነበረ።

ንጉሡ፥ "አልመጣም ብትል አሳንቄ አላመጣህም ነበርን!" አለው። ቅዱሱ፥ "የአበው መጽሐፍ ለመነኮሴ ሞትንና ስቅላትን ተስፋ ከማድረግ የሚበልጥበት የለም[151] ያለውን አልሰማህምን? ራሴ እስኪቆረጥ ድረስ በአምላኬ ኀይል ተማምኜ ነው እንጂ እኔ በሥጋ ነገር እቃወምሃለሁ ብያለሁን?" አለው።

"ለምንድን ነው ሁል ጊዜ አንተ የምትለኝ?"

ንጉሡ ቅዱሱን፥ "ለምንድን ነው በሰግደት ራስክን ዝቅ የማታደርገው?" አለው። (89ᵇ) ቅዱሱ፥ "ሕጉ የሚያዘን ለእግዚአብሔር እንድንሰግድ እንጂ በውስጡ አንተ እንደምትለው እንድንሰግድ ትእዛዝ የለበትም። ለማንኛውም ክኛ ስግደት አትፈልግ፤ ጸሎትና ቡራኬ ይበቃሃል" አለው።

ንጉሡ፥ "ለምንድን ነው ሁል ጊዜ አንተ የምትለኝ? አለው። ቅዱሱ፥ "ለምንድን ነው የማልልህ? አንድ ሰው አይደለህም እንዴ?

---

149. ጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል እንደነበሩ ከላይ በጎዳግ ቍጥር 93 ስር አይተናል።

150. መዝ 105፡ 3።

151. Victor Arras, *Patericon Aethiopice, CSCO*, vol. 277/53 (1967), p. 125.

በብሉይም በሐዲስም የተጻፈው እንደዚሁ ነው፤ አንድን ሰው እንዳንድ ይናገሩታል፤ እንደ ብዙዎች አይደለም። እንኳን ሰውን እግዚአብሔርንም፥ አንተ አትጣለኝ ጌታ ሆይ፤ (89ʰ) አምላኬ አንተ ከኔ አትራቅ፤ የመዳኔ አምላክ ጌታ ሆይ[152] አያልን እንደዚህ ነው የምንጠራው" አለው።

ቅጣት

እንዲህ በሚልበት ጊዜ ንጉሡ አፉን እንዲሉት አዘዘና በቁጣ ጮኸ። ቅዱሱን ፊቱን ወደ ላይ አቅንተው ሁለንተናው ደም በደም እስኪሆን ደበደቡት። የንጉሡ የቀኝና የግራ ወታደሮች ሲያዩ ከራሱ እስከ እግሩ በመደብደብ በቅዱሱ ላይ ተረባረቡበት። ንብ ማርን (እንደሚከብ) ከበቡት። ሰውነቱ አልበቃ ሲላቸው ጊዜ የመልኩ ውበት እስኪለወጥ ድረስ ግማሾቹና ግማሾቹ ተራ በተራ ተፈራረቁበት። (90ᵘ) በእሳት የጠበሱት ዕንጨት መሰለ። ከድብደባው አብጠት የተነሣ የጉንጩ ስፋትና የከንፈሮቹ ሥርዓት (በእብጠት) ከአፍንጫው ጫፍ ጋራ አኩል ሆኑ። ዓይኑም ማየት አልቻለም። ብቻ ደሙ ከድንኳኑ[153] በር እንደውሐ ይወርድ ነበረ።

ከዚያ፥ ቁጣውን ሲያበርድ፥ ከፊቱ እንዲያስወግዱት ትእዛዝ ሰጠ። ወደ መዝገቦቹ ቤት[154] ወሰዱት። አብረውት ቁመው የነበሩ የቅዱሱ ልጆች ወደሚወሰዱበት ሊከተሉት ፈለጉ። ንጉሡ እነሱንም እያንዳንዳቸውን እየያዙ በጥፊ እንዲመቷቸው አዘዘ።

ሽማግሌውን፥ "በርተሎሜዎስ፥ የቤታችንን (90ʰ) ክብር እያወቅህ እንዴት አንተም እንደዚህ በማዋረድ ላይ ትገኛለህ?" አለው። ሽማግሌው፥ "አዎ፥ እኔም ይኸንን ቅዱስ በማንኛውም ረገድ ልመስለው ወድጃለሁ" አለው። አሱንም በጥፊ እንዲመቱት አዘዘ። "ከመጀመሪያው ጥፊ ኃይለኛነት የተነሣ፥ የኋለኞቹን ልብም አላልኳቸው" ይል ነበረ።

ከዚያ በኋላ፥ ሁሉንም ከሽማግሌው ጋራ እንዲገርፏቸው አዘዘ። ከንጉሡ ታላቅ ቁጣ የተነሣ እነዚያ በቀኙና በግራው ተቀምጠው የነበሩ ጳጳሳት መናገር አልቻሉም። ግን ለመገረፍ ካጋደሟቸው በኋላ እንዲተዋቸው አዘዘ። ቅዱሱንም ከወሰዱበት ቦታ አመጡት። (ሲያመጡት) አጉንብሶ ነበረ የሚሄደው፤ ምክንያቱም (91ᵘ) በጢሙ ላይ የወረደው የአፍንጫውና የአፉ

152. መዝ 37: 21-22።

153. በንጉሡ ሰፈር ሁለት ዓይነት ድንኳኖች ነበሩ፤ እንዱ የንጉሡ ችሎት ማስቻያ "ጎይመት" ወይም በገድለ አቡነ ዕዝራ አጠራር "ደመና" (ደበና) የሚባለው ሲሆን፥ ሌላው የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት ተከትለው የንጉሡን ታቦት የሚያኖሩበት ነው፤ እሱ "ደብተራ" ይባላል። በደብተራው ውስጥ የሚያገለግሉት ካህናት "ካህናተ ደብተራ" (የደብተራው፥ የድንኳኑ ካህናት) ይባላሉ። ካህናተ ደብተራ የንጉሡ ታዛጆች ይሁኑ እንጂ መጻሕፍትን በመመራመር የላቁ ነበሩ። መጀመሪያውኑ እዚያ ደረጃ የሚያደርሳቸው ችሎታቸው ያተረፈላቸው ስም ነው። ዘርአ ያዕቆብ አባ አስጢፋኖስንም ከካህናተ ደብተራ አንዱ ሊያደርጋቸው ፈልጎ ነበረ። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላቸው ሰዎች "ደብተራ" የሚባሉበት መሠረቱ ይህ ነው።

154. "ቤተ መዛግብት" ("የመዝገቦች ቤት") የሚለው አስር ቤቱን ነው።

ደም ሲረጋ እንደ ገመድ ሆኖ ሳይበጠስ ከልብሱ ጋራ ተያይዞ ነበር። ሲመቱት ቆቡን ጥለዋት ስለነበረ ራሱ ራቁቱን ነበር፤ ግን በልብሱ መገናኛ ቁልፍ ተይዛ ተንጠልጥላ ነበረ። ልጆቹ አስተካከሉለት፤ ቆቡን ራሱ ላይ አደረጉለት፤ የደሙንም ገመድ ከጢሙ አስወገዱለት። ዐይኑ ግን ጠፍቶም እንደሁ ወይም እንዳለ ለመረዳት አልቻሉም።

ቅዱሱ ለልጆቹ እንዲህ አላቸው፤ "አሁን ታዲያ በዚህ ታዝናላችሁን? ይኸ ድብደባ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ክርስቶስ አጥንቴን ሁሉ እንኳን ቢበታትኑትም እንደዚሁ እደስታለሁ። እናንተ ግን (91^ለ) በእግዚአብሔር ጥኑ። ከናንተ የለዩኝ እንደሆነ እናንተ (ከሌሎቹ) ወንድሞቻችሁ ጋራ ተመካከሩ። ዓለም ሊነጥቃችሁ የማይችለውን እንድታገኙ ለተሰፋችሁ ትምህርት ቅድሚያ ስጧት።"

ቅዱሱ በድካምና በሕመም ሆኖ እንደዚህ ሲመክራቸው የንጉሡ ወታደሮች መጡና እንደታዘዙት እያንዳንዳቸውን እየነጠሉ ለወታደሮቹ አለቆች እንዲያስሯቸው ሰጧቸው። በሰፈሩ አደባባይ አፋፍ ላይ በእሥራት አስቀመጧቸው።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ከእሥራታቸው እንዲፈቱ ንጉሡ ትእዛዝ ሰጠ። ቅዱሱና ሁሉም እርስ በርሳቸው ተገናኙ። (92^ሀ) ንጉሡ ያንን በፊት በዓይነ ቁራኛ ይዟቸው የነበረውን ሉሌውን አሁንም ደግሞ እንደዚያው እንዲጠብቃቸው አዘዘው።

ብርቱ ሕመም

እንደዚህ በመያዝ ባሉበት ጊዜ እነሆ ቅዱሱ መውጣት መግባት፥ ከመኝታውም መነሣት እስኪያቅተው ድረስ በጠና በሽታ ታመመ። ለማውጣትና ለማግባት ልጆቹ እንደ ሕፃን ይሸከሙት ነበረ፤ ከበሽታው ጥናት የተነሣ ሁል ጊዜ የኢዮብን ደዌ እያነሣ ይጫወት ነበረ። ትዕግሥቱንም በማንኛቸው እግዚአብሔርን እያመሰገነ ይፈጽማት ነበረ። የትንቢቱንም ምስጢሮች ይተረጕማቸው ነገረ። በበሽታ ተኝቶ ሳለ እብረውት ላሉት የመንፈስ ጎብስት (92^ለ) በመቀረስ የደስታ ምግብ ይስጣቸው ነበረ።

አንድ ቀን ቅዱሱ በበሽታው እንዳለ፥ ለአቡነ ገብረ ክርስቶስና አብሮት ላለው ወንድም እንዲህ አላቸው፤ "ይቺ በሽታዬ ክሰዎች ተለይቼ በነበርኩበት ጊዜ የደረሰብኝን የጠላት ፈተና ትመስላለች። ምናልባት ይኸ የሰው ድብደባ (ሰይጣን) በማታውቀው በኩል እመጣብሃለሁ ያለኝ እንደሆነ እያልኩ እገምታለሁ።"[155] ብዙ ሰዎችም፥ "የድብደባው ደም ተጨምቆ እንደዚህ አሳመመው" ይሉ ነበር።

የንጉሥ ምሕረት

ቅዱሱ በዚህ ሁኔታ እንዳለ፥ ንጉሡ ቅዱሱን ወደሱ እንዲያመጡት ሰዎች ላከ። ተሸክመው አመጡና አጠገቡ አስቀመጡት። (93^ሀ) እንዲህ ሲል

155. ገጽ 69 ላይ ያለውን ተመልከት።

ላከበት፤ "ሰላም ላንተ ይሁን፤ እንደምን አለህ? አንደታመምክ ሰማሁ፤ አሁንም እግዚአብሔር ይማርህ። ባለፈው ጊዜ በተጣላንበት ጉዳይ አትዘን፤ እኔም ያለፈውንም የሚመጣውንም ትቻለሁ።" ቅዱሱ ለላካቸው፥ "ይኸንን ላስታወሰህ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው። በተጨማሪም ትእዛዙን እንድትፈጽም ልብህን ያብራልህ በሉት" አላቸው። ከዚያ በኋላ ንጉሡ አጠገቡ ማደሪያ እንዲሰጡት ትእዛዝ ሰጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምግባቸውን አንጀራ ይልክላቸው ጀመረ።

ከገዳማቸው ካመጣቸው አንድ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ (93^ሀ) በመልአክት አንዲህ ሲል አሰናበታቸው፤ "ምንኵስናችሁን፥ ጸማችሁን፥ አድባራችሁን፥ እግዚአብሔር ይባርክ። በሰው መመካት እንተ አንዳልከው በእውነት ኃላፊ ነው። አሁንም በእግዚአብሔር ተመኩ። ወደየአድባራችሁ ተመለሱ።"

ቅዱሱን የበሽታው ጣር ለቀቀው፤ ከማደሪያው ለመውጣትና ለመግባት ጥቂት በጥቂት ይንቀሳቀስ ጀመረ። ግን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስማዕትነቱን እስከፈጸመበት ጊዜ ድረስ አርዝሞ ለመሄድ አልቻለም። መሸከሚያ ወንበር አበጅተውለት በታኅሣሥ ፳፮ ቀን ከንጉሡ ሰፈር ለቀቁና የካቲት ፫ ቀን (94^ሀ) ከማደሪያቸው ደረሱ።

አዲስ ክስ፥ ግርፊያና እስራት

ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንዚያ ሰብቀኞች ደግሞ ተበጠበጡ። ንጉሡንም እንዲህ ሲሉ በጠበጡት፤ "እነዚህን እንደዚህ ዝም ካልካቸው ሁሉም የነሱን ፈለግ ይከተሉና ለመንግሥትህ ሥልጣን የሚሰግድ አይኖርም።" ከዚያ በኋላ ንጉሡ ቅዱሱን አባታችንንና ያንን አቡነ በርተሎሜዎስን ከደብሮቻቸው (አውጥተው) ደብረ ማዕየ ወደሚሏት ሀገር እንዲሰዷቸው፥ እርባ እርባ እንዲገርፏቸው አዘዘ። ከዚያ፥ የንጉሡ መልአክተኛ ወደ ቅዱሱ መጣና፥ "ንጉሡ ሰላም ላንተ ይሁን ይልሃል" አለው። ቅዱሱ፥ "የጌታ ሰላም ከሱም ጋራ (94^ሀ) ይሁን" አለው። "ለንጉሡ ስገድ አኮ"[156] አለው። ቅዱሱ፥ "እኔ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ለሌላ አልሰግድም" አለው።

መልክተኛው ቅዱሱን አንዲያስሩት አዘዘ። አንደታዘዙት (አስረው) ከደብሩ አወጡት። ያንንም ቅዱስ ሽማግሌ አስረው አመጡት። ሁለቱን በእንድነት ወደ ደብረ ማዕየ ወሰዷቸው። ጥር ፳፮ ቀን የአፍሐሮም ዋሻ ወደሚሏት ዋሻ አመጧቸው። የሀገሩ ሰው ሁሉ እንዲሰበሰብ አዘዙ። በዚያን ጊዜ እርባ እርባ ገረፏቸውና በማግሥቱ ወደ ተራራው ላይ አወጧቸው። እዚያ በእስራት አኖሯቸው።

ወዲያው የተሻረ አዲስ ምሕረት

(95^ሀ) ከሰስት ወር በኋላ ንጉሡ ሎሌውን አንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "እባቶቼ ያቆዩልኝን አልተውም በማለት ይኸንን አደረግሁ፤ አትዘኑብኝ። አሁንም

156. ለንጉሡ የሚሰገደው ከፊቱ ሲቀርቡ ብቻ ሳይሆን ስሙ ሲነሣም (በተለየ ሰላምታና ትእዛዝ ሲልክ) ነው።

ትቻለሁ፤ ምሬያችኋለሁ፤ ውረዱ::" ማስሪያቸውን ፈቱላቸው:: ቅዱሳኑ ወደ ጽሙናቸው[157] ለመመለስ ከዚያ ወረዱ::

ከአክሱም ከተማ ሲደርሱ ደግሞ የንጉሡ ሌላ መልእክተኛ ወደ ቅዱሶቹ መጣና÷ "ንጉሡ ሰላም ለናንተ ይሁን ይላችኋል" አላቸው:: እንደሚገባ ሰላምታ መለሱለት:: "ስገዱ እኮ" አላቸው:: ቅዱሱ÷ "ይኸ ሁሉ ግርፊያና ስደት የደረሰብን (95^ዓ) በምን ምክንያት ነው? ስለዚህ አይደለምን? አሱ ራሱ ምሬያችኋለሁ ካለ በኋላ አሁን ታዲያ ምን ትፈልጋላችሁ? ታሸፋብናላችሁ ወይስ ስለ እግዚአብሔር ከመሞት እናፈገፍግ ይመስላችኋል? አሁንም ለአብ÷ ለወልድ÷ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ አንሰግድም" አለው::

ከዚያ÷ መልእክቱን እንዲህ ብሎ ነገረው፤ "እግዚአብሔር ሳያነግሠኝ አልነገሥኩም:: አሁንም ይኸንን ነገር ተዉ:: አምቢ ካላችሁ ካሁን ወዲህ ደማችሁ በራሳችሁ ላይ ነው::" ቅዱሱ÷ "ደሙስ በእሱ ራስ ላይ ነው፤ ምክንያቱም የሚጣላን ስለ አባቶቹ ሥርዓት እንጂ ስለ እግዚአብሔር ሕግ--(በሕጉ ላይ) ስለ መጨመር (96^ዓ) ወይም (ሕጉን) ስለ ማጉደል-- አይደለም:: እሱ ይልቅ ይተው እንደሆነ ይተው:: አልተውም ካለ እኛም ስለ አምላካችን ከመሞት ወደ ኋላ አንልም" አለው::

ከዚያ÷ መልእክተኛው አገረ ገዢው ቅዱሶችን እንዲጠብቃቸው÷ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ እስኪፈጽሙ ድረስም ወደ ሌላ እንዳይሄዱ እንዳይለቃቸው አድርጎ አስረከበው:: እዚያ እስከ ሶስት ዓመት አስቀመጧቸው:: የቅዱሱ ልጆች ለነፍሳቸው ኃይል ለማግኘት ሁልጊዜ ይጐበኙት ነበረ፤ እርስ በርሳቸው ይሽቀዳደሙም ነበረ:: አንዳንድ ጊዜ (96^ሰ) በልባቸው እንስራ ከሕይወት ምንጭ ቀድተው ይመጣሉ:: አንዳንድ ጊዜ ወደዚያ ለመሄድ በእሽቅድድም ይወጡ ነበረ:: የበጋው ሙቀት ሳይመጣ በመጸዉ ዘመን አበባ ለመቅሰም ወዲያ ወዲህ ማለትን እንደሚያጣድፉ ንቦች እነሱም እነዚያ አፋቸውን የከፈቱበት[158] (ጠላቶች) ሳይወስዱባቸው ጥቅማቸውን ለመስብሰብ ሊያጽናኑት ይጣደፉ ነበረ::

ከዚያ÷ በየተሰደደበት የተሰበኩ ብዙዎች ቅዱሱን አባታችንን ለመከተል ተጨመሩ:: ከደጎች ሴቶች መነኮሲቶችም ኃይል አግኝተው በገዳማቸው በቅዱሱ አባታችን ትምህርት ሥርዓት (97^ዓ) የቆሙ ነበሩ::[159] አባታቸውን ለመጐብኘት (ቦታው) ስልጆቹ ቅርብ እንደሆነላቸው÷ ፈለጉንም የሚከተሉ ብዙዎች እንደሆኑ÷ ንጉሡ ባወቀ ጊዜ÷ "እነሆ አገሩን

157. "ጽሙና" በዝምታና በጸጥታ ለእግዚአብሔር መጠመድ ነው::

158. መዝ 108: 2 ካለው ጋራ ለማያያዝ ነው::

159. ይኸ እነጋገር የሴቶችም የወንዶችም ገዳሞች የአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች መሆን እንደጀመሩ ያሳያል:: የአባ እስጢፋኖስ ተከታይ የነበሩት የአባ አበከረዙን ገድል የተከተሏቸውን አድባራት ዝርዝር ይስጣል:: ስለ አንዱ ገዳም አበምኔትማ እንዲህ የሚል ተመዝግቧል፤ "ከዚያ÷ በእንድ ቦታ በዚህ ሁኔታ እንዳሉ÷ አንድ አበምኔት ለቅዱሱ እንዲህ ሲል ላከበት፤ ደብሬን ተረከበኝ/ውስድ፤ እኔንም ስለ እግዚአብሔር ብለህ አንተ ቅበረኝ፤ ባንተ ሥርዓት ስር እንድሆን እፈልጋለሁና::" (እዚህም ገጽ 235) የንጉሡም ስጋት ይኸው ነበረ::

ሁሉ በትምህርቱ ዓይነት መጠጠው" አለ። ከዚያ፥ ካለበት ወደ ሌላ አርቀው አንዲሰዱት አዘዘ። ይዘውት ሲሄዱ በመንገድ ላይ ከአሳባቂዎቹ አንዱ አገኘውና ቅዱሱን፥ "ለንጉሡ ለምን አትሰግድም?" አለው። ቅዱሱ ሲመልስ፥ "ራሴን ለቅድስት ሥላሴ ስላስገዛሁ ርባዔ[160] አላደርግም" አለው። ያ ሰው ደግሞ፥ "ለንጉሥ ካልሰገድክ (97^ለ) ታዲያ ከማን ምድር ላይ[161] ትኖራለህን" አለው። ቅዱሱ እንዲህ አለው፥ "ቤተ ክርስቲያን የታነጸችው በቅዱሳን ሐዋርያት ላይ እንጂ በምድር ንጉሦች ላይ አይደለም። ስለዚህ ሞገዶች በማያናውጧት፥ ክርስቶስ በገነባልን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አኖራለሁ።"

ሰባቂው ይኸንን ሲሰማ በጥድፊያ ሮጦ ከአስተማሪው (ከሰይጣን) መንፈስ የሚገኝ ውሸት ጨምሮ ለንጉሡ ነገረው። ከዚያ፥ ንጉሡ በጠባዩ የሚተባበረውን ወታደሩን ወደ ቅዱሱ ላከው። የቁጣውን ጩኸት አንዲያበርድለትም አዘዘው።

ይህ መልአከተኛ (98^ሀ) ብዙ ሠራዊት ያላቸውን የሀገሩን ገዢዎች ሰብስቦ፥ (ሠራዊቱም) የጦር መሣሪያ ታጥቀው፥ በኤጲፋንያ ዕለት፥ በቅድስት ጥምቀት በዓል በትምህርት አደባባይ ተሰብስበው ስለ እስራኤል ልጆች (ከግብጽ) መውጣት የቅድስት አሪት መጽሐፍን እያነበቡና ቅዱሱ እንዳስለመደው ሲተረጉምላቸው መጡ። ያ መልአክተኛ መጥቶ ለአርዳታ የቀጠራቸው አስኪደርሱለት ድረስ የተልእኮውን ከፋት ደብቆ ቅዱሱን በምጸት አነጋገር አነጋገረው።

ክፉዋ ፍላጎቱ ስትገለጽ፥[162] አንድ ሰው ሳይተው ሊደባደብ ተነሣ። ቅዱስ አባታችንን (98^ለ) በንጹሕ መንፈስ ቅባት የጣፈጠ የሕይወቱን ውበት ሳያፍር ጠንካራ ምት መታው። ደግሞም ከሥጋውያንና ከሰይጣናት የመጣ ሕማማት በመሸከም የመነመነ የሰውነቱን አባላት መድረቅ አላሰበም፥ ሁለቱ[163] ከቅዱሳን ጋራ ለመዋጋት ተባባሪዎች ናቸው።

ያንን ቅዱስ ሽማግሌም ለሞት አስኪቀርብ ድረስ ከመሬት ላይ ወቃው። ሁሉንም ደማቸው ከመሬት ላይ አስኪፈስ ድረስ ነዶ በውድማ ላይ እንደሚወቁ በዘንግ ደበደባቸው። ብዙ ዕንጨት ሰብስበው አሳት አነደዱና

160. "ሥላሴ" አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስትሆን፥ "ርባዔ" በሶስቱ አካላት ላይ አራተኛ አካል መጨመር ነው። በአባ አስጢፋኖስ አስተያየት ለንጉሡ ከተሰገደ ንጉሡ ከአብ፥ ከወልድ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አራተኛው አካል መሆኑ ነው። "ሥላሴ" ማለት "ሶስትነት" ማለት ነው። በግዕዝ እንዳንድ እንደዚህ ያሉ ቃላት ("ሥላሴ"ን ጨምሮ) እንስታይ ጾታ ናቸው። እንግዲህ "ሥላሴ" ቃሉ ነጠላ ቁጥር፥ እንስታይ ጾታ ስለሆነ ለምሳሌ እንደ ቅድስት ማርያም "ቅድስት" (ቅድስት ሥላሴ) እንጂ፥ እንደ ጳውሎስ "ቅዱስ" ወይም እንደ ብዙ ጻድቃን "ቅዱሳን" ማለት ስሕተት ነው። "ሥላሴዎች" ማለትማ የስሕተት ስሕተት ነው።

161. ምድር የንጉሥ ንብረት መሆኗን ዜጋው ሁሉ ተቀብሎታል። አባ አስጢፋኖስም "በምድርህ ላይ እንደዚህ እንድንኖር ካልፈቀድክ ወደ ምድረ በዳችን ስደደን" ማለታቸው በዚሁ እምነት ነው። ንጉሡም ማንንም ከሀገሬ ውጣ ሊል ይችላል።

162. "የመጣበትን ጉዳይ አሳውቆ" ሰማለት ነው።

163. ሥጋውያንና ሰይጣኖች።

ቅዱሳኑን እሳት ውስጥ ሊጨምራቸው አስፈራራቸው። ሊገቡ እንደጨከኑ ሲያይ ከለከላቸው። ከዚያ፥ ቅዱሱን በሰደቱ ሁሉ ይሸከሙበት የነበረውን ወምበር (99ᵘ) በእሳት አቃጠለው። የሚተኛበትን ጉዝጓዝም እንደዚሁ አደረገበት።

ደግሞ፥ ባለብዙ ሠራዊት የሆነው አፈ መኰንን ቱልቱላ እያስነፋ መጣ። መልእክተኛው እንዲረዱት ተጣራ። ደብዳቢዎቹ እስኪደክማቸው ድረስ ቅዱሳኑን እያንዳንዳቸውን በዱላ ደበደቧቸው። ሲመሽ ሁሉንም በእንድነት ሰበሰቡና ቅዱሱን በማነቆ አሰሩት--ሽማግሌውንም እንደዚሁ።

ለፍርድ ቀረቡ

በማግሥቱ እንዲያቀርቧቸው አዘዘ። (ሲቀርቡ) ቅዱሱን እባታችንን፥ "ስንኑሥ ሰገድ" አለው። ብፁዑ፥ "እምቢ ብየሃለሁ" አለው። ከዚያ፥ በቁጣ (99ᴬ) መሬት ላይ ወረወረው። በበትርና በዱላ ደበደበው። ደግሞ እያንዳንዳቸውን እንዲሰግዱ ግዴታ አመጣባቸው። እነሱም እንዳባታቸው እምቢ ሲሉት ደማቸው እንደትናንቱ እስኪፈስ ድረስ ደበደባቸው። ሁሉንም ከግንድ ጋራ አሰሯቸው። ከዚያ፥ የቅዱሱን ማደሪያ እሳት ለቀቀበት። የደከሙበትን ሁሉ ወሰዱት፤ ልብሳቸውንም ገፈፏቸው።

ከዚያ፥ ጥር ፲፪ ቀን ወለዳቸው። ቅዱሱ መሄድ ሲያቅተው በወምበር ላይ እንዲሸከሙት አደረገ። የካቲት ፮ ቀን የትግራይ ገዢ ዓጸላ በነበረበት ጊዜ ወደሱ አመጡት። ቅዱሳኑን (ንጉሡ) እንዳዘዘ እንዲቀጣቸው መልእክተኛው የንጉሡን መልእክት ነገረው። (100ᵘ) ቅዱሱን ከበሽታው አልጋ አወረዱና በገዢው ፊት አቆሙት። እንዲሰግድ በማሰፈራራት እያዘዙ በሞኝነት ጭቅጭቃቸው አነጋገሩት። ቅዱሱ በሕግ ቃል እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "ስዎች ለእግዚአብሔር ካልሆነ ለሌላ እንዳይሰግዱ ተጽፏል።"[164]

ያ መልእክተኛ የቅዱሱ እነጋገር የሰዎች ልብ እንደሚማርክ ሲያይ፥ እንዳይናገር ከለከለው። በጥድፊያ አጋድመው ፲፭ ጊዜ ገረፉት። ከዚያ፥ ቅዱሳኑን ሁሉ ደማቸው እንደ ውሐ እስኪፈስ ድረስ በበትር ደበደቧቸው። በተለየም አቡነ ገብረ ክርስቶስን ለሞት እስኪያደርሱት ድረስ (ደበደቡት)። ነገር ግን (100ᴬ) ለዚች ዜና ዝክር ነጋሪ እንዲሆነን እግዚአብሔር (ከሞት) አነሣልን።

ከዚህ በኋላ፥ ቅዱሱን አንሥተው ከበቅሎ ላይ ጫኑና በአገረ ገዢው አጥር ግቢ ውሰጥ ወዲያና ወዲህ አዞሩት። ያም መልእክተኛ፥ "እነሆ ትሕርምትህ ተሻረ" እያለ ያሾፍበት ነበረ። ቅዱሱ ደግሞ የበቅሎውን ልጓም ሳይዝ እንዲሁ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ፥ "ስይጣን ከነሠራዊቱ ይፈር፤ እኔ ዓለምን ክጃለሁ" ይል ነበረ።

አንዳንዶቹ፥ "እንደዚህ ሆኖ ከሄደ በመንገድ ይሞታል፤ ንጉሡ እንዲያገኘው ከፈለገ እንደበፊቱ ይሸከሙት" (101ᵘ) አሉ። ከበቅሎው

164. ዘፀ 5: 10።

እወረዱትና መሸከሚያ አዘጋጁለት። በቀኙና በግራው ሰንሰለት÷ ባንገቱ ማነቆ አሰሩበት። ለልጆቹ የሞፈሮች እና የቀምበሮች ማነቆ አድርገውባቸው ሁለት ሁለቱን በአንድ ማነቆ አቆራኝተው እያስጨነቁ ወሰዷቸው። ደግሞ ደማቸውን በመንገድና በገበያ ያፈሱ ነበረ። ከዚህ በኋላ ልጆቹን በእሰራት እንዲያቆዩዋቸው እዚያ ባሉት ሠራዊት ውስጥ ቢታተኗቸው። ቅዱሱን ግን ከሚከተሉት ከ፬ ወንድሞች ጋራ በጥድፊያ ወሰዱት።

በንጉሡ አደባባይ

በየካቲት ፳፩ ቀን ከንጉሡ ሰፈር እደረሷቸው። (101ᵃ) የክህነት ልብሱን ቀደዳ እስኪጨምርበት ድረስ ከነቢዩ ምለጋናን እንደፈሰገ እንደዚያ እንደ ቂስ ልጅ[165] በስግደት እንዲያመሰግነው ወደ ቅዱሱ በሽንገላ እየላከበት ከፊቱ ሳያቆመው ፫ ወር እስቀመጠው። እንደማይታዘዝለት ንጉሡ ሲረዳ÷ ቅጣት የሚያቃልሉበት መዳኒት እላቸው እንደሆነ ብሎ የቅዱሱንና የልጆቹን የአስኬማ ልብስ እንዲፈትሹ ወታደሮቹን አዘዛቸው። ቀበቶዋቸውን ፈቱ፤ ቆባቸውንና የአስኬማቸውን ማረፊያ አወለቁ። (ምንም ነገር ሲያጡ) የሚሉት ጠፋቸው።

(102ᵘ) ከዚያ÷ ንጉሡ ግንቦት ፲፰ ቀን የእደባባይ ሽንጎ ሰበሰበና ቅዱሱን እንዲያቀርቡት አዘዘ። ከልጆቹ ጋራ በእቅጣጫው ፊት ለፊት አቆሙት። ከዚያ÷ ንጉሡ ወደ ቅዱሱ እንዲህ ሲል ጎከበት፤ "ይኸ እንደ ባልደረቦችህ እንደ (ሌሎቹ) ሰዎች እላደርግም የምትልበት ትዕቢትህና ትምክሕትህ ምንድን ነው? ይኸንን የቀድሞዎቹስ እላደረጉትምን? አብርሃም ለኤሞር ልጆች ሰግዷል፤[166] ያዕቆብም ለዔሳው።[167] ደግሞ ሌሎች ብዙዎች እድርገውታል። እንተ ልታደርገው የኮራህበት ምክንያት ምንድን ነው?"

ቅዱሱ ለጎካቸው እንዲህ በሉት እላቸው፤

> ምንድን ነው ይኸ ብዙዎች ሁሉ እድርገውታል በማለት የነገር ድካም? (102ᵃ) ከብዙዎች አድራጎት ይልቅ "ሰማይና ምድር ያልፋል፤ ቃሌ ግን አያልፍም"[168] ያለው የእግዚአብሔር ቃል ምስክራ ይበልጣል። ምክንያቱም በመጀመሪያ በኦሪት ለሱ ብቻ ካልሆነ ለሌላ እንዳንሰግድ በቃሉ አዞናል። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በሥራው ግልጽ አድርጎ አሳይቶናል። እንደዚያ አድርገን ፈለጉን እንድንከተል አዝዞናል። አሁንም ለሕግ መገዛት ከቻልክ ለኛም ላንተም (ሕግ) በመስነው ይሁንን። እንደዚህ እንዲሆን ካልፈቀድክ ራሱ ጌታ "አንድ ባሪያ ለሁለት ጌቶች መገዛት አይችልም"[169] ብሏል። እኛ ራሳችንን ለቅድስት ሥላሴ አስገዝተናል። ስለዚህ ለሌላ (103ᵘ) መገዛት እንችልም።

---

165. የቂስ ልጅ የሚሉት የመጀመሪያውን የእስራኤል ንጉሥ ሳኦልን ነው። ታሪኩ 1 ሳሙ 19: 22-24 ላይ አለ።
166. ለኬጢ ልጆች፥ ዘፍ 23: 7፤ ኩፋ 17: 30።
167. ዘፍ 33: 3።
168. ማቴ 5: 18፤ ሉቃ 16: 17።
169. ማቴ 6: 24።

(መልእክተኞቹ) እንደዚህ ብለው ሲነግሩት፥ እንዲገርፉት በቁጣ አዘዘ። የማርያም ንጽሕና አርአያ የሆነችውን አስኬማ ልብሱን[170] ቀደዷት። እጆቹንና እግሮቹን አስሩና ያላንዳች መንቀሳቀስ በትዕግሥት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ፫ ጊዜ ገረፉት። ልጆቹንም እንደዚሁ ገረፏቸው።

ከትቦ ወደ ኤፋትና ወደ ጓትር ግዞት

ንጉሡ ለሎሌው እንዲህ አለው፤ "እጆቹን ከተባቸው፤ ባሪያህ አይደለሁም ብሎኛልና መግዛቴን አሁን አሳየዋለሁ።"[171] በረጅሙ ከተበው፤ ልጆቹንም እንደዚሁ።" እጆቹን በምላጭ ተለተሏቸው። ሲተለትሏቸው ሥጋ የሌለው ቆዳ እንደስነጠቁ ሆነ እንጂ ደም ጠብ አላለም። (103[ለ]) የልጆቹንም እጆች ተለተሏቸው።

ከዚያ በኋላ፥ ልጆቹን ከእሱ እንዲለዩዋቸው አዘዘ። ወደ ኤፋት[172] ስደዷቸው፤ ስማዕትነታቸውን እዚያ ፈጸሙ። ቅዱሱን ግን ብቻውን ወደ ጓትር[173] ስደደው። (እዚያ) አስር ቤት ውስጥ እንዲዘጉበት አዘዘ። ሠኔ መባቻ ላይ ጓትር አደረሱት። እጆቹንና እግሮቹን በእግር ብረቶች አስረው፥ ዋዝርማ በምትባል ከተማ ጭለማ ቤት ውስጥ ዘጉበት።

ቅዱሱን ከዘጉበት በኋላ ንጉሡ በየጓዳሞቻቸው ወደሚኖሩት የቅዱሱ ልጆች ዘንድ እንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "አነሆ መምህራችሁ አስጢፋኖስ (104[ሀ]) የመንግሥታችንን የክብር ሥርዓት ሲሽር ነበረ። አሁንም እናንተ ለቃሌ እንደሚታዘዙት አንደሌሎቹ መኮሴዎች ለመንግሥቴ ሕግ የምትታዘዙ ከሆነ (አሁን) እንደምትኖሩት ኑሩ። እንደዚህ የማታደርጉ ከሆነ ከሀገሬ ውጡ።"

የንጉሡ መልእክተኛ መጥቶ ለልጆቹ እንዲሁ ብሎ ነገራቸው። እነሱም በአንድ ቃል እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤ "አባታችን አስጢፋኖስ ወንጌል እንዳዘዘው ክርስቶስን ተከትሏል፤ እንደዚሁ እኛም አባታችንን እሱ እንዳስተማረን እንከተለዋለን፤ ሌላ ነገር አንፈልግም።"

---

170. "አስኬማ ልብሰቶ እንተ ይእቲ አርአያ ንጽሕ ዘማርያም" ("የማርያም ንጽሕና አርአያ የሆነችውን የአስኬማ ልብሱን") የሚለው አነጋገር ትንሽ ግር ይላል። በጎዳግ ቍጥር 24 ስር እንደተገለጠው፥ አስኬማ የስማይ መላእክት ("መላእክት ዘአርያም") የንጽሕና ልብስ ምሳሌ ሆኖ ሳለ፥ ደራሲው ያንን ትቶ ድንገት ከማርያም ንጽሕና ጋራ ያመሳሰለው ምናልባት ወይ ራሱ ደራሲው ወይም ቀጂው ስለ ቅድስት ማርያም የነበረውን ውዝግብ የቀነስ መስሎት "ዘአርያም" ("የሰማይ") የሚለውን "ዘማርያም" ብሎት ይሆናል። ጥያቄውን ያነሣሁት ደቂቀ አስጢፋኖስ የቅድስት ማርያምን ንጽሕና አያምኑም ማለቴ አይደለም፤ ያምናሉ፤ ግን ቦታው "ዘአርያም"ን እንጂ፥ "ዘማርያም"ን መጥቀሻ መስሎ ስላልታየኝ ነው።

171. ባሮች የማን ንብረት እንደሆኑ በሚያሳይ ከትባት ይከተቡ እንደነበረ ያሳያል። የከተቧቸው በ"ዘ" ነው--"የዘርአ ያዕቆብ ባርያ" ስማለት።

172. "ኤፋት" ይፋት ነው። በዚያን ጊዜ ይፋት ዋና የእስላም ግዛት ነበረች። ገዢዎቹ ወላስማ በሚል ስም እስከ ራስ ሣህለ ሥላሴ ዘመን ይገዙ ነበረ።

173. ጓትር ደዋሮ ይባል በነበረው አውራጃ ነበረ። ደዋሮ በኋላ አሮሞዎች ሲይዙት አፋሲ (አርሲ) የተባለውን አውራጃ ሳይጨምር አይቀርም። በዚያን ጊዜ የደዋሮ ሕዝብም እስላም ነበረ።

በዚህ ጊዜ፥ እንደታዘዙት ከየገዳሞቻቸው አባረሯቸው። (104ᴬ) የደከሙበትን ሁሉ ነጠቋቸው። የቅዱሱ ልጆች ወደ ምድረ በዳና እግዚአብሔር እንዲጠበቁ ወዳዘጋጀላቸው ቦታዎች ሸሹ፤ የክርስቶስ የዚህ ዓለም ሙሽራ[174] ሕጓ እንደዚሁ ነውና።

እቡነ ገብረ ክርስቶስ ከንጉሡ ፊት

ከዚህ በኋላ፥ ይኸ መልእክተኛ እንደታዘዘው እቡነ ገብረ ክርስቶስን ከእንድ ወንድም ጋራ ይዞ ከንጉሡ ዘንድ እመጣው። ንጉሡ እንዲህ ሲል ላከባቸው "ይኸ የአባታችንን አንተውም የምትሉበት ትዕቢታችሁ ምንድን ነው? ደግሞ ሌሎችን ወደ ትምህርታችን እንለውጣለን ትላላችሁ። እሁንም እባታችሁ ውሻ ነው፤ እናንተም ውሾች፥ ሰይጣን ጋላቢዎች ናችሁ። (105ᵁ) ለምንድ ነው እንደ ሰው ሁሉ የማታደርጉት?"

ቅዱሱ እባታችን እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕጌንና ትእዛዜን ጠብቁ ብሎ ሥርዓት ሰጠን እንጂ፥ እንደ ሰው ሁሉ ጠባይ እንድናደርግ እላዘዘንም። እባታችን እንደዚህ ሕጉን ጠብቋል፤ ተከትሎታልም። እኛም እንደዚሁ ከእባታችን ፈለግ ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ ፈቀቅ እንልም።"

ንጉሡ ይኸንን ሲሰማ እንዲገርፏቸው ትእዛዝ ሰጠ። ከገረፏቸው ዉኋላ ማመስከሪያ (ከሚባለው) ከአለቆች ማኅኪያ[175] ጣሏቸው።

የእቡነ እስጢፋኖስ ዕረፍት

እባታችን ቅዱስ እስጢፋኖስ (105ᴬ) እስር ቤት ተዘግቶበት እነሆ ስድስት ወር ቆየ። ከዚያ፥ በሰባተኛው ወር፥ በታኅሣሥ ፲፰ ቀን ጠባቂዎቹ፥ "ክርስቶስ" ብሎ ሶስት ጊዜ ሲጣራ ሰሙት። ይኸንን ብሎ ዝም አለ። በዚያን ጊዜ የሀገሬው ሰዎች እንዳረፈ አስኪረዱ ድረስ በዚያ ቦታ ትልቅ አስገራሚ ግርማና (የመሬት) መንቀጥቀጥ ሆነ። ከድንጋጤ የተነሣ እዚያ ቅዱሱ ከአለበት ቤት መቅረብ አልቻሉም።

በሕይወት በነበረበት ጊዜ እነዚያን አስላሞች እንዲህ ሲል አዟቸው ነበረ፤ "ሞቴን ሳደርስ አካሌን የሚገንዝ ከክርስቲያኖች ማህል ጌታ እስኪልክ ድረስ ሥጋዬን አትንኩ።" (106ᵁ) እነዚያ ፈልገው አንድ ክርስቲያናዊ አገኙ። ገብቶ እንዲያየው እሱን ቀጠሩት። ይህ ሰው ከፍቶ ሲገባ እነሆ ቅዱሱን አርፎ ከመሬት ላይ ተጋድሞ አገኘው። የቅዱሱ እጆች ከንፈሮቹንና

174. የክርስቶስ የዚህ ዓለም ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ነች።

175. እንደ ዓለም በቃኝ ሆኖ የፖለቲካ አስረኞች የሚጣሉበት ጎድጓዳ ቦታ መሆን አለበት። በገድለ አቡነ አበበክረዙኝ በገድለ አበው ወአንው ውስጥም ተነሥቷል። እዚያ የቦታዋ ስም ጉንጽ (ጉንጭ) ነው። ከዘርአ ያዕቆብ በፊት የነበሩ ነገሥትም የተጠቀሙበት እስር ቤት ይመስላል፤ ስምሳሌ፥ መነኩሳቱ እዬ ዓምደ ጽዮንን በተቃወሙት ጊዜ በቅጣት ሲበታትናቸው እቡነ ፊልጶስን የወሰዷቸው "ሀገረ

ዐይኖቹን በአንድነት ከድነዋቸው ነበረ። እጆቹና እግሮቹ ላይ የነበሩትን የእግር ብረቶች ከእካላቱ ተለይተው ለብቻቸው ሆነው አገኛቸው።[176]

ያ ሰው ከታየው ግርማ ፍርሃት የተነሣ እየተንቀጠቀጠ ወጣና የቤቱን በር ዘጋው። መሞቱን ለጠባቂዎቹ ነገራቸው። እነሱም ስለ አቀባበሩ፥ (106ʌ) እዚያው ወይም ከሌላ ቦታ እንዲቀበር፥ ያዝዝ እንደሆነ ሊጠይቁት ወደ አገረ ገዢው ላኩበት።

የዚያች ሀገር አካባቢ ክርስቲያኖች ሰምተው ሊቀብሩት መጡ። ግን ጠባቂዎቹ የገዢውን ትእዛዝ ስለሚጠብቁ አልፈቀዱላቸውም። ከአንድ ሳምንት በኋላ መልእክተኛው፥ "እዚያው ቅበሩ" የሚል (መልስ ይዞ) መጣ። ቅዱሱ ሰማዕትነቱን ከፈጸመ ጀምሮ አስከሬኑን ለመቅበር እየጓጓ አዘውትሮ የሚመላለስ አንድ ዲያቆን ነበረ። ለዚያ ዲያቆን ሊቀብረው እንደፈለገ እንዲቀብረው ፈቀዱለት። በታኅሣሥ ፳፬ ቀን በሚገባ ገንዘ ከከተማው አንድ ሰዋራ ቦታ ቀበረው። ጸሎቱ፥ በረከቱ (107ᵁ) ልመናው ለዘላለም ከኛ ጋራ ይሁኑ፤ አሜን።

አስከሬኑን ለማፍለስ የተደረገ ሙከራ

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የቅዱሱ ልጆች አባታቸው ለሰማዕትነቱን እንደፈጸመ ሰምተው፥ ይኖሩበት ከነበረው ሀገር በሩጫ ተጣድፈው እዚያች ከተማ መጡ። መቃብሩ የት እንደሆነ ተረዱ። ከዚያ፥ የመጋቢት ፫ ቀን አጥቢያ ላይ ሌሊቱን የቅዱሱን አስከሬን ወሰዱት። ወደ ትግራይ ሲወስዱት ከግድም ሀገር ኬላ እመንገድ ላይ ያዟቸውና ወደ ሀገረ ገዢው ወሰዷቸው። ሀገረ ገዢው በእስራት እንዲያቆዩዋቸው አዘዘ። (107ʌ) የቅዱሱን አስከሬን ግን ከቤተ ክርስቲያን አስቀመጡት።

አገረ ገዢው ይኸን ነገር፥ የቅዱሱ ልጆች ያባታቸውን አስከሬን ሲወስዱ እንደተገኙ፥ ወደ ንጉሡ ላከ። ንጉሡ ሲሰማ በጣም ተቈጣ። የመምህራቸውን አስከሬን ሲወስዱ የተያዙትንና ሌሎቹንም በፊት ከአባታቸው ጋራ ታስረው በትግራይ ገዢ እጅ የነበሩትን ሁሉ እንዲያመጧቸው አዘዘና ሁሉንም በአንድነት ከፊቱ እንዲያቆሟቸው አዘዘ።

(ከፊቱ ሲቆሙ) እንዲሰግዱለት እያዘዛቸው አባታቸው በተጋደለበት ጉዳይ ይከራከራቸው ጀመረ። እነሱም እንዲህ ሲሉ እምቢ አሉት፤ "እኛ (108ᵁ) ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆ ለሌላ አንሰግድም። ከአባታችን የተማርነው የእግዚአብሔር ሕግ እንደዚህ ነው። እንደተማርነው እንጂ፥ በዚህ ላይ መጨመር ወይም (ከዚህ) ማጉደል አንችልም።"

ጕንጥ" ነው፤ Stanislas Kur, *Actes de Samuel de Dabra Wagag, CSCO*, vol. 287/57 (1968), p. 10. "ጕንጥ" "ጕንጽ" መሆኑ አያጠራጥርም። ምሳሌው ግልጽ ይመስለኛል፤ ከብቶች የበሉትን ከሆዳቸው እያመጡ በጉንጫቸው ይዘው እንደሚያኝኩ፥ የመኳንንቱም ቅጣት እዚያ ጎድጓዳ ቦታ ተጥሎ መታሸት/መታኘክ ነው።

176. ለቅዱስ ጴጥሮስ የሆነውን ተአምር ያስታውሰናል፤ የሐ ሥራ 12: 7።

እሸ. ማሰኘት ሲያቅተው አንዲገርፏቸው አዘዘ። ደማቸው እንደ ውሐ ከመሬት ላይ እስኪወርድ ድረስ ገረፏቸው። ከዚያ በኋላ እያንዳንዳቸውን (ነጣጥለው) ወደ እስላሞች ከተሞች እንዲበታትኗቸውና በእስራት ጭንቅ እንዲያስቃዩዋቸው ትእዛዝ ሰጠ። ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው አደረጉ።[177] የቅዱሱን አስከሬን ግን እንዲቀብሩት አዘዘ። በጥቅምት ፭፪ ቀን፥ ልጆቹ (108ʌ) (አስከሬኑን) ከጓትር ባወጡት በስምንተኛው ወር፥ እግድም ሀገር ቤተ ክርስቲያን ቀበሩት።

ከዚያ በኋላ፥ ንጉሡ የቅዱሱን ልጆች ከሚገኙበት ቦታ ሁሉ እንዲሰበስቡለት ለወታደሮቹ ትእዛዝ ሰጥቶ ወደ ትግራይ አገሮችና ወደ ሌሎች ሀገሮችም ሁሉ ላከ። ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው (እየያዙ) ያመጡለት ጀመረ። ንጉሡም በየጊዜው በማሰቃየት ደከመ። ማሸነፍ ሲያቅተው ጊዜ በዚህ (ሰማዕትነቱን) በፈጸመ በክርስቶስ መልእክተኛ፥ በአባ እስጢፋኖስ ላይ እንዲህ ሲል ተቆጣ፤ "የትምህርቱ ስብከት እንደዚህ መሠረት ያዘች እኮ!"

ከመቃብሩ ፈውስ ማግኘት አስቆጣ

ደግሞ መቃብሩን የጐበኙ በሽተኞች ፈውስ (109ʊ) እንደሚያገኙ ተሰማ። በዚህ ሁሉ ምክንያት፥ የቅዱሱን አስከሬን ከመቃብር አውጥተው ወደሱ እንዲያመጡት እስኪያዝ ድረስ ልቡ ተቃጠለ፤ በቁጣ አረረ። ሰማዕትነቱን ከፈጸመ ከሁለት ዓመት በኋላ፥ ጥር ፪ ቀን ከመቃብር አውጥተው ወደ ንጉሡ ወሰዱት። እዚያ ወስደው ከሰፈሩ አጠገብ ካለው ቤተ ክርስቲያን አስቀመጡት። የመገነጥውን ልብስ ሲገልጡት አስከሬኑን ከቀድሞው ሳይለወጥ አገኙት። ገና በዚያን ጊዜ የሞተ ይመስላል።

---

177. በሕዝብ ዘንድም ከዚህ በታች ያለውን ዓዋጅ እንዳወጀ የራሱ መጽሐፍ ይመሰክራል፤ "በሁለት መንገድ ድንግል የሆነች የማርያም ምእመናን የሆናችሁ ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ፥ ስለ ደቂቀ እስጢፋ እንዲህ እላችኋለሁ፥ እነሱን (በእንግድነት) የተቀበለ፥ ከነሱ ጋራ ምንም ነገር የሠራ፥ በቤቱ፥ በቤተ ክርስቲያኑ፥ በርስቱ ያስቀመጣቸው፥ ሹም ከሆነ ይሻር፤ ቤቱም ገንዘቡም በሞላ ይዘረፍ፤ ርስቱ ለባዳ ይሁን። ሊቃነ ካህናትና ንቡራነ እድ፥ የቤተ ክርስቲያን ሹሞች ሁሉ፥ መነኮሴዎችም ሕዝብም እነሱን ደብቀው ከተገኙ፥ የነሱ ግብር አበሮች ሆነዋልና ቅጣታቸው (ከዚህ) የባሰ ይሁን። ሹመታቸው፥ የቤታቸው ንብረት በሞላ፥ ርስታቸውም ለሌላ ሰው ይሁን። እነዚህ ደቂቀ እስጢፋ በእርግጥ በሁለት መንገድ ድንግል ለሆነች ለማርያምና ለእንድ ልጁ መስቀል ለመስገድ እምቢ ያሉ አይሁድ ናቸው። የሚገባቸው ቅጣት ሞት ነው። ያገኛቸው ክፉ ቅጣት ይቅጣቸው፥ ሆኖም ቃላቸውን እንድንሰማና እንዲፈረድባቸው ከችሎታችን ያምጧቸው እንጂ መግደልስ እይግደሏቸው። ለእስጢፋ ስላምታ ሲሰጥ የተገኘ ሰውም ቅጣቱ ደቂቀ እስጢፋን እንደተቀበሏቸው ይሁን"፤ Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 261/51, p. 48.

ሬሳቸው እስላም አገር እንዲቃጠል ትእዛዝ መጣ

ከ፫ ወር በኋላ ደግሞ፥ ንጉሡ ወደ ደዋሮ ምድር ጻከራ ወደምትባል ከተማ እንዲወስዱት እዘዘ። (109ᴬ) ምክንያቱም እዚያ የዓደል ገዢ የሆነ የእስላሞች መቃብር ስላለና (የዓደሉ ገዢ) ንጉሡን ይቃወመውና በሥጋ ልማድ እርስ በርሳቸው ይዋጉ ስለነበር ነው። ይኸ የክርስቶስ መልእክተኛ የሆነ አባታችን ቅዱስ እስጢፋኖስ ግን ዓለምን የሚቃወማት፥ "የምድር ዳርቾች ሁሉ አስተውለው ወደ እግዚአብሔር ይመለሱ፤ የሕዝቦች አገሮች ሁሉ ከሱ ፊት ይስገዱ፥ መንግሥት የእግዚአብሔር ናትና"[178] ተብሎ እንደተጻፈው ለክርስቶስ መንግሥት ምስክር በመሆን በሃይማኖት ሰይፍ ነበረ። ንጉሡ በዚህ ተቆጥቶ እንደዚህ ያለውን የክርስቶስ መልእክተኛ (110ᵁ) ከሚበላሸው ከዚያ፥ ከሌቦች መልእክተኛ ጋራ አስተካከለው።

በእንድ (ልጁ) የሕማማት (ስሞን) የቅዱሱን ሥጋ እዚያ ወስደው የጌታ ለቅለት ዕለት፥ የፋሲካ ዓርብ ከጻክራ እመጡት። በማግሥቱ በሰባተኛይቱ ዕለት በፋሲካ ዋዜማ፥ ሚያዝያ ፲፫ ቀን የሀገሩ ሰዎች በንጉሡ ትእዛዝ እዚያ እስላሞች መቃብር ዘንድ ተሰበሰቡ። መልእክተኛው የቅዱሱን አስከሬን ከፊታቸው አስቀመጠና የንጉሡን መልእክት እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ "ይህ ሰው ከሐዲ ነው፤ አገሩን ሁሉ ወደ ትምህርቱ ሲያስክድ ነበረ። ጠባዩ ሁሉ እንደዚህ አስላም ነው። ስሙ (110ᴬ) አስጢፋኖስ ነው። አሁንም በድኑን ውሰዱና በእሳት አቃጥሉት።"

ቅዱሱ ሰማዕትነቱን ከፈጸመ ጀምሮ እስከዚያች ዕለት ሁለት ዓመት ከ፬ ወር ሆኖ ነበረ። ብዙ እንጨት አምጥተው በአስከሬኑ ላይ እሳት አነደዱበት። በማንደድ ደከሙ፤ እስኪመሽ ድረስ እንደዚሁ ዋሉበት። ከዚያ በኋላ ብዙ ድንጋይ ሰብስበው ከመሩበትና በዚህ ሁኔታ ተውት። ጸሎቱና በረከቱ ለዘላለም ከኛ ጋራ ይሁኑ። አሜን።

የደቂቀ እስጢፋኖስ አዲስ ስደት

ከዚህ በኋላ፥ ንጉሡ ደግሞ የቅዱሱን ልጆች (ኑሯቸውን) እስኪያጠባባቸው (111ᵁ) ድረስ በግዛቱ እንድም ላለማስተረፍ ፈልጎ ሊያሠቃያቸው በጎይል ተነሣ። እነዚያን ዘመኖች እንደ ሌሊት (ጨለማ) አደረጋቸው። ግን "ሌሊቱ እንደ ቀን ብርሃን ነው፤ በጭለማዋ መጠን ብርሃኗም ያንኑ ያህል ነው"[179] ተብሎ እንደተጻፈው ክርስቶስ በብርሃኑ ምስጢር ረዳቸው።

ከቀጣቸው በኋላ ጦርነትና ግዞት መምጫ ወደሆነው የመንግሥቱ ምሥራቃዊ ወደሆነው ወደ እስላሞች ሀገሮች ይበትናቸው ጀመር። እዚያ በእሥራት፥ በግንድና በማነቆ (እያቆራኙ) ያሰጨንቋቸው ነበረ። ደግሞ በማራቆት ሲቀልዱባቸው የእስኬማ ልብሳቸውን እየገፈፉ፥(111ᴬ) አቧራ በላያቸው ላይ እያቦኑ፥ የራስ ጠጉራቸውን ሲላጩ እየነጩ፥ ያለምንም

178. መዝ 21: 27-28።
179. ?።

ምሕረት በበትር እየደበደቡ፥ ደግሞ በጦር ጫፍ አካላቸውን እየጓጐጡ፥ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲያሠቃዩዋቸው ብዙዎቹ ስማዕትነታቸውን ፈጸሙ።

አቡነ ገብረ ክርስቶስ እግሮቹ ፫ ዓመት ታስረው ተሠቃይቶ መጋቢት ፪ ቀን ስማዕትነቱን ፈጸመ። የጸሎቱ በረከት፥ የሱም የወንድሞቹም ሁሉ፥ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ይሁኑ፤ አሜን።


አስክሬኑን ከመቃብር አውጥተው ደበቁት

(112[ሀ]) የቅዱሱን ሥጋ ካቃጠሉ (ከብዙ) ዓመቶችና ዘመኖች በኋላ፥ እግዚአብሔር (የተረፉ) ወንድሞችን ጠርቷቸው እዚያ ቅዱሱን ካቃጠሉበት ቦታ መጡ። ድንጋዮቹን ቢያነሡ፥ እግዚአብሔር ፈለጉን ለሚከተሉ መመኪያ እንዲሆናቸው የመጋረድ ምስጢሩን ለማላየት የቅዱሱን ዐፅሞች ከአስኬማውና ከመግነዟ ልብስ ጋራ ገለጸላቸው። ከዚያ በኋላ፥ ሠኔ ኻያ አምስት ቀን ወስደው እግዚአብሔር ከፈቀደበት ቦታ ደበቁት።[180] የዚህ ተጋዳይ አቡነ አስጢፋኖስ ጸሎት፥ ልመናው፥ የእርዳታው ጸጋ ከኛ ጋራ (112[ለ]) ለዘላለም ይኑሩ፤ አሜን።

(ይኸንን ገድል) የጻፈውን፥ የአስጻፈውን፥ ያነበበውን፥ ቃሎቹን በእምነት የሰማውን እግዚአብሔር በአንድነት ለዘላለም ይማረን፤ አሜን። ይቅር በሉኝ፥ ባርኩኝ።

---

180. የሙሴን አስክሬን ፍጻሜ ያስታውሰናል። ሁሉንም የሚቀብሯቸው ከአልታወቀ ቦታ ነው።



የማቴዎስ የማርቆስ የሉቃስ ወንጌል አቅማራት
(EMML 7219, f. 14b.)

ገድለ አበው ወአኀው

"ጌታ ሆይ፥ (የተከሰሱትን) ራሳቸውን ገምሰን አንጐላቸውን እንድናፈሰው ለኛ ስጠን::"

የብትር ሠራዊት



በግብጽ ምድረ በዳ የብሕትውና ምንኵስናን የጀመሩ አባ እንጦንስ
(ከደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሐፍ፡ MS Spencer 7, f. 3b.)



(2^{ሀ}) የታኅሣሥ ፭፩ ምንባብ

መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ።

በደብረ ገርዜን የኖሩትን፥ የመድኅንን ሥቃዮች የተካፈሉትን የቅዱሳን መንፈሳውያን አባቶቻችንንና ወንድሞቻችንን፥ የምእመናትና የምእመናንን ገድል በእግዚአብሔር ረድኤት፥ ጌታ በሚቀጥለው ተአምር እየረዳ፥ ቃሉም እያበረታ (መጻፍ) እንጀምራለን፤ አሜን።[1]

የቅዱሳኑን ገድላቸውንና ሰማዕትነታቸውን በመጽሐፍ ለሰው ማሳየት ለኔና ከኔ በኋላ ለሚመጡ እንደኔ ላሉት ጠቃሚ እንደሆነ ሐሳብ ሲመጣብኝ ከብዙ ቀናትና ዓመታት በኋላ ከኔ በፊት የሆነውን እየጠየቅሁ፥ በኔ ጊዜ የሆነውን እንደማውቀው አደርገው ዘንድ ወደድኩ። (2^{ለ}) ግን ከሀገሩ ርቀት የተነሣ ከማኅበሩ አለቃ ፈቃድ አላገኘሁም ነበረ። ተፈቅዶልኝ ቢሆን ኖሮ በየጊዜው የሆነውን (ወዲያው በዝርዝር) እጽፈው ነበረ። ባለመሆኑ፥ ሥራው አንሷል፤ ታሪኩም አጭር ይሆናል።

የመንፈስ አባታችን ሊቀ ማኅበሩ ሲፈቅድ ከወንድሞች አንዱን ይገፋ፥ ከሚያውቁ ዘንድ እየሆንንም በነዚያ ዘመናት የሆነውን ሁሉ ተነጋገርንበት። እነሆ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ ፍጡሮች ሆነው እንደ ፈጣሪ ስብሐትና ስግደት በሚፈልጉ በድብ ፀርና በልጁ በአድማስ በፀር የሆነውን ያስታወስኩትን ያህል በጥቂቱ ጻፍኩላችሁ። በግድያ በማሰፈራራት በግድ ለማስሰገድ ከእግዚአብሔር መጻሕፍት ከብሉይና ከሐዲስ ማስረጃ የላቸውም። ስለዚህ (3^{ሀ}) ከሰይጣንና ከጋጢአቱ ነፃ ትሆኑ ዘንድ በብፁዕና በቅዱስ እስጢፋኖስና በልጆቹ ላይ ከነዚህ ነገሥትና ከመኳንንት ዘንድ ገድል፥ የጻማ፥ የስደት፥ የችግር፥ የመከራ፥ የረኀብ፥ የውሐ ጥም፥ የመራቆት ብዙ ጣር ደረሰባቸው።

(የደቂቀ እስጢፋኖስ ትምህርትና የአባ እስጢፋኖስ ገድል) ...[2]

ጦጵያ ላይ ዓሥር ሞቱ

(25^{ለ}) ከዚህ በኋላ ንጉሡ ቅዱስ (እስጢፋኖስን) ለብቻው ወደ ጓትር እንዲወስዱት አዘዘ። እሰር ቤት እንዲዘጉበትም አዘዘ። እንዴት (ሰማዕትነቱን) እንደፈጸመ ከገድሉ መጽሐፍ ውስጥ አለ።

---

1. የሉቃስ ወንጌል የመግቢያው እጻጻፍ አለበት፤ ሉቃ 1: 1-3፤ የግዕዝ ደራሲዎቻችን ብዙ ጊዜ ይጠቀሙበታል።
2. ትምህርቱ በየአጋጣሚው እየተነገረ እዚህና በሌሎች ገድሎች ውስጥ ስለሚገኝ፥

ልጆቹን ደግሞ ጦጵያ ወደምትባለው ወደ ኤፋት እንዲወስዷቸው አዘዘ፡ እዚያ በብዙ ገድል ኖረው ስማዕትነታቸውን እዚያው በእግዚአብሔር ሰላም ፈጸሙ። ቍጥራቸው ፲ ነው። ጸሎታቸው ዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

"ለምን እንደ ሰው ሁሉ አታደርጉም?"

ከዚህ በኋላ፥ ንጉሡ አቡነ አባ ገብረ ክርስቶስንና አቡነ አባ ተወልደ መድኅንን መጀመሪያ በዐልቶ በምትባለው በቅዳ ካኖራቸው በኋላ ከንጉሡ ዘንድ አመጧቸው። ንጉሡ እንዲህ ሲል ላከባቸው፤[3] "የአባታችንን አንተውም የምትሉት ትዕቢታችሁ ምንድን ነው? ደግሞ ሌሎችን ወደ ትምህርታችን እንመልሳለን ትላላችሁ። አሁንም፥ አባታችሁ ውሻ ነው፤ አናንተም ሰይጣን የምትጋልቡ ውሾች ናችሁ። ለምን እንደ ሰው ሁሉ አታደርጉም?"

(26^{ሀ}) አቡነ ገብረ ክርስቶስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "እግዚአብሔር ሕጌንና ትእዛዜን ጠብቁ ብሎ ሥነ ሥርዓት ሰጠን እንጂ እንደ ሰው ሁሉ ልማድ እንድናደርግ አላዘዘንም። እንደዚሁ ቅዱሱ አባታችን ሕጉን ጠብቆ ተከትሎታል፤ እኛም ደግሞ ከአባታችን ፈለግ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አንወጣም።"

ለንጉሡ እንደዚሁ ብለው ነገሩት። እንዲገርፏቸው አዘዘ። ከገረፏቸው በኋላ ጉንጽ ከምትባለው የአለቆች ማኘኪያ ማመስኩያ (አስገቧቸው)። እዚያ በእስራትና በጽኑ ገድል እስከ ጊዜው ኖሩ።

አስረኛ መጠየቅ ያሳስራል

ከዚያ፥ የብሔረ ትግራይ ማኅበር አባታቸው በምን ሁኔታ እንዳለ፥ ወዴትስ እንደወሰዱት፥ ምንስ እንደሆነ እንዲጠይቁ ፪ ወንድሞች ላኩበት። አነዚህ ፪ ወንድሞች ከንጉሡ አደባባይ ደርሰው እዚያ አጠያየቁ። አንድ ሰው የአባታቸውን ዜና፥ እንዴት እንደገረፉት፥ እጆቹን እንደተለተሉት፥ ዋዝርማ ወደምትባለው ወደ ጓትር እንደወሰዱት ነገራቸው።

(26^{ለ}) ወዴት እንደወሰዱት ከሰውየው ተረድተው ወደዚያች ሀገር ሄዱ። ሲደርሱ አስር ቤት አስረውት አገኙት። መግባት አቅቷቸው ግምቡን ሲዞሩ ቅዱሱ አባታችን ገና ሰላምታ ሳይሰጡት አያቸው። ሲያውቃቸው፥ "እረ እንዳይዟችሁና እንዳይገድሏችሁ" አላቸው። እነሱም፥ "ሰላም ላንተ ይሁን፥ አባ ሆይ" አሉት። እጆቹን ዘረጋላቸው፤ ሳሙት።

ሲያነጋግሩት ቅዱሱን የሚጠብቁ የንጉሡ ወታደሮች ድንገት መጡና ከበቧቸው፤ ያዟቸው፤ ከሰፈሯቸውና ከአገረ ገዢው ዘንድ ወሰዷቸው። አገረ ገዢው ወደ ንጉሡ ላካቸው። (እዚያ) ሲደርሱ እንደታሰሩ (ከንጉሡ ፊት) አቆሟቸው። ንጉሡ እንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "እኛ ካስርነው ሰው ዘንድ ለመሄድ እንዴት ደፈራችሁ? እናንተ ምንድን ናችሁ? መጋረጃችንን

የአባ አስጢፋኖስ ገድልም ተተርጉሞ እዚሁ አብሮ ስለታተመ ይኸንን ከገጽ (ከቅጠል) 3^{ሀ} እስከ 25^{ለ} ያለውን ክፍል ዘልየዋለሁ።

3. ንጉሡ ከፊቱ ቢቆሙም ሰው እየላከ ("በአፈ ንጉሦች") ያነጋግራቸዋል እንጂ በቀጥታ በራሱ አፍ ከዜጎቹ ጋራ አይነጋገርም።

ልትቀዱ እንዴት (ደፈራችሁ)?" ቅዱሳኑ፥ "አዎን፥ በወንጌሉ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር በማስታወስ እንደዚህ አድርገናል። ምክንያቱም እሱ አስተማሪያችን፥ (27ᵇ) ወደ ሕይወት መንገድ መሪያችን፥ የነፍሳችን አባት ነው። ስለዚህ እሱን መጐብኘት እንፈራም" አሉ።

"የእስራኤላዊ ልጅ ነኝ" ስላለ በክስ ያመጡት አንድ የደብረ እምፍራዝ መጋቢ መነኮሴ (እዚያ ነበረ)። "ከሎሌዎቹ ጋራ ወደ እርሻው ሲመጣ ለራሱ የልብስ ተድባብ አድርጎ ይታያል" (በሚል) በዚህ ክስ ከቅዱሳኑ ጋራ አቁመውት ነበረ። (ንጉሡ) ስለዚህ ነገር አልመረመረውም፤ ብቻ፥ "እነዚህ ፪ቱ የመጋረጃችን ሰንጣቂዎች፥ የፀሐይ ጮራዎች ናቸው፥ እሱ ደግሞ መንግሥት ፈላጊ ነው። ስለዚህ፥ በል ቁጣዬን አስተንፍስልኝ" ብሎ እብረው እንዲገረፉ አዘዘ። ብዙ ገረፏቸው፤ እጆቻቸውን በምላጭ ተለተሏቸው። እንደዚህ (ቁጣቸውን) አስተንፍሰው ያንጎ ወደምትባል ወደ ግድም እንዲወስዷቸው አዘዘ። እዚያ ሰማዕታትነታቸውን በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ያንን (የእምፍራዝ) መነኮሴ አቡነ ገብረ ክርስቶስና አባ ተወልደ መድኅን ካሉበት ጉንጽ ከምትባለው የቅጣት ቦታ እንዲወስዱት አዘዘ። (27ᵃ) እንግዴህ የእምላካችንን ቸርነት ተመልከቱ፤ መዳን ሲፈቅድለት ከንስሐ በር አደረሰው። እዚያ ሲያገኛቸውና ሃይማኖታቸውን ሲያውቅ፥ "ንስሐ ስጡኝ" አላቸው። እነሱም ምዕዳን አስምተው ንስሐ ሰጡትና አብሯቸው ሆነ።

የአባታቸውን ዐፅም ሲያፈልሱ የተያዙ

የትግራዩ ማኅበር ቅዱስ አባታችን ሰማዕትነቱን እንደፈጸመ ሲያውቁ ዐፅሙን እንዲያመጡ ፲፪ ወንድሞች ወደ መቃብሩ ላኩ። ከመቃብሩ ደርሰው መጋቢት ፫ ቀን በሌሊት አወጡት። የመቃብሩን መዝጊያ ሲከፍቱት እንደዚያ ሽትቶ የማይታወቅ መዓዛ ወጣ። በዚያን ጊዜ ተደሰቱ፥ ደስ ተሰኙ፤ አወጡት። ለመከተት ጉልበቱንና ወገቡን ሲያጣጥፉት እንደፈለጉት ሆነላቸው። በደረሱበት (ሁሉ) በመንገድ ሽታው ሲያውድ ሰዎች፥ "የንጉሥ እቃ ተሸክማችኋልን?" ይሏቸው ነበረ።

በዚህ ሁኔታ ከግድም ኬላ ደረሱ፤ እዚያ ከነሱ ውስጥ አንዱ ሰይጣን ሆነባቸው፤ (28ᵇ) "ኬላ ጠባቂ ሆይ፥ ልንገርህ፤ ይኸ የሚወስዱት አስከሬን (ለንጉሥ) አልሰግድም ስላለ ንጉሡ አስር ቤት የዘጋበት አስጢፋኖስ ነው" አለው። ኬላ ጠባቂው ሲሰማ ቅዱሳኑን ያዛቸውና የሆነውን ለግድም ገዢ ነገረው። አገረ ገዢው ሰምቶ (ነገሩን) ወደ ንጉሡ ላከ። ንጉሡ (ወደሱ) እንዲያመጧቸው አዘዘ። ዘጠኙን ወንድሞች ወሰዷቸው፤ ፪ቱን እዚያው ከአባታቸው አስከሬን ጋራ ተዋቸው። (አስከሬኑን) ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀመጡት።

ከዚያ፥ ተከሥተ ብርሃን የሚሉት አንድ የደብረ ኮሰያት መነኮሴ ሲያይ፥ "እንደዚህ ለምን ታደርጋላችሁ? ይኸ ከታቦቱ ጋራ የምታጥኑት የንጉሥ ጠላት አይደለምን?" አላቸው። ሲሰሙ ፈርተው ከታቦቱ ዘንድና ከቤተ ክርስቲያን አውጥተው ከእቃ ቤት[4] አስቀመጡት። ንጉሡ የቅዱሱን አስከሬን መካነ ሰላምን እንዲቀብሩት፥ እነዚያን (28ᵃ) ፪ ወንድሞችም ወደሱ

4. "ቤተ መዛግብት"።

እንዲያመጧቸው አዘዘ:: እንደዚያ አደረጉ፤ (እነዚያን) ወንድሞች ወደዚያው (ወደ ንጉሡ አደባባይ) ወስደው ከፊተኞቹ ጋራ አስቀመጧቸው::

ለመበታተን ገዳም የማማረጥ ዕድል

ከዕለታት በኋላ÷ ንጉሡ ቅዱሳኑን ከፊቱ እንዲያቆሟቸው አዘዘ፤ ከፊት ለፊቱ አቆሟቸው:: (ንጉሡ) እንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "ከደብረ ዳሞዎች÷ ከገሊላዎች÷ ከሃሌሎዎች÷ ከሌሎችም÷ ወይም ከኢትዮጵያውያን ሁሉ አነሱ እንደሚያደርጉት እንድታደርጉ የትኞቹን ትመርጣላችሁ?"

ዞሲማስ የሚባለው ከቅዱሳኑ ፩ዱ÷ "የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚገኘው ሕጉን በመጠበቅ እንጂ ብዙ በመሆን ነውን? ኖኅ በውሐ ጎርፍ ቅጣት ከጠፉት ከብዙዎች ውስጥ ከጥቂቶች ጋራ አልዳነምን? ሎጥና ልጆቹስ ከእሳት ዝናም ከሰዶም (አልዳነምን)?" አለ:: ንጉሡ ይሽንን ሲሰማ እንዲገርፏቸው አዘዘ:: አስኬማ ልብሳቸውን ሸርከተው ከመሬት ላይ አስተኟቸው:: ግን ሳይገርፏቸው÷ "ይተዋቸው" አለ:: እስከ ጊዜው በቅያሜ አኖራቸው::

በደጅ ጥናት መጉላላትና "ደብረ ጽዮን"--60 ስው ተገረፈ

ንጉሡ (29[ሀ]) በምድረ ቅዳ የበተኗቸውን በየወታደሩ እጅ እንዲሰበስቧቸውና ወደሱ እንዲያመጧቸው አዘዘ:: ወታደሮች ተልከው እንዳዘዘው አመጡለት:: ንጉሡ ከዕለታት በኋላ÷ በፊት ከመረመራቸው ጋራ አብረው ከፊቱ እንዲያቆሟቸው አዘዘ:: ፩ የንጉሡ የወታደሮቹ አለቃ የሆነ ሲያያቸው÷ "እነዚህ ለንጉሡ ሰገዱ ወይ? አለ:: "የለም (አልሰገዱም)" አሉት:: እንዲደበድቧቸው አዘዘ:: በበትርና በዱላ ብዙ ድብደባ ደበደቧቸው:: ንጉሡ (ከፊቱ) ካቆማቸው (በኋላ) ሳይጠይቃቸው ቀረ:: ሲመሽ ወደየማደሪያቸው እንዲመለሱ አዘዘ:: ደግሞ እንደገና አቆማቸው:: ያን ዕለትም ሳይጠይቃቸው መሸቶ ወደየማደሪያቸው ተመለሱ:: የዚህ ተንኮለኛ[5] ሥርዓቱ እንደዚህ (ማጉላላት) ነው::

ከዚያ በኋላ÷ እንዲያቆሟቸው አዘዘ፤ ይኸ ሶስተኛቸው ነው:: እንዳለፈው ጊዜ÷ "እነማንን ትመርጣላችሁ" ሲል ጠየቃቸው:: ስለ ደብረ ጽዮንም÷ "ደብረ ጽዮን አሁን አለ ትላላችሁ ወይስ በኋላ ጊዜ ይመጣል ትላላችሁ?" ሲል (ጠየቃቸው)::[6] (29[ለ]) ያ ወንድም÷ "በፊትም ብያለሁ፤ አሁንም እላለሁ፤[7] ስለበዙ የእግዚአብሔር ጽድቅ አይገኝም:: ብዙዎች በጎርፍ ቅጣት ሲጠፉ፤ ኖኅ ከጥቂቶች ጋራ ድኗል፤ በሰዶምም ከእሳት ዝናም ሎጥ ከልጆቹ ጋራ ድኗል፤ ስለ ደብረ ጽዮንም (ጽድቅን) ለሚሠሩ አሁንም አለ፤ በኋላም ጽድቅ ለሚሠሩ ይመጣል" አለ::

ንጉሡ÷ "ደብረ ጽዮን ምን ይመስላል?" አለ::

ያ ወንድም÷ "ምን ይመስላል ልበልህ፤ ማሺላ ነው ወይስ ዳጉሳ? መጽሐፉ ዓይን ያላየው÷ ጆሮ ያልሰማው÷ በሰው ልብ ያልታሰበ÷

---

5. ግዕዙ የሚለው "መስተአማኒ" ነው፤ ግን "መስተመይን" ("ተንኮለኛ"÷ "አታላይ"÷ "ሽንጋይ") ለማለት መሆኑ ግልጽ ነው::
6. ስለ "ደብረ ጽዮን" እምነት በመግቢያው የተጻፈውን ተመልከት::
7. ሱቱ 9: 15::

አግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ይላል" አለው::[8] የሠራዊቱ አለቃ፥ "እናንተ እንደነ ኖኅና ሎጥ ጥቂቶች ናችሁ፤ አኖ አንደሚጠፉት ነን?" አለ:: ያ ወንድም፥ "አንተ አልክ"[9] አለው:: የሠራዊቱ አለቃ ሲሰማ ሄዶ ለንጉሡ ነገረው:: ንጉሡ እንዲገርፏቸው አዘዘ::

ቅዱሳኑን ፫ ሰዓት (30[ሠ]) ላይ ከፊቱ አቆሟቸው፤ (አንደቆሙ) አስከ ዘጠኝ ሰዓት ዋሉ:: እነሱ ግን ችሎታ ላለው አምካላቸው ዝማሬና ጸሎት አላቋረጡም:: ከዚያ፥ አጋድመው ደማቸው አንደ ውሐ እስኪወርድ ድረስ ብዙ ግርፊያ ገረፏቸው:: የተገረፉት ቅዱሳን ቍጥር ፮ ነበረ:: ገርፎ አያንዳንዳቸውን በእስራት ከገኒ ድምበር ጀምሮ እስከ ኑላ አራይ ድምበር ድረስ ወደ መንግሥቱ ምሥራቅ እንዲበትኗቸው አዘዘ:: ከተበተኑ እንደ አንበጣ የሚጠፉ መስሎታል:: እግዚአብሔር የመከረውን ምክሩንና በነዚህ በባሮቹ ስብከት ለሕዝቡ የሚያደርገውን መድኃኒት አላወቀም:: እነሱ ቢሆኑ በየገዳማቸው ለራሳቸው የጽድቅን ሥራ አየሠሩ ሊኖሩ ይችሉ ነበረ:: ግን ይህቺ መበታተናቸው ከእግዚአብሔር (የተመከረች) ናት:: በሰይጣን ስሕተት የተበተኑ ነፍሶችን በነሱ አማካይነት ሊሰበስብና ከንጽሕ ሥርዓት ሊያስገባቸው (መክሮ) ነው::

አቡነ በርተሎሜዎስና ፈላጊዎቹ ጉንጽ "ከርቸሌ" ገቡ

ሽማግሌው አቡነ በርተሎሜዎስ ንጉሡን፥ "ሥርዓት አሚላለሁ እያልክ (30[ሀ]) እንደዚህ የምትጥረው ለምንድነው? በጽዋ ውስጥ ያለ ጎደሎ ውሐን ውሐ ይሞሉበታል፤ ከሙሉው ላይ ቢጨምሩበት ግን ይፈስሳል:: አሁን የሐዋርያትና የነቢያት ሥርዓት ሙሉ ሆኖ ላለ በላዩ የምትጨምርበት ምንድን ነው?" አለው:: በዚያች ቀን ከነሱ ጋራ ገረፈውና በቁጣ ድሮር ወደሚሏት ወደ ብሔረ ላጉራ እንዲወስዷቸው አዘዘ:: አስከ ጊዜው በጽኑ ገድልና በብዙ ተአምር ኖረ::

ከዚያ፥ ሁኔታውንና ወዴትስ እንደወሰዱት፥ ስለ ወንድሞችም ሁሉ እንዲያውቁ ማኅበሩ ፫ ወንድሞች ወደሱ ላኩ:: መልእክተኞቹ ሲያፈላልጉ ከምድረ ፈጸጋር ደረሱ:: እዚያ ጥቂቶችን ከተበተኑበት አገኟቸው:: (ማኅበር) እንደላኳቸው ነገሯቸው፤ እነሱም ምን እንዳደረጓቸው ገለጡላቸው:: ሽማግሌውን ግን አላገኙትም:: ሲያጠያይቁ ከንጉሡ አደባባይ ደረሱ:: አገቢያ ውስጥ ያዟቸው፤ ለንጉሡም ነገሩት:: "ለንጉሥ ስገዱ" አሏቸው:: ቅዱሳኑ፥ "እኛ (31[ሀ]) ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አንሰግድም" አሉ:: ንጉሡ አንዲደበድቧቸው አዘዘ:: አአምሯቸውን እስኪስቱ ድረስ በበትርና በዱላ ብዙ ድብደባ ደበደቧቸው:: ከዚያ፥ አቡነ ገብረ ክርስቶስና አባ ተወልደ መድኅን ካሉበት ከጉንጽ አንዲያስገቧቸው አዘዘ:: አዚያ በአስራትና በጽኑ ገድል ኖሩ::

ከመንበርታ ወደ ጓትር--30ውም

ንጉሡ ወታደሮቹን ወደ ብሔረ ትግራይ ላከ:: መርቆርዮስ የሚሉት አንድ አላባቂ አብሯቸው ነበረ:: መንበርታ ከሚባለው ገዳማቸው ከዲቦ ደረሱ::

---

8. ጥቅሱ ከትምህርተ ኅቡኣት ነው:: ከታች ኅዳግ ቍጥር 136ን ተመልከት:: ስለ እምነቱ መግቢያውን ተመልከት፤ የሚናገረው ስለ ደብረ ጽዮን ነው::

9. ጌታ ጴላጦስ፥ "የአይሁድ ንጉሥ ነህ ወይ?" ብሎ ሲጠይቀው እንደመለሰው፤ ማቴ 27፡ 11::

የኤጲፋንያ[10] ዕለት ቅዳሴ ጨርስው ከቄረቡ በኋላ፥ ከቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ሳለ መጥተው ያዟቸው። መኖሪያቸውን ዘረፉት፤ የደከሙበትን ሁሉ ወሰዱት። እነሱንም ወስደው ከንጉሡ ዘንድ አመጧቸው። "ለንጉሡ ስገዱ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "እኛ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አንሰግድም" አሉ። እያንዳንዳቸውን በጥፊ መቷቸው። ከዚያ፥ ወደ ብሔረ ጓትር (31ᵃ) እንዲወስዷቸው አዘዘ። ቍጥራቸው ፴፫ ነበረ። እዚያ አንድ ዓመት ያህል በአስራት ቆዩ።

ወንድም ገብረ ማርያም

በንጉሡ ትእዛዝ ከተበተኑትና ከወንድሞቹ ጋራ የአባታቸውን ዐፅም ሲያፈልስ በፊት በግድም ኬላ ከተያዙት መካከል በነበረው ገብረ ማርያም በሚሉት ፩ ወንድም ላይ ብዙ ገድል ተፈጸመ። በቤተ አረሚ[11] በነበረበት ጊዜ የጋለ ዕንባ በልብሱ ላይ እስኪያንጠባጥብ፥ ከዚያም እስከ መራት ደርሶ መራቱን በሚያርስ (ለቅሶ) በጾምና በጸሎት ላይ ነበረ። ከለቅሶ (ብዛት) የተነሣ ዓይኖቹ ደበዘዙ። ቀድሞም ጻማ[12] የለበሰ፥ የስግያትን ምስጢሮች የሚያይ ነበረ።

እዚያ አንድ ዓመት ቆየ። ፩ ዲያቆን ያገለግለው ጀመር። ዲያቆኑ፥ "አባ ሆይ፤ ለምን ታለቅሳለህ? ዓይኖችህ አይደበዝዙምን? ያለኸው በአረሚ ቤት ነው፤ እያየህ ደጉንና ክፉውን ብትለይ አይሻልህም?" ቢለው፥ "እግዚአብሔር ረድኤት ሳይስጠኝ (32ᵇ) ወይም ነፍሴን ሳይቀበላት ይተወኛልን? የንጉሡን ተንኮል፥ በኛ ላይ የሚሠራውን ተንኮል አታይምን? እያንዳንዳችንን በየአረሚው ቤት በታተነን፤ ነፍሳችንንም ሊያጠፋ ይፈልጋል" አለው።

ከዚያ፥ የሆድ ሕመም የሚያመጣ ከባድ በሽታ አደረበት። ለመሞት ሲቀርብ ዲያቆኑን፥ "እንግዴህስ አትተክዝ፤ ቀኔ ቀርባለች፤ ጊዜዬም ደርሷል። እነሆ ልብሴን ለወንድሜ ለብርሃነ መስቀል ስጠው። ሥጋዬን በእሱ ልብስ ገንዘው። በትሬንም ጠበል[13] እንዲሆነው ስጠው። አሁን እኔ ወደ አምላኬ ስለምሄድ አንተ የምትችለውን ያህል እርዳው" አለው። ያ ወንድም እግሮቹ ታስረው በአረሚ ቤት አጠገቡ ነበረ። ዲያቆኑንም ባርኮ ነፍሱን የሚጠቅማት ምዕዳን በብዙው አስማው፤ የጽድቅንም ነገር ሁሉ አስረዳው። ማስታወሻ እንዲሆነው ቀበቶውን ሰጠው። ከዚህ በኋላ፥ ዲያቆኑም ከቅዱሳኑ ጋራ ተደመረ።[14]

---

10. "የጥምቀት"፤ "የልደት" ሊሆንም ይችላል።
11. "በአንድ አስላም ቤት"። "አረሚ" ማለት በመሠረቱ "ይኸን አድርግ፥ ይኸን አታድርግ" የሚል ሕግ ያለው ሃይማኖት የሌለው "አረመኔ" ማለት ነው፤ ግን በግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ "አረሚ" አስላም ነው። አስላሞቹ አስላም ያልሆነውን ሁሉ (ክርስቲያኑን ጭምር) "ካፊር" እንደሚሉት ማለት ነው።
12. "ጻማ" ለጽድቅ ሲባል ባሕታውያን እንደሚያደርጉት በራስና በስው አጅ የሚፈጸምባቸው የሥጋ ድክመት "ማቀቆ" ነው፤ መማቢያውን ተመልከት።
13. "ጠበል" ማለት "በረከት" ማለት ነው፤ ውሐ ብቻ አይደለም። ቃሉ "ጸበል" ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ነው፤ ትርጕሙ "አቧራ"፥ "ትቢያ" ማለት ሲሆን፥ ከጻድቃን እግር ላይ ለበረከት የሚወሰድ ነው። በኋላ ግን ማናቸውም ጻድቃን የሚነኩት ነገር ሁሉ ለበረከት ስለሚያገለግል ሁሉም "ጠበል" ተባለ።
14. ከደቂቀ እስጢፋኖስ ተደባለቀ።

ከዚያ፥ በዚያች ሌሊት ከተኙ በኋላ፥ ይኸ ጻማ የለበሰው ሰው ካለበት ቤት ውስጥ ብርሃን ወረደ። አረሚው ከአንቅልፉ ነቅቶ (32ᴬ) ያንን ዲያቆን ጠራውና፥ "ይኸ የማየው ወጋጋን ምንድን ነው? አሳት ነዲል ይሆን? ቤት እንዳያቃጥል (አስቲ) እይ" አለው። ዲያቆኑ ከበሽተኛው ጋራ በቤቱ ተገን አብሮት ነበረ። አረሚው ከቤት ውስጥ ነበረ። ዲያቆኑ ሲነቃ የወጋጋኑ ብርሃን ጻማ ከለበሰው በሽተኛ ላይ ሲያንጸባርቅና ከሱ (ነጥሮ) ቤቱን ሲያበራው አየ። ዲያቆኑ ብርሃኑ በሽተኛውን እንደከበበው ዐወቀ። አረሚውን፥ "አሳት የለም" አለው። ተመልሰው ተኙ።

አረሚው አንደገና እንደፊተኛው የብርሃን ወጋጋን አየ። ዲያቆኑን እንደገና ጠራውና፥ "ምንድን ነው የምትሠራው? እሳት ይነድዳልን? ቤት እንዳያቃጥል እይ" አለው። ዲያቆኑ ተነሥቶ አየ። እንደበፊቱ ያንን ጻማ የለበሰ ወንድም ብርሃን ከብቦት፥ እዚያ ያሉት ከወጋጋኑ አያገኙ ሲያበሩ አየ። በቀዳማይ ታስሪን ፷፪ በግዕዝ--ጥቅምት--ዓሥራ ...[15] በጌታ በስላም ሰማዕትነቱን ፈጸመ። ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ (33ᵁ) አሜን፥ አሜን።

ያ ወንድም (ሰማዕትነቱን) እንደፈጸመ የቤቱ ሰዎች ዐወቁ። ለዚያ ብሔር ሹም ነገሩት። ዲያቆኑም ለወንድሞች ነገራቸው። የብሔሩ ሹም ሥጋውን እንዲቀብሩ አዘዘ። ሰዎች አንድ መነኮሴ ከገበያ ሲያገኙ፥ "ና የጓደኛህን በድን ቅበር" አሉት። "ሽቀጤን ማጣራቴን ትቼ አልመጣም" አላቸው። ሹሞች ስለሆኑ እንዲቀብር አስገደዱት። የአረሚዎች ሕጋቸው እንደዚህ ነው፤ የከርስቲያን በድን አይነኩም።

መነኮሴው ሲያጒረመርም አንድ እስላም አይቶት፥ "ምንድን ነው የምታጒረመርመው? ይኸ መነኮሴ ሲዘምር ከአፉ እሳት ሲወጣ አይቻለሁ፤ ጻድቅ ሰው ነው፤ ቅዱሶች ቤቴል መጥተዋል።[16] አንተም አሱን ለመቅበር እታመንታ" አለው። ይኸንን ሲሰማ ሊቀብር ሄደ፤ አግር ብረቱን ከእግሮቹ ላይ አውልቀው ከምድረ በዳ ቀበሩት። (በኋላ) ወንድሞቹ መጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ አፈለሱት። ሌሊት በዚያች ቤተ ክርስቲያን የቅዱሱ መቃብር ካለበት ብርሃን ወረደ። (33ᴬ) ያዩ ፪ ቄሶችና ፪ ዲያቆኖች ምስክሮች ሆነዋል፤ እንደገና ተደጋገመ። ብርሃኑ ሶስት ጊዜ ወረደ። ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

---

15. ቁጥሩ አልተሞላም፤ "የዕብራይስጢውን" ሲያውቁት የኢትዮጵያ የምንለውን እሳወቁትም፤ "የዕብራይስጢውን" የቀን አቈጣጠር በይበልጥ የሚያውቁት ከሆነ ምክንያቱ ግልጽ እይደለም። እባ አበክረዙን "እኔም እንደነሱ ዕብራዊ ነኝ፤ እሥራኤላውያን ቢሆኑም እኔም እንደነሱ አስራኤላዊ ነኝ" ብለው ነበር፤ የእሥራኤላዊነትን ታሪክና ባህል ካመጡልን ሰዎች ውስጥ ይሆኑ እንዴ?

16. ? "ቅዱሶች" ያለው መላእክትን ይሆናል፤ "ቤቴል" ማለት በዕብራይስጥ "የእግዚአብሔር ቤት" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ቦታው "ቤቴል" የተባለው መላእክት ስለወረዱበት ነው፤ ዘፍ 28፡ 12-22። ታዲያ ይህ ታሪክ የሚታወቀውና የሚታመንበት በክርስቲያኖችና በእይሁድ ዘንድ እንጂ በእስላሞቹ ዘንድ እይደለም።

የቊጥራቸው መብዛት አስጋ--ጓደኛም ከዳ

ከዚያ ደግሞ ቅዱሳኑ በትግራይ ብሔሮች በየገዳማቸው ሆነው፥ አርስ በርሳቸው ምዕዳን እያሰማሙና የአባታቸውን ውሳኔዎች አየጠበቁ፥ የትምህርታቸውን ቃል ብዙዎች አስኪቀበሉና በንጽሕ ሥርዓት አብረዋቸው አስኪሆኑ ድረስ የነፍስና የሥጋ ምግብ የሚሆነውን ቃለ መለኮት እያስተማሩ ተቀመጡ። የቅዱሳን ደቀ መዛሙርት ሥራ አንደሚለው በነጋ ቊጥር እግዚአብሔርን የሚያምኑ ይጨምራል።[17] በመጽሐፈ ፍጥረትም እንደዚሁ ይላል፤ የእስራኤል ልጆች ግብጻች ባስቃዩዋቸው መጠን ይበዙ ነበረ።[18]

በዚህ ምክንያት ጠላት ተቆጥቶ፥ የክፋቱን መርዝ በብዙዎች ልብ ሞጀረው። ከዚያ፥ ትዕግሥትን ባለመቻል (34[ሀ]) እንደ ስሙ ያልሆነ፥ በሥራው ስምያል[19] የሆነ ፩ ሳሙኤል የሚባል ወንድም ከማኅበር ተለይቶ ወደ ንጉሡ ሄዶ ቅዱሳኑን በብዙ ውሸት ነገር እንዲህ ሲል ከሰሳቸው፤ "እነሱ ከነመምህራቸው ካሉበት አመራለሁ፤ እንዲያውም እሱ ከፊተኛው አባታቸው የጸናና የከፋ ነው።"

ንጉሡ ይሽንን ሲሰማ በጣም ተቆጣ። ቁጣውን የሚያበርዱለት ወታደሮቹን ላከ። ያም አላባቂ አብሯቸው ነበረ። ዴስአ ከምትባለው የቅዱሳኑ ገዳም መጡ። ብዙዎቹን ያዟቸው። መኖሪያቸውን ዘረፉት፤ የደከሙበትን ሁሉ ወሰዱት። እነሱንም አስረው ወስደው ሌሎቹን ወንድሞቻቸውን አስኪያመጡ ድረስ በዘበኞች እጅ ከመንገድ አስቀመጧቸው፤ ምክንያቱም፥ ንጉሡ ከተገኙበት ቦታ ሁሉ እንዲሰበስቧቸው አዝዞ ነበረ።

ቀጥሎ መንበርታ ወደምትባል ወደ ሌላ ሀገር ሄዱና (አዚያ ያሉትን) ቅዱሳን ያዙዋቸው። የደከሙበትን ሁሉ ወሰዱት፤ እነሱንም አስረው (34[ለ]) ወንድሞቻቸው ወዳሉበት ወሰዷቸው።

ከዚያ፥ ወደ ትግራይ አገረ ገዢ ሄደው ዐጋሜ ውስጥ ያሉትን ቅዱሳን እንዲይዛቸው የንጉሡን መልእክት ነገሩት። አገረ ገዢው ሰምቶ ከንጉሡ መልእክተኛ ጋራ (ሊፈልጋቸው) ሄደ። ቅዱሳኑ ካሉበት ሀገር ደርሰው እነሱን በመፈለግ ደከሙ። ከሀገሩ ሹማምንት ፩ዱን በግዛቱ ያሉትን ቅዱሳን እንዲይዝና እንዲሰጣቸው፥ (ይህን ቢያደርግ) በሀገሪቱ በሞላ የበለጠ ሹመት እንደሚሰጡት ቃል ገቡለት። አሱም በምክራቸው ተደልሎ ቅዱሳኑን በምድረ በዳና በየዋሻው ካሉበት ሄዶ ያዛቸው። መቼም የዚህ ዓለም ድኾች ሕጋቸው እንደዚህ ነው። የደከሙበትንም ወሰዱባቸው።

እነሱንም ወደ አገረ ገዢው ወስደው ከፊቱ አቆሟቸው። ስለሁሉም ነገር ጠየቃቸው፤ በማህላቸው አእምሮና የመንፈስ ቅዱስ ልቦና ያለባቸው ካህናት ነበሩ፤ (አንዱ) አቡነ ይሥሐቅ ለማኅበር ቅድስት ሥርዓት መከታ የሆነ የዕንቊ ሳጥን ነው፤ ሌላው በጽድቅ ሰማዕት የሆነው ባለመልካም መታሰቢያ መልከጸዴቅ ሲሆን ሌሎችም መነኮሲቶችና ቅዱሳን አብረዋቸው

---

17. የሐ ሥራ 2: 47።
18. ዘፀ 1: 12።
19. ስምያል "ስማዝያል" የሚባለውን የክፉ መንፈስ ስም መጥራቱ መሰለኝ፤ ሄኖ 1: 4፥ Michael A. Knibb in consultation with Edward Ullendorff, *The Ethiopic book of Enoch,* vol. I, Oxford 1978, p. 35.

ነበሩ። (35^{በ}) አገረ ገዢው፥ "ለንጉሡ ስገዱ" አላቸው። ቅዱሳኑ፥ "እኛ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አንሰግድም" ሲሉ መለሱ። አሺ ማሰኘት ሲያቅተው፥ በበትር እንዲደበድቧቸው አዘዘ። ደበደቧቸው፤ ብዙ አሳመሟቸው፤ ከዚያ፥ እያንዳንዳቸውን በእስረኝነት ጠበቋቸው።

የንግሥተ ማርያም ዕውቀት፥ ቄራጥነትና ቊንጅና

ከዚያ ደግሞ አነዚያን መነኮሲቶች አገረ ገዢውና በምንኮስና ስም በሚጠሩ ንቡራኔ አዶች[20] በነበሩበት አደባባይ ሁሉ ፊት አቆሟቸው። የንጉሡ መልአክተኛ ከነሱ አንዷን ትልቋን ንግሥት ማርያም የምትባለውን አኅት፥ "ሃይማኖትሽ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቃት። ቅድስቷ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተጐላምሳ የዚህ ዓለም ባለሥልጣኖችን ግልምጫ ሳትፈራ፥ በጣያት አምላኪ ንጉሦች ዘመን ስማዕት እንደሆኑት የቀድሞ ሴቶች፥ "ስለ ሃይማኖቴ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስን አመልካለሁ" አለችው። ደግሞ፥ "መምህርሽ ማነው?" ብሎ ጠየቃት። ቅድስቷ፥ "መምህሬ ክርስቶስ ነው" አለችው። "የምንኮስና ልብስ ያለበስሽ ማነው?" አላት።[21] ቅድስቷ፥ (35^{ሀ}) "የአግዚአብሔር ካህን አለበሰኝ" አለችው። "ደብሩ የት ነው?" አላት። ቅድስቷ፥ "ደብሩ ደብረ አግዚአብሔር ነው" አለችው።

የንጉሡ መልአክተኛ ሲሰማ በጣም አደነቀና አብረውት ያሉትን፥ "ይቺ ሴት ደብረ አግዚአብሔር የምትለው ወዴት ነው?" ብሎ ጠየቃቸው። እነሱም፥ "ደብረ አግዚአብሔር መላው ምድር ነው" አሉት። አዚያ የነበሩ በችሎታ ያደረገችውን ያፏን መልስና የነገሯን ሁሉ አስተዋይነት ሲሰሙ አደነቁ። ምክንያቱም የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ በሷ አድሮ ይናገር ነበረ።

አሷም ቁመቷ ያማረ፥ መልኳ ቆንጆ፥ ፊቷ ደስታ የተመላ፥ ትውልዷም ከአገሬው ታላላቆች፥ ከብሔሩ ሹማምንት ነበረ። ደግሞ ለዚህ ሥርዓት ብዙዎች ሕንፃዎች በላይዋ አስኪሠሩ ድረስ መሠረት ነበረች። በሰማዕትነትም ወንድሞችን እንደ ቅዱሳን ሰማዕታት እናት እንደ ቅድስት አርሴማ ታበረታታቸው ነበረ።[22] ሰማዕትነቷን ፈጽማ የድል አክሊሏን እስክትደፋ ድረስ ሁል ጊዜ ስትጋደል ኖረች።

የንጉሡ መልክተኞች የቃሏ ፍጻሜ ወደፈለጉት (36^{በ}) እንደማይለወጥ ሲያውቁ ከቅዱሳኑ ጋራ አብራ እንድትሄድ አደረጉ። ሴቶቹ ጓደኞቿም አብረዋት ነበሩ።

ያ ከሀገሩ ሹሞች አንዱ የነበረው፥ የዚህን ዓለም ሹመት ተስፋ በማድረግ ቅዱሳኑን እንዲይዝ በነገር ድለላ የተታለለው ሰው እንዲስጡት የተደረገለትን ተስፋ አላገኘም። ነቢዩ፥ "የኃጢአተኛ ሞት ክፉ ነው"[23] እንዳለው ታሞ ክፉ ሞት ሞተ።

ይኸንን አጥብቀው የፈለጉትን የነፍስ አባታችንን ሊቀ ማኅበሩን አላገኙትም። የዚች ቅድስት ሥርዓት አባትና መሪ እንዲሆን አግዚአብሔር ከእጃቸው ሰወረው፤ አጃቸው ላይ አልጣለውም።

---

20. የትላልቅ አድባራት አለቆች።
21. በገዳም ሥርዓት አመንኳሽና መምህር የገዳመ· መምህር (አበምኔቱ) ነው።
22. ቅድስት አርሴማ ባሕታዊት ነበረች፤ ታሪኳ *በተአምረ ማርያም* ውስጥ ተጽፏል፤ ለምሳሌ፥ EMML 2058, f. 117a, *Catalogue* VI, p. 82, (no. 166).
23. መዝ 32፡ 22።

አምሳ ሰባቱንም በማነቆ አስረው አመጧቸው

የንጉሡ መልእክተኞች ቅዱሳኑን÷ መነኮሲቶቹን ጨምረው÷ ከመንገድ ላይ ከነበሩት ስዎቻቸው ጋራ ደባለቋቸው፤ ቍጥራቸው ፶፯ ሆነ፤ ከዚያ÷ በማነቆ አስረው ከንጉሡ አደባባይ አመጧቸው። ከስፊሩ ውጪ÷ ... ወር ያህል አስቀመጣቸው።

በፊት አያንዳንዱን ለያይተው ከበተኗቸው (36^ሀ) ውስጥ ፮ቱን "ፀረ ማርያም ናቸው፤ *መጽሐፈ ተአምረ ማርያምንም* አጅ አይነሡም" በሚል ከስስው አመጧቸው።

"*ተአምረ ማርያምን* እጅ አይነሡም"

ከዕለታት አንድ ቀን÷ (ንጉሡ) ሁሉንም ከብሔረ ትግራይ ካመጧቸው ጋራ በአንድነት አንዲያቆሟቸው አዘዘ። (ሲቆሙ)÷ "ለንጉሡ ስገዱ" አሏቸው። ቅዱሳኑ÷ "እኛ ለአብ÷ ለወልድ÷ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አንሰግድም" አሏቸው። ከዚያ÷ ንጉሡ "*መጽሐፈ ተአምረ ማርያምን* አጅ አይነሡም" በሚል ክስ ወዳመጧቸው ወደ ፮ቱ÷ "የሚሏችሁ አውነት ነውን?" (ብሎ) ላከባቸው።

፩ዱ ወንድም÷ "እኛ እጅ አንነሣም አላልንም፤ ብቻ አንድ ተላላኪ ከወንጌል ንባብ በኋላ (እንዲነበብ) አንድ መጽሐፍ አመጣልኝ፤ ይኼ መጽሐፍ ምንድን ነው? አልኩት። *መጽሐፈ ተአምረ ማርያም* ነው አለኝ። የሐዋርያት ሥርዓት እኮ አንደዚህ አይደለም። ከኦሪት÷ ከነቢያት÷ ከሐዋርያት ዜና[24] መጻሕፍት ሁሉ (ተነብቦ) ከዚያም ቀጥሎ ወንጌል ይነበባል፤ ከጸሎት ፍጻሜ በኋላ ወንጌልና መስቀል እጅ ይነሣል አልኩት። የቃሌን መጨረሻ ስምቶ መጽሐፉን ይዞ ሄደ። ከዚያ በኋላ ያንን መጽሐፍ (37^ሀ) እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት፤ ስጠኝ፤ አንብቤ እጅ ነሣሁት" አለ።

ንጉሡ÷ "ይኸን የምትለው ንቀህ አይደለምን?" አለው። ያ ወንድም÷ "የምንቅ እንደሆነ አሁን ፈትኑኝ" አለው። ንጉሡ÷ "እሳንብሶ? ማንስ ተሳንብሶ?" አለ። ከዚያ÷ ንጉሡ እንዲደበድቡት አዘዘ። በዱላ ደበደቡት።

ለመቀጣት እሽቅድድም

በፊት ወዳመጣቸው ቅዱሳንና መነኮሲቶች አንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው?"

ቅዱሳኑ÷ "ሃይማኖታችን አብ÷ ወልድ÷ መንፈስ ቅዱስ ነው" አሉት። ንጉሡ÷ "ሐዲስና ብሉይ እየጠቀሳችሁ አስረዱኝ" አላቸው። ቅዱሳኑ ስለ ሥላሴ ህልውና ከነቢያት ትንቢት÷ ከሐዋርያት የዜና መጽሐፍም ማስረጃ እያመጡ በሚገባ መለሱለት።

ይኸንን ባስረዱት ጊዜ ደግሞ÷ "በአብርሃም ቤት የተስተናገዱት ስዎች አነማናቸው ትላላችሁ" አለ። ቅዱሳን÷ "*መጽሐፉ ፫ ሰዎች ይላል*" አሉት።[25]

---

24. የሐዋርያት ሥራ።

25. ንጉሡ ስለዚህ *መጽሐፈ ሥላሴ* በሚል ርእስ በለፊው ጽፋል፤ ለምሳሌ÷ Kurt Wendt, *Das Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber*

"አንተስ አነማናቸው ትላለህ?" (አለ)። "ከኛ በግድ ልትማር ትፈልጋለህን? ከኛ ልትማር ከፈልግህ በበጎ (መንገድ) ጠይቀን። እንደዚህ በማስፈራራት (37ᵃ) ከሆነ ሰላምታ እንስጥህም" (አሉት)።

ንጉሡ ሲሰማ በጣም ተቆጣ። የሱን መነኮሴዎች እና ሌሎቹንም እዚያ የነበሩትን እንዲፈርዱ አዘዛቸው። ከንቡራኔ አዶቹ አንዱ ተነሥቶ፥ በቅዱሳኑ ላይ እንዲህ ሲል የሞት ፍርድ ፈረደባቸው፤ "እነሆ እኔ የዓለምን ሩብ ዞሬያለሁ፤[26] ያየሁት ሁሉም ንጉሥ ሲያከብር ነው፤ (እነዚህ) ንጉሥ አያውቁ፥ ለቃሉ አይታዘዙ። አሁንም ወንጌሉ እንዳዘዘው ያድርጉባቸው፤ ከባሕር ጥልቀት ያስጥሟቸው።"[27] አንዳንዶቹ፥ "ሞት ይመቱ" አሉ።

ንጉሡ እንዲደበደቡ አዘዘ። እስኬማ ልብሳቸውን ሸርክተው ወታደሮቹ እየተፈራረቁ በዱላ ትልቅ ድብደባ ደበደቧቸው። ቅዱሳኑ ደግሞ ለመገረፍ አንዱ ከሌላው ይሽቀዳደሙ ነበረ። መነኮሲቶቹም ከነሱ ጋራ ተገረፉ። ሌሎች የጽድቅ ተስፋ የሌላቸው መበለቶች ድንጋይ እያነሡ (መነኮሲቶቹን) ይመቷቸው ነበረ። እነሱ ግን ጽድቅን ተስፋ በማድረግ ይታገሡ ነበረ። ዶሮ እስኪጮህ ድረስ እዚያው ጣሏቸው፤ ከዚያ በኋላ (38ᵇ) ወደየማደሪያቸው መለሷቸው።

የንጉሡ ጉባኤና የብሔረ ምርጋይ ስደት

አንድ ቀን፥ ንጉሡ ጉባኤ አደረገና ቅዱሳኑን ከእደባባይ አንዲያመጧቸው አዘዘ። ንጉሡ፥ "በጳጳስ ታምናላችሁን? ብሎ ጠየቃቸው።[28] "አዎን፥ እናምናለን፤ ክህነት የምንወስደው ከሱ ነው" አሉ። እንዳንድ መነኮሳት ንጉሡን፥ "ጳጳስ እንኳን አይክዱም፤ ግን መምህራችሁን ስደቡ በሏቸው" ብለውት ነበርና፥ "በሉ፥ አስጢፋኖስ ርኩስ ነው ብላችሁ መምህራችሁን ስደቡ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "የወንጌልን ሕግ ስላስተማረን የመምህራችንን ስም አንሰድብም" አሉ። እምቢ ሲሉ እንዲገርፏቸው አዘዘ። ጨጨ በምትባል የመግረፊያ ጅራፍ ብዙ ገረፏቸው። ከዚያ ደግሞ የፀሐይ አገር[29] ወደሆነችው ወደ ብሔረ ምርጋይ እንዲወስዷቸው አዘዘ። እዚያ የወሰዷቸው የንዳድ/የወባ[30] በሽታ ስላለባት በዚያ በሽታ እንዲያልቁ ነው። አስከ ጊዜው እዚያ ቆዩ።

Trinitatis) des Kaizers Zar'a Yā'qob, *CSCO*, vol. 221/41, Louvain 1962 and *CSCO*, vol. 235/43, Louvain 1963, 70-79; Getatchew Haile, "The Homily of *Aṣe* Zär'a Ya'əqob of Ethiopia in Honour of Saturday," *Orientalia Lovaniensia Periodica*, vol. 13 (1982), pp. 196-205.

26. እኚህ ሰው ሮማንና ናፖሊን (ምናልባት ኢየሩሳሌምንም) የነበኙት ንቡረ እድ ፍሬ ሚካኤል ይሆናሉ፤ Taddesse Tamrat, *Church and State*, p. 265.

27. ማቴ 18: 6፤ ሉቃ 17: 2።

28. ደቂቀ ኤዎስጣቴዎስ/ማዕቀበ እግዚእ የሚባሉት ክህነትን እይቀበሉም ነበረ፤ Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān)*, *CSCO*, vol. 261/51, Louvain 1965, pp. 153-156. እነዚህም እንደነሱ መስለው ታል።

29. "ቆላ"።

30. ማቄዶ/ይ።

አቡነ ገብረ ክርስቶስ

ከጕንጽ ያስገቡት አቡነ ገብረ ክርስቶስ በእስራትና በጸና ገድል (38^ሰ) በትዕግሥት በምግብና በልብስ ችግር ፱ ዓመት ከ፯ ወር አሙልቶ ሰማዕትነቱን በመጋቢት ፪ ቀን በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱና በረከቱ ለዘላለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

አቡነ ዞሲማስ

የአባቱን የቅዱስ እስጢፋኖስን ዐፅም ሲያፈልስ ከግድም ኬላ ላይ የያዙት÷ ያ ከንጉሡ ፊት ያቆሙት ጊዜ÷ "የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚገኘው ሕግ በመጠበቅ እንጂ ስለበዙ ነውን?" ያለውና ስለ ደብረ ጽዮን ሲጠይቁት (ደግሞ)÷ "ማሽላ ነው ልበልህ ወይስ ዳጉሳ? መጽሐፍ የሚለው ዓይን ያላየው ጆሮ ያልሰማው÷ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ነው" ያለው አቡነ ዞሲማስ ገድሉን እሚልቶ ከንጉሡ የመጡ ብዙ ቅጣቶችን ታግሦ በእስራትና በግርፋት ላለ ካገኘው የመንፈስ ሲሳይ ለሌሎች እያካፈለ÷ የሚታየውን ተስፋ እየሰጠ ብዙ ነፍሶችን ከሚገድል የዚህ ዓለም ባለሥልጣን የሐሰት ፍርድ ቅጣትን ለሚሸሹ ድጋፍ ሆኖ ሰማዕትነቱን ... ወር ... ቀን በሰላመ እግዚአብሔር ፈጸመ። (39^ሀ) ጸሎቱ ከኛ ጋር ትሁን፤ አሜን።

እነዚያ ወደ ብሔረ ምርጋይ የወሰዷቸው ደግሞ÷ እዚያ በወባ በሽታ በብዙ ጻማ ኖረው÷ ከነሱ ውስጥ ፲፯ቱ በነዚያው ዓመቶች በመልካም ገድል ሰማዕትነታቸውን ፈጸሙ። ከነሱ አንዲ ምእመኒት ነበረች፤ አብራቸው ገድሏን ፈጸመች። ጸሎታቸውና በረከታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ ለዘላለምም ትጠብቀን፤ አሜን።[31]

ለተረፉት እግዚአብሔር (ምሕረቱን) ከፍቶላቸው (እስከ) ደዋሮ በወዴህም እስከ ፈጸጋር ድረስ ደረሱ፤ የነፍስ ምግብ የሆነው የመለኮት ቃል መራቸው። ንጉሡ ወዲያ ወዲህ እንደሚሉና እንደሚያስተምሩ÷ እነሱ[32] እንዳሰቡት እግዚአብሔር አንዳላጠበበባቸው ሰማ። (ንጉሡ) እያንዳንዳቸውን በየአረሚው ቤት የበተናቸው ሃይማኖታቸው እንዲጠፋ÷ ሥርዓታቸውና ትምክሕታቸው እንዲሻር÷ በምርጋይ ያሉትም በወባ በሽታ እንዲያልቁ ነበረ። በምሕረቱ ብልጽግና እና በፍቅሩ ብዛት ያፈቀረን እግዚአብሔር ግን በኃጢአታችን ሙቶች ሆነን ሳለ በነሱ ስብከት ምሕረት አወረደልን። ከተበተንበትም (39^ሰ) ወደምትበልጠው ሃይማኖት ሰበሰበን። በነሱ (ስብከት) ከውሐና ከመንፈስ ቅዱስ የሆነችው ሁለተኛ ልደታችን በንጽሕትና በጸዳች ንስሐ ከከፍተኛ ወደ ከፍተኛ ከፍ ከፍ እያለች ታደሰች። በብዙ አውራጃዎቹ እንደመበተናቸው ብዛት በዚያው ልክ ጥሩዋ ሃይማኖታቸው ተዘራች፤ ብዙ ደጋጎችንም አፈራች። እንደ ስንዴ ዘር--ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ከሞተች ግን ብዙ ዘር ታፈራለች።

እንደገና ሰበሰቧቸው--136ቱ የጋሳ ግዞተኞች

ንጉሡ እንዳሰበው ማድረግ ሲያቅተው ጊዜ በየአረሚው ቤት የበተናቸውንና በምርጋይ ያሉትን ከ፩ ቦታ እንዲሰበስቧቸው አዘዘ። (ሲሰበሰቡ)

---

31. ግዕዙ የሚለው "ጸሎቱና በረከቱ" ነው፤ ሳይታሰብበት የገባ መደምደሚያ ነው።
32. ንጉሡና ወገኖቹ።

እያንዳንዳቸው በየአረሚው ቤት በእስራት እንዲኖሩ ጋሳ ወደምትባል የአረሚ ምድር እንዲወስዷቸው አዘዘ። ወታደሮቹ ትእዛዙን ተቀብለው ወደዚያች ሀገር ወሰዷቸው። ለዚያ ሀገር ሹም እስረከቡትና ንጉሡ ያለውን ነገሩት። ተረክቦ እንዲያስሯቸው ሎሌዎቹን አዘዛቸው። በተበሳ ግንድ አስራቸው፤ (40^{ሀ}) ቀኖተራቸው ፱፻፷ ሲሆን ከነሱ ውስጥ ፲፯ቱ መነኮሲቶች ነበሩ። እዚያ እያሉ ፩ ወንድሞች በእግዚአብሔር ሰላም ገድላቸውን ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ይሁን፤ ለዘላለምም ይጠብቀን፤ አሜን።

በጓትር ካሉትም ፬ ወንድሞች ገድላቸውን በጌታ ሰላም እዚያው ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ይሁን፤ ለዘላለሙም ይጠብቀን፤ አሜን።

አቡነ ይሥሐቅና ሊቀ ማኅበሩ

ይኸም አቡነ ይሥሐቅ[33] በእስራትና፥ በከባድ ገድል፥ በብዙ ትዕግሥት የደረሰበትን ስቃይ ሁሉ እየተቀበለ ከእነሱ ጋራ ኖረ። ወንድሞች ሁል ጊዜ ወደ ላይኛው እንዲያስቡ እንጂ ሐሳባቸውን ከላይ ወደ ጠፊ ዓለም ፍለጋ እንዳያወርዱ ምዕዳን ያስማቸው ነበረ። ከወንድሞች ጋራ በእስራት ከወሰዱት ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ ምክር ወደ ቀድሞ ገዳማቸው እስኪመለሱ ድረስ ፶ ዓመት ያህል እዚያው ኖረ።

እዚያ በነበሩበት ጊዜ ሊቀ ማኅበሩ[34] በአረሚ ብሔር እንደበተኗቸው ስለሰማ (40^{ለ}) አኗኗራቸውን ለማወቅ ጎበኛቸው። ከነሱ ዘንድ ሲደርስ፥ "ሰላም ለናንተ ይሁን" አላቸው።[35] ወንድሞቻቸው እንዴት እንዳሉም ነገራቸው። ታላቅ ደስታ ተደሰቱ፤ እግዚአብሔር ስለሠራላቸው ሁሉ ስብሐት አቀረቡለት።

ከዚያ፥ ወንድሞችን ሁሉ ሰበሰባቸውና፥ "በአረሚ ብሔር ከምትኖሩ ወደ ክርስቲያኑ ምድር ብትመለሱ ይሻላችኋል" አላቸው። ወንድሞች፥ እሺ አሉትና ከዚያ ወጥተው እግዚአብሔር ወደአዘጋጀላቸው ቦታ ሄዱ። አቡነ ይሥሐቅ ግን ከሊቀ ማኅበሩ ጋራ ሄደ፤ እብረው ብሔረ ትግራይ እስኪደርሱ ድረስ ከእሱ አልተለየም።

ከዚያ፥ ከተሰደዱበት እንደተመለሱ ማኅበር[36] አቋቁመው፥ በኃጢአት የተበተኑ ብዙ ነፍሶች ሰበሰቡ።[37] ቤተ ክርስቲያን ተክለው ቀኖባን አሳረጉ። የወንድሞቻቸውን ተዝካር አወጡ። የነፍስ አባታችን ሊቀ ማኅበሩ ወደ ሌሎች ማኅበር[36] ሲሄድ ለተረፉት በሱ ምትክ እንዲሆን እሱን[38] እዚያው

---

33. አቡነ ይሥሐቅ ደቂቀ አስጢፋኖስ በጣም ከሚያከብሯቸው ሽማግሌዎቻቸው አንዱ ነበሩ፤ ገድለ አቡነ ኢሳይያስ እንደሚያመለክተው ደብረ ዝዜንን የሠሯት (ዘሐነጸ) አሳቸው ናቸው፤ Ferenc, "Les Actes d'Isaïe", p. 244. በአቡነ አበክረዙንና በአቡነ ዕዝራ ገድል ውስጥም ተጠቅሰዋል።
34. "ሊቀ ማኅበሩ" የሚለው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስማቸው አንዴም ያልተጠራውን አቡነ አበክረዙንን ይመስለኛል።
35. አነጋገሩ የማናውቀውን ልማድ የሚገልጽ ይመስላል፤ አለዚያማ በኛ ዘመን ባህል ቢሆን "ሰላም ለናንተ ይሁን" ማለት ሊመዘገብ የሚገባው ድርጊት አይደለም።
36. ገዳም።
37. አዲስ ተክታዮች አተረፉ።
38. አቡነ ይሥሐቅን?

ይተወዋል። መንጋውን አንደሚጠብቅ (41ᵘ) እንደ ደግ እረኛ በማሠዳና በማስተማር እንደዚህ ሲጋደልና ሲደክም ብዙ ዓመቶች ኖረ። በደረሰበት ቦታ ሁሉ ቍርባን የሚያሳርግበት ቤተ ክርስቲያን መመሥረትን ያስቀድማል። ከዚያ በኋላ ልብሳቸውንና የዕለት እንጀራቸውን በጽድቅ ደክመው የሚያገኙበትን ያስባል። ደግሞ ከነሱ ላይ ያነሣና ለድኾች ያካፍላል። የጀመረውን ሁሉ እግዚአብሔር ያሠምርለታል።

ከፍ ያለ ስደትና ብዙ ችግር

በእንደዚህ ያለ ለጽድቅ ሥርዓት በመገዛትና ለወንድሞች ጥሩ ነገር ሲያስብ በወንድሞች ላይ የማጎበር ሥርዓት ካቋቋሙ ጀምሮ ያልደረሰ ከፍ ያለ ስደትና ብዙ ችግር መጣ። ብዙ ቅዱሳን የሚበሉት በማጣት ገድላቸውን ፈጸሙ።[39] (ሰማዕትነታቸውን) የፈጸሙትን ጥቂት ወንድሞች (ብቻ) እየረዱት (አቡነ ይሥሐቅ?) ብቻውን ይቀብራቸው ነበረ። የነፍስ አባታችን ሊቀ ማኅበሩም ከሱ ጋራ ነበረ።[40]

በዚህ ጭንቅ ላይ አያሉ የወንድሞቻቸውን ተዝካር ሲያወጡ ቍርባን ማሳረጋቸውን አልተዉም። ምግባቸው የሾላ ፍሬ፥ ዱባ፥ ቅጠላቅጠሉ ሁሉ ነበር። እኑሱንም ቢሆን የሚያገኙት በትንሹ ነበር።

(41ᴬ) (የተረፉት) ጭንቁን ሁሉ አሳልፈው ከዚያ፥ የላይኛው (ጌታ) ወደ ቀኝ እየመራቸው ብሔረ ቅዳ እስኪደርሱ ድረስ ሄዱ። ብዙዎችን በንጽሕት ንስሐ ወደ እምነት እየመለሱ እስከ ጊዜው ድረስ እዚያ ኖሩ።

ከዚያ፥ ወንድሞች አበዙት ከምትባል አገር በተሰበሰቡ ጊዜ በሱ ምትክ ምዕዳን እንዲያሰማቸውና እንዲገሥጻቸው (ወደነሱ) ላከው። እዚያም እንደዚሁ ኖረ። ከዚያ፥ እስከ ምዕራብ ብሔር ድረስ ተሰደዱ። ከዚያ ደግሞ ወደ ብሔረ ትግራይ ተመለሱ። ወንድሞችን ወደፊተኛው ቦታ ሰበሰባቸው። በጥሩ ሕንፃ አሠራር ቤተ ክርስቲያን ተከሉ። ይኸም ቅዱስ ለነፍሳቸው ሕይወት በጸም፥ በጸሎት፥ በልመና ይተጋ ነበረ። ለቍርባን ሲቀድስም ዕንባው እንደ ውሐ ይወርድ ነበረ። (የሰማዕትነት) ፍጻሜው እስከተገለጸለት ድረስ እንደዚህ በጽኑ ገድል ኖረ።

ከዚያ፥ ከባድ ደዌ አደረበት፤ እሱ ግን ሁሉንም ታግሦ ይላላኩት የነበሩትን ወንድሞች ምዕዳን ያሰማቸው ነበረ። ከዚያ፥ በመልካም ሽምግልና በግንቦት ዓሥራ ዘጠኝ ቀን አረፈ። (ገድሉን) ሲፈጽም (42ᵘ) ወንድሞች እሱ ዘንድ ተሰብስበው ሬሳውን በቅዱሳን ሥርዓት ገነዙት። ከመንበር ላይ አጋድመው ከቤተ ክርስቲያን አስቀመጡት። የነቢያትን መዝሙርና ቅዱሳት ወንጌላትን አነበቡ። ከዚያ፥ ቅዳሴ ገብተው ቍርባን ሠሩ። እዚያ እያለቀሱለትና እያዘኑለት ቀበሩት። ጸሎቱና በረከቱ ለዘላለም ከኛ ጋር ትሁን፤ አሜን፥ አሜን።

"ገድለ" ንግሥተ ማርያም

ያቺም ንግሥተ ማርያም[41] የሚሏት ቅድስት የሆነች የመነኮሲቶቹ እናት ጽድቅን በመካፈል በምስክራም ሆነ በችግርና በጭንቅ ውስጥ ሁሉ ለሞት

39. በረኃብ አለቁ።
40. ዐረፍተ ነገሩ የጐደለው ነገር አለ።
41. ከላይ "ንግሥት ማርያም" ያላቸው መነኮሲት ናቸው።

እስክትደርስ ቅዱሳኑን በመንገዳቸው ሁሉ ትከተላቸው ነበረ። ሲገርፏቸውም ከነሱ ጋራ ተገርፋለች። በዚህም ሥቃያቸውንና ትዕግሥታቸውን ተካፍላለች። በእስራት ወደ ብሔረ አረሚ ሲወሰዱቸውም ከነሱ አልተለየችም። በዚህም ሥቃያቸውንና ትዕግሥታቸውን ተካፍላለች። ከዚያ፥ ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ ቅዱሳኑና መነኮሲቶቹ ከተበተኑበት አበዘት ከምትባል ሀገር በየገዳማቸው የተሰበሰቡ ጊዜ (42ᴬ) እዚያም በጽድቅ ሥርዓት ሆና ብዙ የሚድኑ ነፍሶች ሰብስባለች።

ከዚህ ዓለም እና ከስቃዩ እንድትፈልስ (የሰማዕትነቷን) ፍጻሜ በቀረበ ጊዜ የቧን ብጤዎች በመንፈሳዊ በረከትና በሚገባ የምዕዳን ቃል ባረከቻቸው። ከዚያች ዕለት ጀምሮ በከባድ በሽታና በጥውም ትዕግሥት ምንም ቃል ሳትናገር፥ ግን የሰው ልጅ ሊናገረው የማይሆንለት ምስጢር ከማየት ውስጥ ሆና ቆየች። ከዚያ፥ በሐምሌ ፳ ቀን አረፈች። ጸሎቷ ከኛ ጋራ ይሁን፤ አሜን።

ከዚህ በኋላ፥ አባታችን እንዳረፈች ሲሰማ ከመቃብሯ ላይ ቍርባን እንዲያሳርጉ ቄሶችና ዲያቆናት ወንድሞች ላከ። እነሱም ሄደው እንዳዘዛቸው ፴ ቀን ቍርባን አደረጉላት። ይሽንን አድርገው ወደ ማኅበር ተመለሱ። ከዚያ በኋላ ሥጋዋን አውጥተው እግዚአብሔር ወደወደደው (ቦታ) አፈለሱት። ጸሎቷና በረከቷ ከኛ ጋራ ይሁን፤ አሜን፥ አሜን።

፳ወ፫

ወደ ጦር መምጫ ግዞት

(43ᵁ) ከዘመን በኋላ፥ ንጉሡ ቅዱሳኑን ከአረሚዎች ዘንድ በሚመጣ በብዙ ጣር እንዲኖሩ ወንዶቻቸውንም ሴቶቻቸውንም የጦር መምጫ ወደሆነው ወደ መንግሥቱ ምሥራቅ በትኗቸው፥[42] (እዚያ) በሺንቁር ግንድ በማነቆ አሰሯቸው። ልብሳቸውንና ቆባቸውን ገፈፏቸው። አንዳንዶቹን ፊጽሞ ራቁታቸውን አድርገው በብዙ ሥቃይ አስጨነቋቸው፤ አንዳንዱን በጦር ይጓጉጠታል፤ አንዳንዱን በቤቱ ዓምድ ያንጠለጥሉና ጪስ ያጥኑታል፤ አንዳንዱን ሀፈር ይበትኑበታል፤ አንዳንዶቹን እበት ያመጡና (ይለቀልቋቸዋል)፤ የምድጃ አመድ ይደፉባቸዋል፤ አንዳንዶቹን በግንዱ ሺንቁር ውስጥ ጠጠር ይጨምሩና ከሥጋቸው ላይ ይቀረቅሩታል። አንዳንዱን ጢሙን ይነጩታል። ሌሎችም እነዚህን የሚመስሉ ሥቃዮችን (እያመጡባቸው) በዚህ ሁኔታ ኖሩ። "ነፍሳችሁን በትዕግሥታችሁ ታገኟታላችሁ"[43] የሚለውን የጌታን ቃልና (43ᴬ) "መንፈስ እንጂ ሥጋስ

42. አገሩ አደል መሆኑ ነው፤ ከታወቁት ጦርነት አንዱ ከኢማም በድላይ ጋራ የተደረገው ነው። ታሪኩ በንጉሡ ታሪክ፥ በተአምረ ማርያምና በገድለ ጊዮርጊስ ተመዝግቧል፤ Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm, Paris 1893*, pp. 57-67; E. Cerulli, "L'Etiopia del secolo XV in nuovi documenti storici," *Africa Italiana*, vol. V (1933), pp. 57-112; Kurt Wendt, *Das Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis) des Kaizers Zar'a Yā'qob, CSCO*, vol. 221/41, Louvain 1962, pp. 14-20.

43. ሉቃ 21፡ 19።

ምንም አይጠቅምም"[44] የሚለውን ተረድተው፥ "ሰፊውን ተስፋ በማድረግ ጠባቡን ታገሡት::"[45]

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር ምሕረቱን ከፈተላቸው፤ "እግዚአብሔር ሕዝቡን አይተዋቸውም፤ ርስቱንም አይጥላቸውም"[46] የሚል እንደተጻፈ፥ አረሚዎቹን አስታገሣላቸው:: ደግሞ፥ "ምሕረት ከእግዚአብሔር ነው፤ ብዙ ማዳንም ከሱ ዘንድ አለ"[47] ይላል:: ደግሞ፥ "የእግዚአብሔር ምሕረቱ በጊዜው ይመጣል"[48] ይላል:: ከነሱ ውስጥ ፩ መዓልም መጣና የቅዱሳኑን የሥራቸውን ውበትና ብዙ ትዕግሥታቸውን አየና ሲመለስ ሰዎቹን ገሠጻቸው፤ "የእግዚአብሔር ምስኪኖች ስለሆኑ አትክፉባቸው" አላቸው:: "ደግ ነው፤ በቃልህ እንዳልከው ይሁን" አሉት:: መዓልማቸው ስለሆነ ያከብሩታል፤ ይታዘዙታልም:: ፈቷቸውና ከነበሩባቸው ሥቃዮች ጥቂት አረፉ:: ከእጃቸው ሥራ ድካም ይመገቡና ይለብሱ ጀመር:: እስከ ጊዜው እንደዚህ ኖሩ::

የሊቀ ማኅበሩ ጉብኝት

(44^{ሀ}) አቡነ ተወልደ መድኅን በጉንጽ በእስራት ባለበት ጊዜ በጋሳና በጓትር በሌሎችም ቦታዎች ያሉትን ወንድሞች መበታተን አስቦ ወደ ነፍስ አባታችን ወደ ሊቀ ማኅበሩ፥ "በፊት አባታችን ሽማግሌዎችን እንድታጽናናና እንድታረጋጋ፥ ወጣቶችን እንድታጽናናና እንድትጠብቅ፥ ሕፃናትን እንድታሳድግ፥ እስረኞችን እንድትጠይቅ፥ ብዙዎችን እንድትደግፍ ሾመህ የለምን?" የሚል (ቃል) ከሰላምታ ቃል ጋራ ላከበት::

እሱ (ይኸንን) ሲሰማ ተነሥቶ ሄደ:: ከእስረኞቹ ዘንድ ደርሶ ምዕዳን በሚገባ አሰማቸው፤ በጣም ደስ አላቸው::

ከዚያ፥ የቅዱስ አባታችንን ዐፅም ወዳቃጠሉባት አግበራ ወደምትባል ሀገር ሄደ:: ዐፅሙን ከነመግነዙ ምልክት ጋራ ድንጋይ በላዩ ከምረውበት አገኘው:: በሠኔ ፳፫ ቀን አፍልሶ እግዚአብሔር ከፈቀደበት ቦታ ደበቀው:: ከዚያ ሄዶ፥ በጋሳ[49] እና በጓትር ካሉት እስረኞች ዘንድ ደረሰ:: ምዕዳን በሚገባ አሰማቸውና፥ "በአረሚዎች ማህል መኖር አይሻላችሁም፤ (44^{ለ}) (ወደ) እማያስጨንቋችሁ ወደ ምድረ ክርስቲያን ውጡ" አላቸው:: "ጥሩ ነው፤ እንደቃልህ ይሁን:: ከዚህ አገር በራሳችን ፈቃድ እንዳንወጣ እንፈራለን፤ አንተ ከፈቀድክልን ሁላችንም እንስማማለን" አሉት::

ከዚያ ወጥተው በየብሔሩ ሲበታተኑ ዘበኞች ተከታትለው ከነሱ ጥቂቶቹን አግኝተው ያዟቸውና መለሷቸው:: የሆነውን ለንጉሡ ነገሩት:: ንጉሡ፥ "ለመንግሥቴ ክብር አልሰገዱም በማለት ቀጣኋቸው፤ አሁንም መነኮሴዎች አይደሉምን? ከፈለጉበት ሄደው ይኑሩ" አለ::

"ዶክተር" ያፍቅረነ እግዚእና ባሕታዊቷ

ከዚያ ወጥተው ደንጎ ከምትባል አገር ደርሰው እዚያ ተቀመጡ:: እዚያ እቅርባቸው የሚኖር አንድ ያፍቅረነ እግዚእ የሚባል መነኮሴ ነበረ::

---

44. ዮሐ 6: 63::
45. ሉቃ 7: 18::
46. ?::
47. መዝ 129: 4፥ 7::
48. መዝ 68: 14::
49. ግዕዙ "በጋርሳ" ይላል::

ባለመድኃኒት ነው። ቅጠል ይቈርጣል÷ መሬት አና ስራስር ይቈፍራል። አንዳንዱን ያጠጣዋል፤ አንዳንዱን ይቀባዋል÷ አንዳንዱን ይረጨዋል። ስለዚህ ብዙዎች ይወዱታል፤ ይቀበሉታል። እቅርቡ አንዲት በጥሞና ለጸሎት የተጠመደች መነኮሲት ነበረች። ብረት ትታጠቃለች። መነኮሴው እሷ ዘንድ እየሄደ (45[ሀ]) የሆነውን (ሁሉ) ይነግራታል። እሷም የቅዱሳኑን ዜና ስምታ ኖሮ÷ "ላያቸው እፈልጋለሁ" ትል ነበረ።

ቅዱሳኑ ሰምተው ወደሷ ሄዱ። በቤቷ መስኮት በኩል አነጋገሯቸው። እነሱም የምንኮስናን ሥርዓት ነገሯት፤ "የወንጌል ቀምበር እኮ እንዲህ አይደለም፤ ምክንያቱም ጌታ በወንጌል÷ የሞቱን መስቀል ከኔ ያልወሰደና ሊሸከመው ያልጨከነ÷ ከኋላዬ ያልተከተለኝ ሊጠመደኝ አይችልም"[50] ብሏል። ነፍሱን ያገኛት ይጣላት፤ ነፍሱን ስለኔ የጣለ ያገኛታል[51] ብሏል" አሏት። ሌላም ብዙ ይሽንን የሚመስል አስተማሯትና ሄዱ። እሷም ስምታ ሁሉንም በልቧ ታስቀምጠው ነበር።[52]

ከዚያ በኋላ÷ ከዚያ መነኮሴ ጋራ ተገናኙና ስለ ሃይማኖት ጉዳይና የሐዲስንና የብሉይን ሕግ ውሳኔዎች ስለ መጠበቅ ተወያዩ። ወደዳቸውና÷ "እንግዲህ ጐብኙኝ" አሳቸው። ከዚያ÷ ወደ ቤቱ ሲመጡ በውሐ የራሱ ቅጠሎች አዩ። "ይህ ምንድን ነው?" አሉት። "መድኃኒት ነው" አሳቸው።

"ለምን (እንደዚህ) ታደርጋለህ? ይሽ ከንቱ አይደለምን? ምክንያቱም አባቶቻችን ሐዋርያት÷ ወደ ሕጋችን የገባ (45[ለ]) መድኃኒት የሚቀምም÷ ይተው፤ አለዚያ ይባረር[53] ይላሉ። እንተም መነኮሴ ሆነህ ሳለ ይሽንን አታድርግ" አሉት። መነኮሴው (ንግግራቸው) አልጣመውም። እነሱም ወደ ማደሪያቸው ሄዱ።

ከዚያ÷ አየዞሩ በዚያች ሀገር ሁሉ ወንዱንም ሴቱንም አስተማሩ። ከነሱ የተደበቀችውን የነፍስ ምግብ የሆነችውን ቃለ መለኮት ነገሯቸው። ጌታ እንዲህ ያለውን የወንጌልን ምስጢሮች ተረጐሙላቸው፤ "ግን ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ አነማን (?) ያደርጋሉ፤ በስሜ አጋንንት ያወጣሉ፤ በሌላ ቋንቋ አዲስ (ነገር) ይናገራሉ፤ አባቦችን ይይዛሉ፤ የሚገድል (ነገር) ቢጠጡ ምንም እያደርጋቸውም፤ በበሽተኞች ላይ እጆቻቸውን ያሳርፋሉ፤ ይድናሉ"።[54]

ይሽንንና የመሰለውን በነቢዩ÷ "የሚያስተምሩ እግዚአብሔር የጠራቸው ናቸው"[55] እንደተባለው አስተማሩ። ብዙዎች ወንዶችም ሴቶችም ወደ ቅዱሳኑ ትምህርት ተመለሱ÷ በማዳመጥ (ልባቸው) ተሰቀለ። ያንን መነኮሴ ተዉት። አንዳንዶቹ ከነሱ ጋራ አንድ ሆኑ፤ አንዳንዶቹ ወንዶችና ሴቶችም አቤታቸው ሆነው ያስተማሯቸውን ቃል ጠበቁ።

(46[ሀ]) ያቺ መነኮሲትም የመላእክት ንጽሕ ምሳሌ በሆነችው በንጽሕ ሥርዓት ያሉ ወዳጆቿን ከብዙዎች አገሮች ሁሉ ወደ እነሱ ወደ ሥርዓታቸው ለማምጣት አመረተቻቸው። ብዙዎች እየመጡ ከሥርዓታቸው ገቡ፤ ብዙዎች ሆኑ።

---

50. ማቴ 10: 38።
51. ማቴ 10: 39።
52. ቅድስት ማርያም የተናገረችው ዓረፍተ ነገር ነው፤ ሉቃ 2: 51።
53. ሲኖዶሱ፡
54. ማር 16: 17-18።
55. ?።

በዚህ ምክንያት ያንን ያፍቅረነ እግዚእ የሚባል መነኮሴ ቅናት ያዘው፤ በጥፋቷና በዝሙቷ የምድር ሕዝቦችና ከሴሰኗ ጎይል የበሉ የምድር ነገሥትም በወደቀበት የመርዝ ወይን ሰከረ።[56] ሰይጣን ጋሳቢ ሆነ። ጥሩ ጠባይ ያላቸውን (?) የሚተባበሩትን ጓደኞቹን አጥምዷቸው ተሰብስበው ከንቱ ምክር ተማከሩ፤ ቅዱሳኑን የሚከሱበትን ወሰኑ። ከዚያ፥ ናሖም ወደሚባለው ወደዚያች ሀገር ሊቀ ካህናት ሄደው የሆነውንና ያልሆነውን ሁሉ ከመምህራቸው ከሰይጣን መንፈስ ውሸት እየጨመሩ ነገሩት። እሱም ቃላቸውን ሰማ፤ ነገራቸውንም ተቀበለ። ሁሉን የሚያሳምን ከመምህሩ ከሰይጣን መንፈስ ውሸት ጨምሮ የእብለት ደብዳቤ ጽፎላቸው ወደ ንጉሡ ላከ።

ከንጉሡ አደባባይ--ከርክርና ዱላ

ንጉሡ (46^ለ) ያቺን የእብለት ደብዳቤ አይቶ ተቆጣ። እንዲያመጧቸው ወታደሮቹን ላከ። የንጉሡ መልእክተኞች መጥተው ቅዱሳኑን ያዟቸው። ከንጉሡ አደባባይ አመጧቸው።

እነሱም፥ "ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሩ፤ ነፍሳችሁን ግን ሊገድሉ አይችሉም። ግን ነፍሰንም ሥጋንም በገሀነም አበላሽቶ የሚገድልን ፍሩ እንጂ"[57] የሚለውን ልብ ብለው ሥቃዩን ለመቀበል ዝግጁ ሆነው፥ በማነቆ ታሰረው መጡ። ከሰፈሩ ውሰጥ አሰገቧቸው፤ ከአጠገቡም አቆሟቸው።

ንጉሡ፥ "ሰላም ለናንተ ይሁን" ብሎ ላከባቸው። እንደሚገባው ሰላምታ መለሱ። "ለንጉሡ ስገዱ እንጂ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "በምን ምክንያት ሆነና ነው በሕይወታችን ዘመን ሁሉ የምንገረፈው፥ የምንሰደበው፥ የምንሰደደው? በዚህ ምክንያት አይደለምን? እኛ ለእግዚአብሔር ካልሆነ ለማንም እንሰግድም" አሉ።

ቅዱሳኑ ያሉትን ለንጉሡ ነገሩት። ንጉሡ፥ "ለእግዚአብሔርም አትሰግዱም ይባላል። እስቲ ለእግዚአብሔር ሰገዱ" አለ። (47^ዐ) ሊገድሳቸው ምክንያት ሲፈልግ ነው እንጂ ለእግዚአብሔር መሰገድ አሳስቦት አይደለም። እነሱ ግን ተንኮሉን ዐውቀውበታል፤ "እሰ፥ እዚህ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ፤ እንድንሰግድ እዚያ አሰገባን በሉት"[58] አሉ። ለንጉሡ ነገሩት። ንጉሡ፥ "መለኮቱ በሀገሮች ሁሉ ነው ይል የለምን?[59] መጽሐፉ፥ በታላቁ ሕዝብ መካከልም ስብሐት አቀርብልሃለሁ ይላል"[60] አለ።

እነሱ ደግሞ፥ "ከዚህ ሁሉ በወንጌል ሰትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ እነሱ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኵራብና በየማእዘኑ በየመንገዱ

---

56. ራእ 18፡ 3።
57. ማቴ 10፡ 28።
58. በንጉሡ ዓዋጅ ደቂቀ አስጢፋኖስ እንኳን ከቤተ ክርስቲያን ከቤተ ምእመናንም እንዳይገቡ ክልክል ነበሩ።
59. መዝ 102፡ 22፤ ንጉሡና ሌሎቹም የሀገራችን ሊቃውንት የጥንቱን ግዕዙን ስላልተረዱት እንዲህ የሚል መስሏቸው ነው እንጂ፥ "መለኮቱ" ማለት "መለኮቱ" ማለት እይደለም፤ "ግዛቱ" ማለት ነው፤ ጥቅሱም የሚለው "ግዛቱ በብሔሮች ሁሉ" ነው።
60. መዝ 34/35፡ 18፤ ባላችሁበት ስገዱ ሊላቸው ነው።

ቆመው መጻለይ ይወዳሉ፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ዋጋቸው ተበላሽቷል። አንተ ግን ከቤትህ ግባና በርህን ዘግተህ በድብቅ ላለው አባትህ ጸልይ። በስውር የሚያይህ አባትህ በግልጥ ይሰጥሃል[61] የሚለው የእግዚአብሔር የምስክር ቃሉ ይበልጣል" አሉ። ይኸንንም ነገሩት።

ከዚያ፥ ንጉሡ ለሠራዊቱ እንዲህ ብሎ አስሰማ፤ "ለእግዚአብሔር ስገዱ ብንላቸው አንሰግድም ሲሉ ሰሙ።" ቅዱሳኑም ለሠራዊቱ እንዲህ ሲሉ አስሰሙ፤ "እኛንም ሰሙ፤ እኛ ለእግዚአብሔር አንሰግድም አላልንም፤ (47ᴬ) ግን ሊገድለን ምክንያት ይፈልጋል።"

ከዚያ፥ ንጉሡ በቁጣ እንዲደበድቧቸው አዘዘ። በዐውድማ እንዳለ የእህል ነዶ በዱላና በብትር ደበደቧቸው። ከዚያ፥ ንጉሡ፥ "ወርቅ የወደድክ ወርቅ አጠጣሃለሁ ብሏል"[62] አሁንም አፉን አቅኑና ሰርኑን ስበሩት፤ ደሙን በአፍንጫው ይጠጣ" አለ። ይኸ ስሙ ጳውሎስ የሚባለው ወንድም ነገረ ፈጅ ስለሆነ በዚህ በነገረ ፈጅ ወንድምና በጥቂቶች እንጂ በሁሉም ላይ እንደዚህ አላደረጉም። ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ አጋድመው ገረፏቸው። ሁሉንም አጋድመው ጨጨ በምትባለዋ በመግረፊያ ጅራፍ ገረፏቸው። ከዚያ፥ ቁጣውን ካስተነፈሰ በኋላ "(ወዲያ) ውሰዷቸው" አለ።

በማግስቱ እንዲያመጧቸው አዘዘ፤ እንደታሰሩ አመጧቸው። ከሰቀላው ሰፈር አውለው ሲመሽ ከፊቱ እንዲያቆሟቸው አዘዘ። (ሲቆሙ) "ለንጉሡ ስገዱ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "አንሰግድም" አሉ። (48ᵁ) "ጣላቸው፤ የትናንትናው አልበቃህም" ብሎ እንዲገርፏቸው አዘዘ። ያንን ወንድም (ጳውሎስን) አእምሮውን እስኪያጣ ድረስ ብዙ (ገረፉት)። ያቺም ከዋሻዋ ወጥታ ከነሱ ጋራ የሆነችው መነኮሲት በግርፊያው ተለክፋ (ሰማዕትነቷን) እስክትፈጽም ድረስ ብዙ ተገረፈች። ከዚያ፥ ቁጣውን ካስተነፈሰ በኋላ "(ወዲያ) ውሰዷቸው" አለ። ከሰፈሩ ወደ ውጪ አወጧቸውና በእስራት ቆዩ።

ፍሬምናጦስ ዘደብረ መገራን እና ቀሌምንጦስ ዘሀገረ ማርያም ጠላት ሆኑ

ይኸንን ሲያዩ ብዙዎች የሰይጣን አገልጋዮች ተነሥተው ንጉሡን፥ "እንደነዚህ ያሉ እኛም አገር አሉ፤ እንድናመጣቸው መልእክተኞች ስጠን" አሉት። ፍሬምናጦስ የሚሉት የደብረ መገራን መምህርም[63] ተነሥቶ መልእክተኞች እንዲሰጡት ጠየቀ። መልእክተኞች ሰጡት። ሌላውም ከካህናተ ደብተራ ቀሌምንጦስ የሚሉት ሀገረ ማርያም የሚሏት የሀገረ እብሶው (መነኮሴ) እንደዚሁ ቅዱሳኑን ይዞ ከንጉሡ አደባባይ አመጣቸው። ሽማግሌውን (48ᴬ) አቡነ አባ በርተሎሜዎስንም በፊት በሀገረ ሳጉራ ካጋዙበት አመጡትና እዚህ አቀረቡት።

ይኸ ፍሬምናጦስ የሚሉት መነኮሴም በፊት እንዳለው ከንጉሡ አደባባይ አመጣቸው። "ለንጉሡ ስገዱ" አሏቸው። ማቴዎስ የሚባለው አንዱ ወንድም፥ "ወራቱ እንኳን ለሰው ለእግዚአብሔርም እንዲሰገድበት እልታዘዘም፤ አሁን የጸንጠቆስጤ[64] ወራት ነው" አለ። በዚህ ምክንያት ተዋቸውና እንደታሰሩ ከሰፈሩ ውጪ አኖሯቸው።

---

61. ማቴ 6: 5-6።
62. *ታሪኩን ጌታቸው ኃይሌ፥ ባሕረ ሐሳብ፥ የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማሰታወሻ ጋራ፥* ገጽ 56-57 ላይ ተመልከት።
63. "የገዳም መምህር" የሚለው አበምኔቱን ነው።
64. የበዓለ 50።

ከዚያ፥ በሠኔ ፳፭ ቀን ሁሉንም ባንድነት (ከንጉሡ ፊት) አቆሟቸው፤ አቡነ በርተሎሜዎስንም አምጥተው ከነሱ ጋራ አቆሙት። ከዚያ፥ የንጉሡ የሠራዊት አለቃ መጣና፥ "ለንጉሡ አትሰግዱምን" አላቸው። "አዎ፥ ለአግዚአብሔር በቀር (ለማንም) አንሰግድም" አሉት።

ንጉሡ በነገሠባት የበዓሉ ቀን ጭቅጭቅ የለም

የንጉሡ አገልጋዮች ሊደበድቧቸውና ሊቃለሏቸው ፈለጉ። የሠራዊቱ አለቃ አንዲህ ብሎ ከለከላቸው፤ "ዛሬ ሁከትና ጭቅጭቅ አይኖርም፤ (49ᵁ) ንጉሡ የነገሠባት የበዓሉ ቀን ናት፡ ግብር ያገባል። በዚህ ምክንያት ጭቅጭቅ አይኖርም" አለ።

ከዚያ፥ የሠራዊቱ አለቃ አንዲያስሯቸው ትእዛዝ ሰጠ። አስር ቤት አግብተው እጃቸውንና አግራቸውን አሰሯቸው። በአንገታቸውም ላይ ማነቆ (አሰሩባቸው)።

በማግሥቱ ንጉሡ አንዲያወጧቸው አዘዘ። ወደ ሰቀላው አደባባይ አወጧቸው። ንጉሡ አዚያ ስብሰባ አደረገ። የሠራዊቱ አለቃ መጣ፤ ብዙዎች መነኮሳትና ካህናት ያም ኖብ የሚሉት መነኮሴም (መጡ)። "ለንጉሥ ስገዱ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "እኛ ለአግዚአብሔር በቀር ለሰው አንሰግድም" አሉ። "በሉ ለአግዚአብሔርም ቢሆን ስገዱ" አሏቸው።

ቅዱሳኑ፥ "እነሆ እዚህ ቤተ ክርስቲያኖች፤ በቀኝም በግራም ቤተ ክርስቲያኖች አሉ። እዚያ አንድንሰግድ አስገባን" አሉት። ሊገድላቸው ሰበብ ፈልጎ ነው እንጂ ለአግዚአብሔር መስገድ አሱን አሳስቦት አይደለም። ከዚያ፥ አንዲያስፈራሯቸው አሳት አንዲያነዱ ንጉሡ ትእዛዝ ሰጠ። እነሱ ግን ስለ አግዚአብሔር ለመሞት ጨክነው ነበረ። (ግን) ከአሳቱ ውስጥ አልጨመሯቸውም። (49^ሰ) ወደ አስር ቤት መለሷቸው። እንደበፊቱ አንደታሰሩ አደሩ። በማግሥቱ አንዲያወጧቸው አዘዘ። (ሲመጡ) አንዲህ ሊል ላከባቸው፤ "ትናንት ስለመሸ አላደረሰንም፤ ዛሬ ሃይማኖታችሁን ታሳያላችሁ፤ ከአሳት ትገባላችሁ።" ቅዱሳኑ ለላካቸው፥ "ያመጣኸውን ሁሉ በአምላካችን በአግዚአብሔር ስም እንቀበላለን በሉት" አሉት።

ትልቅ ጉባኤና ክርክር

ንጉሡ ከትናንቱ የሚበልጥ ትልቅ ስብሰባ አደረገ፤ የሠራዊቱ አለቃ መጣ፤ ያም ኖብ የሚሉት ንጉሡ የሰይጣን ከበሮ (ያለው) መነኮሴ፥[65] ብዙ መነኮሳት፥ ካህናተ ደብተራም ስለ ጉዳዩ አንዲሟገቱ (መጡ)። መድረኮች አመጡና ኖብ የሚሉትን መነኮሴ ካንድ መድረክ ላይ፥ ወንድም ጳውሎስን ከአንድ መድረክ ላይ አቆሟቸው። የሚመረኮዙበት ዘንግ አስያዟቸው።[66] ከዚያ፥ የሠራዊቱ አለቃ (አሟጋች ሆኖ)፥ "ንጉሡ ለአግዚአብሔር ስገዱ ሲሏችሁ ለምን አትሰግዱም? ከኢትዮጵያ መነኮሳት ጋራ በቆብ ለምን አትተባበሩም?[67] ቁርባንስ ለምን (ለሌሎች) አታቀብሉም? (50ᵁ) ከሌላ ቦታ ስትሄዱ ከነሱ ትቀበላላችሁ፤ እናንተ ግን አታቀብሉም ይላል" አለ።

---

65. Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, p. 12.
66. አስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአገር ቤት የሚሟገቱት ዘንግ ይዘው ነበረ።
67. ቆባቸው የተለየ ነበረ።

ነገረ ፈጅ የሆነው ወንድም አፉን ከፈተና[68] እንዲህ አለ፤ "እኛ ሁል ጊዜ ለእግዚአብሔር እንሰግዳለን፤ ለእግዚአብሔር የምንሰግደው በሰው ትእዛዝ አይደለም፤ ነቢዩ፥ በመቅደሱ ግቢ ለእግዚአብሔር ስገዱ[69] ያለውን እናውቃለን፤ ደግሞ እየፈራሁህ በመቅደስህ አዳራሽ እሰግዳለሁ[70] ይላል::"

አባታችን አባ በርተሎሜዎስም በነገሩ ላይ አስከትሎ፥ "ጊዜው ላይደርስ በተገኘበት ቦታ በሰው ትእዛዝ ይሰገዳልን? ነቢዩ፥ በቀን ሰባት ጊዜ ስብሐት አቀርብልሃለሁ[71] አላለምን?" አለ::

ከዚያ፥ ነገረ ፈጅ የሆነው ወንድም፥ "ስለ መሥዋዕትስ በአባቶቻችን በሐዋርያት ትእዛዝ ሥርዓት የያዘ አይደለምን? እንግዳ ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ሲመጣ ስለ ሃይማኖቱና ስለ ግብሩ ይጠይቁታል:: የሚገባው ከሆነ ያቀብሉታል፤ ካልተገባው ግን ይሰዱታል:: ጠይቆ የሚሰጥ (ባለቤት እንጂ) እንግዳ አይደለም:: እኛም እንግዳ ሲመጣ እንጠይቀዋለን፤ (50^{b}) የሚገባው ከሆነ እናቀብለዋለን፤ ካልተገባው እንስደዋለን:: ወደ ሌላ ቦታ ስንሄድ ግን ልንመረምርና ልናቀብል አይገባም:: ስለ ቆብም አክሊል አይደለምን? ነቢዩ፥ ከክቡር ዕንቁ የተሠራ አክሊል በራሱ ላይ አኖርክ[72] ይላል:: ከሌላ ቦታ ደግሞ፥ እናቱ የደፋችለትን አክሊል[73] ይላል:: በወንጌሉ ውስጥም፥ "ወታደሮች የእሾህ አክሊል ጐንጕነው በራሱ ላይ አኖሩ[74] ይላል:: ደግሞ፥ ጌታ ኢየሱስ የሾክ አክሊል ደፍቶ ወጣ[75] ይላል:: ይኸ የጌታችን የክርስቶስ ሥቃይ አርአያ አይደለምን?" አለ::

ከዚያ፥ ኖብ የሚባለው መነኮሴ እንዲህ አለ፤ "ይኸንንስ እኔ እተረጕምልሃለሁ፤ አክሊል በራሱ ላይ አኖርክ ያለው ስለ ትስብእቱ[76] ነው፤ እናቱ የደፋችለት አክሊል ያለውም ስለ ትስብእቱ ነው" አለ::

ይኸ የሰይጣን ከበሮ እንዲህ ያለው እንደ ነቢዩ ቃል ማለቱ ሳይሆን፥ "በሞኞች አፍ አልጫ ቃል አለ"[77] እንዳለው እንደ ነቢዩ ቃል ከልቡ ግሳት ነው:: አብረውት የነበሩትም የሕግ ጥቅስ የሌለበት የምናምንቴያቸውን ጥርቃሞ አበዙ::

(51^{b}) ቅዱሳኑ መልስ ለመስጠት ሲናገሩ፥ ይኸ ውሸት ልማዱ፥ ኃጢአት ጥጋቡ፥ ፀረ ጽድቅ፥ ንጉሡ የሰይጣን ከበሮነት የሾመው መነኮሴ ሕዝቡን፥ "ለምን ታዳምጢቸዋላችሁ? ዝናብ የሌላት ደመና ናቸው የሚላቸው አይደሉምን? ፍሬ ቢስ ዛፎች ናቸው ያላቸው ናቸው:: ለውርደታቸው የሚፍለቀለቁ ሞገዶች ናቸው የሚላቸው ናቸው"[78] አላቸው::

---

68. በዛሬ ባህል "አፉን ከፈተ" ማለት ጸያፍ ነው፤ በግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ግን የተለመደ ነው፤ "አፉን ዘግቶ/ይዞ ዝም አላለም" ማለት ነው::
69. መዝ 28: 2::
70. መዝ 137: 2::
71. መዝ 118: 164::
72. መዝ 20: 4/ 21: 3::
73. መኃ 3: 11::
74. ዮሐ 19: 2::
75. ዮሐ 19: 5::
76. ወልድ ሰው ስለመሆኑ::
77. ሲራ 20: 24::
78. ይሁ 12-13::

ቅዱሳኑ ግን ይኸንን ሲሰሙ፡ "ልብ በማለት ትሰሙን እንደሆነ ለፊተኛውም ይኸ መነኮሴ አሁን ላለውም የሚገባውን ቃል እንመልስ ነበረ፤ ካልሆነ ግን ሥቃዮቹን ለመሸከም እግዚአብሔር ይረዳናል" አሉ። እነሱ (እንዲህ) ያሉት የመጻሕፍቱን ቃል እና ጉዳዮቹን መመለስ አቅቷቸው ሳይሆን ስለታገሡ ነው።

የጸሎት ሰዓት ደረሰ

በዚህ ሁኔታ እንዳሉ የጸሎት ሰዓት ደረሰ። (እንዲህ) አሉ፤ "እንግዲህ ስሙን፤ መነኮሴ በቤተ ክርስቲያን ወይም በገዳም እንጂ በንጉሦችና በመኳንንት ስፈር ሊጸልይ አይገባውም። ይዛችሁ አመጣችሁን፤ (51^ሀ) ለእግዚአብሔር ስለ መስገድም ጠየቃችሁን። በሚገባ መለስንላችሁ፤ እናንተ ግን ጠረጠራችሁን። እንግዴህ፡ ኑ ለእግዚአብሔር በአንድነት እንስገድ" ብሎ ከመድረኩ ወረደ። ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረው ለእግዚአብሔር ሰገዱ። እንደተለመደው ጸለዩ። ጸሎት ጨርሰው እንደ ሥርዓታቸው እርስ በርሳቸው ሰላምታ ተሰጣጡ።[79] ሌሎቹ ቁመው ያዩዋቸው ነበረ። አንዳንዶቹ ከቅዱሳኑ (አፍ) የሚወጣውን ቃል፡ በተለየም በጸሎታቸው ውስጥ "የአምላክ እናት ሆይ፡ እነሆ ከምሕረትሽ ጥላ ስር ተደግፈናል፤ በጭንቃችን ጊዜ ልመናችንን አትናቂ"[80] የሚሉትን ቃላት ሲሰሙ እደነቁ። ምክንያቱም በፊት ስለ ማርያም ይጠረጥሯቸው ነበረ።

ንጉሡ (እንዲህ ሲል) አዘዘ፤ "እኔ ሳዛቸው እምቢ ይላሉ፤ የጸሎታቸው ሰዓት ሲደርስ ይሰግዳሉ። እኔን መናቃቸው አይደለምን? እንግዲህ በሚሠሩት ሁሉ ፍረዱ።" እንዲህ ሲሉ ፈረዱባቸው፤ "ንጉሥ አይታዘዙም፤ ለክብሩም አይሰግዱም፤ ስለዚህ ይሙቱ።" ነቢዩ፡ "በፍርድ ላይ ትክክሉን ጠብቁ፤ የመድኃኒቴ መምጫ (52^ሀ) የጽድቁም በፍጥነት መገለጽ ቀርቧል"[81] ያለውን፡ በሌላ ቦታ ደግሞ፡ "ሁል ጊዜ ፍርድን የሚጠብቁና ጽድቅን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው"[82] ያለውን አላስታወሱም።

በእሳት እንፈታተን

መነኮሴው ንጉሡን፡ "ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፡ ሃይማኖቴና ሃይማኖታቸው እንዲታይ እኔና እነሱ ወደ (እሳቱ) ውስጥ እንድንገባ ፍቀድልኝ" አለ። ንጉሡ እሳት እንዲያነዱ ቀደም ብሎ አዝዞ ነበር። ንጉሡ ቅዱሳኑን፡ "ስለሚላችሁ አገባ አትሉምን?" አላቸው። ቅዱሳኑ፡ "እኛ (እንድታቃጥለን) ፈቃድ አንስጥህም፤ ግን ያመጣኸውን ሁሉ በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም እንቀበላለን" አሉት።

ከዚያ፡ ንጉሡ ቅዱሳኑን ወደ እሳቱ ውስጥ እንዲወስዷቸው አዘዘ። ያነደዱት እሳት ትልቅ ቤት ያህል ነበረ። ነበልባሉ እንደ ደመና ወደ ላይ ወጥቶ ነበረ። ቅዱሳኑን እየገፈተሩ እንደታሰሩ ወስደው እዚያ አደረሷቸው። እነሱም ከእሳቱ ለመግባት ተዘጋጁ። የለበሱትን ልብሳቸውን አወለቁ፤ ከዚያ፡ እርስ በርሳቸው (አንዱ ለሌላው) እንዲህ ሲሉ ምዕዳን አስሰሙ፤ "ዛሬ እግዚአብሔር (የሚሠራውን) ሠርቶ ከዚህ ዓለም ያሳርፈናል።"

---

79. በቅዳሴ ውስጥ እንደሚደረገው።
80. ከጸሎት መጽሐፋቸው የተጠቀሰ ሊሆን ይችላል።
81. ኢሳ 56: 1።
82. መዝ 105/106: 3።

ከዚያ፥ ንጉሡ መነኮሴውን[83] (52ᴬ) "እንተ (ከእሳቱ) አትግባ፤ ምክንያቱም ሃይማኖትህ የታወቀ ነው። እነሱ ግን ይግቡ" አለው። ሆኖም ንጉሡ ወታደሮቹ ጣር እንዲያበዙባቸው እንጂ ከእሳቱ ውስጥ ጨርሰው እንዲጨምሯቸው አላዘዛቸውም። ጣራቸው እንደዚህ ነበረ፤ ጨርሰው ለመግባት ሲፈልጉ በማነቆው (ይዘው) እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም። ለመውጣት ሲፈልጉ ደግሞ ከእሳቱ አቅርበው ያስጨንቋቸዋል። አንዳንዱ እግሮቹ ዓሣ በፍም (እንደሚጠበስ) ይጠበሳሉ፤ አንዳንዱን አንዱን በሌላው ላይ እየጣሉ እንደ ግንድ ይለበልቡታል። ከዚህ ጣር ይልቅ መሞትን ይመርጡ ነበረ። ግን ወታደሮቹ ይከለክሏቸዋል። ለመውጣት ሲሞክሩ፥ "ለመውጣት ከፈለጋችሁ ለንጉሡ ስገዱ፤ መምህራችሁንም ስደቡ" ይሏቸዋል።

በእንደዚህ ያለ አድራጎት ብዙ አሠቃይዋቸው። እነሱ ግን "ልጄ ሆይ፥ ለእግዚአብሔር ለመገዛት ከሄድክ ራስክን ለሥቃይ አዘጋጅ፤ ስትቸገር አታወላውል"[84] ያለውን የነቢዩን ቃልና፥ "በትዕግሥታችሁ ነፍሳችሁን ታተርፋላችሁ"[85] ያለውን የጌታን ቃል፥ በሐዋርያው ቃል ውስጥም፥ "ትዕግሥት ፍጹም ሥራ አለበት"[86] ያለውን እያስታወሱ ይሸንን ሁሉ ታገሡ።

ቅዱስ አባታችንን (53ᵁ) አባ በርተሎሜዎስን ብዙ አሠቃዩት። ከፍም ላይ ወረወሩት፤ የራሱ ጠጉር ነደደ፤ ሥጋው ተቃጠለ፤ ጭንቅላቱ አዠ። ሽምግልናው አላስፈራቸውም፤ ግርማው አላስደነገጣቸውም፤ ሽበቱ፥ የዓይኖቹ ከባድነት፥ ቃለ መለኮት የሚናገሩ ደስተኛ ከንፈሮቹ፥ የአፉ ቃል እንቅስቃሴ፥ የእጆቹ ቅድስት በረከት አላሳዘኗቸውም። እሱ ግን በራስ ሺበት ጊዜ የጎልማሳነት ጸጋ እግኝቶ ይሸንን ሁሉ ታገሰ።[87] ጠፊ ውዳሴ ከንቱ (ለመናገር) አላጓጓውም። "በመንበሩ ለሚቀመጥ አምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው"[88] እያለ የዘንባባ ዝንጣፊ ከያዙት ጋራ[89] ስብሐት ለማቅረብ ሲል ራሱን ለእግዚአብሔር ቊርባን ለማድረግ ፈለገ። ወታደሮቹም በበኩላቸው ቅዱሳኑን ማሠቃየታቸውን ገብ አላደረጉም። የእሳቱ ነበልባል ወደ ላይ ሲወጣ ወታደሮቹን ያቃጥላቸዋል። ስለዚህ ቅዱሳኑን ትተዋቸው ሊሄዱ ሲፈልጉ፥ የበላዮቻቸው፥ "እናንተ ከኋላቸው ቆማችሁ እዚያው እንዲያጥሩ እንጂ እንዳይገቡም እንዳይወጡም ማነቋቸውን ይዛችሁ አትፍቀዱላቸው" እያሉ ይከለክሏቸዋል።

(53ᴬ) የእሳቱ ነበልባል ወደ ላይ ከፍ ሲል ቅዱሳኑን እንደ ደመና ሆኖ ጥላውን በነሱ ላይ በመጣል ጋረዳቸው፤ እንደ ካፊያም ሆነላቸው። በዚህ ጊዜ ከጌታ ዘንድ የርጥበት መድኃኒት በላያቸው ላይ ስለሆነላቸው እርስ በርሳቸው ተያዩ። (የሆነውን) በዚያን ጊዜ አልተናገሩትም፤ ከእሳቱ ከወጡ

---

83. አባ ኖብን።
84. ሲራ 2፡ 2።
85. ሉቃ 21፡ 19።
86. ያዕ 1፡ 4።
87. አባ በርተሎሜዎስ የአባ እስጢፋኖስ ተከታይ የሆኑት በእርጅና ዘመናቸው ነው፤ ታሪካቸው አባ እስጢፋኖስ ገድል ውስጥም ተነግሯል።
88. ራእ 7፡ 10።
89. ራእ 7፡ 9-10።

በኋላ ግን ከጌታ ዘንድ የምሕረት መድኃኒት በላያቸው ላይ እንደሆነ እርስ በርሳቸው ተጫውተውታል። ለቮቱ ልጆች የሆነውን የላይኛውን ኪዳን አስታወሱ።[90] ስለዚህ እግዚአብሔርን አመሰገኑት። በእርግጥ ምሕረቱን ከባሮቹ የማያርቅ እግዚአብሔር ስሙ ይመስገን።

"ገድለ" እማሆይ መክብዩ

ድብረ ሰላም ከሚባል ቦታ የምትኖር መክብዩ የሚሏት አንዲት መበለት ነበረች። እንግዳ ተቀባይ፥ በምግባሯም ጥሩ የሆነች ነበረች። ወንድና ሴት ልጆች አሏት። ይኸንን ዓለም ለመተው ስትወስን ንብረቷን ከሶስት ከፈለችና፥ ዘመዶቿን ከንብረቷ፥ "ሁለቱ እጅ ለልጆቼ ይሁን፤ አንዱ እጅ የኔ ነው፤ ዕዳ በመጣብኝ በልጆቼና በዘመዶቼ ላይ (54[ህ]) ሐዘን እንዳይመጣ ከሱ እሰጣለሁ" አለቻቸው። እሷ ግድ እንደሚመጣባት[91] እያወቀች ቅዱሳኑን ከቤቷ ታስገባቸው፥ አብራቸውም ለመሆን ትፈልግ ነበረ። (ንብረቷን) እንደዚህ (የከፋፈለችው) ስለዚህ ነው። በዚህ ሥራ ዘመዶቿ ብፅዕት አደረጓት፥ አደነቋትም። "ጥሩ ነው፤ እንዳልሽው ይሁን" አሏት።

ከዚያ በኋላ፥ ቅዱሳኑን፥ "መነኮሲት እንድሆን እፈልጋለሁ" አለቻቸው። "ታገሺ፤ የምንኮስና ሥራ አስጨናቂና ጽኑ ነው፤ ብዙ ሥቃዮችና ስደት አለበት፤ እስከ መሞትም ያደርሳል" አሏት። "እግዚአብሔር ዐቅሙን ይሰጠኛል" አለቻቸው። ሁለቴም፥ ሶስቴም ነገሯት፤ እሷም ያንኑ መለሰች። ወደነሱ ለሚመጣ ሁሉ ሥርዓታቸው እንደዚህ ነው። ከዚያ፥ መንኮሳ በንጽሕ ሥርዓት ኖረች።

ከዚያ በኋላ፥ እንደነገሯት ደረሰባት። ቅዱሳኑን እና እሷንም ከቤቷ ያዟቸው። እሷም እንዳለችው አደረገች፤ (ቅጣቷን) ለተላኩት ከገንዘቧ ሰጠች፤ ልጆቿን አላሳዘኗትም። ወስደው ለብቻዋ አቆሟት።

(54[ሀ]) ንጉሡ፥ "በእነሱ ዘንድ ምን አየሽ? ለምን ከነሱ ጋራ ተባበርሽ?" ብሎ ላከባት። "የእግዚአብሔርን መንገድ ስላገኘሁ ከነሱ ጋራ ተባበርኩ" አለችው። ደግሞ (እንድትመለስ) በብዙ ሸነገላት፤ እምቢ አለቻቸው። ከቅዱሳኑ ጋራ ወደ እሳቱ ወሰዷትና እዚያ ብዙ አሰቃዩዋት። የንጉሡ ወታደሮች በብዙው ሰደቧት። በትር እያነሡ ደበደቧት። እጇን ይዘው ወዲያና ወዲህ እየጎተቱ ከእሳቱ አጠገብ ጣሏት። ትንታጉን እያነሡ እላይዋ ላይ በመበተን አቃጠሏት። ደግሞ ፍም አንሥተው እልብሷ ላይ ጣሉት።

ወታደሮቹ የመራሮች ውጤት ስለሆኑ እሷን ማሠቃየቱን ገብ አላደረጉም። (ሲወለዱ) የወጡበትን በር ሳያፍሩ እግሮቿን (በርግደው) ይዘው እሥጋዋ ላይ የእሳት ትንታግ እያከታተሉ ጨመሩበት። ሥጋዋ እስኪነፍር ድረስ እየተፈራረቁ እንደዚህ አደረጉ። ቅዱሳኑ ያበረቷት ነበረ። እሷም በዚያ የቃጠሉ በሽታ (ሰማዕትነቷን) እስክትፈጽም ይኸንን ሁሉንም ታገሠች።

የሰንበት ዕለት ምሕረት

ሲመሽ ቅዱሳኑን እንዲያስሯቸው አዘዘ። እንዳለው (አድርገው) እስር ቤት አስገቧቸውና እንደበፊቱ አሰሯቸው። በማግስቱ ሰንበት (ቅዳሜ) ስለነበረ ከቮ

90. ለሰለስቱ ደቂቅ፥ ዳንኤል ምዕራፍ 3።

91. ሉቃ 17፡ 1።

ሰዓት በኋላ ውሐ እንዲሰጧቸው አዘዘ። ለአባታችን ለአባ በርተሎሜዎስ ደግሞ÷ (55ᵘ) "እግዚአብሔር ይማርህ፤ አሁንም ምግብህን ውሰድ፤ ይኸንንም ጠጣ" ብሎ እንጀራ÷ ውሐ÷ ማር ላከለት። ቅዱሱ÷ "እኔስ እንግዲህ ወዲህ የዚህን ዓለም ምግብ አልፈልገውም፤ ለፈለግኸው ስጠው" አለ። ለንጉሡ ነገሩት። ከዚህ በኋላ÷ ከአስር ቤት እንዲያወጡት አዝዞ ወደ ሌላ ቦታ ወሰዱት። በዚያን ጊዜ በማግስቱ ቀኑ እሑድ ነበረ። እዚያ ሰማዕትነቱን በጅራፍ ጎዚራን ማለት ሠኔ÷ በማዕዝ በሐምሌ መባቻ÷ በመልካም ገድልና በብዙ ጻማ[92] ፈጸመ። ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራ ለዘላለም ትሁን፤ አሜን።

ያቺም በእሳት ያቃጠሏት መነኮሲት በዚያው የቃጠሎ በሽታ ሰማዕትነቷን በታሙዝ ፭÷ በግዕዝ በሐምሌ ፭፬ ፈጸመች። ጸሎቷና በረከቷ ከኛ ጋራ ይሁን፤ አሜን÷ አሜን።

የተረፉት ቅዱሳን በብዙ ጣር÷ በረኃብ÷ በውሐ ጥም÷ በብርድ÷ በመራቆት÷ በአስር ቤት ቆዩ።

ወደ ደብረ ቅፍርያ ግዞት--በአስጨናቂ ጉዞ

ከዚያ÷ በ ... ቀን በዚያ ወር በግዕዝ በነሐሴ መባቻ ከአስር ቤት አወጧቸው፤ እግር ብረቱን ከእግሮቻቸው ላይ አወለቁላቸው። እዚያው ታስረው እንዲኖሩ ቅፍርያ ወደምትባል ደብር እንዲወሰዳቸው ለትግራይ አገረ ገዢ ሰጧቸው። (55ᴬ) ወታደሮቹ ቅዱሳኑን (ወደ ትግራይ እንዲወስዷቸው) በዚያች ሌሊት ተረከበዋቸው በየበራቸው ጥለዋቸው ነበረ። አንዱን ወንድም ከበቅሎና ከአህያ ጋጥ አጭቃ ላይ ጥለውት ነበረ። በዝናምና በብርድ ጎይል ሲያጣጥር እድሮ ሲነጋ ሰማዕትነቱን ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

አንድ ወንድም ደግሞ ብርድ በዝቶበት የእሳት ጪስ ሲያይ ሊሞቅ ሄደ። በዓይነ ቁራኛ የሚጠብቀው ተከታትሎ ከመራት ወረወረውና በሰንሰለት ጎተተው፤ የክንዱ ቆዳ ተገሸልጦ እስከ መዳፉ ደረሰ። ብዙም ሰደበው። እሱ ግን ከብርዱ ብዛት መታገሥ አቅቶት ከጥቂት ጊዜ በኋላ (እንደገና) ወደ እሳቱ ሊሄድ ተነሣ። እንደገና ከመራት ላይ ወርውሮት እንደበፊቱ ጐተተው። አንዳንዶቹን በማነቆ ይስቧቸው ነበረ።

ወታደሮቹ ተነሥተው ጉዞ ቀጠሉ። ወይራር[93] ከምትባል ትልቅ ወንዝ ደረሱ። ሞልታ አገኟት። ሲሻገሩ አንዱን ወንድም አዚያ ወንዝ ውስጥ ወረወሩት። እዚያ ሰማዕትነቱን ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ያንን በፊት የተጐተተውን ወንድም ከወንዙ ዳርቻ አስቀመጡት። የቀሩትን ወንድሞች በድልድይ አሻገሯቸው። ከማዶ ሆነው ሲያዩ (56ᵘ) ያንን ወንድም ግምብ ተደግፎ÷ የሚጠብቀውም መሬት ሲቆፍር አዩዋቸው። ሌሎች (ከኋላ) መጥተው (የተሻገሩትን)÷ "ወንድማችሁ ሞቷል፤ ተነሡ እንሂድ" ብለው አጣደፏቸው። ወንድሞች÷ "እውነት (ሰማዕትነቱን) ፈጸመን? ከአንድ ግምብ ተደግፎ አላየነውምን?" አሉ። ሰማዕትነቱን እዚያ ፈጸመ።

---

92. መማቀቅ።

93. የንጉሡ ታሪክ "ወራሪ" የሚላትና አፄ ናአድን ስለመስደች "አይራራ" የሚል ስም ወጣላት የምትባለዋ ወንዝ ትሆናለች፤ Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, p. 69.

ያቺም ከዋሻዋ ወጥታ ከቅዱሳኑ ጋራ የሆነችውና ከቅዱሳኑ ጋራ የተገረፈችው ምእመንት በዚያው ዕለት በዚያ የግርፊያ በሽታ ሰማዕትነቷን ከቅዱሳኑ ጋራ ፈጸመች። ጸሎታቸውና በረከታቸው ለዘላለም አብራን ትሁን፤ አሜን፥ አሜን፥ አሜን።

የተረፉትን እያስጨነቁ ወሰዷቸው፤ መሄድ ሲያቅታቸው አንዳንዶቹን ይሸከሟቸዋል[94]፤ አንዳንዶቹን ከበቅሎ ላይ ይጭኗቸዋል። እግራቸው በእሾክና በጉቶ ተሸረካከተ። ከዚያ፥ ቅዱሳኑ አገረ ገዢውን፥ "እነዚህ ወታደሮች ለምንድን ነው እንደዚህ የሚያደርጉት? ድኽቹን ያስጨንቋቸዋል" አሉት።

አገረ ገዢው ወታደሮቹን ሰበሰበና፥ "ለምን እንደዚህ ታደርጋላችሁ? ንጉሡ (የተዋቸው) በእጁ ሰይፍና ጦር እያለ መግደሉን እጥቶበት መሰላችሁ? አህል ከሚበሉበት ውሰዷቸው አላለምን? (56ʰ) አሁንም ፩ ቦታ ሰብስቧቸው። የደከመውንም ተሸከሙት። ሲፈልጉ ይሂዱ፥ ሲደክማቸው ደግሞ ይረፉ" አላቸው።

ሰለሰበሰባቸው አግዚአብሔርን አመሰገኑ። (ሲሰበሰቡ) በላያቸው ሰለደረሰባቸው ተጫወቱ። "ይቺ ሥቃይ የፃዎቹን ወታደሮች ሥቃይ ታሰታውሰናለች"[95] አሉ።

በመንገድ ላይ እያሉ ከደብሩ እግር እስኪደርሱ ፬ ወንድሞች ሰማዕትነታቸውን ፈጸሙ። ጸሎታቸውና በረከታቸው ለዘላለም ከኛ ገራ ትሁን፤ አሜን።

የተረፉትን በእሰራት እዚያ እንዲኖሩ ከተራራው ላይ አወጧቸው። ሌሎቹንም ዴሰአ ከምትባለው ገዳማቸው አመጧቸውና (አብረው) አሰሯቸው። ከቦታው ጥበትና ከምግብ እጦት የተነሣ በጣር ኖሩ። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር (ምሕረቱን) ከፍቶላቸው በሀገር ውሰጥ ወዲያ ወዲህ አሉ። ይበሉም ይለብሱም ጀመር። አያሰተማሩ ሌሎችም ተመለዱላቸው። ብዙዎች ሆኑ። እዚያ እሰከ ጊዜው ኖሩ።

እንደገና ወደ ብሔረ ምርጋይ--40፥ 40 ለመገረፍ

ደግሞ አንደገና ቅዱሳኑን ከምድረ ትግራይ አምጥተው ከንጉሥ ፊት አቆሟቸውና፥ "ለንጉሡ ሰገዱ" አሏቸው። "ለአብ፥ (57ᵘ) ለወልድ፥ ለመንፈሰ ቅዱስ በቀር (ለሌላ) አንሰግድም" አሉ።

ከዚያ፥ ንጉሡ ወደ ብሔረ ምርጋይ፥ የፀሐይ፥ የንዳድና የወባ[96] ሀገር ወደምትባል ወደ ዳዓላ እና ወደ አራማሮ እንዲወስዷቸውና እዚያ እንዲገርፏቸው አዘዘ። ወታደሮቹ ትእዛዙን ተቀብለው ቅዱሳኑን ወሰዷቸው። እዚያ ሲደርሱ ፵ ፵ ገረፏቸው። ከዚያ፥ በእሰራት እዚያው እንዲቀመጡ ለዚያ አገር ሹም አስረከቡት። ተረክቦ ፵ውን ዳዓላ ውሰጥ፥ ፵ውን አራማሮ

---

94. ! ወታደሮቹም የሚታዘንላቸው ናቸው።

95. በሮማውያን ዘመን ለጣኦት አንሰግድም በማለታቸው በረዶ በሆነ የኩሬ ውሐ ላይ ተጥለው ሲሞቱ ሬሳቸውን አቃጥለውታል፤ በዓላቸው የሚከበረው መጋቢት 13 ቀን ስለሆነ የገድላቸው ታሪክም ስንክሳሩ ውስጥ ለዚያ ቀን ምንባብ ተዘጋጅቶ ተመዝግቧል፤ ራሱን የቻለ እጭር ገድልም ተጽፎላቸዋል፤ ለምሳሌ EMML 1826, ff. 59b-65a, *Catalogue*, vol. V, p. 275 (no. 7).

96. ማቄይ።

ውስጥ በእስራት እስቀመጣቸው። እዚያ በብዙ ጣር÷ በረኀብ÷ በውሐ ጥም÷ በመራቆት ጥረው እዚያው በወባ በሽታ (ሰማዕትነታቸውን) ፈጸሙ። ጸሎታቸው ለዘላለም ከኛ ጋር ትሁን፤ አሜን÷ አሜን።

አባ ተወልደ መድኅንና የደብረ እምፍራዙ መጋቢ

ያም አባ ተወልደ መድኅን የእለቆች ማኅኪያ በሆነችው በጉንጽ ... ዓመት ከ፲ ወር ያህል በእስራት ቆይቶ ቅዱስ አቡነ እስጢፋኖስ ለኛ መታሰቢያ ይሆነን ዘንድ በቅዱሱ (ጌታ) በብዙው ጻማው በትንሹ እንኳን ማንም ሳይረዳው እዚያ ገድሉን ፈጽሞ ነበረ። እሱም ገድሉን አሟልቶ ከንጉሡና ከመኳንንቱ የሚመጡ ሥቃዮችን አሳልፎ ሰማዕትነቱን ሠኔ ፲ ቀን ፈጸመ።

(57^ሰ) ያም የደብረ እምፍራዝ መጋቢ÷ በንጉሡ ትእዛዝ እዚያ የታሰሩት ወንድሞች እና ሊጠይቃቸው የመጣ ፩ ወንድም (ሰማዕትነታቸውን) እዚያ በጥሩ ገድል በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎታቸው ለዘላለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

የዝራጌን ልጅ ብርሃነ መስቀልና ጉዳሌ

ከተበተኑት ወንድሞች ውስጥ የአባታችንን ዐፅም ሊያፈልሱ ግድም ኬላ ላይ ተይዞ በምድረ እመዳ እስረኛ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሰው ከገብረ ማርያም አጠገብ በአረሚ ቤት ታስሮ የነበረ እንድ ብርሃነ መስቀል (ዓምደ መስቀል?) የሚባል ወንድም ነበረ። እዚያ ቤት በእስራት እንዳለ አረሚው ታመመ። ከዚያ÷ ምራቁን እንዲተፋበት ቅባት አመጡ። ሰው ሲታመምባቸው አሕዛብ ልምዳቸው እንደዚህ ነው። (በሽታው) ጉዳሌ መሆኑን ሲጠረጥሩ ቅባት ያመጡና ሰውን ሁሉ ትልቁንም ትንሹንም በቅባቱ ላይ ምራቅ እንዲተፉበት ይጠይቋቸዋል።[97] ያንን የጠረጠሩትንም (ሰው) እንዲተፋ ይጠይቁታል። እምቢ ካለ ጉዳሌ ይሉታል። በብዙው ይደበድቡታል፤ ያስጨንቁታል። ያንን (58^ሀ) የተፋበትን ቅባት በቅባቱ የሚድን እየመሰሳቸው በሽተኛውን ይቀቡበታል።

እንደዚሁ÷ አረሚው በታመመ ጊዜ ሰዎቹ በጣም ተከዙ። ቅባት እምጥተው ምራቅ ተፉበት። ያንንም ወንድም ቅባቱን አምጥተው÷ "ምራቅህን ትፋበት" አሉት። "ለምን?" አሳቸው። "ለታመመ መድኃኒት እንዲሆን" አሉት። "እኔ እሳደርገውም" አላቸው። "እኛ ሥርዓታችን እንደዚህ አይደለም። ይኸ የአሕዛብ ሥርዓት ነው" አላቸው። ይኸንን ብሎ እምቢ አላቸው። ከዚያ÷ እነዚያ አረሚዎች ተነሡበትና በጥፊ÷ በብትር÷ በዱላ ትልቅ ድብደባ ደበደቡት። ብዙ አስቸገሩት፤ ልብሱንም ገፈፉት። የእግዚአብሔር ኃይል ከሚጠብቀው በቀር እግሮቹ በእግር ብረት ታስረው÷ ማንም የሚረዳው ሰው አልነበረም።

ከዚያ÷ አንዲት መጀመሪያ ትፈታተነው (?) የነበረች ሴት መጣች። ራቁቱን ሆኖ አየችውና ስታውቀው÷ "ይኼ የዝራጌን[98] ልጅ አይደለም እንዴ? ሰውየው የመንግሥት ዘር ነው" አለች። ድምጿን ሳታሰማ ሄዳ ለዚያ

---

97. "ጉዳሌ" ጥንቆላ የሚያናግር ርኩስ መንፈስ ያለበት የቡዳ ዓይነት ነው፤ በአማራውም ባህል በቡዳነት የተጠረጠረ ሰው አንትፍትፍ እንዲል ይጠበቃል።

98. "ዝራጌን" በአንድ በኩል "ዘንዶ" ማለት ሲሆን በሌላ በኩል በቃሉ ድምፅ "ዘርአ ያዕቆብ"ን ይመስላል። ልጁም ዓምደ መስቀል ሊሆን ይችላል።

ሀገር ሹም (58^ሰ) ነገረችው። ከዚያ፥ የዚያ ሀገር ሹም መጣና የዚያን አረሚ ንብረት አወደመው። ያንንም ወንድም ከዚያ የአረማዊ ማስቃየት አስጣለው። በዚያ አረሚ ቤት ብዙ የቅጣት ሥቃዮች፥ በግርፋት፥ በድብደባ፥ በረኀብ፥ በውሐ ጥማት፥ በመራቆት ፮ ዓመት ከ፮ ወር አሳልፎ ስማዕትነቱን ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፈጸመ። የተበታተኑ ሌሎችም እያንዳንዳቸው በአረሚ ቤት ተበትነው ብዙ የቅጣት ሥቃዮች--ግርፋት፥ ድብደባ፥ ረኀብ፥ ውሐ ጥማት፥ መራቆት፥ ብዙ ሐዘን--አሳልፈው በአስራት እንዳሉ ስማዕትነታቸውን ፈጽመዋል። ቍጥራቸው ፲፪ ነበረ።

ለሐርሳ ለዓደል ነጋዴዎች ሳይሸጥ ያመለጠ ወንድም

በዳዓላ ቤት ከታሰሩት አንዱ ወንድሞቹ ሲያልቁ ብቻውን ቀረ። አረሚዎቹ ሐርሳ ለሚባሉ ለዓደል ነጋዴዎች ሊሸጡት ተመካከሩ። ከነሱ አንዱ፥ "ሊሸጡህ በጥሞና ተማከረው የለም እንዴ? አንተስ የሚሆንህን ለምን አታስብም?" አለው። ከዚያ፥ መንገዱን ሳያውቀው የእግዚአብሔር ኀይል እየጠበቀው በሌሊት ወጥቶ (59^ሀ) ቂሶ ወዳሉት ወንድሞቹ ሄደ። እዚያ (ሁሉም) በጌታ ሰላም (ሰማዕትነታቸውን) ፈጽሙ። ጸሎታቸውና በረከታቸው ለዘላለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

አባ ኤርምያስ ዘገዳመ በኴት

ከዓመቶች በኋላ፥ ሰይጣን ተነሥቶ የንጽሕና ሥርዓት የሚጠብቁትን ሊጣላቸው ሄደ። በኴት በምትባል ሀገር በራሱ መካን[99] የሚኖር አንድ መነኮሴ ነበረ። የአቡነ ቅዱስ አባ አስጢፋኖስን ሥርዓት ተምሮ ልጆቹን በንጽሕ ሥርዓት፥ ምእመናኑንም አንደ ሴኖዶሱ (ሲኖዶሱ) ሕግ አዘጋጃቸው። ከዚያ፥ አሳባቂዎች ቀኑበትና ሄደው ለንጉሡ ነገሩበት። ንጉሡ አሱን ከነልጆቹ እንዲያመጡት (ሰው) ላከበት። ከንጉሡ ዘንድ አመጡት። (ሌሎችም) ከሌላ ብሔሮች (59^ሰ) አመጡና (ሁሉንም) በአንድነት ከንጉሡ ፊት አቆሟቸው።

ንጉሡ ያንን መነኮሴ፥ "ለምንድን ነው ክአድባራቱ ሥርዓት የምትለየው?" አለው። ይህ ኤርምያስ የሚሉት ወንድም፥ "እኔ በመጻሕፍቱ ሥርዓት እኖራለሁ እንጂ ሌላ ነገር አላመጣሁም፤ ለሕዝብ ያስተማርኩትም የሴኖዶሱን ሥርዓት ነው" አለ። (ይኸንን) ለንጉሡ ነገሩት። ከዚያ፥ መልእክተኞቹ፥ "በሉ ለንጉሡ ስገዱ" አሏቸው። "እኛ ለእግዚአብሔር በቀር ለሰው አንሰግድም" አሉ። "በሉ ለእግዚአብሔር ስገዱ" አሏቸው። "ጥሩ" አሏቸው።

(ይኸንንም) ለንጉሡ ነገሩት። (ንጉሡ)፥ "ወዶ ነው ለእግዚአብሔር የሚሰግደው፤ በግድ አይደለምን? ለማርያም ስገዱ በላቸው" አለ። (ለማርያም ስገዱ ቢሏቸው፥) "ለልጇ ስንሰግድ እዚያ እናገኛታለን" አሉ።

ይኸንን ለንጉሡ ነገሩት። ጤጠይ በምትባለው ጅራፍ አንዲገርፏቸው በቁጣ አዘዘ። አጋድመው ብዙ ገረፏቸው። ከዚያ፥ ቁጣቸውን ሲያስተነፍሱ፥ "ተዋቸው" አለ፤ ተዋቸው። ደግሞ፥ በአስራት እዚያው እንዲኖሩ ዘንትር ወደምትባል ሀገር እንዲወስዷቸው አዘዘ።

---

99. በራሱ ገዳም።

"የኢትዮጵያን ሃይማኖት ለምን ከሁለት ትከፍላላችሁ?"

ንጉሡ ደግሞ ከጥቂት (ጊዜ) በኋላ (60^{ሀ}) ዐርበት በምትባል ሀገር ወዳሉት ቅዱሳን ሊደልላቸው በማባበልና በቃል ማጣፈጥ እንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "ንጉሡ ሰላም ለናንተ ይሁን፤ እነሆ÷ ስለ ሃይማኖታችሁና ስለ ምግባራችሁ ስምተናል። የኢትዮጵያን ሃይማኖት ለምን ከሁለት ትከፍላላችሁ? አሁንም÷ እኛ ዘንድ የጐደለውን እናንተ እየሞላችሁ÷ እናንተ ዘንድ የጐደለውን እኛ እየሞላን በመጻሕፍት ይወሰን ብሏልና እንግዴህ ከየአላችሁበት ቦታ ተሰብሰቡ።" ስለ ምግባቸውም የሀገሩ ገዢ እንዲሰጣቸው ንጉሡ እንደነገረው (መልእክተኛው) ነገራቸው።

ዘአማኑኤል የሚሉት ፩ዱ ነገረ ፈጃቸው÷ "ስለ ሃይማኖት በመጻሕፍት ይወሰን ያለው መልካም ነው። ስለ ምግብ (ያለውን) ግን አንፈልገውም፤ በድካማችን እንመገባለን" አለ። መልእክተኛው (ሰብስቧቸው) ለሀገረ ገዢው እንዲቈጣጠራቸው አስረከበው።

ከዚያ÷ መልእክተኛው ሌሎቹ ቅዱሳን ወዳሉባት መርዋ ወደምትባል ወደ ሌላ ብሔር ሂዶ እዚያ ቅዱሳኑን ያዟቸው፤ ወስዷቸውም። እነዚያን ቀደም ብለው የያዟቸውን ከታቦታቸውና ከቅዱሳት አቃቸው ጋራ አምጥተው (60^{ለ}) መልእክተኛው እስኪመለስ ድረስ ከዚያው እንዲኖሩ ለቈርቋራ[100] ገዢ ሰጡት። መልእክተኛው ሂዶ የሆነውን ሁሉ ለንጉሡ ነገረው።

የአባ መክሲሞስ ዘደብረ መዓራ ጠላትነት እና የቅፍርያ እስረኞች

የደብረ መዓራ መምህር የተባለ መክሲሞስ የሚባል የስይጣን መልእክተኛ የጽድቅ ተግራሪ መነኮሴ ተነሥቶ ቅዱሳኑን ለመክሰስ ከንጉሡ ዘንድ ሂደና÷ "ጌታዬ ንጉሥ ሆይ÷ ቅፍርያ ከምትባል ተራራ ያስቀመጧቸው መነኮሳት ሠራዊትህን[101] አበላሹ፤ ብዙዎችን ወደ ትምህርታቸው መለሱ። ስለዚህ ጌታዬ ንጉሥ÷ ቀናተኛ ሆኜ ልነግርህ እዚህ መጥቻለሁ" አለ።

ንጉሡ ይሽንን ነገር ሲሰማ እንዲያመጧቸው ከወታደሮቹ ውስጥ መልእክተኞች ከ፪ መነኮሴዎች ጋራ ላከ። የንጉሡ መልእክተኞች ሂደው ከተራራው አወረዷቸውና ወሰዷቸው። ከዚያ÷ ዲስአ ወደምትባለው ገዳማቸውም ሂዱ። ከዚያም ያዟቸውና አምጥተው ሁሉንም በአንድነት ወሰዷቸው። ቍጥራቸው ፪፻ ወንድና ሴት ሆነ።

ከንጉሡ አደባባይ አመጧቸውና ከስቀላው አደባባይ አቆሟቸው። ከዚያ÷ ታላላቆቹን ወደሱ ወደ ውስጥ እንዲያስገቧቸው አዘዘ። ከፊቱ አቆሟቸው። "ለንጉሡ (61^{ሀ}) ስገዱ" አሏቸው። "ለአግዚአብሔር በቀር ለሰው አንሰግድም" አሉ። ከዚያ÷ ንጉሡ÷ "በሉ ለማርያም ስገዱ" አላቸው። ቅዱሳኑ÷ "ማርያምንማ ለልጇ ስንሰግድ እዚያ እናገኛታለን" አሉ።

ከዚያ÷ ንጉሡ በየስማቸው አንዲህ ሲል ጠራቸው፤ "ያዕቆብ÷ ጳውሎስ÷ ማቴዎስ÷ አንዴት ለማርያም አትሰግዱም? አንዴት! አንዴት!"

---

100. ቈርቋራን የአፄ በእደ ማርያም ታሪክ "ቋርቋራ" ይላታል፤ Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, p. 136.

101. "ሕዝብህን" ማለት ነው፤ "ሠራዊት" መበሠረቱ "ሕዝብ" ማለት ስለሆነ÷ "የጦር ሠራዊት" ካልተባለ ሠራዊት ብቻውን ሁል ጊዜ "የጦር ሠራዊት" የሚል ትርጉም አይኖረውም።

ይኸንን ያለው ዕውቀት ያላቸው ቀሲሶች ስለሆኑ ሊደልላቸው ነው። ምክንያቱም ከሱ ባመጣባቸው የቅጣቶቻቸው፥ የድብደባዎቹ፥ የግርፊያዎቹ፥ የእሳቱ ቅጣቶች ጊዜ አውቋቸዋል።

ይኸንን ሲላቸው፥ ከነሱ አንዱ አብረውት ላሉት፥ "ለመግደል ስበብ ፈልጎ ስለሆነ ለማርያም ብንሰግድም አይለቀንም። ምን እናድርግ? ለአምላክ እናት ለማርያም ስግደት ብንሰግድ አያሳዝነንም" አለ።

ይኸንን ከማለቱ እንዲገርፏቸው በቁጣ አዘዘ። ደማቸው እንደ ውሐ እስኪወርድ ጨጠይ በምትባለው የመግረፊያ ጅራፍ ገረፏቸው። ቁጣውን ካስተነፈሰ በኋላ፥ እንዲተውዋቸው ነገራቸው። ከዚያ፥ የቅዱሳኑንና የምእመናቱን ሁሉ ልብሳቸውን እንዲገፍፏቸው አዘዘ። ልብሳቸውን እና (61ᴬ) ገንዘባቸውን ወስደው ለው ሁሉ እንዲያይ ከስቀላው ሰፈር ፪ ከምር ከመሩ።

ጳጳሱ እንዲያወግዟቸው ታዘዙ

ደግሞ ወደ ጳጳሱ እንዲወስዷቸው አዘዘ። ለሱም እንዲህ ሲል ላከበት፤ "እነዚህን መነኮሴዎች (ፈለሰት) ውሰዳቸው። ሥራቸው ሁሉ የአይሁድ ሥራ ነው። ለማርያም አይሰግዱም፤ እኔንም አይታዘዙም። ውስድና ክርስትናቸውን አውግዝ፤ ከህነታቸውንና ምንኮስናቸውን ሻርና ሰዎች በእንጀራም፥ በውሐም፥ በእሳት (መጫርም)፥ ለሕይወት በሚያስፈልገው ሁሉ እንዳይቀበሏቸው፥ ለሳምታም እንኳን ጨርሶ እንዳይሰጧቸው አድርግ።"

(መልእክተኞቹ) ቅዱሳኑን እያጣደፏቸው ወሰዷቸው። ራቁታቸውን ነበሩ፤ ምግብም አላገኙም። ስንቃቸውን ሁሉ ወስደውባቸው ነበረ። እነሱ ግን፥ "እሁን የሚያለቅሱ ብፁዓን ናቸው፤ ይደሰታሉና። ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና"[102] በሚለው የእግዚአብሔር ቃል ተስፋቸውን በመተማመን ይደሰቱ ነበረ።

በዚህ ሁኔታ (62ᵁ) እያደከሙ ከጳጳሱ ዘንድ አመጧቸው። (ንጉሡ) የላካቸውን ነገሩት። (ጳጳሱ) ከፊቱ አቆማቸው። እነሱም ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ከስላምታ ቃል ጋራ ለጳጳስ በሚገባ ቡራኬ ባረኩት።

እሱም፥ "ይኸ የሚሏችሁ እውነት ነውን?" ሲል ጠየቃቸው። "አይደለም፥ አባ" አሉት። "ታዲያ ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው?" አላቸው።

ቅዱሳኑ፥ "ሃይማኖታችን፥ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ ከሁሉ በላይ በሆነችው በሐዋርያት ጉባኤ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፥ ለኃጢአት ማስተስረያ በምትሆን በአንዲት ቅድስት ጥምቀት፥ በሁለተኛው ትንሣኤ ጊዜ በሙታን ትንሣኤ ማመን ነው። ከቅዱሳን ሐዋርያትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጸጥታ ወደብ ከቀዘፉ ከተከታዮቻቸው በኒቅያ ከተሰበሰቡት ከ፫፻፲፰ የአርቶዶክስ ማኅበር፥ በቊስጥንጥንያ ከተሰበሰቡት ከ፻፶፥ በኤፌሶን ከተሰበሰቡት ከ፪፻ የተለየ ሌላ ትምህርት የለንም። በእካልና በህላዌያት ከሥላሴ አንጨምርም፤ ከሥላሴ አናጐድልም። ይኸንን ከአባታችን ከቅዱስ አስጢፋኖስ (62ᴬ) ተምረናል" አሉት።

---

102. ማቴ 5: 4፥ 6።

ጳጳሱ፡ "ክርስትና፡ ከህነት፡ ምንኮስና የምትወስዱት ከየትኛው (መንበር) ጳጳስ ነው? አላቸው::[103] "ካንተም፡ ከአባትህ ከአባ ሚካኤልም፡[104] ከአባ ገብርኤልም፡[105] ከአባ በርተሎሜዎስም" አሉት::

ጳጳሱ የቅዱሳኑ የሥራቸው ውበት[106] አና የኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው አስደሰተው:: "ሃይማኖታችሁ መልካም ነው፤ ታዲያ ለማርያም ለምን አትሰግዱም?" አላቸው::

"ካሁን በፊት ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ ሲባል እንጂ ለማርያም እሰግዳለሁ ሲባል አላገኘንም" አሉት::[107]

"እኔ የምነግራችሁን ትሰማላችሁን?" አላቸው:: "አዎን፡ አባ፡ አንሰማለን" አሉት:: ከዚያ፡ ጳጳሱ፡ "ዕውቀት የሌሳቸው ናቸው እንጂ ዕውቀት ያላቸው አያቃልሏችሁም፤ ስለዚህ ማርያምን ከሐዲዎች ይሏችኋል:: ለማርያም ባትሰግዱ ስሕተት አይሆንባችሁም፤ ብትሰግዱም ኃጢአት እይሆንባችሁም:: የሞታችሁ ምክንያት ለማርያም ስለ መስገድ እይሁን፤ ለንጉሥ ባለመስገድና የመምህራችሁን ስም ባለመስደብ እንጂ ለማርያም ባለመስገድ አይሁን:: በዚህ ብትሞቱ ጥሩ ይሆንላችሏል:: አሁንም ኑ (63^{v}) አብረን እንስገድ" አላቸው::

ቅዱሳኑ፡ "አንተ አባታችን ነህ፤ በመንፈስ ስትነግረን መልካም ነው፡ አባ ሆይ፤ በፊትም ለማርያም አንሰግድም ያልነው አቃልለን አይደለም:: አኛኮ ሕይወታችን በማርያም ነው:: የትምክሕታችን አክሊል፡ የመድኃኒታችን መጀመሪያ፡ የንጽሕናችን መሠረት የተገኘው ስለ ድኅነታችን ሰው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በወለደች በድንግል ማርያም ነው"[108] አሉት::

ከዚያ፡ ከጳጳሱ ጋራ ከቤተ ክርስቲያን ገቡና ለማርያም አብረው ሰገዱ::

"በቆብም ከኢትዮጵያ ጋራ አይተባበሩም ስለሚሏችሁ የጳኮሚስ ልጆች[109] የሚያደርጉት እንደዚህ አይደለምን? እኔም ይኸንኑ ዓይነት አለኝ"

---

103. ጥያቄው የሚገርም ነው፡ በሀገሪቱ ውስጥ ክህነት የሚሰጥ የሌሳ ቤተ ክርስቲያን ተወዳዳሪ ጳጳስ ያለ ያስመስላል:: እውነትም፡ እንድ ይሥሐቅ ስለሚባሉ ጳጳስ ምንጮቹ የሚናገሩት ጽድስናቸው ከመንበረ ማርቆስ እንዳይደል ነው፡ Getatchew Haile, "A Fragment on the Monastic Fathers of the Ethiopian Church," *Orbis Aethiopicus: Studia in honorem Stanislaus Chojnacki* (ed. Piotr O. Scholz et al), Albstrat (1992), pp. 235-236; Getatchew Haile, "Religious Controversies and the Growth of Ethiopic Literature in the Fourteenth and Fifteenth Centuries," *OrChr*, vol. 65 (1981), p. 105.

104. "ከአባትህ ከአባ ሚካኤል" ያሉት አባ ሚካኤል ከአባ ገብርኤል ቀደም ብለው ስለመጡና ሽማግሌም ስለነበሩ ነው::

105. እዚህ ላይ ስሕተት አለ፤ የሚያነጋግሯቸው ራሳቸው አባ ገብርኤል ናቸው::

106. ሥነ ምግባራቸው::

107. የሚጠቅሱት መጽሐፈ ቅዳሴን ነው:: ምንጮቹ እንደሚሉት ከሆነ፡ እውነትም "እሰግድ ለኪ" ("እሰግድልሻለሁ") የሚለውን ተአምረ ማርያም ውስጥ ያለውን ጸሎት ያመጣው አፄ ዘርእ ያዕቆብ ነው::

108. የጠቀሱት የማክሰኞ ውዳሴ ማርያምን መጀመሪያ ነው::

109. ደቂቀ ጳኮሚስ:: በተጨማሪ አባ ጳኮሚስ የመጀመሪያውን የምንኮስና የማኅበር ሥርዓት ያወጡ ናቸው::

(አላቸው)። ይኸንን ብሎ የራሱን አክሲል አሳያቸው። ቆብም ለያንዳንዳቸው ሰጣቸው፤ ምግብም ሰጣቸው።

የቄርቋራ እስረኞችም ወደ ጳጳሱ ተወሰዱ

ያ ቅዱሳኑን ከታቦታቸውና ከቅዱሳት አቃዎቻቸው ጋራ ከዐርበት አውጥቶ ከምድረ ቄርቋራ ያቆያቸው መልእክተኛ መጣና ከቄርቋራ አውጥቶ ከንጉሡ አደባባይ አመጣቸው። (መምጣታቸውን) ለንጉሡ ነገሩት። ያንን ቀን (አደባባይ) ዋሉ። ሲመሽ መልእክተኛ መጣና፥ "(ከማህሳችሁ) ካህናቱን፥ ዲያቆናቱን፥ ታቦቶቹን አምጡ" አለ። "አንሰጥህም" አሉት። ታቦታቸውንና ቅዱሳት አቃቸውን ነጥቋቸው ሄደ። (63[ለ]) መልክተኛው ከጥቂት ጊዜ በኋላ መጣና፥ "ንጉሡ እንግዴህስ ለኔ መስገድ ይቅር፤ ግን ለአምላክ አናት ለማርያም ስገዱ ብሏል" አላቸው።

ነገረ ፈጅ የሆነው አንድ ወንድም ለላካቸው፥ "ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ብለህ አመጣኸን፤ እሁን ሌሊት ሆኗል። መጽሐፉ የዕረፍት ጊዜና የሥራ ጊዜ፥ ዝም የማለት ጊዜ፥ የመናገር ጊዜ እለ ይላል በሉት" አለ። ከዚያ፥ መልእክተኛው፥ "ያዘዙህን ታደርጋለህ ወይስ አታደርግም?" አለው። "በቀና ካልሆነ አናደርግም" አለው። ይኸንን ሲሰው በጥፊ መታው። አንዱ ወንድም፥ "አሁን የምታስፈራሩን ምንድን ነው? አገዛዛችንን የሚያስተካክል ይመጣ የለምን?" አለ። አሱንም በጥፊ መታው።

ከዚያ፥ መልእክተኛው አብረውት ላሉት (ሎሌዎች)፥ "ልብሶቻቸውን ግፈፏቸው" አለ። አንዱ ወንድም፥ "ልብሶቼን አርስ በርሳቸው ተካፈሉ[110] የሚል ተጽፏል" አለ። አሱንም በጥፊ መታው። የሁሉንም ልብሶቻቸውንና ገንዘባቸውን ሁሉ ወሰዱና አንድ ክምር እደረጉት። ከዚያ፥ ንጉሡ እንደፈተኛቸ ወንድሞቻቸው ወደ ጳጳሱ እንዲወስዷቸው እዘዘ። ቁጥራቸው ፱ ነው። ከጳጳሱ ዘንድ (64[ሀ]) አደረሷቸው። ጳጳሱ ለወንድሞቻቸው (እንዳለው) አሳቸው። እንዳሳቸው አድርገው ከወንድሞቻቸው ጋራ ተደባለቁ። ቁጥራቸው ፫፱ ሆኑ።

የጳጳሱ መፍትሔ

ጳጳሱ፥ "ልጆቼ፥ ሃይማኖታችሁ እንደዚህ ከሆነ ከደብሮቻችሁ ቢያስወጧችሁ አትተክዙ፤ በኔ ደብሮች በፀም በ፤ም አየሆናችሁ አንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ።[111] ንጉሡም ክፉ ነገር አያደርስባችሁም፤ የሚጣሏችሁና ሥርዓታችሁን የሚቃወሚት መነኮሳቱ ናቸው። አሁንም፥ ጌታችን ራሳቸውን የሚያደኸዩ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የነሱ ናትና፤ ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና። ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው። መንግሥተ ሰማያት የነሱ ናትና። ሲሰድቧችሁና ሲያሳድዷችሁ፥ ሲያንጓጥጧችሁ፥ ክፉ ስም ሲያወጡላችሁ በዚያን ጊዜ ተደሰቱ፤ ደስ ይበላችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ብዙ ነውና[112] ያለው ስለ እናንተ አይደለምን። አሁንም ጨክኑ፤ አትጠራጠሩ" አላቸው።

---

110. ዮሐ. 19: 24።

111. ጳጳስም የራሱ የሆኑ፥ እሱ የሚያዝባቸው ደብሮች ነበሩት። ደብሮች ብዙ ርስት ስለነበራቸው መተዳደሪያም ነበሩ።

112. ማቴ 5: 3፥6፥10-12።

ጳጳሱ እንዲህ አያላቸው ምዕዳን አስሰማቸው። (64ᵃ) የንጉሡ መልእክተኞች (ጳጳሱ) ያለውን ሁሉ ይሰሙ ነበረ። ደግሞ ጳጳሱ፥ "ኑ ከኔ ጋራ ቅዳሴ ግቡ" አላቸው። መልእክተኞቹ "ወደ ምሥዋዕስ አናስገባቸውም" አሉ። ጳጳሱ መልእክተኞቹን፥ "ለምንድን ነው የማይገቡት?" አላቸው። "ምክንያቱም እነሱ ከኛ አጅ አይቁርቡም፤ ለኛም እያቁርቡንም" አሉት።

ጳጳሱ ቅዱሳኑን፥ "የሚሏችሁ እውነት ነውን?" አላቸው። "አዎን፥ አባ" አሉት። "በምን ምክንያት?" አለ።

"ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሰዎች ስለ ባዕድ ማምለክም ሆነ መከበር ስለሚገባቸው ሰንበቶችና በዓላት አከባበር፥ በውሽት ስለ መማል፥ ስለ መስረቅ፥ ስለ ዝሙት፥ ነፍስ ስለ መግደል፥ ይኸንን ስለሚመስለው ሁሉ ራሳቸውን በአባቶቻችን በሐዋርያት ሥርዓት አይጠብቁም። ስለዚህ አናቁርባቸውም" አሉት።

"እውነታችሁን ነው፤ ኢትዮጵያውያን ሁሉም ከዚህ ንጹሐች አይደሉም" አለ።

የንጉሡ መልእክተኞች ይኸንን ሲሰሙ ቅዱሳኑን ከቤተ ክርስቲያን አስወጧቸው። ጳጳሱ ሊያስጥሳቸው አቅም እንደሌለው ሲያይ አብሯቸው ወጣ። እነዚያ መልእክተኞች በኃይል ከቤተ ክርስቲያን አስወጧቸው። (65ᵘ) የነጋሚውን ልብ ያውቁታልና። መልእክተኞቹ ተነሥተው ሄዱና ጳጳሱን እየከሰሱ የሆነውን ለንጉሡ ነገሩት።

ጳጳሱም እንዲህ ሲል ለንጉሡ ላከበት፤ "እነዚህን ቅዱሳን የማወግዝበት ምክንያት አላገኘሁባቸውም። ሃይማኖታቸው የቀናች፥ ሥራቸውም መልካም ነው። ማርያምንም ያምናሉ፤ ይሰግዱላታልም።"

ወሳኝ ጉባኤ ታዘዘ

ንጉሡ ግን የጳጳሱን መልእክት በጥሩ (መንፈስ) አልተቀበለም። የአላባቂዎቹን ቃል አመነ። ንጉሡ በጳጳሱ ላይ ተቆጣ። ከሱ ጋራ በጠባይ የሚተባበሩትን ሉሌዎቹን ጠራና እንዲህ ሲል ላከበት፤ "አመኑ፥ ሰገዱ የምትለው ምንድን ነው? የሰገዱት በትርና ግርፊያ በመፍራት፥ ረኀብን፥ ውሐ ጥምን፥ ብርድን፥ መራቆትን በመፍራት አይደለምን? በአንተ በኩል እንዲያምኑ የምታስተምር ከሆነ ለደስከ የሚሰግዱ የወጊ መተተኞች፥ ለባሕር የሚያርዱ ማያ፥ ለማሪት የሚሰግዱ ጉራጌዎች አሉልህ።[113] እንተ ለራስህ ግብጻዊ ነህ፤ እንዴት ነው ኢትዮጵያን የምትሰድባት? የግብጾችን ክሕደት የማናውቅ ነንን? ቅዳሜን ማክበርን እኛ አስተማርንህ እንጂ አንተ አታውቅም።"[114]

---

113. እባ ገብርኤል መካነ ጽጽስናቸውን በራራ ላይ ያደረጉ የደቡብ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ነበሩ፤ ይኸም ከተሳምረ ማርያም ውስጥ ተመዝግቧል።

114. እውነትም ቅዳሜን እንደ እሑድ ማክበር የተጀመረው በእዬ ዘርእ ያዕቆብ ጊዜ ነው። ደቂቀ ኤዎስጣቴዎስ/ማዕቀበ እግዚእ ቅዳሜ ታልተክበረ ብለው የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን የሚያቋቁሙ ስለሆነ ንጉሡ ከጳጳሳቱ ጋራ ተመካክሮ ቅዳሜ እንድትከበር እድርጎ ታረቃቸው፤ Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 261/51, Louvain 1965, pp. 153-156; Getatchew Haile, "The Letter of Archbishops Mika'el and Gäbrə'el Concerning the Observance of Saturday," *JSS*, vol. 26/1 (1981), pp. 73-78.

(65ʰ) ከሳካቸው መልእክተኞች መካከል (የነበሩ)፥ ፩ዱ ከካህናተ ደብተራ ወገን የሆነው አበስኪሮን የሚሉት ክፉ ሰው፥ የባለ ተጐዛጉዛ[115] አለቃ አብርሃም፥ ፩ዱ አስጢፋኖስ የሚሉት የሽመይ መምህር፥ ፩ዱ ቢፋሞን የሚሉት ቀይስ ሐፀይ[116] ናቸው።[117] ቍጥራቸው ፴ ነበረ። ከጻጻሱ ዘንድ መጥተው ንጉሡ የሳካቸውን ነገሩት። ብራራ በምትባለው በጳጳሱ መካን ጉባኤ አደረጉ። ቅዱሳኑን አዚያ በማነቆ እንደታሰሩ አቆሚቸው፤ ጳጳሱም አዚያ አብሯቸው ነበረ።

ከመልእክተኞቹ ፩ዱ አስጢፋኖስ የሚሉት (መጀመሪያ) ተናገረ፤ ለሕዝቡ እንዲህ አላቸው፤ "ስሙ፥ የነዚህ መነኮሳት መምህር የሰማይን ኗ በሮች ከፍቶ እሳት እውርዶ ለልጆቹ ያሳያቸውና መንፈስ ቅዱስ ይኸ ነው ይላቸዋል። እኛን መነኮሴዎቹን ይሰድበናል። ኪዳን አፍራሾች ይለናል።"

በፊት ንጉሡ ለማርያም ስለ መስገድ ከጠየቃቸው ፲ ቄሶች ውስጥ አንዱ ማቴዎስ የሚባለው ይኸንን ከባለሥልጣኖቹ ቃል ሲሰማ፥ የባሕር ሞገዶች የማይችሏት፥ (66ʰ) መሠረቷ ከእምነት ጥልቀት በሆነ ጽኑ ቃል ለመልእክተኛው ሲመልስ፥ "የትምክሕታችን አክሊል የሆነች የማርያም ፍቅርና የዚህን የነፍስ አባት ጳጳስ የምዕዳን ቃሉን እስታውሺ ነው እንጂ እንኳን በትርን፥ መራቆትን፥ ረኀብን፥ ውሐ ጥምን በመፍራት ላደርገው ቀርቶ ጦር አንጀቴን ቢዘረግፈው እንኳን አላደርገውም ነበረ" አለ።

(የንጉሡ) መልእክተኛ ስሙ ሠምረ ሚካኤል ነው፤ ሁለተኛው አበስኪሮን ይባላል።

ከዚያ፥ ይኸ ቁጣ የለበሰ አበስኪሮን ብድግ አለ። (ይህ ሰው) ቀደም ብሎ ፪ ወንድሞችን ከጓደኞቻቸው ነጥሎ ወደ ምድረ በዳ ወስዶ እዚያ እንዲደበድቧቸው አዝዞ፥ ከበሽታ እስኪወድቁና በዚያ በሽታ (ስማዕትነታቸውን) እስኪፈጽሙ ድረስ በዱላ ደብድበዋቸው ነበረ። በዚች ሰዓትም በቁጣ ሰክሮ ጥርሱን አፋጨና፥ "መምህራችሁን ስደቡ፤ አርኩስ ነው በሉት" አላቸው።

ጳውሎስ የሚባለው አንዱ ነገረ ፈጅ ቃሉን ከፍ አድርጎ፥ "ሕዝብ ሆይ፥ ስሙ፤ ለጥሩ ሥራ መጀመሪያው በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ነው፤ መጨረሻው ይኸንን ዓለም መናቅ ነው" አለ።

ይኸንን ሲል ከመልእክተኞቹ አንዱ በቁጣ ብድግ አለና (66ʰ) እንዲህ ሲል ጉሮሮውን አነቀው፤ "(የተጠየከው) መምህርህን አርኩስ ነው ብለህ አንድትሰደብ ነው እንጂ ይኸንን ማን ተናገር አለህ?"

---

115. ሥልጣናቸው ምን እንደሆነ አይታወቅም፤ ግን ከብዙ የግዕዝ ምንጭ ይገኛሉ።

116. የንጉሡ የንስሐ አባት።

117. "ሽመይ" እና "ሲመይ" (ክሌላ ቦታ ደግሞ "ሲማይ"፥ "ሽሜ") የአንድ ቦታ ተለዋዋጭ ስሞች ናቸው፤ የአባ በኪሞስ ሀገረ ስብከት ነበረ፤ Getatchew Haile, "The Monastic Genealogy of the Line of Täklä Haymanot of Shoa," *RSE*, vol. 29 (1982-83), p. 17። "(ሊቀ ደብተራ) ቢፋሞን" እና "(ንቡረ አድ) አስጢፋኖስ" ዘሚካኤልና ገማልያል "እግዚአብሔር መልክ የለውም" ስላሉ በተከሰሱ ጊዜ ጉዳዩን ባየው ሸንጎ ላይ ተገኝተዋል፤ Getatchew Haile, "The Homily of Zär'a Ya'əqob in Honour of St. John the Evangelist," *OrChr*, vol. 67 (1983), pp. 150-151.

ከዚያ፥ አንዱ ወንድም፥ "መምህራችን ጻድቅና ሕግ ፈጻሚ ነው እንጂ እርኩስ አይደለም" አለ። እሱንም አነቀው። ቅዱሳኑ ሁሉም፥ "አቡነ እስጢፋኖስ ቅዱስ ነው፤ ቅዱስ ነው፤ ቅዱስ ነው" አሉ።

ሊደበድቧቸው በቁጣ ተነሡባቸው። ቅዱሳኑ፥ "ክርስቶስ፥ ክርስቶስ፥ ክርስቶስ እርዳን" እያሉ ጮኹ። ይሽንን ብለው ከመሬት ላይ ወደቁ። እላያቸው ላይ ወጡባቸውና እንደ ሀውድማ ነዶ ብዙ ድብደባ ደበደቧቸው። ልብሳቸውን፥ ቆባቸውን፥ ጥምጥማቸውን፥ የአንገታቸውን የማተብ ፍሬ፥ የጃቸውን መስቀል፥ ቀበቷቸውን፥ በትራቸውን ሳይቀር ወስዱባቸው። ከአስኬማቸው አራፊ በቀር ምንም አላስተረፉም፤ ከዚያ፥ ጳጳሱን፥ "በል፥ ንጉሡ አንዳዘዘህ አውግዝ" አሉት። እምቢ አለ።

የጳጳሱ ታላቅ ወንድሙ አባ ሚካኤል እዚያ ነበረ። ከ(አባ ገብርኤል) በፊት ጀምሮ ጳጳስ ነበረ። በዚህ ቀን ነገሩን እንዲሰማ ተሸክመው አምጥተውት ነበረ። (67[0]) ነገራቸውን ሲሰማ ጥሩ ሆኖ አገኘው፤ አርቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸውንም ወደደ። ወንድሙን፥ "አብረሃቸው ብትሞት ይሻልሃል" ብሎ መከረው።

ከዚያ፥ ከጳጳሱ ሎሌዎች አንዱ፥ ደብረ ጽዮን የሚባለው፥ (የጳጳሱ ቃል ለማስመሰል) የጳጳሱን እጅ ይዞ ወደ ላይ አነሣና፥ "እነዚህን መነኮሴዎች ከህነታቸውንም፥ ምንኵስናቸውንም፥ አግደናል። በእንጀራም፥ በውሐም አትቀበሏቸው፤ የሚቀበላቸው የተወገዘ ይሁን" አለ።

ጳጳሱ ግን፥ "ደብረ ጽዮን አለ እንጂ እኔ እንደዘህ አላልኩም፤ አላወገዝኩም" አለ። ጳጳሱ አባ ገብርኤል ቅዱሳኑን ይወዳቸዋል፤ ይቀበላቸዋልም። ለመሞት ግን፥ "መንፈስ ይፈልጋል፤ ሥጋ ግን ይደክማል"[118] እንዳለው እንደ ወንጌሉ ቃል ሆኖ አልጨከነም።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ ንጉሡ ጳጳሱን እስከ ዕለተ ሞቱ ተቀየመው። በማንኛው ያለፈቃዱ የክህነት ሥራ ሳይቀር ያስገድደዋል። ሲታመም እንኳን አያሳርፈውም። በዚህ ምክንያት ጳጳሱ ያጥር ነበር፤ እስኪሞት ድረስ እንደአጣረ ኖረ።

እዘራት ወደምትባል ምድር ግዞት

ቅዱሳኑን ወደ ንጉሡ መውሰድ ጀምረው ሳይደርሱ እንዲመለሱ ትእዛዝ ሰጠ። ሲመለሱ ጻሕጋ[119] ከምትባል ሀገር ደረሱ። እዚያ ሰንበትን አክብሩ። (67[1]) በዚያች ሌሊት ሐምሌ ፳፱ ቀን አንዱ ወንድም ስማዕትነቱን ፈጸመ። ያም ከምድረ ምራዋ ያመጡት ገብረ ሚካኤል የሚባለው ወንድም በጌታ ሰላም አረፈ። ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ከዚያ፥ መካን ስዎች ፩ድ ካህን (ስለ ወንድም ገብረ ሚካኤል) በሌሊት ራእይ፥ "በዚች መካን ትልቅ ከብብ ሲወድቅ አየሁ። ይህ ስው በእርግጥ ጻድቅ ነው። ስለዚህ ተገለጠልኝ" አለ።

ቅዱሳኑን ግን ንጉሡ ወዳዘዘበት እዘራት ወደምትባል ምድር ወሰዷቸው። እዚያች ሀገር በጽኑ ገድል፥ በብርድ፥ የሚለብሱትን ሁሉ

118. ማር 14: 38።
119. ጽሕጋ።

ስለገፈፏቸው በመራቄት ፰ ወር ተቀመጡ። ሣር ይለብሱ፥ በእሮጌ ጨርቅ ይታጠቁ ነበረ። ቆባቸው ከልጥና ከዘንባባ ቅጠል ነበረ። ዝናም ሲጥልባቸው የገብስ ብር ጐንጉነው ከራሳቸው ላይ ያስቀምጡታል። እሱ ግን ዝናም አይከላከልላቸውም፤ እንዲያውም የባሰውን ያጨቀያቸዋል። ከዚያ፥ ክፉ በሽታ መጣባቸው። (ሰማዕትነታቸውን) ሲፈጽሙ (68ᵘ) በሣር ይገንዟቸው ነበረ። በእንደዚህ ሁኔታ ጀግቱ (ሰማዕትነታቸውን) በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን፥ አሜን።

በአዲስ ከስ አዘራት ከምትባለው ምድር መልስ

ከዚያ በኋላ፥ ለተረፉት እግዚአብሔር (ምሕረቱን) ከፍቶላቸው በሌሎቹ ብዙዎች ብሔሮችና ግቢዎች ተመላለሱ። በውስጣቸውም ለሚፈጽማት ለነፍሳቸው የሚገባ ነፃነት ያለባትን አስተማሩ። የትምህርታቸው ውበት በብዙዎች ልብ ቦግ አለች። (አዲሶች) ተወልደውላቸው ብዙዎች ሆኑ።

ከዚያ፥ አንድ እንደ በለቅት የሆነ አባብ ከፍ ከፍ አለ። ምላሱን አውለብልቦ መርዙን በሞኞች የልብ ጉድጓድ ደፋው። (ክፉ) ሥራቸውን አጣፈጠላቸው። እንዳስለመዱት ነፍስ የመግደል መንገድ ከፍቶላቸው ከንጉሡ ዘንድ ሄደው እንዲህ ሲሉ ነገሩት፤ "እነዚህ በትእዛዝህ ያስቀመጥካቸው መነኮሴዎች ትምህርታቸውን የሚቀበሉ ብዙዎች ገቡላቸው። በሚፈልጉት ሁሉ የሚቀበሏቸው (68ᵑ) ብዙዎች ሆኑ።"

ንጉሡ (ሲሰማ) እንዲያመጧቸው መልእክተኞች ላከ። መልእክተኞቹ ሄደው እንደበፊቱ ቆቦቻቸውንና ልብሶቻቸውን ወሰዱባቸው፤ ካስኬማቸው ቍራጭ ሌላ ምንም አላስተረፉላቸውም። (ከንጉሡ) አደባባይ አመጧቸው።

ንጉሡ "ለማርያም ስገዱ" አላቸው። "እጃጃሉ ዘንድ ስግደናል" አሉት። "አሁንም፥ አኛም ሠራዊታችንም እንይና እንመናችሁ" አለ። "ካመንክን ነገርንህ" አሉት። የሚገድልበት ሰበብ ፍለጋ ነው አንጂ፥ ለማርያም መስገድ እሱን አላሳሰበውም።

ከካህናተ ደብተራውና ሌሎች አስተዋዮችና ህዋቂዎች፥ "ምክንያት አትስጧቸው፤ ለማርያም ስገዱ" አሉ። ቅዱሳኑ፥ "ለምን ትጠራጠራላችሁ? ማርያምን የማንወዳት ይመስላችኋልን? ብንሰግድም አይለቀንም፤ ባንሰግድም ፀረ ማርያም ብሎን ይገድለናል። አሁንም፥ የምንሰግደው ስለ ማርያም ፍቅር ብለን ነው እንጂ በትእዛዙ አንሰግድም" አሉና በዚያን ጊዜ ለማርያም ሰገዱ።

እስከ ጊዜው ተዋቸው። እንዲሄዱ ግን አልለቀቃቸውም። እዚያው ጥቂት ቀናት አስቀመጣቸው።

(69ᵘ) ያ፥ ፍሬምናጦስ (የሚባለው) የደብረ መገራን መምህር የያዘውና አበስኪሮን ለበሽታ እስኪዳርገው ድረስ ትልቅ ድብደባ የደበደበው ማቴዎስ የሚባል ወንድም፥ ከንጉሡ የመጣበትን ገድል ብዙ ቅጣቶችና በአረሚ ቤት ለብቻ መታሰርን ፈጽሞ፥ የማርፋቱና የድብደባው፥ በአሳት የማለቃያውም ጊዜ (ተካፍሎ)፥ ንጉሡ ለማርያም ስለ መስገድ "እንዴት ለማርያም አትሰግዱም?" ብሎ ሲጠይቃቸውም አብሯቸው ተገኝቶ፥ በመስከረም ፲፭ ቀን (ሰማዕትነቱን) በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ንጉሡ ከሹመቱ ያባረረው ተክለ ኢየሱስ ጠላት ሆነ

እዚያ በነበሩበት ጊዜ ከካህናተ ደብተራ ውስጥ ንጉሡ ከሹመቱ ያባረረው እንድ ተክለ ኢየሱስ የሚባል ተገናኛቸው።[120] የቅዱሳኑን የሥራቸውን ውበት እየና ወደዳቸው፤ የሚፈልጉትን ይሰጣቸው ጀመር።

ከዚያ፥ "እኔም ከናንተ ጋራ መሆን እፈልጋለሁ፤ ግን መሆን ስላለበት ነገር ምዕዳን እንዲያሰሙኝ መጻሕፍ ዐዋቂዎች ከመኖሪያዬ ላኩልኝ" አላቸው። ቅዱሳኑ በፈለገ ቊጥር (አስተማሪዎች) ይልኩለት ጀመር። የፈለገውን ሁሉ ይጠይቃቸዋል፤ እነሱም በሚገባ ይመልሱለታል።

(69ᵃ) እንድ ቀን (ምዕዳን ሊያሰሙት ከመጡት ጋራ) ሲያወራ የመቢታችንን የማርያምን ሥዕል አሳይቶ፥ "ይኸ ሥዕል እንዴት ነው?" አላቸው። "ጥሩ ነው፤ ግን የእጅ ሥራ ነው፤ ብቻ በልብህ ሣላት" አሉት።

"በየቀኑ የሚተጉበት የደብተራዎቹ ማኅሌትስ እንዴት ነው?" አላቸው። "ሕግን በመጠበቅና ሥጋና ነፍስን በማንጻት ከሆነ ስብሐተ ማኅሌት ጥሩ ነው፤ እለዚያ ግን ጨዋታና ጥፋት ነው" አሉት።

ደግሞ፥ "ሐሳዊ መሲሕ ይመጣል ትላላችሁን? ወይስ እሁን እለ ትላላችሁ?" አላቸው። "መጥቷልም፤ ይመጣልም እንላለን፤ ምክንያቱም መጽሐፉ፥ እሁንም ተገልጿል ይላል"[121] አሉት።

"ይኸንንስ ንጉሥ ምን ትሉታላችሁ? ሥራውስ እንዴት ነው?" አላቸው። "ሕግ ከፈጸመ ክርስቲያን እንለዋለን፤ እኛ እንደምናየው ከሆነ ግን አንተም እንደኛ ታየዋለህ" አሉት።

ደግሞ፥ "የጻፈው *መጽሐፈ ብርሃን* እንዴት ነው?"[122] አላቸው። "በውስጡ መጽሐፈ ሐሰት ያለበትን፥ ከልብ ግሣት ያደረገውን ምን ይሏል? መጽሐፍ የሚለው ውሸት ሁሉ ከእውነት አይመጣም ነው"[123] አሉት።

ከዚያ፥ (ለውየው) ሰይጣን ሆነባቸው፤ በልቡ (70ᵇ) አሰቡ፥ "በዚህ (ነገር) ከንጉሡ ላይ ብከሳቸው ከሹመቴ ይመልሱኛል፤ ወደ ሀገሬም ይሰዱኛል" አለ። ቅዱሳኑን ሸኛቸው። ከዚያ፥ በልቡ አሰቡ፥ "(ግን) እነዚህን ቅዱሳን በዚህ ክስ ያስገደልኳቸው እንደሁ ወዮልኝ፤ ከተውኳቸው ደግሞ የንጉሡን ፊት እንዴት አገኛለሁ? ምን ልሁን? ወደ ቤቴ በምን እመለሳለሁ?" አለ።

ይኸንን ሲያስብ እንድ ተላላኪ ከንጉሡ ወደ እንድ ባለጉዳይ መጣ። ይኸ (ሰው) ወደሱ ሮጦ፥ "ጉዳይ አለኝ፤ ከንጉሡ ዘንድ አቅርበኝ" አለው፥ "(ጉዳዩ) ምንድን ነው አለው?" ያንኑ ነገር ነገረው። ተላላኪው ወደ ንጉሡ ሄዶ ያለውን ለንጉሡ ነገረው።

---

120. "ተክለ ኢየሱስ" ዘሚካኤልና ገማልያል "አግዚአብሔር መልክ የለውም" ስላሉ በተከሰሱ ጊዜ በሸንጎው ላይ የተገኙት ሰው ሳይሆኑ አይቀሩም፤ Getatchew Haile, "The Homily of Zär'a Ya'əqob in Honour of St. John the Evangelist," *OrChr*, vol. 67 (1983), pp. 150-151.

121. 1 ዮሐ 4: 3።

122. ከላይ እንደጠቀሰኩት፥ (ጎዳግ ቊጥር 114) *መጽሐፈ ብርሃን* ታትሟል፤ Conti Rossini and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 250/47, Louvain 1965, and *CSCO*, vol. 261/51, Louvain 1965.

123. ?።

(ሰውየው) በሠራው ክፋት ደንግጦ ፊቱም ሁለንተናውም ጠቆረ። "የተፈጸመ እንደሆነ በዚህ ነገር ወዮልኝ" አለ።

አሁንም በክርስቶስ ያላችሁ ምእመናን ሆይ፥ ኃጢአተኛ ስለ ክፋቱ ወዮለት፤ "ኃጢአተኛ ራሱን የሚያሳስት ነገር ይናገራል"፤[124] "ለኃጢአተኞች ዕዳቸውን አስከፍላቸው"፤[125] "በመፅ የሚፈጽሙ የሱን መንገድ (70^ሰ) አልሄዱም"፤[126] "የወጥመዳቸው ጫፍና የከንፈራቸው ድካም ይቀብራቸዋል"[127] ያለውንና "በክፉዎች እትቅና፥ ዓመፃ በሚሠሩ አትቅና"፥[128] "ለክፉት አትቅና፥ በተንኮል አትሂድ"[129] የሚሉትን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ልብ እንበል። "በሰፈራችሁበት የተንዠረገገና የተትረፈረፈ ይሰፈርባችኋል"[130] ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል እናስታውስ።

ከዚያ፥ ያ ተላላኪ ወጣና፥ "ያለው ይሆናል ወይ ብሏል፥ ንጉሡ" አለው። "አዎን፥ ይሆናል" አለ። ንጉሡ ደግሞ፥ "እንዴት እንደሚሆን አጣራ" አለው።

እሱም፥ "እሞ፥ ይሆናል፤ ብቻ መልእክተኞች ላክ፤ እኔ ከመጋረጃዬ ውስጥ በድብቅ አስገባና እነዚያን ቅዱሳን ጠርቼ እንደበፊቱ ልማዴ አነጋግራቸዋለሁ። መልእክተኞቹ ንግግሬንና ንግግራቸውን ይሰማሉ" አለ።

እንዳለው ንጉሡ መልእክተኞች ሰጠው። መልእክተኞቹን ይዞ ደም ለማፍሰስ በጥድፊያ ሄደ።[131] (ሰውየው) ጥበብ፥ "የኃጢአተኞች ተስፋ ነፋስ እንደሚነፋው አቧራ ነው"[132] እንደምትለው ተስፋ የቈረጠ ነበረ። ወደ ቅዱሳኑ፥ "ሰላም ለናንተ ይሁን፤ መጻሕፍት ዐዋቂዎችና አስተዋዮች የምፈልገውን ምዕዳን እንዲያሰሙኝ ዛሬ ይምጡ" ብሎ መልእክተኞች ላከ።

(71^ሀ) ቅዱሳኑ አራት ሰው--ኪሮስን፥ ፊቅጦርን፥ ገብረ ማርያምን፥ ቴዎድሮስን--ላኩለት። (ከንጉሡ የተላኩትን) ከመጋረጃው ውስጥ ደብቆ ቅዱሳኑን ከቤቱ አስገባቸው። መጽሐፍ አመጣላቸውና እንዳስለመደው ሁሉንም ይጠይቃቸው ጀመር። (እነሱም) በሚገባ ይመልሱለታል። ደግሞ ስለ ሥዕልም፥ ስለ ደብተራዎቹ ቅኔ፥ ስለ ሐሳዊ መሲሕ፥ ስለ ንጉሡ፥ ስለ *መጽሐፈ ብርሃን*፥ ጠየቃቸው።

እነሱ ተንኮሉንና ለይጣን እንደሆነባቸው አላወቁም። የጠየቃቸውን ሁሉ እንደበፊቱ በሚገባ መለሱለት። ስለ ንጉሡም፥ "ከሕግ ውጪ መሆኑ እውነት ነው። ንጉሥ አይደለም" አሉ።

መልእክተኞቹ ይኸንን ነገር ሲሰሙ ከተደበቁበት በቁጣ ወጡና ይዘው ደበደቧቸው። ወደ ንጉሡ ወሰዷቸው። ጊዜው ሌሊት ቢሆንም ከንጉሡ ዘንድ እደረሷቸው።

ምላስና እፍንጫ የመቁረጥ ቅጣት ተጀመረ

(ንጉሡ)፥ "እንተ ገብረ ሰይጣን፥ እኔን በእርግጥ ሐሳዊ መሲሕ ነው ብለሃልን?" አለው። "እኔ ገብረ ሰይጣን (የሰይጣን ባርያ) አይደለሁም፤ ገብረ ማርያም (የማርያም ባርያ) ነኝ። ያልከው ስለ ጠባይህ ከሆነ፥ አዎ፥ ብያለሁ" አለው።

---

124. መዝ 35: 2/36: 1።
125. መዝ 93/94: 2?
126. መዝ 118/119: 3።
127. መዝ 139: 10/140: 9።
128. መዝ 36/37: 1።
129. 2 ቆሮ 4: 2፤ "በተንኮል አንሂድ"።
130. ሉቃ: 6: 38።
131. መዝ 13: 3።
132. ጥበ ሰሎ 5: 14-15።

ከዚያ፥ (71ᴬ) እንዲደበድቧቸው በቁጣ አዘዘ። በበትርና በዱላ ደበደቧቸው። ከዚያ፥ ምላሳቸውንና አፍንጫቸውን እንዲቈርጡ አዘዘ። ቈረጧቸው፤[133] ብዙ ድብደባም ደበደቧቸው። ፲ቱ እዚያው (ስማዕትነታቸውን) ሠጌ ፳፫ ቀን ፈጸሙ። ያንዱ ስሙ ገብረ ማርያም፥ ሁለተኛው ፊቅጦር፥ ሶስተኛው ኪሮስ ነው። ስቡሕ በሆነው ስለ ስሙ ለሚተጋ አርዳታ በሚሆን በአግዚአብሔር ሰላም (አረፉ። ጸሎታቸውና በረከታቸው) ለዘለዓለም (ከኛ ጋራ ትሁን)፤ አሜን፥ አሜን።

ስለ ደብረ ጽዮን ነገር--እንደገና

ሲነጋ ከሰፈሩ ውጪ ያሉትን ቅዱሳን እንዲያመጧቸው አዘዘ። አያጣደፉ አመጧቸው። የሠሩትን አላወቁም፤ የተገደሉትን በድናቸውን በመሬት ላይ አየጐተቱ አመጧቸው። ንጉሡ አንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "እነዚህን ታውቋቸዋላችሁን?" ቅዱሳኑ ሲያዩዋቸው ደነገጡ። በምድር ላይ እንደ ግንድ ሲስቧቸው ሲያዩ ወደነሱ ቀረቡ፤ ዐወቋቸው። ለመልአክተኛው፥ "አዎን፥ እናውቃቸዋለን፤ ወንድሞቻችን ናቸው" አሉት። ይኸንን ብለው ያካላታቸውን አቧራ ወስደው ተቀቡና፥ (72ᴮ) "ቅድስት ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፥ አሜን፥ አሜን" አሉ።

ከዚያ በኋላ፥ አርስ በርሳቸው ምዕዳን አስሰማሙ። ፩ዱ ወንድም እንዲህ አለ፤ "ጌታችን፥ ሌላ ሰው ያደረገውን ባላደርግላቸው ኖሮ ከአበሳ በዳኑ ነበር። ነገር ግን አይተውኛል፤ እኔንም፥ አባቴንም ጠሉን። ነገር ግን በከንቱ ጠሉኝ ያለው የአሪታቸው ቃል ይደርስ ዘንድ በከንቱ ጠሉኝ[134] ብሏል። እኛም ከአባቶቻችን ከሐዋርያት ሌላ ሥርዓት አምጥተን ቢሆን ኖሮ በኛ ላይ የሚሠሩት አበሳና ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበረ። ነገር ግን አሁን ዐውቀዋል፥ ተረድተዋል፤ ተረድተውም መጽሐፍ እንዳለው ዕውሮች ሆኑ። አሁንም፥ ወንድሞች ሆይ፥ አስተውሉ፤ ታለቅሳላችሁ፥ ሙሾም ታወጣላችሁ። ዓለም ግን ይደሰታል። እናንተ ግን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን ሐዘናችሁ ደስታ ይሆንላችኋል[135] ያለው የጌታ ቃል ይፈጸማል።"

መልአክተኞቹ፥ "ለማርያም አትሰግዱምን?" አሉ። ጳውሎስ የሚሉት ፩ዱ ወንድም፥ "ይኸ የምታላግጡብን ምንድን ነው? የምታደርጉት እንዳላችሁ አድርጉ። አለዚያ ከኛ ለማግኘት የምታስቡትን ማግኘት በማትችሉት ላይ በከንቱ ትደክማላችሁ" አለው። (72ᴬ) መልአክተኞቹ የቅዱሳኑን የቃላቸውን መጨረሻ ሲሰሙ ከንጉሡ እንደታዘዙት አደረጉ፤ በደረሱበት ሁሉ ምልክት እንዲሆንላቸው ምላጭ አምጥተው ፊታቸውን

---

133. አጋጣሚው ሌላ ይሁን እንጅ፥ ይኸ ዓይነት ቅጣት *በተአምረ ማርያም* ውስጥም ተመዝግቧል፤ ኢትዮጵያ በታተመው ውስጥ እንዲህ ይላል፤ "ንጉሡም እፍንጫቸውንም መላሳቸውንም እንዲቈርጧቸው አዘዘ፤ ሌሎች እንዳፈሩ ቈረጧቸው። እነዚህ ከሐዲዎች በዚህም ከፉ ሥራቸውን አልተዉም፤ ስለዚህ ሕዝበ ክርስቲያኑ ተሰብስበው፥ እነዚህን ከሐዲ አይሁዶች እንዴት አፍንጫና መላስ በመቍረጥ ለቀቃችኋቸው? በድንጋይ ሊወግሯቸው ይገባል አሉ። ... ከዚያ፥ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ እነዚህን ከሐዲዎች በድንጋይ እንዲወግሯቸው ንጉሡ አዘዘ፤ የክርስቲያኑ ጉባኤ እንደዚሁ አደረጉ።" *ተአምረ ማርያም። በግዕዝና በአማርኛ*፥ ገጽ 115።

134. ዮሐ 15: 24-25።

135. ዮሐ 16: 20።

ተሰተሉት፤ ንጉሡ (ሰዎች) በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዳይቀበሏቸው ስላዘዘ÷ በዚህ ምክንያት ደግሞ ፊታቸውን ተልትሰው ምልክት ይሁንባቸው ብሎ ነበረ።

እንደዚህ እንዳሉ÷ ስሰ ደብረ ጽዮን ነገር እንዲጠይቋቸው ንጉሡ ሠኔ ፳፬ ቀን÷ ከራሱ ደብተራና ከመነኮሳት ላከባቸው። መጥተው በንጉሡ ቃል÷ "ደብረ ጽዮን (አሁን) አለ ትላላችሁ ወይስ (ገና) ይመጣል ትላላችሁ? ወይስ የለም ትላላችሁ?" (ሲሉ) ጠየቋቸው። ቅዱሳኑ÷ "ጽድቅን ለሚሠሩ አሁንም አለ÷ ይመጣልም" አሏቸው። ደግሞ÷ "(ደብረ ጽዮን ምን እንደሚመስል) ሳትደብቁ (እንድትነግሩን) በአብ÷ በወልድ÷ በመንፈስ ቅዱስ÷ በክርስቶስ ሥጋና ደም ይዘናችኋል" አሏቸው።

ቅዱሳኑ÷ "መጽሐፉ ዓይን ያላየው÷ ጆሮ ያልሰማው÷ በሰው ልብ (73^{B}) ያልታሰበ÷ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው[136] ይላል። ልታውቁት ከፈለጋችሁ የወንጌልን ፈለግ ተከተሉ። ካልሆነ በከንቱ አታድክሙን" አሏቸው።

ደግሞ ከነሱ ውስጥ አስጢፋኖስ የሚባለው የብሔረ ሲማይ ነብርአድ÷ "ደብረ ጽዮን እንዳለ እንድትነግሩኝ በዚህ በምትወዱት አባታችሁ ጸሎት ይማጠኋሰሁ" አለ። ሳቁበትና÷ "የአባታችንን ጸሎት ከእብ÷ ከወልድ÷ ከመንፈስ ቅዱስ ስም የበለጠ እንፈራ ይመስልሃልን? ታምን እንደሆነ አለም÷ ይመጣልም። ጽድቅን ለሚሠሩ ሁል ጊዜ ይሰጣል አንላለን" (አሰው)።

ቀኑን በመጨቅጨቅና ነገር በመፈለግ አዋሏቸው። ከዚያ÷ በማግሥቱ አንደገና ስለ ደብረ ጽዮንም ለንጉሥ ስለ መስገድም ጠየቋቸው። ቅዱሳኑ÷ "ታምኑን እንደሆነ የዛሬውን ቃላችንን ከትናንቱ እንለውጠውም፤ የምታደርጉት እንዳላችሁ አሁኑኑ አድርጉት" ሲሉ መለሱላቸው።

የቋንጃ መዘዛ ቅጣት ተጀመረ፤ የ"ዘ" ክትባትና የጣና ግዙት

በንጉሡ እንደታዘዙት አደረጉባቸው፤ ከቅዱሳኑ ውስጥ ቁጥራቸው ፷ የሆነ ታላላቆቻቸውንና ሽማግሌዎቻቸውን ወስደው ምላሳቸውን ቆረጡት፤ (73^{A}) ቋንጃቸውን መዘዙት። የቀሩትን ወንድሞችና ምአመናት በደረሰበት ሁሉ እንዲታወቁ የቀኝና የግራ ጉንጫቸውን በ"ዘ" ፊደል (ቅርጽ) በረጅሙ ተለተሉት።[137]

ከዚያ÷ ወደ ምድረ ጉዛም[138] እንዲወስዷቸውና እዚያ አፍንጫቸውን እንዲቈርጧቸው አዘዘ። በምዕራብ በኩል ወዳሰችው ሰፍ[139] ወደምትባል ትልቅ ባሕር[140] ወስደው ቈራጽ ከምትባል ቀበሌ አጠገብ ከሆነችው "ሐይት መንዘ" ከምትባል ደሴት እንዲወስዷቸው አዘዘ።

---

136. *ትምህርተ ኅቡኣት*፤ Ernst Hammerschmidt, *Äthiopische Liturgische Texte der Bodleian Library in Oxford*, Berlin (1960), p. 70; *መጽሐፈ ቅዳሴ፤ በግዕዝና በአማርኛ÷* አዲስ አበባ 1951 ዓ. ም.÷ ገጽ. 134 (ሠለስቱ ምእት)÷ 177 (ባስልዮስ)÷ 206-7 (ዮሐንስ አፈ ወርቅ)÷ 227 (ቄርሎስ)።

137. "ዘ" የ"ዘርእ ያዕቆብ" ኅጸር ነው፤ መልእክቱ "የዘርእ ያዕቆብ ባሪያ" ለማለት ነው።

138. ኅጃም።

139. ሳፍ÷ አንዳንድ ምንጭ ደግሞ አዛፍ ይላታል።።።

140. የጣና ባሕር።

ለጉላሙ ገዢ እንዲህ ሲል ላከበት፤ "እነዚህን ተቀበልና ያዘዝንህን አድርግ፤ በመንግሥታችን ላይ ያመፁ ናቸው። እንግዲህ መላሳቸውንና አፍንጫቸውን÷ ሽኮናቸውንም ቍረጥ፤ ስማቸውም እለ ቈራጻይ[141] ይሁንና እደሴቱ ይቀመጡ። በህገርህ ሌሎችም እንደነሱ ያሉ ከተገኙ እንደነሱ አድርግባቸው። ካሁን በፊት ባለማወቃቸው ያስጠጓቸውን (74[ሀ]) ምረናል። ከአሁን በኋላ የተገኙበት ግን ቤቱ ይመዝበር፤ ንብረቱም ይጥፋ፤ ሹመቱም ለሌላ ይሁን። የርስቱ ቀበሌ ጉልትነቱ ይሻርበት፤ የተሻረም ከሆነ ለሌላ ይተላለፍ።"

መልእክተኞቹ ይሽንን ከንጉሡ ታዘው ወጡ። ወደሚሄዱበት መንገድ ጀመሩ። ቅዱሳኑንም አንሥተው ሁሉንም በአንድነት ወሰዷቸው። መላሰ ቈራጣዎቹና ቋንጃ ምዝዞቹ መሄድ ሲያቅታቸው ጊዜ በበቅሎ÷ በአህያ÷ በፈረስ አድርገው እያሮጡ ወሰዷቸው። የተጫኑት ሲነቃነቁ የእንጨት ስንጣሪና ሣር በቁስላቸው እየገባ ባለፉበት መንገድ (ሁሉ) ደም ይፈስ ነበረ። ሌሎችም እንደ ረኀብ፤ ውሐ ጥም÷ መራቆት ያሉ ብዙ ሥቃዮችም ነበሩባቸው። በማድከም በጥድፊያ ወሰዷቸው።

ከዚያ÷ ንጉሡ እንዲህ የሚል በፈረስ የሚጋልብ (መልእክተኛ) እንዲከተላቸው አደረገ፤ "መላሳቸውንና ቋንጃቸውን ያልተቈረጡትን መልሷቸው።"

በመንገድ ሳይ ሳሉ ደረሰባቸውና እንዳዘዘው መለሷቸው። (ሲመለሱ) አፍንጫቸውን እንዲቆርጧቸው አዘዘ፤ እንዳዘዘው (74[ለ]) ቈረጧቸው። በመጀመሪያው ቀን ግምባራቸውን ተለተሉት፤ በነጋታው ደግሞ የቀኝና የግራ ጉንጫቸውን በረጅሙ ተለተሉት። በዚያች ዕለት÷ በዚሁ ወር በሰኺ ቀን÷ አፍንጫቸውን ጐመዱት።

ከዚያ÷ በዚሁ ወር በሰኺ ቀን÷ ከፊተኞቹ ጋራ አንድነት ንጉሡ ወዳዘዘበት ወሰዷቸው። በፊት የወሰዷቸውን÷ ዘንትር በምትባለው በወለቃ ህገር ያሉትንም ሁሉንም÷ በአንድነት ወደ ጉዛም ገዢ አመጧቸው። መልእክተኞቹ ንጉሡ ያለውን ለገዢው ነገሩት።

አገረ ገዢው የንጉሡን መልእክት ሰምቶ እንዲህ ሲል ዐዋጅ አስለፈፈ፤ "በብሔሬ ያላችሁ ሹሞች÷ መኳንኖች÷ ባለጸጎች÷[142] ካህናት÷ መነኮሴዎች ሆይ÷ ንጉሡ ያዘዘውን እንድትሰሙና እንድታዩ ከሰዎቻችሁ ጋራ ተሰብሰቡ።"

እንደለፈፈው÷ የሹመቱ ማእከል በሆነችው በጺማ ተሰበሰቡ፤ ብዙ ሕዝብ ሆኑ። ቅዱሳኑን ከዚያ÷ ከሰብሰባቸው ማህል አቆማቸው። ከዚያ÷ መልእክተኛው ከፍ ካለ መድረክ ላይ ወጣና ሕዝቡን በማስፈራራት ቃሉን ከፍ አድርጎ የንጉሡን ትእዛዝ ነገረ።

አገረ ገዢውና ሹማምንቱ ሰምተው÷ "እሺ÷ ጌታችን ንጉሡ ያዘዘንን እናደርጋለን" አሉ። (75[ሀ]) ልብሳቸውን ገፈፏቸው፤ አገረ ገዢው የቅዱሳኑን መላሳቸውንና አፍንጫቸውን እንዲጐመዱ አዘዘ። ንጉሡ ወዳዘዘበት ወሰዷቸውና ከዚያ ከቅዱሳኑ ታሳሳቆቻቸውን አፍንጫቸውን

---

141. "እነ ቈራጥ"፤ "እለ" የወገን--የመነኮሳት ማኅበር፤ የገዢ ቤተ ስብ--ስም መጀመሪያ ነው፤ "እለ ከዲሕ"፤ "እለ ወጲፍ"÷ "እለ ገበዝ"፤ "እለ እዝንጓ"፤ ወዘተ። ንጉሡ ይሽንን ስም የሰጣቸው ሲያሾፍባቸው ነው።

142. ባለጸጎች የጎብረተ ሰቡ እንድ የታወቀ ክፍል ነበሩ።

ጕመዱ። መላሳቸውንና ቋንጃቸውን ግን ከንጉሡ አደባባይ ተቈርጠዋል። ሌሎቹን ወንድሞች መላሳቸውን ቈረጧቸው፤ አፍንጫቸውን ግን ከአደባባዩ (ቈርጠዋቸዋል)። ከዘንተር የነበሩትን ግን መላሳቸውንም አፍንጫቸውንም ቈረጧቸው፤ ዕለቱ ሐምሌ ፳፯ ቀን ነበረ።

በዚያን ጊዜ÷ ከታዘዙበት ለማድረስ ከዚያ አነሷቸው። ደማቸው በደረሱበት ሁሉ ይፈስ ነበረ። በአስጨናቂ ድካምና በብዙ ችግር ሠኔ ፪ ቀን ከባሕሩ ወንዝ ዳርቻ ደረሱ። አለት ድንጋይ ላይ ጣሏቸው። የአለቱ ስም ሙዓለ መህፒል[143] ይባላል። ቀበሌው ቈራጻ ይባላል።[144] ከንጉሡ እንደታዘዙት የሸኮናቸውን ቋንጃ መቍረጥ ጀመሩ። ከነሱ ውስጥ አምነ ማርያም የሚሏት እጆቿ የታመሙ ጕልበቶቿ የተጣበቁ አንዲት መነኮሲት ነበረች። የንጉሥን የቁጣውን ደረጃ ለማሳየት ያለምሕረት በሷ ጀምረው ሁሉንም ፈጸሙ።

(75ለ) ጐን ወደምትባለው ደሴት በታንኳ አሻግረው ከደሴቱ ደጃፍ ላይ ጣሏቸው። ሌሊቱን በሞላ በላያቸው በሚወርደው ዝናም÷ ከባሕሩ ማዕበል በሚመጣ የውሐ ውርጭ÷ በተኙበት ድንጋይ ቅዝቃዜ÷ ከግምባራቸው እና ከጕንጭ መተልተልና ከቋንጃ መቈረጥ በመጣ ቁስል በመቃጥቀጥ ሲያጥሩ አደሩ። ጊዜው ክረምት ስለነበረ በዚህ ዓይነት ሥቃይ ሲያጥሩ አደሩ።

በአንድ በኩል በሙዓለ መህፒል አግጣጫ የባሕር ዳርቻ ነው። በሌላው በኩል÷ ሁሉንም በአንድነት ሰብስበው በማሻገር ፈንታ ከደሴቱ በራፍ ላይ ጥለዋቸው ስለሄዱ÷ የደሴቱ በራፍ ነው። ቍጥራቸው ፻፴፩ ሲሆን ከነሱ ውስጥ ፴፱ኙ መነኮሲቶች ነበሩ። በሙቀት ጊዜ በጠባብ በረታቸው ውስጥ እንደሚታሩ በጎች÷[145] የሰው አግር ከማይደርስበት (በዛፍ) ባላባሊኛ ውስጥ እንደሚጣል እንቁላል ታሳሩ። ለዘለዓለም ሕይወት ነዋሪ ፍሬ እንዲያፈሩና እንዲጥሉ በፈቃዱ ሥቃዩን ለመሸከም ልዑል (ጌታ) ጠርቷቸዋል፤ ሰብስቧቸዋልምና። እዚያ ከፍ ባለ ጣር በብዙ ጻማ÷ ምግብ ከማጣት በሚመጣ አስጨናቂ ድካም ኖሩ። (76ሀ) ቍርበትና ምንጣፍ ከሌለበት አሸዋ መሬት ላይ በተኙበት ከቀኝ ወደ ግራ÷ (ከግራ ወደ ቀኝ) ይንቀሳቀሳሉ እንጂ ከሰውነታቸው መመንመን የተነሣ መቆም መቀመጥ አልቻሉም። እንደ ድርቅ ዘመን መሎክ ጠወለጉ።[146] መልካቸው ተለወጠ፤ ጎይላቸው ደከመ። ሁሉም በራሱ የደረሰበትን ይታገሣል÷ የሥጋን ጭንቅ ይቅር ይላል፤ ቍስላቸውን ለማጠብም ሆነ ለጥማቸው እንዲጠጡም የሚረዳቸው አልነበረም። ብቻ አንዳንድ ከነሱ የበረታ ወደ ባሕሩ ተጕትቶ ይሄድና በአንገቱ ቅል አንጠልጥሎ ለወንድሞቹ ውሐ ያመጣና ቁስላቸውን ያጥብላቸዋል÷ ይጠጡለታልም። ከአስኬማቸው ብጣሽ ጨርቅ በቀር ምንጣፍ÷ ሽፋን÷ ቆብ ከሌለበት መሬትና ትቢያ ላይ አማዚአብሔርን እያመሰግኑ ይተኛሉ። (ብጣሿ ጨርቅም ብትሆን) የሥቃያቸውን ደም ጠጥታ ነበረ።

በዚህ ሁኔታ አንዱ ለሌላው ምዕዳን እያስማ÷ አንዱ ሌላውን እያበረታታ ከእምነት ግንድ ይደገፋሉ። የእምነቱ (ግንድ) ስሮቿ ከገነት

143. "የልብስ እጣቢ መዋያ"።

144. ቦታው ዛሬም ቈራጻ (ቈራጣ) ነው የሚባለው።

145. ሚክ 2: 12።

146. ኢዮ 24: 24።

በምሥራቅ የተተከሉ ሆኖ (76ʰ) ከፍተኛነቷ ከሰማይ ይደርሳል፤ ቅርንጫፎቿ እስከ ባሕር ይዘረጋሉ፤ አወጣጧ እስከ ወንዞች (ይደርሳል)፤ ቅጠሏ የታጨቀ ነው፤ አበባዋ መዓዛማ ነው፤ ፍሬዋ የተንዠረገገ ነው፤ ዘለላዋ አይጐድልም። ከስሮቿ የሕይወት ውሐ ይመነጫል። የከብት ዘር ሁሉ ከሷ ይጠለላሉ። ለፈለጋት በሁሉ ዘንድ ትገለጻለች፤ በባሕርና በየብስ ካለ ሁሉ ትገኛለች። እንግዳ አፍቃሪ ስለሆነች ወደሷ የሄደ ሁሉ ድካም አይኖርበትም። እንደዚሁ፥ እነዘህን የመዓዛዋ ሽታ ጠቅሷቸው ወደሷ የሄዱትን በፍቅሯ መንጥቃ ወስዳ ስለቀራቸው (ጉዳይ) በአደባባይዋ እንዲሟገቱ የቆላምጧን መንገድ አሳየቻቸው።

ከዚያ፥ በወንዟ ውሐ[147] ታጥበው፥ የብረት ልብስ ደርበው፥ በቅዱሱ ደቀ መዝሙር ምስክራ ውስጥ፥ "እኔ ከአባቴ ሥልጣን እንደወሰድኩና እብሬው በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥኩ ድል ለሚነሣ ከኔ ጋራ በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እስጠዋለሁ"[148] (77ᵘ) እንደሚለው ተስፋ የማይታየውን ተስፋ በማድረግ "የሚኖረው መንፈስ ነው፤ ሥጋ ግን ምንም የሚጠቅም የለውም" የምትለው የሊቁ የቃሉ ምዕዳን መጠጊያ ሆናቸው፥ ዓለሞችን ከሚገዙ መኳንንትና አጋንንት ጋራ ሊዋጉ ወደ ጦር ሜዳ ወጡ። ደግሞም "ነፍሱን የሚወዳት ይጣላት፤ ስለኔ ነፍሱን የጣላት ያገኛታል"[149] የምትለው እውነተኛ ቃሉ እያበረታታቻቸው እንዲሁ እዚህ ሥቃይ እስኪደርሱ ክፉ ሐሳብን ሊያሸንፉት ተጋደሉ።

እንደዚህ ተጥለው በዚያች ደሴት የሰው እርዳታ እጥተው የነፍስ ሳይሆን በሥጋ ታላቅ ድኸነት ኖሩ። ግን የሕይወት ዛፍ ከሆነችው የእምነት ግንድ ተደግፈዋል፤ ከምስጢሯ በረከትም ይመገባሉ፤ ከደስታዋ ወንዝ ይጠጣሉ። በቅጠሎቿ ተሸፍነዋል፤ ከጥላዋ ስር ከምስጋናና ከስብሐት ጋራ ተኝተዋል።

ከቀኖች በኋላ፥ የሀገሩ ሰው ከአገረ ገዢው ታዘው ለምግባቸው ፍርፋሪ ያመጡላቸው ጀመር። ፍርፋሪን ከብዙ ቤቶች በግድ ይሰበስቡታል። እንዳንዴ በየቀኑ እንዳንዴ በየማግስቱ፥ እንዳንዴ በየሶስት ቀኑ ያመጡና ይጥሉላቸዋል። እነሱም ከምስጋና ጋራ (77ʰ) ተቀብለው በቀኖናው መሠረት ይካፈሉታል። ምክንያቱም በውስጡ የደረቀ፥ ያረረ፥ የሻገተ አለበት። ስለዚህ የሁሉም ሥጋ አንድ ስለሆነ ማዳላት እንዳይኖር (እኩል) ይካፈሉታል። አንዳንድ ቀን አንድ እፍኝ ሙሉ ይደርሳቸዋል። አንዳንድ ቀን (ከዚያ) ይበልጣል። ይኸም በየሶስቱ፥ በየአምስቱ፥ በየሳምንቱ ነው እንጂ በየቀኑ፥ በየማግሥቱ አያመጡም። ያም ያለወጥ ነው።

ቅዱሳኑ መላስ ጉሮሮች ስለሆኑ ከመዋጡ ሳይ ጣር ነበረባቸው። (መጠኗም) የረኀብን ኀይል የምታበርድ አይደለችም። ሆኖም የምግብ እጦት የሥጋ መሞት ያመጣል እንጂ የነፍስ መሞት በምግብ እጦት አይመጣም። እንደዚሁ፥ እነሱ የሥጋ ምግብ እንጂ የነፍስ ምግብ አላጡም።

አጥሯ ጥልቅ ውሐ ከሆነ አስጨናቂ ቦታ ጥለዋቸዋልና ሕይወታቸው ለሞት አስክትደርስ ለምንም ከማይፈለጉ ጋራ ቁጠሯቸው። ዐዘቅት ከሚገቡ ጋራ ተቁጠሩ። እርዳታ እንደሌለው ሰው ሆኑ። (78ᵘ) የመልካቸው ውበት

147. ግዕዙ የሚለው "በውሐዋ ወንዝ" ነው።

148. ራእ፡ 3: 21።

149. ማቴ 16: 25፤ ሉቃ 9: 24።

ጠፋች። ዓይናቸው ከጉድጓዱ ራቀ፤ ሥጋቸው ካጥንታቸው ተጣበቀ፤ የጐናቸው ዐጥንት እንደ ጉድጓድ ስለሆነ እንጀታቸው/ሆዳቸው ከወገባቸው ዐጥንት ራቀ፤ ጉልበታቸው ደከመ፤ ለመውጣትና ለመግባት መላወስ እስኪያቅታቸው ድረስ ጀርባቸው ጐበጠ። ብቻ እንደ ሕፃናት ይድኹ ነበረ። የበረታ መድረሻው እስከ ባሕሯ በራፍ ነው።

የደሴቷ መጠን ርዝመቷ በሰው ክንድ ፪፻፱፱ ግድሚ ፻፴ ነው። በውስጧ የተመስቀሉት ቅዱሳን ቊጥር ፮ ነበረ። ከማህላቸው የመንፈሳዊ የመድኃኒት መሥዋዕት የሚያርዱበትን የምስጢርን ጒራዴ የሚስግቡ ቄሶችና ...[150] ለሕጎቿ አገልግሎት የሚራወጡ የቤተ ክርስቲያን በር ጌጦች (የሚባሉ) ዲያቆናት፥ በዐጸዷ ያደሩ ክንፋቸውን እያመረገዱ ሁልጊዜ በመስኮቶች የሚጫወቱና አምላካዊ ምስጢራትን ለማየት ከመሣርያ ቤት ግምብ[151] ላይ የሚወጡ ሌሎች ወንድሞች፥ (78^ሀ) በቀለም የማይደክሙ ሕሊናቸውን ሁል ጊዜ አየር ላይ የሚያንቀሳቅሱና በሰው ልጅ አንደበት የማይተረጐም የአዳራሹን የአሠራሩን ጥበብ ሁሉ የሚያዩ፥ በመልኳ ውበት የሚዝናኑ፥ በምኞቷ ደስታ የሚጠግቡ፥ ድካምና ትካዜን የሚረሱ፥ የበጉ ሙሽሮች፥ የጽዮን ግድግዳ ጌጦች (የሚባሉ) ቊጥራቸው ፴፱ የሆነ መነኮሲቶችም ነበሩባቸው።

በዚያች ደሴት በዚህ ጭንቅ ስም ያላቸውና ስማቸው ያልታወቀ ቅጠሎቿ ከዛፎቿ ፍሬዎችም ከጥቂቶቹ ሽዬ[152] ኮክ/ሎሚ[153] አየበሉ፥... ቀን[150] ኖሩ። በዚህ ሁኔታ እንዳሉ ፲፩ ወንድሞችና እንዲት መነኮሲት (ስማዕትነታቸውን) ፈጸሙ።

የረኀብ አድማ

ከ፴፫ ቀን በኋላ፥ እንደታወቀችው፥ "በትክክለኞች ምክር በማኅበር የእግዚአብሔር ሥራ ታላቅ ናት፤ ደስ በምትሰኙበት ሁሉ ዘንድ የተፈለገች ናት"[154] እንደምትለው (ቃል) በእሱ ዘንድ ደግ ለመሥራት የተፈለገ ምክር ሁሉ ለሚፈጸም መንፈሳዊ ምክር ቅዱሳኑ ስብሰባ አደረጉ። በዚህ ምክንያት፥ "የደከማችሁና በጣር ላይ ያላችሁ ወደኔ ኑ፤ እኔ አሳርፋችኋለሁ"[155] እያለች በጥሪዋ የተበተኑትን በምትስበሰብ የጌታችን ተስፋ፥ ከሌላ ቦታም፥ "ጠይቁ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ"[156] በሚለው ቃሉ የበረከት ፍሬ ይቀስሙ ዘንድ ልዑላዊ ሰማያዊ ኪዳኑን ፍለጋ ገቡ። (79^ሀ) ይኸንን ተስፋ በማመን፥ "የሚሆኑንን አንመክርምን? ለሚያደርጋት ሁሉ ምክር ጥሩ ነች[157] አላለምን? በዚህ ምስኪንነት እዚህ ደሴት ውስጥ ኑሯችን ምንድን ነው? ተስፋ የምናደርገው ምን አለን? ወንድሞችን ለማገልገል በየመንደሩና በየሀገሩ መዘዋወር ነው፥ ወይስ ከቤተ መቅደስ አገልግሎት፥ ወይስ ሕዝቡን በሕግ (እንዲኖሩ) ማስተማር፥ ወይስ እግዚአብሔርንና ወንድሞችን በምናስደስትበት (ዓላማ) ከሀገር ወደ ሀገር መሄድ? እንደምናየው ያለነው በብዙ ሥቃይ ነው። ጌታ፥ የምትፈልጉትን ጠይቁ፤ ይሰጣችኋል አላለምን? ስለዚህ እንዲምረንና ቸርነቱን እንዲያሳይልን አሱን እንለምነው" (ተባባሉ)።

---

150. ቊጥራቸው አልተጻፈም።
151. መኃ 4: 4።
152. "ከሞል"።
153. "ከርካዕ"።
154. መዝ 110: 1-2።
155. ማቴ 11: 28።
156. ማቴ 7: 7።
157. መዝ 110-10።

ምክራቸው ከመንፈስ ቅዱስ ምክር ጋራ እንደ ኂቂያው የ[illegible]ቱ (አበው) ጉባኤ በአንድ ቃል ተፈጸመች። ከምህልላ ጋራ የዛፎቹን (79^{0}) ፍሬዎችና ቅጠሎችን (ከመብላት) በማቆም የ፴ ቀን ጾም (ለመፈጸም) ወሰኑ። ከዚያ፥ መስከረም መባቻ ላይ እንዲህ ሲሉ በብዙ መገዛት ጀመሩ፤

"አቤቱ በምሕረትህ (እኛን) ሕዝብህን አስታውሰን፤ በማዳንህ ምሕረት ስጠን"[158]። "አስቀድመህ የፈጠርከውን ማኅበርህን አስታውስ"[159]። "ለዘላለሙ አላልፈህ አትሰጠን፤ ስለ ስምህ የአሰረኞች ጩኸት ከፊትህ ይቅረብ"[160]። "እኛም ሕዝብህ የበጎች መንጋህ ነን"[161]። "ለስምህ ለዘላለም እንገዛለን፤ ስብሐትህን ለትውልድ ትውልድ እንነግራለን"[162] "የሰማዮች ኃይል ሁሉ አንተን ያመለግናሉና።"[163] ስብሐት ለዘላለም ያንተ ናት፤ አሜን።

በነዚህ ስብሐታትና እነዚህን በሚመስሉ ሁሉም እያንዳንዳቸው እግዚአብሔርን እንዲህ እያሉ ይለምኑት ነበረ፤

"በሙሉ ልቤ ፊትህን ጠየቅሁ"[164]። "ከተሰፋዬ አታላፍረኝ"[165]። "መቼ ደርሼ የአምላኬን ገጽ አያለሁ"[166]። "ዕንባዬ ቀን ከሌት ምግብ ሆነኝ"[167]። "በጣም ተሠቃይቻለሁና ልመናዬን አይልኝ"[168]። "አቤቱ ጸሎቴን አልሰማ አትበል"[169]። "ጸሎቴን ዕጣን በፊትህ እንደምትቀበል ተቀበለኝ"[170]። "አቤቱ ማረኝ"[171]። "አቤቱ ተቀበለኝ፥ አቤቱ አላረፈኝ፥ ተቀበለኝና ከዚህ ዓለም አሻግረኝ። (80^{0}) ድውይ ነኝና አቤቱ ዐጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ"[172]። "ነፍሴም በጣም ታውካለች እስከ መቼ ድረስ ፊትህን ከኔ ታዞረዋለህ?"[173]። "አምላኬ አምላኬ፥ ተመልከተኝ፥ ለምን ትተወኛለህ"[174]። "አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ ዕንባዎቼን አዳምጥም፤ ቸል አትበለኝ፤ በምድር ላይ ፈሳሪ ነኝና"[175]። "አቤቱ ጸሎቴን አዳምጥ፤ ልመናዬን ቸል አትበልብኝ"[176]። አቤቱ እኔን ከመርዳቱ ላይ ተመልከት"[177]። "በአርጅናዬ ጊዜ አትጣለኝ፤ ኃይሌ ሲያልቅም አምላኬ አትጣለኝ"[178]። "ልቤና ሥጋዬ በመድኃኒቴ አምላክ አለቁ"[179]። "ሁል ጊዜ ወዳንተ አጮኻለሁና አቤቱ ማረኝ፤ የባሪያህን ነፍስ አስደስታት"[180]። "አቤቱ እንደ ልቤ ሥቃዬ ብዛት (ነፍሴን አስደስታት)"[181]። "አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ፤ ጩኸቴም ወዳንተ ይድረስ፤ (በመከራዬ) ዕለት ፊትህን ከኔ አታዙር፤

158. መዝ 105: 4።
159. መዝ 73: 2።
160. መዝ 78: 11።
161. መዝ 94: 7፤ 99: 3።
162. መዝ 78: 13።
163. የጸሎተ ምናሴ መጨረሻ።
164. መዝ 118: 58።
165. መዝ 118: 116።
166. መዝ 41: 3።
167. መዝ 41: 4።
168. መዝ 114: 7።
169. መዝ 108: 2።
170. መዝ 140: 2።
171. መዝ 40: 5፥ 11።
172. መዝ 6: 3-4።
173. መዝ 12: 1።
174. መዝ 21: 2።
175. መዝ 38: 12።
176. መዝ 54: 2።
177. መዝ 39: 14፤ 69: 2።
178. መዝ 70: 9።
179. መዝ 72: 26።
180. መዝ 85: 3-4።
181. መዝ 93: 19።

ጆሮህን ወደ እኔ አዘምብል፤ በጠራሁህ ቀን ፈጥነህ ስማኝ። ዘመኔ እንደ ጪስ አልቋልና አጥንቴም እንደ ማር ደርቋል”[182]። “ተቀውፍኩ ልቤም እንደ ገል ደረቀ”[183]። “አቤቱ (80^ሀ) ጸሎቴን እምቢ አትበል”[184]። “ለባርያህ የስጠኸውን ተስፋ አስታውስ”[185]። “ይህቺ በመከራዬ ደስ አሰኘችኝ”[186]። “መቼ ታስደስተኛለህ አያሉ ዓይኖቼ ለማዳንህ ደከሙ”[187]። “ከሚያሳድዱኝ መቼ ትፈርድልኛለህ? በዓመፃ ለደውኛል፤ አርዳኝ”[188]። “እንተ አስተምረኸኛልና”[189]፤ “ትእዛዝህን ልብ አልኩ”[190]። “እኔን አይተህ ማረኝ ለሚያፈቅሩህ እንደምታደርገው”[191]። “አቤቱ ልመናዬ ካንተ ዘንድ ትቅረብ፤ እንደ ቃልህም አድነኝ፤ ጌታ ሆይ ልመናዬ ካንተ ዘንድ ትድረስ፤ እንደ ቃልህም አስረዳኝ”[192]። “በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ሁል ጊዜ ስብሐት አቀርብልሃለሁ፤ የሰማዮች ኃይል ሁሉ ለአንተ ስብሐት ያቀርባሉና ስብሐት ለዘለዓለም ለአንተ ይሁን፤ አሜን።”[193]

አሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ ይኸንን ልብ የሚለው ጥበበኛ ማነው? “እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ”[194] (መሆኑንም)? ለጸለየ ጸሎቱን ይስጠዋል። በኦሪት ሕግ የሚያርዱት መሥዋዕት ሰውን ከኃጢአቱና ሕዝብን ከትካዜው አያነጻውም ነበርን? ከቋጥኝ ስር የሠዋው የጌዴዎን ወልደ ዮአስ መሥዋዕት የሕዝብን ትካዝ አስፈጸመች፤ የጠላትንም ከበባ ሰበረ፤[195] (81^ሀ) የሳሙኤል ወልደ ሕልቃናም እንደዚሁ።[196] ከዚህ የሚሻል የለምን? ግን ንግግራቸው ግልጽ ከሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንዳወቅነው፥ መሥዋዕትና ቍርባንን አልፈለኩም፤ ሥጋህን ንጹሕ አድርግልኝ፤ ስለ ኃጢአት የሚሆነውን መሥዋዕት አልወደድኩም[197] የሙክት መሥዋዕትና የበግ ስብ ጠግቤያለሁ። የበሬና የፍየል ደም አልፈልግም፤[198] ዓለም በሞላው የኔ ነውና። የበሬ ሥጋ አልበላም፤ የፍየል ደምም አልጠጣም።[199] ከዚህም የሚሻል የመሥዋዕት መዓዛን መቀበል ሲያበልጥ፥ የተከበረች መሥዋዕት ስብሐት ታቀርብልኛለች[200] (ይላል)። ክብርት መሥዋዕት ከራሱ የሆነ ስብሐት ስብሐት አንዳቀረበችለት እንደዚሁ ከራሷ ስብሐት ስብሐት ታቀርብለታለች። በእሷ ስም የተጠሩም ስማቸው በስብሐቷ ስብሐት ይቀርብላቸዋል።

ስለዚህ አነጋገር፥ ስለምትሻለው መሥዋዕት፥ መንፈስ ቅዱስ ያለውን እነሆ ቅዱሱ ደቀ መዝሙር ምስክር ሆኗል። ስለምትበልጠው መሥዋዕት፥ ስለምትበልጠው መሥዋዕትነት ኢየሱስ የተመረጠ ሆነ፤ ሞትን ቀምሶ የተሳላቱትን፥ ባለፈ ሥርዓት ተስፋ የሰጣቸውን (81^ሀ) ወደ ዘለዓለም ርስት

182. መዝ 101፡ 1-5።
183. መዝ 21፡ 16/22፡ 15 እና 101፡ 5/102፡ 4 ተደባልቆ።
184. መዝ 108፡ 2/109፡ 1።
185. መዝ 118፡ 49።
186. መዝ 118፡ 49-50።
187. መዝ 118፡ 82።
188. መዝ 118፡ 84-86።
189. መዝ 108፡ 102።
190. መዝ 118-104።
191. መዝ 118፡ 132።
192. መዝ 118፡ 169-170።
193. ጸሎተ ምናሴ መጨረሻ።
194. መዝ 102፡ 8፤ 110፡ 4፤ 111፡ 4፤ 144፡ 8።
195. መሳፍ 6።
196. 1 ሳሙ/ነገሥ 11፡ 14፤ 16፡ 5)።
197. መዝ 39፡ 6/7።
198. ኢሳ፡ 1፡ 11-12።
199. መዝ 49/50፡ 12-13።
200. መዝ 49፡ 23።

ጠራቸው::[201] የቀደሙ አይቀድሙም፤ ወደ ኋላ የቀሩም አይዘገዩም፤ በሽቶው መዓዛ ስለሚሮጡ ደስታንና እግዚአብሔር ማዳንን ያሳየባትን መንገድ ያገኛሉ:: ወደ ምሥዋዑ ይወጣሉ፤ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥም በዐጥንታቸው መዓዛ ያገቡለታል::[202] በዚህም እንዲህ ያለው የራእዩ ንግግር ይፈጸማል፤ "የጽድቅን መሥዋዕት፥ መባውንም፥ ቍርባኑንም ስትወድ በዚያን ጊዜ ፍሪዳዎች ከመሠዊያህ ላይ ይወጣሉ::"[203] ስለዚህ የስብሐት መሥዋዕት በእግዚአብሔር ምሥዋዕ ላይ የሚወጡት አንደ ሙሴ ሕግ በእሪት ደብተራ[204] በበሬና በፍየል ደም በቀይ ሐር ሳይሆን በትሑት ልብና፥ በየዋህነት መንፈስ ነው::

ቅዱሳኑ በስብሐታቸው ውስጥ፥ "ጌታ ሆይ፥ ስኛ አይደለም፤ ለኛ አይደለም፤ በምሕረትህና በጽድቅህ ስብሐት የምንሰጠው ለአንተ ስም ነው፤ አሕዛብ አምላካቸው የት አለ እንዳይሉ"[205] አሉ:: በዚህ በስብሐትና በተቀደሰ መሥዋዕት ምክንያት፥ ቅዱሱ የስብሐቱ ስም በአነሱ ላይ ተገለጸ:: (ይህም ጌታ፥) "አብ ሆይ በስብሐትህ ስብሐት አቅርብልኝ" ባለ ጊዜ አብ አንደ ልጁ ስብሐት፥ "ደግሞ ስብሐት አቀርባለሁ"[206] ብሎ ለሚከተለው ሲያስከትል የአዳም ($82^{ሀ}$) መለኮታዊ አምሳካዊ ፍጥረቱ ስብሐት የቀረበለት ነው::[207]

ይኸንን መንፈሳዊ ስብሐት ሲያገኙ ለዚህ ስብሐት መሪ የሆናቸውን እንዲህ ሲሉ ምስጋናና ስብሐት አቀረቡለት፤ "ስብሐትና ምስጋና ይሁን፤ የእግዚአብሔር ስም ስብሐት ይድረሰው፤ ስምህ ለዘላለም የተመሰገነና ስቡሕ ነው::[208] አንተ በኛ ላይ ባመጣኸው ሁሉ ትክክል ነህ:: ሥራህ ሁሉ የሚታመን ነው:: መንገድህ ሁሉ ቀጥታ ነው:: ያደረግኸው ፍርድ ሁሉ ልክ ነው፤ የሠራኸሁ ሁሉ ትክክልና ቀጥታ ነው::"

የአድማው ውጤት

በዚህ ምስጋናና መንፈሳዊ ልዑላዊ ስብሐት ቆይተው፥ ከ፵ ቀን የምህሳቸው ጸም ፍጻሜ ላይ፥ ይህቺ ለነፍስ ዕረፍት የምትሰጥ የመስቀል ስብሐት በማህላቸው ተገለጠች::[209] ዕረፍታቸው በየማግስቱ ሆነ፤ (አሟሟታቸውም በአንድ ቀን) አንዳንዱ ፪ቱ፥ አንዳንዱ ፫ቱ፥ አንዳንዱ ፬ቱ፥ አንዳንዱ ፭ቱ፥ አንድ ጊዜ ፯ቱ ነበረ:: በሰው (አጅ) በጣር ወይም በምትሐት ሳይሆን፥ እንደ ጣፋጭ ሽለብታ ተስፋቸውን አገኙ:: ደስታቸውን ($82^{ለ}$) ሙያተኛ በሰብል ስብሰባ ጊዜ በባለ እርሻው ማሳ ላይ ያደረገው አገልግሎት አልቆ ደሞዙን ሲከፈል አንደሚደሰት ሆነው አገኟት፥ ተቀበሏትም:: ዕረፍታቸው አንደዚህ ሆነ፤ ከጠዋት ጸሎት በኋላ በጥቂቱ ሽለብ አንደሚያደርጋቸው ይሆናሉ:: የ፫

201. ዕብ 9: 15-16::
202. ሄኖ ክፍል 24, Knibb, *Enoch*, p. 90.
203. መዝ 50/51: 19)::
204. ድንኳን::
205. መዝ 78: 10፤ 113: 2::
206. ዮሐ 12: 28-29::
207. "ክርስቶስ የለበሰው የአዳም ሥጋ" ስግለት ነው::
208. የጸሎተ ዳንኤል መጀመሪያ::
209. መሞት ጀመሩ::

ሰዓት (የጸሎት ጊዜ) ሲደርስ አንዱ ሌላውን ሲቀሰቅሰው (ሰማዕትነቱን) ፈጽሞ ያገኘዋል። እንደዚህ ከ፫ ሰዓት (ጸሎት) እስከ ፮ ሰዓት (ጸሎት) ጊዜ አንዱ ሌላውን ሲቀሰቅሰው (ሰማዕትነቱን) ፈጽሞ ያገኘዋል። ከ፮ ሰዓት (ጸሎት) ወደ ፱ ሰዓት÷ ከ፱ ሰዓት ለምሽት÷ ከምሽት ለመተኛው÷ ከመተኛው ለእኩለ ሌሊቱ እንደዚሁ ይሆን ነበረ።[210] ፫ቱ አብረው ተኝተው የቀኙና የግራው (ሰማዕትነታቸውን) ፈጽመው ይገኙና የማህለኛው ተነሥቶ የአምላኩን ቸርነት እያደነቀ የጊዜውን ጸሎት ያደርሳል። መነኮሲቶቹም በየማግሥቱ በየ፫ በየአራቱ (ሰማዕትነታቸውን) ሲፈጽሙ ልመናቸው ባዶ አ፫ን ስላልተመለሰች እማዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

የክቡር ተጋዳይ÷ ጥሩ ቸርነት አፍቃሪው÷ የብፁዕ ቅዱስ ዘአማኑኤል ዕረፍት በታውፊን ወር በ፳፬ ነበረ። አለዳስ[211] ፊት ወንጌል የሚሰብከው÷ የቅዱስ ብፁዓዊ አባታችን÷ የንጹሑና እንደ በግ የዋሁ÷ የብፁዕና የክቡር ያዕቆብ ዕረፍት በዚሁ ወር በ ... ነው። (83^{0}) አለዳስ ፊት ወንጌል የሚሰብከው÷ የእቡነ ብፁዕ÷ በሙቀት ላብና በነፋስ የማይደርቅ÷ ቅጠለ ብዙው ከባድ የበረከት ዛፍ÷ ክቡርና ቅዱስ ጳውሎስ ዕረፍት በአቴር ወር በ፳፭ ነው። የጻፍነው ከብዙ ቀኖችና ዓመታት በኋላ ስለሆነ÷ የሌሎቹን ወንድሞች የዕረፍታቸውን ቀን አላገኘነውም። (የጻፍነው) የጸሎታቸውና የልመናቸው በረከት ለዘለዓለም እንዲደርሰን ተስፋ በማድረግ ነው፤ አሜን።

ጸጸትና ንስሐ

ያንን ሃይማኖቱን የካደውን ወንድምም ከብራ ከምትባለው ከዚያች ባሕር ደሴት አስገቡት። ግን ከዘመናት በኋላ ወደ ወንድሞቹ ተመልሶ÷ "ከናንተ ጋራ ባለመጨከኔ አጥፍቻለሁ፤ አሁንም ንስሐ ስጡኝ" አለ። እነሱም በሚገባ ገሥጸው ንስሐ ሰጡትና÷ "ወዳለህበት ተመለስና ከዚያ ሆነህ ጉብኘን" አሉት። ሄዶ እያገለገላቸው ኖረ። ወደ ቀድሞው ሥራው መመለሱን የደሴቲቱ መነኮሴዎች ዐውቀውበት÷ "የቀድሞዋን ሥራህን አልተውካትምን?" አሉት። "እምን÷ አልተውም፤ ቀድሞውንም ስለተሳሳትሁ በወንድሞቼ እጅ ንስሐ ተቀብያለሁ። አሁንም ስለ ሃይማኖቴ እሞታለሁ" አላቸው። (83^{A}) ያዙትና ዘንጉ በላዩ እስኪሰበር ድረስ ብዙ ድብደባ ደበደቡት። "ለንጉሡ ስገድ፤ መምህርህን ስደብ" እያሉ ሲወተውቱት÷ እሱም አምቢ ሲላቸው ብዙ አሰቸገሩት። ሥራውን እንደተመኙት ማስጣል ሲያቅታቸው ተዉት። እዚያው አንዳለ በትንሹ ታመመና እዚያው (ሰማዕትነቱን) በጥሩ ገድል ፈጸመ። ጸሎቱና በረከቱ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

---

210. የሰዓታት ጸሎት ጊዜያት "ነግህ" (ጠዋት)÷ "ሰለሰት" (3 ሰዓት)÷ "ቀትር" (6 ሰዓት)÷ "ተሰዓት" (9 ሰዓት)÷ "ሠርክ" (ምሽት)÷ "ንዋም" (መኝታ)÷ "መንፈቀ ሌሊት" (እኩለ ሌሊት) ናቸው። ጥንት በትላልቆቹ አድባራት ጸሎቱ 24 ሰዓት አንደነበረ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሰጫ ሰዓታት ይመሰክራል።

211. "አለዳስ" የሚሉት የአፄ ዘርአ ያዕቆብን አደባባይ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ቃሉ "አለዳስ"÷ "አላዳስ" ግሪክኛ ሆኖ ትርጉሙ "ደሴት" ወይም "የፍግ መቆለያ" ነው፤ ሉቃ 14፡ 35፤ "አላደስ" ከሆነ "ደረቅ ጉድጓድ" ማለት ነው።

የመንግሥት (85ᵛ) ወንጌል በሆነች ጌታ በሚያሠማራበት የሚያሠማራ፥ ምንደኛ ያልሆነ፥ ቸር እረኛ ነበረ።[216] ለነቢዩ እንዳለው እንደ መልእኩ ቃል፥ በቅዱሱ ጌታ በዘለዓለሙ ንጉሥ ቤት በኩል፥ በመሰዕ በኩል፥ በቅዱስ ቦታ ላይ ከተተከለ ዛፍ ፍሬ የሚበላና የሚያበላ፥[217] በደስታ የሚደሰት፥ ደስ በሚል ደስ የሚለው ነበረ፤ ምክንያቱም ቅዱስ ቅዱሳን (እግዚአብሔር) በዐፅሞቹ ውስጥ መዓዛ ይጨመርለት ነበረ። ባደረበት የመንፈስ ወላፈን የልብሌኔስን ዝገት[218] ከብዙዎች ልብ ያስወግድ ነበረ።

ንጉሡ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስን፥ "ለመንግሥቴ ክብር ካልሰገድክ የት ትሄዳለህ? በማን ምድርስ ትኖራለህ?" ሲለውና ቅዱሱ ይሽንን ከመልእክተኞቹ ሲሰማ፥ "ያበቀልከውን አልበላሁም፤ ያዘነምከውን አልጠጣሁም። መጽሐፉ ሰማየ ሰማያት የእግዚአብሔር ነው፤ ምድርን ግን ለሰው ልጅ ሰጠ[219] ይላል። እግዚአብሔር ሰማይን ሲፈጥር ረድተኸዋልን? ደግሞ ምድር አትክልት እንድታወጣ ያዘዛት[220] ላንተ ብቻ ነውን? እነሆ፥ በየዘሩ የሚዘራውን አትክልት ሁሉ ሰጥቻችኋለሁ[221] ያለው ለብዙዎች አይደለምን? በሉት" አላቸው።

በዚህም ተቆጣ፤ (85^ᛃ) ብዙ ተንኮል አሰበለት። ምን እንዳደረገው በመጽሐፉ (በገድሉ) ውስጥ አለ። ዲዮቅልጥያኖስ እንኳን ክህደቱን ገልጦ፥ "ለአምላኮቼ ለአጵሎንና ለአርዳሚስ ያልሰገደ ሁሉ ይሙት" ብሎ ነው የመጣው። ይሽ ተንኮለኛ ግን በግ ይመስላል፤ ያሰኘውን ይናገራል፤ በሥልጣኑ የፈለገውን ሁሉ ያደርጋል፤ ለመንግሥቱ ክብር ስግደትን ያዛል። እንቢ ሊለው የፈለገውን እንዲገደል ያዝዝበታል። ሃይማኖት እንዲያስተምር የእግዚአብሔር ጎይል በጳጳሱ በአባ በርተሎሜዎስ እጅ በኩል ወደ ቅዱሱ በመጣ ጊዜ በቃሉ ትምህርት ውስጥ ከመጻሕፍት ቃል፥ "የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስቡ፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለሱ፤ የአሕዛብ ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይሰገዱ፤ መንግሥት የእግዚአብሔር ነውና"[222] የሚለውን አስተማረ። ደግሞ፥ "የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሳርን ለቄሳር ስጡ"[223] አለ። ቅዱሱ አባታችን የሚከተሉትን የጌታን ዲናር ስግደትን ለቄሳር እንዳይሰጡ በእንደዚህ ያለ ትምህርት ያስረዳቸው ነበረ፤ ልጆቹ (86ᵛ) ይሽንን ተረድተው የጌታን ሥቃይ ለመቀበል ተዘጋጁ፤ ያ ተንኮለኛ ቅጣቱን በያይነቱ ከዘመን ዘመን እየለዋወጠ አበዛባቸው። ለጸሎትና ለቊርባን ቅዳሴ የሚመጣ ሁሉ

---

216. ዮሐ 10፡ 11-14።

217. ሕዝ 47፡ 12።

218. ስብሌኔስ፥ ስብልዮስ፥ ሰባልዮስ፥ ስብልያኖስ ያንድ ሰው ስም ናቸው፤ ክህደቱ "አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ ገጽ" ("አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል ናቸው"፤ ሶስቱ ስሞች ያንድ አካል የተለያዩ ስሞች ናቸው ማለቱ ነው፤ Yacob Beyene, Giyorgis di Saglā *Il libro del Mistero (Maṣḥafa Mesṭir) CSCO*, vol. 515/89 (1990), p. 8; Getatchew Haile, "*Fəkkare Haymanot* or the Faith of Abba Giorgis Säglawi," *Le Muséon*, vol. 94/3-4 (1981), p. 249.

219. መዝ 113/115፡ 16።

220. ዘፍ 1፡ 11።

221. ዘፍ 1፡ 29።

222. መዝ 21፡ 28-29/22፡ 27-29።

223. ማቴ 22፡ 21፤ ማር 17:17፤ ሉቃ 20፡ 25።

(እንዲደግመው) በየቤተ ክርስቲያኑ ፊት "እስጢፋኖስ እርኩስ ነው" የሚል ስድብ ተከለ::[224]

አሁንም በክርስቶስ ያላችሁ ወንድሞቻችን ሆይ፡ "እርኩስ ካልነካው ጥላው ቢያርፍበት ቅዱሱ ይረኵሳልን? እንድ ሰው ቅዱሱን በማርኩስ ሰራሱ ቅድስና ይቀበላልን? መጽሐፉ፡ "ቅዱሳት ለቅዱሳን"[225] አላለምን:: ሰዎች ቅድስናን የሚያገኟት በምንድን ነው? በምንስ ይረኵሳሉ? ጌታ በወንጌል፡ "ከአፉ የሚወጣው ሰውን ያረኵስዋል"[226] አላለምን? ይኸም መስረቅ፡ መግደል፡ መላደብ፡ በውሸት ምስክራ፡ ዝሙት፡ መዳራት ነው:: ሰውን የሚያረኵሱ እነዚህና እነዚህን የመሰሉት ናቸው:: ጌታችን ክርስቶስ ያደረበት (ሰው) ሆኖ ላለ ንጉሥ እሱን ፈጽሞ አያረኵሰውም:: አሁንም፡ "በትዕቢትና በንቀት በጻድቅ ላይ ሀሰፃ የሚናገሩ ወዮላቸው"[227] (86ʰ) ደግሞም፡ "የጻድቃን ቃላቸውንና ነገራቸውን የምትለውጡ ወዮላችሁ፤ የሕይወት ተስፋ ለናንተ አይሆንምና:: ትክክሉን ነገር የሚለውጡና የዓለምን ሥርዓት የሚከዱ፡ ራሳቸውን ኃጢአተኞች ያይደሉ የሚያደርጉ ወዮላቸው፤ በምድር ላይ ይረገጣሉ"[228] የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ልብ እንበል:: በዚህ ሰው ይቀደሳል--ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሶ ቅዱስ ይሆናል:: ቅድሳትንም (ቊርባንን) ይቀበላል:: ቅዱሱ ሐዋርያ ጴጥሮስ፡ "ከመለኮቱ ተካፋዮች ሆነናል"[229] እንዳለው ቃሉና ሌላው፡ "ተካፋይነታችንም ከአብና ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ነው"[230] እንዳለው ከሱ ጋራ ተካፋይ ይሆናል:: ይኸም ቅዱስ አባታችን የጌታን መለኮት ተካፍሎ ቅዱስ ሆነ፤ የተከተሉትንም ከተካፈለው አካፋሏቸው የቅድስናው ተካፋዮች ሆኑ:: ታዲያ ይኸ ንጉሥ እንደዚህ ያለውን ሰው ሰይጣን አለው:: ነገሩ ጽኑ ስለሆነ፡ በዘመኑ የእግዚአብሔር ባርያዎች እነ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል፡ ገብረ አምላክ በሱ ተደናቀፉ:: ከልጆቻቸው ጋራ ብዙ አስቃያቸው፤ ግንዱ እንደሱ ጠንካራ ሆነ:: (87ᵇ) የእግዚአብሔርን ሰው በምስጋና ደልሎ ተንኮል ሠራበት፤ በማይነቃነቅ የእምነት ግንድ እንደተደገፈ አላወቀም:: (ሊደልለው) እንዳልተቻለው ሲያውቅ የነቢዩን ልብስ ቀደዳ እንደጨመረ እንደዚያ እንደ ቂስ ልጅ[231] ቢሕገ ወጥ ትእዛዝ ግድያ እስከ መጨመር ደረሰ፤ እንዲሁ ፍሬውም የሐዘን ፍሬ ሆነ::

መልእክተኞቹ (ንጉሡ) እንዳዘዛቸው ወደየመንግሥቱ ብሔሮች ወጡ:: በቅዱሳኑ ላይ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ እንደ ቀን በሌሊት እስኪሆን ድረስ ከፍ ያለ ስደትና መጥበብ ደረሰባቸው:: (በስደት) እስከ ሀገር ዳርቻ ደረሱ፤ ከዋሻና፡ ከጉድጓድ፡ ከድንጋይ ስንጥቅም ገቡ፤ በተራሮቹ ላይ ተንከራተቱ::

---

224. በስፊ ቆዳ ላይ በትላልቅ ፊደል የተጻፈ መሆን አለበት::
225. *ቅዳሴ ሐዋርያት፡ ለምሳሌ፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ በግዕዝና በአማርኛ፡* አዲስ አበባ 1951 ዓ. ም. ገ. 66::
226. ማቴ 15: 11::
227. መዝ 30: 18/19::
228. ?::
229. 2 ጴጥ 1: 4::
230. 1 ዮሐ 1: 3::
231. የቂስ ልጅ የሚሉት የመጀመሪያውን የአስራኤል ንጉሥ ሳኦልን ነው:: ታሪኩ 1 ሳሙ 19: 22-24 ላይ አለ:: አዬ ዘርአ ያዕቆብ አቡነ በጸሎተ ሚካኤልንና አቡነ ገብረ አምላክን ምን እንዳደረጋቸው አልተነገረም::

አንዳንዶቹ በደረታቸው እስከ መሳብ ደረሱ። ከፍ ያለ ችግር ረኀብ፥ ውሐ ጥም፥ መራቆት ደረሰባቸው።

ከዚያ፥ ይኸ ተክለ ኢየሱስና ሌሎቹም ያገኟቸውን አምጥተው ከንጉሡ ዘንድ አደረሷቸው። የንጉሡ ሎሌዎች ቅዱሳኑን ብዙ ነገር እየተናገሩና በብዙ ክርክር አደከሟቸው። ቅዱሳኑ (87^ሀ) "እኛ እናንተን የምንከራከርበት ጉዳይ የለንም፤ አባታችንንም በክርክር አላሰደሰታችሁም" አሏቸው።

የንጉሡ ሎሌዎች፥ "አባታችሁ የት ነው?" አሏቸው። በግድም ኬላ ከአባታችን ዐፅም ጋራ ከተያዙት አንዱ መርቆርዮስ የሚሉት ወንድም፥ "መምህራችን የጌታን ሥቃዮች ተካፍሏል። እኛም አባታችንን እንከተላለን" አለው። በዚህ ምክንያት ተቆጥቶ አንገቱን አንቆ ከመሬት ጣለውና ብዙ ድብደባ ደበደበው። ሌሎቹንም እንደዚሁ ደበደቧቸው። ያሉትንም ሁሉ ለንጉሡ ነገሩት።

ሠራተኞቹንና ሠራዊቱን ተቆጣ

ንጉሡ የራሱን መነኮሴዎች ሰበሰባቸውና፥ "እናንተ (የኔ) ባሮች፥ እንደነሱ ሰዉን አታሰተምሩም። እነሱ ቀን (ማሰተማር) ሳይችሉ ሌሊት ያሰተምራሉ" አሳቸው። ደግሞ ሠራዊቱን፥ "እናንተ ቀን ቀን ከኔ ጋራ ትሠራላችሁ፤ ሌሊት ግን ከነሱ ጋራ ናችሁ" አሳቸው። ከዚያ፥ ንጉሡ በቅዱሳኑ ላይ እንዲህ ሲል አዘዘ፤ "እሺ ካለህ ሰገድ በለው፤ እምቢ ካለ ምላሱንና አፍንጫውን ቀሪጠው፤ ቋንጃውንም ከሁለቱም (88^ዐ) እግሩ እውጣ"።

አበስኪሮን የሚባለው መልእክተኛ ታዝዞ መጣ። ንጉሡ ያለውን ለቅዱሳኑ ነገራቸው። እነሱ ግን ቃሉን አልተቀበሉም። "እምቢ ብለንሃል" አሉት። "መምህራችን የክርሰቶሰን ሥቃዮች ተካፍሏል" ባለው ወንድም ለመጀመር መላሱንና አፍንጫውን ቈረጡት። የሁለቱን እግሮቹን ቋንጃዎች እወጡ። በሌሎችም ወንድሞች እንደዚሁ አደረጉ። ያቺ ቀን የጎዳር መባቻ ዓርብ ዕለት ነበረች። የተቈረጡት ቍጥራቸው ፷፱ ሆነ። ከነሱ ፩ዱ መነኮሲት ናት። ደግሞ ልብሳቸውን ገፍፈው ከውጭ አውጥተው ከሰገራ መውጫ ጣሏቸው። እዚያ ሶስት ቀን አደሩ። እህል ውሐ የሚሰጣቸው አልነበረም። በአራተኛው ቀን ከዚያ አውጥተው ወደ ሌላ ቦታ ወሰዷቸው። አንዳንዶቹ በዝግሚያ ይሄዳሉ፤ አንዳንዶቹን ይጐትቷቸዋል፥ አንዳንዶቹ በሁለት በትር ይመረኮዛሉ። ፪ቱን ወንድሞች መሄድ ሲያቅታቸው ከዋሻ ውሰጥ ጣሏቸው። ከቀናት በኋላ ፩ ወንድም መጥቶ ከወንድሞቻቸው ጋራ ደባለቃቸው። ፪ቱ፥ "በዚህ ሕይወታችን (88^ሀ) እቤተ ክርስቲያን በማገልገልም ሆነ ወይም ወንድሞችን በመርዳት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻለንም" አሉ። ይኸንን ብለው እህልና ውሐ (መውሰድ) አቆሙ፥ አንዱ ሰማዕትነቱን ጎዳር ፴ ቀን፥ ሁለተኛው ታኅሣሥ ፲ ቀን በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ግብጻውያን እንግዶች--በምድረ ፈራኅ

መልእክተኞቹ በፊት እንደታዘዙት ቅዱሳኑን አመጧቸውና በማነቆ እንደታሰሩ ከንጉሡ ዘንድ አደረሷቸው፤ ንጉሡ በዚያን ጊዜ በምድረ ፈራኅ ነበረ፤ ከፊቱ አቆሟቸው። በዚያን ቀን ግብጻዊ እንግዳ መጥቶ ነበረ።[232] ንጉሡ

232. ስለ እንግዶቹ ከመግቢያው ውስጥ ተጽፏል።

ግርማውን ያሳያቸው ነበረ። ቤቶቹን ቀለሙ ቀይ በሆነ ልብስ አስጌጣቸው። ሠራዊቱን ሰበሰበ፤ ሕዝብ ሁሉ ይሰግድለታል። ቅዱሳኑ ግን ሳይሰግዱ ቆሙ፤ በዚህም ምክንያት ተቆጣ። ወታደሮቹን፥ "እነዚህን ቅዱሳን ምን እናድርጋቸው?" አላቸው። "ጌታችን ንጉሥ ሆይ፥ ሥጋቸውን አንድንበላው ስጠን" አሉት። ንጉሡ፥ "የሰው ሥጋ አይበላም፤ ግን የሚገባውን ፍረዱላቸው" አለ። ወታደሮቹ፥ "ሊሞቱ ይገባል፤ ለንጉሥ አይሰግዱ፥ ለክብሩ አይታዘዙ" አሉ።

(89ᵘ) ከዚያ፥ (ንጉሡ) ከቅዱሳኑ አምስቱን ታላላቆቻቸውን በስም እየጠራ ወታደሮቹ እጃቸውንና እግራቸውን እንዲቆርጡና ከገበያ ወስደው በድንጋይ እንዲወግሯቸው አዘዘ። ወታደሮቹ በንጉሡ ታዘው ወጡና ቅዱሳኑን ሁሉንም ወደ ገበያ ወሰዷቸው። እንዳዘዛቸው ከነሱ ውስጥ አምስቱን መርጠው እጃቸውንና እግራቸውን ቈረጧቸው።

ከቆሙት ማህል አንድ ወንድም በድንጋይ ሲወግሯቸው ሲያይ፥ "ልበ ትሑትንና የዋህን እግዚአብሔር አይንቅም"[233] ብሎ ተስፈንጥሮ ከማህላቸው ወደቀ። አብረው ወገሩት ፮ ሆኑ። ሰማዕትነታቸውን ጥር ፲፮ ቀን በጌታ ሰላም ፈጸሙ፤ አሜን።

ከዚያ፥ የተረፉትንና የቀድሞዎቹን ቁርጦች፥ እንዲጠብቋቸው በዘበኞች እጅ አኖራቸው።

የሞት ፍርድ

(89ᵑ) ደግሞ ከጥቂት (ጊዜ) በኋላ፥ መልእክተኞቹ እንደታዘዙት ቅዱሳኑን አምጥተው ከንጉሡ ዘንድ አደረሷቸው። (ንጉሡ) በዚያን ጊዜ በምድረ ፈራኅ ነበረ። ከፊቱ አቆሟቸው፤ "ለንጉሡ ስገዱ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "እኛ ለሰማያዊ ንጉሥ ካልሆነ ለንጉሥ፥ ለምድራዊ ንጉሥ፥ አንሰግድም" አሉት። ንጉሡ ሠራዊቱንና የደብተራውን ካህናት ፍርድ እንዲሰጡ አዘዘ። የሞት ፍርድ ፈረዱባቸው። ንጉሡ ቅዱሳኑን፥ "ካህናቱ የሚፈርዱባችሁን አትሰሙምን?"[234] አላቸው። ከቅዱሳኑ ነገረ ፈጆቹ የሆነው ፩ዱ፥ "ካህናቶችህ ምንድን ናቸው? እንደ ኤልዛቤል ካህናት አይደሉምን?" አለው።[235]

ይሽንን ሲላቸው ልባቸው በቁጣ ተቃጠለ። ንጉሡ እጃቸውንና እግራቸውን እንዲቆርጧቸው በቁጣ አዘዘ። ወታደሮቹ ንጉሡ እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ የእጃቸውንና የእግራቸውን ጫፍ ጫፉን ቈረጡና ከደጅ አውጥተው ጣሏቸው። ቍጥራቸው ፲ ነበረ። እዚያ ሰማዕትነታቸውን በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ይሁን፤ ለዘለዓለምም ይጠብቀን፤ አሜን፥ አሜን።

(90ᵘ) ከዚያ፥ ንጉሡ በጠባቂዎቹ እጅ ያሉትን የቅርቦቹንም የሩቆቹንም ከ፩ ቦታ እንዲሰበስቧቸው አዘዘ። ፩ዱን ወንድም ጠባቂው ልብሱን ገፍፎ ከላዩ ላይ ከአንዲት አስኬማው በቀር ምንም ሳያስተርፍ አንገቱን ከጉልበቱ ጋራ በቀበቶው አስሮ አመጣው። እሱ ግን ከቁርጦቹ ውስጥ ስለነበረ፥ ከተሰበሰቡበት ዘንድ ሲጥለው ተቈጣጣሪው አልቀበልህም

233. መዝ 50፡ 17/19።

234. የጲላጦስን ቃል ሲጠቅስ ነው፤ ማቴ 27፡ 13።

235. ኤልዛቤል የእሥራኤልን ነቢያት ያስፈጀች የእስራኤል ንጉሥ የእክዓብ እቴጌ ነች፤ 1 ነገሥ 18፡ 4።

አሰው፤ እዚያው ተወው። አውሬዎቹ በሕይወት ያሉትን ስዎች ከቤት ሲጎትቱ እሱን ግን ሳይነኩት እዚያው ሶስት ቀን ቆየ። በጣሉት በአራተኛው ቀን እዚያው ስማዕትነቱን በጌታ ሰላም ፈጸመ፤ ጸሎታቸው ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን÷ አሜን÷ አሜን።

ለመቀጣጫ በእምስት ከተሞች ተወገሩ

(90ᴬ) ከዚያ÷ ይኽ ተንኮለኛ ከልቡ ምርረት ብዛት ከቅዱሳን ፅቱን መርጦ ከአምስት አገሮች ወስደው÷ በዚያ ሀገር ያሉ ስዎች እንዲፈሩና ቅዱሳኑን እንዳይቀበሏቸው÷ እጃቸውንና እግራቸውን ቆርጠው በድንጋይ እንዲወግሯቸው አዘዘ። ወታደሮቹ ትእዛዝ ተቀብለው ቅዱሳኑን አንዱን ዋስል÷ ሁለተኛውን ድድኖ÷ ሶስተኛውን ወሰቃ÷ አራተኛውን ብራራ÷ አምስተኛውን የጋድ ወስደው እነዚያ ሀገሮች ውስጥ እጃቸውንና እግራቸውን ቈረጧቸው፤ በድንጋይ ወገሯቸው። ሰማዕትነታቸውን በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን÷ ትጠብቀንም፤ አሜን።

ብርሃን ወረደ

(91ᵁ) ከዚህ በፊት ከቤተ ክርስቲያን የተቀበሩትን ቅዱሳንም (ከመቃብር) አውጥተው በድንጋይ እንዲወግሯቸው አዘዘ። ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው አደረጉ። በዚህ ምክንያት በመንግሥቱ ብሔሮች ሁሉ ትልቅ ፍርሃት ሆነ። ንጉሡ ለነዚህ ጥቂት መንጋ በሆኑ በቅዱሳን ዘንድ በቀር ክሕደቱን እንደ ከሐዲው እንደ ዲዮግልጥያኖስ አልገለጠም። "እግዚአብሔር አማሌቅን ዘር ማንዘራቸውን በድብቅ እጅ ይመታቸዋል"[236] ተብሎ እንደተጻፈው እግዚአብሔርም ሲመታ አይገልጽም። እግዚአብሔር እንዴት እንደመታ (እነሆ)፤ ቅዱሳኑን ባሠቃያቸው ጊዜ እንደሚበተን የወናፍ ምድጃ አሳት ዓይነት አሳት አመጣ፤ በድንኳኑ ላይም ታየ፤ እሱና ሠራዊቱ ግን ተደስተው÷ "ብርሃን በእኛ ላይ ወረደ" አሉ።[237] ከሊቃውንቱ አንዳንዶቹ÷ "ብርሃን አይደለም፤ ይህ እንዲያውም የእግዚአብሔር የቁጣው ምልክት ይመስላል። ይኽ ሰው (91ᴬ) የእግዚአብሔርን ባሮች ስላሠቃያቸው በላያችን ላይ የሚመጣብንን መቅሠፍት እንዴትና ምን (እንደሚሆን ምን) እናውቃለን?" አሉ።

ታላቅ ተስቦ በንጉሡ ሰፈር

ይኽንን እያስቡ ላለ በዚያው ዓመት ከእግዚአብሔር የታዘዘ ታላቅ ተስቦ ተላከ፤ ስዎች እንደዚህ ሆኖ አያውቅም አሉ። (በንጉሡ) ሰፈር ብዙ ሞት ሆነ።[238] አሱም ከዚያ ተነሥቶ አጉላ ወደምትባል ወደ ሌላ ሀገር ሄደ።[239]

---

236. *ዘፀ* 17፡ 13-16?

237. *በተአምረ ማርያም* ውስጥ ተጽፏል፤ እዚህም ከመግቢያው ላይ ጠቅሼዋለሁ።

238. *በተአምረ ማርያም* ውስጥ ተጽፏል፤ "በዚያም ዘመን ሊገልጹት የማይቻል የቸነፈር በሽታ በሰው ላይ መጣ።" *ተአምረ ማርያም። በግዕዝና በአማርኛ፣* አዲስ አበባ 1961 ዓመተ ምሕረት፣ ገጽ 167፤ *Getatchew Haile,* "Power Struggle in the Medieval Court of Ethiopia: The Case of Bätergela Maryam," *JES,* vol. 15 (1981), p. 44.

239. Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, pp. 55, and 93-94.

በማነቆ ከታሰሩ ጋራ ስለ ሃይማኖት ክርክር

በዚያው ዘመን ቅዱሳኑን እንደታዘዙ አመጡና በማነቆ እንደታሰሩ ከንጉሡ ዘንድ አደረሷቸው። መነኮሲቶችም አብረዋቸው ነበሩ። ሌሎቹንም ከምድረ ማያ ኬር ወሰን የሚባለው የሀገሩ ሹም አመጣቸው። ከንጉሡ ዘንድ ላያገቧቸው ከእጠባቡ አስቀመጧቸው። ከዚያ፡ ስለ ሃይማኖት እንዲከራከሩ የደብተራውን ካህናት ወደነሱ ላካቸው። መጡና ጥያቄ አቀረቡላቸው፤ እነሱም ለጥያቄያቸው መልስ ሰጧቸው።

ከዚያ፡ በማይረባ ነገር ለመነዝነዝ፡ የሚከራከረውን ፩ዱን ወንድም፡ "ስምህ ማነው?" አለው። ያ ወንድም፡ "ስሜ (92^{ሀ}) ድምያኖስ ነው" አለው። የሚከራከረው፡ "ስምህ ዲያብሎስ ይሁን" አለው። ሁለተኛውንም፡ "ስምህ ማነው?" አለው። "ስሜ ስምዖን ነው" አለው። እሱንም፡ "ያንተም ስምህ ሲሞን ይሁን" አለው።[240] ሶስተኛውን፡ "ስምህ ማነው?" አለው። እሱም፡ "የኔ ስም ዘአዶናይ ነው" አለው። የሚያሞካሽበት ሲያጣ ተወው። ከዚያ፡ ዘአዶናይ የሚባለው ወንድም፡ "ጠላት እግዚአብሔርን ተሳደበ"[241] አለ። ይሽንን ሲለው ሄዶ ለንጉሡ ነገረው።

"እንዱ እግሬ ተረስቷችሁ ቋንጃውን አላወጣችሁምና ተመለሱ"

ያ ተንኮለኛ፡ "ጠላት እግዚአብሔርን ተሳደበ" ያለውን ወንድም ምላሱን፡ አፍንጫውን፡ ጆሮውን እንዲቆርጡት፡ የሸኮናውን ቋንጃዎችም እንዲያወጧቸው አዘዘ። ሌሎችን ወንድሞች ግን መላሳቸውንና አፍንጫቸውን እንዲቈርጧቸው፡ የሸኮናቸውን ቋንጃዎችም እንዲያወጡ አዘዘ። ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው አደረጉ። የቅዱሳኑን የሸኮናቸውን ቋንጃዎች ሲያወጡ የ፩ዱን ወንድም ፩ እግር ረስተውት ኖሮ በልቡ አሰበና፡ "ሐዋርያ ጳውሎስ (92^{ለ}) የከርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወኛል? ሥቃይ ወይስ ችግር?"[242] አለ። ይሽንን ብሎ የንጉሡን ወታደሮች ጠራቸውና፡ "እንዱ እግሬ ተረስቷችሁ ቋንጃውን አላወጣችሁምና ተመለሱ" አላቸው። ይሽንን ሲሰሙ ገረማቸው። ተመልሰው ቋንጃውን እወጡለት። ፩ዱ ወንድም መላሱን፡ አፍንጫውን፡ የሸኮናውን ቋንጃ ሲቆርጡት ደሙ ስላላቆመ አዚያው ሰማዕትነቱን በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

በአህያ ጭኖ ወደ ብሔረ ኤፋት--በሥቃይ

የተረፉትን ወታደሮቹ ታዝው ወደ ብሔረ ኤፋት ሲሰድዷቸው ደማቸው እየወረደና በቁስላቸው ውስጥ ስንጣሪ እየገባ እንደ ስልቻ በአህያ ጭነው ወሰዷቸው። አህዮቹንም እስኪፈረጥጡ ድረስ ያሮጧቸው ነበረ። ከነሱ ውስጥ ክብርተ ማርያም የምትባል አንዲት መነኮሲት በዚህ ሁኔታና በብዙ ሥቃይ ሰማዕትነቷን ፈጸመች። ወታደሮቹ ሬሳዋን አንሥተው ከገደል ወረወሩት። ጸሎቷና በረከቷ ከኛ ጋራ ይሁን፤ ይጠብቀንም። አሜን፡ አሜን።

---

240. "ሲሞን መሠርይ" የመንፈስ ቅዱስን ጎይል ከሐዋርያት ላይ በገንዘብ ገዝቶ ለጥንቆላው ሊጠቀምበት የሞከረ ጠንቋይ ነበር፡ የሐ ሥራ 8፡ 9-24።

241. 2 ዜና መዋ 32፡ 17፤ "አዶናይ" በዕብራይስጥ የእግዚአብሔር ስም ነው፤ "ጌታ" ማለት ነው።

242. ሮሜ 8፡ 35።

ከወንድሞች ውስጥ ሌሎች ፪ም (93ᵘ) በዚያው ሥቃይ ሰማዕትነታቸውን ፈጸሙ። ሬሳቸውን ከመንገድ ላይ ጣሉት። ደግሞ ከሀገሩ ኬላ ሲደርሱ ከነሱ ፫ቱ ሰማዕትነታቸውን እዚያ ፈጸሙ። ሬሳቸውን ከዱር ጣሉት፤ "የጻድቃንህን ሥጋ ለምድር አራዊቶች አደረጉ፤ ደማቸውንም እንደ ውሐ በኢየሩሳሌም ዙሪያ አፈሰሱ። የሚቀብራቸው አጡ"[243] የሚለው የነቢዩ ቃል በነሱ ላይ ተፈጸመ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን÷ አሜን።

የተረፉትን ዓጋት ከምትባል ሀገር አመጧቸውና እያንዳንዳቸውን በየአረሚው ቤት በተኗቸው። እዚያ በንጉሡ ትእዛዝ አባላቸውን ሲቈርጧቸው ከገፈፏቸው ጀምሮ÷ ካንዲት የአስኬማቸው ብጣሽ በቀር ምንም ሳይኖራቸው በቀኑሉ በሽታ ላይ በምግብ መቸገርና በልብስ ማጣት በታላቅ ገድል ኖሩ። ያችም የአስኬማቸው ብጣሽ የሥቃያቸውን ደም ጠግባ ነበረ። እዚያ ወድቀው (93ᵃ) ብዙ ዘመን ኖሩ።

አረሚዎቹ ፍርፋሪ ሲሰጧቸው ሲውጡ ምላሳቸውን እያመማቸው ነበረ። ዱቄት ብጤ የሰጧቸው እንደሆነም መጠኗ እጅ የሚሞላ ቢሆን ነው። እጅ የሚሞላ የሰጧቸው ቀን በውሐ (በጥብጠው) ስለሚጠጡት ትልቅ ደስታ ይሆንላቸው ነበር።

ከነዚህ ቀኖች በኋላ÷ ትንሽ መውጣት መግባት እንደቻሉ÷ ከአረሚዎቹ ማሳ ቅጠላ ቅጠል ለመሰብሰብ ሲሄዱ ስንጣሪ ቍስላቸውን ይጓጉጠውና ወደ ኋላቸው ይወድቃሉ። እንደገና ደግሞ ቀስ ብለው ይሄዳሉ። በእንደዚህ ያለ ጣር ይሠማሩና ይመለሱ ነበረ። አንጣራ የምትባል የምድር ቅጠል አግኝተው÷ ምግባቸው ሆነቻቸው። ደግሞ የቁልቋል ስር እየቆፈሩ እንቅብ÷ ሰፈድ እና የመሰለውን ይሰፉና ያገኙትን ያህል ይገበዩበታል። ከዚች የአንጣራ ቅጠል ጋራ በደረሰበት ጻማ (94ᵘ) ሁሉ ታጋሽ የሆነው ዘእዶናይ የሚባለው (ወንድም) አለኝታ ሆናቸው።

አንድ ቀን ወጥቶ ሰፍላኒታቸው የሚሆን ለመፈለግ[244] ከጓደኛው ጋራ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ። እግዚአብሔርን ከምትፈራ ከአንዲት ሴት (ቤት) ደረሱ። በጎ ሥራ ሠራችላቸው፤ ካሳት ሰጠቻቸው። ወደ መኖሪያቸው ሲመለሱ አንድ ተሳዳቢ ሰው አግኝቷቸው÷ "ከየት ናችሁ?" አላቸው። ማንነታቸውን ሲነግሩት÷ የቅዱሱ ልጆች መሆናቸውን ዐወቀ፤ ከዚያ÷ በቁጣ ተነሥቶ ከሎሌው ጋራ እስኪደክሙ ድረስ በበትርና በዱላ ደበደባቸው። ይኸንን የደረሰበትን ሁሉ ታጋሽ ወንድም እንደገና ብትር እንሥቶ ራሱን ሲመታው ደሙ በላዩ ላይ ፈሰሰ። ሴትየዋ ሰጥታቸው የያዙትን÷ ያላቸውን ሁሉ÷ ምንም ሳያስተርፍ ወሰደባቸው። ቁጣውን አስተንፍሶ እንደወደቁ ትቷቸው ሄደ።

ወንድሞቻቸውን ሁሉ እንደዚሁ ያደርጉባቸዋል፤ የቅዱሱ ልጆች መሆናቸውን ሲያውቁ በመንደርም ሆነ በመንገድ÷ (94ᵃ) ወይም በዱር ይደበድቧቸዋል፤ ከብዙ ችግር ላይ ይጥሏቸዋል፤ እንደከብት ዕራቁታቸውን እስኪሆኑ ድረስ ልብሳቸውንና ገንዘባቸውን ይወስዱባቸዋል። አንዳንድ ቀን ወደ ሀገረ ገዢዎቻቸውና ወደ ታላላቆቻቸው ወስደው በብዙ ጭንቅ ይነዘንዟቸዋል። "ሰዎች እንደ ገዢያቸው ይሆናሉ" (ተብሎ) እንደተጻፈው[245]÷ ገዢው[246] የሚፈልገው እንዲህ እንዲሆን ነው።

---

243. መዝ 79: 2-3።
244. ለልመና።
245. ሲራ 10: 2።
246. ንጉሡ።

ለጸሎትና ለመቊረብ ወደ ቤተ ክርስቲያንም ሲመጡ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ፡ "እንዳትሳላቱና እንዳትደናቀፉ ይኸንን ነግሪያችኋለሁ። ከምኵሪባቸው ያስወጧችኋል። ነገር ግን የገደላችሁ ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያገባ ይመስለዋል"[247] ያለው ቃል ይፈጸምባቸው ዘንድና "ስለ ስሜ በሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ"[248] ያለው ይደርስባቸው ዘንድ እየሰደቡና እያሸሟጠጡ ወደ ውጪ ያስዟቸዋል፤ ይኸ የሚደርስባቸው ስለዚህ ነው።

ያ የሚደርስበትን ሁሉ ታጋሽ ወንድምም (95^{v}) ከጓደኛው ጋራ በአስጨናቂ ድካም ፍርድ ለሚጸድቀው አስኪመጣ ድረስ ግፋቸውን ተሸክመው ለተገፉ የሚበቀል እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ መኖሪያቸው ተመለሱ። የመነኮሳት ሕጋቸው እንደዚህ ነው። "በየቀኑ ሞትን ይቅመስ፤ ስቅላቱንም ይታገሥ"[249] ይላልና። በእንደዚህ ያለ ገድል ብዙ ዓመት ቆይተው በጌታ ሰላም ምስክርነታቸውን እዚያው ፈጸሙ። ቍጥራቸው ፮ ነው። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ያ የደረሰበትን ሁሉ ታጋሽ ወንድም ከአንዲት መነኵሲት ጋራ ቀርቶ ነበረ። ከሕመም መኝታቸው ተነሥተው ለመውጣትና ለመግባት እስኪያቅታቸው ድረስ ፹ ቀን ያህል ከትልቅ በሽታ ወደቁ። ከዚያ፡ እግዚአብሔር ከወንድሞቻቸው ዘንድ እርዳታ አመጣላቸው፤ (የመጡት) ይላላኳቸው ጀመረ። ከዳኑም በኋላ ወደ ወንድሞች ማኅበር ወሰዷቸው። እሷም ገድሏን ከማኅበርተኞቿ ጋራ በአበው ሕግ በመልካም ጻማና በጣፋጭ ገድል ፈጸመች። ከስዎችና ከስይጣናት የመጣ ብዙ ሥቃይ አሳልፋ (95^{A}) በጌታ ሰላም አረፈች። ጸሎቷና በረከቷ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ይሁን፤ አሜን።

ያ ወንድም ግን ከዚህ ተንኮለኛ ቀጥሎ ከሚመጣው ሌላ ንጉሥ[250] ገና ብዙ ቅጣት ስላለበት እስከ ጊዜው ድረስ እግዚአብሔር እየረዳው ኖረ።

ባሊጋራን ለማጥቃት የጠቀመ ዓዋጅ

ከዚያ፡ ይኸ ተንኮለኛ በቅዱሳኑ ላይ ሊያጠብባቸው እና የሚቀበሏቸውም ፍርሃት እንዲያድርባቸው አስቦ፡ አንዲህ ሲል ዓዋጅ እንዲያስለፍፍ አዘዘ፤ "እነሆ፡ ደቂቀ አስጢፋኖስ የተገኙበት ቤቱ ይዘረፍ፤ ገንዘቡ ይውደም፤ የቀበሌው ርስትም ለባዳ ይሁን። በጠዋትም ሆነ በምሽት ወደኛ ሲያመጧቸው እኳኑን ላይገድሉ መሥዋዕት አያሳርጉ። ይኸንን ላታደርጉ (ብታሳርጉ) መሥዋዕታችሁ የረከሰ ይሁን፤ እኔም ባላደርግ መንግሥታችን ለባዳ ይሁን።"[251]

ይኸንን ሲል ጊዜ እውነትን (96^{v}) ለሚፃረሩ ሰዎች ሰበብ ሆናቸው። ጉዳይ ያስጨነቃቸው ሁሉ (ማላበቢያ) እነሱን ይፈልጉ ነበረ። የንጉሡን ፊት

247. ዮሐ 16፡ 1።
248. ማር 13፡ 13።
249. ?።
250. "ከበእደ ማርያም"።
251. ጦማረ ትሰብእት በሚል ርእስ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ "እኔም እምላለሁ" ይላል፤ Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity of Emperor Zär'a Ya'əqob (Ṭomarä Təsbə't)*, *CSCO*, text vol.522/95, pp. 64, 79 and 112.

ማግኘት ሲያቅታቸው እነሱን ይፈልጋሉ፤ በርስት ክፍያም ሆነ ወይም (በሌላ) ነገር አንዱ በሌላው ላይ ሲያይል (ማሸነፊያ) እነሱን ይፈልጋል፤[252] መኳንንት ከመኳንንት ጋራ፥ ሹም ከሹም ጋራ፥ ባሪያ ከነፃ ጋራ፥ ባሪያ ከጌታው ጋራ፥ ሎሌ ከአገረ ገዢ ጋራ፥ ዲያቆኖች ከቄሶች ጋራ፥ ደኻ ከሀብታም ጋራ ሲጣሉ እነሱን ይፈልጋሉ። በተለየም በየገዳማቱ ያሉ መነኮሴዎች ገዳማቸው እንዲጸናላቸው ሲሉ (ደቂቀ አስጢፋኖስ) ያሉበትን ሲያውቁ ደም ለማፍሰስ ይሮጣሉ። ምግብ አልጫ ሲሆን በጨው ያጣፍጡታል፤ እንደዚሁ ለጉዳያቸው ጨው ሆኑላቸው።[253]

ከዚያ፥ ፍሬ ሊባኖስ የሚሉት ከካህናተ ደብተራ የሆነ የሰይጣን መልእክተኛ ተነሣ። የብሔሩ ስም ዓለት ነው።[254] (96ᴬ) የዚህ የሰይጣን መልእክተኛ ዘመድ የሆነ ፩ ሰው በዚያ ብሔር ተቀብሎ ያስቀመጣቸው ቅዱሳን ነበሩ። (ዘመዱ) በነገር ያይልበት ነበረ። ከሱ ጋራ ሲጣላ ጊዜ፥ ቅዱሳኑን እንዲይዝ መልእክተኞች እንዲሰጠው ንጉሡን ጠየቀው።

መልእክተኞች ሰጥተውት ሄደ። ቅዱሳኑ ካሉበት መጥቶ ፪ቱን ያዛቸውና ከንጉሡ ዘንድ አመጣቸው፤ (ንጉሡ) ያን ጊዜ በመንግሥቱ መካን በአንጣ[255] ነበረ። ከንጉሡ ፊት አቆሟቸው። "(ለንጉሡ) ሰገዱ፤ የመምህራችሁንም ስም ስደቡ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "እኛ አንሰግድም፤ መምህራችንንም አንሰድብም፤ ቅዱስ ነው" አሉ።

ንጉሡ የቃላቸውን ፍጻሜ ሲያውቅ ወዲያው እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን አንዲቈርጧቸው፥ በድንጋይም አንዲወግሯቸው አዘዘ። ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው አደረጉ። ሰማዕትነታቸውን አዚያው በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፥ አሜን፥ አሜን።

የምድረ ፀጋም ኢትዮጵያውያን

ይኸ ተንኮለኛ ቅዱሳኑ በምድሩ እንዳይኖሩ ባጠበበባቸው ጊዜ አስከ (97ᵇ) ብሔሩ ዳርቻ፥ (ነዋሪዎቹ) ቤታቸው ከዛፍ ላይ ከሆነው አስከ ምድረ ፀጋም (ግራ ምድር) ደረሱ። (የዚህ አገር ሰዎች) አገርና አገር፥ የቅርብና የቅርብ መዋጋት ልማዳቸው ነው። አንዳንዶቹ ምድር ቆፍረው ለሰው፥ ለከብት፥ ለንብረት መኖሪያ ዋሻ ያበጁና ከዋሻው በላይ ቤታቸውን ይሠራሉ። ጦርነት ሲያይልባቸው በየሸንቁሮቹ ይገባሉ። ወደ ክርስቲያኑ ምድር ሲዘምቱ ወንድ ወንዱን ይገድላሉ፤ የዓመትም የመንፈቅም ሕፃን አንኳን አይተውም፤ መነኮሴም ካህንም አይምሩም። ቤተ ክርስቲያናቸውን ይመዘብሩታል፤ ሴቶቻቸውንና ንብረታቸውን ሁሉ ይማርኩና ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ። (ከነሱ ውስጥ) አንድ ሰው የሰው ግድያውን ከዓሥር ካደረሰ አንገቱና እጆቹ ላይ ቀይ ፈትል ያስራል፤ የደም ምልክት ነው።

(የምድረ ፀጋም ሰዎች) በሌላ ላይ ይኸንን ሲሠሩ፥ ቅዱሳኑን ተቀበሏቸው፤ የሚገባውን ደግ ሥራ (ሁሉ) ሠሩላቸው፤ "ከሀገራችን ኑሩ" አሏቸው። እግዚአብሔር (97ᴬ) ለቅዱሳኑ እስከ ጊዜው ዕረፍት ስለሰጣቸው

252. ደግመው!

253. ቆላ 4: 6።

254. "ምድረ አላት" Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, p. 90.

255. ? አጉባ።

እመሰገኑት። እዚያ ኖሩ፤ ከተበተኑበትም ተሰባሰቡ። ከዚያ ሀገር ሰዎች ከወንዱም ከሴቱም ብዙዎችን ወደ ትምህርታቸው መለሱ። (እንዲያውም) ከዓለም ወጥተው (መንኮሰው) ሰማዕት እስከ መሆን ደረሱ። እግዚአብሔር ያንን ሀገር ለቅዱሳኑ በሚፈልጉት ሁሉ ከፍቶላቸው ቤተ ክርስቲያን እስከ መትከል ደረሱ። የወንድሞቻቸውንም ተዝካር አወጡ።

ደግሞ÷ ያ ተንኮለኛ እጓብ[255] በምትባለው ምድር በነበረበት ጊዜ ቅዱሳኑን እንደታሰሩ ወደ እሱ እመጧቸው። (መምጣታቸውን) ለንጉሡ ነገሩት። እሱም አጠገቡ እንዲያኖራቸው አዘዘ። እዚያ ያባቶቻቸውን ሥርዓት እንደጠበቁ በትልቅ በሽታ (ሰማዕትነታቸውን) ፈጸሙ። ቍጥራቸው ፲፰ ነው። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

"ገድለ" መርቆርዮስ

ከዘመን በኋላ÷ ቅዱሳኑ በስደት በምድረ ቀወት[256] ከዋሻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ÷ ፩ የሰይጣን መልእክተኛ ቅዱሳኑን በገዳማቸው ካስቀመጧቸው ሰዎች ጋራ ሲጣላ ጊዜ÷ ከሀገሩ ሹም ዘንድ ሄዶ (98[ሀ]) ቅዱሳኑ ያሉበትን--እነዚህ (እተጣላቸው) ሰዎች ገዳም ውስጥ (መኖራቸውን)--ነገረው።

እገሪ ገዢው ሎሌውን ሰጥቶት (ሊያመጣቸው) ሄደ። ቅዱሳኑን ያዛቸው፤[257] ወስዶ ከንጉሡ እደባባይ ሲያደርሳቸው ከሰቀላው ስፈር አቆሟቸው። ለንጉሡ እንዲሰግዱ÷ መምህራቸውንም እንዲሰድቡ አዘዟቸው። ፩ዱ መርቆርዮስ የሚባለው ወንድም÷ "እኛ እንሰግድም፤ መምህራችንንም እንሰድብም፤ ቅዱስ ነው" አለ። ይኸንን ወንድም ከንጉሡ ፊት ሲያቆሙት (እና ሲቀጡት) ይኸ እምስተኛው ነው፤ መጀመሪያ÷ ያባታችንን ሀፅም ሲያፈልስ በግድም ኬላ ላይ የተያዘ ጊዜ ፱ ገርፈው ለብቻው እንፈር ከምትባል ሀገር ወስደውት ነበረ። ሁለተኛ÷ ጋስ[258] ከምትባል የአረሚዎች ብሔር ወስደውት ነበረ። ሶስተኛ ሲያቆሙት ቅጣቱ ብዙ ነበረ። አራተኛ እቁመውት ቅዱሳኑን÷ "እባታችሁ የት ነው ባሏቸው ጊዜ÷ ለንጉሡ ሎሌዎች "መምህራችን የጌታን ሥቃይ ተካፍሏል" ሲላቸው (98[ለ]) አፍንጫውንና መላሱን ቈርጠው ቋንጃውን እውጥተውበት ነበረ። እነሆ እሁን እምስተኛው ጊዜ ነው። "እልሰግድም÷ እልሰድብም" ሲል ጊዜ÷ ይህ ተንኮለኛ ዓይኑን እንዲያወጡት አዘዘ። ወታደሮቹ ታዝዘው ዓይኑን እወጡት። ብረት አግለው ከውስጡ ጨመሩት። እብረውት ያሉትንም እንደዚሁ አደረጉባቸው። ቍጥራቸው ፬ ነው። ከሰፈሩ ውጪ ጣሏቸው። እዚያ እንደወደቁ በብርድ÷ በመራቆት÷ በረኃብ÷ በውሐ ጥም÷ በብዙ ሥቃይ እንድ ዓመት ቆዩ። ሰዎቹም ይሥቁባቸው ይሳለቁባቸው ነበረ። እንዱ ሰማዕትነቱን እዚያው በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

---

256. ይህ ቦታ ዛሬም "ቀወት" ነው የሚባለው፤ ቀወት፡ መሐግል፡ ሰርማት የአንድ አስተማሪ (የአቡነ ቀውስጦስ) ሀገረ ስብከት ስለነበሩ ተቀራራቢዎች ናቸው/ነበሩ ብሎ መገመት ይቻላል፤ Getatchew Haile, "The Monastic Genealogy of the Line of Täklä Haymanot of Shoa," p. 17.

257. ግዕዙ የሚለው "አዘዛቸው" ነው፤ "አዘዘሙ" ("አዘዛቸው") እና "አንዘሙ" ("ያዛቸው") ለማሳሳት ይመቻሉ።

258. ጋሳ መሆን አለበት።

የተረፉትን ወንድሞቻቸው ወስደው ከምእመናን ዘንድ አኖሯቸው። ከ ... ዓመቶች በኋላ ቆገት ካሉት ወንድሞቻቸው ማኅበር ሰብስበዋቸው፥ (እዚያ) እስከ ጊዜው ተቀመጡ።

የፈጸጋር መልእክተኞችና መነኮሲቷ

ከዘመናት በኋላ፥ (99[ሀ]) የቅዱሳኑ ማኅበር ፈጸጋር በምትባል ሀገር ወዳሉ ወንድሞች ቢልኩ፥ እዚያ የንጉሡ መልእክተኞች ያዟቸው። አንዲት መነኮሲትም አብራቸው ነበረች። "ለንጉሡ ስገዱ፤ የመምህራችሁንም ስም ስደቡ" አሏቸው።

ቅዱሳኑ፥ "እኛ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አንሰግድም፤ መምህራችንንም አንሰድብም፤ ቅዱስ ነው" አሉ። ከዚያ፥ እዚያው ደበደቧቸው፤ ያቺንም ምእመንት በአለንጋ ገረፏት፤ ብዙ አስቸገሯት።

እናቷ ቅዱሳኑንና ልጇን እንደያዟቸው ስትሰማ፥ "እኔም ክኑሱ ጋራ እሞታለሁ፤ ልጄንም ሃይማኖቷን እንዳያስክዷት አበረታታለሁ" ብላ ወደ እነሱ ሄደች። ይኸንን ብላ ክኑሱ ጋራ ተደባለቀች። እራቱንም በአንድነት ወስደው ከንጉሡ ፊት አቆሟቸው። ወታደሮቹ ቅዱሳኑን፥ "ለንጉሡ ስገዱ፤ መምህራችሁንም ስደቡ" አሏቸው። እነሱም እንደበፊቱ መለሱላቸው። ንጉሡ፥ (99[ሁ]) "ሥራችሁ (እምነታችሁ) ምንድን ነው? ለማርያምና ለአንድ ልጁ መስቀል አትሰግዱምን?" ሲል ላከባቸው።

ቅዱሳኑ፥ "እንዴታ! ለማርያምና ለሰላም መስቀል እንሰግዳለን" አሉ። "ለሰላም መስቀል" ሲለው መልእክተኛው ጥፋት ያደረገ መስሎት (ለጓደኞቹ)፥ "የእስላም መስቀል አለ" አላቸው። "ለሰላም መስቀል" ስላለው፤ መልእክተኛው፥ "ለመስቀል አትሰግዱምን ብለው፥ ለእስላም መስቀል አለኝ" ብሎ፥ በዚህ ነገር በውሸት ንጉሡ ላይ ከሰሰው።

መድኃኒት የማጠጣት ቅጣት ተጀመረ--"ደሙ ... በሱ በራሱ ላይ ነው"

ይኸ ተንኮለኛ ያንን "ለሰላም መስቀል" ያለውን ከመድኃኒት ቤት ወስደው መድኃኒት (ኮሶ) እንዲያጠጡት፥ የቀሩትን ከገበያ ወስደው አፍንጫቸውን ቁርጠው በድንጋይ እንዲወግሯቸው አዘዘ።[259] ደግሞ ንጉሡ፥ "ሕዝቦችን ሆይ፥ በከንቱ ሲሞቱ ስሙ፤ ደማቸው በራሳቸው ላይ ነው" የሚል እንዲያሰሙ አዘዘ። ያም ከመነኮሲቶቹ ጋራ ያለ ወንድም እንዲህ ሲል አሰማ፤ (110[ሀ])[260] "እኛንም ስሙ፤ ደሙስ በውሸት ሲገድለን በሱ በራሱ ላይ ነው። ሰማይም ምድርም ይስሙ፤ እነሆ፥ በትራችሁም፥ ግርፊያችሁም፥ ሠይፋችሁም፥ ጦራችሁም ይሻራል፤ ይኸም የድንጋይ ወገራ ያልፋል። ለእኛ አምላካችን አለን፤ የቁጣው በትርም ለኃጢአተኞች ይሆናል። የቅጣቱ መቅሠፍትም የማያልፍና የማይሻር አሳት ነው" አለ።

---

259. በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ኮሶ መጠጣት የታወቀ ነበር፤ Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity of Emperor Zär'a Ya'əqob (Tomarä Tæsbə'ət)*, p. 91.

260. መጽሐፉ ላይ ገጽ የጻፈበት ሰው እዚህ ላይ ቀጥር ዘለለ፤ 100 ማለት ነበረበት።

ከዚያ፥ ወደነዚያ መነኮሲቶች መለስ ብሎ እንዲህ ሲል ምዕዳን አሰማቸው፤ "ጨክኑ፤ ልባችሁ ይጠንክር፤ እንዳትክዱ። ዛሬ የእሳቷን ባሕር የምንሻገርባት ቀን ናት፤ ዛሬ ተስፋችንን የምናገኝባት ቀን ናት።"[261]

ከዚያ፥ ወታደሮቹ ንጉሡ እንዳዘዛቸው አደረጉ። እፍንጫቸውን ከከንፈራቸው ጋራ ቈረጡትና በድንጋይ ወገሯቸው። እዚያ መስከረም ፳፮ ቀን ሰማዕትነታቸውን በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

የምድረ ፀጋም ዘመቻ

ከዘመኖች በኋላ ቅዱሳኑ ሙደዌ ከምትባል ምድረ ፀጋም (የግራ ምድር) በነበሩበት ጊዜ በንጉሡ ትእዛዝ በዚያች አገር ላይ ጦር መጣ።[262] (110ʰ) የንጉሡ ወታደሮች ቅዱሳኑን እዚያ አገኟቸው፤ ያዟቸው። ደበደቧቸውና በትላልቅ ማነቆ አስረዋቸው ወደ ንጉሡ ወሰዷቸው። (ሲጓዙ) ከሚያድሩበት ሲደርሱ ወገባቸውን፥ እጃቸውን፥ እግራቸውን፥ በገመድ ያስሯቸዋል። ከንጉሡ እስኪያደርሷቸው ድረስ እንደዚህ ያደርጉባቸው ነበረ። በዓይናቸው ፊት ምሕረት የሌላቸው መራር ሕዝብ ናቸው።

ሲደርሱ፥ ይዘው ከአመጡት ከእንድ ደስክ ጋራ ከንጉሡ ፊት ለፊት አቆሟቸው። ንጉሡ ይሰግዱ እንደሆነ መምህራቸውንም ይሰድቡ እንደሆነ ጠየቀ። መልእክተኞቹ መጡና፥ "ለንጉሡ አትሰግዱምን?" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "እምን፥ እንሰግድም" አሉ። ለንጉሡ ነገሩት። እውጪ በእስራት እንዲያስቀምጧቸው አዘዘ። ያንን ደስክ ግን እንዲገድሉት አዘዘ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ ቅዱሳኑን የሚቆጣጠራቸው ለቀቃቸው። ቅዱሳኑም፥ "እዚህ ምን ያቆየናል? ከለቀቀን፥ ኑ ለቅቀን ወደ ገዳማችን እንሂድ" ተባባሉ።(110ᵘ)[263] ይኸንን ብለው ሄዱ፤ ሲሄዱ ሰርመት ከምትባል አገር ደረሱ፤[264] እዚያ ፩ ወንድም ገድሉን ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

እስላሙ የንጉሡ አማች ጠላት ሆነ

አንድ (ቀን) ሌላ አገረ ገዢ (ተሹሞ) በንጉሡ ትእዛዝ ቅዱሳኑ ካሉበት ሀገር መጣ። የቅዱሳኑ ማኅበር፥ "እንግዲህ ምን እናድርግ? ከቀኝም፥ ከግራም ጠበበብን፤ ወደዚህ (ወደ እዲሱ) አገረ ገዢ እንላከና ደግ ይሁን ክፉ ሁኔታውን እንወቅ" ተባባሉ። ከዚያ፥ ፪ ወንድሞች መርጠው፥ "እግዚአብሔር እንዳቀበላችሁ አነጋግሩት" ብለው ወደ እሱ ላኳቸው። ግን ሰውየው አረማዊ[265] ስለሆነ ሰላም (እንዲሉት) አልላኳቸውም።

---

261. በግዕዙ ሥነ ጽሑፍ መሠረት ሰው ሲሞት ነፍሱ ከክርስቶስ የፍርድ ችሎት የምትሄደው የእሳት ባሕር ተሻግራ ነው።

262. ከንጉሡ ታሪክ ውስጥ የተጻፈው የጻለምት ዘመቻ ሊሆን ይችላል፤ Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, pp. 96-97.

263. ቍጥር 110 ተደገመ።

264. "ሰርማት" እንድ ቦታ "እምነ ፍጥረት፥ የዓቢ ሰርማት" ("ከፍጥረት ሁሉ የሰርማት ሰው ይበልጣል") ይላል፤ EMML 3012, f. 80b, *Catalogue*, vol. VIII, p. የሀገሬው ሰው የደረሰው ይሆናል።

265. "እስላም"።

(መልእክተኞቹ) ወደ አሱ መጥተው፥ "ካንተ ዘንድ ጉዳይ አለን፤ (ለብቻህ እንድናነጋግርህ) ሰዎቹ ካንተ ዘንድ እንዲወጡ ትእዛዝ ስጥ" አሉት። "እሺ" አላቸው። ሰዎቹ ከሱ ዘንድ ዞር አሉ። ጉዳያቸውን ብቻቸውን ሆነው ነገሩት። እሱም አንደ ደግ (ሰው) አዳመጣቸው። የንጉሡ አማች ነበረ።[266]

ነግረውት ሲጨርሱ (110[2ለ]) መኳንንቱ ከፊቱ እንዲሰበሰቡ አዘዘና ቅዱሳኑን፥ "ያላችሁትን ድገሙት" አላቸው። ቅዱሳኑ ክፉ እንደሚሠራባቸው ዐውቁ። "የተናገርነው ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ?" አሉት። ሥራቸውን (እምነታቸውን) ለመኳንንቱ ነገረባቸው። ከዚያ፥ አንዲደበድቧቸው አዘዘ። ሞቱ እስኪባሉ ድረስ ብዙ ድብደባ ደበደቧቸው።

አንዱን ወንድም ወደ ንጉሡ ላከው፤ ሁለተኛውን መሄድ ስለማይችል ተወው። ያንን ወንድም ግን ከንጉሡ እደረሱት፥ ከአስር ቤት አስገቡት፥ አዚያ ሰማዕትነቱን በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን፥ አሜን።

ከዚያ፥ እግዚአብሔር የባሮቹን ደም በቀል በዚያ አረማ አገረ ገዢ ላይ አሳየ። ንጉሡ ወታደሮቹን ልኮ ራሱን ቁረጡት።

ኢባ "ደብረ ብርሃን" ተባለች

ከዘመናት በኋላ ቅዱሳኑ በምድረ ቆገት በነበሩበት ጊዜ ከወንድሞቻቸው ዘንድ ለመድረስ ሲሄዱ ምሕረትን[267] የሚሉት የሰይጣን መልእክተኛ እገኛቸው፤ (111[ሀ]) ይዞ ከአገረ ገዢው ዘንድ ወሰዳቸው። አገረ ገዢው ወደ ንጉሡ እንዲወስዷቸው አዘዘ። ወስዶ ከንጉሡ ዘንድ እደረሳቸው፤ (ንጉሡ) በዚያን ጊዜ ደብረ ብርሃን ብሎ በጠራት በንጉሥ መዲና[268] በሀገረ ኢባ ነበረ።[269] ለንጉሡ እንዲሰግዱ፥ የመምህራቸውንም ስም እንዲሰድቡ አዘዟቸው።

ቅዱሳኑ፥ "እኛ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አንሰግድም፤ መምህራችንንም አንሰድብም" አሉ። ንጉሡ መላሳቸውን፥ አፍንጫቸውን፥ ጆሯቸውን እንዲቆርጧቸው፥ ዓይናቸውን እንዲያወጧቸው አዘዘ፤ ወታደሮቹ አንዳዘዛቸው እደረጉ። እዚያ ፬ ወንድሞች ሰማዕትነታቸውን በእግዚአብሔር ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን። ፭ኛው ግን እስከ ጊዜው ኖሯል።

አግዚአብሔር ግን ይኸንን ተንኮለኛ እና በጠባዩ የሚተባበሩትን በማይታይ ቁጣው በድብቅ ይመታቸዋል። እነሱ ልባቸው በእሳሳቹ የደመናው ጥላ ስር ተጠልለው፥ በስሕተቱ ሕልሞችም ተደልለው፥

---

266. የቀኝ ንግሥቷ የኢቴ ዣን ዜላ እባት ገራድ ምሕማድ ወይም ወንድሟ ማሂኮ ይሆናል፤ Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, pp. 16-17.

267. ግዕዙ የሚለው "ምሕረትን" ነው።

268. "መዲና" ብዬ የተረጐምኩት "ደይም" የሚለውን ቃል ነው፤ "ደይም ዘንጉሥ ስመያ ደብረ ብርሃን"። ምናልባት በአለክንድር ታሪክ ውስጥ "መይድ" የሚለው ይሆናል፤ M. Jules Perruchon, "Histoire des Guerres d"Amda Ṣyon, roi d' Éthiopien," *JA*, vol. 8, ser. 14 (1889), p. 340.

269. ታሪኩ በንጉሡ ታሪክ ተመዝግቧል፤ Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, pp. 69-71.

የሚታየውን ምልክት ያከፋሉ፤ ምክንያቱም እነሱ፥ (111^ሀ) "ትምህርታችን በሞኞች ዘንድ የተከደነ ነው"[270] የሚለውን አያውቁም፤ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የባሮቹን ደም በቀል እያሳየ ሳለም ልብ አይሉትም። አንዳንድ ጊዜ በድብቅ ይመታቸዋል፤ አንዳንድ ጊዜ በግላጭ ይመታቸዋል።

አበስኪሮንና እስጢፋኖስ ዋጋቸውን አገኙ

ቅዱሳኑን በቁጣ ይጣላቸው የነበረውን አበስኪሮንን እግዚአብሔር ከፈጸመው (በደል) የሚበልጥ ከፈለው። በዚህ ተንኮለኛ እጅ ወገረው። በቁጣው በትር አሰቃየው። ሥጋውንም አበላሸለት፤ ሴቶች ዘፈኑበት፤ (የሀፍረት) ጠጉሩን እየነጩ አመድ ነፉበት።[271] ተሳልቀውበት ክፉ ሞት ሞተ።

በበራራ (ጉባኤ) ጊዜ በቅዱሳኑ ላይ የውሸት መስካሪ የሆነውን የሲመይ መምህር እስጢፋኖስንም (ዋጋውን) እግዚአብሔር በቁጣው ከፈለው። በዚህ ተንኮለኛ እጅ ጣለው። በድንጋይ ወግረውት ክፉ ሞት ሞተ። የጽድቅ ሥርዓትን የሚቃወሙትን ዕቡዮች (ዋጋቸውን) ለከፈለ እግዚአብሔር ስብሐት፥ ለመንግሥቱ ሥልጣንም ምስጋና ይድረሰው። በፍጥረት ሁሉ አፍ የተባረከና የተመሰገነ ይሁን፤ ሁሉን የያዘና ለዘለዓለም ለጻድቃን ሕይወት ሰጪ ነውና፤ አሜን። (ለእኔ) ለኃጢአተኛው ጸልዩ፤ ባርኩኝም።[272]

---


270. 2 ቆሮ 4፡ 3።

271. ፈሪ ሲቀጡ ልክ እንዲህ ያደርጉ እንደነበረ ዘርአ ያዕቆብ ነግሮናል፤ Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity*, p. 97.

272. ጸሎትና ቡራኬ ጠያቂው ደራሲው ይሁን ወይም ይኸንን ቅጂ የቀዳው አይታወቅም።



በግብጽ ምድረ በዳ በብሕትውና የኖሩ አባ ጳውሊ
(ከደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሐፍ፡ MS Spencer 7, f. 2a).



(112^{ሀ}) የመጋቢት ፳፭ ምንባብ

መግቢያ

በሥሉስ ቅዱስ ስም፤

ይህ÷ ጌታ እየረዳንና እኛም ለዘለዓለም በሱ እየተማመንን÷ በመጋቢት ፳፭ ቀን የሚነበብ የቅዱሳን ሰማዕታት አባቶቻችንና ወንድሞቻችን የገድላቸውና የሰማዕትነት መጽሐፍ ሶስተኛው ክፍል ነው፤ አሜን::[273]

ከመንበርታና ከዐጋሜ የተያዙ እስረኞች

ከዚህ በኋላ÷ (እንዲህ) ሆነ፤ ቅዱሳኑን በብሔረ ትግራይ መንበርታ በምትባል ቦታና በዐጋሜ በያዙዋቸው ጊዜ÷ ሰብስበው ከብሔሩ ገዢ ዘንድ አመጧቸው:: ስለ ሥራቸው (ስለ እምነታቸው) ጠየቃቸው፤ ስለ ሥራቸው ሲያውቅ በማስፈራራት ለማሳሳት ከነሱ ውስጥ ጥቂቶቹን ገረፋቸው::

በማነቆ እንደታሰሩ ወደ ንጉሡ ላካቸው:: ንጉሡ ደብረ ብርሃን ብሎ በጠራት በመንግሥቱ ሀገር÷ ኢባ በምትባለው በንጉሡ መዲና÷ በነበረበት ጊዜ እዚያ አደረሷቸው:: ሀገሪ ደም እንጂ እንደ ስሟ (ደብረ ብርሃን) አይደለችም:: አምጥተው (112^{ለ}) ከንጉሡ ዘንድ ሳያቆሟቸው ከውጪ እኖሯቸው::

ቅዱሳኑ ወደ ገበያም ሆነ ወደፈለጉበት ሁሉ ይወጡና ይመለሱ ጀመር:: ብዙ ሰዎችና የደብተራው ካህናትም÷ "እነዚህ ደቂቀ አስጢፋኖስ አገር አጠፉ፤ እንደፈለጋቸው ሆኑ" አሉባቸው:: ቅዱሳኑም÷ "እንደናንተ ስላሉት ወንጌሉ÷ "በመንገድ የሚያልፉት ራሳቸውን እየነቀነቁ ያሽሟጥጡት ነበረ[274] ብሏል" የሚል ቃል መለሱላቸው:: በዚህ ምክንያት የደብተራው ካህናትና ሌሎችም (በሰሙት ላይ ሌላ ነገር) ጨምረውበት ከሰሷቸው::

ንጉሡ ቅዱሳኑን እስር ቤት እንዲያስገቧቸው ትእዛዝ ሰጠ፤ ከእስር ቤት አስገቧቸው:: በ፬ም በ፫ም ተከፋፈሏቸው፤ እጅና እግራቸውን አሰሯቸው:: ከምድረ ገይኒም[275] ያመጧቸው (ሌሎችም) ነበሩ፤ አብረው አሰሯቸው:: እዚያ በብዙ ጣር÷ በረኀብ÷ በውሐ ጥም÷ በመራቆት ኖሩ::

---

273. እስከዚህ ያነበብነው የሁለተኛውን ክፍል ምንባብ ትርጉም ነው:: የአንደኛውን ክፍል ምንባብ ያልተረጎምኩበትን ምክንያት በመግቢያው ውስጥ ገልጫለሁ::

274. ማቴ 27: 39::

275. ግኝ?

ሃይማኖት የሚያስተው ሥቃይ

ከሥቃዩ የተነሣ አንድ ወንድም ሃይማኖቱን ለመተው ቃጣው፤ እዚያ ያሉ ወንድሞች ሲሰሙ አዘኑ፤ የሚያደርጉት ጠፋቸው፤ ምክንያቱም የአሰር ቤቱ ዘበኞች እንዲሰበሰቡ አይፈቅዱላቸውም ነበረ። (113ᵘ) ይኸንን ሲያስቡና ሲያዝኑ እግዚአብሔር በምስጢር በጎ ሥራ ሠራላቸው። እዚያ ንጉሡ ያሰራቸው ብዙ የሀገሩ ታላላቅ መኳንንት ነበሩ። ቅዱሳኑን፦ "ከንጉሡ ጋራ ለምን ሰላም አታደርጉም? እኛንም ከንጉሡ ዘንድ ብታግልዱን የብዙዎች አባቶች ትሆኑ አልነበረምን?" አሏቸው።

ከዚያ፦ ጳውሎስ የሚባለው ፩ ወንድም፦ "እኛ ሰላም እንወዳለን እንጂ ጥል እንፈልግም፤ አሁንም ወንድሞቼን ሰብስቧቸው እና ያላችሁኝን ልንገራቸው" አላቸው። ከ፩ አሰር ቤት ሰበሰቧቸው። በዚያ ወንድም ምክንያት እርስ በርሳቸው በተግሣጽና በምዕዳን እንዲጽናኑ እግዚአብሔር በምስጢር ስለሰበሰባቸው ወንድሞች አመሰገኑት። ያ ወንድምም ንሰሐ ሲሰጡትና ተግሣጽ (ሲያስሙት) በረታ።

የዕርቅ ድርድር

ይኸ ነገር--አሰረኞቹ ከቅዱሳኑ ጋራ እንደተወያዩ--ከአሰረኞቹ ዘንድ ወጥቶ ለንጉሡ ደረሰው። ከዚያ፦ ያንን ወንድም ወደሱ እንዲያመጡት ላከበት። ከፊት ለፊቱ አቆሙት፤ (113ᵑ) ሊደልለው ነገር እያጣፈጠ እንዲህ ሲል ላከበት፤ "ሃይማኖታችሁን እናውቃለን፤ ጥሩ ሥራችሁንም አውቃለሁ፤ አንሰግድም በማለት ከጸናችሁበት ቃል በቀር ምን አለባችሁ? ይኸም ይቅር፤ እንግዲህ የጥል ግድግዳ ይፍረስ፤ በማህሳችን ሰላም ይሁን ይላል ንጉሡ።"

ከዚያ፦ ጳውሎስ የሚባለው ወንድም፦ "እኔና ወንድሞቼ ከሰላም በቀር ምን እንፈልጋለን? አሁንም እንዳልከው ይሁን። እኔም ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ" አለ። ደግሞ ንጉሡ፦ "ያንተና የኔ የሰላም (ድርድር) ለወንድሞች ይበቃቸዋልን?" (አለ)። [276]

ያ ወንድም፦ "በእውነት ካደረከው አዎን፦ ይበቃቸዋል። ቃልህን ከዚህ ወደ ሌላ ከለወጥክ አይበቃቸውም። እኔም በሥርዓቴ ሳልኖር ካንተ ጋራ ሰላም ብፈጥር፦ በኔ (መለየት) ምክንያት ምን ይጐድልባቸዋል? ከታላቅ ባሕር እፍኝ ሙሉ ውሐ ቢወስዱለት ምን ይጐድለዋል? እኔም ሥርዓቴን ከተውኩ በእነሱ ዘንድ እንደዚህ ነኝ" አለው።

ደግሞ ንጉሡ፦ (114ᵘ) "ይኸ (አባታችሁ) እኮ በፊት የገረፍኩት ጊዜ እኔና አንተ እግዚአብሔር ፊት እንገናኛለን አለኝ፤ ይኸ እንዴት ይሆናል?" አለ። ያ ወንድም፦ "ንስሐ ለገባ የወደፊቱን ነው እንጂ እግዚአብሔር ያለፈውን አያስታውሰም" አለው። ይኸንን ብሎ (ሰምቶ?) ዝም አለ።

ይኸ ተንኮለኛ ይኸንን የሚለው ሰላም ለመሥራት ሳይሆን ቅዱሳኑን ለማሳሳት፦ በእግዚአብሔር ባሮች ላይ ተንኮል ሊሠራባቸው፦ ይኸንንም ወንድም ሊደልለው ነው። ይህ ወንድም ግን በሃይማኖቱ እንደ አለት ድንጋይ ጽኑ ነው። ይኸም ተንኮለኛ እነሱን መደለል ሲያቅተው በቁጣ ዝም አለ።

ከዚያ በኋላ፦ ወደዚህ ወንድም ዘንድ እንዲህ ሲል ላከ፤ "ይህ ሰላማችን ፍጹም እንዲሆን መምህርህን ትሰድባለህን?" ያ ወንድም፦ "ይኸንን

276. "አንተ ከኔ ጋራ ታርቀህ ከተለየሃቸው ወይም ተዉ ካልካቸው ማኅበሩ ይፈርሳል" ብሎ ማስቡ ይሆናል።

ካልኮማ የፈተኛው ነገርህ ሁሉ ከንቱ ይሆናል፤ አኔ መምህራን አልሰድብም" አለ። ንጉሡ የነገሩን መጨረሻ ሲሰማ ከአስር ቤት እንዲመልሱት አዘዘ። እስከ ጊዜው እዚያው በአስራት ኖሩ።

የጦር ጎይሉ (የሠራዊቱ) ዓይነት

(ከብዙ) ወራት በኋላ፥ በየአስር ቤቱ ያሉትን አስረኞች እንዲሰበስቧቸውና (114ሀ) እንደታሰሩ፥[277] ሥራቸውን[278] እንዲመረምሩ አዘዘ። ወታደሮቹ (የታዘዙትን) አደረጉ። ቅዱሳኑን ከአስር ቤት አወጧቸውና እንደነዚያው መረመሯቸው፤ "ለንጉሡ አትሰግዱምን?" አሏቸው። ቅዱሳኑ ለወታደሮቹ፥ "አዎን፥ እንሰግድም፤ ስሱ ስለ መስገድማ እሱ ለኔ መስገድ ይቅር ብሎ ትቶናል" አሏቸው። ለንጉሡ ነገሩት።

ከዚያ፥ እንዲፈሩ ንጉሡ ጦር፥ ሰይፍ፥ በትር፥ አለንጋ ከያዙ ሠራዊት መካከል እንዲያቆሟቸው አዘዘ። "በሉ፥ ለአግዚአብሔር ስገዱ" ብሎ ወደነሱ ላከባቸው። ይኸንን ነገሯቸው። ከዚያ፥ ይኸ ወንድም፥ "እናንተ ሠራዊት ሆይ፥ የምንሰግደው ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እንጂ በትር በመፍራት አይደለም" አለ። ይኸንን ብለው፥ ሰገዱ፤ ጸለዩም።

ንጉሡ፥ "በፊት አባታችሁ ለኔ አልሰግድም ስላለ ገረፍኩት፤ እናንተ ደግሞ አንሰግድለትም ማለታችሁ ምንድን ነው? አለና በብዙ ማስፈራራት ተጐማለለባቸው። አነሱ ግን የጌታ ጎይል አየመገባቸው በመንፈስ ቅዱስ አርዳታ ጠንካሮች ነበሩ።

ከዚያ፥ (115ሀ) ይህ ተንኮለኛ ወደ አስር ቤት ዘበኞች መለስ ብሎ በቁጣ፥ "እናንተ ባሮቼ አይደላችሁምን? እኔ ስቆጣ እናንተ ትምራላችሁ፤ አሁንም ሂድ ውሰድና አጁንና እግሩን አሰረው" አለ።

ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው አደረጉ። እጃቸውንና እግራቸውን በሰንሰለትና በእግር ብረት በጽኑ አሰራት አሰሯቸው። ቅዱሳኑ ወደ አግዚአብሔር በጭንቅ ጮኹ። ያንን ነገረ ፈጅ የሆነውን ወንድምም በትልቅ አግር ብረት አሰሩት። እጁንም በሰንሰለት (አሰሩት)። እስራቱን በብረት መዶሻ አጠበቁበት።

ይህ ወንድም ግን በሃይማኖቱ ጽኑ ነው። በፊትም ከእነ አባ ያዕቆብ፥ አባ ጳውሎስ፥ አባ ማቴዎስ ጋራ የቆመ ጊዜና ተከራካሪዎቹ፥ "ለንጉሥ ለምን አትሰግዱም፤ ሐዋርያት በሴኖዶሳቸው አክብረውት የለምን?" ባሉ ጊዜ፥ ይህ ሃይማኖተ ጽኑ ወንድም፥ ወንድሞቹን፥ "ስለዚህ ጉዳይ አንድናገር ፍቀዱልኝ" ሲላቸውና "በል ተከራከራቸው" ሲሉት፥ "ንጉሡ በሕግ የሚሠራ ቢሆን እንደምትሉት (115ሀ) እናከብረዋለን፤ ከሕግ ውጪ (የሚሠራ) ከሆነ መምዕላይ[279] ነው"[280] ብሎ ነበረ። "የዱሮዎች አልሰገዱምን? አብርሃም ለኬጢ ልጆች ሰግዷል፤[281] ያዕቆብም ለኤሳው"[282] ሲሉትም፥ "አብርሃም የሰገደው በገንዘብ ሽያጭ ለሚስቱ መቃብር ሲያገኝ በኬጡ ልጆች ፊት

277. የታሠሩበትን ምክንያት?
278. "እምነታቸውን"።
279. "Dictator". ይኸንን የሚለው ሲኖዶሱ ነው።
280. ሁለቱም ወገኖች የሚጠቅሱት ሲኖዶሱን ነው።
281. ዘፍ 23: 7፤ ኩፋ 17: 30።
282. ዘፍ 33: 3።

አግዚአብሔርን ለማመስገን ነው፤ ያዕቆብም ለዔሳው የሰገደው በፍርሃት ምክንያት ነው። ሕግ ገና ስላልተሰጠች ይኸ ኃጢአት አልሆነበትም" አለ።

ተከራካሪዎቹ፥ "ከሕግ በኋላ ቢሆንም ዳዊት ለሳኦል ሰግዷል፤[283] ናታን ለዳዊት ሰግዷል"[284] አሉት። ያ ወንድም፥ "ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ለእንግዳ አምላክ አትሰገዱ[285] ብሏል። ጌታችንም፥ ለአምላክህ ለአግዚአብሔር ብቻ ስገድ፤ አሱን ብቻም አምልክ[286] ብሏል" አላቸው።

ከዚያ፥ ተከራካሪው፥ "ጌታ ይኸንን ያለው ለማን ነው?" አለው።[287] ያ ወንድም፥ "ራስህ ታውቀዋለህ" አለው። ተከራካሪው "አስቲ ንገረኝ፥ ጌታ ይኸንን ለማነው ያለው?" አለው። (116ᵁ) "ራስህ ታውቀዋለህ" አለው።

ተከራካሪው፥ "ያለው ለስይጣን አይደለምን?" አለው። ያ ሃይማኖተ ጽኑ ወንድም፥ "ለራሱ ስግደት የሚወድ ሁሉ ስይጣን ነው" አለ። ተከራካሪውና አብረውት የቆሙትም ይኸንን ሲሰሙ አንዳይሰሙ ሸሹ።

ያለውንም ለንጉሥ ነገሩት። ንጉሥ በቁጣ፥ "በል ስርኑን ስበርና ደሙን ባፍንጫው ይጠጣ" ብሎ አዘዘ። ከዚያ፥ በእንጨት ውስጥ እንዳለ ጉንዳን[288] ከበቡትና በድብደባው ተረባረቡበት። ሞተ አስኪሉ ድረስ ብዙ ድብደባ ደበደቡት። ከዚህ ተንኮለኛ በኋላ ከሚመጣው ከሌላው ንጉሥ ዘንድ ገና ብዙ ሥቃይና የአሳት ቅጣት ስላለበት፥ ያን ቀን አግዚአብሔር (ከሞት) አነሣው።

ቁጣውን አስተንፍሶ፥ "ከመድኃኒት ቤት ውሰዱት" አለ። መድኃኒት እንዲያጠጡት አዘዘ። መድኃኒት በማጠጣት ብዙ ቀኖች ከጣር ላይ ጣሉት። ስሕተቶች የሚያገኙበት[289] መስሏቸዋል።

ተስቅቆ እንደገና ተያዘ

እንደ ሁል ጊዜው ሊያሰድቡት፥ እንድትጠብቀው ለአንዲት ሴት አሳልፈው ሰጡት። (116ᴬ) ያች ሴት እየሰደበቺው እዚያ ብዙ ቀኖች ኖሮ አግዚአብሔር ከስድቧ አዳነው። ከውጪና ከውስጥ የጠላት ተንኮል ላይ ሁሉ የማሸነፍ ኃይል አግዚአብሔር ስጥቶት፥ መውጣትና መግባት ጀመረ። "የት ነው የምትውለው? የት ነው የምታድረው?" የሚለው አልነበረም።

ከዚያ፥ በንጉሥ የሰቀላው ሰፈር ላሉት ሠራዊት እንዲህ ሲል አሰማ፤ "ሠራዊት ሆይ፥ ስሙ፤ እኔ ከደቂቀ አስጢፋኖስ ነኝ። እኔን የሚፈልገኝ የለም። ካሁን ጀምሮ ስላም ዋሉ" አለ። ይኸንን ብሎ መንገዱን አመራ። ከገዳሙ ደረሰ።

ከዓመታት በኋላ፥ በምድረ መንበርታ በነበረበት ጊዜ (አንደገና) ከወንድሞቹ ጋራ ያዙት፤ (ከንጉሥ ዘንድ) አደረሱት። በአንደዚህ ያለ ሥቃይ፥ በረኃብ፥ በውሐ ጥም፥ በብርድ፥ በመራቆት በጽኑ አስራት እንዳሉ፥

---

283. 1ሳሙ/1ነገሥ 24፡ 8።
284. 1/3 ነገሥ 1፡ 23።
285. መዝ 80፡ 9/10።
286. ማቴ 4፡ 10።
287. ጌታ ይኸንን ያለው ለስይጣን ነው፤ ተከራካሪው የጠየቀው ራሳቸውን እንዲስድቡ ነበር።
288. "ምስጥ"?
289. "የሚሸነፍ"።

ከነሱ ውሰጥ ፷ቱ (ስማዕትነታቸውን) ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን÷ አሜን። የተረፉትም እስከ ጊዜው ድረስ በአስር ቤት ኖሩ።

የግራ ሰዎች ወረራ

የንጉሡ ሎሌ÷ (117[ሀ]) "እባትህ የት ነው" ያለው ጊዜ÷ "መምህራችን የጌታን ሥቃይ ተካፍሏል" ያለው መርቆርዮስ የሚባለው ወንድም ገድሉን ፈጽሞ በወንድሞች ማኅበር ላለ የግራ ሰዎች ያስለመዱት ጠራቸው በህገሪቱ ላይ መጣ። ቅዱሳኑን አዚያ አገኟቸው። ያ ወንድም በግራ ሰዎች ጦር ስማዕትነቱን ፈጸመ። ፭ ወንድሞችም ከሱ ጋራ ስማዕትነታቸውን በታኅሣሥ ወር በ፲፱ ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

በዚያ ዓመት ቅዱሳኑ (ስማዕትነታቸውን) የፈጸሙት በነዚያ የግራ ሰዎች ጦር ነው። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ጉዳት ያደረሰው ከዳተኛ ወንድም

ቅዱሳኑ በዚያች ቆጣት በምትባለው ህገር ላሉ÷ ፩ ወንድም እንደ ወንድሞቹ ንጹሕ ሥርዓት መጠበቅ ባለመቻል ከነሱ ተለየ። (አንዲያውም) ሊከላቸው ወደ ንጉሡ ሄደ። በጠባዩ የሚተባበረው ጓደኛ አገኘ። "በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቀት ጥቂቶች ከዓለም ኃጢአት ከሸሹ በኋላ ዳግመኛ በአርኗ ተጠላልፈው በዚያ ቢሸነፉ የኋላው በደላቸው ከፊተኛው የባሰ ይሆናል። (117[ለ]) ዐውቀዋት ከጽድቅ መንገድ ከሚመለሱ ይልቅ ባያውቋት ይሻል ነበረ"[290] የሚለው የመጽሐፍ ቃል በነሱ ላይ እንዲደርስ (ሁለቱ) የሚሠሩትን ተወያዩ። ለንጉሡ ነገሩት።

ንጉሡ ሊሰማ መልእክተኞች ሰጥቷቸው÷ እንዲያመጧቸው አዘዘ። ታዘው ሄዱ። ከወጊ አገረ ገዢ ደረሱ፤ (ንጉሡ) እንደላካቸው ነገሩት። አገረ ገዢው ከብዙ ሠራዊት ጋራ ቀንደ መለከት እያሰነፋ (ፍለጋ) ተነሣ። ቅዱሳኑን በየቤታቸው ከበቧቸው። ንብረታቸውን ወሰዱት፤ ቤታቸውን መዘበሩት። እነሱንም ያዟቸው፤ ቍጥራቸው ፷፰ ነበረ። ወስደው በማነቆ አንደታሰሩ (ከንጉሡ አደባባይ) እደረሷቸው። ንጉሡ ወደሱ አስገብተው በአጠገቡ እንዲያኖሯቸው አዘዘ።

ቀጥሎ ንጉሡ አስር ቤት ያሉትን ቅዱሳን አንዲያወጧቸው አዘዘ፤ አወጧቸው። ደግሞ መጻሕፍት ዐዋቂዎች እንዲሰበሰቡ አዘዘ። ከሱም በኩል ከ፫ቱ መካናት[291] የደብተራ ካህናት በየ፮ቱ እንዲሰበሰቡ አዘዘ። ከበላያቸው እንዲናገር ፍሬ ብርሃን የሚባለውን አዘዘ። ንጉሡ÷ "በሱ በሃይማኖት ነገር ተከራከሩ" ሲል ወደ ቅዱሳኑ ላከ። ቅዱሳኑ "መልካም" አሉ።

ምስጢረ ሥላሴ--ክርክር

ይኼ ፍሬ ብርሃን÷ (118[ሀ]) "ስለ ሥላሴ ህልውና የምታምነው አንዴት ነው? አብ÷ ወልድ÷ መንፈስ ቅዱስ በየቃላቸው ይናገራሉ ትላለህን?"[292] አለው።

---

290. 2 ጴጥ 2: 20-21።

291. "ከ3ቱ ቤተ ክርስቲያኖች" ማለት ነው፤ ቤተ ክርስቲያኖቹ መካነ መስቀል፡ ቤተ ማርያም፡ መካነ ኢየሱስ ይመስሉኛል፤ C. Conti Rossini, "Il libro di re Zar'a-Yā'qob sulla custodia del Mistero," *RSE*, vol. III (1943), p. 8/155.

292. ይሄ ደቂቀ እስጢፋኖስ ከሚታመብት "ክህደት" አንዱ ነው፤ Kurt Wendt, *Das*

ከዚያ፥ ይህ ለወንድሞች ነገረ ፈጃቸው የሆነው ጳውሎስ የሚባለው ሃይማኖተ ጽኑ ወንድም፥ "አምን፥ አላለሁ:: እንደ መጽሐፉ ቃል ከሆነ፥ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ በ(የ)ቃላቸው ይናገራሉ፤ እናንተ የምትሉት በሌላ መጻሕፍት ከሆነ፥ መጽሐፍ እርስ በርሳችሁ ተቻቻሉ ይላል"[293] አላቸው:: እነሱ በዚህ አልተከራከሩትም፤ ቢከራከሩት ምስክር መጥራት አያቅተውም ነበረ::

አብ ስለሚናገር እከራከራለሁ የምትል ሆይ፥ እነሆ በነቢዩ ሄኖክ ውስጥ አብ እንደተናገረ ይሽውልህ፤ "ከዚህ በኋላ የዘመን ራስ ተጸጽቶ በየብስ ላይ የሚኖሩትን ሁሉ በከንቱ አጠፋኋቸው (አለ):: ካሁን በኋላ በየብስ ላይ በሚኖሩ ሁሉ ላይ (እንዲህ) እንዳያደርግ በትልቁ ሰሙ ማለ::"[294] ከአሪትም ይሽውልህ፤ "እግዚአብሔርም አለ፤ ሰውን በመልካችን፥ በምስላችን እንፍጠር::"[295] ከኢሳይያስም፥ "እነሆ፥ ወዳጄ ያስተውላል፥ ከፍ ከፍ ይላል፥ ይከብራልም"[296] የሚልም ይሽውልህ:: ከሕዝቅኤል ውስጥም (118^ለ) አብ ወልድን፥ "ጸዶሬ[297] የለበለውን ለው፥ በመንኰራኵሮች መካከል (ከኪሩቤል በታች ግባ)፤ ከኪሩቤል በታች ካለው የእሳት ፍም እጆችህን ሙላ፤ በሀገሪቱም ላይ በትናት አለው"[298] እንዳለው ያውልህ:: የእሳት ፍም መበተን በሐዋርያት ላይ አንደ እሳት የወረደው መንፈሰ ቅዱስ ነው:: ሶስቱም በኪሩብ ሰረገላ ይኖራሉና:: በመዝሙር ውስጥም ይሽውልህ፥ "ዛሬ እኔ ወልጄሃለሁ፤ ለምንኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ አስጥሃለሁ::"[299] ደግሞ፥ "ጌታ ጌታዬን፥ በቀኜ ተቀመጥ አለው"፤[300] ደግሞ በአሪት ዘፍጥረትም ይሽውልህ፤ "እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ ፩ዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን ይዘረጋና ከሕይወት ዛፍ በልቶ ለዘለዓለም ይኖራል::" (ይላል)[301] በማቴዎስ ወንጌል ውስጥም ይሽውልህ፤ "በሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ ስሙት የሚል ቃል ከሰማይ መጣ::"[302] በዮሐንስ ወንጌልም ይሽውልህ፤ ወልድ አብን፥ "ስምህንና ልጅህን አክብረው ባለ ጊዜ አከበርኩህ፥ ደግሞም አከብርሃለሁ የሚል ቃል ከሰማይ መጣ::" (ይላል)[303] በጴጥሮስ መልእክትም፥ "ቃል ከዚያ(?) (119^ሀ) ከስብሐቱ ትልቅነት በእሱ ላይ ወርዶ፥ የምወደው እኔ የመረጥኩት ልጄ ይህ ነው አለ:: ይኸንን ቃል ከሰማይ እንደወረደለት ከሱ ጋራ በቅዱስ ተራራ በነበርንበት ጊዜ ሰምተነዋል"[304] የሚል እነሆ::

Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis) des Kaizers Zar'a Yā'qob, *CSCO*, vol. 221/41, Louvain 1962, pp. 13 and 38.

293. ቆላ 3: 13::
294. ሄኖ ክፍል 51, Knibb, *Enoch*, p. 151.
295. ዘፍ 1: 26::
296. ኢሳ 52: 13::
297. "በፍታ"::
298. ሕዝ 10: 2::
299. መዝ 2: 7-8::
300. መዝ 109: 1::
301. ዘፍ 3: 22::
302. ማቴ 17: 5::
303. ዮሐ 12: 28::
304. 2 ጴጥ 1: 17-18::

ስለ ወልድ እንኳን አትክደኝም። ስለ መንፈስ ቅዱስም፥ ከነቢዩ ከሄኖክ፥ "የመናፍስት ጌታ እነሆ፥ መቅሠፍቴንና ቁጣዬን በላያቸው አወርደዋለሁ አለ"[305] ከነቢዩ ዳንኤልም፥ "የሰው መልክ ያለው ደግሞ ዳሰሰኝ፤ አበረታታኝም"[306] የሚል ይኸውልህ። በዮሐንስ ራእይም፥ "መንፈስ ቅዱስ ምን አለ፤ ያሸነፈ እንደገና አይሞትም"[307] የሚል ይኸውልህ። ከሐዋርያው ጳውሎስ መልእክትም ይኸውልህ፤ "መንፈስ ቅዱስ እንደዚህ ይላልና፥ ዛሬ ቃሉን ስትሰሙ ልባችሁን ትልቅ አታድርጉ።"[308] በሐዋርያት ሥራ ውስጥም ይኸውልህ፤ "መንፈስ ቅዱስ ጠራቸውና፥ በርናባስንና ሳኦልን ለምፈልጋቸው ሥራ ለዩልኝ (አለ)።"[309] ሊቀ ሐዋርያቱ ጴጥሮስም፥ "መንፈስ ቅዱስ፥ ሳትጠራጠር ከነሱ ጋራ ሂድ አለኝ"[310] ብሏል። መጻሕፍቱ ይኸንን ይላሉ።

ስለ ወልድም እሱ ራሱ (119^ለ) ስለራሱና ስለ አባቱ ለአይሁድ ሲናገር ያለው እነሆ፤ "ይህን እንድሠራውና እንድፈጽመው አባቴ የሰጠኝን ሥራ፥ እንድሠራ አባቴ እንደላከኝ ምስክሬ ነው። የላከኝ አባቴ እሱ ምስክሬ ነው።"[311] እኛ የምናስተምረው እንደዚህ ነው።

ከዚህ በኋላ፥ ያ ፍሬ ብርሃን፥ "እንደዚህ ካልክ በል የአርዮስን፥ የመቅዶንዮስን፥ የንስጥሮስን እና የእንደነሱ ያሉትን ክህደት አውግዝ። የተወገዙ ናቸው በል" አለው።[312] ያ ወንድም፥ "አምን፥ የተወገዙ ናቸው" አለው። ደግሞ ይኸ ፍሬ ብርሃን፥ "አስጢፋ አርኩስ ነው በል" አለው።

ያ ወንድም፥ "አቡነ አስጢፋኖስ ንጹሕ፥ ቅዱስ፥ ጻድቅ ነው፤ ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራና በሠራዊቱ ሁሉ ላይ ትሁን" አለው። ወንድሞቹ፥ "አሜን" አሉ። ይኸ ሃይማኖተ ጽኑ ወንድም ሠራዊቱን፥ "እናንተም አሜን በሉ" አላቸው። እነሱ (ግን)፥ "እኛ አንፈልገውም፤ (ጸሎቱ) ለናንተ ይሁን" አሉ። (እንዲህ ሲሉ) ቅዱሳኑ፥ ደግመው፥ "አሜን" አሉ።

ያሉትን ሁሉ ለንጉሡ ነገሩት። እስር ቤት እንዲያስገቧቸውና እንዲያስሯቸው አዘዘ። ወታደሮቹ እንደዚሁ አደረጉ።

ወደ ሀገረ በሊ ግዞት

(120^ሀ) ፱ ወር ከታሰሩ በኋላ፥ ጥር ፮ ቀን ከእስር ቤት አወጧቸው። እነዚያን ከምድረ ቆጌት ያመጧቸውንም ሰበሰባቸውና ደባለቋቸው። ከዚያ፥ ንጉሡ

---

305. ሄኖ ክፍል 51, Knibb, *Enoch*, p.151-152.
306. ዳን 10: 18።
307. ራእ 2: 11።
308. ዕብ 3: 15።
309. የሐ ሥራ 13: 2።
310. የሐ ሥራ 10: 20።
311. ዮሐ 5: 36-37።
312. አርዮስ "ወልድ ፍጡር ነው"፥ መቅዶንዮስ "መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ነው"፥ ንስጥሮስ "ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ አለው" ያሉ መናፍቃን ናቸው፤ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሁሉንም መጽሐፈ ምስጢርና ፍካሬ መለኮት በሚባሉት ድርሰቶቻቸው ተችተዋቸዋል፥ አውግዘዋቸዋልም፤ Yacob Beyene, *Giyorgis di Saglā Il libro del Mistero (Maṣḥafa Mesṭir) CSCO*, vol. 515/89 (1990), pp. 8, 44 and 72; Getatchew Haile, "*Fəkkare Haymanot* or the Faith of Abba Giorgis Säglawi," p. 250.

ወደ ሀገረ በሊ[313] ጊዘበ[314] ከምትባል ተራራ እንዲወስዷቸው አዘዘ። የንጉሡ ወታደሮች ወሰዷቸው። ቅዱሳኑ ጭንቅ በተሞላ ድካም ሄዱ። በዚህ ወር በሰኔ ቀን ከዚያች ተራራ ላይ አወጧቸው፤ ቍጥራቸው ፮ነ ነበረ። በተሸነቈረ ግንድና፥ በማነቆ፥ በእርጥብ የበሬ ቆዳ አሰሯቸው። አጥር እደረጉባቸውና ለዚያች ሀገር ገዢ አስረከቡት። አረሚ (አስላም) ለለሆነ በጥብቅ እንዲጠባበቃቸው አዘዙት። እዚያ ምግብና ልብስ በማጣት ቅጠልና ከስራ ስሩም የሆነውን እየበሉ፥ የዛፍ ቅጠል እየለበሱ በብዙ ጣር ኖሩ።

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ከፍቶላቸው፥ ከወንድሞቻቸው አርዳታ አገኙ። ካሉበት ከሌላ ሀገር (መጥተው) ጐበኟቸው። እነሱም ወንድሞቻቸውን ሲያዩ ተደሰቱ፥ ደስ ተሰኙ። (120^ለ) "ከዚህ ተራራ ላይ ካወጡን ጀምሮ ከናንተ ሌላ የክርስቲያን ፊት አላየንም" አሏቸው። አብረው እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ እስከ ጊዜው ኖሩ።

ከዚያ፥ ቅዱሳኑ ጉዳያቸውን ፈጽመው ሲመለሱ ፩ ስው አግኝቶ ያዛቸው። ከንጉሡ ዘንድ ወሰዳቸው። ንጉሡ የንጉሡ መዲና[315] በሆነችው ደብረ ብርሃን ባላት በሀገረ ኢባ በነበረበት ጊዜ በማነቆ እንደታሰሩ አመጣቸው። ሌሎቹንም ከምድረ ገደዶ አምጥተዋቸው ነበረ። ንጉሡ አስር ቤት አንዲያስገቧቸው አዘዘ። አስገቧቸውና አጃቸውንና እግራቸውን አሰሯቸው። እዚያ በረኀብ፥ በውሐ ጥም፥ በብርድ፥ በመራቆት፥ በአስጨናቂ በሽታ ኖሩ።

አባ ሀብተ ማርያም ዘደብረ ሊባኖስ ጠላት ሆኑ

ከደብረ ሊባኖስ የቅናት መንፈስ ያደረበት ፩ ሀብተ ማርያም የሚሉት መነኮሴ ቅዱሳኑን ሊከስ ወደ ንጉሡ ሄደ። "አነሆ፥ ደቂቀ እስጢፋ ደብርህን አበላሹ፥ ብዙዎችን ወደ ትምህርታቸው መለሱ፤ አሁንም፥ አንዳመጣቸው መልአክተኞች ስጠኝ፥ ጌታዬ ንጉሥ ሆይ" አለ።[316]

ንጉሡ ሲሰማ (121^ሠ) መልአክተኞች ሰጠው፤ መልአክተኞቹን ይዞ ቅዱሳኑ ወዳሉበት ቁጠመይ ወደምትባል ሀገር ሄደ። አዚያ ሁለት ቅዱሳን አገኘ፤ ያዟቸው። እዚያ ምእመናንም ተያዙ፤ ቤታቸው ተዘረፈ፤ ገንዘባቸውንም ወሰዱባቸው። የቀሩት ቅዱሳን ግን ከዱር ተደበቁ። (ሰዎች) ለቅዱሳኑ (ከተደበቁበት) መጥተው ምእመናንና ቅዱሳን፥ ፬ (ሰዎች) እንደተያዙ ነገሯቸው።

ከዚያ፥ በዱር ያሉት ቅዱሳን ወጥተው ወደ አነሱ ሄዱ። ለንጉሡ መልእክተኞች፥ "እኛን የምትፈልጉን፥ አነሆ መጥተንላችኋል፤ እነዚህን ሰዎች ልቀቋቸው" አሏቸው። ከዚያ፥ ፩ ወንድም፥ "ሐዋርያው ጳውሎስ፥ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ጋሻ አንሡ፤ በጽድቅ ወገባችሁን ታጥቃችሁ ቁሙ፤ የወንጌልን ጎይልም ተጫምታችሁ የጽድቅ ብረትም ልበሱ[317] ብሏል።

---

313. "ባሌ"።
314. "ገዘበ"? ግልጽ አይደለም።
315. "ደይም ዘንጉሥ"።
316. የአባ ሀብተ ማርያም ገድል ታትሟል፤ Osvaldo Raineri, *Atti di Habta Māryām (ፅ1497) e di Iyāsu (ፅ1505) Santi Monaci Etiopici, OCA* no. 235, Rome 1990. ግን ከአዬ ናኦድ እንጂ ከአዬ ዘርአ ያዕቆብ አደባባይ አንደነበሩ አይናገርም።
317. ኤፌ 6: 13-15።

አሁንም የምናሸንፋችሁ በእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ በሥጋ ኀይል ነውን?" አለ። በዚህ ምክንያት ብዙ ድብደባ ደበደቡት።

ነገረ ፈጃቸው የሆኖው ፩ዱ ወንድምም፡ "እዎን፡ ኑሯችሁ እንደዚህ ነው፤ እናንተ ተኵላዎች ናችሁ፤ እኛ በጎች ነን፤ እናንተ ገዳዮች ናችሁ፡ እኛ ሟቾች ነን" ሲል፡ (121^ሀ) የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት ብድግ ብለው ዱላ አንሥተው እግሩን ስበሩት። ከዚያ፡ ቅዱሳኑን ከመነኮሲቶች ጋራ አስረው ከንጉሡ አደባባይ ወሰዷቸው። ያንንም (እግሩን) የሰበሩትን ወንድም ተሸከመው (ሁሉንም) በማነቆ አንደታሰሩ ከንጉሡ ዘንድ አመጧቸው። (መምጣታቸውን) ለንጉሡም ነገሩት። ከአስር ቤት አንዲያገቧቸው አዘዘ። አግብተው እጃቸውንና እግራቸውን አሰሯቸው።

መጽሐፈ ብርሃን

ከዕለታት አንድ ቀን የንጉሡ ወታደሮች ስለ *መጽሐፈ ብርሃን* ሲያወሩ አኖርዮስ የሚሉት ፩ ወንድም፡ "በውስጡ ሐሰት ያለበትን ምን *መጽሐፈ ብርሃን* ይለዋል?" አለ። ፩ ሰው ሂዶ ለንጉሡ አንዲህ ሲል ነገረው፤ "ስለ *መጽሐፈ ብርሃን* ሳወራ በአስር ቤት ያለ ከደቂቀ አስጢፋኖስ ፩ዱ *መጽሐፈ ጽልመት*[318] (ነው) አለኝ።"

ንጉሡ ያንን ወንድም አንዲያመጡት አዘዘ። ወዲያው አመጡት። "እውነት *መጽሐፈ ጽልመት* ብለሃል?" አለው። ያ ወንድም፡ "*መጽሐፈ ጽልመት* አላልኩም" አለ። "*መጽሐፈ ሐሰት*" ሲላቸው ጊዜ እነሱ *መጽሐፈ ሐሰትን መጽሐፈ ጽልመት* አሉት። ከዚያ፡ (122^ሀ) ንጉሡ እንዲገርፉት አዘዘ። ታላቅ ግርፊያ ገረፉት። በዚያ ግርፊያ ታሞ ስማዕትነቱን በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

መሐላ አልታዘዘም--ጊዮርጊስና ኢሳይያስ

፩ ሰው አስር ቤት ያሉትን ቅዱሳን አንዲህ ሲል ከንጉሡ ዘንድ ከሰሳቸው፤ "ደቂቀ አስጢፋኖስ ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ በስመ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሐዱ አምላክ አይሉም።" ንጉሡ ሲሰማ ያን ነገረ ፈጃቸው የሆነውን፡ የደብረ ሊባኖስ መነኮሴዎች አግሩን የሰበሩትን ወንድም አንዲያመጡት አዘዘ። ከንጉሡ ፊት አቆሙት። መረመረው፤ "ልጆቻችሁን ስታስተምሩ በስመ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሐዱ አምላክ የማትሉት እውነት ነውን" አለው። ያ ወንድም፡ "እኔ ከሥላሴ አላጎድልም በሥላሴም ላይ አልጨምርም። አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ ፫ ህላዌዎች፡ ፩ መለኮት (አንደሆነ) አምናለሁ፤ አስተምራለሁም" አለ።

"ከዚህ የተለየ ሌላ ትምህርት እንደሌለህ በል ማል" አለው። ያ ወንድም፡ "እኔ አልምልም፤ (መሐላ) አልታዘዘልኝም" አለው። ንጉሡ፡ "መጽሐፍ ስትምል (122^ሀ) በእውነት ማል[319] ይል የለምን? ደግሞ፡ በሱ የሚምል ሁሉ ይከብራል[320] ይላል" አለው።

---

318. "የጭለማ መጽሐፍ"።

319. ?።

320. መዝ 62: 11/12:

ያ ወንድም፦ "ከዚህ ሁሉ፦ እኔ ግን እላችኋለሁ ፈጽሞ አትማሉ፤ በሰማይም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፦ በምድርም የእግዚአብሔር እግር መረመጃ ነውና፦ በኢየሩሳሌምም የታላቁ ንጉሥ አገር ነቺና፤ ብቻ ቃላችሁ እንድ ይሁን፤ ወይ አዎን፦ አዎን፤ ወይም እይደለም፦ እይደለም።[321] (ያለው ይበልጣል)፤ ሐዋርያውም እንደዚሁ ያስከትላል"[322] አለ።

ከሳሾቹ፦ "እኛ በዚህ እንምላለን" አሉ።

ያ ወንድም፦ "እንድትምሉ እኔ አላዝዛችሁም፤ ከማላችሁ ግን እይሁድ ትሆናላችሁ" አላቸው።

ንጉሡ በቁጣ፦ "ስገድ በለው" አለ።

"መላሴን እፍንጫዬን እንዲቈርጡ፦ የሽኮናዬን ቋንጃ እንዲያወጡ ስታዝ ያን ጊዜ ያልሰገድኩልህ አሁን ምን ተለወጠ? እኔ ያው ጊዮርጊስ አይደለሁም? አንተስ ያው ዘርአ ያዕቆብ እይደለህም?" አለው። ከዚያ፦ ንጉሡ እንዲገርፉት በቁጣ አዘዘ። (123[ሀ]) ታላቅ ግርፊያ ገረፉት።

ደግሞ ንጉሡ በእስር ቤት ካሉት ቅዱሳን (ሌላ ሰው) እንዲያመጡለት አዘዘ። ወታደሮቹ ኢሳይያስ የሚባል ፩ ወንድም እያጣደፉ አመጡት። ያ ወንድም የንጉሡን ወታደሮች፦ "እናንተ የአውነት ጠላቶች፤ ዐውቀናችኋል፤ ልማዳችሁ ነፍስ መግደል ነው" አላቸው። እየደበደቡ ከንጉሡ አደረሱት። እሱንም እንዲገርፉት ንጉሡ አዘዘ፤ ታላቅ ግርፊያ ገረፉት። በዚያች ዕለት ኅዳር ፳ ቀን ሰማዕትነቱን ፈጸመ። ሌላው በማግሥቱ በ፳፩ ቀን (አረፈ)። የታሰሩትም (ሰማዕትነታቸውን) በዚያው ቀን ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን፦ አሜን።

እስረኛ ኅብኚዎቹ ታሰሩ

ወንድሞች በእስር ቤት ያሉትን ጉብኝተው ሁኔታቸው እንዴት እንደሆነ እንዲያውቁ ቅዱሳኑ ወንድሞች ልከው ኖሮ፦ ከንጉሡ ሰፈር ውጪ ደርሰው ስለ ወንድሞች ነገር ሲያጠያይቁ፦ የንጉሡ ተሳላኪዎች እነሱንና ከንጉሡ ሰፈር የነበሩትን ሌሎቹን ወንድሞች ይዘው ከእስር ቤት አስገቧቸው። እጃቸውንና እግራቸውን አሰሯቸው። (123[ለ]) እስከ ጊዜው (እዚያ) ኖሩ።

ከዚያ፦ ከብዙ ጭንቅ፦ ምግብ ከማጣት፦ ከመራቅት ጋራ ትልቅ በሽታ ወደቀባቸው። በዚህ ሥቃይ እዚያው ገድላቸውን ፈጸሙ። ጸሎታቸውና በረከታቸው ከኛ ጋራ ይሁን፤ አሜን። የተረፉትም በዚያ ጭንቅ እስከ ጊዜው ኖሩ።

ያላሰቀ የብሔረ በሊ የግዞት ጉዞ--"ሰይፌን አታደንዝብኝ"

ከብዙ ዘመን በኋላ፦ ንጉሡ በእስር ቤት ያሉትን ቅዱሳን አውጥተው ወደ ብሔረ በሊ እንዲወስዷቸው አዘዘ። ጥር ፮ ቀን ወደ ማታ ግድም አወጧቸው። በበሽታ ላይ ያሉትን መሄድ እንደማይቻላቸው ሲያዩ ከእስር ቤት አውጥተው ከአረሚ ቤት ጣሏቸው። መሄድ የሚችሉትን በዚያች ሌሊት ወደ ታዘዙበት መሰዷቸው። ሲጓዙ ቀጸም ከምትባል አገር ደረሱ። ለኢ[323] ቅርብ ናት፤ የ፩ ሰዓት ጉዞ ናት። እዚያ አደሩ።

321. ማቴ 5: 34-37።

322. ያዕ 5: 12።

323. "ለደብረ ብርሃን"።

ከዚያ፥ ያንን ተንኰለኛ በቅዱሳኑ ላይ ክፋት እንዲሠራባቸው ሐዘን አንቀጠቀጠው፤ በማግስቱ በጠዋት ቢጋላቢ ፈረስ የተቀመጠ (መልእክተኛ) እንዲህ ሲል ላከ፤ "እሺ ይሉህ እንደሆነ ለንጉሥ ስገዱ በላቸው። እምቢ ካሉህ (123[2ሀ])[324] እግራቸውንና እጃቸውን እዚያው ቁረጥባቸው።" (መልእክተኛው) ትእዛዝ ተቀብሎ ወጣ። ቢጋላቢ ፈረስ ሄዶ ቅዱሳኑ ካደሩበት ደረሰ። ቅዱሳኑን ለሚወስዳቸው የንጉሡን መልእክት ነገረው። ከዚያ፥ ቅዱሳኑን፥ "ለንጉሥ ስገዱ" አሏቸው። እሱ እንዳለው መሰገድ እምቢ አሉት።

ከዚያ፥ ያ የኋለኛው መልእክተኛ ለመጀመሪያው መልእክተኛ፥ "ንጉሡ እምቢ ያለውን እጆቹንና እግሮቹን ቍረጥ ብሏል" አለው። ቅዱሳኑ የመልእክተኛውን የነገሩን መጨረሻ ሲሰሙ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። "እነሆ፥ የጽድቃችን ሰብል መግቢያና የገድላችንም ፍጻሜ ደረሰ፤ እግዚአብሔር ድካማችንን እየልን፤ ከዚህ ዓለም ጣር ሊያሳርፈን ፈቅዷል" አሉ።

እርስ በርሳቸው ምዕዳን ሲሰማሙ፥ ፩ዱ ወንድም ሌሎቹን ምዕዳን ሲያሰማቸው እንዲህ አላቸው፤ "ጨክኑ፥ አትጠራጠሩ፥ እትፍሩ፤ የዚህ ዓለም ሥቃይ ጎላፊ ነው። በሃይማኖታችሁ ጥኑ። ምክንያቱም የሙሽራው ሙሽሮችና ቅድስት ሀገር ለመግባት የተዘጋጃችሁ ናችሁ።" ደግሞ ይኸው ወንድም፥ "ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፤ ቀንዴ በአምላኬና በአዳኜ ከፍ ከፍ አለ፤ አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፥ በማዳንህ ተደሰትኩ፤"[325] (123[2ለ]) አለ። ደግሞ፥ "ነፍሴ እግዚአብሔርን ታተልቀዋለች፤ በአምላኬ በመድኃኒቴ ትደሰታለች"[326] አለ።

ይኸን ብሎ እጆቹንና እግሮቹን ሰጣቸው። ከዚያ፥ ከወታደሮቹ አንዱ ሰይፉን ከፍ አድርጎ እጆቹንና እግሮቹን ባንዴ ቈረጣቸው። ከዚያ፥ ያ ወንድም፥ "የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ ለዓለም ሰቡሕ ነው፥ ልዑልም ነው"[327] አለ። አንዳንዱ፥ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ"[328] አሉ። እንዳንዱ፥ "አቤቱ እንደምሕረትህ ትልቅነት ማረኝ"[329] አለ። እንዳንዱ፥ "የሰማይ አባታችን፥ ስምህ ይቀደስ"[330] አለ። አንዳንዶቹ ከመጽሐፍ (እየጠቀሱ) ይዘምሩ ነበረ። ሁሉም መንፈስ ቅዱስ እንዳቀበለው ተናገረ።

ከዚያ፥ በየተራቸው ወደ ሰያፊው ወረዱ። ባለሰይፉ ሰይፉን ከለከለ፤ "ሰይፌን አታደንዝብኝ" አለ። ከዚያ፥ የዚያን አገር ሰዎች፥ "ከየቤታችሁ ቢላዎ አምጡ" አላቸው። ቅዱሳኑ እንዳይጐዷቸው ምላጫቸውን ሰጡ። ሰዎቹም ቢላዋ አመጡ፤ በዚያ ቢላዋና በምላጭ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ቈረጧቸው።

እነሱ ይኸንን (124[ሀ]) ሲያደርጉ ሌላ መልእክተኛ፥ "መላሳቸውንና አፍንጫቸውን ቈረጣ ጨምር ብሏል ንጉሡ" ለማለት ከንጉሡ ዘንድ ቢጋላቢ

---

324. ቍጥር 123ን ደገመው።
325. 1 ሳሙ/ነገሥ 2: 1።
326. የቅድሰት ማርያም ጸሎት መጀመሪያ፤ ሉቃ 1: 47።
327. ጸሎተ ሰለስቱ ደቂቅ።
328. መዝ 40: 14፤ 71: 18፤ 105: 48።
329. መዝ 50: 3።
330. የአቡነ ዘበሰማያት መጀመሪያ፤ ማቴ 6: 9።

ፈረስ መጣ። የተቈረጡት ቍጥራቸው ፲ ሆነ። ይኼ የኋለኛው መልእክተኛ ፮ቱን እግሮቻቸውንና እጆቻቸውን በመቈረጥ (ሰማዕትነታቸውን) ፈጽመው እገኛቸው። ያልሞቱትን ፫ቱን መላሳቸውንና እፍንጫቸውን ቈረጡ። ከ፫ቱ ፩ዱ (ሰማዕትነቱን) ፈጸመ። በዚያች ዕለት በጥር ፱ ቀን (ሰማዕትነታቸውን) በጌታ ሰላም የፈጸሙ ፮ ሆኑ። ጸሎታቸውና በረከታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

በእስር ቤት በነበሩበት ጊዜ ይረዷቸው የነበሩ ፪ ወንድሞች ነበሩ። እንዳስለመዱት (ሊጠይቋቸው) ቢሄዱ አጧቸው። ስለነሱ ሰዎች ቢጠይቁ፥ "ትናንት ወደ ምሽቱ ላይ ንጉሡ ወዳዘዘበት ወሰዷቸው" አሏቸው። የወሰዷቸውበትን መንገድ ጠይቀው በዚያች መንገድ ተከተሏቸው። ፮ቱን (ሰማዕታነታቸውን) ፈጽመው፥ ፪ቱን በሕይወት አገኟቸው። ቀና አድርገው ደሙን ካፋቸው ጠረጉላቸው።

ምን እንዳደረጓቸው ጠየቋቸው። የሆነውን ሁሉ አስረዷቸው። የሞቱትን ቀበሯቸው። በሕይወት ያሉትን፥ "ኑ ወደ ወንድሞቻችሁ እንውሰዳችሁ፤ እህል ውሐም እንስጣችሁ" አሏቸው።

(124^ሀ) "እኛ ከመስቀል አንወርድም፤ እግዚአብሔር ከወደደ እዚሁ እንሞታለን፤ ግን ለወንድሞቻችን ቆገት እና እብሶ ላሉት ማኅበርተኞች ሰላም በሉልን። የጸሎታቸው እርዳታ እንዲያገኘን ስለኛ እንዲጸልዩ (ንገሩልን)፤ እግዚአብሔር ማኅበራችሁን ይባርክ፤ ሥርዓታችሁን ያበርታ፤ ከሰይጣን ተቃውሞ ያድናችሁ በሏቸው። ለናንተም ጥሩውን ዋጋ ይክፈላችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ ስለኛ አትተክዙ፤ እንደሞተ ቁጥራችሁን ሂዱ። ከእንግዲህ ወዲህ በመንፈሳችን እንጂ የሥጋ ሕይወት የለብንም። በሰላም ሂዱ፤ እግዚአብሔር ከናንተ ጋራ ይሁን" አሉ።

ሰላምታ ተሰጣጥተው ሄዱ፤ ወደ ማኅበራቸው ተመልሰው፥ የላኳቸውን ለወንድሞቻቸው ነገሯቸው። ከቈረጧቸው ከዘጠኝ ቀን በኋላ (ሌሎች) ወንድሞች ጐበኟቸው። እዚያ በቀን የፀሐይ ሙቀት፥ በሌሊት ብርድ፥ ከምላስ፥ ከአፍንጫ፥ ከእጅ፥ ከእግር ቁስል ጋራ ሆነው ከሚያጠና ከእግዚአብሔር እርዳታ በቀር ከሰው እርዳታ (125^ሀ) ተሰፋ በመቊረጥ ወድቀው አገኟቸው። እነሱም የደረሰባቸውን ጠየቋቸው። ያደረጓቸውንና ፪ ወንድሞች እንደጐበኟቸው፥ ያረፉትንም እንደቀበሯቸው፤ በቈረጧቸው በ፫ኛው ቀን ፩ ምእመን እንደጐበኛቸው፤ የዱቄት ውሐም እንደሰጣቸው ነገሯቸው።

ሲሰሙ አለቀሱ፤ ልብስ አለበሷቸው፤ የሚተኙበትን አመቻቹላቸው። የቀበሯቸውንም አውጥተው ከውጪ እንደጣሏቸው የደረሰባቸውን ሁሉ ነገሯቸው፤ አስረዷቸውም። ከዚያ፥ ባረኳቸው፤ "እግዚአብሔር ጥሩ ዋጋ ይክፈላችሁ፤ እግዚአብሔር ይባርካችሁ" አሏቸው።

እነሱም ምዕዳን አሰሟቸው፤ "ገድላችሁን ፈጽሙ፤ ከዚህ የሚሻል አታገኙም፤ እግዚአብሔር ከናንተ ጋራ ይሁን" አሏቸው። (ጊዜው) ሌሊት ስለሆነ ሄዱ፤ በቀንማ አይቻላቸውም፤ የእገሩ ሰዎች ይጠብቋቸዋል። የፊተኞቹንም በሌሊት የቀበሯቸውን የሀገሩ ሰዎች ከሳሽ በመፍራት በቀን (ከመቃብር) አወጧቸው።

ከቈረጧቸው ከ፲፬ ቀን በኋላ ወንድሞች ጐበኟቸው። (125^ሀ) እንደዚያው ወድቀው አገኟቸው። በፊት የሰጧቸውንም ልብስ እንድ እግዚአብሔርን የማይፈራ መነኮሴ ወስዶባቸው አገኙ።

ስለ ሁኔታቸውና ያ መነኮሴ ምን እንዳደረጋቸው ሲናገሩ፥ የንጉሥ ወታደሮች መጡና ይዘው ወሰዷቸው። ከተቈረጡት ውስጥ ፪ቱ ሳይሞቱ እንዳሉ፥ ወንድሞቻቸው ሲረዷቸው እንዳገኟቸው ለንጉሡ ነገሩት። ከዚያ፥ ንጉሡ የተያዙትን ከእስር ቤት እንዲያስገባቸው፥ የተቈረጡትንም ተሸክመው እንዲያመጧቸው እዘዘ፡ (እምጥተው) ከሰቀላው ሰፈር አስቀመጧቸው።

ንጉሡ፥ "በሉ መምህራችሁን ስደቡ" ብሎ ላከባቸው። "በዚህ ምክንያት የተቈረጠውን መልካችንን ልትመልስ ትችላለህን? የምትለውን የምናደርገው ቢሆን ኖሮ በጤና በነበርንበት ጊዜ እናደርገው ነበረ። ስለዚህ፥ አንፈልግም፤ እኛ እግዚአብሔር እየረዳን ለመሞት ቈርጠናል በሉት" አሉ። ይኸንኑ ነገሩት።

ንጉሡ የቃላቸውን መጨረሻ ሲያውቅ ወደ ጐሐርብ አገር ደብረ በግው ከምትባል ቦታ እንዲወስዷቸው አዘዘ፤ ወሰዷቸው።[331] (126ᵘ) ሲወስዷቸው አርምጃቸው በጥድፊያ ነበረ። ፩ዱ ወንድም፥ "(የጫናችሁትን) ወንድሜን እንዳይ አውርዱኝ" አላቸው። እምቢ አሉት። "እምቢ ካላችሁኝ እናንተ እዩት" አላቸው። አውርደው ቢያዩት (ሰማዕትነቱን) ፈጽሞ አገኙት። እዚያው ጣሉት። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ያንንም ወንድም ንጉሡ ካዘዘበት አደረሱት። የዚያች ቦታ ሰዎች ተቀብለው ከውጭ አኖሩት። እነሱም፥ "እህል ውሐ እንድንሰጥህ መምህርህን ስደብ" አሉት። እሱም እንደበፊቱ ለንጉሡ እንዳለው አላቸው። እነሱም የቃሉን ፍጻሜ ሲሰሙ፥ ሰው እንዳይደርስለት፥ እህል ውሐም እንዳይሰጡት (በዙሪያው) አጥር አደረጉበት።

ወንድሞች ሁኔታቸውን ለመረዳት እነሱን በመፈለግ ብዙ ደከሙ። ሲፈልጉ እዚያች ሀገር ደረሱ። አጥር ያደረጉበትን ወንድም አገኙት። "ሰላም ላንተ ይሁን፤ በደኅና አለህን? ሁኔታህስ እንዴት ነው?" አሉት። እሱም ሰላምታ መለሰላቸው። ሁኔታውንና፥ ጓደኛውም (ሰማዕትነቱን) እንደፈጸመ ነገራቸው።

"ስለ ሕይወትህስ ምን ትላለህ? እህል ውሐ እንድንሰጥህ?" አሉት። (126ᵃ) "ለሚረዳኝ ሽክም ከመሆን በቀር በዚህ ምስኪንነት በዓለም ውስጥ ኑሮዬ ምን ይጠቅመኛል? ሕይወቴ ተፈጽማለች፤ ወዲያ ወዲህ የምልበት (እግርም) ሆነ የምዳስስበት (እጅ) የለኝም። እንግዲህስ ከመኖር መሞት ይሻለኛል" አላቸው። ይኸንን ብሎ እነሱንም ሌሎቹንም ወንድሞቹን በምትገባ የበረከት ቃል ባረካቸው።

እነሱም ባረኩት። ሰላምታ ተሰጣጥተው ወደ ሀገራቸው ሄዱ። እሱም ፴ ቀን ቆይቶ ሰማዕትነቱን በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ ትጠብቀንም፤ አሜን።

ከእነዚያ፥ መሄድ ሰላቃታቸው በአረሚ ቤት ከጣሏቸው ፩ዱ በዚያ በሽታ (ሰማዕትነቱን) ሲፈጽም አንገቱ ላይ ገመድ አስረው ጎትተው ከገበያ አወጡትና በድንጋይ ወገሩት። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

---

331. የአባ ሀብተ ማርያም ገድል እንደሚያመለክተው፥ ጐሐርብ ወደ ምሥራቅ ነች፤ Raineri, *Atti di Habta Māryām*, p. 38.

ከቆጌት ወደ ፈጸጋር የተላኩ ታሰሩ

በዚያ ዓመት ማኅበሩ ወንድሞችን ከቆጌት ወደ ፈጸጋር ልከዋቸው ነበረ። በመንገድ ያዟቸውና ከንጉሡ ዘንድ አመጧቸው። "ለንጉሡ ስገዱ፤ መምህራችሁንም ስደቡ" አሏቸው። እምቢ እሏቸው። ስለዚህ (127[ሀ]) ከእስር ቤት አስገቧቸው። እግራቸውን በእግር ብረት፥ እጃቸውን በብረት ሰንሰለት አሰሯቸው። እዚያ በብርድ፥ በመራቆት፥ በረኃብ፥ በውሐ ጥም፥ በታላቅ በሽታ ላይ ሳሉ ከነሱ ይቱ ገድላቸውን በጌታ ሰላም ፈጸሙ። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ተስቦ ገባ

ወንድሞች ከተበተኑበት እግዚአብሔር በምድረ ፀጋም (በግራው አገር) ከከፈተላቸው ቦታ በተሰበሰቡ ጊዜ እዚያ አባታቸው ስላዘጋጀላቸው ውሳኔዎች እርስ በርሳቸው ምዕዳን እያለማመሩ ኖሩ። ለብዙዎችም ለነፍስና ለሥጋ መደገፊያ ሆነው ከ፱ ወደ ፪፱ ወደ ፫ እና ፬፱፥ ከዚህም እስኪበዙ ድረስ እጥፍ ሆነው ነበረ።

በእግዚአብሔር ቃል በበሽታ በኩል ጥሪ መጣና በዚያ ዓመት (ሰማዕትነታቸውን) በመንፈሳዊ ገድል የፈጸሙ ወንዶችም ሴቶችም ፸ ሆኑ፡ አንዳንዶቹ የሰማዮች ምስጢር እያዩ በዚያ የሚደሰቱ ነበሩ። እንዳንዶቹ የጻድቃን ነፍሶችን በጉባኤ በደስታ ሲዘመሩና ካፋቸው የማር ወላሎ ሲፈስ እይተዋል። (127[ለ]) እንዳንዱ የሚሆነውን ነገር ከመሆኑ በፊት ያውቅ ነበረ። መጽሐፍ እንደሚለው፥ መንፈስ ቅዱስ ያለበት ሁሉን ያውቃል።[332] ሁሉንም ሰብስበን ልንጽፍላችሁ እልፈለግንም። ምክንያቱም፥ "መጽሐፉ ከሰው ዘንድ ከምንመሰገን እግዚአብሔር ዘንድ ብንመሰገን ይሻላል"[333] ይላል። ሁሉንም ከመናገር መሥራት፥ ከመሠዋት መስማት ይሻላል። የነሱም ዋጋቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እኛም በረከታቸው በአምላካችንና በአምላካቸው በእግዚአብሔር እንዲደርሰን ለዘለዓለም ተስፋ እናደርጋለን። አሜን፥ አሜን።

ከዚያ፥ በዚያው ዓመት እንደገና በእግዚአብሔር ቃል በትልቅ በሽታ ጥሪ መጣላቸው። በዚያ ዘመን ከግንቦት ፪ ጀምሮ እስከ ኅዳር ፬ ድረስ (ሰማዕትነታቸውን) ወንዱም ሴቱም ፪፱፯ቱ በመልካም ገድል ያባታቸውን ሥርዓትና ውሳኔዎች በመጠበቅ ፈጸሙ። እንዳንዶቹ ከክፉ እጋንንትና የንጉሡ የሰይጣን መልእክተኞች ከሆኑት ከታወቁት ሠራዊቱ ብዙ ሥቃይ ያለለፉ መንፈሳውያን ሽማግሌዎች ነበሩ። (128[ሀ]) እንዳንዶቹ በእግዚአብሔር ቃል የሚተዳደሩ ጽኑ ጎልማሶች ነበሩ። እንዳንዶቹ ንጹሐች ሕፃናትና ደስተኛ ድንግሎች ነበሩ። እንዳንዶቹ የእድሜያቸውን ማለቂያ የተናገሩ (የበቁ) ነበሩ።

ሹም ተስፋኑ ክርስቶስ ጠላት ሆነ

በዚህ በሽታ በነበሩበት ጊዜ ተስፋኑ ክርስቶስ የሚሉት የዚያ ሀገር ሹም ተነሣባቸው፥ የቅዱሳኑ ጠላት ሆነ። በዚያ ዓመት ከንጉሡ ፊት ሲመለስ

---

332. ?።

333. ምናልባት Victor Arras, *Patericon Aethiopice, CSCO*, vol. 277/53 (1967), p. 97.

ከጻድቃኑ ጋራ ተጣላ። ቤቶቻቸውን እቃጠለ፤ ገንዘባቸውን ወስዶ ከሀገሩ አባረራቸው። እኡሳም በዚያ በክረምት ዝናም÷ በሌሊት ብርድ÷ በበሽታ ሲንከራተቱ በጌታ ሰላም ገድላቸውን ፈጸሙ። ጸሎታቸውና በረከታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ ለዘለዓለም ትጠብቀን፤ አሜን÷ አሜን።

እባ ብእሴ ሰላምና እባ ሳሙኤል ጠላት ሆኑ

በዚያው ዘመን በየአድባራቱ ያሉ ብዙ መነኮሳት ተነሥተው ከንጉሡ ዘንድ ሄዱና÷ "ደቂቀ እስጢፋኖስ የመንግሥትህን ብሔሮች ሞሏቸው። ብዙዎችንም ወደ ትምህርታቸው መለሱ። አሁንም የምታደርገውን ዕወቅ÷ ጌታችን ንጉሥ ሆይ" ሲሉ ቅዱሳኑን ከሰሷቸው። ይሽንን ሰምቶ ዝም አለ።

ደግሞ ሌሎች ፪ መነኮሴዎች ተነሡ። የአንዱ ስም ብእሴ ሰላም (የሰላም ሰው)÷ ሲሆን የሥቃይና የደም ሰው እንጂ እንደ ስሙ (128^ሀ) ሰላማዊ አይደለም። እግዚአብሔርን አይፈራ÷ ሰውን አያፍር። ሁለተኛው ሳሙኤል ይባላል።[334] ለንጉሡ÷ "ጌታችን ንጉሥ ሆይ÷ ደቂቀ እስጢፋኖስ ያሉበትን እኛ እናውቃለን፤ አሁንም የምታደርገውን ዕወቅ" አሉት።

እነዚህ መነኮሴዎች ከብዙ ተሳላኪዎች ጋራ ወደ ውድ (?) አገረ ገዢ እንዲሄዱ አዘዛቸው። (ሄዳችሁ)÷ "በሀገርህ ደቂቀ እስጢፋኖስ አሉ፤ አሁንም የህገሩን ሹማምንት ሰብስበህ እንዲያመጡልህ ንገራቸው፤ ሲያመጡልህ ለመንግሥቴ ክብር ይሠሩ እንደሆነ መምህራቸውን ይሰድቡም እንደሆነ ዕወቅ÷ መርምርም። እሺ ካላሉህ እዚያው ግደላቸው፤ የተገኙበትም (ሰው) ቤቱ ይመዝበር፤ ንብረቱም ይጥፋ፤ እሱም ከነሱ ጋራ ይሙት በሉት" አለ።

ይሽንን ትእዛዝ ይዘው ከወድ አገረ ገዢ ዘንድ መጡ። ንጉሡ እንዳለው ነገሩት። አገረ ገዢው የህገሮቹን ሹማምንት ሰብስቦ እነሱ ዘንድ ያሉትን ቅዱሳን እንዲያመጡ የንጉሡን ትእዛዝ ነገራቸው።

የንጉሡን ትእዛዝ ሰምተው ወደየህገራቸው ተመለሱ። (129^ሀ) በዓይናቸው ፊት ምሕረት የሌለባቸው ተስፋ የቈረጡ ስለሆኑ ይሰበስቧቸው ጀመሩ። ኬር ወሰን ከህገሩ ከማያ[335] አመጣ፤ ርክነን ከህገሩ ከገዘሞ አመጣ፤ ከጠዘም[336] እንደዚሁ። ከህገረ ገዢው ዘንድ ሰበሰቧቸው፤ እሱ በዚያን ጊዜ ከሹመቱ በታ ከየጐንደት ነበረ። የአገረ ገዢው ስም ደውለይ ነው።

አገረ ገዢው ከነዚያ መነኮሴዎችና ተሳላኪዎች ጋራ ብዙ ሠራዊትና ብዙ የምድሩን ሹማምንት ሰበሰበ። ቅዱሳኑን ከምእመናኑ ጋራ (ከፊቱ) እቀሟቸው። በጋሻ÷ በጦር÷ በበትር÷ በፈረስ (ሠራዊት) በብዙ አስፈራራቸው። ወደ ጦርነት እንደሚሄዱ÷ በፊታቸው ሰልፍ አሳዩ። ቅዱሳኑ ግን ከአምነታቸው ጽናት ሳይንቀሳቀሱ እርስ በርሳቸው ምዕዳን እያሰሙና አንዱ ሌላውን እያበረታታ ቆሙ። ከዚያ÷ "እስጢፋ እርኩስ ነው በሉ" አሏቸው። ቅዱሳኑ÷ "እባታችን እስጢፋኖስ ጻድቅና ቅዱስ ነው" አሉ።

---

334. አባ ሳሙኤል የሚባሉት ሰው ዘሚካኤልና ገማልያል "አግዚአብሔር መልክ የለውም" በማለታቸው በተከሰሱበት ሸንጎ ላይ የተገኙ መነኮሴ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ Getatchew Haile, "The Homily of Zär'a Ya'əqob in Honour of St. John the Evangelist," p. 151.

335. መጽሐፉ "ማየ" ብሎታል።

336. ያገሩ ስም "ጦዘ" ነው።

"ሁላችሁም እንደዚህ ነው የምትሉት?" አሏቸው:: ቅዱሳኑ፥ "አዎን፥ እንላለን፤ ሁላችንም እንደዚህ እንላለን" አሏቸው:: "እያንዳንዳችሁ በቃላችሁ፥ አስጢፋኖስ አርኩስ ነው በሉ አሏቸው:: እያንዳንዳቸው በቃላቸው፥ "አባታችን አስጢፋኖስ ቅዱስ፥ ብርሃን ገላጭ[337] ነው፤ አስጢፋኖስ የክርስቶስን ፈለግ ተከታይ ነው"[338] አሉ::

ከዚያ፥ ብእሴ ሰላም የሚባለው መነኮሴ ከመድረክ ላይ ወጥቶ (129^ዕ) ለሕዝቡ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "እነዚህ ቅዱሳን ፀረ ማርያም ናቸው:: ለንጉሥ አይታዘዙም፥ ለክብሩም አይሰግዱም:: እነዚህም ፪ቱ (የነሱ) ምአመናን ናቸው:: ያባታቸውን የአስጢፋን ተዝካር ያወጣሉ:: ለነሱ መውጫ መግቢያ ሆነዋቸዋል:: ከዚህ የሚበዛ ሥራቸውን እኔ አውቃለሁ::"

ከዚያ፥ ከንጉሡ ዘንድ ያመጣውን መልእክቱን እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ "እነዚህ መነኮሴዎች እሺ ካሉህ ይሰገዱ፤ መምህራቸውንም ይሰደቡ፤ እምቢ ካሉ ግን ትልቅ ነገር አድርሰባቸው"--አዚያው ይግደሏቸው ሰላለ ነው:: ሕዝቡ ለንጉሡ ፫ ሰግደት ሰገዱ:: ቅዱሳኑ ግን ከሕዝብ ማህል ቆመው አምላካቸውን እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበረ:: ሕዝቡ ቅዱሳኑን የሥጋ ሕይወትን ተስፋ እየሰጡ ይደልሏቸው ጀመር--አያንዳንዱን በጦር በማስፈራራትም::

፩ ወንድም አፈገፈገ፤ በጦሩ ምክንያት ፈራ:: ሌላው፥ "ጻማህን[339] አስታውሰው፤ የሠራኸውን አታበላሽ:: መጽሐፉ፥ ሥቃይ የአንድ አፍታ ነው ይል የሰምን?"[340] ሲለው፥ ያ ወንድም፥ "አዎን፥ ወንድሜ፤ እውነትክን ነው፤ ሰይጣን የ፫ ዓመት ጻማዬን ሊያበላሽብኝ ይፈልጋል" አለ:: ይኸንን ብሎ ፊቱን በሥላሴ ስም አማተበ፤ ልቡን (130^ህ) መንፈስ ቅዱስ በዚያ ወንድም አፍ በተናገረው አጠነከረ::

ጳውሎስ የሚሉት ወንድም፥ ወንድሞቹን ሁሉ ምዕዳን ሲያሰማቸው አንዲህ አለ፤ "እንግዲህስ የዓለም ሕይወት ይበቃናል፤ ወንድሞቼ አትፍሩ:: የዛሬው ሂደታችን ወደሚጠፋው ሳይሆን ወደማይጠፋው ነው::" በብዙ ምዕዳን አበረታታቸው፤ ወደ ጎላፊው ከምታዘነብል ከሐሳብ ድልጫ (ለመዳን) አንዲመረኮዙት የረድኤት ምርኩዝ ሆናቸው:: በተለየም፥ ከእጎቶችም ፬ መነኮሲቶች ከነሱ ጋራ አዚያ ነበሩ::

"በል አንደ ወንድ ውጋ"

አንዚያ ወታደሮች እያንዳንዳቸው ጦራቸውን አነሡና እነዚያን ፪ ምአመናን በመግደል ጀመሩ:: ከዚያ በኋላ፥ መኰንኑ፥ "ሁልህም የያዝከውን ግደል" አለ::

ይኸ ጳውሎስ የሚባለው ሁለተኛው (?) (ለክርክር ከወጣበት መድረክ ላይ) እየተደሰተ ወረደ፤ ሌሎቹም ወንድሞቹ ነፍሳቸውን ሰጡ:: በዚያ በጦር መወጋት ሰማዕትነታቸውን ፈጸሙ::

ከአራቱ ምእመናት አንዷ ወታደሩ በትንሹ ወጋ ሲያደርጋት፥ "አወጋግህ ስምን አንደዚህ አንደ ሴቶች ሆነ?" አለችው:: ከዚያ፥ አንገቷን

337. "ከሣቴ ብርሃን"::
338. 1. ጴጥ 2: 21::
339. "የማቀቅከውን"::
340. ?::

ከፍ፥ ደረቷን ሰፋ አድርጋ አስተካክላ ሰጠችውና፥ "በል እንደ ወንድ ውጋ" አለችው። አዚያው ከወንድሞቿና ከአኀቶቿ ጋራ ተወጋች። ቍጥራቸው ፲፩ ነበረ። በጌታ ሰላም ሰማዕትነታቸውን የተቀዳጁት መጋቢት ፬ ቀን ነው። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፥ ትጠብቀንም፤ አሜን፥ አሜን።

እንደገና ተስቦና አፈሳ--"እጁን እንድንሳለመው የታለ?"

(130^ሰ) ከዚያ፥ በዚያ ዓመት በሽታ መጣ። የቆገት ሹም ከሀገሩ ሲያባርራቸው ወልማ ከምትባል ሀገር ደረሱ። የዚያ ሀገር ሰዎች ተቀበሏቸው። የደረሱት በጎዳር ወር ነው። ደውሳይ የሚባለው የወጊ[341] አገር ገዢ ስለ ቅዱሳኑ የንጉሡ መልእክት ሲደርሰውና በዚያች አገር በወልማ መኖራቸውን ሲያውቅ አድሙት የሚባሉትን ሠራዊቱን ሳከ። የወልማን[342] ሹም ከአብሩታ[343] ሹም ጋራ ጉባኤ አድርጎ አገኙት። በሀገሩ የሚኖሩትን ቅዱሳን እንዲልክ የአገረ ገዢውን መልእክት ነገሩት። "መልካም ነው" አለ። የዚያ የወልማ ሹም ስም በጎይለ ማርያም ነው።

ከዚያ፥ ጠቋሚዎች ሰጠው። ጠቋሚዎቹ ወታደሮቹን ከየቅዱሳኑ ቤት አደረሷቸው። ይዘው ከአንድ ቦታ ሰበሰቧቸውና የንጉሡን መልእክት ነገሯቸው፤ "ንጉሡ ሰላም ለናንተ ይሁን ብሏል" ብለው ነገሯቸው። እንደሚገባው ሰላምታ ከቡራኬ ጋራ መለሱ። "እጅ ንሡ" አሏቸው።

(131^ሀ) ሀብተ ጽዮን የሚባለው ፩ ወንድም፥ "እጁን እንድንሳለመው የታለ?" አለ። "ለንጉሡ ስገዱ አይደለም እንዴ የምንላችሁ? ለንጉሥ መስገድ አጅ መንሣት ነው" (አለ)። ያ ወንድም፥ "እኛ እንደዚህ አናደርግም፤ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለአሱ አንድንሰግድ መጽሐፍ አላዘዘንም" አሏቸው። ያንን ወንድም አንገቱ ሳይ መቱት፤ ሕጋቸው እንደዚህ ነው።

ከዚያ፥ ማነቆ አመጡና አንዲታሰሩብት ለቅዱሳኑ ሰጧቸው። ያ ወንድም ለእግዚአብሔር ሰግዶ ለተጠራጣሪዎች ከባድ፥ ለአማኒዎች "ቀምበሬ ቀላል፥ ሸክሜ መልካም ነው"[344] እንዳለው እንደ ጌታ ቃል ልኳን ለሚያውቁ ለአማኒዎች ተድላ የሆነችውን ማነቆውን ተቀበለ።

ከዚያ፥ ከተላላኪዎቹ አንዱ፥ "ትናንሽ ልጆች ለምንድን ነው የምታመነኵሱት" አላቸው። ፩ ወንድም፥ "የቂርቆስ አድሜ ስንት ነበረ? ንገረኝ" አለው። ተላላኪው ዝም አለ።[345]

ከዚያ፥ ቅዱሳኑን ወሰዷቸው፤ መሄድ የማይችሉትን በሽተኞች ግን ለአገረ ገዢው አስኪነግሩት ድረስ አዚያው ከሀገሩ ሹም ዘንድ ተዋቸው። የሄዱትን ግን አምለክ ከምትባል አገር አድርሰው አዚያ አደሩ፤ ቀኑ ዓርብ ነበረ። በማግሰቱ (131^ሰ) ወደ አገረ ገዢው ሊወስዷቸው መጡ። "ዛሬ ሰንበት

---

341. ከሌላ ገጽ ላይ "ውድ"፥ "ወድ" ይለዋል።

342. አዚህ "ወልመ" ብሎታል።

343. ? ሌላ ቦታ "እብሬታ"፥ "እብረታ" ይላል፤ ትክክሉ አይታወቅም።

344. ማቴ 10: 29።

345. ቅዱስ ቂርቆስ ከእናቱ ከቅድስት ኢየሉጣና ከሌሎች ምእመናን ጋራ ለጣኦት አልሰግድም ብሎ ስማዕትነት የተቀበለ የሚጠባ ሕፃን ነበረ፤ ስንክሳራችን የስማዕታቱን ቍጥርና ስማዕት የሆኑበትን ቀን እያለያየ መዝግቦታል፤ ጥር 15፥ ጥር 16፥ ሐምሌ 19፥ ሐምሌ 20ን ተመልከት። ቂርቆስን በሀገራችን ሕዝቡ ጨርቆስ ይሉታል።

ነው" በማለት እምቢ አሏቸውና ከአንድ ቤት ተሰባስቡ። ወታደሮቹ ከዚያም ሊያስወጧቸው መጡ። እጅ ለእጅ ተያይዘው አንወጣ አሉ። በግድ አውጥተዋቸው ብዙ ድብደባ ደበደቧቸው።

(ከዚያ ሌላ) የሚያደርጉትን ሲያጡ ተዋቸው፤ እዚያው አደሩ። ለመምጣት እምቢ እንዳሉ ለአገረ ገዢው ነገሩት። አገረ ገዢው እዚያው እንዲገድሏቸው አዘዘ። በማግስቱ አሑድ ተንኮል ሊሠሩባቸው መጡና፥ "እናንተ መቊረብ አትፈልጉም ወይ?" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "መቊረብ አንጠላም" አሏቸው። "መቊረብ ከወደዳችሁ፥ ኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ" አሏቸው። ቅዱሳኑ ግን ወደሚገድሏቸው ቦታ እንደሚወስዷቸው ዐወቁ። ስለዚህ ነው "መቊረብ አትፈልጉም ወይ?" ያሏቸው። ከዚያ፥ ቅዱሳኑን ወደሚሠዋቸው ቦታ ወደ ምድረ በዳ ሄዱ። ቅዱሳኑ ወደ ምድረ በዳ መሄዳቸውን ሲያዩ፥ "የቤተ ክርስቲያን መንገድ ይኸ ነውን? ለእግዚአብሔር ምለጋና (132[ሀ]) ይድረሰው" (አሉ)።

አሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ "የጽድቅን መሥዋዕት፥ መባውንም፥ ቍርባኑንም ስትወድ በዚያን ጊዜ ፍሪዳዎች ወደ ምሥዋዕህ ላይ ይወጣሉ"[346] የሚለው የነቢዩ ንግግር እነሆ በክርስቶስ ባሮች ላይ ተፈጸመ። በእርግጥ ያን ዕለት የክርስቶስ ባሮች ከቀኑ ፫ ሰዓት ላይ በዕለት አሑድ በምድረ በዳ ከሚሠዋቸው ጋራ ከእግዚአብሔር ምሥዋዕ ላይ ወጡ። ቃኤል በልቡ ተንኮል ይዞ ወንድሙን አቤልን፥ "ና በዱር ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንሠዋ"[347] እንዳለው እነዚህም ሠዊዎች የክርስቶስን ባሮች፥ "ለመቊረብ ኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ" አሏቸው። አቤልስ የወንድሙን ክፋት ሳያውቅ በፍቅር ተከተለው። እነዚህ የእግዚአብሔር ባሮች ግን እነዚያ ሠዊዎች እንደሚሠዋቸው እንደሚገድሏቸው እያወቁ ለአቤዩ፥ በዚያን ጊዜ በደስታ ይደሰታሉ፥ ቅዱሳኑ ውስጥ የዐጥንታቸውን መዓዛ ያገኙለታል"[348] ያለው የመልአኩ ቃል በነሱ ላይ ይፈጸም ዘንድ ከምድረ በዳው እስኪደርሱ ድረስ ተከተሏቸው።

ብእሴ ስላምና ሳሙኤል ሌሎችን አስገደሉ

(132[ለ]) ወታደሮቹን በምድረ በዳው ስብሰባ አድርገው አገኟቸው። ከዚያ፥ ተሳላኪዎቹ፥ ሹማምንቶቹ፥ ታላላቆቹ፥ እነዚም መነኮሴዎች፥ ብእሴ ስላምና ሳሙኤል መጡ። ቅዱሳኑን ከፍርድ አደባባይ አቆሟቸው። ያ ሳሙኤል የሚባለው መነኮሴ እንደ ልማዱ ለንጉሡ ስለ መስገድና መምህራቸውን ስለ መስደብ ጠየቃቸው።

ከዚያ፥ ፩ ወንድም፥ "አንተ እንዲህ ያለ ጥያቄ የምትጠይቀኝ አንተ ምን ሆነህ ነው? ከንጉሡ ወታደሮች ከሆንክ የእንጦንስ ገንዘብ የሆነውን ቆብህን አውርድ፤ መነኮሴ እንደሆንክ በላይህ ያለውን ልብስ፥ የመኳንንቱን ልብስ፥ አስወግድና ከዚያ በኋላ ጠይቀኝ" አለው። ይኸንን ሲለው ዝም አለ።

---

346. መዝ 50: 19/20።

347. የገደለው አርግጥ "ና ወደ ዱር እንሂድ" ብሎ ወስዶት ነው፤ ዘፍ 4: 8። "በዱር ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንሠዋ" ማለቱን የሚመስክር ምንጭ ግን አላነበብኩም።

348. ሄኖ ክፍል 24, Knibb, *Enoch*, p. 90.

ደግሞ፥ "ቁሰቻችሁ እዚህ አሉን? አላቸው። ፩ ወንድም፥ "ቅስናችንን ዛሬ ከእናንተ አንቀበላለን" አለ። ከዚያ፥ ያ መነኮሴ፥ "ቅስናህ ዛሬ ከእንድ ወታደር ጦር ይቺን ጦር ማግኘት ነው" አለ።

፩ ወንድም፥ "ልማዳችሁ ደም ማፍሰስ እንደሆነ ዐውቀናል፤ እናንተ ገዳዮች እኛ ስለ ክርስቶስ ሟቾች ነን" አለ። ያ መነኮሴ ተቆጣና፥ "እስጢፋ አርኩስ ነው ብላችሁ መምህራችሁን ስደቡ" አላቸው።

ቅዱሳኑ በየቃላቸው፥ (133[ll]) "አቡነ እስጢፋኖስ ቅዱስና ጻድቅ፥ ብርሃን ገላጭ[349] ነው፤ አቡነ እስጢፋኖስ ቅዱስ፥ ጻድቅ፥ ጠላት አሸናፊ ነው፤ አቡነ አስጢፋኖስ ቅዱስ ጻድቅ፥ የክርስቶስ ተከታይ ነው" አሉ።

ከዚያ፥ እንደ ንጉሡ ቃል አንዲገድሏቸው አዘዘ። እዚያ በዕለተ እሑድ በጦር ገደሏቸው።

ከነሱ ውስጥ ከነጓደኛዋ ከነሱ ጋራ ያመጧት አንዲት መነኮሲት ቅዱሳኑን ሲወጓቸው ስታይ አላያቸው ላይ ወድቃ ልብሳቸውን ያዘች፤ አሷንም ጓደኛዋንም እዚያው ወጓቸው።

በምድረ እምለከ የገደሏቸው ቁጥራቸው ፸ ነው። በጌንደት የተገደሉት ሰማዕትነታቸውን በጌታ ለላም የተቀዳጁት በማግስቱ መጋቢት ፸፩ ቀን ነው። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ይሁን፤ ለዘለዓለም ይጠብቀንም፤ አሜን።

ከዚያ፥ ልብሳቸውን፥ ቆባቸውን፥ ቀበቷቸውን፥ አስኬማቸውን ወሰዱባቸው። በሬሳቸው ላይ ካለው ልብስ እንዳችም አላስቀሩም። ዕንጨት ከምረው እሳት እነደዱና ልብሶቹን ጨመሩበት። የቅዱሳኑን ሬሳና አሳቱን አየዞሩ በከበሮና በከራር የወንጀል ዜማ አዜሙ፤ በማግስቱ (133[^]) በጌንደትም (እንደዚሁ) አደረጉ። "ጌታ እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች ጉድጓድ አስኪቈፍርና ለሚጸድቅ ፍርድ እስከመጣ ድረስ"[350] ታግሷል።

በምድረ ቆጌት የተያዙ 2 ወንድሞች

በዚያ ዕለት፥ አሑድ ቀን በምድረ ቆጌት ፪ ወንድሞች ያዙ፤ ከተደበቁበት አወጧቸው። በፊት ላኖራቸው ሰው (እንዲህ ብለው) ነገሩት፤ "እዚህ (አንተ ዘንድ) ቅዱሳን እግኝተናል" አሉት። ሲሰማ፥ የቅዱሱ ልጆች የተገኙበት ቤቱ እንዲመዘበር፥ እሱንም እንዲገድሉት ንጉሡ ሀዋጅ እንዳስለፈፈ ስለሚያውቅ ፈራ። ስለዚህ ራሱ ወደ አገረ ገዢው ወስዶ ለሞት አስረከበው። አገረ ገዢው ለንጉሡ ይሰግዱ፥ መምህራቸውንም ይሰድቡ እንደሁ እንደ ልማዱ ጠየቃቸው።

ሳሙኤል የሚባለውን በፊት "መስቀለ ሰላም" ባለ ጊዜ የንጉሡ ሎሌ "ለአስላም መስቀል" አለ ብሏቸው ይኸንን ወንድም አሳብቆበት በዚህ ምክንያት ብዙ ቀጥቶት ነበረ። በተንኮለኛ አጅ መድኃኒት በመጠጣትና በድብደባ ብዙ የቀጣው ወንድም ነው፤ ያቺ ዕለትም፥ "እኛ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አንሰግድም፥ መምህራችንንም ቅዱስና ጻድቅ ነው፤ እንሰድብም" አሉ፡

ከዚያ፥ አገረ ገዢው (134[ll]) በጦር እንዲወጓቸው አዘዘ። ወታደሮቹ ወጓቸውና እዚያ በምድረ ጌንደት ሰማዕትነታቸውን ፈጸሙ፤ የምስክርነት መቀዳጀታቸው የሆነው በመጋቢት ወር በ... ቀን በጌታ ሰላም ነው። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

---

349. "ከሣቴ ብርሃን"።

350. መዝ 93: 15።

ልብሳቸውንም በወንድሞቻቸው ላይ እንዳደረጉት÷ በእሳት አቃጠሉባቸው:: "ጻድቅ በቀልን ባየ ጊዜ ደስ ይለዋል፤ በኃጢአተኛ ደምም እጁን ይታጠባል"[351] እንደተባለው የሚበቀልበት ጊዜ ይመጣ የለምን?

"እንደ ፈሪ ... ፊቴን አልሸፋፈንም"

ይኸ ደውላይ የሚባል አገረ ገዢ ቅዱሳኑን በበሽታ ምክንያት መሄድ ስላልቻሉ በሹሙ እጅ ወደተወበት ወደ ሀገሩ ወደ ወልማ ሎሌውን ላከ:: ከዚያ÷ ከወልማ ሹም ዘንድ ደርሰው÷ "አንተ ዘንድ የተውናቸውን በሽተኞች አምጣ" አሉት:: የሀገሩ ሹም (አንዱን) ከታመሙበት ከአልጋው ላይ አውጥቶ ሰጣቸው:: ከአገረ ገዢው ዘንድ ሊወስዱት ፈለጉ፤ ግን መሄድ አልቻለም:: "ለንጉሥ ስገድ÷ መምህርህንም ስደብ" አሉት::

"እኔ ለአብ÷ ለወልድ÷ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ አልሰግድም፤ መምህሬንም ቅዱስ ነው፤ የሕይወትን መንገድ አስተምሮኛል (አላለሁ) እንጂ አልሰድብም" አለ::

ሲመሽ ወደ መኖሪያው መለሱት:: በማግስቱ እንደገና አውጥተው (134^ለ) ከጉባኤያቸው አዋሉት:: ብዙ ነገርም ጠየቁት:: አሱ ግን ከቃሉ ጽናት አልቀነሰለትም፤ አንዲያውም በመስቀል ረድኤት ተደግፎ (የባሰውን) ያይልና ይጠነክር ነበረ:: ከውስጣዊ የማወላወል ድልጫ (ለመዳን በረድኤቱ) ተመርኩዞ የተከራከሩትን ያሸንፍ ነበረ:: በዚያች ቀንም ሲመሽ ወደ መኖሪያው መለሱት:: እነሱ ሊያሳስቱት ተግተው ነበረ፤ ግን እግዚአብሔር ጠበቀው::

ከዚያ÷ በሶስተኛውም ቀን በጠና ታሞ ሳለ አውጥተው አገረ ገዢው ካለበት ከምድረ የጉንደት ሊወስዱት ፈለጉ:: እሱ ግን÷ "እኔ እዚያ ድረስ መሄድ አይቻለኝም፤ የምታደርጉትን እዚሁ አድርጉ:: ብቻ ፲ ሰዓት[352] ስለደረሰ ለአምላኬ እንድጸልይ ትንሽ ታገሡኝ" አላቸው::

ጸሎቱን ሲጨርስ ከፊታቸው አቆሙት:: ተሳላኪዎቹ የወልማን ሹም÷ "አንተ ራስህ ውጋው፤ ከሰዎችህ ጋራ ግደለው" አሉት:: ነጋሢው ያዘዘው እንደዚህ ነበረ--የእስጢፋኖስ ልጆች በተገኙበት እሱ (ሹሙ) እንዲገድል፤ አምቢ ካለ አብረው እንዲገድሉት:: ስለዚህ የወልማን ሹም÷ "አንተ (135^ሀ) ከሎሌዎችህ ጋራ አብረህ ግደል" አሉት::

የወልማ ሹም ጦር አነሣ፤ የሱ ሰዎችም ጦራቸውን አነሡ:: ከዚያ ወንድም ፊት ለፊት ቆሙና÷ "ፊትህን ተሸፋፈን" አሉት:: ያ ወንድም÷ "እንደ ፈሪ÷ የድካሜ ፍሬም እንዳይጐድልብኝ÷[353] ፊቴን አልሸፋፈንም" አላቸው:: ይኸንን ብሎ ልብሱን ከፊቱ ላይ አስወገደ፤ ደረቱንም አስፍቶ ልቡን ሰጣቸው:: ከዚያ÷ ይኸ በጎይለ ማርያም የሚሉት የወልማ ሹም ወጋው:: ፪ የሱ ሰዎችም ወጉት:: ስማዕትነቱን እዚያ በ፫ ሰዓት÷ በዕለተ ዓርብ÷ መጋቢት ፲ ቀን÷ በጌታ ሰላም ፈጸመ:: ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን÷ አሜን::

---

351. መዝ 57: 10/11::
352. "የጸሎት ጊዜ"::
353. "መጠንጢን ("ቊራጭ"÷ "ብጣሽ") እንዳይሆንብኝ"::

ከዚያ፥ ልብሶቹን፥ ቆቡን፥ እስኬማውን ወሰዱ፤ በአካላቱ ላይ ምንም አላስቀሩም። ዕንጨት ከምረው አሳት አንድደው ልብሶቹን አቃጠሏቸው፤ ጌታ ምርጠቹን ይረዳቸዋል። ፩ ወንድም ዘንድ ስለነዚህ ሰማዕታት ራእይ ሆነ። እንዲህ አለ፤

> በሰደት በነበርኩበት ጊዜ ስለ ቅዱሳኑ መገደል የሌሊት ራእይ አየሁ፤ ፊቴ ተሸፍኖ (135^ሀ) ከብርድ ብዛት የተነሣ መተኛት አቅቶኝ ከዛፍ ስር ቁጭ ብዬ፥ ቅዱሳን ሰማዕታትን በደስታ ብሩህ በሆነ ፊት በጥሩ ልብስ (ተጐናጽፈው) ሲሄዱ አየኋቸው። አካሂዳቸው ስብሐት የሞላበት፥ አፋቸው በረከት ሞልቶበት ልውሉን ሲያመሰግኑ፥ ከመጻሕፍት የስብሐቱን ባሕር ሲቀዱ፥ (ስብሐቱ) ካፋቸው ምን ጊዜም አይደርቅም። ቃላቸው ጣፋጭ ነው፤ ዜማቸው የሚያጓጓ ሆኖ የዝማሬያቸው ጣዕም እንደ ማር ነው፤ አፋቸው የወተት መስኖ ነው። ዝማሬው እንደማስታውሰው እንደዚህ ይላሉ፤ "ፈለጉን እንድንከተል ማዕተቡን ተወልን።" ደግሞ ብዙዎች ከሕያዉ የሰብሐት መጻሕፍት ይቀዳሉ። እኔ (ሁሉንም) ልይዘው አልቻልኩም። እንደዚህ እየዘመሩ ከዓይኔ እስኪሰወሩ ወደ ምሥራቅ አለፉ።
>
> ይሽንን ሳይ በጣም ተከዝኩና፥ "ይህቺ ሕይወቴ ምን ታደርግልኛለች?" አልኩ። ወደ አምላኬ እንዲህ ብዬ ጸለይኩ፤ "ከባሮችህ አትለየኝ፤ (136^ሀ) ከእስደስቱህ ቅዱሶችህ ዋሻ መኖርን ክፈለኝ፤ ስብሐት ለዘለዓለም ያንተ ነው፤ አሜን፥ አሜን።"

በምድረ ጠዞ በረኀብ የሞተው

በምድረ ጠዞ ከያዟቸው ቅዱሳንም ፩ዱን ሽማግሌ መሄድ ስላልቻለ ከመኖሪያው ተዉት። ወንድሞቹን ግን የወጊ ሀገር ገዢ ካለበት ወሰዷቸው። (ሽማግሌው) በጐንደትና በአምለክ እንደገደሏቸው ሲሰማ፥ "ከመኖር መሞት ይሻለኛል። እነዚያ ወንድሞቼ ስለ አምላካቸው ስም ያንን የጦር ስለት ተቀብለው የሞትን ምርረት ቀምሰዋል፤ እኔም ለአምላኬ ስም እሞታለሁ" አለ። ይሽንን ብሎ እህል ውሐ እንዳይቀምስ ለእግዚአብሔር ብፅዓት እደረገ። (የምግብ) ገበታ በመኖሪያው እያለ ስለ እግዚአብሔር ራሱን ዘጋ።

አንዲት ሴት መጥታ፥ "እባ ሆይ፥ እንደዚህ እታድርግ። እህል ብላ፤ እኔ በማናቸውም እገለግልሃለሁ" አለችው። "በውኑ ካሁን በፊት እምጥተሻልን?" (136^ሀ) ወይስ እንቅፋት ልትሆኚኝ ነው (ዛሬ) የመጣሽው? እኔ ቃሌን አላጥፍም" አላት። የቃሉን ፍጻሜ ስትሰማ ጥላው ሄደች።

ሲጠብቁት ቆዩ። ከዚያ፥ ፍጻሜው ሲደርስ ስለ ገንዘቡም፥ ከሱ ዘንድ ስላለውም እህል፥ "ይሽ ለናንተ ይሁን፤ ይሽንን ቅዱሳን የመጡ እንደሆነ እንድትሰጧቸው ከተቱት" አላቸው። "ቅዱሳኑን የት እናገኛቸዋለን?" አሉት። "ደቂቀ እስጢፋኖስን አታጧቸውም" አላቸው። ጧፍም እንዲህ ብሎ ሰጣቸው፤ "ይኼ ደግሞ እንዳትቸገሩ ሰፈጽም (ሰሞት) የምታበሩት ነው" ይሽንን ብሎ እህል ወሐ በተወ በዓሥራ... ቀን ወደ ማታ ላይ ገድሉን በጌታ ሰላም ፈጸመ፤ እዚያው ቀበሩት። ጸሎቱና በረከቱ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን፥ አሜን።

ምድረ ጋዘም ላይ የተያዙት ታረዱ

(137^ሀ) (ወንድሞች) በጐንደት በተገደሉ በሰባተኛው ወር፥ ፪ ወንድሞች ጉዳያቸውን ፈጽመው እብሶ ወዳለው ማኅበራቸው ሲመለሱ፥ ምድረ ጋዘም

ላይ ያዟቸው። ፩ ምእመንም አብሯቸው ነበረ፤ ገና ለምንኮስና ከዓለም መውጣቱ ነበረ። የወድ አገረ ገዢ በቅሎዎች እረኛ አግኝቶ በተንኰል አነጋገራቸው። የሰውየው ስም ደሐረጎት ይባላል። ገንዘባቸውንም እንደሚወስድባቸው፥ እነሱን ግን እንደሚያሳልፋቸው ነገራቸው።

"እንደ ፈሪ ሃይማኖታችንን በገንዘብ እንለውጣለንን? ካሳለፍከን ከነገንዘባችን አሳልፈን፤ አለዚያ ገንዘባችንን እንለቅልህም" አሉት። ከዚያ፥ የወድ አገረ ገዢ ካለበት ወሰዳቸው። (አገረ ገዢው) በዚያን ጊዜ በሹመቱ ቦታ በየጐንደት ነበረ። አዚያ አምጥተው ከአገረ ገዢው ፊት አቆሟቸው፤ የሀገሩ ሹም ገብረ ክርስቶስ የሚባለውን ምእመን፥ "ይኸስ ቶሌ ይከዳል" ብሎ ከቅዱሳኑ ለይቶ ተገናኘው። ቅዱሳኑን ለንጉሡ ይሰግዱ፥ (137^ሀ) መምህራቸውን ይክዱ እንደሆነ ጠየቋቸው።

፩ኡ ብርሃን መዋኢ የሚባለው ወንድም፥ "እኛ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለሌላ (ለባዳ) አንሰግድም፤ በሥላሴ ላይ አራተኛ አንጨምርም፤ መምህራችን ቅዱስ፥ የክርስቶስ ተከታይ ነው፤ አንስድበውም" አለ።

የአገረ ገዢው ሎሌዎች ተሰብስበው በብዙ ማስፈራራት ገላመጧቸው። ቅዱሳኑ ግን ሳቁባቸው፤ አገረ ገዢውንም ተጠቃቀሱበት። ሎሌዎቹ ደበደቧቸው። አገረ ገዢውም እንዲህ ሲል በቁጣ ተነሣ፤ "ጌታዬን ንጉሡን ባዳ እደረገው::"[354] ይኸንን ብሎ ከመሬት አስኪወድቁ ድረስ በበትር ደበደባቸው። በድንጋይም ወገሯቸው። ከዚያ፥ ቢላዋ እምጥተው እረዷቸው። በጌታ ሰላም ሰማዕትነት የተቀጋጁት ነሐሴ ... ቀን ነው። ጸሎታቸው ከኛ ጋራ ትሁን፤ ለዘለዓለም ትጠብቀንም፤ አሜን፥ አሜን።

(138^ሀ) ከዚያ፥ ያንን ገብረ ክርስቶስ የሚባል ምእመን በማግሥቱ አመጡት። አንተስ ምን ትላለህ? ወደ ሀገርህ አትመለስምን? ወይስ መሞት ትፈልጋለህ?" አሉት። "እስቲ ቅዱሳኑ ያሉበትን አሳዩኝ" አላቸው። "ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ?" አሉት። "እስቲ እኮ አሳዩኝ፤ የምፈልገውን ያን ጊዜ ታውቃላችሁ" አላቸው።

ወደ ቅዱሳኑ በድን ወሰዱት፤ እሱም ግዴታውን ወዲያው እንደሚያደርገው እየተማመነ (አብሯቸው) ሄደ። ምክንያቱም በፊትም ጽድቅን ፈላጊ ነበረ፤ (መጠበቅ) የሚገባቸውን ሰንበቶችና በዓሎች ስለ ማክበር፥ የሌላ ሰው ገንዘብ ስለ መውሰድ፥ በውሸት ስለ መመስከር፥ ስለ መሳደብም፥ ሌላ ስለ ማምለክም፥ መድኃኒት ስለ መቀመም፥ ቅዱሳኑ ባስተማሩት ሥርዓት ራሱን የሚጠብቅ ነበረ። የቀንና የሌሊት ጸሎቶችን አያስታጉልም ነበር፤ ቅዱሳኑንም በፈለጉት ሁሉ ያገለግላቸው ነበረ።

የቅዱሳኑ ሬሳ ካለበት ሲደርስ አይቶ፥ "የጸሎታቸው በረከት እንዲደርሰኝ እኔም ይኸንን አፈልጋለሁ፤ በሞቴም (138^ሰ) በሕይወቴም ከነሱ አልለይም" አለ። ይኸንን ብሎ ከቅዱሳኑ ሬሳ ላይ ወደቀ።

ሎሌዎቹም ድንጋይ አንሥተው አዚያው ወገሩት። በጌታ ሰላም ሰማዕትነት የተቀዳጀው ነሐሴ ፳፰ ነው። ጸሎቱ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን፥ አሜን።

---

354. እንደተጻፈው ከሆነ፥ እነሱ ያሉት "ስሌላ" (ለባዕድ) እንሰግድም ነው፤ አማርኛው "ሌላ" ሲሆን ግዕዙ "ባዕድ" ነው። ታዲያ በምን ቋንቋ ቢያነጋግሩት ነው የግዕዙን "ባዕድ" ያገኘው? በግዕዝ ነው ወይስ ዛሬ "ሌላ" የምንለው በዚያን ጊዜ በግዕዝም በአማርኛም "ባዕድ" ነበረ?

(እንዱ) የቅዱሳኑን (ቢድን) ባየ ጊዜ÷ "እስካሁን አሉ እንዲ? ጅብም አልበላቸው?" ብሎ ረገጣቸው:: ይኸንን ብሎ ወደ መኖሪያው ተመለሰ:: ሲመሽ በዚያው ሌሊት ጅብ መጣና የዚያን ሰው እግሩን ጎትቶ ገደለው:: እግዚአብሔር ስለ ባሮቹ እንደዚህ ሁል ጊዜ በቀል ያሳያል:: ቅዱሳኑን በጉንደት[355] ያስገደለውን ሳሙኤልንም በዚያ በተንኮለኛ እጅ ወገረው:: በመግረፊያው ጅራፍ ገረፈው:: ወደ ሌላም ወስዶት ክፉ ሞት ሞተ::

አባ ዘታኦስ ዘሰርማት ያመጡት ጉዳት

(ቅዱሳኑ) በጉንደት[356] በተገደሉ በ፪ ዓመት÷ ፩ (ዘታኦስ) የሚባል መነኮሴ የሰርማት መምህር ስለ ቅዱሳኑ የውሸት ደብዳቤ ጽፎ ከንጉሡ ዘንድ አመጣ::

ንጉሡ የደብዳቤዋን ቃል ሰምቶ (139ᵛ) ዓምዱ ለሚባለው ለፊጸጋር አገረ ገዢ በሀገሩ (በግዛቱ) ያሉትን ቅዱሳን እንዲያመጣቸው ነገረው:: እሱም እነሱ ዘንድ ያሉትን ቅዱሳን እንዲሰጧቸው የንጉሡን ተሳላኪዎች ለሀገሩ ፫ ሹማምንት ሳከላቸው::

የንጉሡ ተሳላኪዎች ከነዚያ ሹማምንት ጋራ በየሀገሩ ሄዱ:: ዘታኦስ የሚባለው መነኮሴም እብሯቸው ሆኖ (ተሳላኪዎቹን ወደ ቅዱሳኑ) ወሰዳቸው:: ቅዱሳኑ በስደት በሀገሩ ዱር ይኖሩ ነበረ:: እንኮይ÷ ናኬ÷ ኮሽም÷ ጣንጦ÷ ቀምጠሮ የሚባሉ የዛፍ ፍሬዎችና ከስራ ስርም ቀጠቤሉ÷ ኡስስ የሚባሉ÷ ከዛፍ ቅጠልም ቀረም የሚባል ከምድር እትክልትና ከእህልም ሲያገኙ ይበሉ ነበረ:: ከሰው ሲደርሱም ወንዱንም ሴቱንም ያስተምሩ ነበረ:: እነሱም ሲያዳምጧቸው ሕሊናቸውን ለቅለው ነበረ:: ከዓለማቸው እየወጡም ከነሱ ጋራ ይደባለቁም ስለነበረ ብዙዎች ሆኑ::

ሲዲ የሚባለው የዚያ ሀገር ሹም በዚህ ምክንያት ቂም ነበረው:: እነዚያን የንጉሥ ተሳላኪዎች ምክንያት አግኝቶ በውሾች እና (139ᴬ) በሰዎች እደናቸው:: ከዱር ሰበሰባቸው:: በማነቆ እንደታሰሩ ወስደው ከንጉሡ አደባባይ አመጧቸው::

(ንጉሡ) በዚያን ጊዜ ከደብረ ብርሃን ነበረ:: ለንጉሡ ነገሩት፤ ንጉሡ ወደ ሰፈሩ ውስጥ በስተግራው የነፋስ መምጫና የብርድ መውረጃ በሆነችው በመጋራዳ በኩል እንዲያስገቧቸው አዘዘ:: ወታደሮቹ እንዳዘዛቸው አደረጉ፡ የካቲት ፬ ቀን አስገቧቸው:: እህልም ውሐም ሳይሰጧቸው ፲፬ ቀን ተቀመጡ::

ከዚያ÷ በእህልና በውሐ የሚረዷቸው ወንድሞች መጡ:: እሱም ቢሆን አተርና ምስር ሌላም እህል ነው:: አንዳንድ ቀን ሲበዛ አንድ እጅ ሙሉ ይደርሳቸዋል:: ያነሰ ቀን ለ፪ ለ፫ ያዳርሱታል:: እንጀራ ሲያገኙ አንዳንድ ቀን አንዱ ለአራት ይደርሳቸዋል፤ አንዳንድ ቀን (አንዱ) ለ፫ቱ (ይደርሳቸዋል):: ውሐም እንደዚሁ ነው::

እነዚያ የሚረዷቸው ወንድሞች (ከአስር ቤት) የሚያገቡላቸው ራሳቸው አይደሉም:: ምክንያቱም ጠባቂዎቹ ማንንም ሰው ወደ ቅዱሳኑ እንዳያስገቡ÷ ከነሱም ማንም እንዳይወጣ ንጉሡ አዟቸው ነበረ:: ስለዚህ (140ᵛ) የሚረዷቸው ወንድሞች መግባት አይችሉም ነበረ:: ዘበኞቹ

355. እዚህ "በጉንደን" ተብሎ ነው የተጻፈው::

356. አሁንም "በጉንደን" ብሎታል፤ ትክክሉ የቱ እንደሆነ አጠራጠረ::

እንዲያገቡላቸው ዋጋ ይከፍሏቸው ነበረ። ዘበኞቹ ተቀብለው ያገቡላቸዋል። እነሱን ግን እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም።

ስለዚህ ከምእመናንም በእህልና በውሐ የሚረዷቸው ነበሩ። ንጉሡ ይኸንን ከአሳባቂዎች ሰምቶ፥ ዘበኞቹን እንዲህ ሲል አዘዘ፤ "እኔ በቀጣሁት (ሰው) ላይ ደግ የሚሠራ ሰው ማነው? ወይ አርፎ ይቀመጥ ወይም ካሳረፈ ለራሱ ይወቅበት።" ዘበኞቹ (ይኸን ሲሰሙ) ፍርሃት ወደቀባቸው። ቢሚረዷቸው ላይ አጠበቡባቸው። በቅዱሳኑ ዘንድ ትልቅ ገድል ሆነ--በተለየም በውሐ ጥም።

የወንድም ገብረ ዋሕድና የእማሆይ ማርያም ሠምራ ጸሎት

ከብዙ ቀኖች በኋላ፥ ከነሱ ውስጥ ገብረ ዋሕድ የሚባል ወንድም ተነሥቶ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "አንተ ጌታ እግዚአብሔር፥ ከዚህ አለት ድንጋይ ውሐ ብታወጣ ምን ያቅትሃል?" ይኸንን ብሎ አለቱን ድንጋይ ቆፈረው፤ ድንጋዮቹን ፈነቀላቸው። እንዲት ማርያም ሠምራ የምትባል አሮጊት መነኮሲት እብራው ትጸልይ ነበረ። ከዚያ አለት ድንጋይ ውሐ ወጣ፤ ሁሉም ከሱ ጠጡ። (140[ሀ]) አብረው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

ቄፈን የሚያመጣ የደብረ ብርሃን ብርድ

እነዚያን ይረዷቸው የነበሩትን ወንድሞች ያ ሲዲ የሚሉት የሰገቢ ሹም ያዛቸውና ለንጉሡ ነገረባቸው። ንጉሡ ወንድሞቻቸው ዘንድ መገርዶ[357] እንዲያስገቧቸው አዘዘ። ወንድሞች እዚያ በነበሩባቸው ፱፪ ቀናት በምግብ እጦት እና በቀን በፀሐይ ሙቀት ትልቅ ፈተና ወደቀባቸው። እዚያ ጥላ የሚያገኙበት ዛፍም ቅጠልም የለም። የሚደገፉት ግምብም ግድግዳም የለም፤ ሜዳ[358] ነው። የሌሊት ብርድም ፊት ከሚያጠቁር ከጽኑ ነፋስ ጋራ አለ።

በፊት ይረዷቸው የነበሩትን ሲይዟቸው ሌሎች ወንድሞች መጥተው ይረዷቸው ጀመረ። መግባት አይቻላቸውም፤ ግን ፊት ለፊት ያዩዋቸው ነበረ። ሲያገኙ ለዘበኞቹ ይሰጧቸዋል። እነሱም ያገቡላቸዋል።

አባ ዕዝራ የያዟቸው በቀጋ እሾክ ተገረቆ

ሌሎች ወንድሞች ከፈጸጋር ወደ ማኅበራቸው ወደ እብሶ ሲመጡ መነኮሲቶችም አብረዋቸው ነበሩ--ዕዝራ የሚሉት አንድ መነኮሴ ያዛቸው። የያዙትን ገንዘባቸውን በሞላ ነጠቃቸው። ልብሳቸውንና የምንኮስና ቀሚሳቸውን (141[ሀ]) ቆባቸውንም (ወሰደባቸው)። በበትርና በጥፊ ከፍ ያለ ድብደባ ደበደባቸው። እሱና የንጉሡ ሎሌ ሆነው ሥጋቸው እስኪበጣጠስ ድረስ በቀጋ እሾክ ገረፏቸው። ገንዘባቸውን ከነጠቋቸው በኋላ፥ እነሱንም ለንጉሡ ወታደሮች አሳልፈው ለጧቸው።

ወታደሮቹ ወስደው ከንጉሡ ፊት አቆሙና፥ "ለንጉሡ ስገዱ፥ መምህራችሁንም ስደቡ" አሏቸው።

ቅዱሳኑ፥ "እንድንሰግድለት (የሃይማኖት) ሕግ አላዘዘንም፤ መምህራችንም ቅዱስ ነው፤ እንሰድብም" አሉ።

---

357. ከላይ "መጋርዳ" ያለውን ቦታ ነው።

358. በትግሪኛ "ጐልጐል" ተብሎ ነው የተጻፈው።

ንጉሡ አንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "የት ነበራችሁ? የያዟችሁ ወዴት ስትሄዱ ነው?" ቅዱሳኑ÷ "ችግራችንን ከምናስወግድበት ላይ ነበርን፤ የምንሄደውም ወደ ወጊ ነበረ" አሉ:: ከዚያ÷ "ወደ ጉራጌ የምትሄዱት÷ ቤተ ክርስቲያን ወደሌለበት ወደ ደስክ ነውን?" አላቸው::

ቅዱሳኑ÷ "የቤተ ክርስቲያን ልጆች ስለሆንን የምንሄደው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንጂ ወደ ደስክ አይደለም" አሉት::

"በጉራጌ ምን ቤተ ክርስቲያን አለ?" አላቸው::

ቅዱሳኑ÷ "ንጉሥ ይሥሐቅ የተከላት ህገረ ማርያም አለች" አሉ::[359]

ከዚያ÷ ንጉሡ ወደ መድኃኒት ቤት (141^ሀ) ወስደው መድኃኒት አንዲያጠጧቸው አዘዘ:: (ይኸን የሚያደርገው) የሚፈልጋቸውን ነገሮች የሚያገኝባቸው አንደሆን በማሰብ ነው:: ወደ መድኃኒት ቤት ወሰዷቸው:: መድኃኒቱን[360] በማጠጣት ብዙ አስጨነቋቸው:: መነኮሲቶቹን የገሰብም ወደምትባል ወደ ሌላ ቦታ ወሰዷቸው::

በገን ያሉት ደቂቀ እስጢፋኖስና ነገረ ፈጃቸው

በገን[361] ባሉት ቅዱሳንና አዚያ ላሉ ቅዱሳን ነገረ ፈጃቸው በሆነው በአንድ ወንድም ላይ (እንዲህ) ሆነ፤ ወደ ዱር ሄዶ እንዲጸልይ ከወንድሞቹ ፈቃድ ለመውሰድ ሲጠይቅ÷ "አንተ የምትፈልገው እዚያ መሞት ነው፤ እኛም አቅመ ቢሶች ሆነን እንወድቃለን፤ ስለዚህ ፈቃድ አንሰጥህም" አሉት::

እሱም÷ "ያለፈቃዳችሁስ ከሞት አልገባም፤ በጸጥታ እንድጸልይ ነው እንጂ:: ስለዚህ እንድትፈቅዱልኝ እጠይቃለሁ" አላቸው:: አንዲጸልይ ፈቀዱለት::

ሄዶ ከአንድ ዋሻ ገባ፤ (ዋሻው) ከገደል ውስጥ ስለሆነ በገመድ አወረዱት:: በዚህ ሁኔታ ሲጸልይ ቆየ::

ከሿ ቀን በኋላ÷ ወንድሞቹ መጥተው÷ "አባ ሆይ÷ የኔፍስ ችግር ገጥሞናልና ወደኛ ውጣ" አሉት:: "አይሆንም" አላቸው:: (142^ሀ) "ስለ አግዚአብሔር (አንዲህ) አታድርግ" አሉና በብዙ ልመና አወጡት::

ከዚያ÷ አንድ ቀን ተሰብስበው ባሉበት ጊዜ÷ የንጉሡ ተላላኪዎች መጡና ከ፭ ወንድም ጋራ ያዙት:: ሌሎቹ ወንድሞች ግን ተበተኑ:: (ግን) አንደያዙት ሲሰሙ አነሱም ተጨመሩ::

የንጉሡ ወታደሮችና ተላላኪዎች መምህራቸውን ያዝነው ብለው ጨፈሩ:: ወሰዷቸውና ከንጉሡ ዘንድ አደረሷቸው፤ ከንጉሡ ፊት አቆሟቸው:: (ለንጉሡ አትሰግዱም ወይ ቢላቸው)[362] "አምን÷ አንሰግድም" አሉ::

ደግሞ÷ "መምህራችሁን ስደቡ፤ አስጢፋኖስ እርኩስ ነው በሉ" አሏቸው::

---

359. ወንድሙ ንጉሥ ይሥሐቅ አባታቸውን አባ አስጢፋኖስን አንዳከበራቸው ሳያውቅ አይቀርም፤ እሱ ግን ያስጠነቀላል ብሎት አምቶት ነበረ፤ Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity*, p. 114. ዘርአ ያዕቆብ ያማውን አነሱ ያመስገኑት አጋጣሚ ሳይሆን አነሱን ስላከበራቸው ሊሆን ይችላል::

360. ኮሶ::

361. ገኒ÷ ገይኒ÷ ገኝ::

362. ቀጂው ጥያቄውን ገድፍት እንደሄደ ግልጽ ነው::

ፍሬ ክርስቶስ የሚባለው ወንድም÷ "አስጢፋ" በግብጽ ቋንቋ የሰይጣን ስም ነው። መምህሬ ስሙ አስጢፋኖስ ነው። እናንተ ግን በሰይጣን ስም አስጢፋ ትሉታላችሁ። መምህሬ አስጢፋኖስ÷ በሥራው ሁሉ ቅዱስ ስለሆነ አልሰድበውም" አላቸው።

ንጉሡ የቃሉን ጽናት ሲያውቅ እንደፊተኞቹ ወንድሞቹ ወደ መድኃኒት ቤት እንዲወሰዱት አዘዘ። ከ፬ ወንድሞች ጋራ ወስደው÷ መድኃኒት በማጠጣት ብዙ ቀኖች አስጨነቁት።

(ይኸን የሚያደርገው) ስሕተቶች የሚያገኝባቸው መስሎት ነው። ቅዱሳኑ ግን (142^ሀ) ቃለ መለኮት ከማንበብ በቀር እንዳሰበው ስሕተቶች አልተገኘባቸውም። የፊተኞቹ ወንድሞችም እንደዚሁ ምንም አልተገኘባቸውም። አራቱም እዚያው አብረው በረኀብና በብርድ ማዕገጽ[363] እየበሉ ብዙ ቀናት ኖሩ። ሲያገኙ ጥሌ የሚሏት ቤሳ ይሰጧቸው ነበረ።[364]

የለከማ እስረኞች÷ እነ አባ አቡናፍር

ንጉሡ ቅዱሳኑን ይዘው እንዲያመጡለት ተላላኪዎቹን ከብዙ ሠራዊት ጋራ ወደ ትግራይ ምድር ላከ። ለከማ ከምትባል ሀገር ደረሱ። አቡናፍር የሚባል ጻማ የለበሰ አንድ ሽማግሌ አገኙ፤ ያዙት። ሲያዩት÷ "መምህራቸውን አገኘነው" ብለው ጨፈሩ። "መምህራቸውን ይዘነዋል" ብለው ወደ ንጉሡ ላኩ።

ንጉሡ ሲሰማ ተደሰተ፤ ቶሎ እንዲያመጡት አዘዘ። ተላላኪዎቹ ቶሎ ቶሎ እንዲሄድ ያጣድፉት ጀመር። ሲሄዱ ደክመ። ምክንያቱም ሽማግሌ÷ ጻማ ለባሽ÷ ከተንኮለኛው ንጉሥ የሰይጣን መልእክተኞች (143^ሀ) በሆኑ ሠራዊቱ (እጅ) በድብደባ÷ በግርፊያ÷ በፊትም እያንዳንዱን በአረሚው አገር ውስጥ በእስራት÷ በውሐ ጥም÷ በግርፊያ÷ እንዲኖሩ በበተናቸው ጊዜ በመሰደድ ሥቃዮችን የተቀበለ ነበረ። የዚህ ሽማግሌ (ገድል) ብዙ ነው፤ ከግርፊያው ብዛት የተነሣ ሥጋው የተጠበሰ ይመስላል።

በዚያች ዕለትም ሲደክመው ጊዜ÷ "ስለደከመኝ÷ መሄድ አልተቻለኝም" አላቸው። በዚህ ጊዜ የንጉሡ ተላላኪዎች በቁጣ ተነሡበትና÷ ከምድር ላይ ጣሉት÷ እንደ በሬ አስተኝተው ሥጋው እስኪላላጥ ድረስ እንደ ግንድ በመራት ላይ ጐተቱት። ደሙ ይፈስ ነበረ። በዓይናቸው ፊት ምሕረት የሌለባት ከመራሮች የወጡ ናቸው። ስለ ሽምግልናው ወይም ስለ ምንኵስና መዓዝ ወይም ስለ የዋህነቱ ብለውም አልማሩትም። እሱ ግን በትዕግሥት ዝም ብሎ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበረ።

በዚህ ሁሉ ሥቃይ ላይ ሆኖ ከሚያድሩበት ቦታ አደረሱት። ዕለቱ ዓርብ ነበር፤ ማግስቱን ወንድሞቹን በብዙ ተግሳጽ ምዕዳን ሲያስማቸውና ሲመክራቸው÷ (143^ሀ) ሲያስረዳቸው ሲደክም ዋለ። እሑድ በመጋቢት ፱ ቀን ምስክርነቱን በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ ለዘለዓለሙ ይጠብቀን፤ አሜን።

ካረፈም በኋላ አልለቀቁትም፤ ሬሳውን ተሸክመው ከንጉሡ ችሎት አመጡት። (ሰማዕትነቱን) እንደፈጸመና ሬሳውንም እንዳመጡ ለንጉሡ

363. ማዕገጽ ምንድን ነው?

364. ጥሬ ገንዘብ ነበረ ማለት ነው። ቃሉ "ጽሌ" ("ሰሌዳ") ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ከሆነ "ቤሳ" ከማለት ይልቅ "ጠገራ" ብሎ መተርጐም ይሻላል። ("ጠገራ" እንደ ገንዘብ የሚያገለግል ጥፍጥፍ ነሐስ ነበር።)

ነገሩት። በጦርነት ድል እንደነሣ (ሰው) ሆ አሉ። ለዚያ ተንኮለኛ የቅዱስና የብፁዕ አስጢፋኖስ ሥርዓት የሚጠፋ መስሎታል። እግዚአብሔር ከምሕረቱ ብልጽግና አንደሚመግባት ከከፍተኛ ወደ ከፍተኛ እንደሚያመጥቃት አሳወቀም።

ንጉሡ የሬሳውን የእጁንና የእግሩን አባሎች ቆራርጠው በእሳት እንዲያቃጥሉ፥ አመዱንም ከወንዝ እንዲጥሉት እዘዘ። ወታደሮቹ ንጉሡ እንዳዘዛቸው እደረጉ፤ የቅዱሱን ሥጋ አቃጥለው አመዱን ወይራር ከምትባል ወንዝ ጣሉት።

በመድኃኒት ቤት ካሉትም፥ ፩ዱ በዚያ መድኃኒት በመጠጣት ታሞና ብዙ ሥቃዮች እሳልፎ ሰማዕትነቱን በሚያዝያ ፮ ቀን (144[ሀ]) በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

የመጋርዳ እስረኞች

እነዚያም በመጋርዳ ከእቅራቢያው ያስቀመጣቸው ቅዱሳን በነዚያ ሥቃዮች በቀን በፀሐይ ሙቀት፥ በሌሊት ብርድ መውረድ፥ ከረኀብና ከውሐ ጥም፥ ከመራቆትም ጋራ እስከ አሁን አሉ።[365]

ከዕለታት አንድ ቀን፥ በንጉሡ አደባባይ፥ "ይኽ ቢወርድበት ከዚህ ማን ይድናል?" እስኪሉ ድረስ ቤት የሚጥል ታላቅ በረዶ ከታላቅ ነፋስ ጋራ ጣለ። የበረዶውና የዝናሙ መውረድ ሲያባራ ሰዎች ወጥተው ቢያዩት፥ የተሰጣ ልብስ ይመስላል። ቅዱሳኑ ካሉበት ግን በረዶ አልጣለም። እግዚአብሔር ድኽነታቸውን አይቷልና።

እንዳንድ ሰዎች ስለነዚህ ቅዱሳን፥ "ቅዱሳን አይደሉምን? አግዚአብሔር ይረዳቸው የለምን? (ካሁን በፊት) ውሐም እመንጭቶላቸዋል፤ አሁን ደግሞ፥ ከዚህ በረዶ መውረድ እዳናቸው፤ በአርግጥ ጻድቃን ናቸው" አሉ። እንዳንዶቹ ደግሞ፥ "ይኽንን የሚያደርጉት በመድኃኒታቸው አይደለምን?" አሉ።

የመጨረሻው ታላቅ ጉባኤ

ቅዱሳኑን እዚያ (144[ሀ]) መጋረዶ ባስገቧቸው በሮች ቀን ንጉሡ ሠራዊቱንና የራሱን መነኮሴዎች እሱ ዘንድ እንዲሰበሰቡ እደረገ። እንዳዘዘው መጡ፤ ትልቅ ጉባኤ ሆነ። በመጋረዶ ውስጥ ያሉትንና በመድኃኒት ቤት ያሉትን ቅዱሳን አምጥተው ከፊቱ እንዲያቆሟቸው እዘዘ።

ወታደሮቹ እያጣደፉ አመጧቸውና፥ "ለንጉሡ ስገዱ" አሏቸው። ቅዱሳኑ፥ "በየቀኑ ስንሰደድ፥ ስንገረፍ የኖርነው በምን ምክንያት ሆነና? በዚህ ምክንያት አይደለምን? እኛ አንሰግድለትም" አሉ።

ከዚያ፥ በእባታቸው ትምህርት ላይ እንዲከራከሯቸው እንዲህ ሲል አዘዘ፤ "አባታችን ቀጥተኛዋን[366] ሃይማኖት አስተማረን የምትሉት ምንድን ነው? አባታችሁ ማርያምን የሚክድ፥ ነቢያትንና ሐዋርያትን የሚሳደብ ነው።"

---

365. "አሁን" የሚለው የትኛውን ጊዜ እንደሆነ አይታወቅም፤ መጽሐፉ ተጽፎ የተጨረሰው አፄ ዘርአ ያዕቆብ ከሞተ በኋላ መሆኑ አያጠራጥርም፤ መግቢያውና መደምደሚያው ያስረዳሉ።

366. "ኦርቶዶክሷን"።

ፍሬ ክርስቶስ የሚባል ፩ ወንድም፡ "መምህራችን ሕግን በእውነት የሚፈጽም እንጂ ማርያምን የሚክድ፡ ሐዋርያትንና ነቢያትን የሚሰድብ አይደለም" አለ።

ንጉሡ፡ "እነሆ የሚያውቁትም፡ በወሬ የሰሙም መስካሪዎች አሉልህ፤ እንግዲህ የአባትክን ሥራ ሲመሰክሩ ስማ" አለና መድረክ አዘጋጁ። ፩ (145^{v}) ሲኖዳ የሚሉት ውሸት ልማዱ፡ ኀጢአት ጥጋቡ፡ የእውነት ጠላት መነኮሴ መጣ። ካሁን በፊትም አባታችንን ከንጉሡ ላይ የከሰሰው እሱ ነበረ። ያን ዕለትም በዚያ መድረክ ላይ ቆሞ እንዲህ ሲል መሰከረ፤

> የአባታቸውን ሥራ (ማለት) የጋኔን ልጅ መሆኑን እንደማውቅ መንፈስ ቅዱስ ምስክሬ ነው፡ ምስክሬ ነው። (አናቱን) ከወርካ ስር ተኝታ አገኛት፤ ከዚያ፡ አሱን ፀነሰች። በተወለደም ጊዜ ካደገ በኋላ፡ በመነኮሳት ገዳም ሲኖር ማኅበሩን ያውክ ነበረ። ወደ አርሻም አብሮ ሲሄድ የመነኮሳት ልብስ ስብስቦ በእሳት ያቃጥል ነበረ። ማርያምንና የወልድን መስቀል እንደሚጠላ እኔ አውቃለሁ። ነቢያትን ተሳዳቢ አንደሆነም አኔ አውቃለሁ። ኢሳይያስን፡ "ኢሳይያስ ከብዙ ውሸቱ ንጉሡ ያዝዮን የሞተ ጊዜ እግዚአብሔርን በመንበሩ ላይ ተቀምጦ በዓይኖቼ አየሁት ይላል" ብሎታል። ጴጥሮስንም፡ "ጴጥሮስ በእንዲት ሌሊት ሦስት ጊዜ ካደው፤ አኔ እስካሁን እልካድኩትም" ብሏል። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ምስክሬ ነው።

ንጉሡ (145^{h}) "በል እንግዲህ ይኸ የምስክር ቃልህ እንደሆነ ማል፤ ሁላችሁም በዚህ ነገር ምስክር የምትሆኑ ማሉ" አለ። በዚህ ተንኮለኛ ሥርዓት ማለ። የዚህ ተንኮለኛ የመሐላው ሥርዓት በጽሑፍ አለ። የፈለገውን በዚያ ያስምለዋል። ከማሉ በኋላ ደግሞ፡ ለካህን በመናዘዝም ሆነ ወይም በመቍረብ፡ ወይም ገዳም በመግባት፡ ወይም ኢየሩሳሌም በመሄድ እግዚአብሔር እንዳይምራቸው ያስምላቸዋል። ሁሉም ያዩትን ሳይሆን የሰሙትን መሰከሩ።

ያንን መሐላ በሚያሚሉበት ጊዜ፡ ለመመስከር ከቆሙት ፩ዱ፡ "ንጉሡ በፊት ስለዚህ ሁሉ ሲመረምረው፡ እሱም መልስ ሲለጥ አላየሁም፤ ግን ለንጉሥ ባለመስገዱ ቀጥተውታል፤ ይኸንን አውቃለሁ" አለ።

ይኸንን ሲል ንጉሡ በጥፊ እንዲሉት፡ እንዲይዙትና እጥብቀው እንዲጠብቁት አዘዘ። ንጉሡ መስካሪ የሆኑትን፡ "ውሸታችሁ እነሆ፤ ልደቱ ከሰይጣን ነው ስለምትሉት፡ በውኑ ሰይጣን ዘር አለውን? ሰይጣን ከሰው ይወለድ ቢሆን (የወለደው) እነ ይኄይስን ነበረ[367]። እናቱ ከኛ ጋራ አለች። እሱን ግን (146^{v}) ጽድቅን በብዙ ፍለጋ ሳለ ሰይጣን ተገናኝቶታል። ለንበት ሻሪ ነው ብለው ከኔ ዘንድ ባመጡት ጊዜ ስገርፈው ደግሞ ከዚያ በኋላ ሰይጣን ገባበት" አላቸው።

ንጉሡ ቅዱሳኑን፡ "ካሁን ወዲያ ምን እንዲሆን ትፈልጋላችሁ? እንዴት ምስክር እንደተመሰከረ ሰምታችኋል"[368] አላቸው።

---

367. እዚህ ላይ የስም መሳሳት ያለ ይመስለኛል። ንጉሡ እንደዚህ የሚጠላው አንድ ጊዜ የትግራይ ገዢ፡ በኋላ ደግሞ ንጉሠ ነገሥ ብሕት ወደድ የሆነውን ኢሳይያስን መሆን አለበት። አሱንና ቤተ ሰቡን መንግሥቱን ለሌላ ሊሰጡ ሲዶልቱ ያዝኳቸው ብሎ እንዳጠፋቸው ይታወሳል፤ Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity of Emperor Zär'a Ya'aqob (Ṭomarä Tasbə't)*, *CSCO*, text vol. 522/95, pp. 66-79.

368. እጻጻፉ የአይሁድ ሊቀ ካህናት ክርስቶስን ለማስቀል ሲፋረድ ከተናገረው ቃል ጋራ (ማቴ 26: 65) ለማመሳሰል ነው።

ገላውድዮስ የሚባል ወንድም÷ "በፊትም የውሸት መስካሪዎች እባታችንን አስገድለውታል። እሁንም ውሸታቸውን ሰምተናል። መጽሐፉም ንጉሡ እንደሆነው ሌሌውም እንደዚያ ይሆናል[369] ይላል። ታዲያ ስለዚህ (ምስክራ) ከጌታ ከእግዚአብሔር በቀር ማን ይመረምራቸዋል" አለ።

ይሽን ሲል ደበደቡት። ሌሎቹን ወንድሞቹንም ብዙ ድብደባ ደበደቧቸው። በብረት እንካሴና በጦር ጎኑጧቸው፤ ራሳቸውን በሺመል መቷቸው።

ያ ገላውድዮስ የሚባል ወንድም÷ "ዝም ስንል በግድ እንድንናገር ታዙናላችሁ፤ ስንናገር ትመቱናላችሁ፤ እንዴት እንሁን? እግዚአብሔር ይርዳን" አለ።

ከዚያ÷ ንጉሡ በሰይፎችና በጦሮች እንዲከቧቸውና በብዙ ማስፈራራት እንዲያስፈራሯቸው አዘዘ። ደግሞ ንጉሡ÷ (146^{ለ}) "መገዛት ትችል እንደሆነ[370] ይሽንን ዐመልህን ተው፤ አለዚያ እነሆ ሰይፍና ጦር አለልህ፤ ደግሞ ምግብ÷ መጠጥ÷ ልብስ÷ ክብር አለልህ፤ መጽሐፉም እሳትና ውሐ እቅርቤልሃለሁ፤ እጅህን ከፈለከው ላይ እሳርፍ ይላል"[371] አለው።

ያ ወንድም÷ "የበላም የጠጣም ከሞት አያመልጥም፤ ብልጽግና÷ ክብር÷ ደስታም ያልፋሉ፤ ይሻራሉ" አለ።

ንጉሡ የነገራቸውን መጨረሻ ሲሰማ ወደነበሩበት እንዲወስዷቸው አዘዘ። ወታደሮቹ ቅዱሳኑን በቀኝም በግራም ይመቷቸው÷ ያንጓጥጧቸውም ነበረ። ስለነሱ የሚሚገትላቸው አልነበረም። እነሱ ግን በሁሉም ነገር እንዲረዳቸው ወደ እምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበረ። ምክንያቱም በረኀብ÷ በውሐ ጥም÷ በብርድ ደክመው ስለነበረ÷ ከድብደባው ብዛት ይወድቁም ነበረ። (በተለየም) በዚያች ቀን (ከንጉሡ ፊት) ማቆሙን ከቀን እስከ እኩለ ሌሊት እርዝመባቸው ነበረ። (በኋላ) ወደየነበሩበት ወሰዷቸው። በመጋረዳ የሚኖሩትም በመድኃኒት ቤት የሚኖሩትም ግፋቸውን ተሸክመው ተመለሱ።

ንጉሡ በማግስቱ በ፫ ሰዓት በመጋረዳ[372] የሚኖሩትን ልብሳቸውን እንዲወስዱባቸው አዘዘ። ያን ጊዜ ሰንበት (ቅዳሜ) (147^{ሀ}) ነበረ። ወታደሮቹ በታማኝነት ልብሳቸውን÷ ቆባቸውን÷ እስኬማቸውን÷ ወሰዱባቸው። ወንዱንም ሴቱንም እንደ እንሰላ ራቁታቸውን ተዋቸው። ቀኑን ዋሉ፤ እንደበፊቱ ራቁታቸውን አደሩ።

በማግስቱ÷ እሑድ መሆኑ ነው÷ ለያንዳንዳቸው የሚታጠቁት ትናንሽ (ልብስ) እንዲሰጧቸው አዘዘ። እንደዚያ ሆነው ተቀመጡ።

ከውጪ ሆነው ይላላኳቸው የነበሩትን ወንድሞቻቸውን÷ "በሰላም ሂዱ፤ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ እንዳገለገላችሁን ዋጋችሁን መልካም ዋጋ ይክፈላችሁ፤ እኛ ካሁን ጀምሮ በሥጋ መኖርን ተስፋ አናደርገውም። ብቻ እግዚአብሔር ከዚህ ዓለም ለመሻገር ችሎታውን እንዲሰጠን እንዲጸልዩልን ለማኅበሩ ንገሩልን። እግዚአብሔር ማኅበራችሁን ይባርክላችሁ" አሏቸው። እነሱም ወደ ማኅበራቸው ተመልሰው ሰወንድሞቻቸው ነገሯቸው። ትልቅ ሐዘን ወደቀባቸው። እግዚአብሔር ሥቃዮችን ለመሸከም እንዲያስችላቸው ምህለላ አደረጉላቸው።

---

369. ሲራ 10: 2።
370. ሮሜ 8: 7።
371. ሲራ 15: 17።
372. መጽሐፉ እዚህ "በመገረደ" ይላል።

የወንድም ፍሬ ክርስቶስ አጠቃላይ ክስ

ያንን ፍሬ ክርስቶስ የሚባል ወንድም ንጉሡ ከአስቀመጠበት ከመድኃኒት ቤት ወደ እሱ እንዲያመጡት አዘዘ። እንዳዘዘው አመጡት፤ "እንደዚህ (147ᴬ) ያለ ካህን ሆነህ ለምን በክንቱ ትሞታለህ? አሁንም አትሳሳት፤ ከዚህ ስሕተትህ ተመለስ" ሲል በብዙ ተንኮል ይደልለው ጀመር።

እሱም፥ "እኔ በሥጋዬ ሞት የነፍሴን ሕይወት ተስፋ አድርጌያለሁ፤ መጽሐፉ በሥጋው የተሠቃየ ከኃጢአቱ ይድናል[373] ይላል። ትተወኛለህ ብዬ ይኸንንም የምትጠይቀኝንም የምንጓለት አይደለሁም፤ ከ(ነፍሴ) ሕይወት በቀር ሌላ ተስፋ የለኝም" አለው።

ከዚያ፥ ንጉሡ፥ "ከመጽሐፍ ባላገኘኸው በመዘጋት ለምን ነፍስ ትገድላለህ?" አለው።

ያ ወንድም፥ "እኔ ነፍስ አድናለሁ እንጂ አልገድልም፤ የምትገድልስ አንተ ነህ። እነዚህን በእህልም በውሐም የተቀበላቸው፥ በገዳሙ ያኖራቸው፥ ከቤቱ ጥላ ያሳደራቸው ሰው ቤቱ ይመዝበር፥ ንብረቱ ይጥፋ፥ የቀበሌው ርስትም ለባዳ ይሁን፤ በሱ ዘንድ የተገኙበትም (ሰው) እነሱን በመግደል እሱ ይጀምር፤ እምቢ ካለ እሱንም ከነሱ ጋራ ይግደሉት (ብለህ ዓወጅክ)።"[374]

ስለ መበለቶችም ከተገኙበት ወዳንተ እንዲያመጧቸው ወታደሮችህንና መነኮሴዎችህን በላካቸው ጊዜ ሲያገኟቸው እንዲሰግዱልህ የመምህራቸውን ስም እንዲሰድቡ ይጠይቋቸዋል። (148ᴮ) እምቢ ሲሉና በሃይማኖታቸው ሲጸኑ ባሮቻቸው ድንግልናቸውን እንዲያጠፉባቸው እና ቅድስናቸውን እንዲያረኵሱባቸው ያዟቸዋል። ለእግዚአብሔር መጠመድ የሚፈልጉትን ሕፃናትም ከቅዱሳን አባቶቻቸው ማህል ይወስዷቸውና ከብት እረኞችና በቅሎ ያዥዎች ያደርጓቸዋል። በዚህ ምክንያት እያለቀሱ ወደኛ ይመጡና እንድንሞት ፍቀዱልን ይሉናል። ስለዚህ እኔም ወንድሞቼም እንፈቅድላቸዋለን፤ ምክንያቱም መጻሕፍቱ ከመራር ሕይወት ሞት ይሻላል[375] እንደሚሉ እናውቃለን። ከሌላ ቦታም ምስጋናዬ ከሚጠፋብኝ መሞት ይሻለኛል[376] ይላል። በገዳም ያሉ ቅዱሳንም ይኸንን ያደርጉታል" አለው።

ንጉሡ፥ "እንተስ ለምን አልሞትክም? የተውከው ፈርተህ አይደለምን?" አለው። "የምፈራ ከሆንኩ፥ አሁን ፈትነኝ፤ እነሆ፥ አለሁ" አለው። ንጉሡ፥ "አዎን፥ መሞት እንደማትፈራስ እኔም አውቃለሁ" አለው።

ከዚያ፥ በብዙ (ንግግር) መደለል ሲያቅተው ተወው፤ ቀድሞ ከነበረበት እንዲመልሱት አዘዘ።

የደራሲው ማጠቃለያ

ይህ ተንኮለኛ በመጋርዳና በመድኃኒት ቤት ያሉትን ቅዱሳን በብዙ ሥቃይ ሐሳባቸውን ከላይ ወደ ጎላፊው ወደ ታች ሊያወርድባቸው ፈልጎ እህል ውሐ ባለመስጠትም ሆነ ልብስ (148ᴬ) በመግፈፍ፥ (ሰው ካጠገባቸው) እንዳይደርስ

---

373. ?።

374. የራሱ የአፄ ዘርአ ያዕቆብ ድርሰት እንደሚያሳየው፥ "ወንድም ፍሬ ክርስቶስ" ዓዋጁን ቃል በቃል ነው የጠቀሰው፤ ገጽ 111 ላይ ጎዳግ ቀኖጥር 177ን ተመልከት።

375. ሲራ 30: 17።

376. 1 ቆሮ 9: 15።

በማድረግም በጣም አጠበበባቸው። እነሱ ግን የእግዚአብሔር ጎይል በሁሉም እየመገባቸው፥ "ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ እነሱ ይጠግባሉና"[377] በሚለው በእግዚአብሔር ቃልና "መደረቢያህን ለመውሰድ ቢታገልህ ልብስህንም ተውለት"[378] በሚለው እየረኩ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ (በእምነታቸው) ጸኑ። የነዚህ ሁሉ የዚያን ዘመን ሥቃዮች የትኛውም ሳያስፈራቸው የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ ታጥቀው የወይን እጸዳቸውን ከጠሳት ቧልት እየጠበቁ የጥፋት ፍሳጻ ነፍሳቸውን እንዳያገኝ ሥጋቸውን ጋሻ አድርገው ኖሩ። እነዚያን ሥቃዮች በሥጋቸው ሲቀበሉ ነፍሳቸውን የእግዚአብሔር ስብሐት በክንፎቹ ስር ሸፍኗት[379] በደኅንነት ትኖር ነበር። "ኃጢአት እስኪያልፍ ድረስ በክንፎቹ ጥላ ተማመንኩ"[380] እንደሚለው እንደ ነቢዩ ቃል ሐሳባቸውን (149^{b}) ወደ ላይ እያወጡ በተሰጣቸው የትልቅ ንስር (ዓይነት) የንጽሕና ክንፍ[381] መጽሐፍ፥ "ያቺን ሴት ምድር ረዳቻት አፏን ከፈተችና ያንን ከእባብ አፍ የወጣ ፈሳሽ ጠጣችው"[382] እንዳለው ከእባቡ አፍ ፈሳሽ ውሐ እንዲያመልጡ እየበረሩ እንደዚሁ ተጋደሉ። የሴቷ የምድር እርዳታ ስለ ጽድቅ ሥቃዮችን የምትቀበል ሥጋ ናት። ሴቲቱም ነፍስ ናት፤[383] ጌታ ለደቀ መዘሙርቱ፥ "ዓሥር ድሪም እንዳላት ሴት ከነሱ አንዲ ብትወድቅባት መብራት አብርታ በቤቷ ውስጥ ያለውን ሁሉ እያነሣች (እትፈልግም)? አጥብቃ (በመፈለጓ) ስታገኛት ጎረቤቶቿን ጠርታ የጠፋችብኝን ድሪሜን አገኝቻታለሁና ተደሰቱልኝ"[384] ሲል በምሳሌ እንደተናገረው እነሱም ለነፍሳቸው መድን ይሆን ዘንድ "የሚኖር መንፈስ ነው፤ ሥጋስ ምንም የሚጠቅም የለበትም"[385] የሚለውን የሰማይ አባታቸውን ምዕዳን እውነትነት ለማሳየት እነሱም እንደዚሁ ሥጋቸውን ለነዚያ ሥቃዮች አሳልፈው ሰጥተዋል። እነሱም እንደዚሁ እርስ በራሳቸው ምዕዳን ይሰማማሉ፤ (149^{a}) ፩ዱ ሌላውን የአንጸክያን፥ የአርመንያን ሰማዕት፥[386] የ፲ሩን

377. ማቴ 5: 6።
378. ማቴ 5: 40።
379. መዝ 60: 4/5።
380. መዝ 56: 2/57: 1።
381. ራእ 12: 14።
382. ራእ 12: 16።
383. ዘርአ ያዕቆብ ሴቲቷን ማርያም ናት ነው የሚለው፤ Getatchew Haile, *The Mariology of Emperor Zär'a Ya'əqob of Ethiopia* (*Orientalia Christiana Analecta*, no 242), Rome 1992, pp. 82-83.
384. ሉቃ 15: 8-9።
385. ዮሐ 6: 63።
386. የፈጃቸው የፋርስ ንጉሥ ነው። ስማዕትነታቸው የሚከበረው ሚያዝያ 19 ቀን ሲሆን፥ የገድላቸው ምንባብም ለዚሁ ቀን ከስንክሳሩ ተመዝግቧል፤ ቍጥራቸው 150 ነው።

ወታደሮች÷[387] የናግራን÷[388] የቀደሟቸውን ወንድሞችን (ሰማዕትነት)[389] ያስታውስ ነበረ። መነኮሲቶቹንም እንደዚሁ ምዕዳን ያሰሟቸው÷ በተግሣጽም ያጠነክሯቸው ነበረ።

የንጉሡ የመጨረሻ ሙከራ

ንጉሡ ልብሳቸውን በገፈፉ በአራተኛው ቀን በብዙ ነገር እንዲደልሏቸው ዐዋቂዎችና አስተዋዮች ላከባቸው፤ ወደነሱ መጡ። ቅዱሳኑ ግን ምግብ አጥተው ከልብስ ተራቁተው እዚያ ወድቀዋል። እያንዳንዳቸውን በብዙ ልመናና ለምትጠፋው (የሥጋ) ሕይወት ተስፋ በመስጠት አባበሏቸው። ቅዱሳኑ ግን÷ "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም"[390] የሚለውን የመጽሐፍ ቃል እያስታወሱ በአምላካቸው ጎይል ጠነከሩ። አባባዮቹ ሄዱ፤ ቅዱሳኑም የአምላካቸውን እርዳታ ተስፋ በማድረግ በብርድ÷ በመራቆት÷ በብዙ ገድል እዚያው ኖሩ። በአንዳንዶቹ ሲያፌዙባቸው እጆሯቸው ውስጥ ጉንዳን[288] ይጨምሩባቸዋል፤ አንዳንዶቹን በድንጋይ÷ በብትር÷ በጥፊ ይመቷቸዋል። ደግሞ ልንዘረዝራቸው ያልቻልነው ብዙ ሥቃዮች አሉ። (150[ሀ]) አንዳንዶቹ ግር እስከ መብላት ደርሰዋል። ይኸንን ሁሉ ስማዕትነታቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ ታግሠዋል።

ከዚያ÷ መጋረዱ ባባቷቸው በሮጌ ቀን ከንጉሡ ፊት አቆሟቸው። በብዙ ነገር ተሟገታቸው። በማግሥቱ ልብሳቸውን እንዲገፏቸው አዘዘ። ልብሳቸውን በገፈፏቸው በአራተኛው ቀን አባባዮች ላከባቸው፤ በአባበሏቸው በሶስተኛው ቀን ንጉሡ ጉባኤ ጠራ። ቅዱሳኑን ከንጉሡ ፊት እንዲያቆሟቸው አዘዘ። በፊት በሌላ ምድሮች[391] በገሰምቤ ያኖራቸውንም እንዲያመጧቸው አዘዘ። (መንድሞቻቸውን) ሲረዱ ይዘው ያን ዕለት (እስር ቤት) ያገቧቸውን ከከተማው ውጪ ያሉትን÷ በማጋረዱ ውስጥ ያሉትን÷ በመድኃኒት ቤት ያሉትን÷ ሁሉንም በአንድነት ሰብስበው ወንዱንም ሴቱንም እንደ ከብት በአንድ በኩል እራቁታቸውን ከፊቱ አቆሟቸው። ያቺንም የታጠቋትን ገፈፏቸው። ወታደሮቹ÷ "እነዚህ ለንጉሥ በመስገድ የማይገዙ እርኩሶች ናቸው" እያሉ በብዙው ይሰድቧቸውና ያንጓጥጧቸው÷ ይተፉባቸው÷ ራሳቸውን ይኰረኩሟቸው÷ በአንካሴና በጦር ይጎሟቸው÷ (150[ለ]) ከምድር ላይ ይወቋቸው ነበር።

ከዚያ÷ ንጉሡ እንዳስለመደው ይሰግዱለት እንደሆነ÷ የመምህራቸውን ስም ይሰድቡ እንደሆነ (ለመጠየቅ) ላከባቸው። ይኸንኑ ነገራቸው። ቅዱሳኑ÷ "እነዚህ ሁሉ ሥቃዮች (የደረሱብን) ለምን ሆነና ነው?

---

387. ?።

388. ንጉሥ ካሌብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ የተበቀለላቸው የብሔረ ላባ አገር ሰማዕታት ናቸው፤ የሚታሰቡት ንጉሡ ባረፈበት በግንቦት 20 ቀን ነው። የዕለቱን የስንክሳር ምንባብ ተመልከት፤ ገድላቸውም ታትሟል፤ K. Conti Rossini, *Vitae Sanctorum Antiquiorum I Acta Yārəd et Panṭalēwon, CSCO,* vol. 26/9 (1961), pp.43-60

389. የራሳቸውን የደቂቀ አስጢፋኖስን ሰማዕታት።

390. ማቴ 4: 4፤ ሉቃ 4: 4።

391. መጽሐፉ የሚለው "ምድር ከልአት" ነው፤ "ከልአት" የሚባል ቦታ ነበረ፤ አዚህ ግን "ካልኣት" "ሌሎች" ማለቱ መሰለኝ።

በዚህ (ነገር) አይደለምን? ከዚህ በኋላ ሥጋን ከመግደል ሌላ ምን ያመጣል? ነፍስን መግደል እንደሆን አይችልም" አሉ። ያሉትን ነገሩት።

ከዚያ፥ ሠራዊቱን ፍርድ እንዲሰጡ አዘዛቸው። "ለንጉሥ አይሰግዱም፤ ለክብሩም አይታዘዙም፤ ስለዚህ መሞት ይገባቸዋል" ሲሉ ፈረዱባቸው።

የሶስቱ የጦር ጎይል ክፍሎች ፍርድ

(ፍርዳቸውን) በየክፍላቸው ስጡ፤

የጦር ሠራዊቱ፥ "ጌታችን ንጉሥ ሆይ፥ ለኛ ስጠን" አሉ።

የብትር ሠራዊቱ፥ "ራሳቸውን ገምሰን እንጐላቸውን እንድናፈሰው ለኛ ስጠን" አሉ።

የአለንጋ ሠራዊቱ፥ "ኧረ፥ ኧረ"፥[392] ጌታችን ንጉሥ፤ ዛሬስ እፎይ እንድናስኝህ፥ በግርፊያ ጎይል ሳምባቸውን እንድናወጣው ለኛ ስጠን" አሉ። ወፎች ሥጋን እንደሚያደርጉት እያንዳንዳቸውን ሊቦጫጭቋቸው ፈለጉ።

ንጉሡ ግን ሁኔታቸውን እያየ ዝም ብሎ ነበረ። ከዚያ፥ (151^{v}) መላሳቸውንና አፍንጫቸውን እንዲጐምዷቸው፥ በመነኮሲቶቹም ላይ እንደዚሁ (እንዲያደርጉ)፥ ሁሉንም በአንድነት ከገበያ ወስደው በድንጋይ እንዲወግሯቸው አዘዘ። ዋሠጋ የሚባሉ ሰዎች እንዲጠሩ አዘዘ። ጉጠት፥ ወስፌ፥ ምላጭ በእጃቸው ይዘው መጡ።[393] ቅዱሳኑን ስጧቸው። መላሳቸውንና አፍንጫቸውን ጐመዱ። ከመነኮሲቶቹ እንዳንዶቹን ጡታቸውን ቈረጡት።

ከዚያ፥ እያጣደፉ ወደ ገበያ ወሰዷቸው። ከድካም የተነሣ ሲወድቁም ይጐትቷቸዋል። በዚህ ዓይነት ሥቃይ (ከገበያ) አደረሷቸው፤ አንዳንዶቹ (ስማዕትነታቸውን) በመንገድ ፈጸሙ።

ከሚወግሯቸው ቦታ ሲደርሱ (መጀመሪያ) ፪ ቈሶች ተጋደሙ፤ አንዱ ስሙ ፍሬ ክርስቶስ፥ ሁለተኛው ሚናስ ነው። ወታደሮቹ በድንጋይ ወገሯቸው። ቅዱሳኑና መነኮሲቶቹ ሁሉም በላያቸው ላይ ወደቁባቸው። በመንገድ ያረፉትን (ራሳቸውን) ጫኑባቸው።

አንዷን ትንሽ መነኮሲት ከወታደሮቹ አንዱ ብድግ አድርጎ ከመሬት ላይ ወረወራትና በእግሩ ቢረግጣት፥ እዚያ ስማዕትነቷን ፈጸመች። ያም በፊት በጐንደት የቅዱሳን ግድያ ጊዜ ራእይ ያየው መርቆርዮስ የሚባለው ወንድም ከነሱ ጋራ በዚች (151^{v}) ዕለት ምስክርነቱን ፈጸመ።

በዚች ዕለት የተወገሩት ቊጥር ፸፫ ቅዱሳንና ፵፫ መነኮሲቶች ሲሆኑ ድምሩ ፻፮ ነው። በጌታ ሰላም የስማዕትነታቸውን አክሊል የደፉት ሚያዝያ ፳፭ ቀን ነው። ጸሎታቸው ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ምዕዳን

መጽሐፉ "ከጌቶች ማእድ ከተቀመጥክ አንተም እንደነሱ ማቅረብ እንዳለብህ ዕወቅ"[394] ይላል። እነዚህ ቅዱሳን ወንድሞቻችን በመውጣት በመግባት አብረውን ከኛ ጋራ ነበሩ። ግን ሐሳባቸውን ወደ ጎላፊው ሳያዘነብሉ

392. "ውሮ፥ ውሮ"።

393. "ዋሠጋ" ከአንድ ጎሳ የመጡ ባለጆች መሆን አለባቸው።

394. Victor Arras, *Patericon Aethiopice*, p. 125.

የማይታየውን ተስፋ ያደረጉ ፍጹሞች ናቸው። የማይታየው ለዘለዓለም ይኖራል። እነዚህ ክፉ ሐሳብን በብዙ ገድልና በብዙ ጻማ አሸንፈው እግዚአብሔር ለሚወዳቸው የሰጠውን ተስፋ አገኙ። ሥራቸውም ቀዳሚ ነው፤ ከበፊቱ አንዳንዶቹ የሚሆነውን ምስጢር ከመድረሱ በፊት አስቀድመው ያዩ ናቸው። አንዳንዶቹ በሁሉም ነገር ችሎታን እንዲሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር ምህልላ ሲይዙ በየቀኑ ዕንባቸው እይደርቅም ነበረ። እኛም እነሱን መምሰል፥ (152[ሠ]) ፈለጋቸውን መከተል፥ ራሳችንን ለሥቃይ ማዘጋጀት ይገባናል። ከናንተ አንዱም የሚተዉት አይምሰለው፤ ምክንያቱም እኛም እንደነሱ በነሱ ዘንድ መስካሪዎች ነንና። ክኃጥአን ይሽንን ያህል የታገሡ (እንዳሉ) እስቲ እናንተ ራሳችሁ አስቡት። ነፍሳችሁ እንዳትዳክርና እንዳትደክም አስቲ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩበት። ደግሞም ለደም አስክትደርሱ ድረስ ኃጢአትን ተጋደሏት፤ አምቢ በሏት፤ የተስፋችሁን ሥርዓት አስቀድሟት። እነሆ ተግሣጽ ሁሉ ለጊዜው ሐዘን እንጂ ደስታ አይመስልም። በኋላ ግን ለሚያደርጋት ሰላምን ታፈራለች፤ ጽድቅንም ትሰጠዋለች። አሁንም ጉባኤያችን ለሥጋ (ጉዳይ) አይሁን፤ ከተግሣጽ አንራቅ። በእፋችን ብቻ "የሥርዓት ልጆች ነን" እንበል። ምክንያቱም የአባቶች ምዕዳን፥ "ከድካማቸው ኃራ ሳትደክም ቅዱሳን አባቶቻችንን ለመምሰል አትድከም"[395] ይላል። የሥርዓት ልጆች ከመጨረሻዋ ማዕርግ እስከደርሱ ድረስ ከተግሣጽ ያልራቁ[396] ናቸው። አሁንም እንበርታ፥ አንጠራጠር፥ አንፍራ፤ በነቢዩ አፍ፥ "የሰዎችን ስድብና (152[ሸ]) ማስፈራራታቸውን አትፍሩ፤ እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ ብል እንደበላውም ይሆናሉ፤ መድኃኒቴ ግን ለዘለዓለም ትኖራለህ፤ ጽድቅም ለትውልድ ትውልድ (ትኖራለች)"[397] የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል እንተማመን። በሌላ ቦታም፥ "የሚያስፈራራችሁን አትፍሩ፥ በሙሉ ልባችሁ እግዚአብሔርን ቀድሱት"[398] ይላል። ስለዚህ ተግሣጽን በመፍራት ቅድስናችንን አናርክሰስ፤ "ከመሠረታችሁ ወደማይጠቅም ትምህርት አትውደቁ"[399] ይላል።

አሁንም፥ የዚህ ተንኮለኛ ስድብ ምን ልክ አለው? ምክንያቱም እሱ የስሕተት በራፍ ነው። ቅዱሳኑን የቱን ያህል ሊወስዳቸው ይፈልጋል! ከነሃኒት ዙፋን ወደሱ ባርነት ሲያወርዳቸው፥ ከአባቶቻችን ከሐዋርያት፥ ከተከታዮቻቸው የኒቅያ ፫፻፲፰፥ የቁስጥንጥንያ ፻፶፥ የኤፌሶን ፪፻ ሃይማኖት በቀር ሌላ ሃይማኖት ሳይኖረን፥ ጳጳስም ከእስክንድርያው የማርቆስ መንበር ዘንድ ከሚመጣው በቀር ሌላ ሳይኖረን፥ የማርቆስ መንበር በሆነ የዲዮስቆሮስ ያዕቆባውያን እንጂ ከአርዮስ፥ ከንስጥሮስ፥ ከሰባልዮስ፥ ከመቅዶንዮስ፥ (153[ሠ]) ከፎንጢዮስ፥ ከልዮን፥ ፀረ ማርያም ከሚሏቸው ከአንጢዲቆንማርያስ፥ ከአፍቲክስ፥ ከአቦርዮስ፥ ከሌሎችም እንደነሱ ካሉት ተከታዮች ሳንሆን እንደገና ወደ ክርስትና እንድንጠመቅ ያዝዛል። ይሽንን የሚያደርገው ለንግሡ ክብር ስብሐት ስላልሰጡ እያራኩሰ እኛን በሕዝብ

395. ?።
396. ግዕዙ "የራቁ"።
397. ኢሳ 51፡ 8።
398. ?።
399. ?።

ዘንድ አረሚዎች አስመስሎ የብዙዎችን ልብ ለመውሰድ ነው። የራሱ ወደእልሆነ[400] ሲዳፈር አባቶቻችን ሐዋርያት በዲድስቅልያቸው እንዲህ ያሉትን ቃል እስከ መካድ ደረሰ፤ "ሁለት ጥምቀት አታድርጉ፤ በፊት የወሰዳችሁት ጥምቀት ይበቃችኋል፤ ምክንያቱም፥ ለከሐዲዎች ባልተሰጠች፥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም (ላጠመቋችሁ) ለቅዱሳን ካህናት በተሰጠች ጥምቀት በክርስቶስ ሞት ተቀብራችኋልና። ጥምቀት እንዲት ናት፤ እግዚአብሔርም ፩ ነው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና የጽድቅ መንፈስ ጸራቅሊጦስ፥ የጌታችንም በሥጋ ሞቱ ፩ ነው። በሞቱ የወሰዳችሁት ጥምቀታችሁም እንደዚሁ ፩ ይሁን። ይኸንን የማያምን፥ እንደዚህም የማያደርግ፥ ክፍሉ (153[ለ]) ከከሐዲዎች ጋራ ከክፋት ትምህርት ይሆናል። እንደዚህ ስለሚያደርጉት እግዚአብሔር፥ ትምህርቴን ከናቃችሁ እኔም እንቃችኋለሁ፥ አተዋችኋለሁ፤ ካህናትም አላደርጋችሁም። ከናንተ (እጅ) የሚጠመቁትም እንደዚሁ ከኃጢአት ይቅርታ የሌላቸው እርኩሶች እንጂ ንጹሐች አይደሉም። ሁለት ጥምቀት የሚቀበሉም እንደዚህ ይሆናሉ። የክርስቶስን ሥራ ጨዋታ ያደርጉታል። ቅዱሳኑን (ከቅድስናቸው) ይመልሷቸዋል፤ መንፈስ ቅዱስንም ይሰድባሉ፤ ክቡር ደሙን ያረኵሳሉ፤ ሥቃዩንና ስማዕትነቱን ይክዳሉ"[401] ይላል።

ደግሞ፥ "የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ጥበብንና ዕውቀትን ልብ እንድትሉ እነሆ ጽፈንላችኋል። የሥራቸውን ውበት ተመልከቱ እንጂ በኛ ስም ከሐዲዎች የሠሩትን ክንቱ ነገር አትቀበሉ። እነሆ፥ የሚለምኑልን ሐዋርያት አሉልን አትበሉ። ምክንያቱም እንዳንዶቹ በክርስቶስ ስም ብዙ ተአምራት የሚሠሩ አሉ፤ ግን (ሥራቸው) የሞት መርዝ የተሞላበት ነው"[402] ይላሉ። በሐዋርያው በጳውሎስ ቃል ዘንድም፥ "ደግሞ እንግዲህ ዕወቁ ሁለተኛ መሠረት እትፈልጉ፤ እርሱም ከሞት ሥራ ንስሐና ወደ እግዚአብሔር ሃይማኖት ወደ ጥምቀቱ እጅ በመጫን ሹመት መስጠት፥ (154[ሀ]) ስለ ሙታን ትንሣኤ ስለ ዘለዓለም ፍርድ ትምህርት ነው። እግዚአብሔር ቢፈቅድ ይኸንን እናደርጋለን። ከጥምቀት በኋላ የሰማይ ጸጋውን ከቀመሱ የመንፈስ ቅዱስ (ተካፋዮች) ከሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ቃልና የሚመጣውን ዓለም ጥሩ ነገርና ኀይል ከቀመሱ በኋላ እንደገና ከወደቁ ለንስሐቸው ማደስ አይቻልም፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና"[403] የሚለውን (ልብ አላለም)። ይኸንን ትእዛዝ እየተላለፈ እንደገና ወደ ክርስትና እንዲጠመቁ እንዲያመነኵሷቸውም አዘዘ።

አሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ ቅዱስ ጳውሎስ፥ "የጸናችሁ ዕለት የተጠበቃችሁበትን መንፈስ ቅዱስ አታሳዝኑት።"[404] "እግዚአብሔር መንፈስ ነውና፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ካለበት እዚያ ነፃነት አለ። እኛም ከክብር ወደሱ ክብር እንድንገባ ፊተ ግልጽ ሆነን የእግዚአብሔርን ስብሐት እናንጸባርቅ፤ በሱም አርአያ እንምሰል"[405] የሚለውን ልብ እንበለው። ታዲያ

400. ግዕዙ "ወደ ሆነ"።
401. J. M. Harden, *The Ethiopic Didascalia*, New York 1920, pp. 152-153.
402. Harden, *ibid.*, p. 153.
403. ዕብ 6: 1-6።
404. ኤፌ 4: 30።
405. 2 ቆሮ 3: 11-18።

(ሐዋርያት) ያልሰበኩልን እነሱ የሚሰብኩት ሌላ ክርስቶስ ሊመጣ ነውን? ወይስ ያልወሰድነው (ገና) የምንወስደው ሌላ መንፈስ አለን? ወይስ ያልተማርነው ሌላ ትምህርት አለን? ልንጸና ይገባናል። ግን እናስተውል፤ ቅዱሱ አባት (154[A]) እስጢፋኖስ ከነቢያት ስብከትና ከሐዋርያት ትምህርት ያጐደለብን (ነገር) የለም። ሁሉንም የገለጸልን ከመጻሕፍታቸው ምስክር እየጠቀሰ ነው። "እኔ ያልነገርኳችሁ ከአባቶቻችን ከሐዋርያት ሥርዓት የቀረባችሁ ሥርዓት አለን? ከትምህርታቸው ያጐደልኩባችሁ አለን?" ይላል። ልጆቹ፥ "አባ ሆይ፥ ያጐደልክብን የለም፤ ማድረጉ ከኛ ዘንድ ቀረ እንጂ" አሉት። እሱ ስለ ማንኛውም ምዕዳን ያሰማቸዋል፤ በተግሣጽም ያስረዳቸዋል፤ "ልጆቼ ጥረት ሁሉ የሚገኝ አይደለም፤ አሁኑኑ በማምባራችሁ ላብ ማርኩ"[406] ይላቸው ነበረ።

እነሱም ቃሉን ሰሙ፤ ተግሣጹን ተቀበሉ፤ ፈለጉንም ተከተሉ። ግን እኛ የኋለኛ ትውልድ ተጠያቂነት ያገኘናል። አሁን የቅዱሱን ስም እንድንሰድብና የእግዚአብሔርን ዲናር ለቄሳር እንድንሰጥ፥ ጥምቀትንም ከመናፍቃን ዘንድ እንድንወስድ ለምን እንደፍራለን? ጌታ "የባሪያ መጠኑ እንደ አለቃው ሲሆን፥ የደቀ መዝሙር መጠንም እንደ መምህሩ ሲሆን ነው"[407] አላለምን? መጽሐፍ "ካብ የሚያፈርስ አባብ ይነክሰዋል ስለሚል፥ አባቶችህ የሠሩትን ሥርዓት አታፍርስ"[408] ያለውን ልብ እንበል። አሁንም (155[B]) በምግባርና በሃይማኖት ፍጹሞች የሆኑ መንፈሳውያን አባቶቻችንን ፈለግ እንከተል።

አሁንም አልሞቱም፤ ይነጋገራሉ

በድንጋይ ከወገሯቸው ቅዱሳን ውስጥ ፫ቱ ድንጋይ ተጭኖባቸው እስከ አራት ቀን ድረስ ሳይሞቱ ቆዩ። ከዚያ፥ ፩ድ ሰው መጥቶ አያቸው። በሕይወት እንዳሉ ሲያውቅ ሄዶ ለንጉሡ እንዲህ ሲል ነገረው፤ "ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፥ በድንጋይ እንዲወገሩ ትእዛዝ የሰጠህባቸው መነኮሳት በሕይወት አሉ፤ አሁንም ይነጋገራሉ።" ይህ ሰው በፊትም ቅዱሳኑን ይፃረራቸው፥ ይከሳቸውም ነበረ። የተወገሩ ጊዜም በላያቸው ላይ (በተከመረው) ድንጋይ ላይ ቆሞ አፌዝባቸው ነበረ።

ለንጉሡ ሲነግረው ንጉሡ፥ "በነሱ ላይ ምልክታችንን (ልታይ) ትፈልጋለህን" አለው።[409] ይኸንን ካለ በኋላ እንዲገርፉት አዘዘ። ብዙ ግርፊያ ገረፉት። እነዚያንም ቅዱሳን እንደገና በድንጋይ እንዲወግሯቸው አዘዘ፤ እንደገና ወገሯቸው።

ያም ንጉሡ የገረፈው[410] በሶስተኛው ቀን ሞተ። (ንጉሡ) የድንጋይ ወጋሪ አለቆችን እንዲያመጧቸው አዘዘ። ከዚያ፥ ንጉሡ፥ "ለምን እኔ እንዳልኩት እነዚያን መነኮሴዎች እንዲሞቱ አላደረጋችሁም?" አላቸውና እንዲገረፉ አዘዘ። ገርፎ እንዲታሰሩ፥ እንዲወሰዱም አዘዘ። ወደ ሌላ (ቦታ) ወሰዷቸው።

---

406. ዮሐ 9: 4።
407. ማቴ 10: 25።
408. Victor Arras, *Collectio Monastica, CSCO*, vol. 238/45 (1983), p. 151.
409. "ንጉሡ ዘርአ ያዕቆብ በድንጋይ ያስወገራቸው" እንዲባል አይፈልግም ለማለት ይመስላል፥ ዓዋጁንም የሚያሳብበው በሕዝበ ክርስቲያኑ ነው።
410. ያስገረፈው።

ይህ ተንኮለኛ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ (155^ሰ) ለማረፍ ጸጥታ አላገኘም። የውጪና የውስጥ ሥቃይ ወደቀበት፤ ቅዱሳኑን ለመቅጣት አልደገመም፤ የሱ ሕይወት አልቃለችና፤ ሥልጣኑም ተፈጽማለች።

ወንድም ሊቃኖስና ረዳቱ

ሊቃኖስ የሚባለውን ምርጋይ ውስጥ ከነበሩት ቅዱሳን አንዱን ወንድም ሁለት ጉልበቶቹ ታጥፈው እስኪቀሩ ድረስ ጭንቅ በሽታ ያዘው። መሄድ ፈጽሞ አልቻለም። የሚሄደው ተሸክመውት አለዚያም እየተንፏቀቀ ነው። ስለዚህ፥ ወንድሞቹ ከሚረዳው ከአንድ ወንድም ጋራ ምድረ ደዋሮ ትተውት ነበረ። እግዚአብሔር (ለሁለቱም) ጥሩ ነገር አደረገላቸው። የዚያ ሀገር ሰዎች ለወንድሞቻቸው መጠጊያ እስኪሆኑ ድረስ ተቀበሏቸው። ያ (ደካማ) ወንድም በመልካም ገድል ኖረ። የዘመኑ ማለቅ ሲደርስ ዐውቆት፥ "ከአሁን ወዲያ እግዚአብሔር ከዚህ ጻማዬ ያሳርፈኛል" ይል ነበረ።

ከዚያ፥ የቅድስት ፴ ጾም ጊዜ ሲደርስ ቅድስት ፴ ጾም እስኪታልቅ ድረስ ከሰንበት (ከቅዳሜ) እና ከእሑድ በቀር አምስቱን ቀኖች እህልና ውሐ ላይቀምስ ይጾም ነበረ። ታላቅ በሽታ አደረበትና ደም የተደባለቀበት መግል ይተፋ ጀመር። ይኸም ሆኖ መጾሙን አልተወም።

(156^ዐ) አንድ ዲያቆን፥ "አባ ሆይ፥ ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ? እንደዚህ (ከሆነ) አትሞትምን?" ሲለው፥ "ጌታ ያለውን አልሰማህምን? የስንዴ ፍሬ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።[411] እኔም በሞቴ እንጂ በሥጋዬ ሕይወት ምን አገኛለሁ? ስለዚህ አያሳዝንህ" አለው። እሱም ሰምቶ አደነቀ።

በዚያች ጾም መጨረሻ በሽታው ጠናበት፤ ከፋሲካ እሑድ ትንሣኤ ዓሥራ ሁለት ቀን በኋላ፥ ሚያዝያ ፳፫ ቀን፥ በጌታ ሰላም ገድሉን ፈጸመ። ከመልእኩ ቅዱስ ሱርያል ቤተ ክርስቲያን ቀበሩት። ጸሎቱና የጻማው በረከት ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

እንደዚሁ፥ ሁለተኛውም ከነዚያ ቀኖች በኋላ በዚያች ሀገር ከሌሎች ወንድሞች ጋራ ሳለ ስደት በጠናባቸውና ከሀገር ባላደጿቸው ጊዜ (ሁሉም) ወደ ሩቅ ዱር ሂደው ከአንድ ዋሻ ገቡ። እሱ ሽማግሌ ስለሆነ ውሐ ብቻ ይጠጣል እንጂ እንደ ወንድሞቹ የሆነውን ፍሬ ሁሉ መብላት አልቻለም።

(156^ሰ) ከዚያ፥ ወንድሞቹን፥ "እንደዚህ ሆኜ መኖሬ ምንድን ነው? ለናንተም ሐዘን አልሁናችሁ። ውሐ (መጠጣቱንም) እንድተወው ፍቀዱልኝ። እናንተ ከወደዳችሁት እግዚአብሔር ከዚህ ጣር እንዲያላርፈኝ እግዚአብሔርን እተማመነዋለሁ" አላቸው። ከዚያ፥ በጎብረት ወደዱለት፤ ውሐ (መጠጣቱን) በተወ በዓሥራ ... ቀን ገድሉን በመልካም ጻማ በ... ወር፥ በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን፥ አሜን።

ቦሌ የሚጠጣው መምህር በርሶማና ወንድም መንቆርዮስ

በዘብር ሀገር መአድ[412] በምትባል ደብር ከሚኖሩ መነኮሳት ጋራ በምንኮስና የሚኖር አንድ ሰው ነበረ። ጉልበቶቹ ተጣብቀዋል። የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ስላለ መጻሕፍት ተመራማሪ ነበረ፤ (ወደ ፊት) የሚሆኑትን ምስጢሮች

411. ዮሐ 12: 24።

412. ማአድ?

ያውቃል። የዚያ ሰው ስም በርሶማ ነው። ሰዎቹን፥ "ለምንድን ነው በመጻሕፍቱ ልማድ የማትሄዱት?" ይላቸው ነበረ። (እነሱ ደግሞ)፥ "በመጻሕፍት ልማድ ለመሄድ እንዴት ይቻላል? ከባድ አይደለምን?" ይሉታል።

ከዚያ፥ በጠባዩ የሚተባበረው ሲያጣ፥ ድምፅ ሳያሰማ ወደ ዱር ወጣ። እዚያ (157ᵘ) በተትረፈረፈ ገድል ተቀመጠ። ከዚያ፥ ከብዙ ቀናት በኋላ ፈልገው መለሱት። እንደገና ከነሱ ወደራቀች ዱር ሄዶ፥ ዋሻ ቆፍሮ ከዚያ ገባና ተደበቀ። ከዚያ፥ አግዚአብሔር ረድኤት ሰጠው፤ አንድ የእግዚአብሔር ሰው መጥቶ እስኪሞት ድረስ አብሮት ተቀመጠ።

ምግቡን ከዚያ ዋሻ የሚቆፍረውን ነጭ ድንጋይ አደረገ። ፈጭቶ በውሐ ይበጠብጠውና ያንን ይጠጣል። ደግሞ ያ የሚረዳው ሰው የትንግ (?) ፍሬ ይሰበስባል። ያንን ምግብ ያደርጋል። አተሩንምር ከትንጉ ጋራ ንፍሮ ያደርጉና ምግብ ይሆናቸዋል።

ከዚያ፥ ቅዱሳኑ በግፍ እንደሚገደሉ እንዴትስ ከአገር ወደ አገር እንደሚሰደዱ ዜናቸውን ሲሰማ ጽድቅን የሚሠሩ ሰዎች ዜና ስለሰማ አግዚአብሔርን አመሰገነው። ቅዱሳኑም ዜናውን ሰምተው ጐበኙት።

ከብዙ ቀናት በኋላ፥ (ምእመናን) መንቆርዮስን ከንጉሡ አደባባይ ተጥሎ ዓይኑን አውጥተውት አገኙና በሌሊት አንሥተው ወደ እሱ አመጡት። አብሮት አንድ ዓመት ኖረ። ስለዚህ (157ᵃ) እሱም የፈለገውን በመጽሐፍ ልማድ የሚሄዱትን ስላገኘ ደስ አለው። ከዚያ፥ "እግዚአብሔር እናንተን ለጠኝ። ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወቴም በሞቴም ከናንተ አልለይም። ከማነበራችሁ ሥርዓት ደምሩኝ" አላቸው። እነሱም፥ "ከኛ ጋራ ለመሞት ከጨከንክ ጥሩ ነው፤ እንዳልከው ይሁን" አሉት። ምዕዳን እያሰሙት በዚያ ገዳም አንድ ዓመት ኖረ።

ከዚያ፥ ሰይጣን ከፍ ከፍ ብሎ ምአድ በምትባለው ደብር ያሉትን መነኮሳት አስነሣቸው። መጥተው ያዙትና ወደ ደብራቸውም ወሰዱት። ለንጉሡ እንዲሰግድና የዚህን የቅዱስ አባታችንን ስም እንዲሰድብ ጠየቁት።

"እኔ የቅዱሱን ስም አልሰድብም፤ ለንጉሡም አልሰግድም፥ አልታዘዘልኝም" አላቸው።

እንደሚገድሉት በብዙ የሚያስፈራ ነገር አስፈራሩት፤ እሱ ግን በሕግ ከሐዲዎች ሞገድ የማይነቃነቅ፥ በሃይማኖት የአለት ድንጋይ ላይ የተመሠረተ ስለነበረ ነገራቸውን ከምንም አልቈጠረውም። ሲከራከሩትም የእግዚአብሔር መንፈስ በሳዩ ስላለ በተናገሩት ሁሉ ያሸንፋቸው ነበረ። (158ᵘ) ከዚያ፥ መሸንገል ሲያቅታቸው ስለፈሩትና ጠባዩን ስላወቁ ከገዳሙ መለሱት።

ከዚያ፥ ሰዎች (ተከታዮች) ተወለዱለትና ብዙዎች ሆኑ። የመጡትን ሁሉ፥ "የጽድቅ ሥራ መሥራት ከፈለጋችሁ ወደነዚያ ቅዱሳን ወደ ደቂቀ አስጢፋኖስ ሂዱ" እያለ ምዕዳን ያስማቸው ነበረ። እነሱም ቃሉን እየሰሙ፥ ምክሩንም እየተቀበሉ ይመጣሉ። በትምህርቱ የዳኑና ከሕይወት በር የደረሱ ብዙዎች ናቸው።

ሲሞት አብሮት ለነበረው ሰው፥ "አሁንም ልጄ፥ የምነግርህን ስማኝ፤ እነሆ ወደ አምላኬ መሄዴ ነው። አንተም ነፍስህን ጠብቅ። ከእነዚህ ከቅዱሳን ከደቂቀ አስጢፋኖስ ዘንድ በቀር ከሌሎች ደብሮች መኖር አትፈልግ" አለው። ከዚያ፥ ስማዕትነቱን እዚያ በ ... ወር በጌታ ሰላም ፈጸመ። ጸሎቱ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን፥ አሜን።

ያም ለው ከቅዱሳኑ ጋራ ተደባልቆ አብሯቸው ወንድሞቹን እያገለገለ በመልካም ገድል ኖረ። ከዚያ፥ ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ (158ᴬ) በንጉሡ እደባባይ የታሰሩትን ወንድሞች እንዲረዳ የወንድሞቹ ማኅበር ላኩት። እሱንም ከጓደኛው ጋራ ያዙት፤ ከእስር ቤት አስገቡት። እዚያ ገድሉን በመልካም በከባድ በሽታ ፈጸመ። ጸሎቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ እስከ ዘለዓለም ይጠብቀን፤ አሜን።

በነዚያ ዘመኖች ከሀገር ወደ ሀገር እየተሰደዱ (ሰማዕትነታቸውን) የፈጸሙ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ብዙዎች ናቸው። በየዋሻው፥ በመንገድ ላይ፥ በዱር፥ በምእመናን ቤቶች፥ በንጉሡ እደባባይ ገና ከእስር ቤት ሳያስገባቸው በወታደሮቹ እጅ እንዳሉ፥ በከፉ ሰዎች እጅና ጥሩ ነገር በሚጠላ ሰይጣንና ክፉ ጋኔኖቹ ብዙ ሥቃያት ያሳለፉ ቊጥራቸው ፱፻፷ ነው። ጸሎታቸው፥ ልመናቸው፥ የጻማቸው በረከት ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ይሁን፤ አሜን፥ አሜን።

(159ᵇ) በድብ ፀር[413] ዘመን ዘብር ከምትባል ሀገር ጀምሮ ደብረ ብርሃን፥ ዝማ፥ ጐዘም[414] እስኪደርስ፥ ከነዚህ አገሮች በስተ ግራ በኩልና በንጉሡ እደባባይም ሁሉ ሰማዕትነታቸውን በመልካም ሰማዕትነትና በመንፈሳዊ ገድል ከፈጸሙት ውስጥ፥ ቊጥራቸውን ያወቅነው የቅዱስ ብፁዓዊ አስጢፋኖስ ወንድና ሴት ልጆች ሰማዕታትና ጻድቃን ጠቅላላ ድምር ፲፻፬ ነው። የማናውቀውን እሱ ንብረቱን ይሰብስብ። እሱ ራሱ፥ "እምሰት ወፎች(?) በሁለት ቤላ (?) ይሸጡ የለምን? ከነሱ አንዲቱም በሰማዩ አባቴ ዘንድ አትረሳም"[415] ብሏል። ስለዚህ ይኸንን ለኛና ከኛ በኋላ ለሚመጡ ማስታወሻ እንዲሆነን እንዳጣኘነው ጻፍነው። በእምላክ እናት በቅድስት ድንግል ማርያም ማርየም[416] ልመና፥ በትጉሃን መላእክት ሁሉ ጸሎት፥ በቅዱሳንና በሰማዕታት ሁሉ ጸሎት እግዚአብሔር የረድኤታቸውን በረከት ለዘለዓለም ይስጠን፤ አሜን፥ አሜን፥ አሜን።

የንጉሡ ፍጻሜ

(159ᴬ) (ንጉሡ) ከሰው በኩል ክፉ ነገሮች እንዳይቀርቡት በማንኛውም ይጠበቅ ጀመር። ምክንያቱም በሰው እጅ የሚሞት መስሎት መጠራጠር ያበዛ ነበረ። በብዙ ምክንያት ጉዳሌ፥ ደስክ፥ ጠፉንይ[417] እያለ ስንት ቊጥር የሌላቸው ብዙዎች መኳንንት፥ ካህናት፥ መነኮሳት ገድሏል! ስለዚህ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ብርጉማና ድንጉጥ ሆነ። በሰው እጅ የሚሞት መስሎት ሥጋውን ይጠብቅ ነበረ። በሁሉም ነገር፥ በሚበላውም ሆነ በሚጠጣው በሚለብሰውም፥ ሰው ሲያየውም ይጠራጠር ነበረ። የእግዚአብሔር ዕለት ባልጠረጠሯት ጊዜ ድንገት እንደምትመጣ አሳወቀም። መምጣቷ እይቀርም፤ ግን በሰው እጅ የሚሞት መሰለው። ጻድቃኑን ሲገድል ሥራቸውን[418] ለሰው ሳያሳይ ገድሏል። እግዚአብሔርም በማይታይ ሥቃይ ይመታል። ግን ሥቃዩን እስኪፈጽም፥ ቃሉ (ካፉ) ወጥቶ ሳይፈጸም፥ ጥብልያኮስ የሚባለው

413. "በዘርአ ያዕቆብ"።

414. ጐ"፤ "ጎ" እና "ጔ" አንድ ኖኔ ሆነው።

415. መሆን የነበረበት "ሁለት ወፎች በአንድ ቤሳ" ነበር፤ ማቴ 10፡ 29።

416. ጸሐፊው ትክክሉ የቱ እንደሆነ ስላላወቀው ይሆናል ሁለቱንም የጻፈልን።

417. እነዚህ ሁሉ "በርኩስ መንፈስ ኀይል" የሚጠነቁሉ የተለያዩ ዛሮችና ቡዳዎች ናቸው።

418. "እምነታቸውን"።

የሞት መልአክ እስኪመጣ ይታገሣል።[419] ይኸንንም ተንኮለኛ (160ᵘ) የሚመረምረው የእግዚአብሔር መልአክ አለበት።

አቡነ ቅዱስ እስጢፋኖስ ትክክለኛዋን ሃይማኖት ስላስተማረና እንደ ነቢዩ ቃል፥ "የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስቡ፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለሱ፤ የአሕዛብ ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይስገዱ፤ መንግሥት የእግዚአብሔር ነችና"[420] ስላለ፥ በዚህ ምክንያት ገረፈው፤ ብዙም ቀጣው። (ስማዕትነቱን) አዚያው አልኪፈጽም ድረስ በእስር ቤት ዘጋበት። ከሱ በኋላ ልጆቹንም ብዙ ተንኮል ሠራባቸው፤ ለንጉሥ መስገድ እምቢ ስላሉ እይሁዳውያን እያስመሰለ ፀረ ማርያም እላቸው። በዚህም ይገድላቸው ጀመር።

ይኸንን በእግዚአብሔር ባሮች ላይ ሲሠራ፥ ጻድቃንንም ሲሰድብ፥ ንጹሕ ደም ሲያፈስ (ስለኖረ) በሰው እጅ የሚሞት ስለመሰለው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ጥርጣሬ አደረበት፤ ስለዚህ ከሚያምናቸው ከጥቂቶች ባሮቹ በቀር ሌላ ወደሱ አያስገባም ነበረ።

ከዚያ፥ ብፁዓን (160ᵑ) ቅዱሳንን አባ ፍሬ ክርስቶስን፥ አባ ሚናስን፥ አባ ገላውድዮስንና ከነሱ ጋራ የነበሩትን በገደላቸው በ፱፭፱ ቀን፥ ከቀኑ ፰ ሰዓት ላይ፥ በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠ የእግዚአብሔርን መልአክ ሲያይ ከመሬት ላይ (ወድቆ) ተዘረጋ። ከፍ ባለ ድምፅ ዋይ ብሎ ጮኸ። ሰው በመጠርጠር (ከሌሎች ለይቶ) የሚያምናት አንዲት ሁል ጊዜ የምትጠብቀው ሴት እዚያ ነበረች፤ ሌሎቹ ነገር የሚያመላልሱ ትናንሾች ባሮቹ (ነበሩ)። የእግዚአብሔርን መልአክ ሲያይ ጮኸ። ከዚያ በኋላ ቃል አልተናገረም። (ሴቲቷ) አንሥታ አቀፈችውና፥ "ፊትህን አማትብ፥ ጌታዬ፤ ፊትህን አማትብ፤ ፊትህን አማትብ" አለችው። እሱ ግን መልስ አልሰጠም።

ከዚያ፥ እነዚያን ባሮች፥ "ሂዱ ቶሎ ብላችሁ ዐቃቤ ሰዓትን የጸሎት ውሐ ይዞ እንዲመጣ ጥሩት" አለቻቸው። ሂደው አመጡት። የሆነውን ነገሩት። የዓቃቤ ሰዓቱ ስም አምነ[421] ነው። የጸሎት ውሐ ይዞ በቶሎ መጣ። አየውና የጸሎት ውሐ ረጨው። "ምንድን ነው የሆነው?" አለ። (161ᵘ) እሱ ግን አልመለሰም። በዚያች ጊዜ ክፉ ሞት ሞተ።

ከዚያ፥ ይቺ ሴትና ዓቃቤ ሰዓቱ፥ "አሁን ምን እናድርግ? ማን ይንገሥ?" ተባባሉ። ሴትዮዋ፥ ሮም ሰገድ[422] ይንገሥ፤ ምክንያቱም እሱ ለሁሉም ይሻላል" አለች። አምነ የሚባለው ዓቃቤ ሰዓት፥ "እሱ አይደለም የሚነግሠው። በእደ ማርያም ይንገሥ፤ ምክንያቱም እሱ ለሁሉም ይሻላል። እሱ የሚናዘዘው በኔ እጅ ነው" አለ። በነገሩ አየለ። "እንተ እንዳልክ ይሁን" አለች።

ከዚያ፥ በእደ ማርያምን እንዲያመጡት ዓቃቤ ሰዓቱ ባሮቹን ወደሱ ላካቸው። በእደ ማርያም በግምብ ውስጥ እስረኛ ነበረ። ቶሎ እንዲመጣ ነገሩት። ቶሎ ተነሥቶ ከነስንሰለቱ ደረሰ። ዐቃቤ ሰዓቱ (ከውስጥ) ወጥቶ፥ "ንጉሡ እንደምን አለህ ይላል" አለው። "መልካም አለሁ" አለ።

---

419. አንዳንድ ቦታ "ጥልብያኮስ" ሲል ይገኛል።
420. መዝ 21: 27/28።
421. "አምነ (ለ)ጽዮን"።
422. የአፄ ዘርአ ያዕቆብ ልጆች ስንት እንደሆኑ አይታወቅም።

ከዚያ ደግሞ፥ "እኛ መንግሥታችን ላንተ እንጂ (161^ሰ) ለሌላ ይሁን አንልም። እንግዲህ በመንግሥቱ ዙፋን ላይ ተቀመጥ፤ አባትህ ሞቷል" አለው። ከዚያ፥ በአባቱ ዙፋን ላይ ተቀመጠ።

ይኸ ታሪክ እስከዛሬ በነሱ ማህል ይነገራል። ሌሎች ግን፥ "በደስታ እስኪያረጅ ነግሦ በመልካም ሞተ፤ ከመሞቱ በፊት ልጁን አነገሠው። ስለ ሁሉም ነገር ምዕዳንም አሰምቶታል (መክሮታል)" ይላሉ። እነዚህ ንጉሡን የእግዚአብሔር ቁጣ ድንገት እንደቀሠፈው የሚያውቁ ናቸው።

ልጁም ሲነግሥ በሙሉ ኃይሉ ግልፍተኛ ሆነ። ብዙዎቹን ወንድሞቹን ለመንግሥቱ በመቅናት ገደላቸው። ከታላላቆቹ መኳንንትም በተቆጣ ቁጥር የገደላቸውን ለተገፉ የሚበቀል እግዚአብሔር ይቀጠራቸው።[423]

423. በእደ ማርያም እንደነገሠ ጨካኝ እንደነበረ ታሪኩም ይመሰክራል፤ ብዙዎቹን ቋንጃቸውን እየቁረጠ እንዳባቱ ጉንጽ ከርቸሌ ሰዷቸዋል። Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm*, pp. 126-129.



በግብጽ ምድረ በዳ የማኅበር ምንኵስናን የጀመሩ አባ ጳኵሚስ
(ከደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሐፍ፡ MS Spencer 7, f. 2b.)

የአባ አበክረዙን ገድል

"ከእግዚአብሔር የተሰጠችውን ጸጋ ከሌላው ዘንድ ሲያይ
የሚቀና ነፍሰ ገዳይ ነው::"

አባ አበክረዙን



የደብረ ገርዜን ሁለተኛው አበምኔት አቡነ አበክረዙን።
(ከደቂቀ እስጢፋኖስ መጽሐፍ፣ MS Spencer 7, f. 113b)



መግቢያ

(114^{ሀ}) መጀመሪያ በሌለው በሕያዉ፥ መጨረሻ በሌለው የዘላለም ብቸኛው ባለሥልጣን፥ በገጽና በአካል ሶስት፥ በመለኮት በማይከፈል በአንዱ፥ በማይሰበሰበው በሁሉ ሙሉው፥ በሥሉስ ቅዱስ ስም፥ ለቤተ ክርስቲያን ከሚቆምላት፥ ከከሐዲዎች ሞገድ ከረጋው፥ ከብዙ ሐሳብ ከተሰወረው፥ ከደብረ ገርዜን መንጋ አረኛው፥ ገድሉን በዕብራውያን በ፳፫ አየር፥ (114^{ለ}) በግዕዝ ግንቦት ፳፱፥ በጥሩ እርጅና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ከፈጸመው ከብፁዕና ከቅዱስ አበክረዙን ገድል በጥቂቱ እንናገራለን፤ አሜን።[1]

ትውልድና አስተዳደግ

የዚህ ሰው የትምህርቱ መሠረት ከብፁዕና ከቅዱስ አባት፥ የክርስቲያን መብራት አስጢፋኖስ ነው። ቅዱሱ እንደደነገገው የሕግ ውሳኔዎችን

---

1. ይህ መግቢያ ረጅም ግጥም ሰለሆነ፥ ከዚህ በተሻለ አማርኛ መመለስ ያስቸግራል፤

በስመ ሥሉስ ቅዱስ ሕያው ዘእንበለ ጥንት፥
ወብሑተ ሥልጣን እስከ ለዓለም ዘእንበለ ተፍጻሜት፥
ሥሉስ በገጻት ወበአካል፥
ወአሐዱ በመለኮት ዘኢይትከፈል፥
ምሉእ በኵለሄ ዘኢይቀብል፥
ንዜኑ ጎዳጠ ዘእምዜና ገድሉ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አበክረዙን፥
ቀዋሚሃ ለቤተ ክርስቲያን፥
ዝጉን አመዋግደ ዕልዋን፥
ወስዉር አምሕሊና ብዘኃን፥
ኖላዌ መርዔት ዘደብረ ገረዛን፥
ዘፈጸመ ገድሉ በሠናይ ርስኣን፤
አሜን።

መልእክቱ፥ "በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም፥ በግንቦት ፳፱ ገድሉን ፈጽሞ ያረፈውን የብፁዕ ወቅዱስ አበክረዙንን ገድል በሥሳሴ ስም ባጭሩ እንጽፋለን" ነው።

አንደዚህ ገድል ቀደም ብሰው የተደረሱ የግዕዝ ምንጮች ዘመን ሲሰጡ "በዕብራውያን" በሚሉት በሱርስትና በግዕዝ ባሕረ ሐሳብ ነው፤ በዚያ ላይ ዘመኑን ብዙ ጊዜ በሱርስት ሲሰጡ ብዙ ጊዜ የግዕዙ ይረሳቸዋል። ስለ ግዕዙ ዘመን ቁጠራ፥ ጌታቸው ኃይሌ፥ *ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቍጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ*፥ ከሌጆቪል (ሚኒሶታ) ፲፱፻፹ ዓ. ም.

እያሳወቀ÷ ከሱ ቀጥሎ ፈለጉን በሚከተሉ ገዳሞች ላይ ጎላፊ ነበረ። የወጣውም ናዕዴር ከምትባል ከአከሱም ቀበሌ÷ ከመደባይ ሕዝብ÷ ከድግኑ ነገድ ነው። የአባቱ ስም ተስፋኑ መስቀል÷[2] የናቱ ስም ታድጎነነ ማርያም[3] ነበረ። ... በሚሏት አገር ተወለደ።[4] ስሙንም አስጢፋኖስ አሉት። አንዱ ከሱ በፊት አንዱ ከሱ በኋላ የተወለዱ ሁለት ወንድሞች አሉት።

እነዚህ ልጆች (115[0]) ከማደጋቸው በፊት ያባታቸው አባት ሞቶ÷ ሹመት ከአባታቸው ወጣች።[5] (አባቱም) ርስቱን ትቶ ከሚስቱና ከ፫ቱ ልጆቹ ጋራ ዘንጉ ወደምትባል ሀገር ሄደ። ትንሽ ጊዜ ከኖረ በኋላ እዚያው ሞተ። ሚስቱ ከአናና ሕዝብ ስለነበረች ልጆቿን ይዛ ወደ አባቷ ምድር ወደ ተንቤን ሄደች። የአባቷ ሹመትም ደምበላ ነው። እግዚአብሔርን የምትፈራ ስለነበረች እዚያ (ሳታገባ) በመበለትነት ኖረች። እዚያ በባሏ ሞት ሐዘን ላይ ሳለች÷ አባቷና ከልጆቿም ትንሹ ሞቱ፤ በሐዘን ላይ ሐዘን÷ በለቅሶ ላይ ለቅሶ ተጨመረባት። እዚያ ከ፪ቱ ልጆቿ ጋራ በድኽነት ኖረች። (ሆኖም ልጆቹን) (115[ʌ]) በጥሩ ጠባይ አሳደገቻቸው። ከዚያ በኋላ መዝሙረ ዳዊት[6] እንዲማሩና ለእግዚአብሔር እንዲገዙ ለትምህርት ሰጠቻቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መልካቸውን አላየችም። እሷም መንኮሳ በመነኮሲቶች ገዳም አረፈች።

ልጆቹ ሐይጉመዜ በሚሏት በሊቀ ካህናቱ ደብር ሆኑ።[7] ይኸም ብፁዕ የመዝሙረ ዳዊት ትምህርቱን ሲያደርስ እንዲያደቁነው ከጻጻሱ ከአባ በርተሎሜዎስ[8] ዘንድ ወሰዱት። በዚያን ጊዜ እድሜው ፲፭ ዓመት ነበረ። ዲቁና ተሹሞ ወደ ደብሩ ተመለሰ።

---

2. "መስቀል ተስፋችን ነው"።
3. "ማርያም ታድነን/ታድነናለች"። የናታቸውና ያባታቸው ስም ከቤተ ክርስቲያኗ ጎላፊዎች ጋራ ከሚያጣላቸው ከቅድስት ማርያምና ከክቡር መስቀል ጋራ የተያያዘ መሆኑ አጋጣሚ ሊሆን ይችላል።
4. የተወለዱበት ቦታ ስሙ አልተጻፈም።
5. ሹመት የሚወረስ ከሆነ የሙት ልጅ ያባቱን ሹመት ለምን እንደማይወርስ ታሪክ ጸሐፊዎች ሊነግሩን ያስፈልጋል።
6. አነጋገሩ የትምህርት ዓላማው ወይም ችሎታው ዳዊት መድገም ይመስላል። አባ አስጢፋኖስም ተማሪ ቤት የገቡት *መዝሙረ ዳዊት* ለመማር እንደሆነ ገድላቸው ይናገራል። *መዝሙረ ዳዊት ተማረ* ማለት "He/she became literate" ማለት ሳይሆን አይቀርም።
7. ደብሮች የገቢ ምንጭ ስለነበሩ መንፈሳዊ ሹማምንት አንዳንዶቹን የራሳቸው ያደርጓቸው ነበረ።
8. ስለ አባ በርተሎሜዎስ ገጽ 58 ላይ ጎዳግ ቍጥር 16ን ተመልከት።

መንፈሳዊ ጥሪ

በዚያን ዘመን እዚያ አንዳለ ጽድቅ ፍለጋ ወደ ገዳማዊው አባ ሳሙኤል ደብር ለመሄድ በልቡ አሰበ።[9] (116ᵛ) የሱ ዓይነት ፍላጎት ያላቸው ፫ ጓደኞች አግኝቶ፥ መንገዱን ሳያውቁ ከደብሩ በሌሊት ወጡ፤ ከወርዕ ወንዝ ደርሰው እዚያ መንገዱን ቢፈልጉ አጡት። ከነሱ አንዱ ተመለሰ።

የቀሩት እዚያው ከዱር ሳሉ ወደ ሚሄዱበት የሚመራቸው ረድኤት እግዚአብሔር ሳከላቸው። ፬ ጾምን ለመጾም በዱር የነበረ አንድ መነኮሴ ነበረ። እሱም በዚያን ጊዜ ከጓደኞቹና ከታቦታቸው ጋራ ወደ ደብሩ በመመለስ ላይ ነበረ።[10] "እዚህ ምን አመጣችሁ? ምንስ ትፈልጋላችሁ? ወዴትስ ትሄዳላችሁ?" አላቸው። "ወደ ገዳማዊው አባ ሳሙኤል ደብር ለመሄድ እንፈልጋለን፤ ግን መንገዱ ጠፋብን" አሉት። መነኮሴው፥ "አትፍሩ (116ᴬ) ልጆቼ፥ እኔ አመራችኋለሁ፤ መንገዱን አሳያችኋለሁ" አላቸው። እንዳለው አደረገ፤ መንገዱን አሳያቸው።

ከፈለጉበት ደብር ሲደርሱ አንድ መነኮሴ ተቀበላቸውና አበምኔቱ ዘንድ ሳያደርሳቸው ከሱ ጋራ አኖራቸው። በዚያው ዓመት አበምኔቱ ሞተ። የደብሩ ሰዎች ያ መነኮሴ አበምኔት እንዲሆን ምክር ያዙ። አንዳንዶቹ፥ "እሱ ከደብረ ቈየጻ[11] ስለሆነ፥ ከዚህ ደብር ያልተወለደ አይስማማንም" አሉ። መነኮሴው ይኸንን ሲሰማ ተቆጥቶ እነዚያን ልጆች ይዞ ወደ ቈየጻው አባ ሳሙኤል ወሰዳቸውና፥ "እንካ እነዚህን ልጆች፤ ልጆች እንዲሆኑህ አመንኩሳቸው፤ የደብረ ዲጋ መነኮሳት (117ᵛ) በላያቸው መምህር አንዳልሆንባቸው ከደብራችን ያልሆነ ብለው ተቃወሙኝ። ስለዚህ እነዚህን ልጆች ስለ ቤቴ ቅናት[12] (ወደዚህ) አመጣኋቸው" አለው። እሱም ተቀብሎ እሱ ዘንድ አኖራቸው።

---

9. ደብረ ሃሌ ሉያ (ሃሌሎ) መሆን አለበት፤ Gérard Colin, *Vie de Sānu 'ēl de Dabra Hāllēluyā, CSCO*, vol. 519/93, Lovanii 1990.

10. ክርስቶስ 40 ጾምን (ሁዳዴን) የጾመው በምድረ በዳ ስለነበረ (ማቴ 4፡ 1-11)፤ መነኮሳቱም እንደሱ ለማድረግ ከገዳማቸው እየወጡ ወደ ዱር ይሄዱ ነበረ።

11. ደብረ ቈየጻ ደቂቀ አስጢፋኖስ የወጡባት ሆና በሌላው አባ ሳሙኤል ስም የምትጠራ ገዳም ናት። ምንኮስናን እትግራይ ላይ በአንድ ቀን ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ከአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ዘበንኰል እጅ ከወሰዱ ኮከቦች ከሚባሉ ስድስት ሰዎች ውስጥ ሶስቱ ሳሙኤል የሚል ስም ወስደው ሁሉም የየራሳቸውን ገዳም እቋቁመዋል፤ እነሱም ሳሙኤል ዘዋልድባ (ዘገዳመ ዋሊ)፥ ሳሙኤል ዘቆየጻ፥ ሳሙኤል ዘጣራጣ ይባላሉ። ሌሎቹ (እነሱም ገዳማትም ያቋቋሙ) ጓደኞቻቸው ዮሐንስ ዘጉራናቋ፥ ታዴዎስ ዘባልታርዋ፥ ያላይ ዘማንዳምባ፥ ያፈቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤን ናቸው። እቡነ መድኃኒነ እግዚእ ዘበንኰል በሌላ ቀን ደግሞ ሌሎች 5 ኮከቦች እመንኮሰዋል፤ እነዚህም፥ እንደ ሌሎቹ የምንኮስና ታላቅ ወንድሞቻቸው፥ ገዳማት እቋቁመዋል፤ እነሱም፥ እሮን ዘክትር፥ መርቆሬዎስ ዘሃባ፥ ዘካርያስ ዘጊፋ፥ ገብረ ክርስቶስ ዘቢታንያ፥ ዳንኤል ዘፀዓዳ እምባ ይባላሉ። René Basset, "Études sur l'Histoire d'Éthiopie," *JA*, vol. 17 (Avril-Mai-Juin 1881), p. 324. ልጆቻቸው በተራቸው ገዳማት እቋቁመዋል።

12. "የቤትህ ቅናት በላኝ" የሚለውን መዝ 68፡ 10 ያስታውሳል።

ምንኵስና

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ አባ ሳሙኤል ቅድስት አስኬማ ሰጣቸው፤[13] በሐምሌ ፳፬ ቀን በሰማዕቱ በአባ ኖብ ዕለት አለበሳቸው።[14] በማግስቱ የሰማዕቱ የአበክረዙን ዕለት ነው።[15] ስለዚህ አንዱን ኖብ ይኸንን ብፁዓዊውን አበክረዙን አሳቸው። በዚያን ጊዜ እድሜው ፲፯ ዓመት ነበረ። እዚያ በጥሩ ጠባይና በብዙ ደግነት ኖሩ። ከብዙ ዓመታት በኋላ አባ ኖብ አረፈ። በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠራ[16] ሰው ነበረ። ይኸንን ብፁዕ (አበክረዙንን) (117[A]) አበምኔቱ የማጎበሩን አትክልት ከሚያበስሉ ጋራ እንዲያገለግል መደበው። እዚያ ለሱ ብጤዎቹ በታዛዥነት ፫ ዓመት ኖረ።

ከአባ አስጢፋኖስ ጋራ

በዚያን ዘመን አቡነ አስጢፋኖስ ወደዚያች ደብር መጣ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳሙኤል ቅድስት አስኬማ ሰጠው። በዚያን ጊዜ እድሜው ፲፱ ዓመት ነበረ፡ የክርስቶስን ቀምበር ካንገቱ ላይ በማነቀ አነገባት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዓለማውያን የሚወዱትን ቅባት ያለበትን ነገር ሁሉ በሥጋው ምኵራብ ውስጥ አላስገባም። ነፍሱን በእንጀራና በውሐ (ብቻ) አቆያት። ያውም ቢሆን የጌታን ስብሐት ለማላረግ (ያህል) ነበረ። ብዙዎች (ፈተናውን) ያልፍ ወይም ያፈገፍግ እንደሁ ለማወቅ ያስተውሉት ነበረ።

ነፍሱ በሕግ ስለምትረዳበት አንድ ራእይ ታየው።[17] (118[B]) ነፍሱን አያስጨነቃት ሥጋውን አያስበረከከ ጎይል ያገኝ ጀመረ። ከላይ ድረስ አየወጣ ጫፉን እስኪይዝ ድረስ (በገድል ላይ) ገድል ይጨምር ነበረ። ይኸንን ገድል በጀመረ በ፫ ዓመት ከመንፈስ ቅዱስ ርዳታ አገኘ። አቡነ ቅዱስ አስጢፋኖስ በዚህ ሁኔታ ሳለ፡ ይህ ብፁዕ አበክረዙን ያስተውለው፡ ነገሩንና ሥራውንም ይመረምር ነበረ።

ከዚህ በኋላ፡ አበምኔቱ (አቡነ አበክረዙንን) አትክልት ከሚያበስሉት (መደቡ) አወጣውና የሰሌን እቃ ሰፊዎች ዘንድ መደበው። እዚያም በመልካም ታዛዥነት ኖረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከዚያም አውጥቶ ከዲያቆናቱ ቤት

---

13. የምንኵስናውን ሥርዓት ፈጽሞ አስኬማ (የመነኰሴ ልብስ) አለበሳቸው።
14. አባ ኖብ በዲዮቅልጥያኖስ ጭከና ካለቁት ግብጻውያን ክርስቲያን መነኮሳት አንዱ ነበሩ፤ ገድል አሳቸው፤ ታሪካቸውን ባጭሩ ለማወቅ የፈለገ ለሐምሌ 24 ቀን ለስንክሳሩ የተዘጋጀውን ምንባብ ማየት ይችላል፤ ለምሳሌ፡ Ignazio Guidi, "Le Synaxaire, Éthiopien, les mois de Sanê Hamê et Nahaê," P.O., vol VII (1911), p. 392.
15. አበክረዙንም ከግብጽ ቅዱሳን መነኮሳት አንዱ ነበሩ። የግዕዝ ገድል እንዳላቸው፡ አላጋጠመኝም፡
16. "በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠራ" ማለት "እግዚአብሔር መርጦ የወሰደው" የመረጠው ማለት ነው።
17. በሕግ መረዳት የሚለው በክርስትና መጻሕፍት መመራትንና ከፍ ባለ የምንኵስና ደረጃ መኖርን ነው።

ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አልቅና ሾመው።[18] ችግረኝነትን አፍቃሪ ስለነበረ፥ እግዚአብሔርን በመልካም ትጋትና በብዙ ደግነት፥ (118^ሰ) በፍጹም ትሕትናም አያገለገለ ኖረ። ስውም እንዳያውቀው ራሱንም ይደብቅ ነበረ። ምክንያቱም ከተከበሩ (መኳንንት) ወገን ነበረ። የደብሩ ሰዎች ግን አላወቁም፤ በነሱ ዘንድ አንድ የተናቀ ሰው ነው። እሱም የሚደርስበትን ብዙ ችግር፥ ረኃብና መራቆት፥ ሁሉ ይታገሥ ነበረ። በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ፰ ዓመት ኖረ።

በዚች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ባለበት ጊዜ የቅዱሱን (የአቡነ አስጢፋኖስን) ትምህርት ለመስማት አየሄደ ነፍሱን ከኃጢአት ባርነት የሚያወጣበትን ጥቅም ከሱ ልብ ይል፥ የሕግንና የሥርዓትን ውሳኔዎች ይማርም ነበረ። በሐዋርያት ትእዛዝ ውስጥ ምአመናንን፥ "ሁሉም አያንዳንዱ (119^ሀ) ወደ ትምህርት ቦታ ለመሄድ ይትጋ"[19] የሚል አንደተጻፈው፥ አሱም "የተጠሙ ወደ ውሐ ይሄዳሉ"[20] የሚለውን ተስፋ ለማግኘት ይሽንን በጉጉት ያደርግ ነበረ።

ከሱ ተምሮ ሥራውን ተከታይ፥ በፍቅሩ መንፈሳዊ ገመድም ተሳቢ ሆነ። በትዕግሥቱ መዓዛ ምክንያት እንደሱ ከቅዱስ አስጢፋኖስ የትምህርቱ ፈለግ ብዙዎች ተጨመሩ። ምክንያቱም በነቢዩ አነጋገር እንደተጻፈው፥ የቅዱሳን መዓዛ አንደ ቁላ የደንጎላዎች አበባ፥[21] እና አንደ በአትክልት ቦታ የሮማን አበባ ነው። የአትክልት ቦታ የሽቶ ቤት ነውና። መዓዛ ያለው ሽቶ በአትክልት ቦታ ካለ፥ የአትክልቱ (ቦታ) መዓዛ ይኖረዋል። በውስጡ ወዲያ ወዲህ የሚሉም ከሱ መዓዛ ይወስዳሉ። ይሽም ብዙሪ ጣዕም ያለው መዓዛ ያለበት የአትክልት ቦታ ስላገኘ፥ (119^ሰ) በሙሽራው የሠርግ ድግስ ለመደሰት ከንጉሡ አዳራሽ ውስጥ ለመግባት መሪ አስኪሆነው ድረስ፥ ሁል ጊዜ ወደሱ ይሮጥ ነበረ።[22]

መነኩሳቱ በአባ አስጢፋኖስ ላይ ተነሡ

አበምኔቱ ብዙው ከቅዱስ አስጢፋኖስ ጠባይ ጋራ ተባባሪ እንደሆነ ሲያውቅበት፥ ለዲያቆናት ቤት ቤተ ክርስቲያን ከሚሰጠው አገልግሎት አስወጣውና በማኅበሩ ሥራዎች ላይ ከተሰማሩት ደቀ መዛሙርት ጋራ መደበው። አሱም አሺ አለ፤ በታዛዥነት ማሳ ውስጥ ያለች የኅብስት ሌማት በዓይኖቹ ፊት ስለጣመችው፥ የአበምኔቱን ትእዛዝ ሳያቃልል ከወንድሞች ጋራ (ከአርሻ ቦታ) አየዋለ ይመለስ ነበረ።

---

18. ዲያቆናቱ የራሳቸው መኖሪያና የራሳቸው ቤተ ክርስቲያን እንዳላቸው የሚያመለክት ይመስላል።
19. ሲኖዶሱ አልታተመም።
20. ኢሳ 55: 1።
21. መኃ 2: 2።
22. "የሙሽራው የሠርግ ድግስ" የሚለው ማቴ 25: 1-11 ያለውን ሲያመለክት ነው።

ከዚያ በኋላ፡ በአቡነ ቅዱስ እስጢፋኖስ ጠባይና በጥሩው ትምህርቱ (120^{0}) በሚተባበሩት ምክንያት የደብሩ ሰዎች ልባቸው ተሸበረ። በቤተ ክርስቲያን በበዓል ዕለት በስብሐት ማኅሌታቸው ጊዜ፡ በጻድቁ ላይ ምርር ያለ ውሸት የሚናገር የማኅሌት ስብሐት ተቀኙ፤[23] ከነሱ ውስጥ ጤማይ የሚሉት ዓይነ ስውር፡ "የደብሩ ልማድ ያልሆነ፡ በመዝገቡም ያልተገኘ (ልማድ ያመጣ)፡ አንድ ሰው ወጣ" አለ።[24] በአቡነ ቅዱስ (እስጢፋኖስ) ጠባይ የሚተባበሩ ሌሎች ሰምተው፡ "እሱን የምናየው በመልካም ጠባይና በጽድቅ ሥራ ላይ ነው እንጂ (እንደዚህ) እናንተ እንደምትሉት አይደለም" አሏቸው።

ከዚያች ዕለት ጀምሮ ጥላቸው ከድብቅ ወደ ግላጭ ወጣ። ባደረባቸው የቅናት ወይን ሰከሩ። ከአበምኔቱ ዘንድ (ሄደው)፡ "ይህ ሰው እነሆ (120^{0}) በደብሩ ልማድ ባልሆነ በራሱ ምክር ይሄዳል፤ ደግሞ ሌሎችን ወደ ባሕታዊነት ትሕርምቱ ይስባል" ሲሉ ከሰሱት። አበምኔቱም ነገራቸውን ተቀበላቸው። ቅዱሱን የሚከተሉትን ከመሥዋዕትና ከ(ማኅበር) ማእድ ያባርሯቸው ጀመር። እሱንም አባረሩት፤ ግፉን ተሸክሞ ሄደ። ብዙዎች ወንድሞች አብረውት ተሰደው እስከ ባሕረ ሳፍ[25] ድረስ ሄዱ።

ተሰድደው ለሥቃይ ተመለሱ

የተሰደደበት ጉዳይና ተመልሶ የመጣበት ምክንያት በገድሉ መጽሐፍ ውስጥ አለ። ጊዜው ክረምት ስለነበር ሲመለሱ በመንገድ ብዙ ችግር ደርሶባቸው ነበረ። ተከዜም ስለሞላ መሻገር አቅቷቸው ነበረ። ግን እግዚአብሔር እርዳታ ልኮላቸው እሻገራቸውና በፊት ወደ ተሰደዱበት ደብር (ወደ ደብረ ቆየጻ/እባ ሳሙኤል) መጡ። (121^{0}) ቤተ ክርስቲያን ተሳለሙ፤ አበምኔቱንም እጅ ነሡት፤ እዚያ በቤተ ክርስቲያኑ የአትክልት ቦታ ነበረ። የአገረ ገዢው ሎሌም አብሮት ነበረ። ሎሌው የቤተ ክርስቲያኗን የሕንፃዋን ጌጥ አይቶ፡ ቅዱሱን፡ "አባ፡ ይቺን ጌጥ አታይምን? እንዴት ትተሃት ወደ ሌላ ትሄዳለህ?" አለው። ቅዱሱ፡ "ይህ የምታየው ሕንጻ ቅዱሳን ሲቀድሱት ይቀደሳል፤ ሲያረክሱት ይረክሳል" አለው።[26]

አበምኔቱ ይኸንን ከቅዱሱ ቃል ሲሰማ፡ "ቤተ ክርስቲያን ሲሳደብ አትሰሙምን?" እስና የሚናገረውን ሳያውቅ በቁጣ ተነሣ። አብረውት

---

23. "ስብሐተ ማኅሌት" ("የማኅሌት ስብሐት") የሚለው በቤተ ክርስቲያን የሚቀኙትን ቅኔ መሆን አለበት። ሥርዓቱ ጥንታዊ ለመሆኑ ይህ አንድ ማስረጃ ነው። በአፄ ዘርአ ያዕቆብም ዘመን ይደረግ ነበረ፤ Getatchew Haile, *The Epistle of Humanity of Emperor Zär'a Ya'aqob (Ṭomarä Tæsbə't)*, *CSCO*, text, vol.522/95, p. 4, tr. 523/ 96 (1991), p. 2.

24. የቅኔው ዓይነት ባይታወቅም፡ ግዕዙ በ "ሩ" ቤት ይመታል፤ *"ብእሲሰ መፅአ ዘኢነ በግዕዘ ደብሩ፤ ዘወኢተረክበ ውስተ ጦማሩ።"*

25. ባሕረ ሳፍ ("የሳፍ ባሕር") የጣና የጥንት ስም ነው።

26. "ሰው ቦታን ይቀድሰዋል እንጂ ቦታ ሰውን አይቀድስውም" የሚለውን *መጽሐፈ ሲናዶስ* ለመጥቀስ ነው።

ያሉትን፦ "እንዴት ዝም ትላላችሁ?" አላቸው። ከዚያ በኋላ ቀደም ብለው እንደተማከሩት፦ እያንዳንዳቸውን ተናጠቋቸው፤ (ለካ) ክፉ ነገር (121ᴬ) ሊያደርሱባቸው ተዘጋጅተው መመለሳቸውን ሲጠብቁ ኖሯል። ከዚያ፦ ቅዱሱን በእግር ብረት አስረው እቤት ውስጥ ዘጉበት። ሌሎቹንም ወንድሞች ዘመዶቻቸው (ሆነው ሳለ) አሰሯቸው። የቅዱሱን ትምህርት በአስራት የሚያስቀሩ መስሏቸዋል።

አበምኔቱ ብፁዕ አበክረዙንን በእጁ ገፈተረውና፦ "በጀመረው መንገድ ሁሉ ረዳትና ጓደኛ የሆንከው አንተ አይደለህምን?" ብሎ አባረረው። ስደቱን ተሸክሞ ከእምነቱ ጋራ ሄደ። ሌላውም ይህችን ማኅበር በማቋቋም ረዳት የሆነው ዮሐንስ የሚባለው ወንድም አብሮት (ተሰደደ)። (አባ አበክረዙን) በዚያን ጊዜ እድሜው ፴፫ ዓመት ነበረ። ከተከዜ አጠገብ ወዳለች ዜራናቋ ወደምትባል ወደ አንዲት ደብር ሄዱ። አበምኔቱን ከአጠገቡ ማጎደር ሰጥቷቸው (122ᴮ) በጽሙና እንዲኖሩ ለመኑት። በተከዜ ምድረ በዳ አንድ ቦታ ሰጣቸው። ከዚያ በኋላ፦ ከዚያች ከተባረሩባት ደብር ፬ ወንድሞች መጡ፤ ፮ ሆኑ። እዚያ ማጎደር አቋቋሙ።

ተሰድደው የራሳቸውን ማኅበር (ገዳም) አቋቋሙ

አቡነ ገብረ ክርስቶስ ከአስራቱ ሲፈታ ወደነሱ ሄዶ፦ ቅዱሱን ሊገድሉት በእስር ቤት እንደዘጉበት ነገራቸው። ሲሰሙ አዘኑ፤ በጣም ተከዙም። አቡነ አበክረዙንና የቅዱሱ ረዳት ተነሥተው (ከጻጻሱ) ከአባ በርተሎሜዎስ ደብር[27] መጡ፤ አላገኙትም። ለደበሩ ሰዎች፦ "እነሆ፦ ምንም ኃጢአት ወይም አበሳ የሌለበትን ደኅ ሰው ሊገድሉት (122ᴬ) ይፈልጋሉ። ረድታችሁን ለአገሩ ሹም እንድትነግሩት እንፈልጋለን" አሏቸው። እነዚያ፦ "ሄዱና ለአበምኔቱ እናንተው ንገሩት፤ (ጳጳሱ) አውን እዚህ የለም" አሏቸው።

ወንድሞች በጎ ነገር እንዳላገኙና የሚረዳቸውም እንደሌለ ሲያውቁ፦ "እዚያ እስክንሄድ ድረስ አባታችን ይሞታል፤ እኛው ራሳችን ወደ ሹሙ ሄደን እንንገረውና እቤት እንበል" ተባባሉና ከህገሩ ሹም ዘንድ ሄደው አባታቸውን በእግር ብረት እንዳሰሩትና እንዲሞት እንደዘጉበት ነገሩት። ይኸንን ነገር ሲሰማ፦ "እንደዚህ ተፈጽሞ ከሆነ አብሬያችሁ ሄጄ እዚያው እዳኛችኋለሁ" አላቸው። ከዚያ፦ አብሯቸው መንገድ ጀመረ። (123ᴮ) ወደዚያ ሊደርሱ ሲሉ አብሯቸው ያለውን ሶስተኛውን ወንድም የቅዱሱን ሁኔታ፦ ሞቶም እንደሁ ወይም በሕይወት እንዳለ ለማወቅ አስቀድመው ላኩት።

በዚያ ደብር ውስጥ ሰላም የሚሠራ[28] ሽማግሌ መነኮሴ አለ። ትዕግሥቱን ያደንቅ ስለነበረ፦ በሌሊት ራእይ በእስር ቤት የተዘጋበትን አቡነ ቅዱስ አስጢፋኖስን የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ (ወርዶ)

27. ጎዳግ ቁጥር 7ን ተመልከት፤ ደብር የመተዳደሪያ ምንጭ ስለሆነ ጳጳሱም የራሳቸው ደብር አላቸው።

28. እነጋገሩ "ሰላም የሚሠሩ ብፁዓን ናቸው" እንዳለው ነው፤ ማቴ 5: 9።

እንደጐበኘው፥ ቅዱሱ ባለበት ቤት ውስጥም እንዳበራ፥ መንፈሳዊ ሰላምታ እንደሰጠው፥ የብርሃን ውበት የተሞላች ቅድስት ፊቱን እንደሳመው አየ።

ራእዩን እንዳየ ከአበምኔቱ ዘንድ ሄዶ፥ "ይህ ሰው ከሞተ (123ስ) የሀገሩ ሹም ደብራችሁን ያጠፋዋል፤ ከሱ ጋራ ሰላም አድርጉ፤ ከእስራቱም ፍቱት" ስላለው፥ አበምኔቱና የደብሩ ሰዎች ይኸንን ሲሰሙ ሐላቡን ወደ ውስጥ ቅዱሱን ከእስር ቤት አውጥተውት ኖሮ፥ አስቀድመው የላኩት ወንድም ሲደርስ ቅዱሱን ከእስራቱ ተፈትቶ አገኘው። (መልክተኛው) ወደ ሀገሩ ሹም ሄደው የሆነውን ሁሉ እንደነገሩት፥ (ሹሙም) ከእጃቸው ሊያድነው እንደመጣ ነገረው። ቅዱሱ ሰምቶ ለዚያ ወንድም፥ "ከእስራት ፈተውኛል፤ ከነሱ ጋራም ታርቀናልና የሀገሩን ሹም እንዳያመጡት ለወንድሞች ንገራቸው" አለው። እሱም ይኸንኑ ነገራቸው። እነሱም ከእስራት እንደፈቱት(124ሀ) ለሀገሩ ሹም ነገሩት። "ሰላምና ዕርቅ ማድረጋቸው ጥሩ ሠርተዋል" አለ።

ከዚያ፥ እነዚያ ወንድሞች አባታቸውን ሊቀበሉ ከደብሩ ጥግ ድረስ መጡ። ቅዱሱ ከዚያች ደብር ወጣ። (ጠላቶች) ከእሱ እስኪነጥሉት ድረስ እህል ውሐ ያቀብለው የነበረውን አሮን የሚባለውን አንድ ወንድም ከእሱ ጋራ ይዞት ሄደ። ቅዱሱ ልጆቹን በደብሩ ጥግ አገኛቸው።

አቡነ አበክረዙን ቅዱሱን ተቀብሎ ብዙ ደብሮችንና ገዳማትን እንዲጐበኙ ሁለቱ (አብረው) ሄዱ። አቡነ አበክረዙን ያኖራቸው ወንድሞች ካሉበት ማጎደር ድረስ ደረሱ። ዮሴፍን በችግርና በታላቅ ሥቃይ ጊዜ አስቀድሞ ወደ ግብጽ አገር ልኮት እንደነበረ፥ ለአባቱና ለወንድሞቹ ማረፊያ እንዲሆን (124ስ) እግዚአብሔር (አበክረዙንን) አስቀድሞ ልኮት ነበር። በኋላ ዘመን በነሱ ጊዜ የሚሆነውን ነገር እግዚአብሔር ለዮሴፍ ስላሳየው ወንድሞቹ በቅናት ሸጡት። በተሸጠበት እግዚአብሔር ጥበብና ምክርን ሰጥቶት፥ በግብጽ ንጉሥ በፈርዖን ፊት ሞገስ አገኘ።[29]

እንደዚሁ ይኸንን ብፁዕ አበክረዙንን በወንድሞቹ ማህል ወገን አልነበረውምና በግፍ አባረሩት። ባለእናት ዮሴፍን የሸጡት ዕለት በወንድሞቹ ማህል ብቻውን እንደሆነ፥ ይኸም ብፁዕ አበክረዙን (125ሀ) በማህላቸው ወገን የሌለው ሆነ። ስለዚህ እነዚያ ናቁት፤ አባረሩትም። እንደዚሁ ይህቺ ቅድስት ሥርዓት በቅዱስ አቡነ አስጢፋኖስ በታች ባለው ብፁዕ እጅ ሆና እስከ ዛሬና እስከ ዘላለም ትመሠረት ዘንድ ለወንድሞቹ ማረፊያ እንዲሆን በተሰደደበት ሁሉ እግዚአብሔር ጥበብና ምክር ሰጠው።

እንግዲህ እንደ እውነት መልእክተኛው እንደ ሐዋርያ ጳውሎስ ቃል (እንዲህ) እንበል፤ "እንግዲህ ተመልከቱ ወንድሞቼ፥ በዚህ ዓለም የተናቁና ዘመዶች የሌላቸውን እግዚአብሔር መርጧቸዋል፤ እግርዚአብሔር ጠንካራዎቹን ያሳፍር ዘንድ የዚህን ዓለም ደካሞች መረጠ--በሥጋ ያለ ሁሉ (125ስ) በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ።"[30]

---

29. ዘፍ 37-45።

30. 1 ቆሮ 1፡ 26-29።

ሰላማዊ ኑሮና እድገት

በዚያ ምድረ በዳ (የገዳም) ማኅበር ማቋቋም በጀመሩበት ጊዜ የዓመተ ምሕረቱ ቍጥር ፹፩÷[31] ንጉሡም የመንግሥቱ ስሙ ገብረ መስቀል የሆነው ይሥሐቅ ነበረ::[32] ጳጳሱም እባ በርተሎሜዎስ ነበረ:: በዚያ ዓመት እልዘሩም፤ መሬቱን የሚያርሱበት ብረት አልነበራቸውም:: ብቻ ከሌሎች አርሻ እየሄዱ ይደክሙና ዋጋቸውን ይሰጧቸው ነበረ፤ ጊዜው የሰብል መሰብሰቢያ ጊዜ ነበረ:: (ክፍያውን) ሲያሳጉሉባቸው አያዝኑም፤ ለገዳማውያን የሚገባውንም ሁሉ ከዱር የዛፍ ፍራ ፍሬዎችና ስራስር ይሰበስቡ ነበረ:: (126^{ሀ}) አንደዚህ መልካሙ ፍሬ እንዱ ፴÷ ፵÷ ፻ ድርብ እስኪሆንላቸው የወንጌልን ማሳ አያረሱ በችግርና በትልቅ ጭንቅ ኖሩ::[33] ከዚያ÷ በሁለተኛው ዓመት መሬት አረሱ፤ ማሳውንም ዘሩ:: በጣም ሠመረላቸው:: እግዚአብሔር ጭንቃቸውን አይቶ የአጃቸውን ሥራ ሁሉ ባረከላቸው::

ከዚያ ደግሞ÷ በፊት ተባርረው እደብሯ አጠገብ የነበሩ ሌሎች ወንድሞች ወጥተው ወደነሱ መጡ:: እነሱንም ከነዚያ ወንድሞች አጠገብ እንዲኖሩ አዘዛቸው:: እነሱም እባ ናትናኤልና አብረውት የነበሩት ናቸው፤ ፪ ማኅደር ሆኑ::

ከዚህ በኋላ ደግሞ÷ አጠገቧ ካለው ደብር የሚኖሩ (ሌሎች) መጡ :: (126^{ለ}) እነሱንም ፫ ማኅደር[34] እደረጋቸው፤ ፭ ማኅደር ሆኑ:: ከዚያ አልፍ ብለው ይባራ ከሚሏት ከሌላ ቦታ ሰፈሩ:: ደግሞ ከዚያ÷ አንደገና ለቅቀው ማየ ጣፋት ከምትባል ቦታ ሰፈሩ:: እዚያ አትክልት ተከሉ፤ የአትክልት ቅጠላ ቅጠሎችን አበቀሉ፤ ለለመናቸው ሁሉ አስኪበቃ ድረስ በጣም ሠመረላቸው::

የቅዱሱን ዜና ሰምተው ፮ ማኅደር የሚሆኑ ብዙ ወንድሞች ከሌሎች አገሮች ተሰበሰቡ:: እነሱንም በየማኅደራቸው እንዲኖሩ አዘዛቸው፤ (በጠቅላላው) ፱፱ ማኅደር ሆኑ::

በዚያ ቦታ እንደዚህ እንዳሉ (127^{ሀ}) አንድ አበምኔት÷ "ደብሬን ውሰድ፤ እኔም በሥርዓትህ ስር ልሆን አፈልጋለሁ፤ ስለ እግዚአብሔር ብለህ እኔንም ቅበረኝ" ብሎ ወደ ቅዱሱ ላከበት:: ቅዱሱ ብፁዕ አበከረዙንን ከራሱ ማኅደር ሰዎች ጋራ ወደዚያ እንዲሄድ ላከው:: እንዳዘዘው ሄደና (ገዳሙን ተረከበ) አብረውት ከነበሩት ወንድሞች ጋራ (አዚያው) ቆየ:: ከዚያ በኋላ÷ ቅዱሱ ማኅበሩን÷ "አነሆ÷ ወንድሞቻችሁ አዚያ ብቻቸውን ይኖራሉ፤ አሁንም ከናንተ ሰው ላኩላቸው" አላቸው:: ፫ ማኅደሮች እንዲሄዱ÷ ፭ አዚሁ

---

31. 81 ዓመተ ስማዕታት ነው፤ ዓመተ ምሕረቱ 1421 መሆኑ ነው:: ባሕረ ሐሳብን ተመልከት፤ ጌታቸው ኃይሌ÷ *ባሕረ ሐሳብ*÷ ገጽ 181:: ዓመተ ሰማዕታትን ዓመተ ምሕረት ማለት በጥንት ስነዶች ዘንድ የተለመደ ነው::

32. 1406-1421:: ንጉሡ አፄ ይሥሐቅ የሞተው ገዳማቸውን ባቋቋሙበት ዘመን መሆኑ ነው::

33. ማር 4: 20::

34. "ማኅደር" እና "ማኅበር" ታናሽና ታላቅ ናቸው:: ብዙ ማኅደሮች አንድ ማኅበር ይወጣቸዋል:: አቡነ አስጢፋኖስ እንዴት አንደዚህ አንዳዘጋጇቸው በገድላቸው ተጽፏል::

እንዲቆዩ ዕጣ አወጡ። አነዚያ (ዕጣ የወጣላ/ባቸው) ፫ቱ ማኅደሮች ሂዱ፤ እዚያ ፬ (ማኅደር) ሆኑ። ቅዱሱም ሊጐበኛቸውና ሊያጽናናቸው ወደዚያ ወረደ። (127^ሀ) የጽድቅን ሥርዓት እያሳያቸውና ኑሯቸውን እየተረጐመላቸው ኖረ።

አባ አበክረዙን እልቅና ተመረጡ

ከዚያ በኋላ÷ (ቅዱሱ) "አንግዲህ ወደ ወንድሞቻችሁ መሄዴ ነው" አላቸው። ወንድሞች÷ "አንተ ከሄድህ አሁን አንተ እንደምታደርገው ባንተ ምትክ ለማኅበራችን ሥራ የሚገባውን ፍላጎታችንን ሁሉ የሚፈጽምልን ማንን እዚህ ትተውልናለህ?" አሉት። ቅዱሱ ለአገልግሎት የሚበቃ አንድ (ሰው) ከማህላችሁ ምረጡ" አላቸው። በዚህ ጊዜ ሁሉም ይኸንን ከመጀመሪያው ጀምሮ የማኅበር ሥርዓት ጀማሪ የሆነውን ብፁዕ አበክረዙንን መረጡ። ቅዱሱም እሱ እንዲሆን ተስማማ፤ ምክንያቱም መጀመሪያውኑም ለአገልግሎት እንደሚገባ ጠባዩን ቀደም ብሎ ያውቅ ነበረ። "እነሆ ወንድሞችህ ሁሉም (128^ሀ) አንተ አለቃቸው እንድትሆን ተስማምተዋል" አለው። (አቡነ አበክረዙን) ግን አልፈለገም ነበር፤ ብቻ ከዚያን ቀን ጀምሮ ለሁል ጊዜ የሚሆነውን ዐውቆ ያዘንና በመራሩ ያለቅስ ነበረ።

ከማኅደሩ ሰዎች ጋራ እየኖረ የማኅበሩን ሥራ ሁሉ ይፈጽም ነበረ። ሲጨርስ ከማኅደሩ ሰዎች ሥራ ይሄዳል። አንደዚህ አያደረገ ብዙ ጊዜ ኖረ። አንድ ጊዜ የማኅደሩ ሰዎች በሱ ምክንያት ተጣልተው ያሳለፉትን ፍርድ ከቅዱሱ አባታችን ዘንድ አመጡበት። ቅዱሱ ሰምቶ የሚገባውን ትክክለኛውን ፍርድ አስረዳቸው። ስለ አሱም (እንዲህ) አላቸው፤ "እንግዲህ ካሁን በኋላ ይኼ ከማኅደሩ ሰዎች ጋራ የሚኖር የማኅበር አለቃ (128^ሀ) ከዚያ ይውጣና በማኅበሩ ማህል ይኑር፤ በሁሉም ላይ አዛዥ ይሁን፤ ምግቡና ልብሱ ከማኅበሩ ዘንድ ይሁን።"

ከዚያ÷ እንደዚህ እንዳሉ÷ ደግሞ ባረካ ወደምትባል ወደ ሲሬ ዳርቻ ምድረ በዳ ሄዱ። ከ፪ቱ ገዳማት ፱ ማኅደሮች ውስጥ ፭ ማኅደሮችና ለየማኅበሩም ተላላኪዎቻቸው የሚሆኑ አዋጡ። እዚያ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚያሳርጉበት ቤተ ክርስቲያን ሠሩ። ሶስት ገዳሞች÷ ፲፭ ማኅደሮች ሆኑ። ቅዱሱም በምዕዳን መጽሐፎቹ ውስጥ ሁሉ እንዳለው÷ በዘርና በእርሻ ምሳሌ÷ በእህል ጎተራዎችም ምሳሌ እያደረገ ሊመክራቸው ይጐበኛቸው ነበረ።

ስይጣን ሞገድ አስነሣ

(129^ሀ) ከዚያ በኋላ÷ ብፁዕ አበክረዙን የሚያስተዳድራቸውን የቅዱሳኑን ገዳማት ለማወክ ስይጣን በአድባሮቹ መነኮሳት እጅ ሞገዶቹን አስነሣ። ወደ ሀገሩ ሹም ሂደው÷ "እነዚህን የተቀበልካቸው ተሳስተህ ነው ወይስ ከነሱ ግብር ትቀበላለህ? እንግዲህ በነሱ ምክንያት ጥፋት ቢመጣብህ

የምታደርገውን አንተ ዕወቅ" አሉት። የአገሩ ሹም ሲሰማ እንዲባረሩ አዘዘ፣ ከዚያ አባረሯቸው። በበረካ ምድረ በዳ ወዳሉት ወንድሞቻቸው ሄዱ።

ብፁዕ አበክረዙን በ፲ ማኅደር ላይ ተጠሪ ነበረ። የትግራይ ገዢ (129ᴬ) ቅዱሱን በውሸት እንደሚያሳብቁበት ዜናውን ስምቶ፥ "እነሆ፥ እንድትታረቅ እኔ ከንጉሡ ዘንድ ሰላም እደርግልሃለሁ።"[35] አሁንም ከኔ ጋራ የሚሄዱ፥ ቃልህን ለንጉሡ የሚያሰረዱ፥ ልጆችህ ይምጡ" ብሎ ላከበት። ቅዱሱ ሰምቶ ብፁዑን፥ "ና፥ ከአገረ ገዢው ጋራ ሂድ፤ ሰላም ሊያደርግ ይፈልጋል። ንጉሡ የሚልህ እውነት እንደሆነ ሰማው። ግን የታሰረ ነገር እንዳትፈታና ከእድልዎ እንዳትገባ ተጠንቀቅ" አለው። ትእዛዝ ተቀብሎ ሄደ።

አባ አበክረዙን ከንጉሡ ፊት--ዕርቅ አልተቻለም

አገረ ገዢው ሄዶ ከቅዱሱ ጋራ እንዲታረቅ ንጉሡን እነጋገረው። ንጉሡ ሰማና (130ᵁ) የአገረ ገዢውን ነገር አልተቀበለም፤ ከ(ቅዱሱ) ጋራ ሊታረቅም አልፈለገም። ብፁዕ አበክረዙን የአገረ ገዢው ነገር እንዳልሠመረ ሲያይ ከክቡር አባት ከአባ ገብርኤል የቅስና ሹመት ወስዶ ወደ ማኅበር ተመለሰ። በዚያን ጊዜ እድሜው ፵፫ ዓመት ነበረ። የሆነውን ሁሉና (ንጉሡ) የአገረ ገዢውን ነገር እንዳልተቀበለም ለቅዱሱ አሰረዳው። ቅዱሱ ሰምቶ "ምንቸገረህ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን፤ <u>ጽኑ ነቢይ ሲነግ እንደዚሁ ጽኑ ንጉሥ ያስነግል</u>"[36] አለ።

አባ እስጢፋኖስ ከንጉሡ ፊት

እንደዚህ በቅድስት ሥርዓት እያሉ፥ ንጉሡ ወደ ቅዱሱ እንዲህ ሲል መልእክት ላከ፥ "በሃይማኖት ጉዳይ እንድንነጋገር፥ ና።" ለአገሩ ሹም ደግሞ፥ (130ᴬ) "ይኸንን መነኮሴ አስገድደህ ላከው" አለው። አገረ ገዢው መጥቶ ያዘውና አሰረው።

ቅዱሱ ከ(ወንድሞች) እንደሚለይ ሲያውቅ በሱ ምትክ እረኛ እንዲሆን የመደበውን ይኸንን የማኅበር አለቃ እንዲህ አለው፥ "እነዚህ ሲበተኑ በልብህ እኔ ብቻዬን እኖራለሁ እንዳትል ዕወቅ። ልብ አድርግ፥ የእግዚአብሔር የበጎች መንጋ ሲበተኑ ዕዳ እንዳይሆንብህ ከነሱ (ተለይተህ) እንዳትሸሽ።" ስለ መታዘዝ እንዲህ አለው እንጂ እንደማያደርገው ያውቅ ነበር። ለወንድሞችም እንዲህ እላቸው፤ "እስከ ሞት ድረስ በክርስቶስ ትምህርት ጽኑ፤ በሥርዓታችሁ (አብራችሁ) ኑሩ እንጂ እትለያዩ። ወደ እግዚአብሔር ፊት ከሄድኩም እትዘኑ። ምክንያቱም (131ᵁ) እንደዚያ ቢሆን ይሻላችኋል። ከኔም በኋላ የሚያበረታታችሁን እግዚአብሔር እጹን

---

35. ስላንጋገሩ ከላይ ጎዳግ ቁ. 28ን ተመልከት።

36. ግዕዙ የሚለው "ያስነግሉ" ነው፤ ስሕተት ይመስለኛል። እግዚአብሔር፥ "እኔም የፈርዖንን ልብ እጸናዋለሁ" ካለው ጋራ ሲያነጻጽር ነው፤ ዘፀ 14፡ 4።

ያሳረፈበትን ይሰጣችኋል። ብቻ እመኑ፤ እትጠራጠሩ።" ወንድሞች ይኸንን ከቃሉ ሲሰሙ በጣም አዘኑ፤ እናት ከልጅ እንደምትለይ አምርረው አለቀሱ።

ብፁዕ አበክረዙን እንደ ቅዱሱ ቃል ለወንድሞቹ ምዕዳን እያሰማቸው ኖረ። እሱንም[37] በአሰራት ሲወስዱት ያጽናናቸውና የውጪና የውስጥ ፍላጎታቸውን ይፈጽምላቸው ነበረ። (ሥራው) ቡኀይልና ራስን በማግነን ሳይሆን ለብዙዎች አርአያ ሆኖ ፍርሃት ባለበት ትሕትና፥ በድኽነት፥ ለሰው ፊት ለትልቁም ለትንሹም ምንም ባለማዳላት፥ በልብ የዋህነት፥ በእውነትና በትክክል ነበረ። (131ʰ) የሚያስተዳድረውም፥ ትእዛዝ የሚቀበለው ችላ እንዳይል ቃሉን በማጠንከር ሳይሆን እያባበለ በማስረዳት ነበረ። ምክንያቱም በጴጥሮስ መንፈስ ይሄድ፥ በጳውሎስ ኃይል ያገለግል ነበረ። እሱ ራሱ በቃሉ፥ "ርጉሞች ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት ከኔ ሂዱ[38] ከሚለው ከጌታ ቃል በቀር ሰውን እንደማዘዝ የሚያስፈራኝ ሌላ ነገር የለም" ይል ነበረ።

በእፈሳ ከንጉሡ ፊት

ከዚያ፥ በ፲፰/፲፯ ዓመት ምሕረት፥[39] ማኅበሩን በአቋቋሙ በ፲፰/፲፯ ዓመት፥ ቅዱሱ ምላዞ በምትባል በስደቱ ቦታ እንዳለ፥ የንጉሡ መልእክተኛ በቅድስት ኤጲፋንያ (ጥምቀት) ዕለት ቅዱሱንና ልጆቹን ያዛቸውና ከንጉሡ ዘንድ ወሰዷቸው። ንጉሡ ደግሞ ወደ (ሌሎቹ) (132ᵘ) የቅዱሱ ልጆች እንዲህ ሲል ላከ፤ "የአባታችሁን ሥራ ከተዋችሁ እንዳላችሁ ኑሩ፤ እንደዚህ የማታደርጉ ከሆነ ከመሬቴ ውጡ።" በአንድ ቃል፥ "እኛ እንዳስተማረን እንሄዳለን እንጂ የአባታችንን ሥራ እንተውም" አሉት። መልእክተኛው ከየእድባራቸው እንዲያባርሯቸው፥ የድካማቸውን ፍሬ ሁሉ እንዲወስዱባቸው እዘዘ። በዚህ ጊዜ አቡነ አበክረዙን በወንድሞች ማህል ቆሞ በእምነት ቃል ሲያጽናናቸው እንዲህ አላቸው፤

> ወንድሞቻችን ቅዱሶች ሆይ፥ ስሙ፤ በነቢያት ዘመን የነበሩ፥ ቃላቸውንም ያመኑ፥ ከኋላቸውም የተከተሏቸው፥ ለነፍሳቸው መድኃኒት ያገኙ፥ በእውነት ብፁዓን ናቸው። ክርስቶስ በመጣበት ዘመንም የተገኙ፥ በሕይወት ስጪ ቃሉም ያመኑ፥ (132ʰ) የዘለዓለም ሕይወትን ያገኙ፥ ብፁዓን ናቸው። ደግሞ በሐዋርያት ዘመን የኖሩ፥ ስብከታቸውን የተቀበሉ፥ በቃላቸው ያመኑ፥ ከነሱ ጋራ በመንግሥተ ሰማያት ተካፋዮች የሆኑ፥ ብፁዓን ናቸው። በከሐዲ ንጉሦች ዘመን ስማዕት የሆኑ፥ ስለ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን አሳልፈው የሰጡ፥ ብፁዓን ናቸው። ደግሞ በዘመናቸው በእውነት መንገድ ሲጋደሉ የኖሩ፥ ለይጣንን ያሸነፉና ከኃጢአት የዳኑ መነኮሳትም ብፁዓን ናቸው። ለእኛም በዘመናችን እንደ ቀድሞ አባቶቻችን የሕይወት

37. "እሱንም" የሚለው አቡነ አስጢፋኖስን ይመስላል።

38. ማቴ 25፡ 41።

39. 1437/8 ዓ. ም.። የመጨረሻው ቁጥር 7 ይሁን ወይም 8 ግልጽ አይደለም።

መንገድ የሚመራንን ነቢይ እግዚአብሔር ሰላስነሣልንና ከሥቃዩ ተሳትፈን ከሱ ጋራ በርስቱ ክፍል እንዲኖረን ሰላደረገን ብፅዕና አለን።

(133^{ሀ}) ወንድሞች በክርስቶስ እምነት እንዲጸኑ፥ በልባቸው እንዳይጠራጠሩ፥ ሃይማኖታቸው እንዳይደክም ይሽንን አላቸው። ያን ጊዜ ዕለቱ ዓርብ ነበረ። ከገዳማቸው እባረሯቸው፤ ጌታ በወንጌል፥ "ከዚች ሀገር ሲሰዷችሁ ወደ ሁለተኛዋ ሺሹ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የእስራኤል ሀገሮች እይፈጸሙም"[40] እንዳለው ግፋቸውን ተሸክመው ወጡ። ከዚያ ወጥተው ሐምሌ በሚሏት ምድረ በዳ ጥቂት ጊዜ ተቀመጡ። በእንዲት ደብር ይኖሩ የነበሩ ሌሎችም ወንድሞች መጡ። እዚያ ከታቦታቸውና ከቅዱሳት እቃቸው ጋራ ተቀመጡ፤ ጊዜው ክረምት ነበረ።

ወደ ምሥራቅ ስደት

ወደ ሌላ ሀገር ለመሄድ አሰበው፥ ከሌላ ደብር ወዳሉ ወንድሞቻቸው (133^{ለ}) እንዲህ ሲሉ ላኩባቸው፤ "በፊት አባታችን መንገዳችንን ወደ ምሥራቅ እንድናደርግ እመልክቶን ነበረ፤ እሁንም ሁላችንም (የምናደርገውን) በምክር እንድ ሆነን እናድርግ። ማረፊያ (የሚሆነን ቦታ) ያገኙ እንደሁ እገር የሚሰልሉ ሰዎች (ወደ ምሥራቅ) እንላክ፤ አባታችን አደራ ያለንን ታቦቶችንም የንጉሡ ሎሌ እኛ ዘንድ እግኝቶ እንዳይቀማን ከሚጠበቁበት ቦታ እናስቀምጣቸው እንጂ አንጥላቸውም።"

መልእክተኞቹ ሂዱና ይሽንን ለወንድሞች አስሚቸው። እነሱም ሰምተው አንዳንዶቹ፥ "ይሽ መልካም ነው፤ እንደዚህ እናድርግ" አሉ። እንዳንዶቹ፥ "እይሆንም፥ መጀመሪያ አባታችን ያለበትን ለመፈለግ፥ ወደ ወሰዱት ቦታ ብንሄድ ይሻላል" አሉ። (መልእክተኞቹ) ተመልሰው (134^{ሀ}) ለወንድሞች ይሽንን ነገሯቸው።

አቡነ አበክረዙን እንደገና እንዲህ ሲል ላከባቸው፤ "ለማረፊያችን ቦታ እንፈልግ፤ ምክንያቱም ብዙዎች ደካማ ሽማግሌዎችና ሕፃናት አሉብን። ከዚያ በኋላ አባታችን ወዳለበት እንሄዳለን።" ሰምተው ጥቂቶች ወደነዚህ ወደላኩባቸው ወንድሞች (ወደነ አቡነ አበክረዙን) መጡ። አንዳንዶቹ ቅዱሱን የወሰዱበትን (ቦታ) ፍለጋ ሄዱ። አቡነ አበክረዙን መኖሪያ ቦታ ያገኙ እንደሆነ ሀገር የሚሰልሉ ብዙዎች ወንድሞች ላከ። ማረፊያና (መኖሪያ የሚሆን) ቦታ እግኝተው ተመለሱ።

ከዚያ ወጥተው ለመሄድ ተነሡ። ሙሴ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ሲወጡ ጉዟቸውን በእግዚአብሔር ቃል በየነገዳቸውና በየአባታቸው ቤት፥ በየሰፈራቸው እንዲያደርጉ እንዳዘዛቸው፥[41] ቅዱሱም የወንድሞች ማኅበርን (134^{ለ}) በመንገድ በየማኅደራቸው ሆነው እንዲጓዙ አዘዛቸው። እነሱም እንደዚሁ እንዳዘዛቸው አደረጉ። እንዲያርፉበት እግዚአብሔር ካዘጋጀላቸው

40. ማቴ 10: 23።
41. ዘኍ 1።

ቦታ አስኪደርስ ድረስ፥ የቀደሙትም የተከተሉትም በየእጣቸው ተጓዙ። ረድፋቸውን ይዘው ሂደው ከመጠራ አገር ሲደርሱ፥ በየማኅደራቸው ፫ ክፍል አበጁ። የተቀበሏቸውንም እገሮች ከ፫ ከፈሏቸውና በእጣ ተካፈሏቸው።[42] እንደዚህ ሁሉም በየክፍላቸው ኖሩ። አቡነ አበክረዙን ሁሉንም (135ᵇ) በተግሣጽ ቃልና በምዕዳን ለማጽናናት ሁል ጊዜ በተራ ይጐበኛቸው ነበረ። ደግሞ በፊት ከላኩባቸው ወንድሞች የተረፉት መጥተው በየማኅደራቸው ኖሩ።

ከዚያ በኋላ፥ አባታችን አባታቸውን እንዲፈልጉ ፮ ወንድሞች ላከ። ሂደው ካለበት ከአጠገቡ ደረሱ። ከማህላቸው የሚሰልሱ ፪ ሰዎች ላኩ። ሲደርሱ በሕይወት አገኙት። ግን መግቢያውን ሰላጡት ወደ ውስጥ አልገቡም፤ ብቻ ከውጭ ሆነው፥ "አባ ሆይ፥ ሰላም ላንተ ይሁን" አሉት። ቅዱሱ፥ "የእግዚአብሔር ሰላም ከናንተ ጋራ ይሁን" አላቸው።

አባታቸውን ሲፈልጉ ተያዙ

ይኸንን ሲል ዘበኞች መጡና ያዟቸው። ወደ ንጉሡ ወሰዷቸው። (ወስደው) ምን እንዳደረጓቸው በገድላቸው ሰማዕትነት ይገኛል። የቀሩት ፬ (135ᵃ) ወንድሞች አባታቸው ሰማዕትነቱን እንደፈጸመ እዚያው እንዳሉ ሰሙ። አብረውት ያሉትን (ያስጠጋቸውን?) ሰው ሂዶ ከሰው አርቆ ከዱር እንዲቀብረው፥ ከመግነዙ የተረፈውንም ጠበል እንዲሆናቸው እንዲያመጣላቸው ነገሩት።[43] ያ ዲያቆን የነበረ ሰው እንደዚያ አደረገ፤ ሂዶ ቅዱሱን ገንዞ ቀበረው። ከመግነዙ የተረፈውን ለወንድሞች ሰጣቸው።

እነዚያ ወንድሞች ወደ ማኅበሩ አለቃ ተመልሰው፥ ቅዱሱ በአሰራት ላይ እንዳለ የገድሉን ሰማዕትነት እንደፈጸመ ነገሩት። አቡነ አበክረዙንና አብረውት ያሉት ወንድሞች የቅዱሱን ፍጻሜ ሲሰሙ በነሱ ዘንድ ታላቅ ለቅሶ ሆነ። በጣም ብዙ ሰቆቃና ዋይታ አደረጉለት። ወንድሞች ብፁዑን፥ (136ᵇ) "አሁን የአባታችንን ሥጋ (በድብቅ) እናፍልሰውን? መቃብሩ ከሀገሩ ሰዎች ዞር ያለ ነው" አሉት። "አሁን ታገሡ፤ ጊዜው አልደረሰም። እሱም ቢሆን በሕይወት በነበረበት ጊዜ ሥጋዬን አትግለጡ፤ እዚህ እኛ ዘንድ አለ እያላችሁ ለማንም አታሳዩ፤ ሥጋችሁን ለመጥቀም ስትሉ እትሸጡት ብሏል። ግን ኑሯችንን እግዚአብሔር እንዲያሳምር ምህልላ (ጸሎት) አናድርግ" አላቸው።[44]

---

42. አገሩን የተካፈሉት ስማስተማርና ለዕለት ራታቸው እርዳታ ለማግኘት ይሆናል።

43. ጠበል "ጸበል" ከሚለው የግዕዝ ቃል ነው። ትርጒሙ "አባራ" ትቢያ ማለት ሲሆን ከጻድቃን አማር የሚወስድም ፈዋሽነት አለው ተብሎ ይያዛል። ጻድቃን የሚያመነጩት ምንጭ "ጠበል" የሚባለው፥ እዚህም ከመግነዙ የተረፈውንም ጨርቅ "ጠበል" የሚሉት ከጻድቃኑ የአማር ትቢያ ጋራ ባለው ምስጢር ነው።

44. "ምህልላ" ወይም "ምህላ" በሀገር ወይም በማኅበር ላይ እንደ ቸነፈር፥ እንደ ተስቦ፥ እንደ ድርቅ ያለ ችግር ሲደርስ አብሮ የሚጸለይ ጸሎት ነው። ቤተ ክርስቲያን ለዚህ የሚሆኑ ጸሎቶች አሏት፥ አንዱን የደረሰው አፄ ዘርአ ያዕቆብ ነው። ደቂቀ አስጢፋኖስ ግን የራሳቸውን የጸሎተ ምህላ ሥርዓት አውጥተው እንደነበረ ቀጥሎ ያለው ትእዛዝ ያመለክታል።

ምህልላ ያዙ

ወንድሞች በዚህ ምክር ተሰማሙ፤ "ጥሩ ነው፤ ይሁን" አሉ። እሱም እንዲህ እንዲያደርጉ ይሽንን አሳያቸው፤

> እያንዳንዱ በየራሱ ይለይና ለብቻው ይሁን፤ ከሌላው ጋራ አይነጋገር። ሁሉም በየራሱ ሆኖ ብቻውን ይጸልይ፤ የሚሆነውን (136^ለ) ለማወቅ ወደ እግዚአብሔር ያልቅሰ። በተለመደው የሰዓታት ጸሎት ጊዜ ግን በአንድ ቦታ ተሰብስበው ተጨናንቀው ይጸልዩ። ሰግደት ያብዙ። (የሰዓታቱ) ጸሎቱ ሲያልቅ እንደገና ሁሉም እያንዳንዱ ወደየቦታው ሄዶ ብቻውን ይጸልይ። ሰግደትም በየቀኑ ፯፻ ጊዜ ይሰገድ። ያለፈውንና የሚመጣውን ሁኔታቸውን እየገመገሙ በመልካም ጥረትና በጋለ ዕንባ መንፈሳዊ ትጋት ይትጉ። ስለ ምግባቸውም የእንዱን ቀን ለ፫ ቀን እንዲያደርጉት ነገራቸው።

የምህልላቸው ጊዜ መጨረሻ ድረስ እንደዚህ (አደረጉ)። ሌሎች ወንድሞችም ይሽንን በብዙ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ላከባቸው። (ይህንን ያደረጉት እግዚአብሔር) (137^ሀ) ከመቅደሱ ረድኤት እንዲልክላቸው እንጂ፥ (ሱባኤ ገብተዋል እየተባለላቸው) የዚህን ዓለም ጥቅም እንደሚፈልጉት አንደሌሎች (ለማድረግ) አይደለም። የሚፈልጉት የአባታቸውን ፈለግ መከተል፥ እንደሱም ከመሰቀል ላይ መውጣት፥ የሃይማኖታቸው ሰብከትም በምድር ሀገሮች ሁሉ እንድትጸና ነበር።

ወደ ሌሎች አገሮች ስደትና እሰራት

ከዚያ በኋላ፥ በዚያ ዓመት በየቦታቸው በመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ላሉ፥ እግዚአብሔር እንደገና ወዳልደረሱባቸው አገሮች እንዲበትናቸው፥ በዚያም ብዙ ነፍሶችን ወደ ሕግ ትምህርት እንዲሰበስቡ ፈለገ። አንድ ሰው ቅዱሳኑን ከንጉሡ ዘንድ በውሸት ነገር እንዲህ ሲል ከሰሳቸው፤ "እነሱ ካሉበት አመራለሁ፥ መምህራቸውም አበክረዙን ነው፤ እሱ ከቀድሞው አባታቸው የጸና እና የከፋ ነው።"

(137^ለ) ንጉሡ ይሽንን ሲሰማ በጣም ተቆጣ። ቁጣውን የሚያበርዱለት ወታደሮቹን ላከ። ያ አሳባቂም አብሯቸው ነበረ። ከትግራይ ገዢ ዘንድ ሄደው በግዛቱ ያሉትን ቅዱሳን እንዲይዛቸው የንጉሡን መልእክት ነገሩት። አገረ ገዢው (መልእክቱን) ሲሰማ ሄዶ ቅዱሳኑን ያዛቸው። አቡነ አበክረዙንንም አጥብቀው ፈልገውት ነበረ፤ ግን እግዚአብሔር ከእጃቸው ሰለሰወረው አላገኙትም።

በእርሻ ላይ ረኃብ

ከዚያ በኋላ፥ የተረፉት ወንድሞች፥ "ንጉሡ አንተንም ሊነጥቀን ስለሚፈልግ፥ ና ከዚህ ወደ ሌላ ሀገር ሂድና እስከ ጊዜው ተደበቅ" አሉት። ከወንድሞች አንዱን እስጢፋኖስ የሚባለውን ሰጡት። ከዚያ ለቀው ምድረ

(138ᵇ) ተምቤን ወደ መነኮሳት ገዳም ወደ ደብረ ሰማዕት መጡ። የገዳሙ ሰዎች ይሽንን አስጢፋኖስን በፊት ያውቁት ነበረ። የደብሩ ሰዎች እንዲህ አሉት፤ "አንተ በቤተ ክርስቲያ እንደ ባሕታዊ ተቀመጥ፤ ማንም አያውቅህም፤ ይሽ ጓደኛህ ግን ከውጪ በእርሻ ጥበቃ ይኑር።" ችግራቸውን ስለሚያውቁ እሺ አሏቸው።

ያ ወንድም በደብሩ ተቀመጠ፤ አቡነ ብፁዕ ወደ አርሻ ጥበቃ ሄደ። እዚያ ትንሽ ማደሪያ ለራሱ ሠራና እንደዚህ በትዕግሥትና በችግር ኖረ። አስጢፋኖስ ከደብሩ እየመጣ ይጐበኘው፥ ምግቡን ከአትክልት ግንድና ከሌላ ስራስር ያመጣለት ነበረ። አንዳንድ ቀን ከእህልም ጥቂት (138ᵃ) ቆሎ ወይም ንፍሮ (ያመጣለታል)። እንጀራ የሚያገኝበት ጊዜ ግን በጭንቅ ነበረ፤ ምክንያቱም (ዘመኑ) የችግር ዘመን ነበረ።

ታላቅ የውጪና የውስጥ ፈተና ይደርስበት ጀመረ። የውጪው ምግብና ልብስ በማጣት ሲሆን የውስጡ ከክፉ የሌሊት አጋንንት የሚመጣ (ፈተና) ነበረ። ስለ ሁሉም--ስለ ገዳሞቹም ስለተበተኑት ወንድሞቹም--ብዙ ሐሳብ ገባው። "የዓመቴ ቍጥሮች ስንት ናቸው? አካሌም በፊትህ እንደ ኢምንት ነው"፥[45] "አቤቱ ከፊትህም አትጣለኝ"[46] ይል ነበረ። ደግሞ፥ "ይቺ ፈተና አቡነ ቅዱስ ከሱ በተለየሁ ጊዜ፥ ሁሉም ቢተውህና ብቻህን ብትቀር አትፍራ፥ ያለኝ ትመስለኛለች" አለ። ስለዚህ የተሰፋውን ረድኤት እየጠበቀ (139ᵇ) በትዕግሥት ግንድ ተደገፈ። በዚህ ሁኔታ ብዙ ዘመን ኖረ።

ከዚህ በኋላ፥ ከደብር አንድ መታር የሚሉት መነኮሴ መጣ። አቡነ ቅዱስን አይቶ ዐወቀው። ለደብሩ ሰዎች፥ "ይህን ሰው ታውቁታላችሁን? የደቂቀ አስጢፋኖስ መምህር አይደለምን?" አላቸው። ሲሰሙ፥ "ሁኔታውን ሳናውቅ የእግዚአብሔርን ሰው እንደዚህ አደረግነውን?" ብለው አዘኑ። መነኮሴው ቅዱሱን ከዚያ ወስዶ ከወንድሞች ዘንድ አመጣው። እሱም ከማኅበር ተደባለቀ።

ሱባኤ

ከዚያ በኋላ፥ ቅዱሱ ወንድሞችን፥ "ምን ብናደርግ ይሻለናል? (139ᵃ) የአባታችንን መጨረሻና የወንድሞቻችንን መበታተን እናንተ ታውቃላችሁ። አሁንም ስጸሎት እንድዘጋጅ ፍቀዱልኝ፤ ማንኛውም በጸሎት ነው የሚደረገው። እግዚአብሔርም ያሰብናትን መንገዳችንን ያስተካክልልናል" አላቸው። ወንድሞች፥ "ደኅና ነው፤ እንዳልከው ይሁን" አሉት።

ከዚያ በኋላ፥ ሁለቱን ዲያቆናት ወንድሞች፥ አትናቴዎስንና በርተሎሚዎስን፥ ሰጡት። የ፫ ሰዓት መንገድ ወደ ዱር ሄዱ። ለየቀኑ የአንድ እንጀራ ሩብ ታስቦ ለ፵ ቀን የሚበቃ ምግብ ይዘዋል። እዚያ ሲደርሱ ቅዱሱ ብቻውን አንዲት ዋሻ ውስጥ ገባ። እነሱም እያንዳንዳቸው ለየብቻቸው

45. መዝ 38: 5።
46. መዝ 50: 11።

በመንፈሳዊ ትጋት (140ᵇ) በስብሐት ቃል ለራሳቸውና ለሌሎቹም የሚበቃ ልመና ቀንም ሌሊትም ይጸልዩ ጀመር። ያዕቆብ ወደ ግብጽ ሲሄድ፥ "ወደ ግብጽ መውረድን አትፍራ፤ እኔ ካንተ ጋራ ነኝና"[47] የሚል ድምፅ እስኪሰማ ድረስ እንደጸለየ፥ ነቢዩ ዳንኤልም መልአኩ፥ "ጥበብን አንዳስረዳህ መጥቻለሁ፤ የፍሊጋ ሰው ስለሆንክ ልነግርህ መጥቻለሁ። ነገርክን ልብ በል፤ ያየኸውን አስተውል"[48] የሚል የመልአክ ቃል እስኪሰማ ድረስ፥ ዕዝራም፥ ስለ ሕዝቡ መጋዝ በምድረ በዳ እንደጸለየ፥[49] እንደዚሁ ቅዱሱ አባታችን ስለራሱና ስለ ወንድሞቹ ጸለየ፥ ለመነም። እነዚያ ወንድሞችም ሁል ጊዜ፥ "አቤቱ (140ᵃ) ምሕረትህን አሳየን፤ አምላካችን ማዳንክን ስጠን"[50] እያሉ ለምህልላ የተወሰነው ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ በዚህ ዓይነት ጸሎት ኖሩ። ይኸም ቅዱስ አባታችን ለሱና ለነዚያ ወንድሞች የሚበቃ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ አግኝቶ፥ "ብዙ የጸጋ ሀብት አገኙ" ብሎ መሰከረ።

የብፅዕ ዘመናቸውን[51] ፈጽመው በደስታ ወደ ማኅበራቸው ተመለሱ። ከገዳሙ ሲመለሱ ከማኅበር ፊት ቆሙና ቅዱሱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤

> አሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ ወደ ዱር የወጣነው ከዚች የምትሻል ሌላ ሥርዓት ለማግኘት አይደለም። ከዚች ማኅበር ጽድቅ የምትበልጥ ጽድቅንም ለማየት አይደለም፤ ስለ ወንድሞች መበተን ጥቂት ጸሎት አንድንይዝ ነው አንጂ፤ በፊትም (141ᵇ) አባታችን ወደ ዱር የወጣ ጊዜ ሲመለስ፥ ለወንድሞች፥ "ይኸንን አኔ መንፈስ ቅዱስ ባሳየኝ አደረግሁት፤ አንደዚህ አደርጋለሁ የሚል ካለ ራሱን ይወቅ" ብሏቸው ነበር። እኛም ይኸንን ያደረግነው ቃሉን ጥሰን ላይሆን በናንተ መስማማት ነው።[52]

በየሀገሩ ያሉ አስረኞችን ጉብኝት

ከዚያ በኋላ፥ ቅዱሱ ለወንድሞች ማኅበር እንዲህ አላቸው፤ "የታሰሩትን ወንድሞቻችንን ለመጐብኘት፥ ወደ ተበተኑት ዘንድም (ለመሄድ) አፈልጋለሁ። ወንድሞች ሆይ፥ መጽሐፍ ሰዎች ሊሠሩላችሁ እንደምትፈልጉት እናንተም አድርጉላቸው[53] የሚለውን ራሳችሁ ታውቃላችሁ። ደግሞ፥ ሁላችሁም የእግዚአብሔርን ፍላጎት እንደወሰዳችሁ እንደ ደግ አገልጋይ አገልግሉ[54] ብሏል።"

---

47. ዘፍ 46: 3።
48. ዳን 9: 22-23።
49. 2 ዕዝ 9: 1።
50. መዝ 84: 8።
51. ለብፅዓት፥ ለብቃት ያደረሰ ምህልላ።
52. ከማኅበር ተለይተው ምህልላ ስለያዙ ሌሎቹ ቅር ያላቸው ይመስላል።
53. ማቴ 7: 12።
54. ማቴ 25: 21-24፤ ሉቃ 19: 16-17 ይሆናል።

ወንድሞችም፥ "መልካም ነው፤ እንዳልከው ይሁን" አሉት። (141ᴬ) በመስቀል እስከተሰየው ድረስ ሁል ጊዜ ረዳቱ የሆነውን ቀሲስ ስምዖንንና ገብረ ክርስቶስ የሚባለውን ሌላውን ወንድም፥ 2ቱን ወንድሞች ስጡት። "እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ መልአኩን በፊታችሁ ይላክላችሁ፤ ወደምትሄዱበት ሁሉ መንገዳችሁን ያቅናላችሁ። ከጠላት ተቃውሞ ያድናችሁ፤ አሜን" አሏቸው።

ከዚያ፥ ተነሥተው ሄዱ። ቤተ ማርያ ከሚሏት አገር ኬላ ሲደርሱ አብረውት የነበሩ ወንድሞች እንዲህ የሚል የአሳቻ ጋኔን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤ "እነሆ ካልደረስበት ሊደርስ ወጥቷል።" እነሱም፥ "ይህ የምንሰማው ድምፅ ስለኛ ነው ወይስ ስለ ሌላ?" አሉት። (142ᴮ) ቅዱሱ፥ "እናንተ ዝም በሉ" አላቸው። የጩኸቱ ድምፅ እንደገና እያከታተለ እንደዚሁ እያለ ደጋገመ።

ወንድሞች፥ "ይኸ ጩኸት ስለ እኛ እንደሆነ ምን እናድርግ? አባ ሆይ፥ እንደበቅምን?" አሉት። እሱ ግን የስይጣን ፈተና እንደሆነ ዐውቋል። "እናንተ ዝም በሉ፤ መንገዳችንን እንተውም። ምንም የሚታይ ነገር የለም" አላቸው። ወንድሞችም ለመሄድ ቃሉን አመኑ። የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ እየተከተለቻቸው ሁሉም ከፊለገው አስኪሄድ ድረስ ምንም እልነካቸውም። ነቢዩ ሙሴ በምድረ በዳ በተገለጸለት እግዚአብሔር ቃል መሠረት ወንድሞቹን ሊጎበኛቸው ወደ ግብጽ በሄደ ጊዜ መንገድ ሄዶ ከሚያድርበት ሲደርስ (142ᴬ) የቅናት መንፈስ የሆነ መልአክ ሊገድለው ቢፈልግ እግዚአብሔር አልፈቀደለትም ነበር፤[55] እንደዚሁ ይህ አባታችንም የተበተኑትን ካንድነት ለመሰብሰብ ያደረገው ሂደት በእግዚአብሔር ቃል ነበረ። ምክንያቱም አገልጋዩ ሐዋርያ እንዳለው፥ እሱ ከእግዚአብሔር አብ ልጅ የተወለደ የትንቢት ውጤት ነው።[56] ምክንያቱም፥ "እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይሠራል፤ የእስራኤልን መበተን ይሰበስባል፤ ልበ ቁስሎችንም ይፈውሳል፤ ቍስላቸውን ያክማቸዋል"[57] ያለው የነቢዩ የትንቢት መዓዛ በላዩ አርፏል።

እንደዚሁ በዚች የጉዞ ሂደቱ የተፈጥሮ የሥጋ የንክኪት በሽታ ያለበት ሰው ባለ መድኃኒት ሲያገኝ ከሕመሙ እንደሚድንና (143ᴮ) ከበሽታው እንደሚላቀቅ ብዙዎች ከቀሰላቸው ድነዋል። ስይጣን በራሱ ምክር ለሚሄድ ሰው በሚያጣፍጣት የነፍስ በሽታ በሆነች በሥጋ ፍላጎት ይታወኩ የነበሩ ብዙዎች ወንድሞች ሲያገኙት ተደሰቱ።

በዚህ ሁኔታ ጉዟቸው፥ አባ በርተሎሜዎስና አባ አቡናፍር በስደታቸው ታስረው ካሉባት ድሮር ከምትባል ከኤፋት ምድር ደረሱ። (ከነሱ ጋራ) እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ስለሆነውና ስለሚሆነው ሁሉ ተጫወቱ። ከዚያ በኋላ፥ በዚያ ብዙ ጽኑ ኬላዎች ባሉባት በሰዝ መንገድ ላይ በሚገኘው የደብረ ሩራን ዐቀበት ወደሆነው ወደ አርሶ ቁልቁለት፥ ወደ ሰርማት መንገድ አለፉ፤ ከሰም ከምትባል ወንዝ ደረሱ። (143ᴬ) ታላላቅና ጎይለኞች

55. ዘፀ 4: 24።
56. 1 ጢሞ 1: 18(?)።
57. መዝ 146: 2።

የሀገሩ መኳንንት ከተከማቹባት÷ የአለቆች ማኘኪያ ከሆነች ጕንጽ ከምትባል ከመንደሮቹ እንዲ ዘንድ ገቡ።[58] በውስጧ እባ ተወልደ መድኅንን እብረውት ከነበሩት ወንድሞች ጋራ እገኘው።[59] ስለሆነው ሁሉ ተጫወቱ፤ በፊት አንደላከባቸውና በማኅበሩ ውሳኔ እሰረኞች ለመጐብኘት÷ የተበተኑትንም ለመሰብሰብ እንደመጣ (ነገረው)። እሱም÷ "መምጣትህ ጥሩ ነው፤ አግዚአብሔር መንገድህን ያሳምርልህ" እለው።

ተባርከው ከዚያ÷ የአቡነ እስጢፋኖስን ሥጋ ወደ አቃጠሉባት እግበራ ወደሚሏት አገር ሄዱ። ዐፅሙን አውጥተው (በድብቅ) ከሚጠበቅባት እኖሩት። ከዚያ÷ (144[ሠ]) ወንድሞች በእረሚ እጅ ታስረው ወደተበተኑበት ሄደ። ከጋሳ ሀገር ሲደርስ ስበሰባቸውና÷ "ሰላም ለናንተ ይሁን" እላቸው። እነሱም÷ ሰላም መለሱለት። ለአግዚአብሔር አብረው ሰገዱ። እጅ ነሥተውት÷ ልጅ እናቱን ሲያገኝ እንደሚደሰት ታላቅ ደስታ ተደሰቱ። (ልጅ የናቱን) ፊት ሳያይ ቆይቶ ሲያገኛት በጣም ይደሰታል። እሷም የጡቷን ወተት ትመግበዋለች። እነሱም በአረሚ እጅ ሐዘንተኞችና የተከዙ ሆነው ኖረው ነበረ። ሲያዩት በጣም ተደሰቱ።

ከዚያ÷ ቅዱሱ÷ "በዚች በእረሚ ሀገር ኑሯችሁ እንዴት ነው?" እላቸው። እነሱም ኑሯቸውን ሁሉ ነገሩት። ቅዱሱ÷ "እዚህ መኖር እይስማማችሁም፤ (144[ሰ]) ወደ ክርስቲያኑ ምድር ውጡ። ብትኖሩም ብትሞቱም እዚያ ይሻላችኋል" እላቸው። እነሱም÷ "አባ ሆይ÷ አንተ እንደምትለው ጥሩ ነው። በፊቱንም ቢሆን (እዚህ) ያለነው ፈቃድ ስላላገኘን ነው። እንግዲህስ የሚያስተክዘን ነገር አይኖርም፤ እንዳልከን ይሁን" አሉት።

ቅዱሱ÷ "እኛም እኮ የመጣነው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በፈቃዳችን አይደለም። አሁንም ውጡ፤ አትጠራጠሩ። የእግዚእብሔርን ቃል ብትሰሙ ይሻላል" እላቸው። በተግሣጽ አያጽናና ስለ ሁሉም ነገር ምዕዳን አሰማቸው፤ የምታስረዳ መንፈሳዊት የንጽሕና ምግብ ሰጣቸው።

ከዚያ ደግሞ÷ በጓትር በአስራት ላይ ወዳሉት ወደ ሌሎቹ ወንድሞች ሄዱ። ለነሱም (145[ሀ]) ለወንድሞቻቸው እንደነገራቸው ነገራቸው። እነሱም÷ "ጥሩ ነው÷ አባት ሆይ÷ በቃልህ ረድኤት ለሰጠን ለእግዚአብሔር ስብሐት ይሁን" አሉት። ከዚያ÷ እያንዳንዳቸው ወንድሞች በእስራት

---

58. አንደ ዓለም በቃኝ ሆኖ የፖለቲካ አስረኞች የሚታሳሩበት በገደል የተከበበ ጠባብና ጎድጓዳ ቦታ መሆን አለበት። በገድለ አቡነ አስጢፋኖስና በአፄ በአደ ማርያም ታሪክ ውስጥም ተነሥቷል። "ጕንጽ" የሚለው የቦታዋ ስም ትርጕሙም "ጉንጭ" ማለት ነው። ይኸም "ማኘኪያ" ከሚለው ጋራ ይሄዳል። የአስር ቤቱ ስም "ቤተ መዛግብት" እንደሆነ በገድለ አቡነ አስጢፋኖስ እና በገድለ አቡነ ዕዝራ ውስጥ ተነግሯል።

59. አቡነ ተክለ ሐዋርያትም አፄ ዘርአ ያዕቆብ ደጃፍ በግልቢያ ጨዋታ ደኝ በፈረስ አየተረገጠ ሲሞት አይተው ቢቆጡት የተቀባ ንጉሥ እንዴት ትደፍራለህ ብሎ አዚሁ ቦታ "ምንድቅ" ("ጉድጓድ") ውስጥ አስሯቸው ነበረ፤ Getatchew Haile, "Martyrdom of Abunä Täklä Ḫawarəyat of Shoa and the Translation of His Relics," *Etiopia e Oltre Studi in onore di Lanfranco Ricci* (ed. Yacob Beyene et al), Naples (1994), p. 99.

ወደተበተኑበት ወደየቀበሌው ሄደ፤ በየሀገሩ ተመላለሰ። ጐበኛቸው፤ እጅ ነሣቸው። ስለ ማንኛውም መከራቸው፤ ልባቸውን ከመንገዳገድ መለሰው፤ የእርዳታ ምርኩዝ ሰጣቸው፤ ከመስቀል ላይ ለመውጣት እንዲችሉ በእምነት አጸናቸው።

ሱባኤ

ከዚያ፥ በነሱ ተባርኮ ሽማግሌው በርተሎሜዎስ ታስሮ ወዳለበት ወደ ሳጉራ ሀገር ተመለሰ። የሠራውን ሁሉ ነገረው። እሱም በሚገባ የበረከት ቃል ባረከው። ቅዱሱ፥ "ወደዚህ ልመጣ ስል (145^ለ) እንተ ዘንድ በደኅና እንዲያደርሰኝ፥ ስለ እስረኞች ወንድሞች ያሰብኩትንም ሁሉ እንዲያስፈጽመኝ በማኅበሩ ምክር ልዩ ጸሎት እድርጌ ነበረ። እግዚአብሔር ደጉን ሁሉ ሠራልኝ፤ ምንም ክፉ ነገር አላደረሰብኝም። አሁንም አንተ ዘንድ ላደርገው እፈልጋለሁ" አለው። ወደ ዱር ሄዶ እንዲጸልይ ሽማግሌው ፈቀደለት።

ካጠገባቸው ራቅ ካለ ቦታ ማደሪያ ሠሩለት። እዚያ የ፵ ቀን ጾም ምህልላ አደረገ፤ አምስት ቀን እህል ውሐ ፈጽሞ በመተው ይጾምና በሰንበቶቹ ቀን ጾም እንዳይሆንበት ትንሽ ውሐና ቅጠል ይቀምሳል።[60]

በዚህ ጊዜ የሰይጣን ፈተና መጣበት፤ ፈርቶ (ምህልላውን ይተው) እንደሁ ወይም ይበረታበት እንደሁ ሁል ጊዜ ሊሰልለው፥ በጦርነት ላይ እንዳለ (146^ሀ) ብዙ ሠራዊት ድምፅ የሚያስፈሩ ክፉ አጋንንት ላከበት። ከሱ ጋራ በግላጭ ሲተያዩ ይደነግጡና ይሸሻሉ። በላዩ ላይ ያለው የእግዚአብሔር ብርሃን ያበናቸዋል። "ሰይፍህን በጠላትህ እጅ ላይ (እውርድበት)"[61] ተብሎ በነቢዩ ምስክራ እንደተጻፈው፥ የክንዱ የማማተብ ምልክትም ያባርራቸዋል። ነፍሱን ሊያሸብሯት፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ እንደገና ዝምቦች በበክት ላይ እንደሚያደርጉት ግር ብለው ይሰበሰባሉ። ግን በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ስለሚጠበቅ ሊነኩት ሥልጣን አልነበራቸውም። ብፁዕ አስጢፋኖስ፥ "እግዚአብሔር እጁን ያሳረፈበት ሰው (146^ለ) ይሰጣችኋል" ያለው ቃሉ እንዲፈጸም እስከ ዕለተ ሞቱ የክፉዎች ሰዎች እጅም ሆነ የእርኩሶች አጋንንት እጅ በክፉ ነገር አልነካውም። "በእግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነ በቀር በኔ ላይ ክፉ ልታደርግ እንደማትችል አውቃለሁ፤ እኔ ግን ስለ ስሙ በሞት ጥላ መካከልም ብሄድ ክፉ ነገርን አልፈራውም"[62] እስኪለው ድረስ ለማስፈራት በግላጭ ይመጣበታል።

እንደዚህ ሁል ጊዜ ይጐበኘዋል፤ ግን ለዘመቻ እንደተዘጋጀ ሰው በጦር መሣሪያ ተዘጋጅቶ ያገኘዋል። እጠገቡ ያሉት ወንድሞችም በሂዱ ቁጥር፥ "ይኸ ሌሊት ሌሊት እንደ ብዙ (ሰው) ድምፅ የምንሰማው ምንድን ነው? ወደዚህ ስንመጣ ደግሞ ምንም እናገኝ" ይሉታል። ቅዱሱ፥ "ስለዚህስ

60. የሰንበቶቹ ቀን የሚለው ቅዳሜና እሑድን ነው። ቅዳሜና እሑድ እንዳይጸሙ *መጽሐፈ ሊኖዶስ* ይከለክላል።

61. መዝ 16፡ 13።

62. መዝ 22፡ 4።

ምንም የሚሆን ነገር የለም፤ በሉ ሂዱ" ይላቸዋል። ግን አጋንንት እንደሆኑና ያለ ጌታ ፈቃድ እንደማይችሉት ያውቃል።

(147ᵁ) ሰይጣን ሊገድለው ሁል ጊዜ ስለሚፈልግ፥ የፃው ፍጻሜ ሊቀርብ በታላቅ ዓውሎ ነፋስ (እስመስሉ) የጋኔን ጎይል አመጣና ማደሪያውን እፍርሶ በላዩ ደረመሰበት። ካሁን በፊትም በእቡነ ቅዱስ እንጦንስ ላይ በጎልማሳ ሰው አምሳል ቤቱን በመቄፈር እንዳደረገው[63] ደግሞ የላይ ላይ ግብጽ ህገር በእርሳይመትረይድስ ቅዱስ ሲኖዳ ላይ ቤተ ክርስቲያኑን በድልቅልቅና በዓውሎ ነፋስ ሊደመስስ እንዳደረገው፥[64] ክቅዱሳን ጋራ መጋደል ልማዱ ነው። ግን የእግዚአብሔር መልአክ አባረረውና ቤተ ክርስቲያኑን ስሯን ፰ ክንድ ከመሬት በታች በማድረግ መሠረቷን አጸናው። እንደዚሁ ቅዱስ እቡነ አበክረዙንንም በሌሊትና በቀን በድብቅና በግላጭ (147ᴬ) በማስፈራራት በብዙ ፈተና ተጋደለው። በዚህ ሁሉ አቅም ሲያጣ ተቆጥቶ፥ በዚያ የሚሞት መስሎት የትልቅ ዓውሎ ነፋስ ኃይል አመጣበትና ማደሪያውን በላዩ ላይ ደረመሰበት። ግን የእግዚአብሔር እጅ ይጠብቀው ስለነበረ ሊነካው በነፍሱ ላይ ሥልጣን አልነበረውም። ስለዚህ አፍሮ ሄደ፤ ኃይሉ የዛለ፥ የተወጋ፥ በሞት የቈሰለ ነውና።

ሆኖም ስለሱ፥ "ለሞቱ የሆነውም ቁስል ዳነ፤ ምድር በመላዋ እደነቀችው"[65] እንደተባለ፥ የሱ በሆኑ ዘንድ ሕያው የመሆን ሥልጣን አለው። ሁለተኛም ስለሱ፥ "ይህ ያየኸው እውሬ አለ፤ የለምም"[66] ይላል። እንደዚህ የሚኖረው የሱ በሆኑት ዘንድ ነው። ምክንያቱም በአሕዛብ፥ (148ᵁ) በሕዝብ፥ በነገድ፥ በህገሮች ላይ ሥልጣን ተሰጥቶታል። በምድር በሚኖሩ፥ በሰገዱለት፥ ስማቸው በበጉ መጽሐፈ ሕይወት ባልተጻፈው ዘንድ ሥልጣን ተሰጥቶታል። የክርስቶስ በሆኑት ዘንደ ስላለመኖሩ እንዲህ ይላል፤ "ለአውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱ፥ ምልክቱንም በግምባራቸውና በእጃቸው ላይ ያልጻፉ፥ እነሱ ይኖራሉ፤ ከክርስቶስ ጋራም እንድ ሺህ ዓመት ይነግሣሉ። ሌሎች ሙቶች ግን አይነሡም።"[67]

ይህ ቅዱስ ግን በፊት በጻድቃንና በቅዱሳን ላይ ያደርጋት የነበረችውን የተንኮሉን ምስጢር ስለሚያውቅ፥ ሥልጣኑን "ምድር በመላዋ እንዳደነቀችው" አያደንቅም። ምክንያቱም በኢዮብ ላይ በሕመም፥[68] በሙሴ ላይ በመንገድ፥[69] በጴጥሮስ ላይ በባሕር ላይ[70] በጊዮርጊስ ላይ በመንገን

---

63. ምንጩ ገድለ እንጦንስ ይሆናል።
64. ከታተመው ገድል ውስጥ የለም፤ Gérard Colin, *La Version Éthiopienne de la Vie de Schenoudi, CSCO*, vol. 444/75 (1982), p. 68? "እርሳይመትረይድስ" በግሪክና በቅብጥ ቋንቋ "እበምኔት" ማለት ነው።
65. ራእ 13: 3።
66. ራእ 17: 8።
67. ራእ 20: 4-5። ራእይ ውስጥ "በግ" የሚለው ክርስቶስን ነው።
68. ኢዮ ።
69. ዘፀ 4: 24።
70. ማቴ 14: 28-33 ውስጥ ያለውን ሊጠቅስ ይሆናል።

ፈት÷[71] በእንጦንስ ላይ (148ᴬ) በጎልማሳ ስው ምስል÷[72] በሌሎቹም ቅዱሳን ላይ በተለያየ ፈተና÷ በኛም ዘመን በአቡነ ቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ በዘንዶና በአራዊት አምሳል÷ በሱ ዘንድ ደግሞ ወንድሞች አስኪስሙት ድረስ እንደሚናድ የቋጥኝ ድንጋይ በትልቅ ዓውሎ ነፋስ አምሳል (ተንኮል እንደሠራ ያውቃል)። ያ ስይጣን በጻድቃን ላይ ሥልጣን እንደሌለው በታጋዳዮች ዘንድ እንደሚዋረድ÷ ቄስሉ እንደሚሄድ ስለሚያውቅ ተሸንፎ ሄደ። በአሸነፋቸው ዘንድ ግን ሕይወት ያገኛል።

ከዚህ ጊዜ በኋላ÷ ወንድሞች ወደሱ ሲመጡ ማደሪያውን ከላዩ ላይ ደርምሰበት አገኙት። ያለበት እንኳን አይታይም ነበረ። የሞተ መስሏቸው በጣም ደነገጡ። ከዚያ ሲያወጡት ሕያው ሆኖ አገኙት። ወደ ማደሪያቸው አመጡት።

(149ᵁ) በዚህ ትጋትና ጽሙና ብዛት ምክንያት ከጭንቅላቱ ትል እስኪወጣ ድረስ የሁል ጊዜ በሽታ አደረበት። ይህች በሽታ እስከ ዕለተ ሞቱ በራሱ ላይ ነበረች። ለጌታ አገልጋይ÷ "አጋዬ ይበቃሃል፤ ጎይል በበሽታ ያልቃል"[73] እንዳለው÷ እሱም ትጋትና ጽሙና ሳያቆም ሁል ቀን ይጋደል ነበረ።

ብቃት

ከዚህ በኋላ÷ ወደ ነፃነት የምትስብ አምላካዊት ጸጋ አረፈችበት፤ ምስጢሮቿንም አሳየችው። የሚሆነውንም ከመሆኑ በፊት ትገልጽለት ጀመር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አረጋዊ መንፈሳዊ[74] እስኪሆን ድረስ ከከፍተኛው ደረጃ አወጣችው። በነጋ በጠባ ቊጥር በጎይሏ ይታደስ÷ ብዙዎች ነፍሶችን በጥበቧ ለመስብሰብ እስኪችል ድረስ ከጎይል ወደ ጎይል ይሻገር ነበር።

በብዙ አገሮች በኩል ወደ ትግራይ መልስ

(149ᴬ) ከጥቂት ጊዜ በኋላ÷ ከዚያ÷ ወደ ትግራይ ሀገር ለመሄድ ተነሣ። የፊተኞቹንም የኋለኞቹንም ወንድሞች ለሄደታቸው ሥርዓት አበጀላቸው። ለአስረኞችም የሚላላኳቸውን ተወላቸው። አቡነ ይሥሐቅንና ሌሎቹን ወንድሞች ይዟቸው ሄደ። መነኮሲቶቹንም በሥርዓታቸው እንዲኖሩ አዘዛቸው።

---

71. ገድለ ጊዮርጊስ÷ Wallis Budge, *George of Lydda*, London 1930, p. 82.
72. *ገድለ እንጦንስ*
73. 2 ቆሮ 12: 9።
74. "አረጋዊ መንፈሳዊ" ("መንፈሳዊ ሽማግሌ") ዮሐንስ ሳባ የሚባለው ከሶስቱ መጻሕፍተ መነኮሳት አንዱን የጻፈ መነኮሴ ስም ነው፤ ማንም መንፈሳዊ ሽማግሌ ሊጠራበት ይችላል።

በሚጓዙበት ጊዜ ምድረ ዜጋ ከምትባል ሀገር ደረሱ። ቅዱሱ እዚያ ያሉትን የሃይማኖት ቃል አስተማራቸው። በቅድስት ሥላሴ አምነትንም ነገራቸው። ወደዚች ሥርዓት ብዙዎች ተጨመሩ። ከዚያ አልፈው ምድረ ገኒ ደረሱ። (እዚያም) የእግዚአብሔርን ቃል ሰበከ፤ የሕግንም ሥርዓትና የሐዋርያትን ትእዛዝ አስረዳቸው። (150^{ዐ}) ከነሱም ብዙ ወንዶችና ሴቶች ወደ ምንኵስና ገቡ። ከዚያ÷ ወደ ምድረ ላከማ ሄዱ። (እዚያም) እንደዚሁ አስተማራቸው፤ ደጎቻቸው ወጥተው ፈለጉን እስኪከተሉ ድረስ የሕይወትን መንገድ አሳያቸው።

በዚህ ሁኔታ እየተጓዙ ምድረ ትግራይ መካኖቻቸው ደረሱ። ወንድሞችን በስደት ምክንያት በተበተኑበት አገኟቸው። የቅዱሱን መምጣት በሰሙ ጊዜ ብዙዎች ከተበተኑበት ተሰባሰቡ። ከዚያች አገሮች አንዲ በሆነችው በውታፋ ምድረ በዳ ቤተ ክርስቲያን አቆመላቸው። በሥሩ ኤጲስ ቆጶስ በያዕቆብ መልእክት እንደተጻፈው የምንኩስና ፍጻሜ አደረገላቸው።[75]

ሰይጣን ተነሥቶ የአጋንንቱን ሽብር አስነሣ

በዚያ ዓመት (150^{ሰ}) ሰይጣን ተነሥቶ የአጋንንቱን ሽብር አስነሣ፤ አድባራቱን አሸበራቸው። ወደ ንጉሡ ዘንድ ሄደው÷ "የአስጢፋኖስ ስም ውዳሴው በመንግሥትህ ምድር ሁሉ ሞላ፤ ከሕዝብህ ታላላቆቹንም ያመነኵሱ ጀመር። ላንተ ለጌታችን ለንጉሡ እንዳይታዘዙ ብዙዎችን ወደ ክህደት ትምህርታቸው መልሰዋቸዋል" ብለው እንዲያሳብቁ በብዙዎች ልብ ውስጥ የተንኮል ምክር ጨመረ።

ንጉሡ÷ "ያዟቸውና ወደኔ አምጧቸው" አለ። ከቅዱሳኑ ታላላቆቹን ሰበሰቧቸው። እንደለመደውም ተሟገታቸው። እሺ ማለኝት ሲያቅተው ቅፍርያ ወደምትባል ደብር (ተራራ) እንዲሰደዱ አዘዘ። በትግራይ ባሉት መካኖቻቸው ዘንድ ያሉትንም (151^{ዐ}) እየያዙ ወደዚያ ደብር ወሰዷቸው። ቅዱሱን አባታችንን ግን አላገኙትም። ከዚያ ዓመት (ስደት) የተረፉ ሌሎችም ብዙዎች ነበሩ። ጸጥታ ሆኖላቸው በቻቱ ገዳሞቻቸውና ሌሎቹ ወንድሞቻቸው በታሰሩበት በደብረ ቅፍርያም በዘህ ቅዱስ አባታችን የምዕዳን ቃል እየወጡና እየተመለሱ በጥሩ ሁኔታ ኖሩ። እየተመላለሱ በብዙዎች ቀበሌዎችና መንደሮች አስተማሩ። ብዙ ነፍሶችን ለምንኵስና አበቁ። ግማሾቹም በሲኖዶስ ሕግ መሠረት በምእመናን ሥርዓት (በትዳር) ኖሩ። እሱም በየቦታቸው ይጐበኛቸው ነበረ።

የመነኮሲቶቹ ጥያቄ መልስ አገኘ

ከዕለታት አንድ ቀን÷ በየገዳሞቻቸው ያሉ መነኮሲቶች (151^{ሰ}) ቅዱሱን አባታችንን÷ "አባ ሆይ÷ እንደዚህ ሆኖ ኑሯችን እንዴት ነው? ጥሪያችንስ እንዴት ነው?" አሉት። ቅዱሱ÷ "አትፍሩ÷ አትጠራጠሩም። ምሕረት ያወርድላችኋል" አላቸው። ደግሞ አንድ ቀን÷ "በኢትዮጵያ ንጹሐኖች ደናግል አሉ። ስለነሱ እኔ ምስክር ነኝ፤ መንፈስ ቅዱስም ምስክራቸው ነው" አለ።

75. ?።

ከዚያ በኋላ፥ በዚያ ዓመት ከአግዚአብሔር ዘንድ ጥሪ መጣ። ከነሱ ውስጥ አንዷ በ(ጥሪው) በሽታ ላይ እንዳለች፥ "አቡነ አስጢፋኖስ በአግዚአብሔር ፊት ቆሞ፥ ይኸም ሽማግሌ አቡነ አበክረዙን ፫፪ መነኮሲቶች ለአቡነ ቅዱስ አስጢፋኖስ፥ (152ᵇ) "እነሆ መንፈስ ቅዱስ ምስክራቸው የሆነ ንጹሐች ድንግሎች" ብሎ ሲያስረክባቸው፥ አሱም (ተቀብሎ) ለአግዚአብሔር ሲያስረክባቸው ራእይ አየሁ" አለች። ቅዱስ አበክረዙን አንዳለውና አንደ መነኮሲቷ ራእይ ሆነ። የአግዚአብሔር ጥሪ ወደነሱ መጥቶ ፫፪ቱ፥ ከወንድሞች ፯፩ቱ ፍጻሜያቸው ሆነ። ራእይ በጊዜው ይደርሳል፤ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ያለ ሁሉን ያውቃል፤ አሱን ግን የሚያውቀው የለም። አንደዚሁ ይኸም አቡነ አበክረዙን ሥራውን የሚያውቁት (ለምች) ካልሆኑ በቀር ለትምክሕት (ለሌሎች) ሳያሳውቅ በጥሞና ኖረ።

የአባታቸውን ተዝካር ሲያወጡ ተከበቡ

በእንደዚህ እንዳሉ፥ የአቡነ ቅዱስ አስጢፋኖስ የተዝካር ዕለት ደርሶ (152ᵃ) ቅዱሳኑ የተዝካር በዓል ሊያደርጉ በተሰበሰቡበት የንጉሥ መልእክተኞች ከብዙ ሠራዊት ጋራ ሆነው መጡ። የቅዱሳኑን ሰፈር ከበቧት፤ በደረሱበት ያለውን ሀገር ሁሉ አጠፉት። ቅዱሳኑን፥ ደብረ ቅፍርያ በምትባል የታሰሩትን ጭምር፥ ሰብስበው ሁሉንም በአንድነት ወደ ንጉሡ ወሰዷቸው። (መስደው) ምን እንዳደረጓቸው በገድላቸው መጽሐፍ ውስጥ አለ።

አቡነ አበክረዙንን ግን አግዚአብሔር ስለደበቀው አላገኙትም። ግን ከሀገር ወደ ሀገር፥ ከምድረ በዳ ወደ ምድረ በዳ ስለሚያሳድዱት ማረፊያ እስኪያጣ ድረስ የሀገር ጥበት ደረሰበት።

ከዚያ፥ ንጉሡ እንደገና ደግሞ በዚያው ዓመት እዚያ አገር በየቀበሌውና በየገዳሙ (153ᵇ) የተረፉትን ቅዱሳን አንዲሰበስቡ መልእክት አሰተላለፈ። አንዳዘዘው ሁሉንም ሰበሰቡለት። ከ፯ መነኮሲቶችና ከ፪ ቅዱሳን ሽማግሌ ቄሶች--ከአባ አቡናፍርና ከጓደኛው ከዮሐንሰ--በቀር የተረፈ አልነበረም። እነሱም ቢሆኑ በምድረ በዳ በብዙ ችግር ላይ ነበሩ።

ቅዱሱ ከዚያ ሲሄድ መነኮሲቶቹ፥ "አንተ ከዚች ሀገር ከሄድክ፥ ከወንድሞችም ሌሎች ካላገኘን፥ ታዲያ አባት ሆይ፥ እኛ እንዴት እንሆናለን? ከማን ዘንድስ አንተርፋለን? ስለዚህ በዚህ ምድረ በዳ በጽሙና አንድንሞት ፍቀድልን" አሉት። ቅዱሱ፥ "ታገሡ፤ መድረሻችንን አስክታውቁ ድረስ ተጋደሉ" አላቸው። "አግዚአብሔር ከናንተ ጋራ ይሁን" ብሎ ባረካቸው።

(153ᵃ) መንገዱን ቀጥሎ ከገዳማቸው ካንዷ ደረሰ። የሚይዙት አዘያም መጡ። ወንድሞች ቅዱሱን ከ፫ቱ--ከአባ ይሥሐቅ፥ ከመጀመሪያው ጀምሮ አብሮት ካለው ከስምዖን፥ ከረዳቱ ከአብሮኮሮስ--ጋራ ከአንዲት ዋሻ ደበቁት። በዚያ ምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ የዚያ ሀገር ሰዎች ቅዱሳኑን በመፈለግ በጣም አየደከሙ መጡ። ስምዖንን አገኙት፥ ያዙና ወሰዱት። ሰማዕትነቱን ተቀበለ። ቅዱሱን አባታችንን ግን ለብዙዎች ነፍስ ድጋፍ ይሆን ዘንድ አግዚአብሔር ከዓይናቸው ሰወረው።

ደጋፊ ከሚያገኙበት አገር ደረሱ--ዮሐንስና በኮረ ጽዮን

ቅዱሱ ፪ቱን ወንድሞች--አባ ይሥሐቅንና ረዳቱን እብሮኮሮስን--"እዚህ ሀገር ምን እንጠብቃለን? (154[ሀ]) የወንድሞቻችንን ፈለግ ካልተከተልን፥ ወይ እግዚአብሔር ማረፊያ ካልሰጠን እንዴት ይሆናል? እግዚአብሔር የፈቀደውን እስኪያደርግ እንሂድ" አላቸው። ከዚያ፥ ወንድሞችን በወሰዱበት ጎዳና በግሳጭ መንገድ ጀመሩ። ሲጓዙ ከዚያች ... ሀገር ደረሱ።[76] እዚያ ጥቂት አረፉ።

ከላከማ ሰዎች አንድ ምእመን አገኙ። የሰውየው ስም ዮሐንስ ነው። "ወዴት ትሄዳላችሁ? ይኸ ጉዟችሁ ምንድነው?" አላቸው። ሽማግሌው፥ "ለመሞት በወንድሞቻችን ፈለግ እየሄድን ነው፤ ንጉሡ (ወንድሞችን) ከየሀገሩ ሁሉ ሰበሰባቸው፤ እኛም ማረፊያ አጣን" አለው። ምእመኑ፥ "በሀገራችን ሰፊ ምድረ በዳ አለ፤ ሕዝባችንም ባለጥሩ ጠባይ ነው፥ ለሀገሩም (154[ለ]) ሹም እኔ እነግረዋለሁ። አሁንም ኑ፥ እንሂድ" አላቸው።

ወሰዳቸውና ከሀገሩ ምድረ በዳ አስቀመጣቸው። በኮረ ጽዮን ለሚባለው ለዚያ ሀገር ሹም ነገረው። ቅዱሳኑ ካሉበት ምድረ በዳ ሄዶ ተገናኛቸው። "ወደኛ ኑ፤ በምድራችን (በድብቅ) የምትጠበቁባቸው ብዙ ዱሮች አሉ" አላቸው። ቅዱሱ፥ "እንደዚህ ካደረጋችሁ ጥሩ ነው" አላቸው። ወሰዳቸውና አጠገቡ ካለ ዱር አስቀመጣቸው። የዚያች አገር ሰዎችም የሚጠቅማቸውን እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ልባቸውን ስላነቃሳቸው፥ በጣም ተቀበሏቸው።

ከዚያ፥ ወደ ቅዱሱ መጡና፥ "የሚፈለገውን (ትምህርት) ብናገኝ ካላደረግነው (155[ሀ]) ምን ይጠቅመናል? እንደምታየን አረኛ የሌላቸው የተጣሉ በጎች ነን።[77] አሁንም ካንተ ዘንድ ባለው የመንግሥተ ሰማያት ቍልፍ ሕይወት የምናገኝበትን መንገድ አብጅልን" አሉት። ከዚያ፥ ሽማግሌው አሰበና እንዲህ አለ፤ "እነሱ እንደሚሉት፥ እዚህ በሥራ ፈትነት መኖራችን ምንድነው? ወይ እንደ ወንድሞቻችን አልሞትን፥ ወይ ካገኘናት ጸጋ ካልሰጠን፥ የምትገዛልህን ነፍስ ለአራዊት አትሰጣት[78] የሚለው ይኸ አይደለምን? አሁንም ደግ ነገር እንሥራ" አለ።

"ቄሶች የላችሁምን?" አላቸው። "ከቄሶቹ ማንኛው ነው ሕጉን ተከትሎ የሚያስተምር?" አሉት። "እነሱን አምጧቸው" አላቸው። ሲመጡ ቅዱሱ፥ "እናንተ ቄሶች፥ ለምንድን ነው በእውነት መንገድ ራሳችሁንም የማትጠብቁት? መንጋችሁንም (155[ለ]) በጽድቅ አትጠብቁም፤ የቀኖናውን ሚዛንስ ለምን ልብ አትሉትም? ጨው ካልጣፈጠ ይጣላል እንጂ ጥቅም እንደሌለው በወንጌል ውስጥ ተጽፎ የለምን?"[79] አላቸው። "አባ ሆይ፥ የሚሻለውን አስረዳን" አሉት። ሊሆን የሚገባውን ሁሉ ነገራቸው። አብረውት

---

76. የአገሯ ስም አልተጻፈም። ስሟን ሊጠሯት ያልፈለጉት የንጉሡ ወይም የልጆቹ የትውልድ ሀገር ስለሆነች ወይም በኋላ የመጡ አሱን በመጥላት ፍቀውት ይሆናል።
77. ማቴ 9፡ 36ን ሲጠቅስ ነው።
78. መዝ 73፡ 19።
79. ማቴ 5፡ 13።

ካሉት እንዱን ካህን ሲሆን የሚገባውን ሁሉ እንዲያስተምራቸውና ንስሐ እንዲሰጣቸው ሰጣቸው።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ በሽማግሌው ቃል ለምእመናኑ ምሕረት ወረደ። እንደዚህ እያስተማራቸው ፲፫ ዓመት ከ፲ ወር ኖረ። ከዚያች ሀገር ብዙዎች ሕይወታቸውን በጽድቅ ፈጸሙ። አንዳንዶቹ ወንዶችም ሴቶችም ለዚች ሥርዓት ሕንፃ ሊሆኑ ወደ ምንኵስና መጡ። (156ᵇ) ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ሃይማኖታቸው፥ ስለዚህ ሽማግሌ አባታችንም፥ "ነፍሱን ለወንድሙ ምትክ የሚሰጥ ብፁዕ ነው"[80] የሚለው የእግዚአብሔር ቃል የሚፈጸምበትን ብፅዕና ለማግኘት ከንጉሡ ወታደሮች ጋራ ሲጣሉ ከደምና ከሞት እስኪደርሱ ድረስ የንብረታቸውን መመዝበርና የቤቶቻቸውን መቃጠል በመታገሥ ብዙ ስደት ደርሶባቸዋል። አባታችን በዚያች ሀገር ከምድረ በዳ ወደ ምድረ በዳ፥ ከማደሪያ ወደ ማደሪያ ሲንከራተት ብዙ ስደት ደረሰበት።

ታብርሃ ጽዮን

ከዚያች ሀገር ሹማምንት ወገን የሆነች ታብርሃ ጽዮን የምትባል እንዲት የንጉሦች ወገን የሆነች ሴት ቅዱሱን በስደቱ ሁሉ ታገለግለው ነበረ። እንደዚሁ ለሌሎችም ወንድሞች (156ᵃ) ካላት (ሀብት) መስጠትን አላስታጐለችም። በዚያች ሀገር በመላዋ ዝናዋ እስኪሰማ ድረስ ብዙ በጎ ሥራ ትሠራ ነበረ። ሽማግሌው አባታችን፥ "ይህቺ ሴት ብዙዎችን ረዳች፤ እኔንም እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ረዳት እንደ ፊቤን ረዳችኝ። (ጳውሎስ)፥ "ለቅዱሳን እንደሚገባቸው በደስታ ይቀበሏት፤ በፈለገችበትም ሁሉ ይርዷት። በችግራቸውም እንድትረዳ ያድርጉ"[81] እንዳለው እኔም እንደሱ በሁሉ ይቀበሏት፤ በመጽሐፍም ያስታውሷት፤ ለትልቅ ወይም ለትንሽ፥ ለቅርብ ወይም ለሩቅ ላታደላ ብዙ ደክማለችና እላለሁ" እስከ ማለት ደርሷል። የተደበቁ ምሥጢሮችን የሚናገር አንድ ቅዱስ ካህንም በዕረፍቱ ጊዜ ስለሷ፥ "ይቺ ሴት (157ᵇ) ኤልያስን በስደቱ ጊዜ እንደተቀበለችው እንደ ሲዶናዋ ስረጵታ ነች።"[82] (እንደሷ) ይኸንን የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ሽማግሌ አባታችንንና ሌሎችንም ቅዱሳን ተቀብላቸዋለች እላችኋለሁ" አለ።

ከዚያ፥ ከዘመናት በኋላ፥ እዚያ በመጡ በ፲፫ ዓመት፥ የሰይጣን ፈተና ወደዚያች ሀገር እንደመጣች ቅዱሱ ሲያውቅ አብረውት ላሉት ወንድሞች፥ "በዚች ሀገር ፈተና በግድ ይመጣል፤[83] በግድ ስለሚመጣው ስለ ማንኛውም ሊደረግ የሚሻለውን አስቡበት። ከተቻለ እስከ ጊዜው (ሳትታወቁ) የምትጠበቁበት ምድረ በዳ ብትፈልጉ ይሻላል። ሰይጣን ከቶ እንደ ሌሎቹ ሊገድለኝ የሚፈልግ አይደለምን? በጽኑ (157ᵃ) ይከታተለኛል። እነሆ፥

80. ዮሐ 15: 13።
81. ሮሜ 16: 2።
82. 1 ነገሥ 16: 8-15።
83. ዕብ 9: 16።

የብዙዎችን ልብ አሸበረ። ይቺም አገር መጽሐፍ፥ "የድሆችን ተስፋ መሸከም አትችልም"[84] እንዳለው የቻለችውን አድርጋለች። የሚያጣድፋት ደርሷል፤ በውስጧ ጣር ሞልቷል" አላቸው። ወንድሞች፥ "እንግዲህ አንተ እግዚአብሔር እንዳሳየህ የሚገባውን አሳየን እንጂ፥ እኛ ምን እንበል? እኛም (የምትለውን) ሰምተን እናደርጋለን" አሉት።

ለአዲስ ሰይጣናዊ ክስ መዘጋጀት

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ ብዙዎች ወንድሞች ለቅድስት ኤጲፋንያ (ለጥምቀት) በዓል ዕለት በተሰበሰቡ ጊዜ፥ ቅዱስ አባታችን ደግሞ እንዲህ አላቸው፤ "እነሆ የፈተናና የሕመም ጊዜው ደርሷል፤ ሳናውቀው ድንገት አገኘን እንዳትሉ። አሁንም ለሞት ጨክናችሁ እንደሁ ወይም እንደዚያ አንዳይደለ (158^{ሀ}) የሚሆናችሁን ዕወቁ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ እስኪሆን ድረስ ራሳችሁን እንድትጠብቁ (የሚያዛቸሁ) ሥርዓት አላችሁ። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ነገር አይሆንም። እኛ የምንሞተው ለራሳችን አይደለም፤ የምንኖረውም ለራሳችን አይደለም። ብንሞትም ለእግዚአበሔር፥ ብንኖርም ለእግዚአብሔር ነው።[85] አሱ እንደፈቀደው ይሆናል" አላቸው።

ወንድሞች፥ "እኛስ የተጠራነው ስለዚህ እይደለምን? አሁንም በህገር ውስጥም ሆነ በምድረ በዳ እግዚአብሔር ይረዳናል። በሥርዓታችን እንደሆንን እንሞታለን። ስላንተ ግን ምን እናድርግ? የምትደበቅበት ምድረ በዳ አናገኛለንን?" አሉት። ቅዱሱ፥ "ስለኔስ አትተክዙ፤ እሱ በፈቀደ ይሆናል። (158^{ለ}) አገሪቱ በኔ ምክንያት ፈተና ስለሚመጣባት፥ ከተቻለስ እንዳትጠፋ ከበሯ ላይ ልጠብቃቸው እፈልጋለሁ" አላቸው።

ከዚህ ነገር በኋላ፥ ምንም ሳይቆይ፥ ሰይጣን ሞገዶቹን እነሣ፤ የስክለቱን[86] መርዝ በብዙ ሰዎች ልብ አስቀመጠ። ቅዱሱንና ልጆቹን በውሸት እንዲህ ሲሉ ለመክሰስ ወደ ንጉሡ ሄዱ፤ "ደቂቀ አስጢፋኖስ ምድርን ወረሷት፤ ብዙዎችን ወደ ክሕደት ትምህርታቸው መለሱ፤ በመንግሥትህ ህገሮች ሞሉባቸው። የሚገዛልህ የለም። ይኸ አበክረዙንም በግላጭ ይሰብካል። የሱ ባልሆነች በጽድስና ተቀምጧል። የችሎቱም መቀመጫ ባለ ፮ ዓምዶች ታላቅ ሰቀላ ነው። (159^{ሀ}) እዚያ የሚሰበሰበው የወንድም የሴትም ሠራዊት ብዙ ነው። ግብር ሲያገባ ፱ በሬ ቢታረድ ትንሽ ትንሽ እንኳን ቢካፈሉ አይባቃም። የንጉሡ ልጅም ከነሱ ጋራ አለ።[87] እንደ ንጉሥ ይታዘዙለታል። የሐር ጭራ ሠርተውለታል። ሌሌዎቹም የምድሪቱ (የሱ) ሹማምንት ሆነዋል። ለመንግሥትህ አስተዳደር የሚገዛ የለም። እኛ ስላንተ ቀናተኞች ሆነን ልንነግርህ መጣን፥ ጌታችን ንጉሥ ሆይ።"

---

84. ?።

85. ሮሜ 14: 8።

86. "ስክለት" የሚለውን ቃል አላውቀውም። ከገድለ አስጢፋኖስ ውስጥም አለ፥ ከግዕዝ መዝገበ ቃላት ውስጥ ግን አላገኘሁትም። ትርጕሙ "ተንኮል" ማለት ይመስላል።

87. ገድለ አበው ወአኃው ውስጥም የአፄ ዘርአ ያዕቆብ ልጅም የአባ አስጢፋኖስ ተከታይ እንደሆነ ምልክት አለበት (ገጽ 145፥ ኅዳግ ቍጥር 98)።

ንጉሡ ሲሰማ፥ "ይህ ሁሉ ነገር እውነት ነውን? መርምሩ" (አለ)። ከአሳባቂዎቹ አንዱ፥ "አዎን እውነት ነው፥ ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ብቻ መልእክተኞች ስጠኝ። እሱ ካለበት እኔ አደርሳቸዋለሁ። እሱን ካሳገኙት እኔን ይግደሉኝ" አለ።

ንጉሡ ሎሌዎቹንና (159^ሀ) የሀገሩን ጠባይ የሚያውቁ ታሳላቅ ሰዎቹን ከሠራዊቱም ብዙዎች ጠራና ከዚያ ካሳባቂ ጋራ ላካቸው። "ሂዱና ቁጣዬን አብርዱልኝ፤ ያቺንም አገር አጥፏት። አባታቸውን አበከረዙንን ግን ወደኔ አምጡት። ወደ ቀኝም ቢሄድ ወይም ወደ ግራ እንዳያመልጣችሁ" ብሎ አዘዛቸው።

እንደዚህ ታዘው ወደዚች ሀገር ድምፃቸውን አጥፍተው መጡ። ጻማ የለበሰውን ቅዱስ ሽማግሌ አቡናፍርን አብረውት ካሉት ወንድሞች ጋራ አገኙት። ሽማግሌውን ያዙትና ከመሬት ላይ ወርውረው እንደ ግንድ በመንገድ ላይ ጐተቱት። "መምህራቸውን ያዝነው" እያሉ ጨፈሩ። ወደ ንጉሡም ወሰዱት። (ወስደው) ምን እንዳደረጉት (160^ሀ) ከገድሉ መጽሐፍ ውስጥ አለ።[88] ሠራዊቱ አገሪቷን አጠፏት፤ ቅዱሱን ሲፈልጉ አገሮች አበላሹ። አሱን ግን እግዚአብሔር ከዓይናቸው ፊት ስለሰወረው አያዩት አላገኙትም። ከብዙ ወንድሞች ጋራ ሆኖ ባጠገባቸው አልፏቸው ሄደ። የሀገሩ ሰዎችም፥ "እሱን ያመጣ እኛ ዘንድ ክብርና ሞገስ ያገኛል፤ የሀገር ሹም ከሆነም ሳይለወጥና ግብር ሳይከፍል ሰባት ዓመት ይኑር" የሚለውን የንጉሡን ትእዛዝ ሰምተው፥ ይፈልጉት ነበረ።

በዚህ ምክንያት እሱን ፍለጋ አጥብቀው ያዙ። ያለበትን ቦታ ሲጠቁሟቸው እየመጡ የሰዎች ቤት ይመዘብራሉ። በዚህ ምድረ በዳ አለ ሲሏቸው እዚያም (160^ሀ) ሊፈልጉት ይሄዱና ሲያጡት የሚዳውንና የተራራውን ሰብል እሳት ይለቁበትና ያጋዩታል። በእሳት ቃጠሎ አገር ያበላሻሉ። አሱን ግን እግዚአብሔር ይጠብቀው ነበር። በቀኝ እጁም ይጋርደው ነበር። አንዳንድ ቀን ሲያገኙት በላዩ ላይ ስላለ ግርማ ፈርተው ይተውታል። አንዳንድ ቀን እያዩት እግዚአብሔር ከዓይናቸው ይሰውረዋል። እነሱ ግን ባለማግኘታቸው ይጮኻሉ።

ወደ ሌላ ሀገር ሄደ ሲሏቸው፥ እዚያም ከኋላው በጥድፊያ እየተከተሉ ይሄዳሉ። ሰይጣንም በመልእክተኞቹ አፍ ስለሱ፥ "እነሆ፥ ይህ ለሀገር ጥፋት ምክንያት የሚሆን ሰው መጥቷል" እያለ ለፈፋውን አስቀድሞ ያሰማል። እሱ ግን በአምላኩ ጎይል ይጠበቃል። (161^ሀ) "ከዚችኛዋ ሊያሳድዷችሁ ወደ ሌላዋ ሂዱ"[89] በሚለውና፥ "በትዕግሥታችሁ ነፍሳችሁን ታተርፋላችሁ"[90] በሚለው በእግዚአብሔር ቃል ይደሰታል። የአበው የትምህርት ቃላቸውም፥ "ደካማ ወፍ ከበረረ ጽኑ አንበሳ ምን ሊያደርገው ይችላል?"[91] ይላል። ሽማግሌውም በሥጋ ጎይል ረገድ ደካማ የሮዐ ዓመት

88. የታተመ ገድለ አቡነ አቡናፍር አላየሁም።
89. ማቴ 10: 23።
90. ሉቃ 21: 19።
91. ተረትና ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

ልጅ ነው፤ ግን በመንፈስ ጎይል ጐልማሳ ስለሆነ ወደሚጠበቅበት ቦታ (እንደ ወፍ) ይበርራል።

ዋሻ ውስጥ ወምበዴ ዘረፋቸው

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ በቀን በፀሐይ ሙቀት፥ በሌሊት ጨለማም በብዙ ችግር እየተሰደደ አልቤታ ከምትባል ከሀገሩ ቄላ ደረሱ። እዚያ አንድ ዋሻ ውስጥ ገብተው ሰባት ቀን አረፉ። አብረውት ያሉት ወንድሞች ብዙዎች ነበሩ። (161^ሀ) ከነሱ ጋራ እንደማይደበቅ ሲያዩ ተመልሰው የሀገሩን ሁኔታ እስኪነግሩት ድረስ እንዲያርፍ እዚያ ትተውት (ሄዱ)። በስደቶቹ ሁሉ ተካፋይ ከሆነው ከረዳቱ ከአብሮኮሮስና ከሌሎች ፬ ወንድሞች ጋራ እዚያ እንዳለ፥ የሀገሬው ሰዎች እዚያ መሆናቸውን ሰምተው (ኖሮ)፥ ድምፃቸውን አጥፍተው መጡና ልብሳቸውን፥ ስንቃቸውን፥ የድኽነት ገንዘባቸውን፥ የሽማግሌውን ደበሎ ሳይቀር፥ ገፈፏቸው። ደግሞ የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍና ምላጩን ከረዳቱ እጅ ወሰዱበት፤ ከዋሻ ውስጥ ያለውን የሣር መኝታ በእሳት አቃጠሉት።

ሽማግሌው፥ "ለምንድን ነው (162^ሀ) እንደዚህ የምታደርጉት? እግዚአብሔርን አትፈሩምን?" አላቸው። ከነሱ አንዱ ቅዱሱን፥ የሞገሱን ውበትም ሆነ ቅድስት ሽምግልናውን ላያፍር፥ በስድብ ቃል ከፋት ሲናገር፥ "ይኸ ሽማግሌ ምን ይላል! ዝም አልል አለ" አለው። ቅዱሱ፥ "ጌታ ሆይ፥ የፈለጉትን ሁሉ እንዲናገሩ ለነዚህ ሰዎች ስድብ ተውከንን?" አለ። ወንድሞችንም፥ "ስጧቸው፤ ምንም አትከልክሏቸው። በእግዚአብሔር ትእዛዝ ውስጥ እንደዚሁ ተጽፏልና"[92] አላቸው።

እነዚያ ሰዎች ዘርፈው ወደ ሀገራቸው ሄዱ። ቅዱሳኑንም ከዚያ አባረሯቸው፤ እየገፈተሩ አስወጧቸው። እንደ ልማዳቸው እየተባረሩ ሄዱ። በመንገድ ሲጓዙም ቅዱሱ (162^ሀ) ልጆቹን እንዲህ እያለ ምዕዳን ያስማቸው ነበረ፤ "የክርስቶስን ሥቃይ እንድትካፈሉ ለዚህ ተጠርታችኋልና በዚህ ምክንያት አትተክዙ፤ አትጠራጠሩም። የአባቶቻችን የቅዱሳን ሐዋርያት መንገድም እንደዚህ ነበረ። እነሱም ስለ ስሙ እንዲያዋርዷቸው እንደዚህ ስለከፈላቸው ሲሰደዱ፥ ሲገረፉ፥ ሁልጊዜ ሲቸገሩ በጣም ይደሰቱ ነበረ።" ረዳቱ አብሮኮሮስ፥ "አባ ሆይ፥ እንኳን አንተ ከኛ ጋራ እያለህ ብቻችንንም ብንሆን የጸሎትህ ጎይል እየረዳችን ለመሞት ጨክነናል" አለው።

ቅዱሱ ከዚያች ሀገር ወጣና ወደሌላዋ ሄደ። ያ የቅዱሶችን ንብረት የቀማና አባታችንን ከፉ ነገር የተናገረው ሰው፥ ለተገፉ የሚበቀል ልዑል እግዚአብሔር እጁን በሱ ላይ ሲያላይ፥ በኋላ በዚያች ዕለት (163^ሀ) በመንገድ ሲሄድ ገደል ገብቶ ከመሬት ላይ ተወቃ። ምላሱ ካፉ ተጐልጕሎች። ያችም ከቅዱሳኑ የቀማት ምላጭ ገደል ገብቶ ሲወድቅ እንገቱ ላይ እንደ ፍላጻ ተተክላበት እዚያው ሞተ። የዚያች ሀገርና በአካባቢዋ ያሉ ሰዎች ይኸንን

92. ማቴ 5፡ 40፤ ሉቃ 6፡ 29።

ሲሰሙ በጣም ፈሩ። ድንጋጤና ታላቅ መገረም ወደቀባቸው። የቅዱሳኑን ንብረትና ልብሳቸውንም መለሱላቸው።

ቅዱሳኑም ከተከዜ አጠገብ ደወልወላ ከሚባል ቦታ እስኪደርሱ መንገዳቸውን በሰላም ቀጠሉ፤ እዚያ አረፉ። ቅዱሱ÷ "ድካማችንን ተሸክሞ እዚህ ላደረሰን እግዚአብሔር ስብሐት ይግባው" አሰ። (163ᴬ) ወንድሞችንም÷ "ሰይጣን እፍሯልና አትፍሩ፤ ሊከተለን አይችልም። አሁን እንግዴህ እረፉና እግዚአብሔርን አመስግኑ። የእስራኤል ነቢይ ኤልያስም ስለ እግዚአብሔር ቀንቶ በኤልዛቤልና በንጉሥ አካአብ እንደዚህ እስከ ደብረ ኮሬብ ድረስ ተሰዷል። ወደ ሕዝቡ እስኪመለስም ድረስ እዚያ ኖሯል"[93] አላቸው። ወንድሞች ይሽንን ከቃሉ ሲሰሙ እግዚአብሔርን አመስጉት÷ ስብሐትም አቀረቡለት። እዚያ ፫ ሳምንት ያህል አረፉ።

በተምቤን ምድረ በዳ

ከዚያ በኋላ÷ ከዚያ ወጥተው በተምቤን ምድረ በዳ ወዳሉት ወንድሞች ሄዱ። ቅዱሱ እዚያ ፲ ወር ያህል ተቀመጠ። እዚያ የመኖሩን ዜና ሌሎች ወንድሞች ሲሰሙ (164ᵇ) እንደሰመዱት የሩቆቹም የቅርቦቹም ወደሱ እየመጡ የቃሉን ምዕዳንና በረከቶቹን አግኝተው ወደየገዳማቸው ይመለሱ ነበር። ቅዱሱ እዚያ ያሉትን ወንድሞች መሥዋዕት እንዲያዘጋጁ አዘዛቸው። እንደዚያ አደረጉ።

ከዚያ በኋላ÷ ከገዳሞቹ ወደ አንዷ÷ ከስዋ ወደምትባለዋ÷ ሄደ። ከእሷ ከወጣ ፲፬ ዓመት ከ፬ ወር ሆኖት ነበረ። እዚያ ሀገር ያሉ ወንድሞች ተሰባሰቡና ስለሱ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። እሱን በማግኘታቸው ታላቅ ደስታ ተደስቱ፤ ልባቸው እስከትበራ ድረስ በምዕዳን እያጽናናቸው አብሯቸው ቆየ። የውጪና የውስጥ የእጅ ሥራቸውን እግዚአብሔር አሳመረላቸው።

ከዚያ በኋላ÷ (164ᴬ) ቅዱሱ÷ "የእግዚአብሔርን ስብሐት የምታሳርጉበት መሠዊያ ከማህላችሁ ሥሩ" አላቸው። ወንድሞች÷ "ካሁን በፊት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን አጠፋብን፤ ክርስቲያን ሆነው ሳለ በእሳት አቃጠሉት። አሁንስ ቢሆን ማን ይተውልናል ብለን እንደክማለን? እነሱ ስለኛ÷ በተሰየም በዚች ቤተ ክርስቲያን ላይ÷ በቅናትና በቁጣ ተሞልተዋል" አሉት። ቅዱሱ አባታችን እንዲህ አላቸው፤

> ጳውሎስ በመልእክቱ÷ "እዚህ የምንቆይበት አገር የለንም÷ የምትመጣዋን እንፈልጋለን እንጂ"[94] ያለውን አልሰማችሁምን? ምክር እንዲሆንባቸው እናንተ ይሽንን (ያልኳችሁን) አድርጉ። "ካልተዉልን እንደክምም" አትበሉ። (165ᵇ) "፩ አብ ቅዱስ÷ ፩

93. ታሪኩን 1 ነገሥ 17: 1-18: 30 ተመልከት።
94. ዕብ 13: 14።

ወልድ ቅዱስ÷ ፩ ውአቱ መንፈስ ቅዱስ" ብላችሁ አንድ ቀንም ቢሆን በውስጧ ለአግዚአብሔር መሥዋዕት ካሳረጋችሁ አይበቃችሁምን? ስለ አንደዚህ ያለ ምክንያት መጽሐፍ ይናገራል፤ አብርሃም ለአግዚአብሔር መሠዊያ ሠርቶ ቍርባን አሳርጓል::[95] ይኼ (መጽሐፉ) ያለው ሁል ጊዜ የሚኖር ሳይሆን የአንድ ጊዜ አንደሆነ ዕወቁ:: አሁንም አግዚአብሔር የፈቀደውን ያድርግ:: አናንተ ግን ልባችሁን አታድክሙ:: ስለ ቤተ አግዚአብሔር መድከምን አትተዉ፤ የድካማችሁ (ፍሬ) ይበዛላችኋል:: "ስለ አምላኬ ስለ አግዚአብሔር ቤት መልካምነትሽን ፈለግሁ"[96] ያለውን የነቢዩን ቃል አስታውሱ:: አናንተም በስደት ምክንያት አትሰልቹ:: በደረሳችሁበት ሁሉ የአግዚአብሔርን ታቦቶች ሳትይዙ አትሂዱ:: አናንተንም በጉዟችሁ ሁሉ የአግዚአብሔር ጎይል (165^ሀ) ይረዳችኋል÷ ያጠነክራችኋልም:: አግዚአብሔር ባለ ወርቅና ባለ ብር ጌጥ ሕንፃ አይፈልግም፤ የሚፈልገው ነቢዩ÷ "የተከበረች መሥዋዕት ስብሐት ታቀርብልኛለች"[97] አንዳለው በንጹሕ ስብሐት ማሳረግ ነው::

በተቃጠለችባቸው ቤተ ክርስቲያን ምትክ

ይኸንን ምዕዳን ሲጨርስ÷ ጥር ፲፪ ቀን በፊት ካቃጠሉት ቦታ ላይ ቆመ:: አይቶ÷ "ክርስቲያኖች በአግዚአብሔር ቤት ላይ እንዲህ ያደርጋሉን? የጣያት ቤት መሰላቸውን ወይስ እንዴት ነው?" አለ:: በዚያው ዕለት እዚያው መሠረት ጥለው እንዳቅማቸው ስብሐትና ጸሎት ለማሳረግ የሚበቃቸውን ያህል አቋቋሙ:: ቅዱሱ አባታችንም ኤልሳዕ ከመምህሩ እንዳሳንደለ አንደዚሁ አሱም እንደ (166^ሀ) አባታችን እንደ አቡነ አስጢፋኖስ መገሠጽና ማስተማር ሳያጓድል የመሥዋዕትን የሕጉን ሥርዓት ሁሉ ያስረዳቸው ነበረ::

አቡነ አበክረዙን ልጆቹን አንዲያጸናቸው መንፈስ ቅዱስ አሱን ያጸናው ነበረ:: እዚያ አንደ ጥበበኛ አስተዳዳሪ በማድጋ መለኪያ ፱÷ በጫን መለኪያ ፭ ያለበትን (ባለአዳ) ከማረው ከቅዱስ ወንጌል ምስክራ ጋራ አንዲስማማ[98] እያደረገ ለጌታው ባሮች ያመኑትን ያለባቸውን ዕዳ አያቃለለላቸው 3 ዓመት ያህል ኖረ:: ለነሱም በይቅርታው ምክንያት ነፍሳቸው ቸር ሆነች:: የተጻፈባቸውን (ክፍያ) በደስታና ደስ በመሰኘት ይሰጡ ጀመር:: በእውነት ሥርዓት ሁሉ የሚፈርድባቸውን ነፍሳቸው አንድትፈጽመው ሁል ጊዜ ያበረቷት ነበረ:: የባሕርን ቦታ በሮችና (166^ሀ) በጥልቅ ባሕርና በአሳት መካከል የሰው እግር ማሳረፊያ ያህል የሚሆነውን ጠባቡን መግቢያዋን[99] ይገልጽላቸው ነበረ:: በመጀመሪያዋ ሕግ ውስጥ

---

95. ዘፍ 22: 9::
96. መዝ 121: 9::
97. መዝ 49 23::
98. ሉቃስ 5: 7::
99. ማቴ 7: 14:: በቤተ ክርስቲያን ባህል÷ ይኼ በሞት ጊዜ ወደ ክርስቶስ ዳኝነት የሚወስደው መንገድ ከጥበቱ የተነሣ በአንድ ጊዜ ከአንድ ሰው ይበልጥ አያስኬድም፤ ጥበቱ በጣም ቀጭን ሆኖ በባሕርና በአሳት መካከል የተዘረጋ ስለሆነ÷

ያለችው ቃል ይቺ ናት፤ "ጓደኛህን እንደራስህ ውደድ::"[100] በጓድነቷ የታወቀች መመላለሻዋም በወንጌላዊው ዮሐንስ መልእክት (እንደተጻፈው)÷ "ጓደኛውን እየጠላ እግዚአብሔርን አፍቃሪ ነኝ"[101] የሚል ሰውን የምታስረዳ ቃል ናት::

ቃለ ምዕዳን

የተሳሳቱትን (ትክክለኛውን) መንገድ ሲመራ÷ የዋሆቹን ፍርድ ሲያስተምር÷ ለአስተዋዮቹ መንገድ ሲያሳይ እንዲህ ይል ነበረ፤

> እንግዴህ ልጆቼ እላችኋለሁ፤ እንደ ሐዋርያው ዮሐንስ ቃል የምታዩትን ወንድማችሁን ለመውደድ ያልቻላችሁ የማታዩትን ጌታችንን እንዴት ልትወዱት ትችላላችሁ? አሁንም እርስ በርሳችሁ ከተዋደዳችሁ (167^{ሀ}) ከእግዚአብሔር ጋራ እንደምትኖሩ ዕወቁ፤ እሱም ከናንተ ጋራ ይኖራል:: የእግዚአብሔር ቃል እውነትና የሚታመን ስለሆነ÷ "እኔም እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁል ጊዜ ከናንተ ጋራ አለሁ"[102] ያለውን እናውቃለን:: በዚህም እግዚአብሔር ከኛ ጋራ እንዳለ ዐውቀነዋል፤ እሱ ራሱን ስለኛ አሳልፎ ሰጥቷልና:: እኛም ራሳችንን በጓደኞችን ምትክ መስጠት ይገባናል:: ደግሞ ለራሳችን የማንፈልገውን በጓደኞችን ላይ እናድርገው::[103] በዚህ ዓለምን እናሸንፋለን:: በዓለም ውስጥ ያለው ሁሉ የሥጋ ፍላጎትና የዓይን አምሮት ነው:: (እነዚህ) "የእግዚአብሔር ጠላት ናቸው" የተባሉ የሥጋ ሕግ ናቸው:: እኛ ግን በእግዚአብሔር ሕግ እንኖር ዘንድ ይገባናል፤ "ከአእላፍ ወርቅና ብር÷ (167^{ለ}) የአፍህ ሕግ ይሻለኛል"[104] ብሏልና:: የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ ሁሉ ነገር ይገኛል:: በእሱ አባባል÷ "ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔርን መንግሥቱንና ጽድቁን ፈልጉ፤ ይኸስ ሁሉም ይጨመርላችኋል"[105] ለመንፈስ ልጅ ትክክሉ የመንፈስ አባቱን ነገር መጠበቅ÷ የቃሉን ምስክርነት ልብ ማለት÷ (ባባቱ) ቁመት ልክ ለመቆም እስኪደርስና ከፍ እስኪል ድረስ የፈለጉን መዓዛ መከተል ነው፤ (ክርስቶስ) ሲመጣ በፊቱ ሞገስ ያገኛል፤ አያፍርም:: እሱ ራሱ÷ "ነፍሱን የሚወዳት ይጣላት፤ ስለኔና ስለ ወንጌሌ ነፍሱን የጣለ ያገኛታል"[106] ብሏል::

እየር ላይ በተወጠረ ገመድ ላይ እንደሚሄድ ሰው በብዙ ጥንቃቄ ካልተራመዱ ወይ ወደ ቀኝ ወይ ወደ ግራ መውደቅ ይመጣል::

100. ዘሌ 19: 15::
101. 1 ዮሐ 4: 19::
102. ማቴ 28: 20::
103. ማቴ 7: 12፤ ሉቃ 6:31::
104. መዝ 118: 72::
105. ማቴ 6: 33::
106. ማቴ 10: 39፤ ዮሐ 12 25::

ቀጥሎም፡ "ሰው (168ᵘ) ነፍሱን ካጣ፡ ዓለምን በሞላ ቢያተርፍ ምን ይጠቅመዋል?"[107] ይላል።

በተግሣጹ መጨረሻም፡ "ያፈረብኝና በቃሌም ያፈረ የሰው ልጅ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋራ በስብሐት ሲመጣ ያፍርበታል"[108] አለ። ደግሞም፡ እንዲህ ይላል፤

አሁንም እሳችኋለሁ፤ (እዲስ) ሥርዓትን ፈሳጊ ሰው በሃይማኖት የጽድቅ እንጀራ ካሳገኘ ለነፍሱ ሕይወት እያገኘም። የሥራው በረከትም ፈለግ አይኖረውም። የመጓጓት መንፈስ ስለሚያበሳሽው (ወጥቶ) የሚገባውም በውጪ ጎይል ይሆናል። (ቢፈጭም) ዱቄት ከውስጡ አይወጣም፤ ቢወጣም ጠሳት ይበሳዋል። ምክንያቱም ሥራው በእምነትና በተስፋ ሳይሆን በሥጋ ሕግ ጎይል ነው። ስለዚህ በውስጡ ኃይል አይኖርበትም፤ የቅናት እሳት ያቀልጠዋል፤ ምክንያቱም (168ᵃ) ዝንባሌው ወደ ፀሐይ ሳይሆን ወደ እሳት ነው። እሳት ከወደቀበት ፀሐይ አትታይም፤ የሐዘን ደመና ይሸፍናታል። አሁንም አስቀድሞ የጽድቅ እንጀራን መስብሰብ ይሻሳል፤ (የጽድቅ እንጀራ) የማኅበር መሠረት ናት። መጽሐፉ፡ "ቤቱን በብድር ገንዘብ የሚሠራ ሥራው እንደ ክረምት የቤት ሥራ ይሆናል"[109] ይላል። እንደዚሁ አሁንም የጽድቅ እንጀራ የሚሰበሰበው ቅናትና ሐዘን ሳይኖርበት በእምነት፡ በሃይማኖት፡ በፍቅር እንጂ ቡጎይል አይደለም፡ በውጪ ጥበብም አይደለም። እርስ በርስ መቀናናት ካለበት እዚያ ሁከት ታድራለች። ከእግዚአብሔር የተሰጠችውን ጸጋ ከሌሳው ዘንድ ሲያይ የሚቀና ነፍስ ገዳይ (169ᵘ) ነው። ስለዚህ ጉዳይ በሕግ ምስክርነት ስለ አቤል የሆነው ተጽፏል።[110] (ጸጋ) የተሰጠችውም፡ "ይች የኔ ናት፡ የግሌ ናት" አይበል። (ካለ) ስለሷ የሚሰጠው የመልስ ቃል እንዳለ ይወቅ፤ "በከንቱ ያገኛችሁትን በከንቱ ስጡ"[111] ተብሏልና። በሌሳ ቦታም፡ "የእግዚአብሔርን ፍሳጎት እንደተቀበላችሁ እንደ ደግ አገልጋይ እገልግሉ"[112] ይላል። ይህቺ ጸጋ በብዙ ስብከትም ሆነ ወይም በመንፈስ ወይም በግሳጭ ሳትታይ የሥርዓቱ በርና የመንፈሱ አባት በሆነው በመልአኩ እጅ በምልክት (ብቻ) ስትጠራው፡ ለግሉ ከፍ ከፍ ካደረጋት ትወሰድበታለች። ለዚህ ምስክር ከሰማይ ያልተሰጠውን ምንም መውሰድ የሚችል እንደሌለ (169ᵃ) ተጽፏል።[113] ትእዛዝን ሁሉ (መጠበቅ) ሕይወት ነው፤ መተሳለፉ ሞት ያመጣል። አሁንም ፍሳጎታችሁ እንዲታነጽ፡ "የድካምህን ፍሬ ትመገባለህ፤ ምስጉን ነህ፤

107. ማር 8፡ 36።
108. ማር 8፡ 38።
109. ሲራ 21፡ 8።
110. ዘፍ 4፡ 3-8።
111. ማቴ 10፡ 8።
112. ማቴ 25፡ 21-24ን እና ሉቃ 19፡ 16-17ን መጥቀሱ ይሆናል።
113. ዮሐ 3፡ 27።

መልካምም ይሆንልሃል።"[114] ስለሚል፥ ሕይወታችሁ በሌላ ድካም ላይሆን በእውነት እንጀራ ይሁን። ለዕረፍት በሌላ ሰው ማእድ ከመወርወር ይልቅ በሥራ መሠቃየት ይሻላል። በሌላ ሰው ማእድ ከማረፍ ይልቅ ስለ ጽድቅ እንጀራ ማሰብ ይሻላል። "ስለ ቤቱ የማያስብ፥ ዘመዶቹን የሚከዳ፥ ከማያምን ይበልጥ ይከፋል"[115] ይላል። በሌላ ቦታ ደግሞ፥ "የሰው እህል መብላት እፍረት ነው"[116] ይላል። ደግሞ፥ "ከመሰለመን መሞት ይሻላል"[117] ይላል። ስለዚህ እላችኋለሁ፥ (170ᵘ) በስላም ማሰሪያ የጓደኛችሁን ሕመም እንደ ሌላ ላይሆን እንደራሳችሁ በቃልም በሥራም አየታመማችሁ በአንድ መንፈስ በአንድ አካል እንድትኖሩ።

የማኅበር ሃይማኖት የምትጠበቀው የትእዛዝን ሥርዓት በመጠበቅ ነው። የማኅበር ሥርዓት አርአያዋ በሰማይ አለች። "በሰማይ እንደሆነ በምድርም እንዲሁ"[118] (ይላልና)። የተከበረ የትእዛዝ ነገር የሚጠበቀው በማኅበር ነው። ተለይቶ ብቻውን በሆነ ዘንድስ አትኖርም። በትዝብርት ሐሳብ ይሸነፋል። ስሙ አሉን ከሚመስሉ ይለወጣል። የተስጠችውም ህብት ትወስድበታለች። ከሁሉ ዘንድ ያየውን ሁሉ በሚያስደስትበት ይደክማል፤ የሚመለስበትን ሁኔታ አያስብም። ብቻውንም ቢመክር፥ ከወገኖቹ የተለየ ዕለት ልቦናው ስለሚከዳው፥ (ምክሩ) ወደ ሞኝነት ይቈጠራል። (170ᵅ) ምክንያቱም ውሳኔው ሁሉ የውጪውን አንዱት እንደሚሰበሰብ ይሆናል። ትክክሉን ሲያስብ ኀይሉ ይደክምበታል። (ተለይቶ ብቻውን መሆን) የብዙዎችን ኀይል አስቀርቷል። ስለዚህ በጉድለት ይኖራል። የነገሩ እውነትነት አትሞላለትም። በሚያየው ዓይንም ሆነ በሚሰማው (ጆሮ) ዘንድ አያምርለትም፤ በዚህ ሁሉ የራሱን ኀይል አሉ ብቻውን ያደንቃል። በሕይወት ያለ ይመስለዋል። (ግን) የጠላት ኀይል ይቈራኘዋል። በማያውቀው በኩል ይመጣበታል። የ(አዲስ) ሥርዓት ፈላጊ ከማኅበር ከተለየ ሥራው ይህ ነው።[119]

በማኅበር የሚኖር ግን ኑሮው በእግዚአብሔር ቃል ተስፋ ላይ ይሆናል። ምግቡ የማኅበር በረከት ነው። ተልእኮውም በማኅበር ኀይል ይሆናል፤ የማኅበር መንፈስ ስለሚዘልፈው ለግሉ ክብር አይፈልግም፤ (171ᵘ) እንዲያጠፋም አይተወውም። ሁል ጊዜ ወደ ማመን ይጣደፋል። ስለዚህ ሂደቱ በእግዚአብሔር ቃል ተስፋ ይሆናል። በተስፋ የሚሄድ በሰረገላ እንደሚሄድ ነው። የማኅበር ተግሣጽ

114. መዝ 127: 2።
115. I ጢሞ 5: 8።
116. ሲራ 41: 2።
117. ሲራ 40: 29
118. ሉቃ 11: 2።
119. እዚህ "ሥርዓት" የሚለው የገዳማት መተዳደሪያ ነው፤ ገዳማት የሚቆረቆሩት ሥርዓት በሚያወጡ የመነኮሳት አባቶች ነው። እባ አበክረዙን የሚቃወሙት ከገዳም አየወጡ ብዕዕ ፍለጋ ለብቻቸው የሚኖሩትን ነው።

መስቀሉ ይሆናል። ፍላጎቱን መተውም መሥዋዕቱ ይሆናል። ሁል ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋራ ይኖራል።

ደግሞ እንዲህ ይላል፤

አሁንም እነግራችኋለሁ፤ አዘውትራችሁ ራሳችሁን ከኃጢአት የምታነጹበትን አስቡ፤ ነፍሳችሁ ወደ ኋላ ከሐዘን እንዳትገባ ሕሊናችሁን በከንቱ (ሐሳብ) ውስጥ እንዲባክን አትተውት። ምክንያቱም ሰው እርሻውን ከተዋት ሣርና እሾኽ ይበቅልባታል። በኋላ (ለማረም) ድካምና ሥቃይ ይበዛበታል። (171ᵃ) የሚያነቃችሁ ካለ ሲጠራችሁ እምቢ አትበሉት፤ እንዲህ ሲል ተጽፏልና።[120] ዛሬ ቃሉን ስትሰሙ ልባችሁን አታደንድኑ። የጠራውን ችላ የሚል በኋላ በተግሣጹ ይተከዛል። ሰው ደኻ ሲሆን ባለጸጋን ከማገልገል አይዘገይም፤ የሚከፈለው ዋጋ አለውና። ምንደኛ በታዘዘበት ሰዓት ሲያገለግል ተስፋውን ያገኛል። ባለጸጋም የሰጠውን ተስፋ ሊከለክል አይችልም። ገንዘቡን እንደፈቀደው ቢያደርገው ተፈቅዶለታል።[121] ስለዚህ በጎ ነገር ለመሥራት አትዘግዩ። ሲደርስ ታውቁታላችሁ። የቤቶቻችሁ መስኮቶች ዝግ ይሁኑ። የሌባ ዓይን በውስጡ ያለውን አይይ። ያንን አይቶ ገዳይ እንዳይገባ የምልከቱ ደም በመቃኑ ላይ ይቀባ።[122] ከተዘጋ ቤት ውስጥ የከበረ ዕንቁ ይጠበቅበታል። (172ᵇ) ቤታቸው ክፍት የሆነ ግን የሚገቡበት ብዙዎች ናቸው። ዓይናቸው ገንዘቡን ከሩቅ ይመለከተዋል።[123] ስለ እንደዚህ ያሉት በእበው ምስክራ ውስጥ፥ "ለቤታቸው መዝጊያ የለውም፤ የፈለገ ገብቶ አህያቸውን ፈትቶ ይወስደዋል"[124] ይላል። ስለዚህ ቅዱስ አባታችን ሥርዓት ያወጣልን ይኸንን ሁሉ እንድንል ነው፤ እንዲህ እንዲህ ይመስለኛል። (መስኮት መዝጋት) ከጠላት ጉብኝት (ከምትመጣ) ዳጥ አጥር ናት።

ስለ ጸሎት ማሳረግም እላችኋለሁ፤ ሕሊናን ከማንኛውም ሰብስቦ በጊዜው መፈጸም ያስፈልጋል። ሕሊና ያልሰመደውን (አዲስ ነገር) ወደ መቃኘት እንዳይሄድ፥ (ጸሎታችሁ) ሁልጊዜ ከተለመደበት ቦታ ይሁን፤ (ከቃኘ) የምሥዋዕ መልአክ ይቆጣዋል። ስለዚህ ሕሊናውም ሕግ እንደሚመስክረው ከማንኛውም (172ᵃ) አወላዋይ ነገር ሁሉ ይሰብሰብ። "በሕጉ መሥዋዕት የሚያደርጉ ጻድቃኑን ሰበሰቡለት"[125] ይላልና። የጸሎት ሕግ በሚፈጸምበት እዚያ እግዚአብሔር ይኖራል። ስለዚህ ወደዚያ ለመሄድ (ሁሉም) ይጣደፍ። በአበው ነገር ውስጥ እንደተጻፈው፥ "የእጅህ ሥራ አያሞኝህ።"[126]

120. ማቴ 22: 1-8።
121. ማቴ 20: 15።
122. ዘፀ 12: 13።
123. ኢዮ 39: 29።
124. Victor Arras, *Patericon Aethiopice, CSCO*, vol. 277/53 (1967), p. 4.
125. መዝ 49: 5።
126. ?።

ስለ ሰንበታትና ስለ በዓላት አከባበርም ከጊዜው አስቀድሞ በዋዜማው ሊጀመር ይገባዋል::[127] ቅዱስ እባታችን ማስረጃ ከመጻሕፍት እያመጣልን ያዘዘን እንደዚህ ነው::

ትክክሉን ለማወቅ በአንድ ልብ እንዲተባበሩና አንዱ ለሌላው በመሄድም ሆነ በመመለስ፡ በቃልም ሆነ በሥራ፡ ከልብ ፈቃድ ራሱን ዝቅ እንዲያደርግ፡ እነሆ እንደዚህ በማንኛውም የዋህነት ያስተምራቸው ነበረ:: ምክንያቱም (አነዚህ) (173[ህ]) በቅዱስ ብፁዓዊ እስጢፋኖስ የትምህርቱ ዜና የተወለዱት አዲስ ሕዝብ ናቸው::

ከዚያ በኋላ፡ አግዚአብሔር የእጃቸውን ሥራና የውጪና የውስጥ ድካማቸውን ሁሉ አሳምሮላቸው የመንፈሳዊ ሕይወት ሕያዋን ሆኑ:: ምክንያቱም እሱ ከነሱ ጋራ ይውል ያድር፡ በመሠማሪያቸው ቦታም አብሯቸው ይሠማራ ነበረ:: የሥራ ጥበብንና ልብስ፡ ማጣፊያ፡ ቆብ፡ የአንጀራ፡ የአትክልት፡ የውሐ መለኪያ (እንዴት እንደሚሠሩ) ያሳያቸው ነበረ:: ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከካህናቱና ከዲያቆናቱም ዘንድ እየሄደ ያገልግሎትን ሥራና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የተወሰነውን የንስሐ መመጠኛ ሁሉ ያስረዳቸው ነበረ:: እንዲህም ይላል፤

(173[ሀ]) ከሐሜት፡ ከኑፋቄ፡ ከግጭት እንድትድኑ እንደዚህ አድርጉ፤ ግጭት ካለበት ምሕረት አይወርድም:: የድኽነት ሥሩ ግጭት ነው:: አሁንም እንደ ሐዋርያዊው ቅዱስ ያዕቆብ ቃል፡ "ከናንተ ውስጥ ጥበበኛ ማነው? ሥራውን በጠባዩ ውበት በየዋህነትና በጥበብ ያሳይ:: እርስ በርሳችሁ መቀናናትና መራር ክሕደት በልባችሁ ካለባችሁ አትመኩ፤ እውነትንም ውሸት አታድርጓት:: ይቺ ጥበብ ከምድር፡ ከእጋንንት እንጂ፡ ከላይ የምትወርድ አይደለችም:: መቀናናት ካለበት ቦታ እዚያ ክሕደትና ግጪት፡ የምግባር ክፋት ሁሉም አለ:: ከላይ የምትወርድ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት:: ታራቂ፡ (174[ህ]) ገር፡ እሺ ባይ፡ ምሕረት የሞላባት ሆና፡ የጽድቅ ፍሬዋም ሰላምን ለሚያደርጉ በሰላም ይዘራል"[128]

እንግዲህ ሳለሁ (ብቻ) ሳይሆን ሳልኖርም ቃሌን አስታውሷት:: ሥርዓታችሁንም ጠብቋት፤ ከእግዚአብሔር የተሰጠቻችሁ ተስፋችሁ ናት:: የመነኮሴ ግዴታው ዓይኑን ጨፍኖ በእምነት መታገል ነው:: በእምነት የሚሆን ትግል በውስጡ ድካም የለበትም:: ምክንያቱም፡ ትንሽ ሥቃይ እንዳለፈ ወዲያው ክብርና ስብሐት ይገኝበታል:: ስለዚህ የተመሰገነው ሐዋርያ መልእክት እንዲህ ሲል ይጠራናል፤ "ሳናይ ካመንን ተስፋ እንዳደረግነው ትዕግሥታችን ይታወቃል:: (174[ሀ]) ስለዚህ ድካማችንን መንፈስ ቅዱስ ይሸከምልናል"[129] እንደዚሁ ሌላውም እንዲህ ሲል ያተጋናል፤ "ጥሪያችሁን አጽኑ፤

127. Getatchew Haile, "The Forty-Nine Hour Sabbath of the Ethiopian Church," *JSS*, vol. 33/2 (1988), pp. 233-254.

128. ያዕ 3: 13-18::

129. ሮሜ 8: 25-26::

ሥራችሁ ጽኑ እንድትሆን፥ ሐላባችሁንም እንድትሰጡ ትጉ"[130] ስለዚህ አሳችኋለሁ፤ ኑሮን ለማርዘም አታስቡ። በዚህ ምክንያት የመነኮሴ ልብ (ወዲያው ምንኩስናውን) እንደጀመረ ይደክማል። ያለፈውን ዘመኑን ያስብና ስለሚመጣውም፥ "እኔ እስከ መቼ እንደዚህና እንደዚህ እሆናለሁ" ብሎ ትዝብት በረጅሙ ሲጀምር፥ እንደዚያ እንዳለ ሳይታወቀው ሞት ድንገት ይመጣበታል። አዲሱ ባለቤት በምን ቀን እንደሚመጣ ስለማያውቅ እንዲተጋ[131] የተባለው እኮ ለእንደዚህ ያለው ነው። ደግሞ፥ "ራሳችሁን ዕወቁ፤ በመብላት፥ በመጠጣት፥ ኑሮ በማሰብ ልባችሁን አታደንድኑ፤ ያቺ (175[ሀ]) ቀን በምድር ላይ በሚኖሩ ሁሉ ዘንድ እንደምትጣል ወጥመድ ድንገት ትመጣባችኋለች። እንግዲህ በጸሎታችሁ እንድታመልጡ ትጉ። ዕውቀት ባላቸው በረጅሙ በሚያስቡ የጽድቅ ሥርዓት ትጠነክርባቸዋለች፤ ሆኖም የጨከኑ ይሻገሯታል፤ በአምነት የሚኖሩ የዋሆችም ክብደቷን ላያውቁ ያልፉታል። ስለዚህ የዋሆች፥ ቸሮች፥ የእግዚአብሔርን ቃል አማኞች፥ የወንድሞቻችሁን ጉዳይ (ለመፈጸም) ታዛዦች እንድትሆኑ አነግራችኋለሁ። በሥጋ ለዋቂቶች መታዘዝ ብዙ ትጠቅማለች፤ ፍጹምም ታደርጋለች። ወደ ጥበብ ምክርም ታደርሳለች። የነፍስንና የሥጋን ፍላጎት ሁሉ ትፈጽማለች። ይቺ (ጸጋ) ከጥቂቶች ዘንድ በጭንቅ (175[ለ]) ትገኛለች አንጂ ከብዙዎች ዘንድ የምታድር አይደለችም። በቃሉ ያዳጠው ስው (ጥፋቱን) ላይደብቅ ካመናት ከሚሰሙት ገና በረከት ላይቀበል አስቀድሞ እንደ ቃሉ ስርየት ያገኛል፤ አርምጃውም እንደየዋህነቱ ይሆናል። ይኸ በጭንቅ ከጥቂቶች ዘንድ አንጂ በብዙዎች ዘንድ አይገኝም። ሆኖም ከማዳለጥ ቃልን በትክክል መጠበቅ ይሻላል። ካዳለጠ ግን ማመኑን አይፈር። "ኃጢአትህን መናገር አትፈር"[132] ይላልና። ደግሞ፥ "የእግዚአብሔርን መንገድ በብዙ የፈለገ ሰው ሂደቱ በሱ ይጸናል። ቢወድቅም አያዳልጠውም፥ የእግዚአብሔር እጅ ይደግፈዋልና"[133] ይላል።

ከወንድሞች እንዱ በሥርዓት ጉዳይ ጠብ እንሥቶ (176[ሀ]) ሕሊናውንም ወደ ብዙ ብጥብጥ ሲያመጣራ ቅዱሱ እንዲህ ይለዋል፤ "ስማኝ፥ መልሱን እንድትስጠኝ አንድ ነገር ልጠይቅህ፤ የጻድቅ ኃጢአቱ ምንድን ነው?" ያ ወንድም የሽማግሌውን ሕሊና ስለሚያውቅ፥ "የጻድቅ ኃጢአቱ እኔ ዐውቃለሁ ያለ ጊዜ ነው"[134] ይላል። ሽማግሌው እንዲህ ይላል።

በዚህ ምክንያት ከዕቡያን ጋራ ይቈጠራል። (ኑዛዜውን) በሚሰማው ዘንድ ሞገስ አያገኝም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነችው ረድኤትም መምጣቷን አታፈጥንም። "እግዚአብሔር ዕቡዮችን ችላ ይላቸዋል"[135]

130. 2 ጴጥ 1፡ 10።
131. ማር 13፡ 35፤ ሉቃ 12፡ 36።
132. ?።
133. ?። "ቢያዳልጠውም አይወድቅም" ለማለት ይሆን?።
134. 2 ቆሮ 8፡ 1።
135. ያዕ 4፡ 6፤ 1 ጴጥ 5፡ 5።

የተባለው ቃል በእሱ ላይ ይደርሳል። ሐዋርያው ጳውሎስም ስለዚህ፥ "ዕውቀት ያስታብያል፤ ፍቅር ግን ያንጻል"[136] ይልሃል። ምክንያቱም መፋቀር ምን ጊዜም አያዋርድም፤ አይጥልምም።

ስለ ሌሎችም (176^ለ) የራሳቸውን ታላቅነት ፈልገው መምህራን ለመሆን ስለሚወዱ እንደዚህ ይላል፤ "ዕውቀት (ብቻውን) ሰውን አይጠቅመውም፤ ምግባርም ያለመዓዛ አይጥምም። ዕውቀት በምግባር ሲጣፍጥ ብዙዎች በመዓዛዋ ይሰበሰባሉ። የክርስቶስ መንጋዎች ልብ ስላላቸው መዓዛ ያለውን እረኛ ይከተላሉ። አሁንም መጀመሪያ መዓዛችሁን አሳዩ፤ አለዚያ በከንቱ አትድከሙ፤ ለሰውም እንቅፋት አትሁኑ። የጽድቅ ሥርዓት በሥራ እንጂ፥ በነገር አይታነጽም።

ደግሞ እንዲህ አለ፤

አሁንም አላችኋለሁ፤ ጥበበኛ ሰው የወይን አትክልት መትከል ሲፈልግ የሚሠራውን፥ የት እንደሚተክል፥ ሐረጉ የት እንደሚደርስ፥ (177^ሀ) ድጋፉንም የት እንደሚተክል፥ ደግሞም ዘለላው የት እንደሚጠበቅ አስቀድሞ አያስብምን? እንዲህ ካላደረገ የወይኑ አትክልት አይጠቅምም። ድካሙም ከንቱና ሐዘን (ብቻ) ይሆናል። አንደሚጠበቅ አድርጎ አልሠራምና። እንደዚሁም የሚሠራውን ሳያውቅ የሚያንጽ፥ የሚኖርበትንና የሚያኖርበትን ሳያገኝ ሥርዓት አቋቁማለሁ፥ ማኅበርም እሠራለሁ፥ የሚል ፍላጎቱ አትፈጸምለትም፤ ድካሙም ከንቱ ይሆናል።

አሁንም አላችኋለሁ፤ መዓዛ ያለባት ምግባር ከሩቅ ትታያለች። ብዙዎችም እሷ ዘንድ ይሰበሰባሉ። ስለዚህ አላችኋለሁ፤ መጀመሪያ ስለ ሃይማኖት ስለ ምግባር፥ ስለ መፈቃቀር አስቡ። ሃይማኖት ትረዳለች፤ (177^ለ) ምግባር ታስችላለች፥ ፍቅር ፍጹም ታደርጋለች።

ደግሞ እንዲህ አለ፤

አሁንም አላችኋለሁ፤ ጽድቅን ፈላጊ ሰው የገድሉ ፍጻሜ (የሚያምረው) ድኽነትን የሚወድ ሲሆን ብቻ ነው። እንግዲህ የሥርዓታችሁ መጀመሪያዋ ነፍስን መጣል፥ ፍላጎትን መተው፥ ገንዘብን አለማከማቸት እንደሆነ ታውቃላችሁ። እነዚህ ፫ቱ የነፍስ ሕንጻ መሠረቶች ናቸው። በነዚህ ላይ የታነጸ ሰው የሐዘን፥ የሁከት፥ የድንጋጤ ሞገዶች አያነቃንቁትም። መሠረቱ ድኽነት ላይ ተጥሏልና። ድንጋጤና ሞት ሲመጡበት መሠረቱ ነፍስን መጣል እንደሆነ ይወቅ፤ ሐዘንና ቁጣ ሲመጡበት መሠረቱ ፍላጎትን መተው እንደሆነ ይወቅ፤ ሁከትና የገንዘብ ፍቅር ሲመጡበት (178^ሀ) መሠረቱ ድኽነት እንደሆነ ይወቅ። አንድ ሰው እነዚህን ፫ቱን ሀብቶች ካገኘ ከማንኛው የፍላጎት ጦርነት ይድናል። ብልጽግና፥ ደስታ፥ ዕረፍት ሲመጡበት የሱ አንዳይደሉና በነሱ ላይ እንዳልተመሠረተ ያውቃል።

---

136. 1 ቆሮ 8፡ 1።

በነሱ ምክንያት እይደሰትም። ሳያገኛቸው ሲቀርም በነሱ ምክንያት አያዝንም፤ መሠረቱ ከድኽነት ላይ ነውና። እኔም ድኽነትን ባላስበልጥ ኖሮ በዚህ ውስጥ መኖር ባልተቻለኝ ነበረ።

ደግሞ እንዲህ ይላል፤

እናንተ ወንድሞች ሆይ፥ አሁንም እላችኋለሁ፤ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋራ ሳይፈታተን፥ የሚሆነውንም ሳያውቅ፥ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ኑሮው እንዴት ሊሆን ይችላል? አሁንም እላችኋለሁ፤ እግዚአብሔርን ብትፈትኑት ይሻላል። (178ᴬ) "ለምኑ እሰጣችኋለሁ፤ ታገኙማላችሁ"[137] ብሏል። እግዚአብሔርን ልመና እንድ ጊዜ ብቻ የሚሆን አይደለም። (ልመናዋ በጠበቀበት) ጊዜ ካልተፈጸመች እግዚአብሔር አልመለሰልኝም አይበል። መጽሐፍ፥ "ይመጣል፥ አይዘገይም፤ ከዘገየም አጠብቀዋለሁ"[138] ይላልና። በሌላ ቦታ ደግሞ፥ "እግዚአብሔርን ጠብቁ ጠበቅሁት፤ ሰማኝ፥ መለሰልኝም"[139] ይላል። ስለዚህ ሰው ልመናው ብትዘገይበት አይሰልች። የሆነውን አያውቅም። ብቻ ጊዜው እስኪደርስ ልመናውን አያቁም።

ከዚያም ደግሞ እንዲህ ይል ነበረ፤

አሁንም እላችኋለሁ፤ ይኸንን ሁሉ ከእግዚአብሔር የሆነውን ስጦታ ልብ ካላችሁት ለብዙ ዓመታት ያቆያችኋል። እንደዚህ ሁል ጊዜ የዕርፍት ዘመን አይገኝም። ጊዜው ሲመጣ እንድታስታውሱት፥ እሁን ልብ አድርጉት፤ (179ᵇ) ከናንተ በኋላ ለሚመጡ ምስክር እንዲሆን፥ አይተውም እንዲደሰቱበትና እንደዚያ እንዲያደርጉ፥ ከናንተ በፊት ስለነበሩት ወንድሞቻችሁ ገድልና ጻማ ሁሉ አሁን ጻፉት።

እንደዚህ ለነፍሳቸው የሚገባ የጽድቅ ነገር ሁሉ እያስረዳቸው ቆየ። ሰይጣን ግን እንደለመደ ሁከት ማንሣቱን አልተወም። ቅዱሱም አንዳንድ ጊዜ ወደ ምድረ በዳ ይወጣል፤ አንዳንድ ጊዜ ወደ ገዳም ይመለሳል።

ከዳተኛው ባስልዮስ

ከማኅበር ጋራ በነበረበት በሶስተኛው ዓመት መጨረሻ አንድ መነኮሴ መጥቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ ከናንተ የተለየው ባስልዮስ በልብስ አሸብርቆ የንጉሡን ሎሌ ይዞ መጣ። አብረውት ብዙ ሠራዊት አሉ።" (179ᴬ) ወንድሞች ሲሰሙ በጣም ደነገጡ። "እነሆ፥ ይህ ሰው የመጣው ሽማግሌውን ስሞት አሳልፎ ለመስጠት ነው" አሉ። ምክንያቱም ሊበቀለው (ቂም ይዞበት) ነበረ። ተግሣጽ የሚጠላ፥ በነገር ማሸነፍ የሚወድ ሰው ነበረ። (ቅዱሱ) በማኅበር ላይ

137. ማቴ 7: 7።
138. ምናልባት ዕንባ 2: 3።
139. መዝ 39: 2።

አንዲሰለጥን መብት ስላልሰጠው÷ በዚህ ምክንያት አባታችንን ሊበቀለው (ቂም ይዞበት) ነበረ። ሰውየው ታሪኩ ብዙ ነው፤ ወንድሞቹን እንዳስገደለም በሌላ ቦታ ይነገራል።

(ወንድሞች) ወደ ቅዱሱ ሄዱና በቤተ መቅደስ ቆሞ ሳለ ይሽንን ነገሩት። ጊዜው ከ፫ ሰዓት (ጸሎት) ቀደም ብሎ ነበረ። "ከዚህ ውጣ" አሉት፤ ምክንያቱም መልእክተኛው አፋጥኗቸዋል፤ (ሲነግራቸው) አጠገቡ የደረሱ አስመስሎ ነበረ። እንደተጻፈው እንዲህ ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነው፤ "አባት ሆይ÷ ጊዜው ደረሰ፤[140] (180^{ሀ}) ለአግዚአብሔር ስብሐት ይድረሰው፤ በግ ረኛውን ይገድለዋልና። ይሽም ትልቅ ግፍ ነው።"

(ከቤተ ክርስቲያን) ወጥቶ ከማኅደሩ ተቀመጠ። ወንድሞች መሥዋዕት አሳርገው ሲጨርሱ እሱ ዘንድ ተሰበሰቡ። ሕፃን ልጅ እናቱ ስትለየው እንደሚያለቅስና እንደሚጮህ÷ ትልቅ ለቅሶ÷ ዋይታ÷ እየየ ሳይ ሆኑ። "ምን ያሳዝናችኋል? ተስፋችን ስለ አግዚአብሔር መሞት ነው። አሁንም ለመነኮሴ በሥርዓቱ እንዳለ ከመሞት የሚሻለው የለም።[141] ሥርዓት ለሚሞትላት ነች።"

በሶስተኛው ቀን ከዚያ ወጥቶ ሄደ። በመንገድ ብዙ ችግር ደረሰበት። ምክንያቱም አገሩ ገደል÷ (ዘመኑ) ከረምት÷ ሌሊቱ ጥቅጥቅ ያለ ጭለማ ነበረ። የጉዞውም መንገድ በአረሚ ምድር ነበረ። (180^{ሀ}) (ግን) አግዚአብሔር መንገዱን ሁሉ አቀናለት፤ ሊያደናቅፈው÷ "ከየት መጣህ? ወዴትስ ትሄዳለህ?" ብሎ ክፉ ቃል ለመጠየቅ የደፈረ አልነበረም። ምክንያቱም በሳዩ ሳይ ያለው የመንፈስ ግርማ ያስፈራቸው÷ የሞገሱ ውበትም ለማየት ያምራቸው ነበረ። አግዚአብሔር አብረውት ካሉት መንገድ ከሚመሩት ወንድሞች ጋራ በጽኑ አጅ ጠብቆት÷ አስክ ጊዜው ሊደብቀው ከፈለገበት ሀገር በሶስተኛው ሳምንት በሰላም ደረሰ። ከቀሳውስቱና ከማኅበሩ ታላላቆች በቀር÷ ማንም ሳያውቀው አንድ ዓመት ያህል ተቀመጠ።

ከዚያ በኋላ÷ አዚያ አገር ያሉ መነኮሴዎችና መነኮሲቶች ሁሉ÷ (181^{ሀ}) ምእመናኑም እዚያች አሰበት ገዳም መጡ። ሲያዩት ታላቅ ደስታ ተደሰቱ። "ህብት/ስጦታ ሁሉ በጆ ላለ÷ ሲፈልግ ደግ ነገር ቢሠራ የሚከላከለው ሰሌለ÷ ለአግዚአብሔር ስብሐት ይድረሰው፤ አሱ ለጸለየ ጸሎቱን ይሰጣል። አሁንም ፊትህን እማኅበራችን ማህል እንዲያሳየን ስላንተ እግዚአብሔርን ስንለምነው ይሽው ብዙ ዓመታት ሆነ። ደግሞ ልመናችንን ቸል ሳይል ፊትህን ስለአሳየን የእግዚአብሔር ስሙ ይመስገን፤ ስብሐትም ይድረሰው። አሁንም አግዚአብሔር የእውነት አገልጋይ ስላደረገህ÷ ምዕዳን አስሰማን፤ በምትችሰውም ገሥጸን" አሉት።

ከዚያ÷ "አውነት ለአግዚአብሔር ስብሐት ይድረሰው። ከዚህ አገር ከወጣን እነሆ ይህ ፲፰ኛ (181^{ሀ}) ዓመት ነው። አሁንም አስካሁን የቄየነው ችላ በማለት ወይም በዳተኝነታችን አይደለም። ኑሯችን በስደትና በግፍ እንደሆነ አናንተም ታውቁታላችሁ። እንዳሰብነው ከሁሉ ዘንድ ልንደርስ

140. ማቴ 26፡ 45።

141. ጥቅስ ይመስላል።

አልተቻለንም። ግን እኔም ስጸልይ እንደናንተ፥ "እምላኬ ሆይ፥ ኑሯቸውን እንዳይና እንዳውቅ እንዴት ነው የምታደርሰኝና ከማህላቸው የምታቆመኝ?" እል ነበር። አሁን እነሆ የእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጸመ። አሁንስ ኑሯችሁ እንደምን ነው?" አላቸው። "ኑሯችን በምግባር ላይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ተስፋ በማድረግ በእምነት ነው" አሉት። እሱም እንዲህ አላቸው፤

> የእግዚአብሔርን ቃል ከማመን የሚበልጥ የለም፤ እሱ ራሱ፥ (182ᵁ) "ለሚያምን ሁሉም ነገር ይቻላል"[142] ብሏል። አሁንም ለነፍሳችሁ ሕይወት እንድታገኙ በዓለም ውስጥ መንቀሳቀስን ተዉ። የአበው ነገር፥ "ሕዝባውያንን ማየት የመነኮሳትን ልብ ያደክማል"[143] ይላል። እናንተ በራሳችሁ ገዳም በድካማችሁ ኑሩ። እግዚአብሔር እሱ ራሱ በፈቀደው ያኖራችኋል። እስቲ አግዚአብሔርን ፈትኑት፤[144] እንደዚህ ማድረግ አይቻለውምን? ብቻ በዚህ ጽኑ፤ ለሚያፈቅሩትና ትእዛዙን ለሚጠብቁ (የፈለጉትን) መሥራት እንደሚችል እመኑ። አሁንም አሳችኋለሁ፤ ለተጠሩ ብዙዎች የተሳከች የሰማይ ጸጋ ጠባቧን ታግሠው ስፈውን ተስፋ ለሚያደርጉ ጥቂቶች ምርጦች ትሰጣለች። (182ᴬ) ስለዚህም ነገር ከአበው አንዱ የታጋዮች ጸጋ ከሚለለቹ (ተወሰዳ) ለታገሡት ለትሰጣቸው እንዳለ ተጽፏል።[145] አሁንም፥ "በትዕግሥታችንና መጻሕፍትን በመተማመን ተሰፋችንን እናገኛለን" ያለውን ስሙት[146]። ግን አላችኋለሁ፤ በዚህ ካልታገሣችሁ እናንተ የኔ አይደላችሁም፤ እኔም የናንተ አይደለሁም። ቅዱሱ አባታችን የሰጠን ሥርዓት እንደዚህ ነውና--እያንዳንዱ ሌላውን ወደ ስሕተት እንዲሄድ እንዳይተወው። ስለዚህ አላችኋለሁ፤ በሰው ገንዘብ አትሳሳቱ።

እንደዚህ በምዕዳንና በተግሣጽ ሁሉ ሲያሞቃቸው ቆየ። ከዚያ በኋላ፥ ወደ ደብሩ ተመለሰና የወንድሞችን የማኅበራቸውን ሥርዓት ሁሉ--ስለ ተግባርም፥ (183ᵁ) ስለ ቤተ ክርስቲያንም፥ ስለ መነኮሴዎቹና ስለ መነኮሲቶቹ መውጣት መግባት--እንዲህ እያለ አስተካከለ፤ "ሳትጨምሩም ሳታሳድሉም በጽድቅ ሥርዓት ቁሙ። ምክንያቱም በሥርዓታችሁ እንዳላችሁ መሞት ይሻላችኋል። እግዚአብሔር ሲፈቅድ ሕይወታችሁን በሥርዓታችሁ እንድትኖሩት ያዘጋጅላችሁ፤ የጃችሁንም ሥራ እሱ ይባርክ። እንግዲህ አትጠራጠሩ፤ ከእግዚአብሔር ጋራ መኖር ይሻላችኋል።"

ሩቅ ለሚኖሩት ወንድሞችም እንዲህ የሚል የተግሣጽ ጠማር ላከላቸው፤

---

142. ማቴ 21: 22።

143. Victor Arras, *Patericon Aethiopice, CSCO*, vol. 277/53 (1967), p. 63.

144. በግዕዝ "ፈተነ" እና "አመከረ" የተለያዩ ናቸው፤ በአማርኛ ግን ሁለቱም "ፈተነ" ናቸው። "አመከረ"ን "ተፈታተነ" ብሎ መተርጉሙ ይሻል ይሆናል። ወደ እንግሊዝኛ ቢተረጉሙ፥ "ፈተነ" "to test"፥ "አመከረ" "to tempt" ይሆናሉ። ማቴ 4: 7 የሚከለክለው ፈተና "አመከረ" ("ተፈታተነ") የሚለውን ነው፤ "ኢታመክሮ ለአግዚአብሔር አምላክከ"።

145. ?።

146. ?። ይኸንን ያሉት አባ አስጢፋኖስ ይሆናሉ።

እሁንም እናንተም በጽድቅ ሥርዓት ከኖራችሁ እኔም አብራያችሁ አለሁ፤ እናንተም ከኔ ጋራ አላችሁ። በአባቶቻችሁ (183ᴬ) የጽድቅ ሥርዓት ሁሉ ካልሄዳችሁ ግን ከድካማችሁ ንጹሕ ነኝ። በዚህ ምክንያት አይኩንንኝም። (ሲጠይቀኝ) እንዳስተማርኩ፥ እንደነገርኳችሁም እናገራለሁ። እሁንም መነኮሴዎችም ሆናችሁ መነኮሲቶች በመንፈሳዊ አባታችሁ ሥርዓት እንዳላችሁ ብትሞቱ .. ይሻላችኋል። መጽሐፍ፥ "ካብ የሚንድ አባብ ይነክሰዋል"[147] ይላል። በሌላ ቦታ ደግሞ፥ "አባቶችህ የሠሩትን ሥርዓት አትናድ"[148] ይላል። እንደዚሁ አሁንም ወደ ፊተና እንዳትገቡና የመንፈሳዊ አባታችሁን ሥርዓት እንዳትንዱ። አንግዲህ መጥፋትን ከፈለጋችሁ (ጉዳቱን) በኋላ ታገኙታላችሁ፤ አሁን (እርግጥ በሕይወት) ትንሽ ያስቆያችኋል። ለለሚጣሏችሁ ታገሡ፤ ምክንያቱም (184ᵁ) ትዕግሥት ያለውን እግዚአብሔር አይተወውም። የቀድሞዎች ብዙዎች የተከተሳቸውን ደስታ ያገኙት ትዕግሥታቸውን በማራዘም ነው። እንደዚሁ አሁንም የመሥዋዕቱ ዕጣን በሠመረበት እግዚአብሔር ይኖራል። የሚታበየውን በትሑቱ እጅ ያስገዛዋል።

እንደዚህ ሁል ጊዜ በጽድቅ ቃል ሁሉ ምዕዳን ያስሰማ ነበረ። እንዲህም ይል ነበረ፤ "እንግዲህ አሁንም እናንተ ወንድሞች ሆይ፥ ትጉ፤ ምክንያቱም ልባዊ ትጋት ሁልጊዜ እይገኝም። ከደብሩ ከጫፉ እስከትደርሱ ድረስ ትጉ እንጂ ከሞኑ ቁሞ አትበሉ።"

ከወንድሞች አንዱ ሰምቶ፥ "እኔስ እውጪ በሀገር (ከምገኝ) ይልቅ በደብሩ (በተራራው/በደብሩ) ሞን ብገኝ ይሻለኛል እላለሁ፤ ደብር መውጣት ግን ይርቅብናል" አለ። ሽማግሌው፥ "በደብሩ እራዊት ያገኟችኋል፤ ግን በድንጋይ (184ᴬ) ተደባዳቢዎች ጥቂቶች ናቸው" አለው።[149]

ለቅርቦቹም ለሩቆቹም እንደዚህ ይነግራቸው ነበረ። እንድ ጊዜ ወደ ምድረ በዳ ይሄዳል፤ እንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ደብሩ ይመለሳል። ያ የውሸት አሳባቂ በፊት እንዳደረገው፥ ህገር ለማበላሸት የቅዱሱን ዜና በደረሰበት ይሰልል ነበረ። (በፊት) የእግዚአብሔርን የመሠዊያ ቦታ አቃጠለው፤ የወንድሞችን የድካማቸውን (ፍሬ) ለእርዳታ ባመጣቸው የንጉሡ ሠራዊት አስከብቦ እጠፋው። የፊለገውን ሁሉ ፈጽሞ ወደ ንጉሡ ተመለሰ።

ደግሞ እንደገና እርዳታ ይዞ መጣ አሉ፤ ምክንያቱም በፊት ስላሳገኘው ከንጉሡ እና ከመነኮሳቱ ዘንድ እጥብቆ የውሸት ነገር ያሳብቅ ነበረ። ወንድሞች በሰሙ ጊዜ፥ (አባ አበክረዙንን፥) "እዚች ህገር እንዳለህ ተሰምቷልና ወደ ምድረ (185ᵁ) በዳ ዞር በል" አሉት። ወደ ምድረ በዳ ሄደ። እዚያ ባለበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እያሳየው የሚሆነውን ሁሉ ያውቅ ነበረ። መንፈስ ቅዱስ ያናገረውን ብዙ ነገር ተናግሯል። ስለ ልዑሉ የሕጉ ሥርዓት (በጸሎትና በስግደት) በጣም ይተጋና ይደክም ነበረ። ማታ ስለሰማው ነገር

147. ?።

148. ምናልባት፥ Victor Arras, *Collectio Monastica, CSCO*, vol. 238/45 (1983), p. 151.

149. ምክሩ፥ "መነኮሴ ብዙ ፈተና ካለበት መገኘት አለበት" ነው።

"ጠዋት አደርገዋለሁ" ብሎ (አያሳድርም)፤ ጠዋት ስላወቀው "ማታ አደርገዋለሁ" ብሎ (አያውልም)። "ነገ የምትወልደውን አናውቅም" ይላል።

ከማይድን በሽታ ላይ ወደቁ

እንደዚህ ሲኖር ሚያዝያ ፭፱ ቀን ከበሽታ ላይ ወደቀ። የምዕዳን ቃል ማብዛት ያዘ፤ ከዚህ ዓለም እንደሚወስዱት ስላወቀ፥ ልጆቹን ያዘጋጃቸው ጀመረ። ዕዝራን፥ "ከሰው ማህል ይወስዱሃልና ቤትህን አዘጋጅ"[150] አንዳለው፥ (185ʌ) ይኸም አባታችን (ይህ ከመሆኑ) በፊት በትግራይ ምድር ያሉትን ወንድሞች ሁሉ አየዞረ (ጎበኘ)። ልጆቹ ቃሉን አልሰማንም፥ ፊቱን አላየንም እንዳይሉ ከሁሉም ዘንድ ዞረ። ለመዳን ለሚፈልጉ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያደርሰውን፥ ሊያደርገው ለማይፈልግ ደግሞ የሰማው ቃል ምስክር እንዲሆንበት (ሰሁሉም) ትክክለኛውን የጽድቅ መንገድ አሳያቸው። በሽምግልናውና በድካሙ ምክንያት ሊሄድበት ከማይችለው ከሩቅ (ሳሉት) እንዲህ ሲል ቃሉን ይልክላቸዋል፤

> ከፈለጋችሁ ወደዚህ ወደ ወንድሞቻችሁ ኑ፤ መምጣት ካልፈለጋችሁ ነፍሳችሁንና ሥጋችሁን ጠብቁ። ሕሊናችሁን ንጹሕ አድርጉ፤ መንገዳችሁን አቅኑ። የፈጣሪያችሁን ሥርዓት አታበላሹ፤ (186ᵇ) በአጃችሁ ሥራ ኑሩ፤ የሌላ ሰው የድካም (ፍሬ) አትውሰዱ። ከሰው ኃጢአት አትካፈሉ። ቤት በዓመፅ አትሥሩ፤ ወንድሞቻችሁን አየጠላችሁ ቤት በዓመፅ መሥራት አይጠቅማችሁም። በአባታችሁ ሥርዓት ውስጥ ማመፅ የለም። ከተቻላችሁ ይኸንን ጠብቁና ባላችሁበት ኑሩ። ካልቻላችሁ ግን በመንፈሳዊው አባት ሥርዓት ከወንድሞቻችሁ ጋራ በምድረ በዳ መሞት ይሻላችኋል።"

ለሩቆቹም ለቅርቦቹም ይኸንን ብዙ ጊዜ ያሰማቸው ነበረ። ቃሉን አልሰማሁም፥ አልነገረኝም የሚል የለም። እሱ ራሱ፥ "ይህ ቃል ምስክር እንዲሆንባቸው እኔም ችልተኛ እንዳልሆን እነግራቸዋለሁ" ይል ነበረ። ደግሞ እንዲህ ይል ነበረ፤

> እኔም በሰው (186ʌ) ኃጢአት እንዳልኮነን እንግዲህ ያልነገርኳቸው ምን ተርፎኛል? ምክንያቱም፥ የቃሉን ማሰሪያ በሳዬ ላይ ስላጸና፥ የዚያ መንፈሳዊ አባት ቃል በጣም ያስፈራኛል፤ "ይኸንን ሥርዓት ሁሉም ቢተዉት፥ ብቻዬን ቀረሁ፤ እኔም አሄዳለሁ፤ ብቻዬን አልቆምም አትበል" ብሎ ይኸንን የቃል ማሰሪያ በኔ ላይ ትቷል። አሁንም እስከዚች ሰዓት ላደረሰኝና ከዚህ መንፈሳዊ አባት ቃል ማሰሪያ አንዳልሸሸ ለጠበቀኝ አግዚአብሔር ስብሐት ይድረሰው። ለትልቁም ሆነ ለትንሹ፥ በቅርብ ላለውም ሆነ በሩቅ ላለው፥ በልብስም ሆነ በምግብ ወይም በማንኛውም ነገር (ትእዛዝ) ያከበድኩበት የለም። (187ᵇ) በማህላቸው ስለ አግዚአብሔር ፍቅር ደከምኩ አንጂ የነዘነዝኩት፥ ያስገደድኩት፥ ያደከምኩት የለም። በኔ የተመኩም

150. ሱቱ 14፡ 13-14።

የሉም፤ የረዳኝን እግዚአብሔር ይርዳው። እኔ ዛሬ የሰማኒያ አንድ ዓመት ልጅ ነኝ። አሱ አምላክ ከፈቀደ ወደሱ ከመሄድ የሚሻለኝ የለም። በተቻለኝ መጠን ልቤን በማህላቸው አስፋኋት እንጂ ያደላሁለት የለም፤ የከፋሁበትም የለም። ቸል ያልኩትም የለም።

ይሽንንና ይሽን የመሰለ ስላለፈውም ስለሚመጣውም ብዙ ተናገረ። እነዚህን የያዝናቸውን ጥቂቶቹን ከማስታወስ በቀር ሁሉንም ለማጽናት አልቻልንም። ምክንያቱም ሁሉም ወደ ትካዜና ወደ ሐዘን ገብቶ ነበር። (187ᴬ) አሱ ግን እንዲህ ሲል ይገሥጽ ነበረ፤ "ቃሌን መስማትና ወንድሞቻችሁን ምዕዳን ማሰማት ትታችሁ ወደ ሐዘንና ወደ ትካዜ መግባት አይጠቅማቸሁም።"

ከዚያ፥ በሽታው ጸናበት። በአሱ አጠገብ ያሉት ሁሉ አሱ ዘንድ ተሰበሰቡ። ቄሶቹ፥ ዲያቆኖቹ፥ አብረውት የነበሩ ወንድሞች፥ ከማኅበርም ታላላቆቹ ሊጠይቁትና ሁኔታውን ሊያዩ ወደሱ መጡ። ከታመመ እንሥቶ እስከዚያች ዕለት ድረስ ፳፭ ቀን ሆኖ ነበረ። ያን ጊዜ ግንቦት ፲፱ ቀን ነበረ።

ከዚያ በኋላ፥ ወንድሞች እንዲህ አሉት፤ "እኛ በምድረ በዳ በሥርዓታችን እንዳለን እንሞታለን። ያላንተ መኖር አይቻለንም።" አሱም እንዲህ ሲል አሳያቸው፤ "ፎ የምንኮስና በሮች ተዘጋጅተው አሉላችሁ። እነዚህም (188ᴮ) በጽድቅ ሥርዓት መታገል፥ በነገሥት አደባባይ የሰማዕትነት መንገድ፥ ወይም ደጎች አባቶች በገለጡት በገዳም መዘጋት ናቸው። ከነዚህ መንገዶች በሚቀናችሁ (ባንዱ) ሂዱ፤ አድርጉትም።" ወንድሞች፥ "በምድረ በዳ መሞት ትሻለናለች" አሉት። አንዳዶቹ፥ "በሥርዓት እንታገላለን" አሉት።

ከዚያ ደግሞ፥ በዚሁ ወር በ፳፪ መንፈስ ቅዱስ ገለጸለትና እንዲህ አለ፤ "የጽድቅ ፈለግ እንዳልተዘጋ እንድታውቅ፥ አሱ ከቃሉ እያመጣ ይነግረናል እንዳትሉ ምስክር አቁሜ እንድነግራችሁ የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት አምጡ። አሁንም ጉባኤ አድርጉ፤ (188ᴬ) መነኮሴም ሆነ መነኮሲት ከቃሉ አልሰማንም እንዳይሉ ከበሽተኞችና ከማኅደር ጠባቂዎች በቀር ማንም ሳይቀር ሁሉም ይምጣ።"

ከዚያ፥ በዚያው ወር በ፳፫ ቀን ታላቅ ጉባኤ አደረጉ። መጻሕፍቱንም እንዳላቸው አመጡ። ማኅበሩ ሁሉም እንደመጡ ሲያይ እንዲህ አለ፤ "ከፍተኛ መንበር የተዘጋጀው ሰዎች እንዲሰሙ አድርገው የእግዚአብሔርን ቃል ለሚናገሩ ለእንደዛሬው ቀን ነው። ዲያቆናት የኤጲስ ቆጶስ ቃል ለሕዝብ እንዲያሰሙ የተዘጋጁት ለእንደዚህ ያለው ቀን ነው።" ይሽንን ያለው በበሽታው አልጋ ላይ ስለነበረና በድካሙ ምክንያት ቃሉን ከፍ ማድረግ ስላቃተው ነው።

ከወንድሞች አንዱ፥ "እንዲሰሙ እንዳች ቃል እንድትናገር ተነሣ" አለው። ቃሉን ለተሰበሰቡት ለመናገር ተነሣ። ሆኖም ድምፁን ከፍ ማድረግ አቃተው። ብቻ (189ᴮ) ሁሉንም በደካማ ቃል ይነግረዋል፤ ያ ወንድም ድምፁን ከፍ አድርጎ በጎላ ቃል ይደግመዋል።

ከዚያ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ጎይል ጎይል አገኘ፤ ጠነከረም። ያዕቆብ እሥራኤል ለመሞት በቀረበ ጊዜ ጎይል አግኝቶ፥ "ልጆቼ ተሰብሰቡ በኋላ

ዘመን የሚያገኛችሁን እነግራችኋለሁ"[151] እንዳላቸው፥ እንደዚሁ ይኸም ሽማግሌ እባታችን በመንፈስ ጎይል ጎይል አገኘ፤ ጠነከረም። "ታላቅነቱን እንድንናገር ሁላችንንም የሚስበስበንን ይኸንን ምድረ በዳ ሰሰጠን እግዚአብሔር ስብሐት ይድረስው" አለ። መጀመሪያ የአቡነ ቅዱስ ብፁዓዊ አስጢፋኖስን ውዳሴና ሥርዓቱን ከፍ ከፍ እያደረገ አስታወስ። "ስሥርዓቱ ምንም እንከን እንደሌለበት እኔ ምስክር ነኝ" አለ። እንደሚገባው በጣም አመሰገነው።

ደግሞ (189^ለ) ለልጆቹ እንዲህ አላቸው፤ "አሁንም እናንተ በምን ምክንያት ነው ያላንተ መኖር አይቻለንም፤ እንሞታለን የምትሉት?" እንዲህም አለ፤ "ይኸ ከሁሉ የበለጠ ያሳዝነኛል። የሚያፈቅሩት እንዲሄዱበት እግዚአብሔር ቀድሞ ያዘጋጀው የጽድቅ በር እኔ ዘንድ ሲደርስ ይዘጋልን?" ከዚያ፥ (ድምፁን) ከፍ አድርጎ ጻድቃኑን አነሣ። የሙታን በኵር በሆነው በአቤል በመጀመር እንዲህ አለ፤

> አቤል ሲሞት ከሱ በኋላ የጽድቅ ፈለግ ተዘጋን? ክሱ በኋላ የጽድቅ ተክል ሴት አልተወለደምን? አባቱ አዳም፥ "እግዚአብሔር በአቤል ምትክ ዘር አነግልን"[152] አለ። ከሱ በኋላ ሄኖክ ቆመ፤ መላእክትን ስለ ኃጢአታቸው አስኪዘልፋቸው ድረስ ምድራዊ መልአክ ሆነ።[153] ከሱ በኋላ (190^ሀ) ኖኅ ተተከለ፤ በሱም ምድር ታደሰች። ጽድቅንም አዳኗ ሆነ፤ ኪዳኑም ላቀ፤ ጠናም። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የፈጣሪ ወዳጅ የተባለ አብርሃም (መጣ)። ከዚያ ደግሞ የማለላቸውና ከነሱ ጋራ ኪዳን ያቆመላቸው ይስሐቅና ያዕቆብ (መጡ)። ከዚያ፥ ሙሴ ሕግን ተቀበለ። ደግሞ ኢያሱ የሙሴን መንፈስ ተቀብሎ ምድረ ርስትን (ለእስራኤል ልጆች) አወረሳቸው። ነቢያት ሁሉ በሕይወታቸው እግዚአብሔርን አስደሰቱት። ኤልያስስ ወደ ሰማይ ሲያርግ መንፈሱ በረዳቱ በኤልሳዕ ላይ አላደረችምን? ከጌታችንም በኋላ የሃይማኖት አለት ድንጋይ ጴጥሮስ ተሾመ፤ ከሱ ቀጥሎ ቀሴምንጦስ በሱ ወምበር ላይ ተቀመጠ።[154] ከጳውሎስ በኋላ (190^ለ) ጢሞቴዎስ (ወረሰ)።[155] ከነሱ በኋላ ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን መምህራን ተነሡ። (ጽድቅ) እንደዚህ በየትውልዱ (ከጻድቃን) ወደ ጻድቃን ነፍስ ትሸጋገራለች። የእግዚአብሔር መንፈስ ለትውልደ ትውልድ ነች እንጂ ያንድ ጊዜ ብቻ አይደለችም። ከነሱም በኋላ ደግሞ በዘመናችን በትግላችን ጊዜ ረዳት እንዲሆነን እግዚአብሔር አቡነ አስጢፋኖስ አስነሣልን።[156]

---

151. ዘፍ 49: 1።
152. ኩፋ 4: 25።
153. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10 ከመጀመሪያው ላይ መነኮሳትን "ምድራውያን መላእክት" ይላቸዋል።
154. ምንጮቹ ሁሉ በዚህ ይስማማሉ፤ ከነዚህም አንዱ የአባ ጊዮርጊስ ስዓታት ነው።
155. አንዳለፈው።
156. አንዳቸውንም ሌሎቹን የኢትዮጵያ መነኮሳት፥ ለምሳሌ የደብረ ዳሞውን አባ ዮሐኒን፥ የደብረ አስቦት/ደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አያነሡም።

ይኸንን ካለ በኋላ ዝክራቸውን ያነሣው (ጻድቃን) ያሉባቸውን መጻሕፍት አንብቡ አሰ። ደግሞ ከማቴዎስ ወንጌል ጌታ ከተነሣ በኋላ ሰደቀ መዛሙርቱ በተገለጸላቸው ጊዜ ሰደቀ መዛሙርቱ÷ "የሰማይና የምድር ግዛት ለኔ ተሰጥቷል፤ ሂዱና ለአሕዛብ ሁሉ አስተምሩ፤ ስታጠምቋቸው÷ (191ᵘ) በአሙ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በሉ፤ ያዘዝኳችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው። አኔም እስከ ዓለም መጨረሻ በሁሉ ዘመን አብሬያችሁ አለሁ"[157] ያሰውን ቃል እንዲያነቡ ነገራቸው። ከዚያ÷ እንዲህ አላቸው፤

> ይህ ሁሉ የተነገረው የመለኮት ቃል ለዚያን ጊዜ ዘመን ብቻ አይደለም፤ ለኛም ዘመን ነው እንጂ። ሰው ጸጋ በሌላ ሰው ላይ አይቶ እሷን ለማግኘት ለሱ እንደማይቻለው ሲያውቅ ቀንቶበት ገደለው። ምድርም የተገደለውን ሰው ደም ጠጣች። ስለዚህ÷ "የእቤልን ደም ለመጠጣት አፏን የከፈተች ምድር የተረገመች ትሁን"[158] የሚል ቃል በላይዋ ላይ አረፈ። <u>እንደዚሁ እስከ ዛሬ ድረስ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠውን ለመውሰድ የሚፈልግ የሰው ልጅ (191ᴬ) ለጓደኛው በጎ ነገር እያሰብም።</u> ጓደኛው ሰው ብቻ ሳይሆን÷ እግዚአብሔርም በጠባዩ እንዲተባበረው ይፈልጋል። በነቢዩ የተጻፈው እንደሚለው÷ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን÷ "ኃጢአት እሰገራችሀን? እኔም እንዳንተ እንድሆን አሰብክን?" አለው። በድንጋይ ሰሌዳ የተጻፈች የእግዚአብሔር ሕግ÷ "ጓደኛህን እንደራስህ እድርገህ ውደድ"[159] ትላለች። <u>አሁንም የሌላውን ጸጋ ለመውሰድ የሚፈልግ ሰው ሳይቻለው ሲቀር ምኞት÷ ቅናት÷ ቁጣ÷ ሁከት ይመጡበታል።</u> ይህ ሰው እነዚህ ከሰይጣን እንደሆኑ ይወቅ። (192ᵘ) (ከሰይጣን) ተቀብሏቸው እንደ ምድር በሕሊናው ይጠጣቸዋል። በዚህም ምክንያት ሰለ አቤል ደም የተነገረው እርግማን ይመጣበታል።
>
> አሁንም ደግ ለሚሠራ የመጻሕፍት ምስክራ እነሆዋችሁ። ታዲያ ለምን እንሞታለን÷ እንሞታለን ትላላችሁ? ፈለጌንም ልትዘጉት ትፈልጋላችሁ። ከጽድቅ መንገድ እጓድየባችሁ እንደሆነ ዛሬ በእግዚአብሔር ፊት ግለጹልኝ፤ ሁሉንም በፊቴ ተናገሩ። የጽድቅ መንገድ ሳይጎድል ሙሉ ሁኖ ተዘጋጅቶላችሁ የለምን?"

ወንድሞች እንዲህ አሉት፤ "አንተ ያጐደልክብን የለም። የአባታችን ሥርዓትም ጉድለት የሌለበት ሙሉ ነው። ኢያሱ ከሙሴ አንሷልን? ምድረ ርስትን ተዋራሽ÷ ለሕዝብ አካፋይ÷ (192ᴬ) በጠላት አገር ሳይም÷ ከጦር የተረፉትን (ባለቤቶቹን) ገባሮች አድርጎ (ምድር) ሰኪ አልሆነምን? በአምኑቱ ጎይል እንደዚህ አይሷል። ኤልሳዕም ከመምህሩ አሳነሰም። ኤልያስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ባሕርን የተሻገረው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ኤልሳዕ ካንዲም ሁሰቴ ተሻግሯል። ለነሱ እንደሆነው ሳንተም የሃይማኖትህ ጎይል ጸንቶልሃል። የትምህርትህ ውበት በኢትዮጵያ ምድር ሁሰ በሰፊው

157. ማቴ 28: 18-20።
158. ኩፋ 4: 11።
159. ሌዋ 19: 18።

ተዘርግታለች። ብቻ በእስራኤል (መጽሐፍ) ተርጓሚዎች ባለቁ ጊዜ በሕዝበ ርስት ላይ የደረሰውን ከመጻሕፍት ስናውቅ እንፈራለን÷ እንደዚሁም ጌታ÷ የዓለም ማለፊያ ሲደርስ "ብዙዎች ሃይማኖታቸውንና ፍቅራቸውን ይተዋሉ። ከክፋት መብዛት የተነሣ ፍቅር ከብዙዎች ዘንድ ትጠፋለች"[160] ብሏል።

ሰባቱ የምንኵስና መንገዶች

(193ᵘ) "በእስራኤል ዘንድ ስለሆነው የምትሉት (የደረሰው) በሕዝብ ኃጢአት ነው ወይስ በነቢይ?" አላቸው። "በሕዝቡ ስሕተት ነው እንጂ በነቢይ ኃጢአትስ አይደለም" አሉት፤ ከዚህ በኋላ እንዲህ አላቸው፤

> የቀድሞውን እንድታውቁት÷ ሕጋቸው እንድ ነው--የፍርድና የሥርዓት ሕግ። በሕግ ምስክርነት እንደተጻፈው (ሰው) በሠራው ይፈረድበታል።[161] አሁን ግን እንደዚህ አይደለም፤ በረከቶቹ ሁሉ ሰዎች ግፍ እድርሰውባችሁ የምትቀበሏቸው ናቸው። ፫ መንገዶች አሏችሁ። እንግዲህ በፍላጎት ተቀበሏቸው፤ አንዷ መንገዷ ግፍ በመቀበል ካልሆነ የማትገኝ ጠባብና አሰጨናቂ የሆነች÷ ከውጭዋ የተደበቀች ቅድስት የምንኵስና ሥርዓት ናት፤ ሁለተኛዋ ለማዕትነት ያለባት ነች፤ ሰው ብፅዐቱን ከመተው ይልቅ (193ᵃ) ጦርና ሠይፍ በእጃቸው ውስጥ ያለ የነገሥትና የእገሪ ገዢዎች ግርማ ሳይፈራ ይሞታል። ደግሞ አሳትና÷ በድንጋይ መወገር÷ የእንበሶች ኃይል አና ሌሎችም በግርፋትና በእስራት÷ በነሐስና በብረት ማነቆ የሚመጡ ቅጣቶች አሉባት፤ ይኸም የሚገኘው ግፍ በመቀበል ነው። ሶስተኛዋ ከሰው ወደ ራቀች ምድረ በዳ ፈልሶ በጽሙና መኖር ነው። እሱም ግፍ (በመቀበል) ነው። እነሆ ፫ቱ የተገፉ ሰዎች መደገፊያዎች እነዚህ ናቸው። ከኃጢአት የሚሸሽ ሁሉ ወደነሱ ይሂድና ጠላት እንዳይገድለው ራሱን ይክሰስ። አሁንም ቃሌን ስሙ፤ ልብም በሉ፤ የሚሞትን ሰው ነገሩን ይሰሙታል። ብትሰሙ ሕይወት ታገኛላችሁ፤ ካልሰማችሁ (194ᵘ) ኮነኔ ይደርስባችኋል። እኔ ከማልፈራበት (እድሜ) ደርሻለሁ። ስለዚህ የሚጠብቃችሁን ስለማውቅ ቃሌን አልሰማንም እንዳትሉ ጉሮሮዬን እየመረረኝ በድፍረት እናገራችኋለሁ።

አነሱም የጽድቅን ነገር ሁሉ የተቻለውን ያህል እንዲህ አሉት፤ "እግዚአብሔር ይርዳን፤ ከዚች ሥርዓት (ወጥተን) የት እንሄዳለን? ልባችን በቃልህ ተጽናንቷል። አንተ ብትሞትም ብትኖርም ይህቺ ቃል ለኛ ትበቃናለች።"

ቃላቸውን ሲሰማ÷ "እንግዲህ እግዚአብሔር ሊሆን የሚገባውን እንዲያደርግ ጸልዩ" አላቸው። (194ᵃ) "እንዴት እንደምንጸልይ አንተ አባባየን፤ አንዳንዶቻችን ሁላችን እንድንጸልይበት በቀኖና (የጸሎት)

160. ማቴ 24: 12።

161. ለምሳሌ÷ ኢዮ 34: 11።

ጎርመት[162] እናውጣ እንላለን፤ እንዳንዶቻችን ደግሞ ሁሉም እንደተቻለው ይጸልይ እንላለን። ስለዚህ ትክክሉን አንተ አሳየን" አሉት። ቅዱሱ እንዲህ አላቸው፤

> ከአንዲት ጎርመትስ ሁሉም ሊደርስ አይችልም፤ ሁሉም ለያንዳንዱ እንደተቻለው ይጸልይ። የማየው ለቅሏችሁ ግን እንዲህ አይሁን፤ እግዚአብሔርን እንደሚፈታተነው አትሁኑ። ቢወስዱት የሚሻለውን ስለሚቀሩት ተብሎ አይከለከልም። ብቻ አሁንም ይኸንን ከኔ የሰማችሁትን ኪዳን ጠብቁ። በመገሠጽም ሆነ ምዕዳን በማስማት፥ ስለ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ስለ ማኅበር ሥርዓት፥ ለቅርበቹም ሆነ ለሩቆች ያልነገርኳችሁ የቀረ ነገር የለም። (ስለ ቦታ ርቀት የምለው) በብዙ ሀገሮች ስለተበተኑት ነው። አንዳንዶቹ ራሳቸውን ለወንድሞቻቸው እንዳያስገዙ (195^{ሀ}) ፍቅር አጥተዋል። አንዳንዶቹ የመስቀልን መንገድ አጥተውታል። ሁሉም የሚሻለውን ራሱ ያውቀዋል፤ እኔ የምለው በየዕለቱ ስላየሁት ነው። አሁንም የብዙዎች ወንድሞችንና ከመነኮሲቶች የብዙዎቹን አኗኗራቸውን አውቃለሁ። የአንዷንማ የሁል ጊዜ አኗኗሯን አውቃለሁ። "አንተ ከማን ነህ? ስምህ ማነው?" የሚል የምርምር ቃል ላይደርስባት አስፈሪውን የሰማይ በር (ለተት ብላ) የምትገባ እሷ ናት። ሌሎች ጻድቃንና ንጹሐት ግን ያለመመርመርና የመጣበትን ሳያለታውቅ፥ የክርስትና ወይም የምንኵስና ስሙን (ሳይናገር) የሚያልፍ የለባቸውም። ይህች ግን ከሥጋ ፍትወት ሁሉ ምንም ነውር አልተገኘባትም። እኔ ስለሷ ምስክር ነኝ። (195^{ለ}) ያችን በር ሳይመረመሩ የሚገቡ ስለ በጉ ደም ለሞት እስኪበቁ ድረስ ነፍሳቸውን ያሳሰቀደሙ ሰማዕታት ናቸው።

ይኸን ተናግሮ ወደየአድባራቸው አንዲመለሱ እንዲህ ሲል በሰላም አሰናበታቸው፤ "አሁን እንግዲህ እንዳርፍ ተዉኝ። ለእግዚአብሔር ስብሐት ይግባው፤ ብዙ አገሮች ዞሬ ለዕረፍቴ ይኸንን ምድረ በዳ ስጠኝ። አሁንም ሂዱ፤ እግዚአብሔር ከናንተ ጋራ ይሁን።"

አጅ ነሥተውት ወደየአድባራቸው ተመለሱ። እንዳመለከታቸው እነዚያን ስባት ቀናት አያንዳንዱ አንደተቻለው አንዳቅሙ ይጸምና ይጸልይ ጀመረ። "አቤቱ ከተቻለህ እንድንጽናናበት አሱን ለኛ ተውልን፤ ካልሆነም ፈቃድህ ይሁን። (196^{ሀ}) ከወሰድከው በኛ ላይ የሚያርፍ አጽናኚውን ቅዱስ መንፈስህን ላክልን።[163] አንተ በፊት ትንቢት ይናገሩ በነበሩ በቅዱሳን ነቢዮችህ፥ እነሱ ዘንድ አድራለሁ፤ በማህላቸውም ወዲያ ወዲህ እላለሁ፤ እምላካቸውም እሆናለሁ[164] ብለሃል። በዓለም ውስጥ በታየህም ጊዜ ለመረጥካቸው፥ እኔ እናንተ ዘንድ እኖራለሁ፤ የሙት ልጆች እንድትሆኑ አልተዋችሁም[165] ብለሃል።"

---

162. "Formula."
163. ዮሐ 14፡ 26፤ 15፡ 26።
164. ዘሌ 26፡ 12።
165. ዮሐ 14፡ 18።

ከዚያ፡ በሶስተኛው ቀን አንድ ወንድም እንዲህ አለ፤

በምድረ በዳ ካንድ ዛፍ ስር ቆሜ ስጸልይ ዓይኔን አንቅልፍ ከብዶት ሳለ ሽማግሌውን አባታችንን ከማህላችን ሲወስዱት በፊቴ ራእይ ሆነ። ፊት ለፊት ከሚታየኝ ከአንድ ትልቅ ተራራ ላይ በወምበር አስቀመጡት። (196ᵃ) የአበባ ቀለም ያለበት ልብስ ለብሷል። መጎናጸፊያው እንደ በረዶ ነጭ ነው። በታላቅ ግርማና በተሟላ ሞገስ አየሁት። ከሱ ጋራ ከፊቱ ያሉትን አገሌን ወስደው ከአልጋው ላይ እንዲያስቀምጡት አዘዛቸው። እያየሁ ከአልጋው ላይ አስቀመጡት። እሱም እንዲሁ ሲታመም አየሁ። ፍርሃትና ድንጋጤ መጣብኝ። ሽማግሌው ወዳለበት ለመሄድ ስፈልግ አንድ ገደል ይከለክለኛል። ከዚያ፡ በጣም ደነገጥኩ። ሽማግሌውን እንደሚወስዱብን አወቅሁ። ከዚያ፡ ምርር አድርጌ አለቀስኩ። "አቤቱ ጌታ፡ ሕይወቴ ምንድነው? ከተቻለ ይኸንን አታድርግ፤ ካልሆነም ፈቃድህ ይሁን፤ (197ᵇ) የሚሻለውን ታውቃለህና" አልኩ።

ሌሎችም አንደዚሁ በተሰጣቸው መጠን አይተዋል። አንዱ፡ "በሞገስ ውበትና በክብር ሙሉ የሆኑ ቅዱሶች ሰዎች ብርሃን በተሞሉ ወምበሮች ላይ ተቀምጠው አየሁ። በተገለጠልኝና በአሳየኝ እንዳወቅሁት፡ ከነሱ አንዱ አቡነ አበክረዙን ነበር። ከኛ እንደሚወስዱት በዚህ አውቅሁ" አለ። አንዱ ደግሞ፡ "እኔም ሽማግሌውን ከማውቃቸው ከስማዕታት ወንድሞቻችን ጋራ አየሁት፤ እንደሚወስዱት በዚህ አውቅሁ" አለ። ሌሎችም ብዙዎች ወንድሞች የሩቆቹም የቅርቦቹም የፍጻሜውን ምልክት ያመለክቱ ነበር። እሱም፡ "እንግዲህስ ሕይወቴ ተፈጸመ። ላንተ በጽዮን ስብሐት ይገባሃል"[166] ይል ጀመረ።

ከዚያ በኋላ፡ (197ᵃ) መልኩ ተለወጠ፤ "በልቡ መጽናናት ፊቱ አበራ።"[167] ከማይታዩ ከቅዱሳን መላእክት ጋራ ይነጋገር ጀመረ። የእላታውያንን (መላእክት) መልክ ያደንቃል፤ ለሚጠይቁት መልስ ይሰጣቸዋል። አብረውት የነበሩ ወንድሞች (ሲነጋገር ሰምተው) ይፈሩት ጀመር። ሊጠይቁት (ግን) አልጨከኑም።

እነዚያን ቀኖች እንደዚህ ሲኖርባቸው፡ ከረዳቶቹ አንዱ ወንድም ሊጎበኘው ሲገባ (ቅዱሱ) እንዲህ አለው፤ "አብረውህ ያሉት የማያቸው እነማናቸው?" ያ ወንድም፡ "አባ ሆይ፡ እኔ ብቻዬን ነኝ፤ አብሮኝ የመጣ የለም" አለው። ሽማግሌው፡ "ከመሬት ላይ የወርቅ እንከብሎች የሚበትኑ ካንተ ጋራ ሲገቡ አያለሁ" አለው። ያ ወንድም፡ "ነገሩ ምንድን ነው? (198ᵇ) እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ" አለው። ሽማግሌው፡ "አሁን ታገሥ፤ ዝም በል" አለው።

166. መዝ 64: 2።

167. "የሰው ልብ ፊቱን ይለውጠዋል" የሚለውን (ሲራ 13: 31) መጥቀሱ ይሆናል።

ከኢትዮጵያ ጋራ እየተፋረድኩ ነው

በዚያው ወር በሰኟ ቀን÷ ከቀኑ ዓሥራ አንድ ሰዓት ላይ የነገሩ ትርጉም በማይታወቅ በአንድ ነገር ላይ እንደሚፋረድ ከብዙዎች ጋራ ይሚገት ጀመረ። ወንድሞች÷ "አባ ሆይ÷ ምንድን ነው የምትለው? ከሰዎች ጋራ ስትሚገት እናይሃለን" አሉት። አፉን ከፈተና÷ "ምንድን ነው የምትሉት? (ዝም በሉ፤) በመፋረድ ላይ እኮ ነው ያለሁት" አላቸው። "ከማን ጋራ ነው የምትሚገተው? እዚህ ካንተ በቀር ሌሎች አናይም" አሉት። "እኔ ከኢትዮጵያ ጋራ እየተፋረድኩ ነው" አላቸው።

ሕይወቱ በማለፍ ላይ ስለነበረች÷ ወንድሞች ጥያቄያቸውን አቆሙ። (198[ሀ]) ግን እያዩት ሥራውን ያደንቁ ነበረ። ደግሞ÷ "እኔስ እግዚአብሔር ይረዳኛል፤ እግዚአብሔር ይረዳኛል። እግዚአብሔር ይረዳኛል" ይል ነበረ። እነዚህን ቃላት የሚላቸው አንዴ÷ ሁለቴ÷ ሶስቴ ሳይሆን ያለ ቊጥር ነበረ።

ደግሞ÷ ለወንድሞች እንዲህ አላቸው፤ "ኢትዮጵያውያን ካሁን በኋላ በናንተ ላይ የሚመኩበት የላቸውም፤ አትሸነፉላቸውም። ከቡሩኩ ሐዋርያ መልእክት÷ ዕብራውያን ናቸውን? እኔም እንደነሱ ዕብራዊ ነኝ፤ እሥራኤላውያን ቢሆኑም እኔም እንደነሱ እስራኤላዊ ነኝ[168] የሚለው መጽናኛ ቃል ምልክት አላችሁ።[169] ቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝቡን እግዚአብሔር አልጣላቸውም። ብቻ (199[ሀ]) በእግዚአብሔር ጽኑ።" ይሽንን ብሎ ዝም አለ።

ያቺን ሰዓት÷ ከዚህ በፊት በብፁዕ አባ መቃርስ ዘንድ እንደሆነው÷ ቅዱሱ ከሰይጣንና ከሰዎች ጋራ ይነጋገርባት ነበረ። ሰይጣን (አባ መቃርስን) ከልጅነቱ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ሊከሰው ይፈልገው ነበረ። ግን በሁሉም በኩል ፍጹም ሰው ስለነበረ÷ ምንም የሚወቀስበት ነገር አልተገኘበትም። ነፍሱ በምትወጣበት ጊዜም ሰይጣን በአየር ላይ ሆኖ÷ "መቃሪ÷ መቃሪ÷ አመለጥከኝ" አለው። (ቅዱሱ)÷ "አሁንም ገና አላምንህም"[170] አለው።

እንደዚሁ ይሽም ቅዱስ አባታችን በፊት ከለው ተለይቶ በነበረበት ጊዜ እንደ ደረስበት የሚያስደነግጥ ግርማ ሊደርስበት÷ በሥሉስ ቅዱስ ስም አማተበ። ያ የውሸት ከሳሽ (199[ሀ]) አፍሮ ወጣ። በሽንገላ በመጣበት ጊዜ ሁሉ አዘውትሮ ያሸንፈዋል። ያን ጊዜም ከሱ ለዘላለም በረጅሙ አስኪርቅ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል አሸንፎ አባረረው። በዚያች ጊዜ ቅዱሱ ዝም አለ።

ዘለዓለማዊ ዕረፍትና ቀብር

ያቺ ሌሊት በሞላ በጣም የምታስፈራና የምታስደነግጥ ሆነች። የለውም ሆነ የአራዊት ድምፅ አልነበረባትም። ምድረ በዳው ሰው ካለበት ሩቅ ነበረ። እሱን ይጠብቁት ከነበሩት ከጥቂቶቹ ወንድሞች በቀር ሌላ ማንም አልነበረም።

---

168. 2 ቆሮ 11፡ 22።

169. "እኔም እንደነገሥቱ እስራኤላዊ ነኝ" ማለታቸው ነው።

170. Victor Arras, *Patericon Aethiopice, CSCO*, vol. 277/53 (1967), p. 90.

ጊዜው ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ሲሆን÷ በሁሉ ጊዜና በሁሉ ሰዓት ከሰው እጅና ከሰይጣናት ይጠብቀው በነበረ በእግዚአብሔር ጸባያት ሰላም እንደጣፋጭ እንቅልፍ በወንድሞች እጅ መካከል አረፈ:: (ለእግዚአብሔር) በፍጥረት ሁሉ አፍ ስብሐት ይገባዋል፤ አሜን::

(200^{ሀ}) ጠረኑ የጣፈጣቸው ወንድሞች እስኪያደንቁ ድረስ በሳዩ እጅግ ጥሩ መዓዛ ነበረበት:: ከዚያ÷ ቅዱሳን ወንድሞች ተሰብስበው ምርር እድርገው እያለቀሱ በእበው ሕግ በክብር ገነዙት:: የጻድቃንና የታጋዮች ተስፋና÷ ከዳግም ትንሣኤ እስቀድሞ የምትሆነው የነፍስ እስቀድሞ መነሻ የሆነውን ቊርባን ቀደሱ::

ሁሉንም እንደተጻፈው ፈጽመው በአየር ወር ፭፱ ቀን[171]--ይኸውም ግንቦት ነው--ከሰው ከተደበቀ ምድረ በዳ በጌታ ሰላም ቀበሩት:: ጸሎቱና በረከቱ ለዘለዓለም ከኛ ጋራ ይሁን አሜን÷ አሜን::

(ይኸንን ገድል) የጻፈውን÷ ያስጻፈውን÷ ያነበበውን÷ የተረጐመውን÷ ቃሎቹን በእምነት የሰማውን እግዚአብሔር በእንድነት ይማራቸው፤ ለዓለመ ዓለም÷ አሜን::

---

171. ከመግቢያው ጋራ ለማስታረቅ በአየር ፭፫÷ በግንቦት ፭፱ መሆኑ ነው::



የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌል አቅማራት
(EMML 7219, f. 15a.)

የአባ ዕዝራ ገድል

“ከክህነት ምስጢር በቀር ሴቶች የማያውቁት ለወንዶች በድብቅ የተሰጠ ትምህርት አለን?”

አባ ዕዝራ



እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ
(EMML 7219, f. 21b)



መግቢያ

(72) በማይሞቱ÷ የሕይወት ሕይወቶች በሆኑ÷ በማይሻሩ ሹሞች÷ በኪሩቤል ሰረገላ ላይ በሚኖሩ÷ በነፋስ ክንፍ በሚሄዱ÷ በአንዲት ምክር ዓለምን ሁሉ በፈጠሩ÷ በሥሉስ ቅዱስ ስም÷ በሞገስ ከተሞላው÷ ትሕትናን ከለበሰው÷ እንደ መንገድ ጠራጊው እንደ ዮሐንስ[1] ከናቱ ሆድ ከተመረጠው÷ ገድሉን በአግዚአብሔር ጸባያት በዕብራውያን የዘመን ሐሳብ በሜሴር ፱÷ በግዕዝ በነሐሴ ፲፮ ቀን ከፈጸመው ከጥበበኛው ከአቡነ ዕዝራ ገድልና ከደግነቱ ውበት በጥቂቱ አንናገራለን፤ አሜን::

አቤቱ ጌታዬ÷ ከልጅነቱ ጀምሮ እስከ አበቃ ድረስ ያደረጋቸውን ጥሩ ሥራዎቹን እንድናገር ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች የደበቅኸውን ጥበብና ዕውቀት ስጠኝ::

ትውልድና አስተዳደግ

ይህ ሰው (የስሙ) ትርጉም "የጥበበኛ ልጅ" በሆነው በሰሎሞን ልጅ በ"አብነ ሕልክም" ዘመን ከጽዮን ጋራ ከወጡ ከሌዊ ነገድ÷ ከስቡሐ ሕዝብ ነው::[2] የአባቱ ርስት ሰውኔ÷ የአባቱ ስም ይሥሐቅ÷ የናቱ ስም ልዑል ሠምራ ነበረ:: (እናቱ) ለአካለ መጠን ስትደርስ አባቶቿ ለዱስአ ሹም ዳሯት:: አንድ ልጅ ከወለደች በኋላ ባሏ ሞተ::

ከዚያ ደግሞ ለስቡሐ ሹም ሰጧት:: ያለ ልጅ (ብዙ ጊዜ) ኖረች፤ (በዚህ ምክንያት) ከጥልቅ ሐዘን ገባች:: በመልአኩ በሚካኤል ስም ወደተጠራች ቤተ ክርስቲያን ሄዳ እዚያ አለቀሰች:: አንድ በግ ሠዋች፤ ዕጣንም አሳረገች:: ከካህንም ዘንድ ለንስሐ ተናዘዘችና ወደ ቤቷ ተመለሰች:: ከዚህ በኋላ÷ እግዚአብሔር የልመናዋን ቃል ሰምቶ መልአኩን ላከላት:: በሌሊት ታይቷት አንዲህ ሲል ካንዱም ሁለቴ÷ ሶስቴ ተናገራት፤ "ካህንና አስተዋይ የሚሆን (ልጅ) ትወልጃለሽ:: ራሱ ላይ መስቀል የሚመስል ምልክት ይገኝበታል::"[3]

---

1. መጥምቁ ዮሐንስ ከክርስቶስ በፊት መጥቶ ለስ ክርስቶስ መምጣት ስለተናገረ ለክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ይባላል፤ ማቴ 3: 1-15::
2. የከብረ ነገሥቱን ታሪክ መጥቀሱ ነው:: የእንዳንድ መነኮሳት ትውልድ ታቦቷ ከኢየሩሳሌም ስትመጣ እጅበው ከመጡት እስራኤላውያን ጋራ የተያያዘ እንደሆነ ገድላቸው ይመሰክራል:: እቡነ እስጢፋኖስም ከስቡሐ ሕዝብ መሆናቸውን ገድላቸው ይናገራል::
3. ደቂቀ እስጢፋኖስ መስቀልን እንደሚያከብሩ ለማሳየት የሆነ ተእምር ነው::

እሷም÷ "ጊዜው ሲደርስ ስብሐት እንዳቀርብልህ እንተ ማንህ?" አለችው:: "እኔ መልአኩ ሚካኤል ነኝ፤ የነገርኩሽን ጠብቂ" አላት:: በቃሉ ተገረመች:: ከዚህ በኋላ÷ ይሄ ሞገሳዊ ከሳድ እንባ በሚሏት ምድር ተወለደ:: ይኸ (ምድር) የጠላቶቻቸው ወጣቶች በሽመቃ መውጫ ነው::[4]

መልአኩ እንደነገራት ምልክቱን ከራሱ ላይ አገኘችው:: ስሙንም ዐቅበ ሚካኤል አለችው:: አባቱና ዘመዶቹ የስቡሐ ሹሞች ስለነበሩ ተደሰቱ:: የናቱ አባቶችም የዐጋሜ ሹሞች ናቸው:: እነሱን ጋብዘው ለሙሽራ[5] እንደሚገባው ድግስ ደገሱ:: የሰማቸው ሁሉ እስኪያደንቅ ድረስ ቀንደ መለከት÷ ክራር÷ ማሲንቆ÷ ከበሮ÷ ድንበሐት[6] አሰሙ::

(73) ብፁዓዊው ሳያድግ አባቱ ሞተ:: እናቱ በመልካም አስተዳደግ አሳደገችው:: (ልጁ ገና) በጎና ክፉ ሳይለይ እስጢፋኖስ የሚባለው ታላቅ ወንድሙ ወስዶ የከስዋ የጸጋዋ ጌጥ÷ የገርዜን አለቃ÷ የነጫጭ በጎች ጠባቂ÷ ለሞኞች ጥበብ ሰጪ÷ ብርሃኑ የማይጨልም መስተዋት÷ ለተጠሙ መጠጥ÷ የወተትና የወይን ወንዝ ከሆነው ከእቡነ ይሥሐቅ ዘንድ አመጣው::[7] "ይኸ ምንህ ነው?" አለው:: "ወንድሜ ነው" አለው:: ብፁዓዊውን ያን ጊዜ÷ "እግዚአብሔር ካንተ ጋራ ይሁን፤ የሁሉን ልብ የምታስደስትበት መንፈሳዊ ጥበብና ዕውቀት ይስጥህ" ብሎ ባረከው::

ከዚያ÷ በጥበብና በተግሣጽ አሳደጉት:: በሙሽራ ወተት አሳለመሱት፤ እነሱም በብሉይና በሐዲስ ያሉት ሰማንያ አንዱ (መጻሕፍት) ናቸው::[8] መጻፍና የሚገባውን ሁሉ አስተማሩት::

ምንኵስና

ደግሞ ሳያድግ በልጅነቱ÷ ገና የ፲፪ ዓመት ልጅ እንደሆነ÷ የምንኵስና ልብስ አለበሱት፤ ስሙንም ዕዝራ አሉት:: በዚያች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያው ዕዝራ (እንዳጠጣው) የጥበብና የዕውቀት ጽዋ አጠጣው::[9] ከዚያ በኋላ ድንጋይ ተሸክሞ ወደ ዋላው[10] ላይ የሚያወጣ መንኰራኵር ይሠራ ጀመር:: (አበምኔቱ) ብፁዕ አቡነ አበክረዙን ሲያይ አደነቀ::

---

4. በዚያ አካባቢ ጎሳዎች ይገዳደሉ እንደነበረ ያመለክታል::
5. በመንፈሳውያን አነጋገር "ሙሽራ" የሚሉት ቤተ ክርስቲያንንና ክርስቶስን ነው::
6. ዓይነቱን የማላውቀው የሙዚቃ መሣሪያ ሊሆን ይችላል::
7. እኝህ በደቂቀ እስጢፋኖስ ዘንድ የሚደነቁ ስው ደብረ ገርዜንን የቆረቆሩ ናቸው::
8. የቤተ ክርስቲያኗ ባለሥልጣኖች ከደቂቀ እስጢፋኖስ ጋራ መጽሐፈ ሲኖዶስ በመዘገባቸው የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ጥል እንደሌላቸው እንደዚህ ያሉ ብዙ ምልክቶች አሉ:: ቢጣሉ ከዚያ ውጪ በሆኑት ላይ ነው:: የብሉይና የሐዲስ ቅዱሳት መጻሕፍት ሕግንን እንደሚመግቡ የእናት ሁለት ጡቶች ይመስላሉ::
9. ሉቱ 13: 38-39::
10. "ዋላ" ምን ይሆን?

"አስተዋይነቱን ታያላችሁን?" አላቸው። በኋላ የሚሆነውን ሁሉ ስላወቀ፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያሰበውን ሁሉ እንዲያደርግ ፈቀደለት።

በቤተ እስጢፋኖስ ላይ ስለመጣ ግፍ

(በዚያን ጊዜ) በቤተ እስጢፋኖስ ላይ ከንጉሡ ዘንድ ግፍ መጥቶባቸው ስለነበረ፥ ስደት በዛባቸው፤ ጭልፊት ወፎችን እንደምትቀልብ ልጆቹን ተቃለቧቸው። ታቦቶቻቸውንና ቅዱሳት አቃዎቻቸውን የሚደብቁበት ቦታ አጡ። በዚህ ጊዜ የደብተራቸውን[11] አቃ የሚከቱበት የአለት ድንጋይ ቀዳዳና የመሬት ጉድጓድ እንዲፈልግ መንፈስ ቅዱስ ይኸንን ብፁዓዊ አነሣሣው። ከዚያ በኋላ፥ ለዳንኤል እንደተገለጸለት[12] በሌሊት ራእይ ተገለጸለት። (መልአኩ) መጥቶ ካንዴም ሁለቴ፥ ሶስቴ ዳሰሰው፤ "ተነሣ፥ እኔ የምሰጥህን ተመልከት" እለውና ምልክት ሰጠው። ሄዶ አገኘው፤ ሲገባ መልኩ የሚያስደነግጥ እባብ ቆየው። በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እማተበበት፤ ጉዳት ሳያደርስበት ወጣ።

የሆነውን ሁሉና የፈለገውን እንዳገኘ ለወንድሞቹ ነገራቸው። ምክንያቱም ቀደም ብሎ በሌሊቶች ትጋት ላይ ነበረ።[13] ሁሉን የሚያውቅ ጥበበኛ ልጅ እግዚአብሔር ስለሰጣቸው በጣም ደስ አላቸው። "እንደ ቀደሙ አባቶችህ የደብተራዋን ዕቃ ጠብቅ"[14] አሉት።

ከዚያች ጊዜ ጀምሮ በሃይማኖቱ የጸና ሆኖ፥ ፍርሃት ራቀው። ራሰ ጥሩው ብፁዓዊ አበክረዙን ስለ እግዚአብሔር ፍቅር በተሰደደበት ጊዜ የሚደበቅበት ምድረ በዳ ሲፈልግ እንደ ዋልያ ተራሮችን ሲዞር የቀድሞዎቹ የከተቱበት ያልተገለጸውን ከአለት ድንጋይ ቀዳዳ ውስጥ ያለውን ለማየት በቃ።[15]

ካህን ቸገረ--የኢየሩሳሌም ጉዞ

ስደት በጣም ጸና፤ ቅዱሱ (ጳጳስ) አቡነ ገብርኤል ስለሞተ ክህነትም ታጣ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ ብፁዕ አቡነ አበክረዙን ስብሰባ ጠርቶ፥ "ሕይወታችንን እንዴት እንምራ? አኗኗራችንስ እንዴት ይሁን? ያለክህነት መቆም ይሆንልናልን?" አላቸው። ይኸንን ከቃሉ ሲሰሙ እንዳንዶቹ፥ "አባ ሆይ፥ ካንተ ፈቃድ ብናገኝ ኢየሩላሌም ሄደን፥ ከጌታ መቃብር ዘንድ ሰግደን፥

11. "ደብተራ" ማለት "ድንኳን" ማለት ሲሆን፥ እዚህ የሚያመለክተው እንደ ብሉይ ዘመን የታቦት ማደሪያውን ነው።
12. ዳን 7።
13. "የሌሊቶች ትጋት" የሚሉት ሲጸልዩ ሲሰግዱ ማደርን ነው።
14. "የቀደሙ አባቶቹ" የብሉይ ዘመን ሊዋውያን ናቸው፤ አቡነ ዕዝራ ትውልዳቸው ከነገደ ሌዊ እንደሆነ "ትውልድና አስተዳደግ" ከሚለው ስር እይተናል።
15. እዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ግዕዙ እንዳንድ ቃላት ጐድለውታል።

ከጳጳሱ ፊት ቆመን ግፋችንን ሁሉ ልንነግረው እንፈልጋለን። አዚህስ ኢትዮጵያ ትታናለች"[16] አሉት።

"ያመጣችሁት ሐሳብ ጥሩ ነው፤ በፊትም (74) ወንድሞቻችሁ ይኸንን አስበው ተስማምተውበት ነበረ። ግን በደረሰባቸው ከባድ ስደት ምክንያት ሊደርሱ አልቻሉም። አሁንም አግዚአብሔር ይርዳችሁ" አላቸው። ከዚያ በኋላ፥ የሚሄዱ (ሰዎች) ከየአድባራቸው አዋጡ። የእስራኤል ልጆች የከነዓንን ምድር እንዲያዩ ከየነገዳቸው (ሰው) እንዳዋጡ፥[17] እነሱም እንዲሁ አደረጉ። ቍጥራቸው ፲፪ ሆነ።[18]

የከስዋ ማኅበር አቡነ አበክረዙንን፥ "አቡነ ይሥሐቅ[19] እንደሌለ ታውቃለህ። አሁንም ታቦቶቹንና የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን ሁሉ የሚጠብቁ ተውልን። እስጢፋኖስ የሚሄድ ከሆነ ይኸንን ብፁዓዊ (አቡነ ዕዝራን) ተውልን፤ መብራታችንና የተደበቁትንም፥ የተገለጡትንም የሚያውቅ፥ የምንመረኰዘው፥ የምንደገፈውም መቋሚያችን ነው" አሉት። ቅዱስ አቡነ አበክረዙን፥ "ዕዝራንስ ተዉት ይሂድ፤ ወደናንተ በሰላም ተመልሶ የወንድሞቻችሁን ዜና የሚነግራቸሁ እሱ ነው" አላቸው።

ከዚያ በኋላ፥ የተረፉትና የሚሄዱትም እስከ አርባ ዕሰት ምህልላ ያዙ። ብፁዕ አቡነ ዕዝራ ካስለመደበት ሆኖ ሲጸልይ እንዳንድ ትንሽ ጉልማሳ አየጠበቀ ካንዲም ሁለቴ፥ ሶስቴ አደናቀፈው፤ (ግን) ብፁዓዊው አየሰበት።

---

16. ጸሐፊዎቹ ብዙ ጊዜ ኢየሩሳሌምንና ግብጽን አንድ ያደርጓቸዋል። ሁለተኛም፥ ወደ "ኢየሩሳሌም" (ወደ ግብጽ) ለመሄድ የፈለጉት ጳጳሱ ስለሞቱ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ስለተወቻቸውም ነው። ጳጳስም ቢኖር እንዳይካኑ ተቃዋሚዎቻቸው ይከለከሏቸው ነበር።

17. ኢያ 4: 1-4።

18. ከ1450 ዓ. ም. ጀምሮ እስከ አፄ እስክንድር (1471-1487) ዘመን ድረስ ለስላሳ ዓመት ያህል ቤተ ክርስቲያኗ ጳጳስ አልነበራትም። ይህ የጳጳስ እጦት በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ከፍ ያለ ችግር ፈጥሮ ነበረ፤ ቅዳሴ የሚቀድሱ፥ ፍታት የሚፈቱ፥ ሕፃናትን ለክርስትና የሚያጠምቁ ካህናት ጠፉ፤ ለዚያን ጊዜ ሰው አድሜ ስላሳ ዓመት ቀላል አይደለም፥ አለቁ። ለችግሩ ፈጣን መፍትሔ ባለመገኘቱ ብዙ ስዎች ዲቁናና ቅስና ለመሾም እግብጽና ኢየሩሳሌም ድረስ በእግር ሳይሄዱ አልቀሩም። በሀገሪቱ ላይ ከደረሰው ችግር ጥናት የተነሣ በእፄ በአደ ማርያም ዘመን (1461-1471) ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ ስምን የራሳችንን መምህራን አናጳጵስም እስከ ማለት ደርሰው ብዙ ተከራክረውበት ነበረ። Stanislas Kur, *Actes de Marḥa Krestos*, *CSCO*, vol. 330/62 (1972), p. 237; Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia*, pp. 245-247. እንደሌላው ጊዜ ጳጳስ ማምጣት የተቸገሩበት ምክንያት ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም፤ ከግብጽ ሡልጣኖች ጭቆና የተነሣ ሊሆን ይችላል። ግን በእፄ እስክንድር ዘመን ጳጳሳት መምጣታቸው ቅድስት ማርያም ስአፄ እስክንድር ተአምር እንደሠራችለት መመዝገቡ ችግሩ የወሳዲተ አምላክን እርዳታ ያስፈለገው ታላቅ ችግር እንደነበረ አያጠራጥርም። Carlo Conti Rossini, "Il Convento di Tsana in Abissinia e le sue laudi alla Vergine," *Accademia Nazionale dei Lincei*, vol. 19, ser. 5 (1910), pp. 598-599.

19. ጎዳግ ቍ 7ን ተመልከት።

ስይጣን ያመጣው እንደሆነ ዐውቆ በመስቀል ምልክት አማተበበት። "በሞት ጥላ መካከል ብሄድም ክፉውን አልፈራውም፤ አንተ ከኔ ጋራ ነህና"[20] አለ። ደግሞ፥ "እግዚአብሔር ያበራልኛል፤ ያድነኛልም፤ ምን ያስፈራኛል?"[21] ካለ በኋላ፥ ካስለመደበት ቦታ ቆመ። ስይጣንም ተሸንፎ ሄደ። ብፁዓዊው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለሁል ጊዜ ሞገስ እንዳገኘ ዐወቀ።

ከዚያ በኋላ፥ ያዕቆብ ወደ ሶርያ ሲሄድ ከአባቱ ከይሥሐቅ በረከት እንደተቀበለ፥[22] ሙቢያ ወደ ሜዶን ራጊስ ሲሄድ ከአባቱ ከጦቢት በረከት አንደተቀበለ፥[23] ከሽማግሌ አባቱ ከአበክረዙን በረከት ተቀብሎ፥ ከወንድሞቹ ጋራ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ተዘጋጀ። በ፸፰፰ ዓመተ ምሕረት[24] ተነሥተው ጥቅምት ሠላሳ ቀን ገበሉል ከሚሉት ቅዱስ ደብር ከአባ ዮናስ ደብር ደረሱ። በደስታ ተቀበሏቸው።

በመንገድ ላይ የተነሣ ሁከት

ከዚያ፥ ወደ ማርያ ወረዱ። ደግሞ ብዙዎች መነኮሳት ከብሔረ ጉዛም፥ ከብሔረ ሴዋ፥ ከአንጎትና ከብዙ የኢትዮጵያ ብሔሮች መጡ። እነዚያ ውስጥ ደቂቀ ሲኖዳ፥ ደቂቀ አምጎ፥ ደቂቀ ማቲያን፥ ደብተራም፥[25] ከ(ደብረ) ቢዘን፥ ከደብረ ማርያም[26] ነበሩ። ማንም በግላጭ ላይናገር፥ ሁሉም በውስጥ ነበሩ፤ ግን እርስ በርሳቸው ይተማሙና ይጨቃጨቁ ነበር።

ከዚያ በኋላ፥ ከንቡራነ እዱ አንዱ ከአባ ዮናስ ልጆች አንዱን እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ "ከናንተ ጋራ ደቂቀ አስጢፋኖስ አሉ የሚባለው አውነት ይሁን ወይም ሐሰት ግልጥ አርገህ ንገረኝ።" (ስውየው) "የሉም" አለው። ካንዴም ሁለቴ ሲነዘንዘው ጊዜ፥ "አዎን፥ አሉ" አለው። "ምን ያህል ይሆናሉ?" አለው። "፴" አለው።

ይሽንን ከሱ ስምቶ ወደ ጓደኞቹ ሄደና ሁሉንም ነገራቸው። (ሲነግራቸው) "እነዚህ የንጉሥ ጠላቶች ስለሆኑ ከነሱ ጋራ መሄድ አይሆንልንም"[27] አሉ። ከነሱ አንዱን ወደ ቅዱላኑ እንዲህ ሲሉ ላኩ፤ "ሥጋ የማትበሉት፥ ወይንና ጠላ (ጠጅ?) የማትጠጡት፥ እንደ ሌሎች መነኮሳት

20. መዝ 22፡ 4።
21. መዝ 26፡ 1።
22. ዘፍ 28፡ 1-2።
23. ጦቢ 5፡ 16።
24. "ዓመተ ምሕረት" የሚሉት ፥"ዓመተ ሰማዕታትን ነው። 128 ዓመተ ሰማዕታት 1468 ዓመተ ምሕረት ነው። ጌታቸው ኃይሌ፥ ባሕረ ሐሳብ፥ ገጽ 186።
25. እነዚህ የቤተ መንግሥቱን ታቦት የሚያገለግሉ ናቸው።
26. ደብረ ማርያም ከደብረ ቢዘን ልጅ ገዳሞች እንዲ ነበረች። ምናልባትም ጸሐፊው፥ "ከቢዘን ገዳማት አንዲ ከሆነችው ከደብረ ማርያም" ማለቱ ይሆናል።
27. ጥላቸው ከንጉሡ ጋራ እንጂ የሃይማኖት ጉዳይ አለመሆኑን ሁሉም ያውቃል። ይሽንን ያህል የሚቃወሟቸው ምናልባት ለምን ከነሱ ጋራ ሄዳችኋል ተብለው እንዳይቀጡ ፈርተውም ይሆናል።

ወተትም (የማትጠጡት) ጠባያችሁ ምን ቢሆን ነው? ደግሞስ ደቂቀ እስጢፋኖስ ናችሁ የሚሏችሁ እውነት ነውን?"

እነማን እንደሆኑ ግልጥ መሆኑን ሲያውቁ፥ "ደቂቀ (75) እስጢፋኖስ ነን፤ አባ ዮናስም አባታችን ነው፤ ከልጆቹ ጋራ አንድ ማኅበር ሆነናል፤ አሁን ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ነን" አሉት። ይኸንን ሲሰማ ሄዶ ለሁሉም መነኮሳት ነገራቸው። ከዚያ፥ ከሽንጎ አደባባይ ጠሯቸውና፥ "ከደቂቀ አባ ዮናስ ጋራ አንድ ከሆናችሁ፥ ለማርያም፥ ለመስቀል፥ ለንጉሥ ትሰግዳላችሁን? የእስጢፋኖስን ስም ትሰድባላችሁን? (ይኸንን ካደረጋችሁ) አንድ እንደሆናችሁ በዚህ እናውቃለን" አሏቸው።

ቅዱሳኑ እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ "ለማርያምና ለመስቀል መስገድ እንሰግዳለን፤ ለንጉሥ እንድንሰግድ ግን መጽሐፍ አላዘዘንም። ስድብም አንሳደብም፤ ምክንያቱም፥ "የሚሳደቡ ስለሷ ይጠየቁባታል"[28] ይላል።

ይኸንን (መልስ) ሲሰሙ ትልቅ ሁከትና ጥል ተነሣ። ደቂቀ አባ ዮናስም እንዲህ ሲሉ በጣም ተቆጡ፤ "ደቂቀ ዮናስ (ነን) ብለው ከኛ ጋራ አንድ ሆነው ሳለ፥ እንዴት ይኸንን ትሠራላችሁ?" (ደቂቀ ዮናስን)፥ "ከነሱ ጋራ አንድ ከሆናችሁ፥ በመካናችሁና በአባታችሁ ላይ ክፉ ሠራችሁባቸው" አሏቸው።

የማርያሙ ሹም አስታራቂ ዳኝነት

ከዚያ፥ ደቂቀ አምኑ፥ (ደቂቀ) ሲኖዳ፥ ቢዘኖች፥ ደብተራዎች አንድነት ሆነው ወደ ማርያ ሹም ሄዱና እንዲህ ሲሉ ከሰሷቸው፤ "እዚህ ለማርያምና ላንድ ልጁ መስቀል የማይሰግዱ ፈላሻዎች በደቂቀ አባ ዮናስ ውስጥ ተደብቀው አሉ።" ይኸንን (ክስ) ሲሰሙ ወደ (ሹሙ) ሄደው፥ "ችግራችንን እንድንነግርህ (ልትረዳን) ቃል ግባልን" አሉት። ቃል ገባላቸው። እንዲህ አሉት፤ "እኛስ ለማርያምና ለአንድ ልጁ መስቀል እንሰግዳለን፤ ግን ሥጋ ካልበላችሁ፥ ወይን፥ ጠላ፥ ወተት ካልጠጣችሁ ከናንተ ጋራ መንገድ አንሄድም የሚሉን መነኮሳት እዚህ አሉ።" እሱም፥ "ከዚህ በቀር ሌላ ጉዳይ አላችሁ ወይ?" አላቸው። "ሌላስ የለንም" አሉት።

ቃላቸውን ከሰማ በኋላ፥ የደብተራ ካህናትን ጠርቶ አስታረቃቸው፤ አንዱ ሌላውን እንዳይተላለፍ ቃል ኪዳን አስገባቸውና በሰላም ሸኛቸው። መሪውን በድብቅ እንዲህ ሲል አስማለው፤ "የእግዚአብሔር ሰዎች ስለሆኑ ምድረ ግብጽ እስኪደርሱ ድረስ እንዳትተዋቸው፥ አደራህን ጠብቅ" ሌሎቹንም መሪዎች እንደዚሁ አደራ ሰጥቶ አስማላቸው።

በበረሐ የእምላክ ረድኤት

ከዚያ፥ በዘጠነኛው ወር በከሴል ወር--ታኅሣሥ ነው--በ፲፯ ቀን (1468 ዓ.ም.) ከኢትዮጵያ ምድር ተነሥተው በመንገድ ሲሄዱ ብዙ ችግርና ጭንቅ

28. ማቴ 5፡ 22።

ደረሰባቸው። ከዚያ፥ እንዲህ ሆነ፤ አንድ ቀን አንድ ወንድም ሲደክመው አቡነ ዕዝራ አብሮት (ወደ ኋላ) ቀረ። ምድሩ ደረቅ፥ አገሩም ድንጋያማ ስለነበረ፥ የሚጠጡት ውሐ አጡ። እግዚአብሔርን ለመኑት፤ ጸለዩም። የሚመራቸው ረዳት ቁራ ልኮላቸው፥ የውሐ ምንጭ ካለበት አደረሳቸው። ጠጥተው ነፍሳቸው ሕይወቷ ተረፈ።

የአባ እስጢፋኖስ ዕረፍት

በማግሥቱ ተነሥተው ወንድሞቻቸው ወዳሉበት ሄዱ። በአራተኛው ወር በመጋቢት... ቀን[29] ከግብጽ አገር የላይ ላይ ምስር ግብጽ ግዛት ከሆነችው ከራፋ ምድር ዳርቻ፥ ከአስና እና ከረሜ፥ ደረሱ። መሐረቅ--ማለት ደብረ ቊስቋም--ሲደርሱ ይኸ ዘመን የማይወሰነው የባሕርይ ዕንቁ አባ እስጢፋኖስ በዕብራውያን የዘመን ሐሳብ በአየር በ ... ቀን፥[29] በግዕዝ ግንቦት ... ቀን አረፈ።[29] የወንድሞቹና የደቂቀ አባ ዮናስ መሪ ስለነበረ ታላቅ ሐዘን አደረጉለትና እዚያ ቀበሩት።[30] ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

ከሱ ቀጥለው ምድረ በዳውን ካለፉት ከኟቱ ወንድሞች በቀር ሁሉም ሞቱ። (76) ይኸ ብፁዓዊም ከባድ ሕመም ከታመመ በኋላ ሰብዙዎች ድጋፍ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ፈወሰውና ጉዟቸውን ሊቀጥሉ ከዚያ ተነሡ።

በምድረ በዳ ስንበት ማክበር

ምድረ በዳ ሲደርሱ፥ ዕለቱ ዓርብ ነበረ፥ ስንበት ለማክበር ብቻቸውን (ወደ ኋላ) ቀሩ። ደቂቀ አባ ዮናስ፥ "ለምን ከኛ ትለያላችሁ? ነጋዲያኑ[31] ሁሉ እየሄዱ ነው" አላቸው። ብፁዓዊው እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "ዛሬ የእግዚአብሔር ስንበት ነው፤ መሄድ አይሆንልንም። ዕለተ ሰንበትንና እሷንም ማክበርን አስታውስ፤ ስድስት ዕለት ሥራህን ትሠራለህ፤ በሰባተኛው የእግዚአብሔር ሰንበት ትሆናለች፤ በሷ ከሥራው ሁሉ እርፍባታልና፤ ባርኳታል፥ ቀድሷታልም።[32] የገጽ መላእክትና የቅዳሴ መላእክት በሰማይ

---

29. ቊጥሮቹ አልተጻፉም፤ ዘመኑ ግን ያው 1468 ዓ. ም. መሆኑ ነው።

30. "ደብረ ቊስቋም" ንጉሥ ሄሮድስ ሕፃኑን ክርስቶስን ሊገድለው ሲፈልገው ቅዱስ ዮሴፍ ልጁንና ቅድስት ማርያምን ወደ ግብጽ እሸሽቶ ያረፈባት ቦታ ነች። ኢትዮጵያ ውስጥ ቅዱሳት ቦታዎች "ቊስቋም" የሚል ስም የሚወጣላቸው ይኸንን ቦታ በማስታወስ ነው። ዛሬ ስሙ በዓረቢኛ "ዴር መሐረቅ" ("የማቃጠያ ገዳም" ነው። ንብረትነቱ የኢትዮጵያውያን ገዳም ነበረ። በ17ኛው ምእት አመት እንድ ልዑል እዚያው ቆይቶ ነበረ፤ ምናልባትም እንደ አባ አስጢፋኖስ እዚያው ተቀብሮ ይሆናል፤ Enrico Cerulli, *Etiopi in Palestina. Storia della communita etiopica di Gerusalemme* vol. 2 Roma 1947, p. 494.

31. ነጋዲ/ት፥ ነጋድያን/ት "መንገደኛ/ኞች" ማለት ሲሆን ሌላው ትርጉሙ "pilgrim/s", "*hajj*" ማለት ነው።

32. ዘፀ 20፡ 8-10።

አብረው ሰንበትን አክብረዋል::[33] ስለዚህ ልንሄድ አንችለም::" እንደጨከኑ ባዩ ጊዜ ትተዋቸው ጓዛቸውን ሁሉ አነሡ:: እዚያ ብቻቸውን ቀሩ::

ከዚያ÷ አንድ ዐረብ በዚያች መንገድ ሲያልፍ ብቅ አለ:: ብቻቸውን ቁጭ ብለው ሲያያቸው አደነቀ:: ሁኔታቸውን ለማወቅ ሎሌውን ላከ:: ሊያያቸው ወደነሱ ሄዶ÷ "ምንድን ነው ነገራችሁ? ከየት ናችሁ? ወዴትስ ትሄዳላችሁ? ለምንስ ብቻችሁን ተቀምጣችኋል? ይኸኮ የወምበዴ አገር ነው" አላቸው::

ብፁዓዊው÷ "ነጋድያን ነን፤ አገራችን ኢትዮጵያ ነው:: እዚህ ብቻችንን (ወደ ኋላ) የቀረነው ዛሬ የአግዚአብሔር ሰንበት ስለሆነ ነው:: ሌሎች እንዲፈሩ የሚሸራትን ሰው ሁሉ በድንጋይ እንዲወግሩት መጽሐፍ ያዛል::[34] ስለዚህ አኛም እንጠብቃታለን" አለው:: ዐረቡ÷ የአስላሞቹ መኳንን÷ አደነቀና ሠራዊቱን÷ "ረኀብና ጥም÷ ወይም ሞት ሳይፈሩ ሕጋቸውን እንደማይሸሩ ታያላችሁን? በሉ ከያዛችሁት ምግባቸውን ስጧቸው" አለ:: የጸም ምግባቸውን ሰጧቸው፤ አንዳንዶቹ ሙዝና ስኳር ሰጡ፣ አንዳንዶቹ ቴምርና ለውዝ ሰጡ፤ አንዳንዶቹ ዳቦና ማር ሰጡ፤ አንዳንዶቹ ወይንና ዘይት ሰጡ፤ ሁሉም የሚችሉትን ያህል ሰጧቸው::

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ይኸንን እግዚአብሔር ለነሱ የሠራውን ሲያይ ደስ አለው:: እንዲህም አለ፤

> "ሐሳብክን እግዚአብሔር ላይ ጣለው፤ እሱ ይመግብሃል:: ለጻድቅ ሁከትን ለዘላለም አይሰጠውም"[35] ያለው የነቢዩ ዳዊት ትንቢት ዛሬ ተፈጸመ:: ደግሞ ነቢዩ÷ "ከሚባላ የሚበላ ወጣ፤ ከብርቱም ውስጥ ጣፋጭ ወጣ"[36] ብሏል:: ያን ጊዜ የመጡት ሊገድሉን መሰሉን ነበረ:: እነሱ አባትና እናት ሆኑን:: አሁንም ከቀማኛና ከግፈኛ ላዳነን÷ በክንፎቹ ጥላ ለሸፈነንም÷ የተማመኑትን ባሮቹን ላልተወ÷ ለእግዚአብሔር ስብሐት ይግባዋል::

ከዚያ በኋላ ለመሄድ ተነሡ:: ተሰፋ ካደረጓት ከኢየሩሳሌም ደረሱ:: ከቅጥር ግቢዋ ሲቆሙ÷ "ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ስላሉኝ ተደሰትኩ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ÷ ቅጥር ግቢሽ ውስጥ እግሮቻችን ቆሙ"[37] አሉ:: ደግሞም÷ "የጌታችን እግር ከቆመበት ቦታ እንስገድ"[38] አሉና አዚያ ሰግደው ጥቂት አረፉ::

ኢየሩሳሌምም ተጨቃጨቁ

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ መነኮሳት ደግሞ ተጣሏቸው:: ከጳጳሱ ዘንድ አንዲህ ሲሉ ከሰሷቸው፤ "እነሆ÷ አይሁድም÷ አረማውያንም ያልሆኑ መነኮሳት ወደዚህ መጥተዋል፤ በሥላሴ አያምኑም፤ ለማርያም÷ ለመስቀል

---

33. ኩፋ 3: 3-4::
34. ዘኍ 15: 32-36::
35. መዝ 54: 22-23::
36. መሳ 14: 14::
37. መዝ 121: 1-2::
38. መዝ 131: 7::

እይሰግዱም:: ታቦትም የላቸውም፤ (77) ቍርባንም እይቈርቡም፤ ሲጸልዩም አቡነ ዘበሰማያትና ጸሎተ ሃይማኖት እይደግሙም:: የኢትዮጵያ ንጉሥ ይገድሳቸዋል፤ ጳጳሱም ያወግዛቸዋል፤ ሕጋቸው እንደ ሕጋችን እይደሰም::"[39]

ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ዮሐንስ[40] ይኸንን ሲሰማ ጉባኤ አደረገና ሕግ ዐዋቂዎችና የግብጽ ታሳሳቆቹን ሐረዘወይላ[41] ከሚሏት ቤተ ክርስቲያን ጠራ:: ከሳሾቹ ለብቻቸው ቆሙ፤ ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ከወንድሞቹ ጋራ ለብቻው ቆመ:: ከዚያ፥ እፉን ከፈተና እንዲህ አለ፤

> ፍርድ የሚሰጥ ለሰጠን ለእግዚአብሔር ስብሐት ይድረሰው:: እኛም እዚህ የመጣነው ሃይማኖታችንን ልናስማ ነው:: እኛ ከሐዋርያው ማርቆስ መንበር የወጣን ያዕቆባውያን ነን::[42] እነዚህ እንደሚሉት ሌላ ሃይማኖት የለንም፤ እብ በእየሮቹ ርዝመትና በውሐና በባሕሮቹ ጥልቀት የሚያንጸባርቅ ፀሐይ ነው፤ ወልድ በሰማዮች ስፋት፥ የሚያበራ፥ በውሐና በባሕሮች ጥልቀት የሚያንጸባርቅ ፀሐይ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ በሰማዮች ስፋት የሚያበራ በውሐና በባሕሮች ጥልቀት የሚያንጸባርቅ ፀሐይ ነው :: (እምሳክ) በገጽ ሶስት ሆኖ፥ በመለኮት እንድ ነው:: ሃይማኖታችን ይህ ነው:: ለመለኮት እሳት ልብሱ ለሆነች፥ የዚህ ዓለም ቁሻሻ ላልነካት ለማርያም እንሰግዳለን:: ለመስቀልም የሥቃዩ እልጋ ስለሆነ እንሰግዳለን:: ነቢዩ ስለሱ፥ "በመሰዕ እግጫ የተተከለ የተመሰገነ እንጨት እየሁ፤ ከፍሬው ለምርጦች ይሰጣል"[43] ይላል:: ይህ ስለመስቀል ነው:: ስሎሞንም፥ "ክጥላው ስር እምሮኝ ተቀመጥኩ፤ ፍሬውም ለጉሮሮ ይጣፍጣል"[44] ይላል:: የመስቀል ፍሬ ይህ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው:: የሱ "ምርጦች" ስለስሙ የሞቱ ሰማዕታት ናቸው:: ታቦት የላቸውም ስለሚሉት፥ ቅድስት አሪት የምትለውን ስማ፤ "ከማይነቅዝ እንጨት ቁመኟ እንድ ክንድ ተኩል፥ ወርዷ እንድ ክንድ ከሩብ የሚሆን ታቦት ሥራ::"[45] ታቦት የሁሳችን መመኪያ፥ የመላእክትም መመኪያ

---

39. ኢየሩሳሌም ሄደው እንደተጣሉ የሚነግሩን ደቂቀ እስጢፋኖስ ብቻ አይደሉም፤ ከተአምረ ማርያም ውስጥም ተጽፏል፤ Enrico Cerulli, "L'Imperatore Na'od e gli Stefaniti a Gerusalemme in un documento inedito (Vaticano Etiopico 298)," *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies, Addis Ababa 1966*, vol. II, Addis Ababa 1970, pp. 243-253.
40. አባ ዕዝራ ግብጽ በነበሩበት ጊዜ ሊቀ ጳጳሱ አባ ዮሐንስ የሚባሉ አልነበሩም::
41. "ሓረት ዘዊላ" (የዘዊላ መንገድ) ካይሮ ከተማ ውስጥ ከመንበረ ፓትረያርኩ አጠገብ ያለች ዝነኛ ቤተ ክርስቲያን የምትገኝበት መንገድ ስም ነው:: ቤተ ክርስቲያኗ በመንገዱ ስም ትጠራለች::
42. ያዕቆብ አልበራድዒ በ542 ዓ. እ. የኤዴሳ ጳጳስ ነበር:: በስደት ዘመን እንዳይታወቅ እንደ ደኻ ቡትቶ (በረዳዕ) ለብሶ ተዋሕዶዎችን ያበረታ ሶርያዊ ቅዱስ ነው:: ተዋሕዶዎች በሱ ስም ያዕቆባውያን ይባላሉ::
43. ሄኖ 25: 22::
44. መኃ 2: 3::
45. ዘፀ 25: 23::

ማርያም ነች። አቡነ ዘበሰማያትን አይደግሙም ስለሚሉት ደግሞ፥ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ጸሎት እንዳስተማራቸው ወንጌሉ፥ "ስትጸልዩ አቡነ ዘበሰማያት፥ ወዘተ በሉ"[46] ያለውን ስማ። ስለ ቊርባን መቊረብም፥ "የስውን ልጅ ሥጋ ያልበላ ደሙንም ያልጠጣ ሕይወት የለበትም። በእምነት ሥጋውንና ደሙን የበላ ግን የዘለዓለም ሕይወት አለው"[47] ይላል። ይኸንን ትእዛዝ እየሰማን ቊርባን የማንቈርበው ዕውሮች ነን እንዴ? እንዲያው በቅንአት ይከሱናል።

የቃሉን እንቅስቃሴ ሲሰሙ፥ ሕዝቡ በፍሊሙና ቃል እንደተመለሰ[48] ልባቸው ወደሱ ተመለሰ። የተሰበሰቡት፥ "ምን ትሏቸዋላችሁ? (እነዚህ) በእውነት የሙሽራው ልጆች፥ የክርስቶስ ወንጌል ተሸካሞች፥ እንደ ሐዋርያት ሰባኪዎች ናቸው" አሉ። ሊቀ ጳጳሱም ከነሱ ጋራ አንድ ሆኖ በዚያች ጊዜ የዲቁና ሹመት ሾማቸው።

ለነአባ ዕዝራ ብርሃን ወረደላቸው

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራም በእግዚአብሔር ፊትና በሰው ፊትም ትልቅ ሆነ። ከዚያ፥ (ጠላቶቻቸው) ዶለቱ፤ በሶስቱ ሕፃናት ላይ እንደሆነው፥ ክሳቸውን አልተውም። "ደቂቀ እስጢፋኖስ ባሉበት ብርሃን አይወርድም" አሉ።[49] ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ሲሰማ ከወንድሞቹ ጋራ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "የነዚህ መዛበቻ ስድብ አታድርገን፤ አቤቱ ምሕረትህን አሳየን፤ በብርሃንህ ብርሃን እንይ፤[50] ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክ።"[51] ደግሞ፥ (78) "ብርሃን ከአዳራሽህ ይምጣ፤ ሥራህም ይገለጽ፤ አሕዛብ እምላካቸው የት አለ እንዳይሉን"[52] የሚሰውን (ጸሰየ)።

የፋሲካ ዋዜማ ሲደርስ የሚገባውን ሥርዓት ሠሩ። ምስክር የሚሆኑት ሊቀ ጳጳሳቱ፥ የቤተ ልሔም ቄሰ ገበዝ፥ የንጉሡ ሎሌ[53] ከውስጥ ነበሩ። እንደ ሥርዓታቸው፥ "ለኛ ትንሣኤህን ለአመንን ብርሃንህን

---

46. ማቴ 6: 9።
47. ዮሐ 6: 53።
48. ገድለ ሐዋርያት፥ E. A. Wallis Budge, *The Contendings of the Apostles,* vol. 1, (1899), p. 184.
49. በትንሣኤ በዓል አከባበር ሥርዓት ካህናቱ ትልቁን (የመቃብሩን) ቤተ ክርስቲያን ያጨልሙና ቅዳሜ ለአሑድ አጥቢያ እኩለ ሌሊት ላይ ብርሃን ቦግ ያደርጋሉ፤ የኛ ስዎች ያንን ሲያዩ ብርሃኑ ከሰማይ የወረደ መስሏቸው ይሆናል። ብርሃን መጀመሪያ የሚወርደው ለኢትዮጵያውያን ተብሎ ተወርቶም ነበር። አዬ ዘርአ ያዕቆብ በዚህ አትመኩ በሚል ደብዳቤ መነኮሲዎቹን አስጠንቅቃቸዋል።
50. መዝ 35: 9/10።
51. መዝ 42: 3።
52. መዝ 78: 10።
53. የሡልጣኑ ወኪል መሆን አለበት።

አውርድልን"[54] እያሉ ዑደት ሲያደርጉ ብርሃኑ እነሱ ካሉበት ወረደ። እነዚያ ከሳሾች አፈሩ። አባታችን ቅዱስ ሞገሳዊ ብርሃኑን ባይኑ ሲያይ አግዚአብሔርን ከወንድሞቹ ጋራ አመሰገኑ። የአባታቸውን ዝና እየነገሩ አንድ ዓመት ቆዩ።

የአቡነ ዕዝራ ተግሣጽ

ደግሞ የፋሲካ ዓርብ ሲደርስ እንዳስለመደው ጎልጎታ ከስቅለቱ ቦታ ቆሞ ሳለ፥ የስቅለቱን ሥዕል ራሱን ወደ ሰሜን አድረገው ሲገንዙ አየ። በዚህ ጊዜ ሞገሳዊ አቡነ ዕዝራ አፉን ከፍቶ፥ "ለምንድን ነው አንደዚህ የምትገንዙት?" አላቸው። የግብጽ ስዎች፥ "ሥርዓታችን እንደዚህ ስለሆነ ነው፤ አንት ሐበሻዊ (ጎበሲ) ምን ታውቃለህ? እኛኮ አስተማሪዎችህ ነን፤ አንተ (የኛ) ልጅ ነህ፤ ለምን ትጣላናለህ? አባቶቻችን ያስተማሩን እንደዚህ ነው" አሉት። ሞገሳዊ ዕዝራ፥ "አባቶቻችሁ መጻሕፍቱን አያውቁምን?" አላቸው። "መጽሐፍ ምን ይላል?" አሉት። ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ፥ "ጌታ አይሁድ እንደሚገንዙና አንደሚቀብሩ ፊቱ ወደ ምሥራቅ ሆኖ እንደተቀበረ ወንጌል ቅዱስ ይነግረናል፤ ጽሑፉን ካላመናችሁ አይሁድ ይናገሩ" አለ። አይሁድን ጠየቋቸው፤ "የምንቀብረው ወደ ምሥራቅ ነው" አሏቸው።

ከአምላኩ አርዳታ ስላገኘ አንደዚህ በአውነት ረታቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፈሩት፥ አከበሩትም። የብፁዕና የቅዱስ ሞገሳዊ አቡነ ዕዝራ የሃይማኖቱ ስብከት በሞላ ኢየሩሳሌም ቀበሌ ሲሰማ፥ አንድ መጻሕፍት ሀዋቂ ግብጻዊ ከብሉይና ከሐዲስ ያወጣውን በልቡ ያለውን ሊነግረው መጣ። (አቡነ ዕዝራ) ፍላጻ መድኃኒት ከአፎቱ አውጥቶ በ(መንፈሳዊ) መሣሪያ ተዘጋጅቶ አገኘው።[55]

ፈተና

ግብጻዊው ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራን ስለ ሃይማኖቱ ያለውን ጥንቃቄ ሲያይ አውሬ ሆነበት፤ "አንተ ዐዋቂ ጥበበኛ ነህ፤ ለምንድን ነው ለሰው ልጅ ሥራ ለዕንጨትና ለድንጋይ የምንሰግደው? አፍ አላቸው፥ አይናገሩም፤ ዓይን አላቸው፥ አያዩም ፤ ጆሮ አላቸው፥ አይሰሙም ፤ አፍንጫ አላቸው፥ አያሽቱም፤ እግር አላቸው አይሄዱም፤ በአንደበታቸው አይናገሩም፤ ነፍስ የለባቸውም።[56] ደግሞ ነቢዩ፥ ለግማሹ ትሰግዳለህ፤ ግማሹን ታነዳለህ፤ ሥጋም ትጠብስባቸዋለህ[57] ይላል" አለው።

---

54. "ለመስቀልከ ንስግድ ኦ ሊቅነ ወለትንግኤከ ቅድስር ንሴብሕ ኮልነ" ጸመ ድጓ ዘለቅለት፥ አምሰቱ ጸዋትወ ዜማዎች፥ አዲስ አበባ 1965፥ ገ. 92፥ ዓምድ 1።

55. አነጋገሩ ስምና ወርቅ ቅኔ ነው። "ፍላጻ" ጠላትም ሆነ አውሬ መንደፊያ ወስፈንጥር ሲሆን መድኃኒትነቱ ከጠላት የተወረወረ ከበሽታ የሚቈጠር ተንኮል ላለበት ጥያቄ ነው።

56. መዝ 134: 16-17።

57. ኢሳ 44: 15። እነዚህ ሁሉ አንቀጾች ከገድሉ ውስጥ የገቡት የደቂቀ እስጢፋኖስ አምነት እንደሚታሙት አለመሆኑን ወይም መመለሳቸውን ለማሳየት ነው።

ይኸንን የጠየቀው የተደበቀ ሃይማኖት ያገኘ እንደሆነ ምክንያት ፈልጎ ነው። ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ሲስማ ተቆጣው። "እንዲህ ለመናገር ለምን ደፈርክ? የምንሰግደው ለዕንጨትና ለድንጋይ አይደለም፤ ሊቀ ጳጳስ ሲቀድሰው ስለሚቀደስ ነው እንጂ፤ ቅዱስ ሜሮን ሲቀባው በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ያድርበታል። የምንሰግደው ስለዚህ ነው። ክርስቲያናዊ ሆነህ ሳለ ተጠራጣሪና ሃይማኖተ ጎደሎ አትሁን" አለው። ያ ግብጻዊ፥ "በእውነት እንደ ሐዋርያት የወንጌል ሰባኪ ነህ፤ እኔም በኢየሩሳሌም አካባቢ ሁሉ፥ በገሊላና በይሁዳ ቀበሌም ስላንተ አስብካለሁ" አለው። በሰላም ተሰማሙ።

ክህነት ከማን መንበር ጳጳስ ይቀበሉ?

በሶስተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ ከጌታችን መቃብር ካለው (79) የሶርያ መንበር ቅስና ሊሾም ፈለገ።[58] "ክህነትን ከእስክንድርያ ትወስዳላችሁ እንጂ ይህች (የሶርያ) መንበርስ የናንተ የኢትዮጵያውያን አይደለችም" አሉት። ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ፥ "የኛ እንደሆነች እረታችኋለሁ፤ ምክንያቱም እኛ የሶርያው አባ ሰላማ ልጆች ነን" ብሎ መለሰላቸው። "በል እርታን" አሉት። "እስቲ የምስር ታሳላቆች ይናገሩ" አላቸው።

በዚህ ጊዜ ከሚቃወሙት መካከል አንድ ሽማግሌ ተነሣና ወገኖቹን እንዲህ አላቸው፤ "ሁኔታውን ስለማውቀው፥ እዚህ ነገር ውስጥ አትግቡ።" ለሚያስታርቋቸው፥ "የሆነውን እንድነግራችሁ አነሱን ራቅ አድርጓቸው" አላቸው። የሚከራከሩትን አራቁቸው። ሽማግሌው፥ "ነገሩ እውነት እንደ ሞገሳዊው አቡነ ዓዝር[59] ነው፤ ብቻ አባ ሰላማ ከሞተ በኋላ፥ ዐዋቆች አስተካክለውታል። ከሀገሩ ርቀት የተነሣ ብዙ ጳጳሳት ኢትዮጵያ ምድር ሳይደርሱ ስለሞቱ፥ "ኢየሩሳሌም ለሶርያ፥ ኢትዮጵያ ለእስክንድርያ ይሁኑ አሉ። በማስረጃ ከረታችሁ (ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን) ይወጣሉ፤ እንግድነታቸውን አስባቸሁ (የሚፈልጉትን ክህነት) ስጧቸው" አለ።

የሰሙት፥ "የመንበሩ ተድላ ፍርድና ትክክልነት ነው"[60] አሉ። "ምስክሮች ሳይነግሯችሁ ኖራችኋል፤ አሁን ግን በእግዚአብሔር ፍርድ ረታችሁ" አለ። እዚያ የነበሩ የኢትዮጵያ ሰዎች፥ "በፊት ፈልሳ የነበረችውን መንበር የመለሰ ጎልማሳ አባታችን፥ ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ተነሣልን" እያሉ ጮሁ። ያለፈቃዳቸው ወደዱት፤ በዚያን ጊዜ የ ... ዓመት[61] ልጅ ስለነበረ አባ ዮሐንስ ቅስና ሰጠው።[62]

---

58. ወደ ሶርያ ጳጳስ ከሄዱ እውነትም በሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ተጽእኖ የግብጹ ጳጳስ ክህነት ቢከለክላቸው ነው።
59. በዓረብኛ ዕዝራ "ዓዝር" ነው። የግብጽ ክርስቲያኖች ቋንቋቸው ዓረብኛ ሆኗል።
60. መዝ 96: 2።
61. የዕድሜው ቍጥር አልተጻፈም።
62. ጎዳግ ቍጥር 40ን ተመልከት።

ወደ ኢትዮጵያ መልስ

ከዚያ፥ የፈለገውን ሲያገኝ፥ ጦቢያ የአባቱን ነገር እንዳስታወሰ፥[63] የብፁዕ አቡነ አበክረዙንን ነገር አስታወሰ። ከዚያ በኋላ፥ በሊቀ ጳጳሳቱ ተባርኮ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ከአንድ ወንድም ጋራ ተነሣ። ሀገራቸው በሰላም ደረሱ።

(ኢትዮጵያ ያሉ ወንድሞቹ) ዜናውን ሲሰሙ ተደሰቱ፥ ደስ አላቸው። የከሰዋ ማኅበር ተቀበሉት፤ እጅ ተነሣሡ፤ የአስራኤል ልጆች ዮሴፍን ሲያገኙ እንዳለቀሱ[64] መራር ለቅሶ አለቀሱ፤ "የመረግድ አልማዝ አስጢፋኖስን የት ተውከው? የሰንፔር አልማዝ ጴጥሮስ፥ የጳዝዮን አልማዝ ጸጋ ሥሉስ፥ የወራውሬ አልማዝ አብረኮሮስስ፥ ሌሎቹስ የባሕርይ ዕንቁዎች የት አሉ?" አሉት። "ሁሉም በሥርዓታቸው (ሳይከዱ) አበቁ" አላቸው። ብዙ አለቀሱላቸው።[65] እንደ ብፁዕ አቡነ አበክረዙን ቃል፥ ዜና ያመጣላቸውን (አቡነ ዕዝራን) ያሳያቸውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

ጥቂት ካረፈ በኋላ እነሱም የአባታቸውን የአበክረዙንን ዕረፍት አረዱት። ጢሞቴዎስ በመምህሩ በጳውሎስ ላይ እንዳለቀሰ[66] አምርሮ አለቀሰ። ጥቂት ቀናት ከቆየ በኋላ፥ የውሐ ወፍጮ ሠራ፤ የግብጽን ጥበብ ሁሉ ተምሮት ነበረ። የሰሎሞን ጥበብ እንደተሰማ የሱም ጥበብ በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ ተሰማ። ከዚያ፥ የ(እሴ) አስክንድር[67] ዘመን መኳንንት ፈለጉት፤ ግን አላገኙትም።

ንጉሥ ናኦድ አቡነ ዕዝራን ስለ መፈለጉ

ከዚያ፥ በሀገሩ ላይ አንበሳ ለፀር የተባለው እንደ ቄስጠንጢኖስ ሃይማኖት ወዳጅ ንጉሥ ናኦድ ነገሠ።[68] እሱም ጥበቡን ሰምቶ ወደ ዐጋሜ ሹም እንዲህ ሲል ላከበት፤ "ዕዝራን ካገኘኸው ከፉ ነገር እንደማናደርስበት የኪዳን ቃል ስጥተኸው ወደኛ አምጣው።" (80) ለመልከተኛው፥ "(ዕዝራን) አላውቀውም፤ ምክንያቱም እኔ ዘንድ ደቂቀ አስጢፋኖስ የሉብኝም" አለው። የዐጋሜው ሹም መልእክተኛውን በጥሩ ቃል ከሸኘ ከኋላ ሞገሳዊው አቡነ

---

63. ጦቢ 10፡ 8።
64. ኩፋ 35፡ 18።
65. ግዕዙ የሚለው "ብዙ አለቀስላቸው" ነው። ሊያረዳ የፈለገው "ወንድሞቹ እዚያው እንዳረፉና እሱም ብዙ እንዳለቀስላቸው" ሊሆን ይችላል።
66. *ገድለ ሐዋርያት፥* E. A. Wallis Budge, *The Contendings of the Apostles,* pp. 50-66 ይሆናል።
67. 1471-1487 ዓ. ም.።
68. አፄ ናኦድ የገዛው ከ1488 እስከ 1500 ነው። በአይሁድነት ስለተጠረጠሩ ከቤተ መንግሥቱ እንዲያጠፋቸው ካህናቱ የጠየቁትና እሱም እጠፋቸው የተባለው ደቂቀ አስጢፋኖስን ነው የሚባለው ከዚህ ዘገባ ጋራ እይስማማም፤ Carlo Conti Rossini, "Il Convento di Tsana in Abissinia," pp. 599-600; Osvaldo Raineri, *Atti di Habta Māryām (ፆ1497) e di Iyāsu (ፆ1505), Santi Monaci Etiopici*, Roma 1990, pp. 114 and 214.

ዕዝራን በድብቅ ጠርቶ፥ "ከኛ ጋራ ወደ ንጉሡ መሄድ ትፈልጋለህን? ምክንያቱም ሊያገኝህ ጓጉቷል፤ (ብትሄድ) የአባትክን ሃይማኖት በግብጽ እንዳስረዳኸው እዚያም ትነግራለህ፤ ለኛም ምስጋና ይሆነንና በንጉሡ ዘንድ ሞገስ አናገኛለን" አለው።

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ፥ "መምህርና ማኅበር ከፈቀዱልኝ (እሄዳለሁ፤) ስለ ክርስቶስ ሃይማኖት ስቅላትንና ሞትን አልፈራም" አለው። ይኸንን ሲሰማ እንዲህ ብሎ ለንጉሡ ደብዳቤ ላከ፤ "የፈለጋችሁትን ሞገሳዊው ዕዝራን አገኘሁት፤ አንግዴህ የኪዳናችሁን ቃል የሚያስማው መልእክተኛ ላኩ።" ንጉሡ ሲሰማ ተደሰተ። እንዲህ ሲል መልእክተኞች ላከ፤ "ለኔ መስገድ ይቅርልህ፤ መምህርህን መስደብም እንደዚሁ (ይቅርልህ ብለናል) በሉት።" መልእክተኞቹ መጥተው ይኸንን ቃል ለዐጋሚው ሹም ነገሩትና፥ "አንተም አብረኸው ና" (ተብለሃል አሉት)። ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ሲሰማ ለመሄድ ተዘጋጀ። በመሄዱ ምክንያት በቀሩት ማኅበር ዘንድ ትልቅ ሐዘን ሆነ። ምርር ያለ ለቅሶ ተላቀሱ።

ከዚያ፥ በታኅሣሥ ... ቀን[69] ለመሄድ ተነሣ። የንጉሡ መልእክተኞች ተቀብለው ንጉሡ አንዳዘዘ በክብርና በደስታ (አጅበው) ወሰዱት። ከልጆቹ አንዳንዶች አብረውት ሄዱ። ከመስቀሉና ከማኅበሩ በረከት በቀር ለመንገዱ (የያዘው) ስንቅ አልነበረም። የማኅበሩ አለቃ አቡነ ገብረ መሲሕ ሁኔታውን አስኪሰሙ ድረስ በደብሮቹ ሁሉ ዘንድ ምህላ እንዲይዙ አዘዘ።

ንጉሥ ናኦድ አቡነ ዕዝራን በክብር ተቀበላቸው

ጥር ፤ ቀን[70] ከንጉሡ ስፈር ደረሱ። ንጉሡ መምጣቱን ሲሰማ ድንኳኑን በቀይ ልብስ አስጌጠው፤ ወታደሮቹንም በየሥርዓታቸው አስለፋቸው። በቀኝና በግራ አንበሶች አቆመና ከስቀላው[71] አንዲያስገቡት አዘዘ። የዐጋሚው ሹምም አብሮት ነበረ። (ንጉሡ) ግርማውን አወረደባቸው። ግን ለማስፈራት እንጂ ክፉ ነገር ሊያደርስባቸው (አስቦ) አልነበረም፤ በሰላም ቃል ተቀበለው። የሠራዊቱን አለቃ እንዲህ ሲል ላከበት፥[72] "እንኳን በሰላም መጣህ፤ ሃይማኖትህ ምንድን ነው? ለማርያምና ለአንድ ልጁ መስቀል ትሰግዳለህን?"

ጥበበኛው አቡነ ዕዝራ፥ "እንዲህ በሉት" ብሎ፥ እንዲህ መለሰ፤

> ስለ ሰላም ስላልከው፥ የእግዚአብሔር ሰላም ካንተ ጋራ ይሁን። ደግሞ ስለ ሃይማኖት ስላልከው፥ ሃይማኖቴ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ (ማመን) ነው። ለማርያምና ለአንድ ልጁ መስቀል ስለ መስገድ፥ እኔ እስግዳለሁ፤ መምህሮቼም (ይሰግዳሉ)፤ ምክንያቱም መጽሐፉ፥ "የጌታችን እግር በቆመበት ቦታ እንሰግዳለን"[73] ይላል።

---

69. ቊጥሩ አልተሰጠም።
70. ቊጥሩ 10 ብቻ አልነበረም፤ ግን የቀረው አልተጻፈም።
71. የነገሥቱን የአደባባይ አዳራሽ "ስቀላ" ይሉታል።
72. ንጉሥ ዜጋውን በ"አፈ ንጉሥ" አንጂ በቀጥታ አያናግርም።
73. መዝ 131: 7።

ቦታው የማርያም ሆድ ነው። ሌላው ነቢይ፥ "የምድር ንጉሦች ሁሉ ይሰግዱልሻል፤ የእግርሺንም ትቢያ ይልሳሉ"[74] ይላል። ብዙ መጽሐፎች ታላቅነቷንና ክብሯን ይናገራሉ። ሰለ መስቀልም በመለኮት ደም ስለተቀደሰ፥ ሊቃውንቱ እንዲህ ሲሉ እዝዘዋል፤ "ሊቃችን ሆይ፥ ለመስቀልህ እንሰግዳለን፤ በቅድስት ትንሣኤህም ሁላችንም እናምናለን።"[75]

ይሽንን ለንጉሡ ነገሩት። ከዚያ፥ መልእክተኞች በወርቅ ቀለም ከልጇ ጋራ የተሣለ የመቤታችንን የማርያምን ሥዕልና በአልፋ[76] ጐን ደም የሰዘበ መስቀል አመጡለትና፥ "በል ስገድና ሃይማኖትህን በሕዝብ ፊት አሳየን" አሉት። ጥበበኛው አቡነ ዕዝራ (81) የመቤታችንን ሥዕልና መስቀሉን ሲያይ፥ ወዲያው በእደባባዩ (በሰው) ሁሉ ፊት ከልጆቹ ጋራ በፍጥነት ሰገደ። ከልጆቹ ጋራ እንዲህ ብሎ እጅ ነሣ፤ "ነቢዩ ዳዊት አሕዛብ በጉባኤ ከፍ ከፍ ያደርጉታል። በሊቃውንት ሽንጎም ስብሐት ያደርሱለታል"[77] ያለው ለእንደዚህ ያለው ቀን ነው እኮ። በእርግጥ ይሽ ጉባኤያችንና የሊቃውንታችን ሽንጎ ማርያም ነች።"

የሆነውን ሁሉ ለንጉሡ ነገሩት። ከዚያ፥ እንደገና ንጉሡ ጠቢቡን አቡነ ዕዝራን፥ "መምህርህ የማርያም ጠላት ከሆነ ርኩስ ነው በል" አለው። ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ሲመልስ፥ "በሱ ላይ ክሕደት እሳየሁበትም፤ ሃይማኖቱን ጠይቄ የማርያምን ፍቅር ያገኘሁት ከሱ ትምህርት ነው። (ለምሳሌ) እናንተ ሕግና ትእዛዝ የተዉልንን ጴጥሮስንና ጳውሎስን ከሐዲ ታደርጓቸዋላችሁን?[78] ደግሞ ጌታ ቶማስን እንዲህ ብሎታል፤ ሳያዩኝ የሚያምኑኝ ብፁዓን ናቸው[79] እስ በሉት" አለ።

እንደዚሁ ያለውን ለንጉሡ ነገሩት። ከዚያ በኋላ፥ ንጉሡ፥ "ማርያምንና መስቀልን የሚጠላን እትስድበውምን?" አለው። እንዲህ አለ፤

> የምሰድበው እኔ ላልሆን ነቢዩ ብሎታል፤ እንዲህ ሲል ረግሟቸዋል፤ "ጽዮንን የሚጠሏት ሁሉ ይፈሩ፥ ይዋረዱም፤ ሳይነቀል እንደሚደርቅ በሰገነት ላይ እንደበቀለ ሣር ይሁኑ፤ ለሚያጭደው እጁን፥ ነዶዎቹም ለሚለበስበው እቅፉን የማይሞላለት ይሁኑ።"[80] ሌላው ነቢይ ደግሞ፥

---

74. ኢሳ 49፡ 23።
75. ጸመ ድጓ፥ ዘስቅለት፥ በስድስቱ ሰዓት፥ አምስቱ ጸዋትወ ዜማዎች፥ አዲስ አበባ 1965፥ ገጽ 92፥ ዓምድ 1።
76. አምላክን "መጀመሪያውም መጨረሻውም አንተ ነህ" ለማለት ራእየ ዮሐንስ እንደሚያደርገው በግሪክ ፊደል መጀመሪያና መጨረሻ "እልፋ እና አሜጋ" ይሉታል።
77. መዝ 106፡ 32።
78. ጴጥሮስና ጳውሎስ ስለ እመቤታችን ብዙ አልጻፉም። ይሽ ፀረ ማርያም አያደርጋቸውም ማለታቸው ይመስላል።
79. ዮሐ 20፡ 29።
80. መዝ 128፡ 7።

"በምድር የምትኖረውን፥ የኤዶምያስ ልጅ ሆይ፥ ተደሰቺ፥ ደስ ይበልሽ"[81] ይላል። የሚጠሏትንም፥ "ፈታቸው ከጥቀርሻ ይልቅ ጠቊሯል፤ ቈዳቸው ወደ እጥንታቸው ተጣብቋል። መንገዳቸውም እልታወቀም"[82] ይላል። ነቢያት ይኸንን ይላሉ። እኔም ከእዳም እስካሁን ርኩሶች ናቸው፤ ራሴም ብሆን የእምላክ እናት ማርያምን ከጠላሁ (እንደዚሁ ነው) በሉት።

ይኸንንም ለንጉሡ ነገሩት። ሰምቶ፥ "ሃይማኖትህን ተረድተናል፤ እግዚአብሔር ምንኵስናህን ይባርክ፤ ወደ ማረፊያህ ሂድ" አለ።

ከጳጳሱ (ከአቡነ ይሥሐቅ) ፊት

ከዚህ በኋላ፥ ወደ ጳጳሱ (ወደ አቡነ ይሥሐቅ) ሄደ፤ በዚያን ጊዜ ሰልጎኒ ነበረ። ለጳጳሱ፥ "ነጋዲው ዓዝር መጥቷል" አሉት። "ከፊቱ አቁሙኝ፤ እግብጽ ያውቀኛል፤ እኔም ጳጳስ ሳይሆን አውቀዋለሁ" ስላለ ይኸንን ነገሩት። (ጳጳሱ፥) "ወዲህ አምጡት" አለ። ከፊቱ ቆመ። ጳጳሱ አየውና ወዲያው ዐወቀው። "እዚህ ምን አመጣህ?" አለው። "የእስጢፋኖስ ልጅ ስለሆንኩ ሃይማኖቴን እንድናገር ነው። ኢትዮጵያውያን፥ እንዳይካኑ ጳጳስ አውግዟቸዋል ይሉናል። እኛም (በዚህ ጉዳይ) ከሁለት ተከፍለናል፤ አንዳንዱ (ክፍል)፥ ነፍስ ስላስገደለ ከሱ እጅ ክህነት አንቀበልም[83] ይላል። አንዳንዱ፥ ከ፹፩ የሕግ መጻሕፍት አልወጣንም፥ ከአባቶቻችን ከሐዋርያትና ከተከተሏቸው ሊቃውንት የተለየ ትምህርት አላመጣንም፤ ስለዚህ ግዘቱ አይነካንም ይላል። አንዳንዱ ደግሞ፥ ግዝት አንጥስም፥ ክህነት አንቀበልም፥ ምክንያቱም ሳያጣራ እንዳስገደለን ራሱ ያውቃል ይላል" አለው።

ጳጳሱ አቡነ ዓዝርን፥ "አንተስ የምትተባበረው ከየትኞቹ ጋራ ነው?" አለው። እኔ፥ "ክህነት እንቀበል፤ ምክንያቱም ነቢዩ እንዳላፍር በፍርድ ልቤ ንጹሕ ይሁን[84] ይላል" አለው። ጳጳሱ፥ "ጥሩ ብለሃል" አለው። ጳጳሱ ደግሞ፥ "(እስከ ዛሬ) የት ነበርክና ነው ይኸንን ሃይማኖትህን ልትነገረኝ ያልመጣኸው?" አለው። "አሁንም ቢሆን የንጉሡ ቃል ባይሆን ኖሮ አልመጣም ነበረ፤ በመንገድ እንደሚይዙን፥ ንብረታችንን እንደሚቀሙን፥ በኛ ላይ የፈቀዱትን እንደሚያደርጉብን አላወክምን? ማንም አያመልጣቸውም። ስለዚህ መምጣት አልተቻለኝም። እንደመደነቂያ[85] በብቸኝነት ኖርኩ" አለው።

---

81. ሰቆ 4: 21።
82. ሰቆ 4: 8።
83. ደቂቀ እስጢፋኖስን ንጉሡ ሲያስገድላቸው ጳጳሱ አለመቃወማቸውን ነፍስ እንዳስገደሉ ቈጥረውት ሊሆን ይችላል።
84. መዝ 118: 80።
85. መዝ 70: 7።

በቀድሞ ጳጳሳት የተገዘቱት ተፈቱ

ቀጥሎ÷ (82) "ሥልጣን ስላለህ የሞቱትንም በሕይወት ያሉትንም ግዝት ፍታ" አለው:: በዚያን ጊዜ ጳጳሱ ወገኖቹን ግብጻውያኑን÷ እንጦንስ ወልደ አኅተን÷ ሁለተኛ ሠዓሊውን መርቆርዮስን÷ ሶስተኛ ፋሲለደስን÷ አራተኛ ነጋዲ ኢትዮጵያዊውን ገብረ መንፈስ ቅዱስን ምስክር አቁሞ እንዲህ ሲል ፈታ፤ "በጠዋት ያሰርኩትን በምሽት እፈታለሁ፤ በምሽት ያሰርኩትን በጠዋት እፈታለሁ፤ አሁንም በሥሉስ ቅዱስ አፍ የተፈቱ ይሁኑ::[86] የማርያምና የመስቀል ፍቅር ያለባችሁ ዛሬ ጥር ፳፩ ቀን የማርያም በዓል ነው:: ለኔም ለናንተም ምስክር ትሁንን፤ ላንተም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በዕለተ ፱ (በጰንጠቆስጤ) በሐዋርያት ላይ (እንዳደረ) ይደርብህ" አለ::

አቡነ ዕዝራና ወንድሞቻቸው ከንጉሡ ፊት ቀረቡ

ከዚህ በኋላ÷ ጥቂት አረፉ:: ንጉሡ ደግሞ ጠራቸው፤ ከወንድሞቹ ጋራ (ከፊቱ) ቆመ:: ንጉሡ ጥበበኛውን አቡነ ዕዝራን እንዲህ አለው፤ "እስቲ የጅ ሥራህን አሳየኝ፤ ጥበብህን እትደብቀኝ::" ጥበበኛው አቡነ ዕዝራ እንዲህ አለው፤ "የሥጋ ጥበብ ጥቅም የለውም፤ ሐዋርያው÷ እግዚአብሔር የዚህን ዓለም ጥበብ ሞኝነት አድርጓታል[87] ይላል:: አሁንም መጀመሪያ የሰማዩን ጥበብ እንፈጽም::"

ንጉሡ ሲሰማ ድንቅ ሆነበት፤ "የሰማይ ጥበብ ምንድን ነው?" አለ:: ጥበበኛው አቡነ ዕዝራ፤ "የሰማይ ጥበብ የነፍስና የሥጋ ሕይወት÷ የጥል ግድግዳን የሚያፈርስ ፍቅርና ሰላም ነው:: እኔ የመጣሁት የአባቶቼን ሃይማኖት ስላከፉብኝ (ትክክሉን) ላስማ ብዬ ነው እንጂ ስለ ጥበቤ በሰዎች ለመመስገን አይደለም" አለው:: ንጉሡ ሰዎቹን÷ "ጥበቡን በዚህ ዕወቁ" አላቸው::

በንጉሡ ትእዛዝ የሃይማኖት ክርክር ተደረገ

ከዚያ በኋላ÷ ንጉሡ የደብተራውን ካህናት ሰበሰበና መጋቢት ፲ ቀን ጥበበኛውን አቡነ ዕዝራን ከወንድሞቹ ጋራ ጠርቶ ከፊቱ አቆመው:: ንጉሡ የደብተራውን ካህናት እንዲህ አላቸው፤ "ሃይማኖቱን ያለጭቅጭቅ በአውነት ተረዱ:: ከናንተ ጐቱ (ለክርክሩ) ይቁሙ፤ የተረፋችሁት ያለማዳሳት ፈራጆች ሁኑ::" ከዚያ÷ የጣናው አባ ሲኖዳ÷ የወርወሩ ቶማስ÷ የደብተራው ገብረ መስቀል እና ሌሎች ከነሱው ውስጥ ፪ ብድግ አሉ:: የሚሰሙ የንጉሡ መኳንንትም በቀኝና በግራ ቆሙ::

ከዚያ÷ የደብተራው ካህናች ጥበበኛውን አቡነ ዕዝራን÷ "ለንጉሡ ስገድ፤ መምህርህንም ተሳደብ:: ይሽንን እምቢ ካልክ አንሰማህም:: ካንተ

---

86. ካህኑ የተገዘተን ሲፈታ የሚለው የተለመደ ዓረፍተ ነገር መሆን አለበት::
87. 1 ቆሮ 1: 20::

ጋራም አንነጋገርም፤ ተገዝተናል" አለው:: ጥበበኛው አቡነ ዕዝራም÷ "አኔም ከናንተ ጋራ አልነጋገርም፤ ለመሳለቅ አንጂ አውነትን ለማግኘት አልመጣችሁም" አላቸው:: ይኸንን አንደተባባሉ ለንጉሡ ነገሩት::

ንጉሡ÷ "ሃይማኖቱን አንድትመረምሩት ነው አንጂ ይኸንን አንድትናገሩት ማን አዘዛችሁ?" አላቸው:: የንጉሥ ቃል ጎይለኛ ስለሆነ ያለፈቃዳቸው ተዉት:: "በል ንገረን፤ በማን ታመልካለህ?" አሉት::

ዕውቀት የተመላው ጥበበኛ አቡነ ዕዝራ አንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤ "በአብ÷ በወልድ÷ በመንፈስ ቅዱስ አመልካለሁ፤ አባቴም አኔም÷ ወንድሞቼ ሁሉ ትምህርታችን አንደዚህ ነው:: አብ የወለደ÷ ወልድ የተወለደ÷ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣ÷ የአብና የወልድ መንፈስ÷ ያልተወለደ ያልወለደ ነው:: ከህላዌው ጭማሪም ቅናሽም የሌለበት ፫ ገጾች ነው:: በነቢዩ (አፍ) ÷ ገጽህን ፈለግሁ፤ አቤቱ ያንተን ገጽ አፈልጋለሁ፤ ገጽህን ከኔ አታዙር::[88] አንዳለው÷ ፫ ህላዌ አና ፩ ህላዌ ይባላል:: ፫ ስም÷ ፩ መለኮት÷ ፩ መንግሥት÷ ፩ ግዛት÷ ፩ ሥልጣን÷ ፩ ሕሊና (አንላለን)::"

ይኸንን ከቃሉ ሲሰሙ÷ "ይኸንንማ መበለትም (83) ታውቀዋለች÷ ከብሉይና ከሐዲስ ማስረጃ አምጣ አንጂ" አሉት::

ከዚያ÷ ጥበበኛው አቡነ ዕዝራ አፉን ከፍቶ አንዲህ አላቸው፤ "ከክህነት ምስጢር በቀር ሴቶች የማያውቁት ለወንዶች በድብቅ የተሰጠ ትምህርት አለን? መጻሕፍት (አስመስክር) ስለምትለው÷ አንግዲህ የሚሉትን ስማ፤ ከሁሉ አስቀድሞ ቅድስት ኦሪት÷ "በመጀመሪያ አግዚአብሔር ሰማይን ፈጠረ፤ ምድር ግን ከጥንት ጀምሮ አለች፤ አትታይም ነበረ:: የምትመችም አልነበረችም በጥልቁ ላይ ጭለማ ነበረ:: የአግዚአብሔር መንፈስ ከውሐው ላይ ስፍፎ ነበረ" ትላለች::[89] "በመጀመሪያ አግዚአብሔር ሰማይን ፈጠረ" ሲል÷ "አግዚአብሔር ዓለምን በልጁ አንደፈጠረ"÷ "ምድር አልታየችም" ያለው ይኸ ደግሞ "ከማርያም ሰውነትን ከመውሰዱ በፊት የሆነውን (ሲያመለክት) ነው፤ "የአግዚአብሔር መንፈስ በውሐው ላይ ሰፍፎ ነበር" ያለው ይኸ ደግሞ "ስለ መንፈስ ቅዱስ" ነው::"

ከነሱ ማህል ገብረ መስቀል የሚሉት ከደብተራዎቹ ፩ዱ አንዲህ ሲል መለሰ፤ "ይኸ የምትለው ትክክል አይደለም:: ይኸ ግልጥ ነው::" ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ÷ "አስቲ አንተ የምትለውን ንገረኝ" ብሎ ጠየቀው:: አሱ ሐሳቡን ከፍ በማድረግ÷ ዐዋቂ መስሎ÷ አንዲህ አለ፤ "አግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ÷ ይኸ ስለ ወልድ ነው::"

---

88. መዝ 26: 8::

89. ዘፍ 1: 1:: መጽሐፍ ቅዱሱ "ምድር ግን ከጥንት ጀምሮ አለች" አይልም፤ ስሕተት ነው:: ከቀጂ ማሳሳት የተነሳ ይህ ስሕተት በብዙ የጥንት ብራና መጻሕፍት ውስጥ ይታያል:: በግዕዙ "በቀዳሚ ገብረ ስማየ ወምድረ፤ ወምድርሰ ህለወት ዕራቃ" ሲል "ምድር" የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ ተከታትሎ ሲመጣ ጊዜ የመጀመሪያውን ወምድረ ጥለውት የመጀመሪያው አረፍተ ነገር "ስማየ" ላይ አልቋል:: ውጤቱ "በመጀመሪያ አግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ:: ምድርም ራቁቷን አለች" በመሆን ፈንታ ይኸው እንዲህ ሆነ::

አቡነ ዕዝራ የዕውቀቱን ስሕተት ባየ ጊዜ አፉን ከፈተና እንዲህ አሰ፤

የሙሴ መጽሐፍ ያለውን ስማ፤ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይን ፈጠረ::" ዳዊትም÷ "የመጀመሪያው በቅዱሳን ብርሃን በኃይል ዕለት አብሮህ አለ"[90] ብሏል:: ባለ ከፍተኛው ቃል ኢሳይያስም÷ "እኔ ለዘለዓለም የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነኝ"[91] ብሏል:: ወንጌላዊው ማርቆስም÷ "የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል÷ በነቢያት መጽሐፍ እንደተጻፈው÷ መጀመሪያው የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው" ብሏል[92] ወንጌላዊው ዮሐንስም÷ "መጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ያ ቃል እግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ያ ቃል እግዚአብሔር ነው:: እንደሱው ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ሁሉም በሱ ሆነ፤ ያለ እሱ የሆነ ምንም የለም"[93] ብሏል:: በመልእክቱ ደግሞ÷ "ስለ ሕይወት ነገር የመጀመሪያው÷ የሰማነው÷ በዓይናችን ያየነው የጠየቅነው÷ እጆቻችን የዳሰሱት ይህ ነው:: ሕይወትም ታወቀልን:: ምስክሮችም ሆነናል፤ እናበሥራችኋለን"[94] ብሏል:: በራእዩ ደግሞ÷ "እኔ ለዘለዓለም የምኖር÷ የመጀመሪያውም የኋለኛውም ነኝ:: የሞትና የሲኦል ቍልፍ እኔ ዘንድ አለ:: እንግዲህ ያየኸውን ጻፍ"[95] ብሏል:: ደግሞ÷ "እልፋና አ÷ የመጀመሪያውና የኋለኛው÷ ጫፍና ማለቂያ÷ ጥንትና መጨረሻ እኔ ነኝ::"[96] "እኔ ኢየሱስ ይኸንን ለናንተ ለቤተ ክርስቲያን እንዲያስማችሁ መልእኬን ልኬዋለሁ::"[97] እንግዲህ ይህን ጥቅስ ከልብህ አስተውለው፤ የእግዚአብሔርን ልጅ እንደዚህ ብርሃን ፍጡር ታደርገዋለህን? ብርሃንን የፈጠረው ሥራው እንዲታይበት ነው:: ስለዚህ ነቢዩ ዕዝራ እንደዚህ ይላል፤ "ጌታ ሆይ÷ ጌታዬ÷ በመጀመሪያው ግዛትህ በመጀመሪይቱ ዕለት÷ ሰማይና ምድር ይሁን ማለትን አልክ:: ቃልህ ፍጥረት ይፈጥራል:: መንፈስ ይሰፍፍ ነበረ:: ጨለማውም ሞልቶ ጸጥ ብሎ ነበረ:: ድምፅ አልነበረም:: የሰው ልጅ ድምጽም ከቶ አልነበረም:: በዚያን ጊዜ ከአዳራሽህ ብርሃን እንዲመጣ÷ ሥራህም እንዲታይ አልክ::"[98]

ያ ደብተራ የሞገሳዊውን የአቡነ ዕዝራን የቃሉን ስይፍ ሲሰማ÷ በቁጣ ፈዝዞ ቀረ:: "እንተ እንደምትለው ካልሆነ አንገትህን ትቈረጥ ወይ?" አለው:: አቡነ

90. መዝ 109: 3::
91. ኢሳ 44: 6::
92. ማር 1: 1:: ይኸም ስሕተት አለበት:: "የሕያው የአግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያው" የሚለው "የወንጌል መጀመሪያው የሕያው የአግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" ሆኖ ነበር::
93. ዮሐ 1: 1-3::
94. 1 ዮሐ 1: 1-2::
95. ራእ 1: 17-18::
96. ራእ 22: 13::
97. ራእ 22: 16::
98. ሱቱ 6: 38-40::

ዕዝራም፡ "አንተም (ወልድ) ፍጡር ነው እንዳለው እንደ ንስጥሮስ[99] ሃይማኖት ለዋጭ ሆነሃልና አንገትህን እንድትቈረጥ። የአህያ ወፍጮ አንገቱ ላይ አስረው፡ ከባሕር ጥልቀት ቢያስጥሙት (ይሻለው ነበር)[100] ያለው አንተን ነው" አለው።

(84) ለደብተራዎቹ ደግሞ፡ "ይኸ (ሰው) በሚለው እናንተም ትስማማላችሁን?" አላቸው። "የያዝከውን ጨርስ፤ እኛን አትጠይቀን" አሉት።

ይኸንን ሁሉ ሰንጉሥ ነገሩት። ንጉሡ ደብተራዎቹን፡ "ሃይማኖቱን እኔ እንደጠየኩት አንድትጠይቁት ነው እንጂ ከመጻሕፍት ጥልቅ አንድትገቡ ማን አዘዛችሁ?" አላቸው። አቡነ ዕዝራንም፡ "ትርጓሜ የጠየቁህ እንደሆነ ንጉሡ ይዘዘኝ እንድትል" አለው።

ደብተራዎቹ አቡነ ዕዝራን ደግሞ፡ "አስቲ በሰላመ ገብርኤልን ድገም"[101] አሉት። ጥበበኛው አቡነ ዕዝራ አፉን ከፈተና አነሱ ያላሰቡትን፡ "በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ" (ከሚሰው ጀምሮ፡) "መልአኩ ከእርሷ ሄደ"[102] እስከሚለው ድረስ አለ። ገረማቸው።

ደግሞ፡ "ክርስቶስ በማርያም ሆድ ስማደር ያስበው መቸ ነው?" አሉት። "ይኸንን የምትጠይቁት (መልሴን) ለማጽደቅ ነው ወይስ ሰመጣል?" አላቸው። "ስሕተት ካገኘንብህ ለመጣል እንፈልጋለን" አሉት። ከዚያ፡ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤

> ለትናንሽ ሕፃኖች የተገለጠውን፡ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ድብቅ፡ ምስጢር[103] በእግዚአብሔር ኃይል እነግራችኋለሁ። አንግዲህ (ነቢዩ) ዕዝራ ያለውን ስማ፤ "ጌታ ሆይ፡ ጌታዬ፡ ለባርያህ ንገረው፤ ዓለምክን በማን ትጐበኘዋለህ?" (አልኩት)፤ "መጀመሪያ በሕያዉ ልጅ፡ በኋላ ግን እኔው ራሴ፤ ምክንያቱም፡ ምድርና ሀገሮች ሳይፈጠሩ፡ የዓለም መንገድ ሳይቀደድ፡ የነፋሶች መንፈሶች ሳይነፉ፡ የነጐድጓድ ድምፅ ሳይሰማ፡ የመብረቅ ብርሃን ሳይበራ፡ የአትክልት ምድር ሳይመሠረት፡ የአበቦች ውበት ሳይታይ፡ የድልቅልቅ ኀይል ሳይጸና፡ የመላእክት ኀይል ሳይቈጠር፡ የሰማይ ምጥቀት ሳይታይ፡ የሰማዮች መለኪያ ሳይዘጋጅ፡ የሚመጣው የዓለም ፈለግ ሳይታወቅ፡

---

99. "ወልድ ፍጡር ነው" በማለት የሚታወቀው አርዮስ ነው፤ ንስጥሮስ በይበልጥ የሚታወቀው ክርስቶስ ቃል ያደረበት የማርያም ልጅ ስለ ሆነ ሁለት ባሕርይ አለው" በማለቱ ነው።

100. ማቴ 18፡ 6።

101. "(በመልአኩ) በገብርኤል ሰላምታ... ።" በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቊጥር 28 ላይ የተመሠረተ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ከአቡነ ዘበሰማያት ጋራ የሚደግሙት የዘወትር ጸሎት።

102. ሉቃ 1፡ 26-38።

103. ማቴ 11፡ 25።

ሃይማኖትን የሚመዘግቡ ሳይታተሙ፥ በዚያን ጊዜ እኔ ብቻዬን አስብኩ፤ ሌሳ አልነበረም::"[104] ይላል::

የንጉሡ ፍርድ

ይኸንን ሲሰሙ አደነቁ:: ለንጉሡ ነገሩት:: ንጉሡ፥ "አግዚአብሔር ሃይማኖትህን ይባርክ፤ ወደ ማረፊያህ ሂድ" አለ::

ወደ ማረፊያው ከሄደ በኋላ ንጉሡ ደብተራዎቹን እንዲህ አላቸው፤ "በጎች የምትበትኑ አረኞች ሆይ፥ ነቢዩ የጠፋውን አትፈልጉም፤ የደከመውን አታበረቱም[105] ያለው እናንተን ነው:: በተንኮል ልትገድሉት ፈልጋችሁ ነበረ፤ ሰበብ አጣችሁበት:: እሱ ግን ብርሃን ይሁን፤ ብርሃን ሆነ (ያለው) ስለ ወልድ ነው የምትሉትን የቃል ጉድለት አገኘባችሁ:: በእርግጥ አሱ እንዳለው ተሳስታችኋል:: አናንተ እንደምትሉት ብሎ ቢሆን ኖሮ እንዲገደል ትጮኹ ነበር:: ግን እግዚአብሔር ዳንኤልን እንዳዳነው አዳነው:: እኔም ትቻለሁ፤ የደቂቀ እስጢፋኖስን ደም ከማፍሰስ አልጨመርም::"

ስለ ተግባረ እድ የንጉሡ ጥያቄና የአባ ዕዝራ መልስ

ንጉሡ በማግስቱ ጥበበኛውን አቡነ ዕዝራን ጠርቶ፥ "መንፈሳዊ ጥበብን ፈጽመናል፤ ያለህን ጥበብ ንገረኝ" አለው:: "የማውቀውን ጥቂቱን ስለ አህያ (የድንጋይ) ወፍጮ፥ ስለ ውሐ ወፍጮ፥ ስለ ነፋስ ወፍጮ፥ ስለሚሽከረከር ሰረገላ፥ ስለሚጠርብም ውሐ፥ ቅባት ስለሚያወጡበት ማኅሠራ፥[106] ውሐ ስለሚያስቀዳ ውሐ እናገራለሁ" አለው::

መልእክተኛው ሲሰማ ደነገጠ:: "አባ ሆይ፥ ልብ አድርግ፤ በነጋሢ ቤት ውሸት አይናገሩም:: (ይህን ሁሉ አደርጋለሁ የምትለው) እግዚአብሔር ነህ እንዴ?" አለው:: ይኸንን ብሎ ሄደና ለንጉሡ ነገረው:: ንጉሡም አደነቀ:: ነገሩን የሚሰሙ ከታላላቆቹ ፪ት (ሰዎች)፥ (85) "አስረዳ በሉት" ብሎ ላከ:: (ለአቡነ ዕዝራ) ይኸንን ነገሩት:: "ይኸንን ብቻ አይደለም የምለው፤ ደግሞ ፻፱ በቀኝ፥ ፻፱ በግራ የሚሆኑ ማብሪያዎችም እሠራለሁ፤ (ለማብራት) አንድ መዘውር ሲሽከረከር ቅባቱ አይደፋም:: ሌላም ላንተ ካልሆነ ለሌላ የማልናገረው ጥበብ አለኝ (ብሏል በሉት)" አለ:: (ይኸንንም) ለንጉሡ ነገሩት:: "የአህያ ወፍጮ ሥራና ልይ በሉት" አለ:: (ሲነግሩት) "እሺ" አለ::

---

104. ሱቱ 4: 1-6::

105. ሕዝ 34: 4::

106. "ማኅሠራ"፥ "ማሕሰራ" የመሣሪያው ስም መሆን አለበት::

አባ ዕዝራና ወንድሞቻቸው ስሥራ ወደ አለመሌ ተላኩ

ንጉሡ ለልጆቹ በቍጥራቸው ልክ ... ቍርጥ ድርጎ÷[107] ለእሱ ግን ከሺህ ጋራ ብዙት[108] እንዲሰጧቸው አዘዘ። ብረትም የሚበቃቸውን (እንዲሰጧቸው አዘዘ።) ከመልአክተኛው ጋራ ብዙ ዕንጨት ወዳለበት ወደ አለመሌ ላካቸው።

እዚያ ሲደርሱ መልአክተኞቹ ንጉሡ ያለውን ለአገረ ገዢው ነገሩት፤ "ይኸ መነኮሴ የሚልህን አድርግ፤ ምግባቸውንም ስጣቸው።" ቀለባቸው[109] ሲሰማ ሠራዊቱን ሰብስቦ÷ ልጆቹ የመረጡትን ብዙ እንጨት አስቈረጠ።

(አቡነ ዕዝራ) በፈጣሪው ዘንድ ሞገስ ስላገኘ÷ ኖኅ መርከብ ሲሠራ እንዳደረገው ይሠራ ጀመር። ልጆቹን÷ "ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስድብ እንዳንሆን ጸልዩ፤ በጸሎት ማንኛውም ይቻላል።[110] በተለየ አንተ አባ ገብረ ሚካኤል ዕውቀት አለህ፤ ታላቃቸውም ነህ" አላቸው። እሺ አሉት።

የአባ ዕዝራ ጸሎት በሽተኛ ፈወሰች

እዚያ በነበሩበት ጊዜ እንዲት ሴት ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራን ሲያልፍ እየችውና÷ የሱን ሰዎች÷ "ማነው ይኸ" አለቻቸው። "የደቂቀ እስጢፋኖስ መምህር ነው" አሏት። "በእሱ አምላክ ተማፅኛለሁ" አለች። ዝም እንድትል ገሠጿት። እንደ ባለሹቶዋ ማርያም የእምነት እሳት በልቧ ነደደ።[111] "ወደሱ አቅርቡኝ" አለች። ወደሱ አቀረቧት፤ በእሱ ተባረከች። "አባ ሆይ÷ የማካፍልህ ችግር አለብኝ፤ ሆዴን በሽታ ከያዘኝ እነሆ ፴፩ ዓመት ሆነኝ። አሁንም በጸሎትህ ተማምኛለሁና በእጆችህ ዳሰሰኝ" አለችው።

ጥበበኛው አቡነ ዕዝራ ቃሏን ሲሰማ÷ "ጌታዬ ሆይ÷ ጸሎቴን ስማኝ÷ ፈትህን ከኔ እታዙር÷ የጠራሁህ ዕለት ቶሎ ስማኝ፤ ጌታ ሆይ÷ ምሕረትህን አሳየኝ፤ አምላካችን ማዳንህን ስጠን"[112] ብሎ ይኸንን ሁሉና የመሰለውን ጸልየና÷ "እሱ የተማመንሽው በሽታሽን ይፈውስልሽ" አላት። ይኸንን ብሎ ሐዋርያው እንዳለው የጸሎት ዘይት ቀብቶ÷[113] በእጆቹም ዳሰሳት። ልጆቹም በላዩዋ ላይ ጸልየው በሰላም ሸኟት። ወደ ቤቷ ሄደች።

---

107. የግዕዙ ቃል "ቈራጽ" ነው፤ የድርጎው ዓይነት ምን እንደሆነ አላውቅም÷ ብዛቱም አልተጻፈም።

108. (ባዘቶ?) ለሱም የተቈረጠለት ምንና ምን ያህል እንደሆነ ለኔ ግልጽ አይደለም።

109. "ቀለባስ" የማዕረግ÷ የሹመት ስም ነበረ።

110. ያዕ 5፡ 16።

111. "ባለሹቶዋ ማርያም" የሚሏት "ዋጋው እጅግ የበዛ የናርዶስ ሽቶ በጌታችን ራስ ላይ÷ ዕንባዋን በእግሩ ላይ ያፈሰሰችውን÷ ጌታችንም ጎጢአቷን ይቅር ያለላትን ሴት ነው፤ ማቴ 26፡ 6-13፤ ማር 14፡ 3-9፤ ሉቃ 7፡ 36-50።

112. መዝ 142፡ 1÷7፤ 137፡ 3፤ 84፡ 8።

113. ያዕ 5፡ 14።

የሀገሬው ሰዎች ምልክት ፈላጊዎች ስለሆኑ የሚዶን ልጆች የራጉኤልን ልጅ ላራን እንደሰለሏት ሰለሏት::[114] ከዚያ በኋላ፥ በሰባተኛው ቀን በታመመችበት ዘመን ቍጥር ልከ ፴፭ ከንድ የሚሆን አባብ ከሆዷ ወጣ:: እንደዳነች ስታይ ከዘመዶቿ ጋራ ወደሱ ሄደች:: እዚያ ስትደርስ ከእግሮቹ ላይ ወደቀችና፥ "አባ ሆይ፥ በጸሎትህ ተፈወስኩ" አለችው:: ዘመዶቿም እጅ ነሡት:: ከዚያ፥ አስቀድመው ደቂቀ እስጢፋኖስን ግብጻውያን የአሰራኤልን ልጆች እንደተጸየፉ[115] ይጸየፏቸው ነበረ:: ብፁዓዊው አቡነ ዕዝራ ሲሰማ ከልጆቹ ጋራ ተደሰተ:: "ጌታ ሆይ፥ ስለተቀበልከኝ አመሰግንሃለሁ፤ የጠላት መሳለቂያ አላደረከኝም፤[116] ሁል ጊዜና በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ስብሐት አቀርብልሃለሁ:: የሰማዮች ኀይሎች ሁሉ ስብሐት ያቀርቡልሃልና:: ስብሐት ለዓለም ዓለም ላንተ ይሁን፤ አሜን" አለ::

ሴትዮዋን፥ "እንግዲህ እንደ ፈቤን[117] በክርስቶስ ሃይማኖት ጽኚ" ብሎ፥ ባረካትና በሰላም ሸኛት:: የአገሬው ሰዎችም የሠራውን ተአምር ሰምተው ወደሱ መጡና በእሱ ተባረኩ:: "ታላቅ ነቢይ ተነሣ"[118] አሉ:: ትምሕርቱን መማሩን ግን በድብቅ ያደርጉታል እንጂ (86) ከደቂቀ አስጢፋኖስ ጋራ ተባበሩ እንዳይባሉ አልገለጡም:: ወንጌሉ እንዳለው፥ "ለአግዚአብሔር ከማድሳት ይልቅ ለሰው ልጅ አደሉ::"[119]

የወፍጮው መሣሪያ ተገጣጠመ

ብፁዑ ለአሀያ ወፍጮ የሚሆኑትን ክፍሎች ሲያገጣጥም ቆይቶ በአራተኛው ወር ጨረሰ:: ስንዴ አምጥቶ በአሀያ አስፈጨ:: የንጉሡ መልእክተኞች ሲያዩ ተገረሙ፤ እዚያ የነበሩት ሁሉ አደነቁ:: ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራም ከልጆቹ ጋራ ተደሰተ:: "የታመኑበትን ባሮቹን ያላሳፈረ እግዚአብሔር ስብሐት ይድረሰው" አለ:: መልእክተኞቹ ሄደው ለንጉሡ ነገሩት:: "እውነት ተፈጸመ?" አለ:: "አዎን" አሉት:: ከአንዴም ሁለቴ፥ ሶስቴ ጠየቃቸው:: እንደመጀመሪያው አስረዱ::

በዚያን ጊዜ በጥድፊያ እንዲያመጡት አዘዘ:: ለሎሞን ጠርቡን የሚሸከሙትን የሚነዱ እንዳደረገ[120] የሚነዷቸው ታላላቅ ሰዎች ላከ:: ሲደርሱ ወደ እሱ እንዲያመጧቸው (ንጉሡ) ማዘዙን ለጥበበኛው አቡነ ዕዝራ ነገሩት:: ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ሲሰማ፥ "ብልሹ እንዳይሆን ከዕንጨቶቹ ምንም እንዳታስቀሩ" አላቸው:: ሊሄድ ከልጆቹ ጋራ ተነሣ:: የንጉሡ ሠራዊትም ሸክማቸውን አንሥተው አብረውት ሄዱ::

---

114. ጦቢ 3: 7::
115. ዘል 43: 32::
116. መዝ 29: 2::
117. ሮሜ 16: 1::
118. ሉቃ 6: 16::
119. የሐ ሥራ 5: 9::
120. 1/3 ነገሥ 5: 12-16::

ወፍጮው በንጉሡ ፊት ተሞከረ

ሲደርሱ ለንጉሡ ነገሩት። ዘመኑ ክረምት ስለነበረ ንጉሡ በማግሥቱ ለአህያው ወፍጮ ድንኳን እንዲተክሉ አዘዘ። ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ እንደሚያውቅበት በንጉሡ ፊት ገጣጠመው። ወዲያው በአህያ አሰፈጨ። (ሊሠምር) የሰማይ አምላክን አመሰገነ፤ ምክንያቱም በፊት በሌሊቶች ትጋት በድብቅ በጸሎት ላይ ሳለ÷ "እግዚአብሔር የእጆችህን ሥራ ሁሉ ያሳምርልሃል" የሚል ቃል ሰምቶ ነበረ።

ንጉሡ አይቶ አደነቀ፤ በዘመነ መንግሥቱ ስለተሠራም ተደሰተ። ንግሥቶቹም[121] ሠራዊቱም ሁሉ ተገረሙ። ቀጥሎ ንጉሡ (ያሰፈውን) የሚያስታውሱ መኳንንቱን ሰብስቦ÷ ጳጳሱንም ጠርቶ÷ "ካሁን በፊት ከአብርሃና ከአጽብሐ አንሥቶ እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ እንደተሠራ በውኑ ሰምታችኋልን?" አላቸው። አንዳንዶቹ÷ "አልሰማንም" አሉ። አንዳንዶቹ÷ "ያለምትሐት እንደዚህ ማድረግ ይቻላልን?" አሉ። ጳጳሱ ግን÷ "እግብጽ ያለምትሐት እንደዚህ ይደረጋል" አሉ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ ሞገሳዊውን አቡነ ዕዝራን እንዲህ አለው፤ "ብዙ ጥበበኞች ከሮም÷ ከግብጽ÷ ከህንድ÷ ከቱርክ÷ ከፈረንሳይ÷ ከፋርስ÷ ከሊባኖስ÷ ከየሀገሮቹ ሁሉ መጥተዋል። (አንዱም) አንተ እንደሠራኸው የሠራልን የለም። አሁንም በመንግሥቴ ሰር ካለው (የቱንም) ተመኝ፤ ልብህ የፈለገውን እሰጥሃለሁ።"

በሄደበት ሁሉ ዕውቀቱ ሙሉ የሆነ ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "አላፊ አግዳሚው ሁሉ ርኩስ የሚለውን የአንድ ልጁን ሰማዕት የአባቴን የአስጢፋኖስን ስድብ እንድታሰጥልኝ እንጂ ለሹመትና ለምሰፍና ወይም ለመመስገን አልመጣሁም። እኛን ልጆቹንም ክርስቲያኖችና መነኮሴዎች ሆነን ሳለ÷ ባገኙን ቦታ ይገድሉናል፤ ልብሳችንንም ያስገፍፉናል፤ ንጉሥ ከሐዲዎች ይሉናል። ፍርዳችንን እግዚአብሔር ይንገርህ፤ ሰሎሞን÷ "ብይን በንጉሥ አፍ ይገኛል፤ በፍርድ ጊዜ አይሳሳትም"[122] ይላል። "እንደ ኪዳንህ እንዲሆን በመንግሥትህ አገሮች ሁሉ ዓዋጅ አስለፍፍልን።"

ንጉሡ የማኅበሩ መንፈስ በሄደበት አብሮት የሆነን ሞገሳዊውን አቡነ ዕዝራን እንዲህ አለው፤ "እንዳንተ ያሉ መነኮሳት ከኛ ዘንድ (ሰራሳቸው) ሹመት÷ ለልጆቻቸው ጉልት ይቀበላሉ። አንተ ሰምንድን ነው የምትመኳው÷ ከነሱም የምትለየው?" ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ÷ አዎን እለያለሁ፤ (87) የአባቴን ሥርዓት አልተውም፤ ምክንያቱም መጽሐፉ÷ "(የዚህን) ዓለም ገንዘብ የሚፈልግ በሁለቱም ዓለም÷ በዚህም በሚመጣውም÷ የተጐሳቈለ ይሆናል ይላል"[123] አለው።

---

121. በዚያን ዘመን ነገሥቱ ባንድ ጊዜ ከአንድ ሚስት የበለጠ ያገቡ ነበረ። ግን የንጉሥ አናትና ሚስትም ንግሥት ይባላሉ።

122. ምሳ 16፡ 10።

123. ?።

ንጉሡ ደግሞ÷ "ሹመት አምቢ ካልከ ለልጆችህ ማረፊያ ጉልት ውሰድ" አለው:: ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ÷ "ይኸንንም አልፈልግም፤ ሞቻለሁ÷ ታጥኛለሁ፤ ተገንዣለሁ÷ በአግዚአብሔር ታቦቶች ፊት ኪዳን ገብቻለሁ ያልኩ÷ አሁን ወደ ዓለም እመለሳለሁን?[124] መጽሐፍ ውሻ ወደ ትፋቱ ተመለሰ፤ አሳማም ታጥባ ወደ ጪቃ ተመለሰች[125] ይላል" አለው::

ንጉሡ የነገሩን ፍጻሜ ሰምቶ ባረከው:: "እግዚአብሔር ምንኵስናህን ይጠብቅልህ፤ በኋለኛዋ ዕለት አያሳፍርህ፤ አውነትም የምትሰው ሁሉ ኀላፊ ነው:: በመሞቴ ካልሆነ ከኔ አትለይ(ም)" አለው:: በዚያን ጊዜ ለምግቡ ፲፱ ሞፈ የሚሉት (ዳቦ) ከማር ወለላ ጋራ ዳርጎት ወደ ማደሪያው ተመለሰ::

አቡነ ዕዝራና ደቂቀ አስጢፋኖስን የሚጠላ መኰንን

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ከዚያ በኋላ ደግሞ አንድ መኰንን ደቂቀ አስጢፋኖስን እንደሚጠላ ሰምቶ ከቤቱ ሄደና ከፊቱ ቆመ:: "ሰላም ላንተ ይሁን" ቢሰው÷ "ሰላምታህን አልፈልግም፤ ካንተ ጋራ ወዳጅነት የለኝም" የሚል መልስ ሰጠው:: ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ÷ "ይኸንን የምትለው ለምንድን ነው?" ቢለው÷ "ምክንያቱም እንደሌሎች መነኮሴዎች ተአምር አታሳይም፤ አባ ኤዎስጣቴዎስ÷ አባ ገሪማ (ቢሆኑ) ተአምር ይሠራሉ" አለው::[126]

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ÷ "ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው÷ ተአምር ለአረሚዎች ነው እንጂ ለአማኞች አይደለም ይላሉ:: አንተም ተአምር ፈላጊ አትሁን" አለው:: ሲሰድበው÷ "ሃይማኖት ካለህ በላዬ ላይ ተአምር ሥራ" አለው:: ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ÷ "በል ላንተም ለኛም ጊዜ እንወስን" አለው:: የዓሥር ቀን ቀጠሮ አደረጉ::

ከዚያ በኋላ÷ አባታችን ወደ ማደሪያው ተመለሰ:: ልጆቹን÷ "ዛሬ ጸልዩ፤ ምክንያቱም÷ በአደባባይ ሁሉ ፊት÷ እስቲ በል በኔ ላይ (ተአምር) አሳይ ብሎኛል" አላቸው:: ከዚያ÷ አቡነ ዕዝራ መራር ዕንባ እያፈሰሰ በቆራጥ ልብ ይጸልይ ጀመረ:: እንዲህ አለ፤ "ጌታ ሆይ÷ ጌታ ሆይ÷ አንተን ፈለግሁ፤

---

124. ይህን መልስ አቡነ አስጢፋኖስም ሰጥተውታል::

125. 2 ጴጥ 2: 22::

126. አባ ኤዎስጣቴዎስ ቅዳሜ እንደ አሑድ ካልተከበረች ቢሉ ኢትዮጵያ ሰሚ ስላጡ ለማስመስከር ወደ ግብጽ÷ ከዚያም ወደ አርማንያ ሄደው እዚያው የሞቱ ጻድቅ ናቸው:: ከሠሩት ተአምራት ውስጥ ዓሥራ ስድስቱ ከገድላቸው ውስጥ ተመዝግበዋል:: ከነዚያ አንዱ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በሄዱ ጊዜ ባሕረ ኢያሪኮን (Mediterranean Sea) ልብሳቸውን ጀልባ አድርገው ወደ ቆጵሮስ መሻገራቸው ነው፤ B. Turaiev, *Monumenta Aethiopiae Hagiologia, vol. V: ገድለ ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ Vita et Miracula Eustathii*, Petropoli, 1905, pp. 134-176.:: አባ ገሪማ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ከመካከለኛው ምሥራቅ ከመጡት ተስዓቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን ከሚባሉት አንዱ ናቸው:: ከሠሩት ተአምራት ውስጥ ዓሥራ ሁለቱ ከገድላቸው ውስጥ ተመዝግበዋል:: ከነዚያ ሁሉ በጣም የታወቀው ታምራቸው በአንድ ቀን ዘርተው በዘሩበት በዘሩበት ቀን ማምረታቸው ነው፤ Carlo Conti Rossini, "L'Omelia di Yohannes, Vescovo di Aksum, in onore di Garimâ," *Actes du onzième Congrès International des Orientalistes*, Paris, 1897, pp. 159-169.

ካንተ በቀር ሌላ አላመልክም፤ ጠላቶቼ አሸነፍነው እንዳይሉ::"[127] ደግሞ እንዲህ አለ፤ "ጌታ ሆይ÷ በአንተ ተማምኛለሁና ለዘላለም አላፍርም:: ጠላቶቼም አይሣቁብኝ"[128] ደግሞ እንዲህ አለ፤ "አሁንም ለሚፈሩህ ለባሮችህ አፍረትና ስድብ ሆነባቸውና ነው እንጂ አፋችንን እከፍት ዘንድ አይገባንም:: ግን ለደግ የሚሆን ምልክት አድርግልን::"

ይኸንንና ይኸንን የሚመስለውን በጸሎቱ ውስጥ ሲናገር አንዲህ የሚል የዜና ብሥራት መጣ፤ "ንጉሡ ያንን መኰንን ተቆጥቶት÷ በከባድ እግር ብረት አሰረውና የጎያላን (መኳንንቱ) መቅጫ ከሆነችው ቤተ መዛግብቱ[129] አስገባው::" የቀጠሮው ጊዜ ሳይደርስ÷ በሶስተኛው ዕለት ታስረ::

ከዚያ በኋላ÷ ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ከልጆቹ ፪ቱን አንዲህ ሲል ላከበት፤ "ሰላም ላንተ ይሁን፤ እግዚአብሔር ይፍታሕ::" (መኰንኑ) ልጆቹን÷ "መምህራችሁን÷ እንድታሰር አድርገሃል፤ አንዳምንብህ እንድፈታም አድርግልኝ በሉት" አላቸው::

ተመልሰው እንዳላቸው ለአባታቸው ነገሩት:: ልጆቹን ደግሞ÷ "አሁንም ጸልዩ፤ እግዚአብሔር ያስባችሁትን ሁሉ ያደርግላችኋል" አላቸው:: እሱ ራሱ ግን የዚህን መኰንን ፍርድ (መጨረሻ) አስኪያይ ድረስ ከመጀመሪያው ጀምሮ ጸሎት አላቋረጠም ነበረ:: ከሁለት ሳምንት (ሱባዔ) በኋላ ደግሞ ንጉሡ ያንን መኰንን ከአስራቱ እንደፈታው ሰማ::

አንደበፊቱ ሁለቱን ልጆቹን÷ "አንኳን አግዚአብሔር (88) ፈታህ" እንዲሉት ላካቸው:: እንደዚህ ነገሩት:: "መምህራችሁ እኔ ዘንድ ይምጣ" አላቸው::

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ መጣና ከፊቱ ቆመ:: መኰንኑ÷ "በልብህ የማርያም ፍቅር እንዳለ ሃይማኖትህን ንገረኝ፤ ደቂቀ እስጢፋኖስን ስገድላቸውና ስገርፋቸው ኖሬያለሁ" አለው:: አባቶቹ ያስተማሩትን ሃይማኖቱን በዝርዝር ነገረው:: በዚያን ጊዜ መኰንኑ ወደደው:: ሰላምታም ተሰጣጡ:: "ከሞቱት ጋራ ማን ያስታርቀኛል?" አለው::

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር በቀል የሚተው ስለሆነ÷ ንስሐ ለገቡ የቀድሞ ሥራቸውን ሁሉ እንደማያስታውስ አላወቅክምን?" አለው:: መኰንኑ ሃይማኖቱን ተረድቶ እንደ ናቡክድናጸር አመነ::[130] አባትና እናት ሆነው፤ እንደ (ራሱ) ልጅም ምግቡን ሰጠው:: መኰንኑ ወደ እምነት ሲመለስ ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ እግዚአብሔርን

---

127. መዝ 12: 4/5::

128. መዝ 24: 2-3::

129. "ከመዝገቦቹ ቤት"፤ ይሄ አስር ቤት *በገድሰ አቡነ አስጢፋኖሽ* በገድሰ *አቡነ አበክረዙን* ውስጥም ተነሥቷል:: የቤቱ መዝገብነት ለእቃ ሳይሆን የፖለቲካ ወንጀለኞች ለማሳሪያ ነው:: ቦታው ከሌሎቹ ገድሎች ውስጥ "ጉንጽ" የሚባለው ሳይሆን አይቀርም::

130. ናቡክድናጸር ከክርስቶስ ልደት በፊት 600 ዓመት ግድም የገዛ የባቢሎን ንጉሥ ነበረ:: ኢየሩሳሌምን ወርሮ ቤተ መቅደሱን አፍርሶ፥ ሕዝቡንና ቅዱሳት እቃዎቹን ወደ ሀገሩ እግዟቸው ነበረ:: በአዬ ዘርአ ያዕቆብ አባባል ታቦቷንም ይዟት ሂዷል::

አመሰገነው። "ምሕረትን ወዳጅ ነው፤ ኃጢአቶቻችንን ያስጥማቸዋል፤ አበሳዎቻችንንም ከባሕር ጥልቀት ይወረውራቸዋል"[131] አለ።

የጳጳሱ በጎ ሥራ

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ በንጉሡ ደጃፍ ባለበት ጊዜ ጳጳሱ አቡነ ይሥሐቅ[132] ሞተ። በመንበሩ ላይ አባ ማርቆስ[133] ተቀመጠ። ከአቡነ ዕዝራ ጋራ ይስማሙ ስለነበረ ወደ መምህሩና ወደ ሩቆቹም ወደ ቅርቦቹም (ወንድሞች) ሁሉ እንዲህ ሲል ደብዳቤ ልኮ ነበረ፤ "ከጳጳሱ ጋራ ታርቀናልና ከህነት አንድትወስዱ ኑ። (ይህ ዕድል) ሁልጊዜ የሚገኝ አይደለም፤ ዘመን ይለወጣል።"

ወንድሞች ሰምተው ወደሱ ዘንድ መጡ። ወደ ጳጳሱ ወስዳቸውና በፊቱ ክህነት ተቀበሉ። (አሁን) "ደቂቀ አባ ዕዝራ" ስለተባሉ አንደበፊቱ የጐዳቸው አልነበረም። ወደየአድባራቸው በሰላም ተመለሱ። እነሱ ሲመለሱ ሌሎች ደግሞ በተራቸው መጡ። ከእሱ ዘንድ ደረሱ። ከንጉሡ በራፍ ከሱ ጋራ የተጠመቁ ቍጥራቸው ፫፻ ሆነ፤ (ዕለቱ) ዕለተ ጥምቀት ነበረ፤ ያዩዋቸው አደነቁ።[134]

ዮሴፍ ለወንድሞቹ ማረፊያ ሆኗቸው እንደነበረ እሱም የክህነት መስጫ ሥርዓት እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ ማረፊያ ሆኗቸው አዚያው ቆዩ።[135] መጠለያ አንዲሆናቸው ድንኳን ተከለላቸው።

ከነሱ ማህል ኪን የሚችሉ አናጢዎችና ጸሐፊዎች ለጳጳሱ ላከለት። ጳጳሱ ያዘዛቸውን ሁሉ አደረጉ። ከሱ ጋራ ጥቂት ጊዜ ቆዩ። አስተዋዩና ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ በጳጳሱ ቤት የክህነት መስጫ ሥርዓት መጀመሩን ሲሰማ ልጆቹን ላካቸው፤ እንዲህ ሲልም ባረካቸው፤ "የእስራኤል ልጆች ግብጻውያን እያዩዋቸው ክፋት ሊያደርሱባቸው ሳይችሉ እንደወጡ እንደዚሁ እግዚአብሔር በናንተ ላይ ተአምርና ትግርምት ያድርግ። ሂዱ፤ አትጠራጠሩ። የዕንጨትና የእብነ በረድ ጽላቶች ይዛችሁ ሂዱ። በኔ ምትክ የሚሆኑ ጳጳሱ የሚያውቃቸው ከልጆቼ ፪ቱ አዚያ አሉ።"

ስለስቱ ደቂቅ የሚባሉትን ሶስት እስራኤላውያን ልጆች ከእሳት ምድጃ የጨመራቸው ይህ ንጉሥ ነበረ። መልአኩ ጋርዷቸው ሳይቃጠሉ ከምድጃው ሲወጡ አይቶ በእግዚአብሔር አምኗል። ዳን 4: 34።

131. ሚክ 7: 18-19።

132. ኢትዮጵያ የመጡት በ1474 ዓ. ም. ነው።

133. ያረፉት በ1522 ዓ. ም. ነው።

134. ጥምቀቱ ክርስትና ለመነሣት ሳይሆን ዓመታዊ የጥር 11 ቀን የጥምቀት አከባበር መሆን አስበት።

135. ካኩ ያሳተመው የሚለው "እዚያው ቆየ" ነው፤ ስሕተት ነው። እቡነ ዕዝራ ደጅ የሚጠኑበት ቤተ መንግሥቱና የጳጳሱ ግቢ በምን ያህል እንደሚራራቁ ባይታወቅም እንግዶቹን የተቀበሏቸው ከንጉሡ ደጃፍ ነው።

ሄዱና እዚያ ደረሱ፤ (ተቃዋሚዎቻቸው) የአድባሩ መነኰሳት እንዲህ ሲሉ ዓዋጅ አስለፈፉ፤ "ደቂቀ አስጢፋኖስን ከገደላችሁ ክህነት ይሆንላችኋል::" ብዙዎቻቸው አንደ አንበጣ ተሰበሰቡ:: ሊገድሏቸው ልባቸውን አስጨክነው መጡባቸው:: (፪ቱ) የቅዱሱ ልጆች÷ "እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ነው፤ እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ነው:: አሕዛብ ዕወቁና ተሸነፉ" እያሉ ተቀበሏቸው:: የደብተራው መነኰሳት እነሱን የወገሩባቸው ድንጋዮች በአባታቸው ጸሎት እንደደረቅ ኩበት ሆኑ:: ክፉ ሊያደርስባቸው የቻለ ማንም አልነበረም::

ጳጳሱ ክህነት ሰጣቸው:: ታቦቶችም ቀደሰላቸው:: ለደቂቀ አስጢፋኖስ የተቀደሱት ታቦቶች ቍጥር ፹ ነበረ:: (ጳጳሱ) በሰላም ሸኟቸው:: አባታቸው (አቡነ ዕዝራ) ዘንድ ደረሱ:: ሲያያቸው (89) ተደሰተ፤ ምክንያቱም ሁኔታቸውን እስኪያውቅ ድረስ ያላንዳች መተኛት በሌሊት (የጸሎት) ትጋት ላይ ነበረ:: ስለዚህ÷ "አንተ እንደረዳኸንና እንዳስደሰትከን ጠላቶቻችን ይዩ እና ይፈሩ"[136] አለ::

እንደዚህ ብሎ ሰገደ፤ ታቦቶቹንም አጅ ነሣ:: "ረድኤት ይሆኗችኋልና ጠብቋቸው" አላቸው:: ከዚያ÷ ከፊታቸው እያለቀሰ እንዲህ አለ፤ "እንግዳና ፈላሲ ሆንኩ::[137] አንደ ሙሴ በምድረ ምድያም÷[138] እንደ ኤርምያስ በምድረ ባቢሎን[139] በነጋሢው ቤት ኑሮዬ እንደዚያ ሆነ:: ለሥጋ ጥቅም ሳይሆን ለአባቶቼ ቤት በመቅናት ነው::[140] አሁንም ጸልዩልኝ፤ አትርሱኝ::" ወንድሞች (ይኸንን) ከቃሉ ሲሰሙ ከእሱና (አብረውት) ከቀሩት ልጆቹ ጋራ አንገት ለአንገት ተያይዘው አምርረው አለቀሱ:: "ኤርምያስንና ባሮክን ከግዞት ወደ ሀገራቸው የመለሳቸው (አምላክ)[141] እንደዚያ ያድርግልህ:: እግዚአብሔር ካንተ ጋራ ይሁን፤ ልመናህን ሁሉ ይፈጽምልህ፤ ፊትህን በደኅና ያሳየን" አሉት:: ከዚያ÷ በሰላም አሰናበታቸው::

መመለሳቸውን ሲሰሙ ሁሉም የየአድባሮቻቸውን (ሰዎች) በጩኸትና በብዙ ማጎሌት ተቀበሏቸው:: የሳሚስ ልጆች[142] ታቦቷን ባዩ ጊዜ እንዳደረጉት እየጮኹ ታቦቶቹን ተቀበሉ:: ሲደርሱ ለማኅበሩ አለቃ ለአቡነ ገብረ መሲሕ የሆነውን ሁሉ ነገሩት:: ሲሰማ÷ "መጽሐፍ ከመግዛቴና እግዚአብሔር ከረገማት ምድር የሚያሳርፈኝ ልጄ ይህ ነው"[143] ያለው ደረሰ÷ ተፈጸመም" አለ:: ከአቡነ አስጢፋኖስ በኋላ በማላጭ ታቦቶች ያስቀደሰ ክህነትም ያስገኘ ያለ ዛሬ አልተገኘም::[144] ስለዚህ÷ "ለእግዚአብሔር ዘምሩ

136. መዝ 85: 17::
137. መዝ 38: 13::
138. ዘፀ 2: 15::
139. ተረፈ ኤር 9: 16::
140. መዝ 68: 10::
141. ተረፈ ኤር::
142. 1 ሳሙ/ነገሥ 6: 13::
143. ዘፍ 5: 29::
144. ደቂቀ አስጢፋኖስ ማንነታቸውን ላያስታውቁና ላይታወቅባቸው በድብቅ ክህነት ይወስዱ÷ ታቦታቸውን ያስቀድሱ እንደነበረ ይህ አንድ ማስረጃ ነው::

ቸር ነውና፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤[145] አሁንም እንደ ነቢዩ ቃል÷ "ከጠላቶቹ ረዳት ሁነው፤ በሚቃወሙት ላይ ከባዱን አውርድ"[146] አለ።

አቡነ ዕዝራ ለንጉሡ የሬሳ ሳጥን ሠሩለት

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ በንጉሡ ደጃፍ ሲኖር÷ ከደብሩ በወጣ በሶስተኛው ዓመት ንጉሡ ለራሱ መቀበሪያ (የሬሳ) ሳጥን እንዲሠራለት አዘዘው። ግብጻውያን ለጻጻሶችና ለንጉሦች እንደሚሠሩት ሠራለት። ንጉሡ አይቶ ደስ አለው። "ከኪራም[147] እና ከሰሎሞን በቀር እንደዚህ ያለ ሰው ይገኛልን?" አለ። ...[148] ዘይት የሚያወጣ ማሕሰራ÷ አልጋዎች÷ ቆሬዎች÷ ወናፍ÷ ሌሎችም የሚያስደስተውን ለንጉሡ ሠራለት። ንጉሡም ያሰበውን ሁሉ እሱ ዘንድ ስለአገኘው በጣም ወደደው። መኳንንቱና መኮሳቱ ግን ትሕትናውንና እንደ ሕፃን የዋህነቱን አይተው ወደዱት።

አቡነ ዕዝራና የቀንጡራሬ መነኮሳት

ከዕለታት አንድ ቀን ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ አባ በስሩን[149] ጐበኘ። እዚያ "ወልድ ብቻ አንጂ ከሱ በቀር አብ አና መንፈስ ቅዱስ አይናገሩም" የሚሉ የቀንጡራሬን መነኮሳት አገኘ።[150] ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ÷ "የምትሉት ልክ አይደለም" አላቸው። "በል አብ የተናገረውን ንገረን" አሉት። እንዲህ አላቸው፤ "አብ÷ የምወደው ልጄ ይኸ ነው[151] ብሏል፤ ደግሞ ስብሐት አቅርቤልሃለሁ÷ ደግሞም ስብሐት አቀርብልሃለሁ[152] ብሏል" አላቸው። "ይኸን ያለውማ አብ የፈለገውን በልጁ ይናገራል" አሉት። "ለወልድም ልጅ አለውን?" አላቸው። ማስረዳት አቃታቸው።

ደግሞ÷ "መንፈስ ቅዱስ ምን ተናገረ?" አሉት። ደግሞ እንዲህ አላቸው፤ "መንፈስ ቅዱስ አምን አለ፤ ከድካማቸው እንዲያርፉ ሥራቸው ይከተላቸዋል[153] ወደ ሕይወት ውሐ ምንጭ ይወስዳቸዋል[154] ብሏል።" ደግሞ

145. መዝ 105: 1።
146. ዘዳ 33: 7÷ 11።
147. ኪራም ከንጉሥ ሰሎሞን ጋራ የጠበቀ ወዳጅነት የነበረው የጢሮስ ንጉሥ ነበረ። ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሲሠራ ብዙ የቁዳር ዕንጨት (ዝግባና ጥድ) ከሊባኖስ ተራሮች ልኮለታል። 1/3 ነገሥ 5። ጢሮስ (ደቡብ ሊባኖስ) የፍሬምናሞስ አገር ናት።
148. ግዕዙ ውስጥ እዚህ ቦታ ሳይጻፍ የቀረ ቃል አለ።
149. ዘገባው አባ በለሩ በዘመኑ የታወቁ ሰው እንደነበሩ ያመለክታል፤ ማን እንደሆኑ ግን አሁን አይታወቅም።
150. ቀንጡራሬ/ቀንጦራር የደቂቀ ኤዎስጣቴዎስ ገዳም ነበረች። ግን በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድል ውስጥም ስለምትጠቀስ የተቋቋመችው ከአቡነ ኤዎስጣቴዎስ በፊት መሆን አለበት። ስላባታቸው ስለ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ከላይ ጎዳግ 126ን ተመልከት።
151. ማቴ 3: 17።
152. ዮሐ 12: 28።
153. ራእ 14: 13።
154. ራእ 7: 17።

እንዲህ አለ፤ (90) "መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን አናገረው፤ እንዲህም አለው፤ ሂድ÷ ይኸንን ሰረገላ ተከተለው::"[155] ደግሞ እንዲህ አለ፤ "መንፈስ ቅዱስ ጴጥሮስን ተናገረው÷ ሳትጠራጠር ከነሱ ጋራ ሂድ አለው ይላል::"[156] ይኸንን (መልስ) ከቃሉ ሲሰሙ ደነገጡ:: ተነሥተው እንዲህ ሲሉ እጅ ነሡት፤ "በእፉ መላም ይሰመኛል::"[157]

አባ በስሩ ሲሰማ÷ "እንደኛ ያለ የለም ትሉ ነበረ:: ዛሬ ግን የእስጢፋኖስ ልጅ አንበሳው ዕዝራ አገኛችሁና እንደ ቀበሮች አደረጋችሁ:: (እሱን) እናንተ ብቻ አይደላችሁም፤ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በመጽሐፍና በጥበብ አልቻሉትም" አላቸው::

የንጉሥ ናአድ ዕረፍት÷ የአቡነ ዕዝራ ሽሽት

ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ከንጉሡና ከሠራዊቱ ሁሉ ጋራ በመግባባት ፱ ዓመት ተቀመጠ:: ከሥርዓቱ አላጓደለም፤ እግሮቹ ላይ ጫማ አላደረገም፤ ከሱ በኋላ ለሚመጡ አርአያ ይሆን ዘንድ ሥጋውን አደከመ:: (ያን ያህል) ሞገስና ጥበብን እግኝቶ በንጉሥ ዘንድ መከበርን እንደሱ የናቀ ከሱ በቀር በዘመናችን ማን አለ?

፱ኛው ዓመት ሲሞላ የሚወደው ንጉሥ ሞተ:: መኳንንቱና መነኮሳቱ በድብቅ ሊያስገድሉት ፈለጉ:: ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ እንደዶለቱበት ሲሰማ÷ ንጉሡ በሕይወት ባለበት ጊዜ÷ "ከኔ በኋላ የሚሆንህን አድርግ" ያለው ትዝ አለው:: በልቡ ያለውን ለእንድ ምእመን አዋየው:: እሱም÷ "ጠላቶችህ ሳያዩህ በፍጥነት ከዚህ ውጣ" አለው::

ከዚያ÷ ድንኳኑን እንደተተከለች ትቶ ቡትቶ ለብሶ ከ፪ ልጆቹ ጋራ በጥድፊያ ወጣ:: ያ ምእመን የሚመራቸው ሎሌ ላከላቸው:: ለክማ ከምትባል ከዳጎ... [158] አገር እደረሳቸው:: እዚያ አንድ ዓመት ተቀመጠ:: የማኅበሩ አለቃ ሲሰማ የሚቀበሉት ሰዎች ላከለት፤ (ተቀብለው) አሱ ዘንድ አመጡት፤ በዚያን ጊዜ አሱ ምድረ ዱስአ ነበረ:: ሲደርስ ያዕቆብ ያባቱን እጆች እንደሳመ አጎንብሶ የአባቱን እጆች ሳመ::[159] አሱም ይሥሐቅ በልጁ በያዕቆብ አንገት እንደተንጠለጠለ[160] በአንገቱ ተንጠለጠለ:: ሁለቱ ተላቀሱ::

በዚያች ጊዜ በሽማግሌው አፍ የትንቢት መንፈስ ወረደና እንዲህ አለ፤ "ለዳዊት ቤት ስሙ ኢዮስያስ የሚባል ልጅ ይወለዳል::[161] የያዕቆብ ረድኤት እንደዚህ ይሁን፤ መድኃኒቱም ለእስራኤል::[162] ይህቺ እኔን

155. የሐ ሥራ 8: 29::
156. የሐ ሥራ 10: 20::
157. መኃ 1: 1:: ስላምታ የሚስጣጡት በመላላም መሆኑ ነው::
158. የቦታው ስም ሙሉ በሙሉ አልተጻፈም፤ ለክማ ከአስጢፋኖሳውያን ገዳሞች አንዷ ነበረች::
159. ያጎነበሱት የሽማግሌውን እጅ ፍለጋ ነው ወይስ አጎንብሶ እጅ መንሣቱንም ተቀብለውታል?
160. ኩፋሌ 27: 8::
161. 1 ሳሙ/3 ነገሥ 13: 2::
162. የጸሎተ ዘካርያስን መጀመሪያ (ሉቃ 1: 68) ይመስላል::

በሕይወቴ ያየህባት÷ እኔም አንተን ልጄን ያየሁባት ዕለት የተባረከች ትሁን::"

አብሮት ጥቂት ጊዜ ቆየ:: እግዚአብሔር የሠራለትን ሁሉ ነገረው:: የገሪዘን[163] ገበዝ ወደ ሆነችው ወደ ደብረ ከስዋ እንዲመለስ አሰናበተው::[164] እዚያ ታጎግሥ ፷፫ ቀን በሰላም ደረሰ:: ሊቀበሉት ወጡ፤ ሲያዩት ከታቦቶች ጋራ ስለነበረ÷ ለእግዚአብሔር ሰገዱ:: እጅ ነሡት፤ "ስብሐት ለደረሰው እግዚአብሔር ስብሐት እናደርስለታለን"[165] አሉ:: ደግሞ÷ "የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ ለዘለዓለም ስቡሕም ነው፤ ልዑልም ነው"[166] (አሉ):: ዳዊት እንደዘፈነ ከታቦቱ ፊት ዘፈኑ::[167] ከዚያ÷ በደስታ ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገቡት:: እሱ ራሱ÷ "ይቺ ለዘላለም ማረፊያየ ናት"[168] አለ:: እዚያ በሰላም ኖረ::

ሰይጣን ሞገዶቹን አስነሣ

ከተመለሰ በኋላም ደግሞ ሰይጣን ሞገዶቹን አስነሣ:: ንጉሡ ላያውቅ መኳንንቱ አጥብቀው ፈለጉት:: ላያገኙት ጊዜ በቤተ አስጢፋኖስ ላይ ስደት አመጡባቸው:: ቤተ ክርስቲያኖቻቸውን አቃጠሏቸው:: ወንድሞች ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራን በጥድፊያ አውጥተው ከአንድ ወንድም ጋራ ከምድረ በዳ ደበቁት:: ሲመለስ የከስዋን ቤተ ክርስቲያንን (አቃጥለዋት ኖሮ) ቃጠሎውን አየና አለቀሰላት:: ወንድሞችን÷ "ነቢዩ÷ በጽዮን ቃጠሎዋ ላይ መኖር ይሻለናል[169] ብሏልና አትፍሩ" አላቸው:: ወንድሞች÷ "እግዚአብሔር ይረዳናል" አሉት:: ደግሞ÷ (91) "ሰይጣን ደስ እንዳይለው ተነሡ እንሥራት" አላቸው:: ሠሯት፤ እንደበፊቱ አደሷት::

በጠና በሽታ ላይ

እዚያ ወንድሞችን ለነፍስና ለሥጋ በሚጠቅም በምዕዳንና ተግሣጽ እያጽናናቸው ኖረ:: ከዚያ በኋላ÷ አቡነ ገብረ መሲሕ ስለሸመገለና ወደ ሩቅ ቦታ ለመሄድ ስለማይችል÷ ወደሱ እንዲመጣ ላከበት፤ ወንድሞችንም÷ "ላኩት" አላቸው:: የአባቱን ትእዛዝ እንዳይጥስ ተባርኮ ወጣ:: በወጣ በሶስተኛው ቀን እመንገድ ላይ በጽኑ በሽታ ታመመ:: ይሞታል ብለው ተስፋ

163. ገሪዘን የሚለው ደብረ ገርዜንን ነው::

164. ከስዋን የደብረ ገርዜን ገበዝ ሲላት ታላቅነቷን መናገሩ ይሆናል::

165. ዘፀ 15: 1:: ዳዊት ውስጥ ከገቡት መጋልየ ነቢያት ጸሎተ ሙሴ ፩ የሚባለው ጸሎት መጀመሪያ ነው:: ፊርያን ከነፈረሱ ከቀይ ባሕር የሰጠመ ጊዜ አስራኤላውያን የጸለዩት ስለሆነ÷ ክርስቲያኖች በጠላታቸው ላይ ድል ሲያገኙ ለአምላክ ምስጋና የሚያቀርቡት በዚህ መጋልይ ነው::

166. የሠለስቱ ደቂቅ ጸሎት መጀመሪያ ነው::

167. 2 ሳሙ/1 ነገሥ 6: 14::

168. መዝ 131: 14::

169. ሱቱ 11: 44::

ስለቆረጡ የሰማው ሁሉም ደንግጦ ነበር። ትንሹም ትልቁም ወደሱ መጡና አለቀሱለት። እግዚአብሔር ሐዘናቸውን አይቶ ከበሽታው ፈወሰው። ሰው ሁሉ ደስ አለው።

ከዚያ፥ በከባድ ድካም ወደ ጠራው አባቱ ሄደ። ሲደርስ በሱ ተባረከ። በልባቸው ያለውን ተነጋገሩ። ሥርዓታቸው የሚጸናበትን ቲመካከሩ። ከዚያ፥ የማንበሩ አለቃ አቡነ ገብረ መሲሕ ጉባኤ አድርጎ፥ (አቡነ ዕዝራን) ከማህሳቸው አቆመውና፥ "የሁሉ መመኪያ ስለሆነን ጸልዩለት" አላቸው። ወንድሞችም ሰሰሱ ጸለዩ። ባረኩት፤ "(እግዚአብሔር) መብራታችንን አያጥፋብን" አሉ። የጉባኤውን ጉዳይ ሁሉ ሲጨርሱ ወንድሞችን ወደ የአድባራቸው አሰናበታቸው። "እሱን ግን ከፍ ያለ ድካም ስለደረሰበት ከኔ ጋራ ተዉት" አላቸው። ተዉት፤ እዚያው ቀረ።

ዘለዓለማዊ ዕረፍት

ጥቂት ቆይቶ ነሐሴ ፫ ቀን ታመመ። ከቅርቡ ያሉት ሲሰሙ ተሰበሰቡ። ሽማግሌውም በቃሬዛ ተሸክመውት (መጥቶ) ጠየቀው፤ አለቀሰለት፤ "ውድ ልጄ፥ የዓይኔ ብርሃን፥ ልትተወኝ ነውን?" አለ። እሱም፥ "አባ ሆይ፥ ባርከኝ። የተቻለኝን ያህል ደክምኩ እንጂ፥ የሩቁንም ሆነ የቅርቡን ችላ ያልኩት የለም።" ይሽንን ብሎ በዚያው ወር በ፲፩ ቀን አንደጣፋጭ እንቅልፍ እረፈ። ጸሎቱና በረከቱ ከኛ ጋራ ትሁን፤ አሜን።

የሚጠብቁት ከድንጋጤ ብዛት የተነሣ መናገር አቃታቸው። አንዳረፈ ለሽማግሌው ነገሩት። እሱም ወደሱ እንዲያመጡት አዘዘ። አመጡለት፤ በአጆቹ ገነዘው። ጊዜው ምሽት ስለነበረ ከመኖሪያው አሳደረው። በማግሥቱ የመልአኩ ሚካኤል በዓል ነበረ፤ መነኮሲዎቹና መነኮሲቶቹ፥ የሀገሩ ሹማምንትም፥ ወንዱም ሴቱም ሁሉ ተሰበሰቡ። ከሬሳው ላይ እየወደቁ አለቀሱ። ከዚያ በኋላ፥ በቃሬዛ ተሸክመው ወደ ቤተ ክርስቲያን ወሰዱት። ሽማግሌውንም የ፱፱ ዓመት ልጅ ስለነበረ በወምበር ተሸክመው (አመጡት)። ሲሄድ፥ ዳዊት ለአበኔር እንዳሰቀሰ ከኋላው ያለቅስ ነበረ።[170] ሬሳውን ከሬሳ ሳጥን ውስጥ አስቀመጡት። (ለፍትሐት) የሚገባውን ሁሉ አነበቡለትና በእግዚአብሔር ሰው[171] መቃብር ውስጥ ቀበሩት። ጸሎቱ፥ አማላጅነቱ፥ የረድኤቱ ሰጦታ ከኛ ጋራ ትሁን፤ ለዘላለምም ትጠብቀን፤ አሜን፥ አሜን።

መርዶ

ደግሞ፥ እስከ ፵ ቀን ድረስ፥ መሥዋዕት እንዲያደርጉ (አበምኔቱ አቡነ ገብረ መሲሕ) አዘዘ። ከዚያ በኋላ፥ ዕረፍቱን እንዲያረዱ ፪ ወንድሞች ወደ ከሰዋ

170. 2 ሳሙ/ነገሥ 3: 32-34።

171. ግዕዙ የሚለው "ብእሴ እግዚአብሔር" ነው፤ ከአረፉት ጻድቃቸው ያንዱ ስም ሊሆን ይችላል። ወይም "ብእሴ እግዚአብሔር" ("የግዚአብሔር ሰው") ወይም አቡነ ይሥሐቅን ይሆናል።

የቤቱ ልጆች ላከ። እዚያ ሲደርሱ ለነገረ ፈጂው÷ "መልእክት ስላለ ማኅበሩን ሰብስብልን አሉት።" ሲሰማ ወንድሞችን ሰበሰባቸው። በዚያን ጊዜ የማርያም ፍልሰታ ስለነበረ ስብሰባው ትልቅ ሆነ።[172]

ከዚያ÷ ከማህላቸው ቆመው ከፍርሃት ብዛት የተነሣ መናገር አቃታቸው። "አባታችሁ ዕዝራ አርፏል" አሏቸው። ሲሰሙ ጮኸው ከመሬት ላይ ወደቁ። አንዳንዱ አመድ ለበሰ፤ አንዳንዱ ጉሮሮውን አነቀ። ከለቅሶው ብዛት የተነሣ አንደ በድኖች ሆኑ። ሁሉም አንድ ስለሆኑ የሚቆጣ ሽማግሌ ጠፋ። ጩኸታቸው (92) በአብርሃም ቤት እንደተሰማ[173] በአድባራቱ ተሰማ። "ነጋዲው የት አለ? ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ወይስ ከኢትዮጵያ ነጋሢ ቤት አለ" አሉ። የሀገሬው ሰውም እየየ እያሉ ከነሱ ጋራ ሐዘን ተቀመጡ።

ከዚያ በኋላ÷ ፫ የሚሆኑ ወንድሞች ወደ መቃብሩ ሄደው÷ ከመምህሩ ጋራ ተገናኙ። አብረውትም አለቀሱ፤ ሐዘን አናቆምም አሉ። የዱስአ ሹምም አብሯቸው አለቀሰ። "ልባችሁን አርጉ፤ ሐዋርያው ሁላችንም እንሞታለን[174] ። ያለውን አስታውሱ" አላቸው።

ወንድሞች÷ "እንደሱ ያለ አናገኝም፤ አሉ አንደ ሙሴ ዝነኛ÷ እንደ ኤልያስ ለሃይማኖት ሕግ ቀናተኛ÷ እንደ ዳዊት አስተዋይ÷ እንደ ሰሎሞን ጥበበኛ÷ እንደ ኢዮብ ትዕግሥተኛ÷ እንደ ጴጥሮስ የአለት ድንጋይ÷ እንደ ጳውሎስ ፍጹም ነበረ። ጎልማሳ ሆኖ ሕፃን ይመሰል÷ በሁሉ ቦታ ይገኝ ነበረ፤ ስለዚህ ልባችን ይቃጠልብናል። እንደ ወፍ ጫጩት አቅመቢስ ሆንን" አሉ።

አስከሬኑን አምጡ

ከዚያ በኋላ÷ የማኅበሩን አለቃ÷ "መመኪያ እንዲሆነን ሥጋውን ስጠን፤ ብዙዎች ተስፋ አድርገውታል" አሉት። "አሰጊዜው እንደዚህ ማድረግ ይቻላልን? ካረፈ ገና ፴ ቀኑ ነው" አላቸው። ከዕንባ ጋራ÷ "አባ ሆይ÷ ምሕረት አድርግልን፤ በሕይወት በነበረ ጊዜ ሥጋዬን ከሌላ ቦታ አትተዉ ብሎናልና (አባከህ) አሱን ትተን (ባዶ አጃችንን) ወደ ሀገራችን እንመለስ" አሉት። አሱም እንዲህ አላቸው፤ "እኔንም ለራስህ የምታደርገውን ለኔም አድርግልኝ ስላለኝ እንዳለኝ አድርጌለታለሁ። (ደግሞ) ያለ ሀገሩ ሹም ብቻዬን (መወሰን) አይቻለኝም።"

ከሹሙ ዘንድ ሄደው (ሥጋውን) እንዲሰጣቸው አነጋገሩት። "እግዚአብሔር ለኔ ስለሰጠኝ አልሰጣችሁም" አላቸው። በፊቱም አለቀሱ። "ለቅሶ በዛባችሁ፤ ሰዉን ተዉትና እንበላዎችም በሞቱ አልቅሰዋል፤ ከመቃብሩ ዘንድ ሲያጓሩ ነበረ። ስለዚህ እኔም የሀገሬው ሰዎችም በጣም ተስፋችን አድርገነዋል። (መጽሐፍ) የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል ይላልና"[175] አላቸው።

---

172. ደራሲው ባጋጠመው ቁጥር ስለ ቅድስት ማርያም የሚታሙበትን ያስተባብላል።
173. አብርሃም የሞተ ጊዜ ከሆነው ጋራ ሲያስተያይ ነው፤ ኩፋ 21: 4።
174. 1 ቆሮ 15: 22።
175. መዝ 111: 7።

ከዚያ በኋላ÷ ሂደው (ሹሙ) ያለውን ለአባታቸው ነገሩት:: አሱንም ደግሞ÷ "አባት ሆይ÷ ተስፋ ስጠን" አሉት:: መርበድበዳቸውን[176] ሲያይ÷ "በኔ ዘመን የምታገኙት ነገር የለም፤ ከኔ ቀጥሎ የሚሾመውም ሥልጣን ስላለው የፈለገውን ያደርጋል" አላቸው::

ይኸንን ከቃሉ ሲሰሙ በሱ ተባርከው ወደ ገዳማቸው ተመለሱ:: የሆነውን ሁሉ ለሽማግሌዎቹም ለሕፃናቱም ነገሯቸው:: ከዚያ በኋላ÷ "እግዚአብሔር ከስጠን የሚከለክለን አይኖርም:: ሁሉ ነገር በጸሎት ስለሚሆን እንጸልይ" ተባባሉ:: ለመጀመሪያው ኮርቤሳ[177] አንድ ዓመት ሐዘን ላይ ቆዩለት:: ከዚያ ደግሞ÷ ይኸ የበጎቹ አረኛ አቡነ ገብረ መሲሕ አረፈ:: በለቅሶ ላይ ለቅሶ÷ በሐዘን ላይ ሐዘን ተጨምሮባቸው ለሱም አለቀሱለት:: ያዕቆብ÷ "ዮሴፍን አጣሁ÷ ስምዖንንም አላየሁትም"[178] እያለ እንዳለቀሰ እነሱም አለቀሱላቸው:: ጸሎታቸውና በረከታቸው ለዘላለም ከኛ ጋራ ይሁን፤ አሜን::

(አዲሱ) ሊቀ ማኅበር ከተሾመ በኋላ[179] ስለ ሞገሳዊው አቡነ ዕዝራ ዐፅም ጠየቁት፤ "እግዚአብሔር ይንገርህ" አሉት:: "ጸልዩ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን፤ በዚህ ምክንያት አትተክዙ" አላቸው::

ከዚያ በኋላ÷ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ÷ ይኸ የተሾመው የማኅበር አለቃ÷ አብረውት ካሉት ከጥቂቶች በቀር ማንም ሳያውቅ÷ ተስፋ ያደረጉትን ይዞላቸው መጣና አስረከባቸው:: (ያደረገውን) ከቃሉ ሲሰሙ÷ "እግዚአብሔር ሐዘናችንን የሚያጽናና አረኛ ስለሰጠን ስብሐት ይግባው" አሉ::

ከዚያ÷ (93) ዐፅሙን በሣጥን አስቀመጡት፤ ማኅሌት አድርገው በማዕጠንት አጠኑት፤ መብራት አበሩ፤ ወንጌሎችንም አነበቡ፤ የሚገባውን (ሥርዓት) ሁሉ ፈጸሙ:: በ(ዕብራውያን ሐሳብ) በታሙዝ ፲፩ ቀን÷ በግዕዝ በሐምሌ ፳፩ ቀን÷ በማርያም በዓል ዕለት÷ በሕይወቱ በተመኘበት መቃብር ቀበሩት:: የማኅበሩ አገልጋይ (ያቡነ ዕዝራ) ጸሎትና የብርሃን እናት የእመቤታችን ጸሎት ከኛ ጋራ ለዘላለም ይኑር፤ አሜን÷ አሜን፤ ይሁን÷ ይሁን::

እነሆ÷ እንዳይረሳ (ያህል) በጥቂቱ ተጻፈ እንጂ ሁሉም አልተጻፈም:: (ይኸንን ገድል) የሚጽፈውን÷ የሚያስጽፈውን÷ ቃሎቹን በእምነት የሚሰማውን እግዚአብሔር በመንግሥቱ ይማራቸው፤ ለዓለመ ዓለም÷ አሜን÷ አሜን፤ ይቅር በሉኝ÷ ባርኩኝም::

---

176. "መርበድበድ" ብየ የተረጐምኩት "ነጸርጸር" የሚለውን ነው:: ቃሉ እዚህና ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ውስጥ አንጂ ከግዕዝ መዝገበ ቃላትም ሆነ ወይም ከሌላ ቦታ አላገኘሁትም፤ ገጽ 81 ላይ ተመልከት::

177. ግዕዙ የሚለው "ሐርጌ" ነው፤ የ"ሐርጌ" ትርጕም "ወጠጤ" ሲሆን ግዕዙ ይሆናል እንጂ አማርኛውስ ለአቡነ ዕዝራ ዓይነት ሰው አይስማማም:: "እውራ" ወይም ያልተለመደው "ኮርቤሳ" ይሻላል::

178. ዘፍ 42: 36::

179. አዲሱ ሊቀ ማኅበር አቡነ ሀብተ ሥላሴ ናቸው::



ዋቢ መጻሕፍት

(ከምጎጻረ ቃላት ጋራ)

መጽሐፈ ቅዳሴ፡ በግዕዝና በአማርኛ፡ አዲስ አበባ 1951 ዓ. ም.::

መጽሐፈ ቅዳሴ፡ አስመራ፡ በ፲ወ፱፻ወ፸ ዓመተ ምሕረት::

ሦስቱ መጻሕፍተ መነኮሳት እነርሱም ፩ኛ ማር ይስሐቅ ፪ኛ ፊልክስዩስ (ገብረ ክርስቶስ) ፫ኛ አረጋዊ መንፈሳዊ፡ አዲስ አበባ ፲፱፻፹፪ ዓ. ም.::

ተአምረ ማርያም:: በግዕዝ እና በአማርኛ:: አዲስ አበባ ፲፱፻፷፩ ዓመተ ምሕረት::

ተአምረ ኢየሱስ: በGrébaut, Sylvain ስር ተመልከት::

ትምህርተ ኅቡኣት: በHammerschmidt, Ernst, *Äthiopische Liturgische Texte* ስር ተመልከት::

ዘርአ ያዕቆብ (አፄ)፡ *መጽሐፈ ሚላድ ወመጽሐፈ ሥላሴ*፡ በWendt, Kurt ስር ተመልከት::

——፡ *መጽሐፈ ብርሃን*፡ በConti Rossini, Carlo, and L. Ricci ስር ተመልከት::

——፡ *ጦማረ ትስብእት* በGetatchew Haile, *The Epistle* ስር ተመልከት::

ገብረ ሥላሴ (ጸሐፌ ትእዛዝ)፡ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*፡ አዲስ አበባ ፲፱፻፶፱::

ገድለ ሐዋርያት፡ በBudge, E. A. Wallis, *The Contendings* ስር ተመልከት::

ገድለ አበው ወአኃው፡ በEMML 4 ስር ተመልከት::

ጌታቸው ኃይሌ፡ *ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቁጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ*፡ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.::

ጸሙ ድጓ፡ አምስቱ ጸዋትወ ዜማዎች፡ አዲስ አበባ 1965 ዓ. ም.፡ ገጽ 1-101::

AB = Analecta Bollandiana (Bruxelles).

AÉ = Annales d'Éthiopie (Paris).

Arras, Victor, *Collectio Monastica, CSCO*, vol. 238/45 (1963).

——, *Patericon Aethiopice, CSCO*, vol. 277/53 (1967).

Basset, René, "Études sur l'Histoire d'Éthiopie," *JA*, vol. 17 (Avril-Mai-Juin 1881).

——, *Les Apocryphes éthiopiens V. Les prières de la Vierge à Bartos et au Golgotha*, Paris 1895.

Beylot, Robert, "Un épisode de l'histoire écclésiastique de l'Éthiopie. Le mouvement stéphanite. Essai sur sa chronologie et sa doctrine," *AÉ*, vol. 8 (1970), pp. 103-116.

Budge, E. A. Wallis, *The Contendings of the Apostles*, vol. I, London 1899.

——, *George of Lydda*, London 1930.

Caquot, André, "Les Actes d'Ezrā de Gunda-Gundē," *AÉ*, vol. 4 (1961), pp. 70-121.

Cerulli, Enrico, "L'Etiopia del secolo XV in nuovi documenti storici," *Africa Italiana*, vol. V (1933), pp. 57-112.

——, *Il libro etiopico dei miracoli di Maria e le seu fonti nelle letterature del Medio Evo latino*, Rome 1943.

——, *Etiopi in Palestina Storia della comunità etiopica di Gerusalemme* vols. 1 & 2 Roma 1943 & 1947.

——, "L'Imperatore Na'od e gli Stefaniti a Gerusalemme in un documento inedito (Vaticano Etiopico 298)," *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies, Addis Ababa 1966*, vol. II, Addis Ababa 1970, pp. 243-253.

Colin, Gérard, *La Version Éthiopienne de la Vie de Schenoudi*, *CSCO*, vol. 444/75 (1982).

——, *Vie de Sāmu 'ēl de Dabra Hāllēluyā*, *CSCO*, vol. 519/93 (1990).

Conti Rossini, Carlo, "L'Omelia di Yohannes, Vescovo d'Aksum, in onore di Garimâ," *Actes du onzième Congrès International des Orientalistes*, Paris, 1898, pp. 139-177.

——, "Il Convento di Tsana in Abissinia e le sue laudi alla Vergine," *Accademia Nazionale dei Lincei*, vol. 19, ser. 5 (1910), pp. 581-621.

——, "Il libro di re Zar'a-Yā'qob sulla custodia del Mistero," *RSE*, vol. III (1943), pp. 148-166.

Conti Rossini, K., *Vitae Sanctorum Indigenarum I Gadla Abuna Abakerazun seu Acta Sancti Abakerazun*, *CSCO*, vol. 56/25 (1954), pp. 1-64.

——, *Vitae Sanctorum Antiquiorum I Acta Yāred et Panṭalēwon*, *CSCO*, vol. 26/9 (1961), pp. 43-60.

——, *Vitae Sanctorum Indigenarum I Gadla Baṣalota Mikā'ēl seu Acta Sancti Baṣalota Mikā'ēl, II Gadla Anorēwos seu Acta Sancti Honorri, CSCO*, vol. 28/11 (1962).

——, *Vitae Sanctorum Indiginarum I Acta Marqorēwos, CSCO*, vol. 33/16 (1965).

Conti Rossini, Carlo, and L. Ricci, *Il libro della luce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān), CSCO*, vol. 250/47 (1964), and vol. 261/51 (1965).

CSCO = Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium (Louvain); the second number of the volume refers to the Ethiopian series. የቅጹ የመጀመሪያው ቁጥር የሚያመለክተው ድርጅቱ የሚያሳትማቸውን ሁሉ (ለምሳሌ፥ የሶርያ፥ የግብጽ፥ የኢትዮጵያ፥ ወዘተ) ሲሆን ሁለተኛው ቁጥር የሚያሳየው የተለያዩ ሀገሮችን ሰነድ ነው፤ ለምሳሌ እዚህ vol. 261/51 ብዬ ብጠቅስ በ51 የማመለክተው የኢትዮጵያውን ነው::

Dillmann, August, "Über die Regierung, insbesondere die Kirchenordnung des Königs Zar'a-Jacob," *Abhandlungen der Königl. Akademie der Wissenschaften zu Berlin*, Philos.-histor. Cl. vol. 2 (1884).

Dillmann, Augusto, *Chestomathia Aethiopica*, Darmstadt 1965, pp. 57-76.

EMML = Ethiopian Manuscript Microfilm Library (Addis Ababa and Collegeville).

EMML 4 *(ገድለ አበው መኑ'ሙ)*, W. F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa, and for the Monastic Manuscript Library, Collegeville*, vol. I, Collegeville (Minnesota) 1975, p. 7.

EMML 1826, ff. 59b-65a *(ገድለ አርብዓ ሐራ)*, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville*, vol. V, Collegeville (Minnesota), 1981, p. 275.

EMML 2058 *(ተአምረ ማርያም)*, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue*, vol. VI (1982), pp. 70-94.

EMML 2969 *(መጽሐፈ ቅዳሴ)*, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue*, vol. VII (1983), pp. 282-284.

EMML 3012, f. 80b *(የታሪክ ማስታወሻ)*, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue*, vol. VIII (1985), p. 20.

EMML 7219 ላስታ የምትገኘው የገነተ ማርያም አርባዕቱ ወንጌላት::

Ferenc, Aleksander, "Les Actes d'Isaïe de Gunda-Gundē," *AÉ*, vol. 10 (1976), pp. 243-294.

Getatchew Haile, "*Fəkkare Haymanot* or the Faith of Abba Giorgis Säglawi," *Le Muséon*, vol. 94/3-4 (1981), pp. 235-258.

——, "Power Struggle in the Medieval Court of Ethiopia: The Case of Bätergela Maryam," *JES*, vol. 15 (1981), pp. 37-55.

——, "Religious Controversies and the Growth of Ethiopic Literature in the Fourteenth and Fifteenth Centuries," *OrChr*, vol. 65 (1981), pp. 102-136.

——, "The Letter of Archbishops Mika'el and Gäbrə'el Concerning the Observance of Saturday," *JSS*, vol. 26/1 (1981), pp. 73-78.

——, "A New Look at Some Dates on Early Ethiopian History," *Le Muséon*, vol. 95 (1982), pp. 311-322.

——, "The Homily of *Aṣe* Zär'a Ya'əqob of Ethiopia in Honour of Saturday," *Orientalia Lovaniensia Periodica*, vol. 13 (1982), pp. 196-205.

——, "The Monastic Genealogy of the Line of Täklä Haymanot of Shoa," *RSE*, vol. 29 (1982-83), pp. 7-38.

——, "The Cause of the Ǝsṭifanosites: A Fundamentalist Sect in the Church of Ethiopia," *Paideuma*, vol. 29 (1983), pp. 93-119.

——, "The Homily of Zär'a Ya'əqob in Honour of St. John the Evangelist, EMML* 1480, ff. 48r-45v," *OrChr*, vol. 67 (1983), pp. 144-166.

——, "The Forty-Nine Hour Sabbath of the Ethiopian Church," *JSS*, vol. 33/2 (1988), pp. 233-254.

——, "The Homily of Abba Eləyas, Bishop of Aksum, on Mäṭṭa'," *AB*, vol. 108 (1990), pp. 29-47.

——, *The Epistle of Humanity of Emperor Zär'a Ya'əqob (Ṭomarä Təsbə't)*, *CSCO*, vol. 522/95 (1991).

——, *The Mariology of Emperor Zär'a Ya'əqob of Ethiopia*, *OCA*, no. 242 (1992).

——, "A Fragment on the Monastic Fathers of the Ethiopian Church," *Orbis Aethiopicus: Studia in honorem Stanislaus Chojnacki* (ed. Piotr O. Scholz *et al*), Albstrat (1992), pp. 231-237.

——, "The Translation of the Relics of Abunä Filəppos of Däbrä Libanos," *RSE*, vol. XXXIV (1992), pp. 75-113.

——, "Martyrdom of Abunä Täklä Ḥawarəyat of Shoa and the Translation of His Relics," *Etiopia e Oltre Studi in onore di Lanfranco Ricci* (ed. Yacob Beyene *et al*), Naples (1994), pp. 93-113.

——, see EMML.

Grébaut, Sylvain, "Les Miracles des Jésus," *P.O.*, vol. XII (1919), pp. 551-649.

Guidi, Ignazio, "Le Synaxaire, Éthiopien, les mois de Sanê, Hamlê et Nahasê," *P.O.*, vol. VII (1911), pp. 207-456.

Hammerschmidt, Ernst, *Äthiopische Liturgische Texte der Bodleian Library in Oxford*, Berlin (1960), pp. 48-72.

——, *Stellung und Bedeutung des Sabbats in Äthiopien*, Stuttgart 1963.

Harden, J. M., *The Ethiopic Didascalia*, New York 1920.

JA = Journal asiatique (Paris).

JES = Journal of Ethiopian Studies (Addis Ababa).

JSS = Journal of Semitic Studies (Manchester).

Kinefe-Rigb Zelleke, "Bibliography of the Ethiopic Hagiographical Traditions," *JES*, vol. 13, no. 2 (1975), pp. 57-102.

Knibb, A. Michael, in consultation with Edward Ullendorff, *The Ethiopic Book of Enoch*, vol. 1, Oxford 1978.

Kur, Stanislas, *Actes de Samuel de Dabra Wagag, CSCO*, vol. 287/57 (1968).

——, *Actes de Marḫa Krestos*, *CSCO*, vol. 330/62 (1972).

Kur, Stanislaw, "Les stéphanites à la lumière des *Actes d'Isaïe* de Gunda-Gundē" (ed. Claude Lepage *et al*), *Étude éthiopiennes vol. I, Actes de la X^e conférence Internationale des études éthiopiennes*, Paris 1994, pp. 359-361.

Macomber, W. F., see EMML.

Mordini, Antonio, "Il Convento di Gunde Gundiè," *RSE*, vol. 12 (1953), pp. 29-70 (+ 31 figures).

OCA = Orientalia Christiana Analecta (Rome).

OrChr = Oriens Christianus (Munich).

Perruchon, M. Jules, "Histoire des Guerres d'Amda Ṣyon, roi d'Éthiopien," *JA*, vol. 8, ser. 14 (1889), pp. 271-363, 381-493.

——, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et Ba'eda Mâryâm, rois d'Éthiopie de 1434 a 1478*, Paris 1893.

——, "Histoire d'Eskender, d''Amda-Ṣeyon II et de Nâ'od, rois d'Éthiopie," *JA*, vol. 9, ser. 3 (1894), pp. 319-366.

P.O. = Patrologia Orientalis (Paris).

Raineri, Osvaldo, *Atti di Habta Māryām (†1497) e di Iyāsu (†1505) Santi Monaci Etiopici, OCA,* no. 235 (1990).

RSE = Rassegna di Studi Etiopici (Rome and Naples).

Strelcyn, Stefan, *Catalogue des Manuscrits Éthiopiens de l'Accademia Nazionale dei Lincei Fonds Conti Rossini et Fonds Caetani 209, 375, 376, 377, 378,* Roma 1976.

Taddesse Tamrat, "Some Notes on the Fifteenth Century Stephanite 'Heresy' in the Ethiopian Church," *RSE*, vol. 22 (1966), pp. 103-115.

——, *Church and State in Ethiopia 1270 - 1527*, Oxford 1972.

Turaiev, B., *Monumenta Aethiopiae Hagiologica, vol. V: ገድለ: ቅዱስ: ኤምስጣቴምስ:: Vita et Miracula Eustathii*, Petropoli, 1905, pp. 134-178.

——, *Vitae Sanctorum Indigenarum III Gadla Aron seu Acta Sancti Aaronis, IV Gadla Filpos seu Acta Sancti Philippi, CSCO*, vol. 30/13 (1961).

Ullendorff, Edward, "Hebraic-Jewish Elements in Abyssinian (Monophysite) Christianity," *JSS*, vol. I, no. 3 (1956), pp. 216-256.

——, see Knibb, A. Michael.

Wendt, Kurt, *Das Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis) des Kaizers Zar'a Yā'qob, CSCO*, vol. 221/41 (1962), and vol. 235/43 (1963).

Wessel, Klaus (ed.), *Christentum am Nil*, Recklinghausen 1964.

Yacob Beyene, *Giyorgis di Saglâ Il libro del Mistero (Maêîafa Mesœir), CSCO*, vol. 515/89 (1990).



መጠቀሚም

(የቦታና የሰው ስም፤ ጎ = ጎዳና፤ n = note)

- ሀ -

ሀብተ ማርያም (አባ): 190÷ 190(ጎ)÷ 195(ጎ)
ሀብተ ሥላሴ (አባ): 314(ጎ)
ሀብተ ጽዮን (ወንድም) : 199
ሀገረ ማርያም: 137÷ 207
ሀገረ ሳጉራ: 123÷ 137÷ 246
ሀገረ በሊ: 190
ሀገረ ኢባ: 54÷ 180÷ 183÷ 190÷ 192
ሀገረ አብስ: 137÷ 194
ሀገረ ደም: 54
ሃሌሉ/ደብረ ሃሌ ሉያ: 229(ጎ)
ሃሌሉዎች: 122
ሄሮድስ (ንጉሥ): 287(ጎ)
ሄኖስ (የብሉይ): 101(ጎ)
ሄኖክ (ነቢይ): 188÷ 189÷ 271
ህንድ: 304

- ለ -

ለከማ: 208÷ 310(ጎ)÷ 310
ሉቃስ (ወንጌላዊ): 119(ጎ)
ሉተር÷ ማርቲን: 14÷ 24
ሊቃኖስ (ወንድም): 219
ሊቢያ/ሎንያ: 73(ጎ)
ሊባኖስ: 304÷ 309(ጎ)
ሊንቼ (ሕዝባዊ አካዴሚ): 19÷ 45
ላከማ: 249÷ 251
ላይ ላይ ግብጽ: 52(ጎ)÷ 247
ሌዊ (የብሉይ): 281÷ 283(ጎ)
ሌዋውያን: 283(ጎ)
ልዑል ሠምራ (የአባ ዕዝራ አናት): 281
ልዮን (የሮማ ሊቀ ጳጳስ): 216
ሎስ አንጀለስ: 19
ሎንያ/ሊቢያ: 73(ጎ)
ሎጥ (የብሉይ): 85÷ 122÷ 123

- ሐ -

ሐምሌ: 239
ሐረዘወይላ: 289
ሐርላ: 146
ሐይት መንዞ: 158
ሐይጉምዜ: 228
ሐዲያ: 46-47
ሓሪት ዘሞላ: 289(ጎ)
ሓንባር ጎድባ: 60
ሔዋን (የብሉይዋ): 25÷ 72(ጎ)
ሕዝቅኤል (ነቢይ): 188
ሕጉር: 63(ጎ)

- መ -

መልከጸዴቅ (አባ): 126
መሐረቅ (ዴር): 287
መሐግል: 177(ጎ)
መረግድ: 293
መርቆርዮስ (ክሳሽ): 123
መርቆርዮስ (ወንድም): 170÷ 177÷ 187÷ 215
መርቆርዮስ (ሠዓሊ): 297
መርቆሬዎስ ዘሃባ: 229(ጎ)
መርዋ: 57÷ 147
መስፍን ወልደ ማርያም (ፕሮፌሰር): 16÷ 18
መቃርስ/መቃርዮስ/መቃሪ (አበ መነኮሳት): 32÷ 63÷ 63(ጎ)÷ 81÷ 276
መቅዶንዮስ: 189÷ 189(ጎ)÷ 216
መታር (አባ): 242
መንቆርዮስ (ወንድም): 219÷ 220
መንበርታ: 123÷ 126÷ 183÷ 186
መንግሥተ ስማያት: 26÷ 51÷ 76-77÷ 89÷ 94÷ 150÷ 238÷ 251
መአድ: 219
መካነ መለቀል: 187(ጎ)

መካነ ሥላሴ: 49
መካነ ሰላምጌ: 121
መካነ ኢየሱስ: 187(ጎ)
መካከለኛው ምሥራቅ: 32÷ 305(ጎ)
መክሲሞስ (መምህር)): 147
መክብዩ (እማሆይ): 142
መዓራ: 147
መደዓይ: 228
መድኃኒነ እግዚእ ዘበንኩል: 229(ጎ)
መገረደ: 211(ጎ)
መገራን: 137÷ 154
መገርዶ: 206
መጋረጃ: 211
መጋረደ: 209÷ 214
መጋራዳ: 205
መጋርዳ: 206(ጎ)÷ 209
ሙሴ (ነቢይ): 37(ጎ)÷ 58÷ 86÷ 90÷ 115(ጎ)÷ 165÷ 239÷ 247÷ 271-272÷ 299÷ 308÷ 311(ጎ)÷ 244÷ 247
ሙሳለ መሀፒል: 160
ሙደዋ: 179
ሚላኖ: 44
ሚኒሶታ: 17÷ 19
ሚናስ (እባ): 222÷ 215
ሚካኤል (መልአክ): 52÷ 281-282÷ 312
ሚካኤል (ጳጳስ): 41(ጎ)÷ 84÷ 84(ጎ)÷ 102(ጎ)÷ 149÷ 149(ጎ)÷ 153
ማሂኩ: 180(ጎ)
ማርቆስ (ሐዋርያ): 289÷ 299
ማርቆስ (መንበረ): 149(ጎ)÷ 216
ማርቆስ (ጳጳስ): 307
ማርታ እማረ (ወይዘሮ): 18
ማርያ: 285-286
ማርያም (ባሰሽቶዋ): 302
ማርያም ሠምራ (እማሆይ): 206
ማርያም (ቅድስት): 19÷ 22÷ 26÷ 28-31÷ 36-39÷ 37(ጎ)÷ 41÷ 52-53÷ 52-53(ጎ)÷ 69÷ 69(ጎ)÷ 72(ጎ)÷ 85÷ 86(ጎ)÷ 94÷ 107(ጎ)÷ 110÷ 110(ጎ)÷ 113(ጎ)÷ 135(ጎ)÷ 140÷ 146-152÷ 154-155÷ 157÷ 178÷ 209÷ 210÷ 213(ጎ)÷ 216÷ 221÷ 228(ጎ)÷ 280÷ 284(ጎ)÷ 286-290÷ 294-298÷ 295(ጎ)÷ 300÷ 300(ጎ)÷ 306÷ 313÷ 313(ጎ)÷ 314
ማቴዎስ (ወንድም): 137÷ 147÷ 152÷ 154
ማቴዎስ (ወንጌላዊ): 188÷ 272
ማቴዎስ (ሊቀ ጳጳስ): 52(ጎ)÷ 185
ማአድ: 219(ጎ)
ማዕቀበ እግዚእ/ኢዎሰጣቴዎስ (ደቂቀ): 129(ጎ)÷ 151(ጎ)
ማየ: 197(ጎ)
ማየ ጣፋት: 235
ማያ: 151÷ 173÷ 197
ማጋረዶ: 214
ሜሮን: 52÷ 292
ሜዶን: 303
ሜዶን ራጊሰ: 285
ምሕማድ (ገራድ): 180(ጎ)
ምሥራቅ እማረ (ወይዘሮ): 18
ምራዋ: 153
ምርጋይ: 129-130÷ 144÷ 219
ምስር: 287÷ 292
ምእድ: 220
ምዕራብ: 132
ምድረ ክርሰቲያን: 134
ምድረ ፀጋም: 48
ምድያም (ምድረ): 308
ሞርዲኒ÷ አንቶኒዮ (ሲኞር): 34÷ 42-44÷ 44-45(ጎ)÷ 78(ጎ)

- ሠ -

ሠለስቱ ደቂቅ: 311(ጎ)
ሠምረ ሚካኤል (ተሳላኪ): 152
ሣህለ ሥላሴ (ራሰ): 110(ጎ)
ሥሩግ: 249

- ረ -

ረሜ: 287
ሬቺ÷ ሳንፍራንኮ (ፕሮፌሰር): 19÷ 42÷ 45
ራጉኤል (የብሉዶ): 303
ራፋ: 287
ርቱዓ ሃይማኖት (መምህር): 27
ርክነ: 197
ሮማ: 19÷ 45÷: 53(ጎ)÷ 129(ጎ)
ሮማውያን: 53(ጎ)÷ 144(ጎ)
ሮም: 304
ሮም ሰገድ (ልዑል): 222

- ሰ -

ሰለስቱ ምእት: 31(ጎ)
ሰለስቱ ደቂቅ: 142(ጎ)÷ 307(ጎ)
ሰላማ (ጳጳስ): 292
ሰላምጌ: 121
ሰልጎኒ: 296
ሰሎሞን (ንጉሥ): 27(ጎ)÷ 281÷ 289÷ 293÷ 303-304÷ 309÷ 309(ጎ)÷ 313
ሰሜን አፍሪካ: 99(ጎ)
ሰርመት/ሰርማት: 35÷ 177(ጎ)÷ 179÷ 179(ጎ)÷ 205÷ 244
ሰባልዮስ/ሰብሌኔስ/ሰብልያኖስ/ሰብልዮስ (መናፍቅ): 73÷ 73(ጎ)÷ 168÷ 168(ጎ)÷ 216

ሰንደፋ: 52(ጎ)
ሰውኔ: 281
ሰዶም: 85÷ 122
ሰገቢ: 35÷ 206÷ 244
ሰፍ: 158
ሱርስት: 227(ጎ)
ሱርያል (መልአክ): 219
ሲመይ/ሲማይ (ሽሜ): 152(ጎ)÷ 158÷ 181
ሲሞን: 173÷ 173(ጎ)
ሲራ: 236
ሲኖዳ (አርሳይመትሪይስ): 247
ሲኖዳ (አባ): 89÷ 297÷ 210
ሲኖዶስ: 29÷ 29(ጎ)÷ 77÷ 77(ጎ)÷ 82÷ 87÷ 89-90÷ 135(ጎ)÷ 185(ጎ)÷ 231-232(ጎ)÷ 246(ጎ)÷ 249÷ 282(ጎ)÷ 305
ሲኦል: 299
ሲዲ (ሹም): 35-36÷ 205-206
ሲዶና: 252
ሳሙኤል: (የከዳ) 126÷ 200÷ 205
ሳሙኤል (ከሳሽ): 197÷ 197(ጎ)
ሳሙኤል (ወንድም): 201
ሳሙኤል ዘቆየግ/ጻ: 60÷ 60(ጎ)÷ 62÷ 95(ጎ)÷ 197÷ 197(ጎ)÷ 229÷ 229(ጎ)÷ 230÷ 232
ሳሙኤል ወልደ ሕልቃና: 164
ሳሙኤል ዘዋልድባ: 229(ጎ)
ሳሙኤል ዘጣራጣ: 229(ጎ)
ሳሚስ (የብሉዩ): 308
ሳራ (የአባ አስጢፋኖስ እናት): 57÷ 303
ሳባ: 214(ጎ)
ሳኦል: 109(ጎ)÷ 169(ጎ)÷ 186÷ 189
ሳጥራ: 123÷ 137÷ 246
ሳፍ/ሰፍ: 158: 158(ጎ)÷ 232÷ 232(ጎ)
ሴም (የብሉዩ): 46
ሴት (የብሉዩ): 101(ጎ)÷ 271
ሴኖዶስ 146
ሴዋ (ሽዋ): 285
ስማዝያል (መልአክ): 126(ጎ)
ስምዖን (የብሉዩ): 314
ስምዖን (ቀሲስ): 173÷ 244÷ 250÷ 314
ስምዖን ዘዓምድ: 33
ስምያል (መልአክ): 126÷ 126(ጎ)
ስረጽታ: 252
ስቡሐ: 57÷ 281÷ 281(ጎ)÷ 282
ስፔንሰር: 44
ሶርያ/ሶርያዊ: 32÷ 53÷ 53(ጎ)÷ 285÷ 289(ጎ)÷ 292÷ 292(ጎ)
ሶስና: 19

- ሸ -

ሺራ/ሽራ: 82÷ 90
ሽመይ/ሽሜ: 152÷ 152(ጎ)

- ቀ -

ቀሌምንጦስ (አባ): 137÷ 271
ቀንዙራራ/ቀንጦራር: 309(ጎ)
ቀንጦራር/ቀንዙራራ: 309(ጎ)
ቀወት: 177÷ 177(ጎ)
ቀውስጦስ (አቡነ): 177(ጎ)
ቀይ ባሕር: 311(ጎ)÷ 214(ጎ)
ቀጸም: 192
ቁስጥንጥንያ: 216
ቂርቆስ (ሰማዕት): 199÷ 199(ጎ)
ቂስ (የብሉዩ): 109(ጎ)÷ 169÷ 169(ጎ)
ቂስ: 146
ቃኤል (የብሉዩ): 200
ቄርሎስ (ቅዱስ): 31(ጎ)
ቄሳር: 81
ቄዳር: 309(ጎ)
ቄጠመይ: 190
ቅብጥ: 247(ጎ)
ቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርሲቲ: 19
ቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ የማይክሮፊልም ቤተ መጻሕፍት: 45
ቅዳ: 132
ቅፍርያ: 143÷ 147÷ 249
ቆላ: 188(ጎ)
ቆረኒስ (አባ): 29
ቆጥት: 178÷ 180÷ 187÷ 189÷ 194÷ 196÷ 201
ቆጵሮስ: 305(ጎ)
ቈራጻ: 160÷ 160(ጎ)
ቈራጽ: 158
ቈርቋራ/ቋርቋራ: 147(ጎ)÷ 150
ቈስጠንጢኖስ: 293
ቈየጻ/ቈየግ: 229
ቍስቋም: 287(ጎ)
ቍስጥንጥንያ: 53÷ 53(ጎ)÷ 148

- በ -

በሊ: 190÷ 192
በሳዔ ስብእ: 26
በረካ/ባረካ: 236÷ 237
በራራ/ብራራ: 84(ጎ)÷ 151(ጎ)÷ 152÷ 172÷ 181
በርስበይ (ሠልጣን): 52(ጎ)
በርሶማ (አባ): 219÷ 220
በርበሮች: 99(ጎ)
በርተሎሜዎስ (ዲያቆን): 242
በርተሎሜዎስ (አባ): 100÷ 103÷ 105÷ 123÷ 137-138÷ 139÷ 141÷ 141(ጎ)÷ 143÷ 244÷ 246
በርተሎሜዎስ (ጳጳስ): 60÷ 60(ጎ)÷ 71÷ 84(ጎ)÷ 149÷ 168÷ 228÷ 228(ጎ)÷ 233÷ 235

በርናባስ (ሐዋርያ)፡ 189
በስሩ (አባ)፡ 309(ጎ)፥ 309-310
በትራ፡ 60
በጎይለ ማርያም (ሹም)፡ 199፥ 202
በእደ ማርያም (አፄ)፡ 147(ጎ)፥ 175(ጎ)፥ 223(ጎ)፥ 222፥ 245(ጎ)፥ 284(ጎ)
በኪሞስ (አባ)፡ 152(ጎ)
በኴት (ገዳመ)፡ 146
በዕሪ ጽዮን (ሹም)፡ 251
በዐልቶ፡ 120
በድሳይ (ኢማም)፡ 53(ጎ)፥ 133(ጎ)
በግዑ፡ 195
በጸሎተ ሚካኤል (አቡነ)፡ 169፥ 169(ጎ)
ቢዘን፡ 285፥ 285(ጎ)፥ 286
ቢፍሞን (ቀይስ ሐፀይ)፡ 152፥ 152(ጎ)
ባለ ተጐዛጕዛ፡ 152
ባሌ፡ 190(ጎ)
ባሕረ ሳፍ፡ 232፥ 232(ጎ)
ባሕርይ (አባ)፡ 17፥ 19
ባረካ፡ 236
ባሮክ (ነቢይ)፡ 308
ባሴ፥ ሬኔ፡ 94(ጎ)
ባስልዮስ (ቅዱስ)፡ 31(ጎ)
ባስልዮስ (የከዳ)፡ 265
ባቢሎን፡ 86፥ 306(ጎ)፥ 308
ቤሎ፥ ሮቤር፡ 43
ቤተ ልሔም፡ 290
ቤተ ማርያ፡ 244
ቤተ ማርያም፡ 187(ጎ)
ቤተ ኢየሱስ፡ 58
ቤቴል፡ 125፥ 125(ጎ)
ብሔረ ሳባ፡ 214(ጎ)
ብራራ፡ 152፥ 172
ብርሃነ መስቀል (የአባ እስጢፋኖስ አባት)፡ 57
ብርሃነ መስቀል (ወንድም)፡ 124
ብርሃነ መስቀል (ወንድም)፡ 145
ብርሃን መዋኢ (ወንድም)፡ 204
ብእሲ ሰላም (ክሳሽ)፡ 197-198፥ 200
ብእሲ አግዚአብሔር፡ 312(ጎ)
ቦሩ ሜዳ፡ 37(ጎ)
ቦሻ፡ 46-47

- ተ -

ተምቤን፡ 242፥ 256
ተስዓቱ ቅዱሳን፡ 305(ጎ)
ተስፋነ መስቀል (የአባ አበከረዙን አባት)፡ 228
ተስፋነ ክርስቶስ (ሹም)፡ 196
ተንቤን፡ 228
ተክሥተ ብርሃን (ክሳሽ)፡ 121
ተክዜ፡ 75፥ 232-233፥ 256
ተክለ ሃይማኖት (አቡነ)፡ 24፥ 50፥ 229(ጎ)፥ 271(ጎ)፥ 309(ጎ)
ተክለ ሐዋርያት (አቡነ)፡ 245(ጎ)
ተክለ ኢየሱስ (ንቡረ እድ)፡ 155፥ 155(ጎ)፥ 167፥ 170
ተክለ ውሽት፡ 167
ተወልደ መድኅን (አባ)፡ 120-121፥ 123፥ 134፥ 145፥ 245
ቱርክ፡ 304
ታብርሃ ጽዮን (ልዕልት)፡ 252
ታውኒ፡ 14
ታየ አሰፋ (ዶ/ር)፡ 19፥ 45
ታደሰ ታምራት (ፕሮፌሰር)፡ 41(ጎ)፥ 43፥ 52(ጎ)
ታዴዎስ ዘባልታርዋ፡ 229(ጎ)
ታድኅነነ ማርያም (የአባ አበከረዙን አናት)፡ 228
ቴዎድሮስ (አባ)፡ 156
ትግራይ፡ 24፥ 33፥ 46-48፥ 99፥ 108፥ 112-113፥ 120-121፥ 123፥ 126፥ 128፥ 131-132፥ 143-144፥ 183፥ 208፥ 210(ጎ)፥ 229(ጎ)፥ 237፥ 241፥ 248-249፥ 269
ቶማስ (ሐዋርያ)፡ 295፥ 297

- ቸ -

ቸሩሊ፥ ኤንሪኮ፡ 42
ቻይናውያን፡ 13

- ኀ -

ኀበሲ፡ 291
ኀድግ አንበሳ፡ 57

- ነ -

ኒቂያ፡ 163፥ 216
ኒው ዮርክ፡ 18፥ 45
ኒው ዮርክ ሕዝባዊ ቤተ መጽሐፍት፡ 44፥ 46
ናሖም (ሊቀ ካህናት)፡ 136
ናቡቴ፡ 91፥ 91(ጎ)
ናቡክድናጾር፡ 306፥ 306(ጎ)
ናታን (የብሉዩ)፡ 186
ናትናኤል (አባ)፡ 235
ናእድ (አፄ)፡ 57(ጎ)፥ 143(ጎ)፥ 190(ጎ)፥ 293-294፥ 293(ጎ)፥ 310
ናዕዴር፡ 228
ናግራ፡ 214
ናፖሊ፡ 129(ጎ)
ንስጥሮስ (መናፍቅ)፡ 189፥ 189(ጎ)፥ 216፥ 300፥ 300(ጎ)

ንግሥተ ማርያም/ንግሥት ማርያም (ምእመንት): 127÷ 132÷ 132(ጎ)
ኖብ (አባ): 138-139÷ 141(ጎ)
ኖብ (ስማዕት): 230÷ 230(ጎ)
ኖብ (የአባ አበክረዙን ጓደኛ): 230
ኖኅ (የብሉዩ): 85÷ 122-123÷ 271÷ 302

- አ -

አለመሌ: 302
አለዓስ: 166÷ 166(ጎ)
አል-መሲክ አል-አሽረፍ ስይፉ አድ-ዲን በርስበይ: 52(ጎ)
አልበራድዒ÷ ያዕቆብ: 289(ጎ)
አልቤታ: 255
አመጻ: 145
አሚሾች: 32
አማሌቅ: 172
አማራ: 47-48÷ 145(ጎ)
አማር: 19
አሜሪካን: 32
አምስክ: 199÷ 201÷ 203
አምኀ (ለ)ጽዮን (ዓቃቤ ስዓት): 222÷ 222(ጎ)
አምኀ ማርያም (እማሆይ): 160
አምኀ አስፋው (አቶ): 18
አረሚ/አረማዊ/አረማውያን: 50÷ 95÷ 99(ጎ)÷ 100÷ 124-125÷ 124(ጎ)÷ 130-131÷ 133-134÷ 145-146÷ 154÷ 174÷ 177÷ 179÷ 180÷ 190÷ 192÷ 195÷ 208÷ 245÷ 266÷ 288÷ 305
አሩሲ/አርሲ: 110(ጎ)
አራማሮ: 144
አራስ÷ ቪክተር: 75(ጎ)
አርመንያ/አርማንያ:213÷ 305(ጎ)
አርሲ/አሩሲ: 110(ጎ)
አርሴማ (ቅድስት): 127÷ 127(ጎ)
አርስ: 244
አርዮስ (መናፍቅ): 189÷ 189(ጎ)÷ 216÷ 300(ጎ)
አርዳሚስ (ጣዖት): 168
አሮን (የብሉዩ): 40
አሮን (ወንድም): 234
አሮን ዘክትር: 229(ጎ)
አስመራ: 38(ጎ)
አስቄጥስ:: 29
አስና/አስና: 287
አሸሪፍ (ንጉሠ ምስር): 52(ጎ)
አበስኪሮን (አባ): 152÷ 154÷ 170÷ 181
አበኔር: 312
አበክረዙን (ስማዕት): 230
አበክረዙን (አባ): 42÷ 46÷ 75(ጎ)÷ 90(ጎ)÷ 106(ጎ)÷ 125(ጎ)÷ 131(ጎ)÷ 282-285÷ 293÷ 306(ጎ)
አበዘት: 132-133
አቡናፍር (አባ): 208÷ 244÷ 250÷ 254÷ 254(ጎ)
አቤል (የብሉዩ): 79÷ 200÷ 259÷ 271-272
አብረታ/አብሬታ/ አብሩታ: 199÷ 199(ጎ)
አብረኮሮስ (ወንድም): 293
አብርሃ (አፄ): 304
አብርሃም (የብሉዩ): 85-86÷ 109÷ 128÷ 185÷ 257÷ 271÷ 313÷ 313(ጎ)
አብርሃም (ባለ ተጐዛጉዝ): 152
አብሮኮሮስ (ወንድም): 250-251÷ 255
አቦርዮስ (መናፍቅ): 216
አትናቴዎስ (ዲያቆን): 242
አናና: 228
አንበሳ ለፀር/በፀር: (አፄ): 57(ጎ)÷ 293
አንጎት: 285
አንጢዲቆንማርያስ: 216
አንጾክያ: 213
አንፈር: 177
አኖርዮስ (አቡነ): 23
አኖርዮስ (ወንድም): 191
አክሱም: 57÷ 57(ጎ)÷ 75(ጎ)÷ 99÷ 106÷ 228÷ 305(ጎ)
አክሱም ጽዮን: 57(ጎ)
አክዓብ/አካአብ (ንጉሥ): 171(ጎ)÷ 256
አውሮፓ/አውሮፓውያን: 14÷ 41
አዘራት: 153-154
አዛፍ: 158(ጎ)
አዜብ: 167
አያ ጂቦ: 28
አይሁድ/አይሁዳዊ: 14÷ 53÷ 58(ጎ)÷ 72(ጎ)÷ 94÷ 113(ጎ)÷ 122÷ 123(ጎ)÷ 125(ጎ)÷ 167÷ 189÷ 192÷ 210(ጎ)÷ 222÷ 288÷ 291÷ 293(ጎ)÷ 157(ጎ)
አይራራ: 143(ጎ)
አደል: 53(ጎ)÷ 133(ጎ)
አዲስ አበባ: 19÷ 45
አዲስ አበባ የአርኬዎሎጂ ኢንስቲትዩት ቤተ መጻሕፍት: 44
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጻሕፍት: 43÷ 45
አዳም (የብሉዩ): 25÷ 85-86÷ 101(ጎ)÷ 165(ጎ)÷ 188÷ 271÷ 296
አድሙት: 199
አድማስ በፀር (አፄ): 119
አዶናይ: 173(ጎ)
አገው: 46
አግዐ: 134÷ 245
አጽሎን (ጣዖት): 168

አጽብሐ (እዜ): 304
አፍሐሮም ዋሻ: 105
አፍቲክስ (መናፍቅ): 216
ኢሳይያስ (ብሕት ወደድ): 210(ጎ)
ኢሳይያስ (ነቢይ): 188÷ 210÷ 299
ኢሳይያስ (አባ): 131(ጎ)
ኢባ: 54÷ 180÷ 183÷ 190÷ 192
ኢትዮጵያ/ኢትዮጵያውያን: 13-18÷ 23-25÷ 28÷ 32-33÷ 35(ጎ)÷ 41÷ 41(ጎ)÷ 44÷ 46÷ 52÷ 52-53(ጎ)÷ 60(ጎ)÷ 75(ጎ)÷ 84(ጎ)÷ 98(ጎ)÷ 99(ጎ)÷ 122÷ 125(ጎ)÷ 138÷ 147÷ 149÷ 151÷ 151(ጎ)÷ 157(ጎ)÷ 167(ጎ)÷ 176÷ 249÷ 271(ጎ)÷ 272÷ 276÷ 284÷ 284(ጎ)÷ 285÷ 286÷ 287(ጎ)÷ 288-289÷ 290(ጎ)÷ 292-293÷ 292(ጎ)÷ 296÷ 300(ጎ)÷ 302÷ 304÷ 305(ጎ)÷ 307(ጎ)÷ 310÷ 313
ኢየሉጣ (ስማዕት): 199(ጎ)
ኢየሩሳሌም: 101÷ 129(ጎ)÷ 174÷ 192÷ 210÷ 244÷ 281(ጎ)÷ 283÷ 284(ጎ)÷ 285-286÷ 288÷ 289(ጎ)÷ 291-292÷ 306(ጎ)÷ 313
ኢየሱስ: 32÷ 127÷ 139÷ 164÷ 169÷ 187÷ 217÷ 227÷ 227(ጎ)÷ 299÷ 299(ጎ)
ኢየሱስ ሞእ (እቡነ): 50
ኢያሪኮ: 305(ጎ)
ኢያሱ (ነቢይ): 271-272
ኢዮስያስ (ንጉሥ): 310
ኢዮብ (የብሉዩ): 68÷ 104÷ 247÷ 313
ኤልሳዕ (ነቢይ): 257÷ 271-272
ኤልዛቤል (የብሉይዋ): 91÷ 91(ጎ)÷ 171÷ 171(ጎ)÷ 256
ኤልያስ (ነቢይ): 252÷ 256÷ 271-272÷ 313
ኤሞር: 109
ኤርምያስ (ነቢይ) : 308
ኤርምያስ (አባ): 146
ኤሳው: 185
ኤውሳጦን: 167
ኤዎስጣቴዎስ (እቡነ): 305÷ 305(ጎ)÷ 309(ጎ)
ኤዪሳ: 289(ጎ)
ኤጶምያስ: 296
ኤጲፋንያ: 107÷ 124÷ 238÷ 253
ኤፍት: 110÷ 110(ጎ)÷ 120÷ 173÷ 244
ኤፌሶን: 148÷ 216
ኤፍሬም (ቅዱስ): 30
እለ ቄራጸይ: 159
እለ እዝጎን: 159(ጎ)
እለ ክዲሕ: 159(ጎ)
እስ ወጺፍ: 159(ጎ)
እለ ገበዝ: 57(ጎ)÷ 159(ጎ)
እምፍራዝ: 121÷ 145
እሥራኤል/እሥራኤላውያን: 125(ጎ)÷ 171(ጎ)÷ 270÷ 276
እስራኤል/እስራኤላዊ: 76-77÷ 81-82÷ 86÷ 86(ጎ)÷ 87÷ 87(ጎ)÷ 88÷ 91÷ 91(ጎ)÷ 107÷ 109(ጎ)÷ 121÷ 125(ጎ)÷ 126÷ 169(ጎ)÷ 193÷ 239÷ 239÷ 244÷ 256÷ 271÷ 273÷ 276(ጎ)÷ 281(ጎ)÷ 284÷ 293÷ 307÷ 307(ጎ)÷ 310÷ 311(ጎ)÷ 303
እስክንድር (እዜ): 180(ጎ)÷ 284(ጎ)÷ 293
እስክንድርያ: 52÷ 52(ጎ)÷ 216÷ 292÷ 292
እስጢፋ/ፈ: 28÷ 113(ጎ)÷ 167÷ 189÷ 197-198÷ 201÷ 208
እስጢፋኖሳዊ/እስጢፋኖሳውያን: 30-32÷ 42-43÷ 44(ጎ)÷ 54(ጎ)÷ 86(ጎ)÷ 91(ጎ)÷ 310(ጎ)
እስጢፋኖስ (ወንድም): 241-242
እስጢፋኖስ (ወንድም): 293
እስጢፋኖስ (የሲመይ ነብርእድ): 152÷ 152(ጎ)÷ 158÷ 181
እስጢፋኖስ (ስማዕት): 58(ጎ)
እስጢፋኖስ (አባ): 13÷ 15÷ 17÷ 19÷ 23-25÷ 28-30÷ 33-34÷ 42÷ 114÷ 119÷ 120(ጎ)÷ 121-130÷ 141(ጎ)÷ 146÷ 148÷ 153÷ 167-169÷ 197-198÷ 201-202÷ 207÷ 207(ጎ)÷ 208-209÷ 218÷ 221-222÷ 227÷ 228(ጎ)÷ 230-234÷ 235(ጎ)÷ 237÷ 238(ጎ)÷ 245-246÷ 248-250÷ 257÷ 262÷ 267(ጎ)÷ 284÷ 286-287÷ 287(ጎ)÷ 296÷ 304÷ 310÷ 114÷ 145÷ 253(ጎ)÷ 271÷ 281(ጎ)÷ 305(ጎ)÷ 308÷ 314(ጎ)
እስጢፋኖስ (አባ እበክረዙን): 228
እስጢፋኖስ (የአባ ዕዝራ ወንድም): 282
እስጥምቡል: 53(ጎ)
እስፓኝ: 25
እብሶ: 137÷ 194
እብነ ሕልክም (ቀዳማዊ ምኒልክ): 281
እነ ቄሬጥ: 159(ጎ)
እናርያ: 46
እንግሊዝ/እንግሊዞች: 14÷ 50
እንጦንስ/እንጦንዮስ (አባ): 32-33÷ 63÷ 63(ጎ)÷ 75(ጎ)÷ 81÷ 118÷ 200÷ 247-248
እንጦንስ ወልደ እጎተ: 297
እጉላ/እጉላ/እጉባ: 53(ጎ)÷ 172÷ 176÷ 176(ጎ)÷ 177
አሮሞች/አሮሞዎች: 17÷ 110(ጎ)

- ከ -

ከልአት: 214(ጎ)
ከሰም: 244
ከስዋ: 256÷ 282÷ 284÷ 293÷ 311÷ 311(ጎ)÷ 312
ከነዓን: 284
ኩር÷ ሰታኒስላው: 43(ጎ)
ኪሩቤል (መልአክ): 188÷ 281
ኪራም (የብሉዩ): 309÷ 309(ጎ)
ኪሮስ (ወንድም): 156÷ 157
ካሌብ (አዜ): 50÷ 214(ጎ)
ካሉ÷ አንድሬ: 42÷ 46÷ 307(ጎ)
ካይሮ: 289(ጎ)
ካፈር: 124(ጎ)
ኬር ወሰን (ሹም): 173÷ 197
ኬጢ (የብሉዩ): 109(ጎ)÷ 185
ኮሳ አራይ: 123
ክርስቶስ/ክርስቶላውያን: 28÷ 31-32÷ 37(ጎ)÷ 38-40÷ 50÷ 53÷ 63÷ 67-68÷ 72(ጎ)÷ 78-79÷ 85(ጎ)÷ 87÷ 89÷ 94-95÷ 100÷ 104÷ 107÷ 110-111÷ 111(ጎ)÷ 114÷ 127÷ 127÷ 139÷ 153÷ 156÷ 158÷ 165(ጎ)÷ 167÷ 169-170÷ 173÷ 179(ጎ)÷ 187÷ 189(ጎ)÷ 198÷ 200-201÷ 204÷ 210(ጎ)÷ 217-218÷ 227÷ 227(ጎ)÷ 229(ጎ)÷ 230÷ 237-239÷ 247÷ 247(ጎ)÷ 255÷ 257(ጎ)÷ 258÷ 264÷ 281-282(ጎ)÷ 287(ጎ)÷ 289-290÷ 294÷ 299-300÷ 299(ጎ)÷ 300(ጎ)÷ 303÷ 306(ጎ)
ኮሰያት (ደብረ): 121
ክላድ እንባ: 282
ክብራ: 166
ክብርተ ማርያም (አማሆይ): 173
ኮሌጅቪል: 17
ኮንቲ ሮሲኒ÷ ካርሎ: 42÷ 45-46

- ወ -

ወሰቃ: 159÷ 172
ወላስማ: 110(ጎ)
ወላይታ: 46-47
ወልመ/ወልማ: 199÷ 199(ጎ)÷ 202
ወራሪ: 143(ጎ)
ወራውሬ: 293
ወርወር: 297
ወርዕ: 229
ወያኔ: 15
ወይራራ/ወይራር: 48÷ 143÷ 209
ወድ/ውድ: 197÷ 199(ጎ)÷ 204
ወገራ: 73
ወጊ: 187÷ 199÷ 203÷ 207
ዋሊ: 229(ጎ)
ዋላ: 282
ዋልያ: 283
ዋሠጋ: 215÷ 215(ጎ)
ዋስል: 172
ዋዝርማ: 110÷ 120
ውታፋ: 249
ውዱ ጣፊጠ ካሱ (አቶ): 19÷ 45
ውድ: 199(ጎ)

- ዐ -

ዐረብ: 50÷ 288
ዐርበት: 147÷ 150
ዐቅበ ሚካኤል (አባ ዕዝራ): 282
ዐጋሜ: 126÷ 183÷ 282÷ 293÷ 294÷ 294
ዓለማየሁ (ሕፃን): 19
ዓሰት: 71÷ 176
ዓምደ መስቀል (ወንድም): 145÷ 145(ጎ)
ዓምደ ጽዮን (አዜ): 23÷ 111(ጎ)
ዓምዱ (ራስ): 35÷ 205
ዓረቦች: 50
ዓዝር/ዕዝራ (አባ ዕዝራ): 292÷ 292(ጎ)÷ 296
ዓደል (ዓዳል): 114÷ 146
ዓጋት: 174
ዓጸላ: 108
ዔላው (የብሉዩ): 109÷ 186
ዕብራዊ/ዕብራውያን: 227(ጎ)÷ 276÷ 281÷ 287÷ 314
ዕዝራ (ነቢይ): 243÷ 282÷ 299÷ 300
ዕዝራ (አባ): 15÷ 31÷ 42÷ 46÷ 131(ጎ)
ዕዝራ (አባ): 206
ያዝዮን (ንጉሥ): 210

- ዘ -

ዘሚካኤል (መምህር): 28(ጎ)÷ 31÷ 155(ጎ)÷ 197(ጎ)
ዘርአ ያዕቆብ (አዜ): 17-18÷ 23÷ 25-29÷ 31÷ 35÷ 41-42÷ 48÷ 51-52÷ 52(ጎ)÷ 57(ጎ)÷ 72(ጎ)÷ 73(ጎ)÷ 78(ጎ)÷ 84(ጎ)÷ 90÷ 91(ጎ)÷ 100-101(ጎ)÷ 103(ጎ)÷ 110-111(ጎ)÷ 145(ጎ)÷ 149(ጎ)÷ 151(ጎ)÷ 158(ጎ)÷ 166(ጎ)÷ 169(ጎ)÷ 178(ጎ)÷ 181(ጎ)÷ 190(ጎ)÷ 192÷ 207(ጎ)÷ 209(ጎ)÷ 212-213(ጎ)÷ 218(ጎ)÷ 221-232(ጎ)÷ 240(ጎ)÷ 245(ጎ)÷ 253(ጎ)÷ 290(ጎ)÷ 306(ጎ)

ዘርዓ ያዕቆብ (ፈላስፋ): 15
ዘብር: 219÷ 221
ዘታአስ (የሰርማት መምህር): 35÷ 205
ዘንትር: 146÷ 159-160
ዘንጉ: 228
ዘአማኑኤል (ወንድም): 147÷ 166
ዘአዶናይ (አባ): 173-174
ዘካርያስ (ነቢይ): 79÷ 310(ጎ)
ዘካርያስ ዘጊፋ: 229(ጎ)
ዜራናቋ: 233
ዜጋ: 249
ዝማ: 221
ዝራጐን: 28÷145÷ 145(ጎ)
ዝቀላይ: 57
ዞሲማስ (አባ): 122÷ 130

- ዠ -

ዣን ዜላ (ንግሥት/ኢቴ): 180(ጎ)

- የ -

የገስብም: 207
የጋድ: 172
ያሬድ (ቅዱስ): 27÷ 30
ያላይ ዘማንጻምባ: 229(ጎ)
ያንጎ: 121
ያዕቆባውያን: 53(ጎ)÷ 216÷ 289÷ 289(ጎ)
ያዕቆብ (ሐዋርያ): 262
ያዕቆብ (የብሉዩ): 109÷ 185-186÷ 243÷ 271÷ 285÷ 310÷ 314
ያዕቆብ (ወንድም): 147÷ 166
ያዕቆብ አልበራድዒ: 289(ጎ)
ያዕቆብ ዘሥሩግ: 249
ያግብአ ጽዮን (አፄ): 24
ያፍቅረነ እግዚአ (ባለ መድኃኒት): 134÷ 136
ያፈቅረነ እግዚአ ዘጉጉቤን: 229(ጎ)
ይሁዳ (የተለየው ሐዋርያ): 91÷ 292
ይሥሐቅ (የብሉዩ): 271÷ 310
ይሥሐቅ (አፄ): 24-25÷ 60(ጎ)÷ 82÷ 84(ጎ)÷ 90(ጎ)÷ 207÷ 207(ጎ)÷ 235÷ 235(ጎ)
ይሥሐቅ (አባ): 75(ጎ)÷ 126÷ 131-132÷ 131(ጎ)÷ 248÷ 282÷ 312(ጎ)÷ 250-251÷ 284
ይሥሐቅ (ጳጳስ): 296÷ 307
ይሥሐቅ (ጳጳስ): 149(ጎ)
ይሥሐቅ (የአባ ዕዝራ አባት): 281÷ 285
ይባራ: 235
ይጌይስ: 210
ይፋት: 110(ጎ)
ዮሐኒ (አባ): 271(ጎ)
ዮሐንስ (አቡነ): 250
ዮሐንስ (ምእመን): 251
ዮሐንስ (መጥምቅ): 281÷ 281(ጎ)
ዮሐንስ (ሊቀ ጳጳስ): 52(ጎ)÷ 289÷ 289(ጎ)÷ 292
ዮሐንስ (ኤጲስ ቆጶስ): 84(ጎ)
ዮሐንስ (ወንጌላዊ): 72÷ 98÷ 188÷ 189÷ 258÷ 299
ዮሐንስ (ራእይ): 31÷ 295(ጎ)
ዮሐንስ ሳባ: 248(ጎ)
ዮሐንስ አፈ ወርቅ: 31(ጎ)
ዮሐንስ ዘጉራናቋ: 229(ጎ)
ዮሴፍ: (የብሉዩ): 234÷ 293÷ 307÷ 314
ዮሴፍ (ቅዱስ): 287(ጎ)
ዮናስ (አባ): 285-286

- ደ -

ደሐረጎት: 204
ደመቀ ብርሃኔ (አቶ): 19
ደምበሳ: 228
ደርግ: 15
ደቂቀ ማቲያን: 285
ደቂቀ ሲኖዳ: 285-286
ደቂቀ ተክለ ሃይማኖት: 24
ደቂቀ አምኑ: 285-286
ደቂቀ አባ ዕዝራ: 307
ደቂቀ አባ ዮናስ: 286-287
ደቂቀ ኤዎስጣቴዎስ/ማዕቀበ አግዚእ: 35÷ 35(ጎ)÷ 129(ጎ)÷ 151(ጎ)÷ 309(ጎ)
ደቂቀ አስጢፋ: 28÷ 52÷ 43÷ 113(ጎ)÷ 190
ደቂቀ ጳኮሚስ: 149(ጎ)
ደብረ ሃሌ ሉያ/ ሃሌሉ: 229(ጎ)
ደብረ ሊባኖስ/ደብረ አስቦት: 17÷ 24÷ 190-191÷ 271(ጎ)
ደብረ መዓራ: 147
ደብረ መገራ: 137÷ 154
ደብረ ማርቆስ: 17
ደብረ ማርያም: 285÷ 285(ጎ)
ደብረ ማዕያ: 105
ደብረ ምጥማቅ: 52(ጎ)÷ 53(ጎ)
ደብረ ስላም: 142
ደብረ ሰማዕት: 242
ደብረ ሲና: 17÷ 58
ደብረ ቅፍርያ: 143÷ 249-250
ደብረ ቆየጻ/ቈየጻ: 229÷ 229(ጎ) 232
ደብረ ቍስቋም: 52÷ 287÷ 287(ጎ)
ደብረ በግዑ: 195
ደብረ ቢዘን: 285(ጎ)
ደብረ ብርሃን: 17÷ 51÷ 54÷ 180÷ 180(ጎ)÷ 183÷ 190÷ 192(ጎ)÷ 205-206÷ 221
ደብረ አስቦት/ደብረ ሊባኖስ: 17÷ 24÷ 190-191÷ 271(ጎ)

ደብረ አባ ሳሙኤል: 60
ደብረ አምፍራዝ: 121÷ 145
ደብረ አግዚአብሔር: 127
ደብረ ክስዋ: 311
ደብረ ኮሲያት: 121
ደብረ ኮራብ: 256
ደብረ ዲጋ: 229
ደብረ ዳሞ: 17÷ 122÷ 271(ጎ)
ደብረ ገረዛን: 227(ጎ)
ደብረ ገርዜን: 42÷ 75÷ 75(ጎ)÷ 90(ጎ)÷ 119÷ 131(ጎ)÷ 226-227÷ 282(ጎ)÷ 311(ጎ)÷ 311(ጎ)
ደብረ ጽዮን: 28÷ 31-32÷ 85(ጎ)÷ 99÷ 99(ጎ)÷ 100÷ 122÷ 122(ጎ)÷ 123(ጎ)÷ 130÷ 157÷ 158
ደብረ ጽዮን (ሎሌ): 153
ደብረ ፋራን: 244
ደንጎ: 134
ደዋሮ: 110(ጎ)÷ 114÷ 130÷ 219
ደውለይ: 197
ደውላይ: 199÷ 202
ዱስአ (ዲስአ): 281÷ 313÷ 310
ዲልማን: 41÷ 75(ጎ)
ዲቦ: 123
ዲያብሎስ: 173
ዲዮስቆሮስ (ሊቀ ጳጳስ): 216
ዲዮቅልጥያኖስ: 167÷ 168÷ 172÷ 230(ጎ)
ዲድርከም: 59
ዲድስቅልያ: 29÷ 217
ዳሞ: 122
ዳጎ...: 310
ዳንኤል (ነቢይ): 189÷ 243÷ 283÷ 301
ዳንኤል ዘፀዓዳ አምባ: 229(ጎ)
ዳዊት (ነቢይ/ንጉሥ): 86÷ 186÷ 288÷ 295÷ 299÷ 310-313
ዳዊት (አፄ): 25
ዳዓላ: 144÷ 146
ዴር መሐረቅ: 287(ጎ)
ዴር አል-መግጠስ: 52(ጎ)
ዴስአ: 126÷ 144÷ 147
ድምያኖስ (ወንድም): 173
ድራጎን: 28
ድሮር: 123÷ 244
ድብ ፀር (አፄ): 28÷ 57(ጎ)÷ 119÷ 167÷ 221
ድንበሐት: 282
ድድኖ: 172
ድግኑ: 228

- ጀ -

ጀርመን: 24
ጀቅማቅ (ሠልጣን): 52(ጎ)÷ 53(ጎ)
ጂብራ: 29
ጅብ ጠሳት: 28÷ 57(ጎ)

- ገ -

ገሊላ: 122÷ 292
ገላውዴዎስ (አባ): 221-222
ገማልያል (መምህር): 28(ጎ)÷ 31÷ 152(ጎ)÷ 155(ጎ)÷ 197(ጎ)
ገሪማ (አባ): 305÷ 305(ጎ)
ገርዜን/ገሪዘን: 119÷ 311÷ 311(ጎ)÷ 131(ጎ)÷ 282
ገርጌሳ: 60
ገስምቤ: 214
ገበሉል: 285
ገበዘ አክሱም: 57(ጎ)
ገብረ መሲሕ (አባ): 294÷ 308÷ 311-312÷ 314
ገብረ መስቀል (አባ): 297-298
ገብረ መስቀል (አፄ) : 235
ገብረ መንፈስ ቅዱስ (ነጋዲ): 297
ገብረ መንፈስ ቅዱስ (አቡነ): 50
ገብረ ሚካኤል (ወንድም): 153÷ 302
ገብረ ማርያም (ወንድም): 124÷ 145
ገብረ ማርያም (ወንድም): 156-157
ገብረ አምላክ (አባ): 169÷ 169(ጎ)
ገብረ ክርስቶስ (ደቀ መዝሙር): 75÷ 98÷ 104÷ 108÷ 111÷ 115÷ 120-121÷ 123÷ 130÷ 233
ገብረ ክርስቶስ (ምአመን): 204
ገብረ ክርስቶስ (ወንድም): 244
ገብረ ክርስቶስ ዘቢታንያ: 229(ጎ)
ገብረ ዋሕድ (ወንድም): 206
ገብርኤል (መልአክ): 300÷ 300(ጎ)
ገብርኤል (ጳጳስ): 30÷ 41(ጎ)÷ 84(ጎ)÷ 102(ጎ)÷ 149÷ 149(ጎ)÷ 151(ጎ)÷ 153÷ 237÷ 283
ገነት: 71-72÷ 72(ጎ)÷ 75(ጎ)÷ 85÷ 160
ገኒ/ገኝ/ገይኒ: 123÷ 183(ጎ)÷ 207(ጎ)÷ 249÷ 207
ገዘሞ: 197
ገዘበ: 190(ጎ)
ገይኒ: 207(ጎ)
ገይኒም: 183
ገደዶ: 190
ጉራጌዎች: 151
ጉንዳጉንዴ: 42
ጊዘበ: 190
ጊዮርጊስ (ስማዕት): 247
ጊዮርጊስ (ወንድም): 191-192÷ 271(ጎ)
ጊዮርጊስ ዘጋስጫ/ዘስግላ: 27÷ 73(ጎ)÷ 166(ጎ)÷ 189(ጎ)
ጋሞ: 46-47

ጋሳ/ጋስ: 130-131÷ 134÷ 177÷ 177(ጎ)÷ 245
ጋዘም: 203
ጌዲዎን ወልደ ዮአስ: 164
ግሪክ: 51÷ 53(ጎ)÷ 247(ጎ)÷ 295(ጎ)
ግራ ምድር: 48÷ 176÷ 179÷ 187÷ 196
ግድም: 112-113÷ 121÷ 124÷ 130÷ 145÷ 170÷ 177
ግፍሜላ: 57÷ 61
ጎልጎታ: 24÷ 291
ጎጃም: 158(ጎ)
ጐሐርብ: 195÷ 195(ጎ)
ጐን: 160
ጐንደት/ጐንደን: 197÷ 201-205÷ 205(ጎ)÷ 215
ጐዘም: 221
ጐዛም/ጐዘም: 221÷ 285
ጒራጌ/ጒራጌዎች: 151÷ 207
ግብጽ/ግብጻዊ/ግብጻዊች:÷ 29÷ 32÷ 50÷ 52-53÷ 52-53(ጎ)÷ 63(ጎ)÷ 75(ጎ)÷ 76÷ 86÷ 86(ጎ)÷ 90÷ 99(ጎ)÷ 107÷ 118÷ 151÷ 170÷ 182÷ 208÷ 224÷ 126÷ 230(ጎ)÷ 234÷ 239÷ 243-244÷ 247÷ 284(ጎ)÷ 286-287÷ 287(ጎ)÷ 289÷ 289(ጎ)÷ 291-294÷ 292(ጎ)÷ 296÷ 297÷ 303-304÷ 305(ጎ)÷ 307÷ 309÷ 230(ጎ)
ጒንጒ: 112(ጎ)
ጒንጽ: 111-112(ጎ)÷ 120-123÷ 130÷ 134÷ 145÷ 223(ጎ)÷ 245÷ 245(ጎ)÷ 306(ጎ)
ጒዛም/ጒዛም: 158-159
ጒዳሌ: 145÷ 145(ጎ)÷ 221
ጓትር: 110÷ 110(ጎ)÷ 113÷ 119÷ 120÷ 123-124÷ 131÷ 134÷ 245

- ጠ -

ጠዞ: 203
ጠፋንይ: 221
ጢሞቴዎስ (ሐዋርያ): 271÷ 293
ጢሮስ: 309(ጎ)
ጣና: 158(ጎ)÷ 232(ጎ)÷ 297÷ 73
ጤማይ: 232
ጤጠይ/ጤጤ: 146÷ 148÷ 129÷ 137
ጥልብያኮስ: 2221÷ 222(ጎ)
ጥናትና ምርምር ቤተ መጻሕፍት (የኢትዮጵያ): 19÷ 45
ጦቢት (ብሉይ): 285
ጦቢያ (ብሉይ): 285÷ 293
ጦዘ/ጠዞ: 197÷ 197(ጎ)÷ 203
ጦጽያ: 119-120

- ጨ -

ጨርቆስ/ቂርቆስ (ስማዕት): 199(ጎ)

- ጸ -

ጸራቅሊጦስ: 217
ጸንጠሌዎን ዘጸማእት÷ አባ: 50
ጸንጠቆስጤ: 69÷ 137÷ 297
ጲላጦስ: 123(ጎ)÷ 171(ጎ)
ጳኩሚስ (አባ): 32÷ 75(ጎ)÷ 149÷ 149(ጎ)÷ 224
ጳውሊ (አባ): 182
ጳውሎስ (ወንድም): 137-138÷ 147÷ 152÷ 157÷ 166÷ 184-185÷ 188÷ 198
ጳውሎስ (ሐዋርያ): 89÷ 94÷ 107(ጎ)÷ 264÷ 173÷ 189÷ 217÷ 234÷ 238÷ 252÷ 256÷ 271÷ 293÷ 295÷ 295(ጎ)÷ 313
ጳዝዮን: 293
ጴጥሮስ (ሐዋርያ): 112(ጎ)÷ 169÷ 188-189÷ 210÷ 238÷ 247÷ 271÷ 295÷ 295(ጎ)÷ 310÷ 313
ጴጥሮስ (ወንድም): 293

- ጸ -

ጸሐጋ (ጽሐጋ): 153
ጸጋ ሥሉስ (ወንድም): 293
ጺማ: 159
ጻክራ: 114
ጽሐጋ: 153(ጎ)
ጽዮን: 37(ጎ)÷ 85÷ 275÷ 281÷ 295÷ 311

- θ -

θጋም (ምድረ/ስብአ): 176÷ 179÷ 196

- ፈ -

ፈላሲዎች: 80
ፈላሻዎች: 286
ፈረንሳይ: 25÷ 304
ፈራኅ: 170-171
ፈርያን: 234÷ 237(ጎ)÷ 311(ጎ)
ፈጸጋር: 35÷ 49÷ 123÷ 130÷ 178÷ 196÷ 205
ፊልጶስ (ሐዋርያ): 95÷ 310
ፊልጶስ (አቡነ): 23÷ 111(ጎ)
ፊቅጦር (ወንድም): 156-157
ፊቤን: 252

ፋርስ: 213(ጎ)÷ 304
ፋሲለደስ (ግብጻዊ?): 297
ፈራንክ÷ አሌክሳንደር: 43÷ 44
ፈቤን: 303
ፍሊሙና (ደቀ መዝሙር): 290
ፍልስጥኤም: 25
ፍሬ ሊባኖስ (አባ): 176
ፍሬ ሚካኤል (ንቡረ እድ): 129(ጎ)
ፍሬ ብርሃን (አባ?): 187÷ 189
ፍሬ ክርስቶስ (ወንድም/አባ): 208÷ 210÷ 212÷ 212(ጎ)÷ 215÷ 222
ፍሬምናጦስ (መምህር): 137÷ 309(ጎ)÷ 154
ፎንጢዮስ (መናፍቅ): 216

- ፕ -

ፓሳዲና: 19
ፔሩሾ÷ ዠል :: 42

- ቨ -

ቪክተር አራስ: 75(ጎ)
ቬበር÷ ማክስ: 14
ቬንት÷ ኩርት: 42

Accademia Nazionale dei Lincei: 45
Astor, Lenox and Tilden Foundation: 18-19
Collegeville: 19
Conti Rossini, Carlo: 19
Hill Monastic Manuscript Microfilm Library: 19
Lincei, Accademia Nazionale dei : 19
Mediterranean: 305(n)
Minnesota: 19
New York: 18
New York Public Library: 44, 46
Parsons, Talcott: 14(n)
Ricci, Lanfranco, Professor: 19, 45
Roma: 19
Saint John's University: 19
Spencer Collection: 18
Weber, Max: 14(n)